# የዝንተ-ዓለሙ የሐሰት እውነት፤

## የእውነት እውነት

በወንጌላዊ ሳሙኤል ባላ

ጥር 2004 የመጀመሪያ እትም

# የዝንተ-ዓለሙ የሐሰት እውነት፣

## የእውነት እውነት

በፀጋው የሆነ ከኖ፣ የተባለው ሳሙኤል
በስውር የኢየሱስ ደቀ መዝሙር፤ (ዮሐ.19፡38)



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፤ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፤ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

የጌታ ሥጋ መድረሻና ምንነቱ፣

© የደራሲው መብት «አትሥረቅ» በሚለው፣ በጌታ ሕግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከግድግዳ ሠርሳሪ፣ ከምድር ቆፋሪ ይህ የተናቀው ክቡርና ሕያው ሕግ ንብረቴንና እኔን ይጠብቀኝ፡፡ በጌታ ወይም በባሪያው ፈቃድ መውሰድ ግን ይቻላል፡፡ ብዙ፣ ተባዙ ምድርን ሙሉ፡፡

በመጽሐፉ ላይ ያሎትን አስተያየት፣ ጥያቄ፣ እርማት ወይም ሐሳብ ከዚህ በታች
ባለው አድራሻ ብልኩልን እናመሰግናለን፡፡
ፖ.ሣ.ቁ. 12182
ኢ.ሜል indryasmulu@yahoo.ca



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፤ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፤ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

**የትንሣኤው ፅልመት፣**
**የጌታ ሥጋ ከየት ወዴት?**
**የእግዚአብሔር ተዓምር፣**
**በሦስት ቀን ባዶ መቃብር**
**ጥልቅ፣ ጥልቅ ምስጢር**





መታሰቢያነቱ፣

በጌታ የሆኑ ወንድሞቼ

- አቶ አባተ ኮይራ አሴኮን፣
- አቶ ተስፋለኝ ሸኖ ሳደሞን አስባቸዋለሁ፣

## ምሥጋና

፩/ ምስጋና፣ ውዳሴና ሞገሥ ከሰው መቀበል፣ ዋጋውን እዚሁ መከፈል በመሆኑ ተቀባዩን በጌታ ዘንድ ባዶ ያደርጋል፡፡

፪ ምሥጋና፣ ሞገሥ፣ ክብር ለሰው መስጠትን ኢሳ.42፡8 ይቃወማል፡፡ ስለሆነ፣ ለረዱኝ ለማንም በሰው ሥርዓት ምሥጋና አላቀረብኩም፣ መጽሐፍ በሚገልጸው መሠረት፣ ከረዱኝ ወገኖቼም ጋር በጋራ ሆነንና የተቀደሰውን እጅ ወደ ላይ በማንሣት፣ ምስጋና፣ ውዳሴ፣ ክብርና በረከት ሊቀበል የሚገባው የታረደው በግ ብቻ ስለሆነ፣ (ራዕይ 5፡12) አብረን እርሱን እናመሰግን እያልኩ፡

በዚህ ፈንታ የረዱኝንና የደገፉኝን አገልግሎቱ ቅዱስ እንደመሆኑ መጠን እግዚአብሔር እንደማይረሳቸው እጠቅሳለሁ፣ «እግዚአብሔር፣ ቅዱሳንን ለላገለገላችሁ፣ እስከ አሁንም ስለምታገለግሉአቸውና ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ አመፀኛ አይደለምና፣ (ዕብ. 6፡10» ሲል፣ ከዚህም ጋር «... እነሆ ዋጋው ከእርሱ ጋር፣ ደመወዙም በፊቱ ነው፣ (ኢሳ. 40፡10፣ ራዕይ 22፡12»፡፡

ስለሆነ ከዚህ በታች በስም ለተጠቀሱት በሥራዬ ለረዱኝና ፣ ላበረታቱኝ፣ ተስፋ ለሰጡኝ፣ ወንድሞቼን አቶ ተክሌ ታኪሶ ተንቱን አቶ ብርሃኑ መና መሰኔን፣ አቶ ታደሰ ባሌ ገራዶን፣ ልጆቼን፣ አቶ ዳዊት ዳና አኔቦን (ከአሜሪካ)፣ ወይዘሪት ዓይናለም ሰይፉ ካሣን (ከኢጣሊያ) ልጅ ታምራት ለፌቦ ቀልቦሮን፣ ልጅ ደምሴ ዳካ ደስታን እና፣

>> አርትዖቱን በፍፁም አትኩሮት ከመሥራትም በተጨማሪ ላበረከተው ጠቃሚ ምሁራዊ ምክሩና ቀና አስተያየቱ ሁሉ አርታዒ ዳንኤል ተሾመን፣

>> እውነትን አፍቃሪ እንደመሆኑ መጠን፣ ብርሃን በተሞላ አእምሮው በመጽሐፉ ላይ በባለቤትነት ስሜት ተቀስቅሶ ልዩ ትኩረት፣ አክብሮት፣ አድናቆትና አፍቅሮትን በቸረ መልኩ አጠቃላይ ምርመራ በማድረግና በመጨረሻ የተገኙ ግድፈቶችን በተሻሉ ቃላት በመተካት በፍፁም ቅንነት ትልቅ አስተዋፅዖ ላበረከተ ልጄ ለሚሆን አገልጋይ መጋቢ ብሥራት ታደለን፣

>> እንደዚሁም በምሑራዊ ችሎታው መጽሐፉ ጥልቀታዊ ነው፣ በማለት ለብዙኃን አንባቢያን እንዲመቻች በሚለው ሐሳብና ፍሰቱንም በሚመለከት ዙሪያ ላይ አትኩሮት በመስጠት ተደጋጋሚ አስተያየትና ተጨማሪ እርማት ያበረከተውን ልጄን ደሲታ ቡኩሎ ለፋሞን፣

>> በመጨረሻም በመጠኑም ቢሆን ጠቃሚና ቋሚ አስተያየት ላከለ ልጄ ስምዖን ሔልሶን፣





>> ሁላቸውንም በአንባቢያንና በራሴ ስም፣ በውሪምና በቱሚም የሚፈርደው (ባለ መክፈቻው) ካህን እስኪነሣ ድረስ ለዘመናት ተዘግቶ የኖረውን መልካሙን መዝገብ (ሰማዩን) ጌታ ይከፈትላቸው፣ በረከትንም አትርፎ ያፍስላቸው አሜን፣ እያልኩ (ዘዳ.28፡8፣ ቁ. 12፣ ዕዝራ 2፡63፣ ነህ.7፡65፣ ሚል.3፡10)፡፡ እነርሱም ሳይለግሙ የቀድሞ ጎተራቸውን አፍርሰው በረከቱን ለማከማቸት የሚችል አዲስና ቅዱስ ሠፊ ጎተራውንና መጋዘናቸውን በር ያለ ገደብ ይከፈቱ እላለሁ፡፡

| ቁጥር | ማውጫ | ገጽ |
|---|---|---|
| i | የመጽሐፉ ዋና ርዕስ የሐሰት እውነት፣ የእውነት እውነት የተባለበት | 11 |
| ii | የጸሓፊው መልእክት | 14 |
| iii | እልሀ አስጨራሹ የጸሓፊው እውነት ፍለጋ | 16 |
| iv | ፈረሱን ከሙታን ለማስነሣት የተደረገ ጸሎትና ወደ ሙሉ ጥያቄ መመለስ፣ በሰበቡም የተቀጣጠለው ወንጌላዊ ሰደድ | 18 |
| v | ትንሽ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ | 21 |
| vi | መግቢያ | 25 |
| | ክፍል አንድ | |
| 1 | ፋሲካ | 31 |
| 1.2 | የግብፁ የፋሲካ አፈፃፀም መመሪያና ዝግጅት | 32 |
| 1.3 | የታረደው እንስሳና ዓይነቱ | 32 |
| 1.4 | ፋሲካ በታሪካዊነቱ | 33 |
| 1.5 | ‹‹ፋሲካ›› በትምህርታዊነቱ | 35 |
| 1.6 | ፋሲካ (ትርጓሜው) | 35 |
| 1.7 | ሞት የማያመልጡት ዕዳ የበደል ዋጋ ነው፤ | 37 |
| 1.8 | የፋሲካው ሕግ እና መስፈርቱ፦ | 59 |
| 1.8.1 | እንግዳ ሰው ከእርሱ አይብላ፤ | 61 |
| 1.8.2 | በብር የተገዛ ባርያ ቢኖር፤ ከተገረዘ በኋላ ከርሱ ይብላ፤ | 62 |
| 1.8.3 | መፃተኛና ሙያተኛ ግን ከእርሱ አይብሉ፤ | 63 |
| 1.8.4 | በአንድ ቤትም ይበላ፤ | 63 |
| 1.8.5 | ከሥጋው አንዳች ወደ ሜዳ አታውጡ፡- ሜዳ? (ውጭ) | 64 |
| 1.8.6 | አጥንትም አትሰበሩበት፡- አጥንት?? | 68 |
| 1.8.7 | እንግዳ ሰው በመካከላችሁ ቢቀመጥ ለእግዚአብሔር ፋሲካ ሊያደርግ ቢወድድ አስቀድሞ ወንድ ሁሉ ይገረዝ፣ | 70 |
| 1.8.8 | ‹‹ከናንተ አንድ ሰው እስኪነጋ ድረስ ከቤቱ ደጅ አይውጣ›› | 71 |
| 1.8.9 | ያልተገረዘ ሁሉ ግን ከእርሱ አይብላ፣ | 79 |
| | | |






የጌታ ሥጋ መድረሻና ምንነቱ፣


| ቁጥር | ማውጫ | ገጽ |
|---|---|---|
| | ክፍል ሁለት | |
| 2 | የሰገነቱ እራት፣ | 82 |
| 2.2 | ከንጉሥ ማዕድ መብላት፤ (መካፈል፤) | 86 |
| 2.3 | ፋሲካን ሳይገባ ስለ መካፈል | 89 |
| | ክፍል ሦስት | |
| 3 | ከመስቀሉ፣ የፈሰሰው ደምና ውኃ | 94 |
| 3.1 | መስቀል፤ | 94 |
| 3.2 | ውኃ | 95 |
| 3.3 | ውኃ ከደም ጋር | 97 |
| 3.4 | ደም በታሪክ ደረጃ | |
| 3.5 | ደም ሳይፈስ ሥርየት የለም፤ | 106 |
| 3.6 | የጌታን ሞት ስንመለከት፣ | 117 |
| 3.7 | ቃል፣ ውኃ ስለመሆኑ፤ | 125 |
| 3.8 | ነፍሰ-ገዳዩና ተበቃዩ | 133 |
| | ክፍል አራት | |
| 4 | ሥጋ እና አፈር | 150 |
| 4.1 | ሥጋና መንፈስ | 153 |
| 4.2 | ቃል ሥጋ ሆነ | 156 |
| 4.3 | መሰቀል እንዴት ነው? | 162 |
| 4.4 | የሰው ሥጋ ተቃራኒነት | 185 |
| 4.5 | (ሞትና ሕይወት፣ በሥጋና በመንፈስ መካከል፤) | 189 |
| | ክፍል አምስት | |
| 5 | መቃብር | 192 |
| 5.1 | መቃብር በውጭ በአሕዛብ፤ | 192 |
| 5.2 | መቃብር በእስራኤል፤ | 201 |
| 5.3 | የእስራኤል አገር የሞትና የትንሣኤያቸው ልዩነት፤ | 208 |
| 5.4 | አምስት ዙሩ የእስራኤል ሞትና መቀበር | 212 |
| 5.5 | መቃብር በመለኮታዊ፣ (በሰማያዊ ሥፍራ) | 216 |
| 5.5 | የሙሴ መቃብር | 218 |




በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፤ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፤ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

| ክፍል ስድስት | | |
|---|---|---|
| 6 | በሦስተኛ ቀኑ ባዶ የሆነው መቃብር (የሥጋው መድረሻና ምንነቱ፤) | 235 |
| 6.1 | የሄኖክ፣ የሙሴና የኤልያስ ሥጋ ወዴት ደረሰ? | 243 |
| 6.2 | የቀብሩ ሥነ-ሥርዓት | 250 |
| 6.3 | ደቀ-መዛሙርቱ በመቃብር ዙሪያ | 259 |
| 6.4 | እኛ አሕዛብ በትንሣኤ ዙሪያ | 263 |
| | ማጠቃለያ | 273 |








የመጽሐፉ ዋና ርዕስ የሐሰት እውነት፣ የእውነት እውነት የተባለበት

«የሐሰት እውነት፣ የእውነት እውነት» የሐሰት እውነት፣ የእውነት እውነት ለሚቀጥሉ መጽሐፎቼ ሁሉም ዋና እርዕስ ነው፤ ይህኛው ከሚቀጥሉት መጽሐፎቼ አንደኛ ምስክር ሆኖ በሐሰት እውነት ላይ ቀርቧል፡፡

‹‹ሐሰት›› ሐሰት እንጂ እንዴት ከእውነት ጋር ተዛረፈ? በግልፅ ስሙስ ምንድነው? ሐሰት ራቁቱን ከሆነ፣ ካልተሸፋፈነ የሌለ ባዶ ነገር ነው፡፡ ሐሰት የሚጠራው በውስጥ ማንነቱ ሳይሆን በውጭ ሽፋኑ ነው፡፡ ሐሰት አንድ መልክ የሆነ (Identity) የለውም፡፡ በነጭ ከተሸፈነ በነጩ፤ ጥቁር ከለበሰም በጥቁሩ ይጠራል፤ ቀይ ከለበሰም ቀይ ሳይሆን ቀይ እየተባለ በመጋረጃው እየተጠራ ያለቋሚ አድራሻ ከሽፋን፣ ወደ ሽፋን እየቀያየረ እንደ ሽሽ ይኖራል፡፡ ሐሰት የበግ ለምድ ተሸፋፍኖ በግ ሳይሆን፣ በግ ተብሎ እንጂ በማንነቱ ግልፅ ሆኖ፣ ተራቁቶ፣ በሰው ፊትም ሆነ በእግዚአብሔር ፊት ደፍሮ ለመቆም ከቶ ፅናት የለውም፤ አዳሞች ተፈጥሮው ከዳቸውና ብቻቸውን በንፁህ ማንነታቸው መቆም አቅቷቸው አስቀድሞ ቅጠላ ቅጠልን ተሸፋፈኑ አላዋጣም፣ ቀጥሎ ዛፎችን ተከለሉ አልተሸፈኑም፤ የተጋረዱት ነገር ሁሉ በንኖ ጠፋና ሲቅበዘበዙ ተደረሰባቸው፤ (ዘፍ. 3፡7-8)፡፡ ማንነት ራቁት ነው፡፡ ራስን በመቀያየርና በመለዋወጥ በመደባበቅ በአስመስሎ እስከ ዛሬ ያለ መቆሚያ የቀጠለ ነገር የተጭበረበረ ቅይጥ እንጂ የጠራ ሐሰት ወይም የጠራ እውነት ሆኖ ስላላገኘሁት ይህን እውነትንም ሐሰትንም እየሆነ ዘላለም ተቅበዝባዡን የሐሰት እውነት ብዬ ጠራሁት፡፡ የሐሰት እውነት ማለት ነጥሮ፣ ተነጥሎ ወጥቶ ደረቱን ነፍቶ የሚቆም አይደለም፡፡ የሐሰት እውነት፣ ዲያብሎሳዊ የሆነው፣ መልኩ እውነት፣ መንፈሱ ሐሰት ሆኖ ተቀናጅቶ ሲጓዝ ለዝንተ ዓለሙ የኖረ፣ የጭቃ ውስጥ እሾህ፣ ማር የተቀባ መርዝ፣ በዔሣው ሽፋን ያዕቆብ፣ በራሄል ሽፋን ሊያ፣ በወንጌል ሽፋን ወንጀል፣ በስም ብቻ ክርስቶስ፣ በእባብ ሽፋን ዲያብሎስ በመልኩ ብቻ ጴጠሮ-ጳውሎስ...ወዘተ ማለት ነው (ማቴ.24፡23-24፣ 2ቆሮ.11፡12-15)፡፡

የሐሰትን መሸፈኛ የገፈፈውና በብርሃኑ ኃይል አራቁቶ፣ ቁልጭ አድርጎ በቀጥተኛ ስሙ ብርሃኑን፣ ብርሃን ሲል፣ ጨለማውን ጨለማ ብሎ በመጥራት ሊገልጥ የቻለው ብርሃን የሆነው ጌታ እግዚአብሔር ብቻ ሆኖ እናገኛለን፡፡

ሐሰት የተጋለጠበት ስሙ ምንድነው? የተጋለጠበት ስሙ በባለሥልጣኑ ዲያብሎስ ተብሎ ተለየ፤ (ዮሐ.8፡44) ጓዙ ጨለማ፡፡ ከዚህም ሌላ ለምሳሌ፣ የቤተ-ክርስቲያን መሠረት ሆኖ የተጠራውን ጴጥሮስን መስሎ/ተሸፋፍኖ ይከተለው የነበረውን ጌታ ኢየሱስ መሸፈኛውን ገፍፎ በትክክለኛ ስሙ ‹‹ሰይጣን›› ብሎ ገለበው፤ (ማቴ.16፡21-23)፣ የሰውን አካል ተጋርዶ፣ ሰውን መስሎ፣ ተደበላልቆ ይልቅም ‹‹ምስጋና ለእግዚአብሔር›› በሚል ስያሜ የሚጠራውንና (ዘፍ.29፡35) ወንጌላዊ ሆኖ፣ በሽተኞችን እየፈወሰ፣ አጋንንትን እያወጣ፣ ሙታንን እያሥነሣ፣ ዓለምን ትቶ፣ ለወንጌል ሙሉ ጊዜውን ሰጥቶ የተከተለውን ይሁዳን አበጥሮ፣ አንጠርጥሮ አውጥቶ ‹‹ዲያብሎስ›› በማለት ከእውነት የተደባለቀውን ሐሰት ለየው፣ (ዮሐ.6፡70-71) የሐሰት እውነት ደግሞ የዲያብሎስ እውነት ነው፡፡

- እውነት ምንድነው?
- የእውነት እውነት ማለትስ ምን ማለት ነው?

እውነት ክርስቶስ፣ የእውነት እውነት የክርስቶስ እውነት፤ ወደ እውነት ሁሉ የሚያደርስ መንፈስ ነው፤ (ዮሐ.16፡13፣ 1ዮሐ.5፡7) እውነት ግን ማንንም ሳይጠጋ፣ የማንንም ድጋፍ ሳይፈልግ ምንንም ሳይመስል ብቻውን ራሱን ብቻ ሆኖ በራሱ የሚኖር ግልፅ፣ ብርሃን ስለሆነ በምንም የጨለማ ጥገኛ አይደለም፤ ‹‹ጨለማ ከቶ በእርሱ ዘንድ የለምና፤ (1ዮሐ.1፡5፣ 1ጢሞ. 6፡16)፡፡

የእውነት እውነት፣ በክፉ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ያልተዳቀለና ያልተከላለሰ ከዋናው ምንጭ ከእግዚአብሔር ዙፋን በቀጥታ የሚፈልቅና ማንም ሰይጣን ሆነ ሰው ባንተና በጌታ መካከል ጣልቃ ሳይገባና ሳይሰማ በቀጥታ በገዛ ጆሮህ ከእግዚአብሔር የምትሰማው ቀጥተኛ ቃል ማለት ነው፡፡ ይህም ቃል ሰው ቢያደርገው ኖሮ በሕይወት የሚኖርበት፣ ቢያፈርሰው ወደ ሞት የሚወርድበት (ዘፍ. 2፡16-17፣ ዘሌ. 18፡5፣ ሕዝ. 20፡11፣ ቁ. 13፣ 21፣ ዳን.7፡10፣ ራዕይ 22፡1) ዘላለማዊ እውነት የሆነ ሕግ ማለት ነው፤ ሕጉም ቃል፤ ዘዳ.30፡11-14፣ ቃሉም ሕያው ቃል፤ (1ዮሐ.1፡1-2፣ ዮሐ. 6፡68) ነው፡፡







ከእግዚአብሔር ቀርቦ በቀጥታ በራሱ ጆሮ የማይሰማ ሰው ሁልጊዜም የተበከለውን (የተዳቀለውን) የሐሰትን እውነት ይሰማል፡፡ ሔዋን ከእግዚአብሔር በአዳም ጣልቃ ገብነት ድፍርሱን ስለሰማች ዕፁ መሠረት ላይ አልቆመችም ...ወዘተ፡፡ ድፍርስ ማለት፣ ያልጠራ የሐሰት እውነት ማለት ነው፡፡ ጌታ ሁላችሁም እኔን ስሙ፤ ስሙ ብቻም ሳይል አስተውሉም የሚለው ለምንድን ነው? (ማር. 7፡14) በሰው ላይ እምነትን ስላጣ አይደለሞይ? ከምድር የሆነ የምድሩንም ይደባልቃል፤ (ዮሐ. 3 31)፡፡ የሐሰት እውነት፣ የዝንተ ዓለሙ፣ የዘላለሙ ሆኖ የኖረ የጨለማው ኃይል፣ ውሸቱን ትልቅ፣ ሐሰቱን ኀሊያድ፣ አስመስሎ ተራራ ስለሆነ ‹‹...እናንተ ትለዩአቸዋላችሁ፣ (ሚል. 3፡18) ተብሎ እንደ ተጻፈ እንድለይ ይህችን ደረቷን ነፍታ የቀረበችና እሳት የሆነች ኩራዝ ይዘን በጨለማው ግርዶሽ ላይ እንዝመት፡፡

ከኖ በተባለው ሳሙኤል

የጸሓፊው መልእክት፡

«የተከበራችሁ አንባቢያን (ቴዎፍሎሶች) ሆይ፤ ከመጀመሪያ በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን፣ በእኛ ዘንድ ስለተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራ ለማዘጋጀት ስለሞከሩ እኔ ደግሞ ስለተማራችሁት (ስለሰማችሁት) ቃል እርግጡን፣ የእርግጡን እርግጥና የእውነቱን እውነት እንድታውቁ በጌታ ጸጋ በተቻለ ጥንቃቄ ይህችን መጽሐፍ በፊታችሁ አኖሬያለሁ፣... (ሉቃስ 1፡1-4)» ወደ ውስጧ ግቡ፣ ኅራ በሉ፣ ዝለቁ፣ ቅመሱዓት ፍሬው እውስጥ ነው፤ ሰው፣ ሰው በነበረበት ወቅት እንዲበላ የተፈቀደው የወጪ ገለባው ሳይሆን የውስጡ ፍሬው ነውና (ዘፍ.1፡29)፡፡ የውስጡ መከፈቻ አለንና ፍሬው እውስጥ፣ ውስጥ ነው፡፡

ለውስጡ ታውረን ኖረናል፤ በገሃዱ ዓለም ጨለማን አስወጋጁ፣ የምድርን ዕውርነት ፈዋሹ፣ በተለምዶው ማነው? የተለምዶውን ጨለማ አስወጋጁ የምድርን ዕውርነት ፈዋሹ ፀሓይ ነው አይደል? ፀሓይ ብቅ ሲል የምድረ ጨለማ ይወገዳል፡፡ በውስጧ ጨለማ የተቀበረ፣ የተዘራ ነገር ሁሉ ፀሓይን ሲያይ ወደ ፀሓይ እየተሳበ ይበቅላል ያድጋል፤ ለፍሬ ይበቃል፡፡ ይህ ማለት ክርስቶስ ሲነሣ ሁሉን ወደ ራሱ እንደሚስብ ሁሉ (ዮሐ.12፡32) ፀሓይ ድምፅአልባ አስተማሪያችን ነው፡፡ የተለምዶ ፀሓይም በራሱ የብርሃን ምንጭ እንደ መሆኑ መጠን የፈጣሪው የክርስቶስ ምስክር፣ መንፀባረቅ ነው፤ ፀሐይ የክርስቶስ ምስክር እንደ መሆኑ መጠንም የምድርን ዕውርነት ከማስወገዱም በላይ የሞትን ጥላ ገፍፎ (ኢዮብ 34፡







22፣ አሞፅ 5፡8) ከእንቅልፏ በማንቃትና በማስነሣት በብርሃን እንድትቦርቅ፣ እንድትለመልም ያደርጋታል፡፡ እኔስ? እናንተ/ችስ? ድምፅ አልባ የሆነው ፍጥረት እንኳ የፈጣሪው ምስክር ሲሆን (መዝ. 19፡1-4) እርሱ የዓለም ብርሃን የሆነው ጌታ በገዛ-ራሱ የክብር ስሙ ሲጠራን «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፣ (ዮሐ.8፡12' ማቴ.5፡14)» በማለት ሰይሞናልና ምስክሩ እንደ መሆኔ መጠን ትንፀባረቅ ዘንድ ይህችን የብርሃን ጨረሬን ልኬላችኋለሁ፡፡

## እልሀ አስጨራሹ የጸሓፊው እውነት ፍለጋ

በ1956 ዓ.ም በወጣትነት ዕድሜ፣ አዲስ በሥራ በተሠማራሁበት አካባቢ ከለመድነው ሥርዓት በተለየ ሁናቴ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰብኩ ሰዎችን አገኘቸዋለሁ፡፡ የራሴን ቤተ-ክርስቲያን አስተምህሮ በመደገፍ ባቀረብሁት ክርክር በደፈናውም ቢሆን ለጊዜው እንደ አሸናፊ ተቆጠርሁ፡፡ ይህ ገጠመኝ ሞራል ሆኖኝ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ተጨባጭና አስተማማኝ እውነት እደርስ ይሆን? የሚል ብርቱ ስሜት በውስጤ ተቀሰቀሰና በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ዲፕሎማ ደረጃ ያለውን ሰው ለማነጋገር በአሁኑ ስያሜ ‹‹ክልል›› አቋርጬ ወንዝ ተሸግሬ ሄድሁ፤ ቀደም ሲል ይህ ሰው የወንጌል ፍቅርን ተሞልቶ ሲሰብክ ሰምቼው ነበርና፡፡ በቤቱ ቡና እየፈላ ሳለ ሌላ ጎረቤቱ ቀደመና ቡና ጠጡ ሲለን በጎረቤቱ ቤት ሳለን ቡና ቀረበና ስኒ በእጄ ይዤ እንዳለሁ፣ ወንጌላዊውን፣ ‹‹እኔም አንተ በተማርህበት ትምህርት ቤት መጽሐፍ ቅዱስ መማር ስለምፈለግ ስንቅ አዘጋጅለሁ፡፡ ነገር ግን እስከዚያ ድርስ ባጋጣሚ ከሞትሁ እውነቱን ሳልጨብጥ መሞቴ ስለሆነ «እባክህን! ለእውነት አንገቴን እሰጣለሁና»፣ የሆነ የተረጋገጠ ትምህርት አሁን አስጨብጠኝ አልሁት፡፡ ሰውዬውም አስደንጋጭ ጥያቄ ሆኖበት ጥቂት ካሰበ በኋላ አስተማሪዎችን (ፈረንጁ) ያለውን ልንገርህ፣ አለኝና «ከመላ በአውራጃችን ከሚገኙ በሚሊዮን ከሚቆጠሩ ምእመናን ውስጥ በቁጥር ሦስት የሚያህሉ ሰዎች ድነው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት የሚችሉ ቢሆን በጣም ብዙ ነው ብሎናል» ብሎ ሲመልስልኝ ጊዜ በመደነቅ የያዝሁትን ስኒ ከነቡናው መሬት ላይ ቁጭ አደረግሁና በድንጋጤ ተሞልቼ ኧረክ!! ነገሩ እንዲህ ከሆነ ታዲያ የእኔ እምነት ምን ዋጋ አለው!! አሁን እክዳለሁ፤ መካዴን ግልጽ ለማድረግ አሁን አረቄ ፈልጌ እጠጣለሁ፤ አረቄ ጠጥቼ በደንብ እረክሳለሁ እያልሁ በኀዘን የተሞላ ድምፄን ከፍ አድርጌ እያሰማሁ ቡናው መሬት እንዳለ ከቤቱ ወጥቼ አረቄ ሱቅ ፍለጋ መንገድ ቀጠልሁ፡፡ ፈረንጁ ሦስት ሰዎች ሲል ያስቀመጠው ቀጥር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ በፊደሉና በመንፈሱ አኳያ መታየት ነበረበት፡፡ እኔም በመንገድ እየገሠገሥሁ ራቅ እንዳልሁ ልቤ በኀዘን ተሞልቶና እንደ ካድሁ ቆጥሮ ይመታኝ ጀመር፤ እየተንዘሁ እንዳለሁ ውስጤ እንዴት አንድ ቀን እንኳ ወደ ኃጢአት የማልገባበትን መንገድ የሆነ ሙከራ ሳላደርግ እንዲህ በቀላሉ ልክድ ነው? እያለ እየታገለኝ ስሄድ እመንገዱ ዳር አንድ ቦታ ከፍ ብሎ ያደገ ሣር አየሁ፡፡ ከዚያም እሣሩ ውስጥ ገባ አልሁና መንበርከክ የሚባለው ትክክል መስሎኝ ተንበረከክሁና «ጌታ ሆይ በዚህች በዛሬዋ ቀን ስሕተት ውስጥ ሳልገባ እንድውል ኃይል ስጠኝ» በማለት ድምፅ አሰማሁና ከቦታው ተነሣሁ፡፡ ዛሬ ኃጢአት ካሸነፈኝ፣ ነገ አረቄ እጠጣለሁ አልሁና፣ ዛሬ እፌ ሳይከፈት እንደ ተዘጋ ቢውል ኃጢአትን አሸነፍሁ ከሚል ስሜት ጋር ወደ ማርፍበት ሰፈር እየተንዝሁ፣ እኔ ማንበቡን እችላለሁ፣ መጽሐፉ የሚለውን ሁሉ እንዳለ እፈፅማለሁ፤ በቃ! እፈጽማለሁ ቢገለጥልኝ ይገለጥ እያልሁና ቃል እየገባሁ ስጓዝ ብቻ ይህ ነው በማይባል ደስታ ተውጬ ፀጥ፣ ዝም እንዳልሁ ማደሪያዬ ሰፈር ደረስኩ፡፡

ፈረሱን ከሙታን ለማስነሣት የተደረገ ጸሎትና ወደ ሙሉ ጥያቄ መመለስ፣

ይህ በእንዲህ እንዳለ ጥማት በተሞላ መንፈስ መጽሐፍ ቅዱሴን ከፍቼ ስጀምር የማነብበት ክፍል ሁሉ ተዓምር ሆኖ እየጣፈጠኝ ከመቀጠሌም በላይ መጽሐፉ የሚለውን ሁሉ እሺ! እኔ እፈጽማለሁ!! ከእግዚአብሔር የሚበልጥ ማን ቢያዘኝ እሺ ልል ነው? የሚል ቃል እየገባሁ ቀጠልሁ፡፡ የማይተረጎም ዜማ ከውስጤ ይፈልቃል፡፡ ልቤ በክንፍ በርሮ በሌላ ዓለም ውስጥ እያለ የነበረኝ ኃይለኛ ፈረስ በዚያው ሰሞን ይሞታል፡፡ ሰዎችም ጎትተው ጫካ ውስጥ ጣሉት፡፡ መዳን የሚባል የፈረንጁ ውስን ቁጥር በአእምሮዬ ሳይመጣ በደስታ መሞላቴ ብቻ በቅቶኝ ጥናቴን እጅግ ከፍ ባለ ፍቅር ተሞልቼ እንደ ቀጠልሁ አስቤበት ሳይሆን (ዮሐ.15፡7/ን ካነበብሁ በኋላ በጥቅሱ ተመርቼ ደግሞ ም. 14፡13-14/ን ጨምሬ አነበብሁና እንዲያው በፊደሉ ቃለ መልእክት ተጽናንቼና ተማምኜ ፈረሴ ጅብ ሳይበላው ካደረልኝ በመጽሐፉ ቃል መሠረት በጸሎቴ ከሞት አሥነሣዋለሁ በሚል ጥንካሬን ተሞልቼ አደርሁ፡፡

ጠዋት ሲነጋጋ አጠና ገንጥዬ ይዤ ዱካውን እየፈለግሁ ስሄድ ፈረሱ ጅብ አልበላውምና ተጋድሟል፡፡ ቀረብ በዬ ቆምሁና የጸሎት ቃሎቼን በዝርዝር ካሰማሁ በኋላ በቃለ-አጋኖ በአጠናው መታ አድርጌ በኢየሱስ ስም ተነሥ! አልሁ፤ ከዚያም ዓይኖቼን ስገልጥ ንቅነቅ አላለም፡፡ በሁለተኛ ዙር ከፊተኛው በተጠናከረ ጸሎት በጥሩ-ጥሩ ቅዱሳን ቃላት በታጀበ አንድ ባንድ ካሰማሁ በኋላ እምነትን እንደተሞላሁ እየተሰማኝ በአጠናው መታ አድርጌ በኢየሱስ ስም ተነሥ!! አልሁ፡፡ ፈረሱ ግን







ምንም አልንቀሳቀስ አለ፡፡ አሁንም እንዴ! ከፊተኞች ቃላት በመደነቅ ስሜት ሆኜ ለሦስተኛ ጊዜ በተመሳሳይ ቃል ከደገምሁ በኋላ ዓይኔን ብገልጥ ፈረሱ ባለመነቃነቁ እየተደነቅሁ አጣናውን ከእጄ ጣልሁና ታዲያ ምን ማለት ይሁን? እውነቱስ ምንድን ነው? እያልሁ ወደ ቤት ተመለስሁ፡፡ ምን ማለት ነው? የሚል ጥያቄ እንጂ በውስጤ የነበረ ፍላጎትና ጥማት እንደ ነበረ ነበር እንጂ አልቀነሰም፡፡ ጥቅሶቹን እያመሳከርሁና ንባቡን ብቀጥልም እያንዳንዱን ቃል ምን ማለት ነው? ምን ማለት ብቻ ሳይሆን፣ የማለትስ ማለት ደግሞ ምን ማለት ይሆን? እውነቱስ? እያልሁና ለማነበው ቃል ጌታ ሆይ፣ ካንተ በላይ ለማን እሺ እላለሁ? በረጅሙ ቃል እሺ!! እያልሁ፣ ተአምሩን እየሰማሁና እያየሁ ጥናቴን ቀጠልሁ፡፡ ሰዎች፣ ምስክርነቴንና ሁኔታዬን እያዩና እየሰሙ እየተደነቁ ምን ሆኗል? አበደ? እያሉ ሲደነቁብኝና በምናገረው ሁሉ እየተገረሙብኝ በቤትም በውጭም ምስክርነቴን እያሰማሁ ቀጠልሁ። በየምሽቱ ሊሰሙኝ ሰዎች ይሰበሰባሉ፡፡ የሚሰማኝ ሁሉ እንደ እኔም በደስታ መዝሙር ይሞላ ነበር፡፡ በየጣልቃም ብድግ እያሉ ይዘምሩ ነበር፡፡ ማንበብ የማይችሉ ሁሉ እያዳመጡኝ እንዴት ነው? የሳሙኤል መጽሐፍ ቅዱስ ከናንተ መጽሐፍ ቅዱስ ሌላ ነው ወይ? እያሉ ይጠይቃሉ፡፡ እርሻ የሚያርሱ፣ በቤት የሚሠሩ፣ ከብት የሚጠብቁ፣ ሣር የሚያጭዱ፣ ለውኃ ወንዝ የሚወርዱ ሁሉ ይዘምራሉ፡፡ አካባቢው ማዶ፣ ወዲህ ማዶ ሁሉ መዝሙር ይሰማል፡፡ ወጣ ብዬ ሰብከት ባቀረብሁ አካባቢ ወረዳው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሳይቀር ምን አዲስ ነገር መጣ? በሚል ይጠያየቅ፣ ይደነቅ ነበር፤ ነገር ግን ተቃዋሚዎች በርከት ብለው ተነሥተውብኝ ስለነበረ ከአካባቢው ብሸሽም እንዲህ እያንዳንዱን

ቃል ምን ማለት ነው በማለት መጠየቄና ማጥናቴ በጠቅላላ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተስማማ ሆኖ ግን የተለየ አመለካከት ፈጠረብኝ፡፡

እንግዲህ ይህን እንደ እኔም እውነቱ ምንድን ነው? በሚል የሚቅበዘበዙ አያሌ ጠያቂዎችና ተመራማሪዎች ይኖራሉና ለብጤዎቼ ድጋፍ ይሆን ዘንድ የተረዳሁትን ላካፍል በሚል ይህን በመጽሐፍ መልክ ከአንደኛ መጽሐፌ ሁለተኛውን አስቀድሜ አቅርቤያለሁና፡፡







ትንሽ ስለ መ ጽ ሐ ፍ ቅዱስ (መክፈቻ ነውና)

ጽሑፉ የቀረበው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ስለሆነ እንደ መክፈቻ ትንሽ ስለመጽሐፍ ቅዱስ አየት ማድረጉ ይጠቅመናል፡፡

- «መጽሐፍ ቅዱስ» ምን ዓይነት መጽሐፍ ነው?
- ተልእኮውስ ምንድን ነው?
- «ቅዱስ» መባሉስ እንዴት ነው?
- መጽፍ ቅዱስ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ነው ወይስ የመጽሐፍ አመልካች ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ፣ ቅዱሱ (ስውሩ) የእግዚአብሔር ሐሳብ በሰው ፊደል (በገሃዳዊ) (በብሬል) /Braill/ ተጽፎ ወደ ውጭ ለሰው የቀረበ መልእክት መሆኑ በስፋት ሊረጋገጥ የሚቻል ነው:: «ብሬል» ፀሐፊው ሊልም ዳሰሳ፣ በእምነት ሳይሆን በማየት፣ በቁስ ዓይን ተዳስሶ ለማለት ነው:: በመንፈሳዊ ደረጃ ሲታይ ቁሳዊ ዓይን ቁስን ማየቱን ዳሰሳ (/Braill/) ብሎታል ጸሐፊው:: የቁስ ዓይን የሚያረጋግጠው በሚዳሰሰው በኮኺው (በጥላው) ሲሆን፣ እምነት ግን የማይዳሰሰውን ዋናውን (አካሉን) ስለሚያሰጨብጥ እምነት ከዓይን ይበልጣል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ቅዱስ እንደመሆኑ መጠንም የሰውን ቋንቋ ተላብሶ (ተጋርዶ) ሲተላለፍ በእኛ ላይ ደርሷል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በሰው ቋንቋ (በሐሰት እውነቱ) ግርዶሽ የእግዚአብሔርን መልእክት (የእውነት እውነቱን) በሽፋን ሲያስተላልፍ እስከ መጋረጃ መቀደድ ድረስ ኖሮአል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ተልእኮውም፤ ወደ ውጪ ጨለማ የተጣለውን (ዘፍ.3፡ 24) አዳም ልጅ መልሶ ወደ ውስጥ ብርሃን የሚጠራ መልእክት ነው፡፡

*መጽሐፍ ቅዱስ ምንጩ መንፈስ ቅዱስ መሆኑን እንዲህ ይገልፃል፣ «ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ-ራሱ ሊተረጉመው አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ (2ጴጥ.1፡20-21)» ቅዱስ መባሉም፣ ልዩ፣ (የተለየ) {SET-APPART} ተብሎ ይተረጎማል፡፡*

*መጽሐፍ ቅዱስ፤ ቅዱስ የመሆኑ እውነታው ከማንም አዳማዊ እይታ የተሠወረ፣ የተጋረደ፣ በእርሻ ውስጥ የተሰወረ መዝገብ፣ በሰውርም የተደበቀ ሀብት በመሆኑ ነው (ማቴ.13፡44፣ ኢሳ. 29፡10-12፣ ም. 45፡ 3)፡፡ እንዲህ ሲባልም ፊደላዊው መጽሐፍ ቅዱስ የቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል የመንፈሱ የክብር መጋረጃ ነው፤ በጨለማነቱ በውጭ የውስጥን ክቡር ገጽ ዙሪያውን ይከብባል፡፡ ማለት መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ መሆኑ በብዙኃኑ ሰዎች ዘንድ የታመነ ቢሆንም፤ ለሰው ሕይወትና ብርሃን የሚሆነው የፊደሉ መጋረጃ በጌታ መንፈስ ሲገለጥ ነው፣ (2ቆሮ. 3፡16)፡፡ መጽሐፉ ሕይወት ወደሚሆነው ክርስቶስ አመልካች እንጂ በራሱ ሕይወት አይደለም፤ (ዮሐ.5፡39-40) ቃልም ራሱ እግዚአብሔር ዓለማትን የፈጠረበት የተሠወረ የእግዚአብሔር ጥበብ/ምስጢር የሆነው ክርስቶስ (ቆላ. 2፡2-3፣ 1ቆሮ.1፡30፣ ምሳሌ 8፡1-36) ነው እንጂ በውጭ የምናነበው መጽሐፍ አይደለም፡፡ ነገር ግን በመጽሐፉ አማካይነት የተላከልን ቃል ራሱ እግዚአብሔር ነው፣ (ዮሐ.1፡1፣ ቁ. 14፣ ም.6፡68)፡፡ እንዲህ ሲባልም በመጋረጃ የተገለጠው ቃሉ (ክርስቶስ) ጥልቅ ነው ማለትም በእርሻ ውስጥ የተደበቀ መዝገብ፣ የተሰወረ መና፣ ነጩ ድንጋይ ስለሆነ ከማስተዋል የሚያልፍ ነው (ራዕይ 2፡17)፡፡*







*የመጽሐፍ ቅዱስ እውነታ፣ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት የሚረጋገጠው፣ ለማንም ወደ ውጭ ተራቁቶ (ተጋልጦ) በረከሰው በውጫዊ ማለት በፊደል (ፍጥረታዊ)(ገሃዳዊ) ገጹ ምስክርነት ብቻ ሳይሆን፣ ለማንም ባልተገለጠው ማለት በተጋረደው በውስጣዊው በመንፈስ ገጹ ምስክርነት ጭምር ሲሆን ነው፡፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስን፣ ቅዱስ የሚያሰኘው ውጫዊው (ግልፁ) የንባብ ገጹ ሳይሆን፣ የውስጡ የተሰወረው ገጹ ነውና፡፡ ክርስቶስ ወደ ዓለም ሲገለጥ በመጋረጃ እንደ እንደታየ ሁሉ እንዲሁ መጽሐፍ ቅዱስ የውስጥ፣ የብርሃን ገጹ በውጫዊው፣ በፊደል (ፍጥረታዊ)(ገሃዳዊ) (ጨለማ) ገጹ ክብር መጋረጃ የተሠወረ (የተሸፈነ) ነው፡፡ የንባብ ገጹ ለማንም የተጋለጠው ውጫዊ የሚታየው ጊዜያዊ እውነት ሲሆን፣ ውስጣዊው የማይታየው የዘላለም (2ቆሮ.4፡18) እውነት ነው፡፡*

*መጽሐፍ ቅዱስ ውስጣዊው የእውነት እውነተኛ ገጹ ግን ከታረደው በግ በስተቀር ወይም በጉ ከሚገልጥለት በስተቀር ከማንም (የተሠወረው)፥ በመጋረጃዎች ተለይቶ የተከለለ ቅዱስና ክቡር ገጽ ያለው በመሆን፣ የውጭና የውስጥ ገጽ፣ የፊደል (ፍጥረታዊ)(ግልፁ) እና የመንፈስ ገጽ፣ የድንጋይ ፅላትና የልብ ፅላት ገጽ፣ የሰው ጣትና የእግዚአብሔር ጽሕፈት ገጽ፣ የጨለማና የብርሃን ገጽ፣ የሞትና የሕይወት መጽሐፍ ሆኖ የቀረበና ከአእምሮ በላይ የሆነ የማረጋገጫና ማመሳከሪያ ያለው በመሆኑ ማንም አነበብሁ፣ ዐውቀዋለሁ ብሎ ደፍሮ ዝና ለማግኘት የጉራን ኃጢአት ተሞልቶ ሊተቸው ከቶ የማይችለው ልዩ መጽሐፍ መሆኑ ነው፡፡ የሞት መጽሐፍ የተባለው ለማንም ግልፅ የሆነው ነው ወይስ ከማንም የተሠወረው ነው? አንባቢ ይመልስ፤ መጽሐፍ ቅዱስን ለመተቸት በመጽሐፍ ቅዱስ መስፈርት መሠረት አስቀድሞ ቅዱስ ሰው ሆኖ ሳይገኙ ዝም ብሎ በተቃራኒ መንፈስ ተሞልቶ ቀድሞ ላረገዙት ኃጢአት ሰህተት*

ማደበሪያነት ወይም ድጋፍ በመፈለግ መጽሐፍ ቅዱስን መጥቀስ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥልን ተሞልቶ ስሀተት ከመፈለግ ጉጉት አንፃር መተቸትም ሆነ እንዲህ ነው ብሎ ደፍሮ ማውራት በገዛ ራስ ላይ መፍረድ ነው፡፡ የትኛውም ሃይማኖት ተከታይ ቢሆን መጽሐፍ ቅዱስን ለማየት አስቀድሞ የውስጥ መብረት መለኮስ አለበት እንጂ በውጭ መብራት፣ በውስጥ ጨለማ አንብቦ ዐውቃለሁ የማለት ኃጢአት በምንም ፆም፣ በምንም ጸሎት፣ በምንም ራስ እግር ሆኖ ስግደት አይሠረይም፡፡ ይኸው ኃጢአቱ ከልቡና መዝገብ ሲፋቅ ከቶ ያልቻለው ቁልጭ ብሎ ለባለቤቱ ይታያል፣ ይነበባል፤ ለምን እንዋሻለን? ለምንስ ከቶ በማናውቀው ነገር ዕዳ፣ ከሜዳ?

(ቅዱስ-ቅዱስ-ቅዱስ፤)







## መግቢያ

የሰው የጋራ ወላጆች የነበሩ ቀዳሚ ሰዎች የጋራ አምላክ በተባለው ፈጣሪ ላይ አመፀኛ/መንግሥት ግልበጣ ማካሄዳቸው በብርሃን ምስክሮች የተረጋገጠው ቃለ-ምስክር በብዙኃኑ ታምኖና ተጽፎ በተለያዩ የዓለም ቋንቋዎች እንደ ተተረጎመ እሙን ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ሰው ተብዬው ሲንጠራራ ወሰን ጥሶ ራሱን ከእግዚአብሔር ከዋክብት/ብርሃናት በላይኛው ወንበር ላይ ለማስቀመጥ ያለ ዕቅዱ (ኢሳ. 14፥ 12-20) እጅ ሳይነካው በራሱ ከሸፏል፡፡ በራሱ ተገልብጦ ዕዳ ከሜዳ ሆኖበት የመጨረሻዋን ሳንቲም እስኪከፍል ድረስ ከዚያ ከቶ ወደ ማይወጣበት ወሀኒ ጨለማ ጣረ-ሞት ለጨካኙ ሎሌ አልፎ ተሰጧል (ማቴ.5፥25-26)፡፡ ወደ ላይ ዐረግሁ ሲል ለማዩ ምድር ሆኖበት ተገልብጦ፣ ላዩ ታች ዞሮበት ተደፍቶ፣ መቅረቱ ከፍታን በተመኘበት ጨለማ ዓይን አልታየም፡፡ ማንም ሰው ወደ ላይ ከፍ፣ ከፍን ሲመኝ ሌላኛውን ገጽ ስለማማያይ ዕውር ይሆናል፡፡ ማንም እግዚአብሔርን ካላየ በጨለማ ነው፡፡

የመጨረሻዋ ሳንቲም ምንድን ነች? የመጨረሻዋ ሳንቲም ሁሉ ነገር ረግፎ አፈር ሲሆን፣ በመጨረሻ የምትቀር ከገንዘብ ሁሉ አነሥተኛ የሆነች የመጨረሻዋ ገንዘብ መሆኗን ጥናቱ (ማቴ. 5፥26)ን ጠቅሶ (አ.መ.ት) ያሥረዳል፡፡ የመጨረሻዋ ሳንቲም መጨረሻ የተባለችው ለምንድን ነው? ከፍ ያለው ክቡሩና ፊተኛው የሆነው መጀመሪያው መጨረሻ እስከሚሆንበት ጊዜ ድረስ ተንቃ፣ ተጨቁና፣ በሰው ዘንድ ተረስታ የምትኖረውና ጌታ እጅግ የሚፈልጋት ገንዘብ ምን እንደሆነች (ዘፍ. 9፥5/ለ፣ ሕዝ. 18፡4) ያስታውሰናል፡፡ መጀመሪያውና ፊተኛው በሰው ዘንድ ክቡሩ ከፍ፣ ከፍ እየተደረገ ከፍታ ላይ የሚኖረው ማን ነው? ሳንቲሟን የበላውና መክፈል የሚገባው ባለዕዳስ ማን ነው? አዳም በደሙ ውስጥ ከነበረ ዘሩ ሁሉ ጋር የበላና መክፈል የሚገባው ባለዕዳ ለመሆኑ ራሱ በራሱ ላይ በአፉ መመስከሩን መጽሐፍ ጨምሮ አረጋግጧል፤ (ዘፍ. 3፡9-

13) ከመርዝ ጋር አምነ የበላትን ነፍስ ከመራራ ቅጠል (መርዝ) ጋር አምነ በልቶ እንዲከፍል (ዘፀ.12፥8) የተመለከተው ፋሲካ አበላል ያመለክታል፡፡

ከየት አምጥቶ፣ ምን ይከፈል? ዕዳው (ዋጋው) ሞት ሳይሆን፣ የሞት፣ ሞት ነው፣ (ሮሜ 6፥23) በበላህ ቀን ሞትን፣ ትሞታለህ ተብሎ አስቀድሞ ተፈርዷል፣ (ዘፍ. 2፥16-17) አዳም፣ ድንጋጌውን አስቀድሞ አንብቦ አይቶ አረጋግጦ በድፍረት ነው የበላው፣ የበላነው፡፡ እርሱ ከእርሷ ጋር በላ፣ እኛ ከእርሱ ጋር በላን፡፡ ሕይወትን በልቶ ሞትን መክፈል አይሆንም፤ ደህና በሬ በልቶ የሞተ በሬ ቢከፍሉህ አንተምኮ አትቀበልም፣ አይሆንም፡፡ ሕጉ የሚለው ነፍስ በነፍስ / ሕይወት በሕይወት ነው፣ (ዘፀ. 21፥23-25) የነፍስ ዋጋ ነፍስ ሲሆን፣ አዳም ያላት ነፍስ በብርሃን በኩል ሆኖ ሲታይ በኃጢአትና በበደል የሞተች ናት፤ (ኤፌ. 2፥1፣ ሕዝ. 18፥4፣ ቁ. 20)፡፡ በጨለማ ሲታይ ግን ሕያዊት ናትና ጠጅ ትጠጣለች፣ ትደንሳለች፣ ትዘፍናለች፣ እልል ትላለች፤ ታሸበሽባለች፣ ታጨበጭባለች ታላቅ ኃጢአት፡፡ አዳም ያላት ነፍስ አንድ ብቻ ናት፤ እርሷም ሙት፡፡ ምን ይከፈል? አዳም መርዝ በልቶ ወደዚህ ወደ እግዚአብሔር ሞቶ ወደዚያ ወደ ሰይጣን ሕያው ነው፡፡ አሁን በሰይጣን መልክ ምሳሌ ተለውጦ ተቀርፆአል (ሞዲፋይድ ሆኗል)፡፡ አሁን ሰይጣን ስለሆነ ዓለም ሁሉና ቤተ-ክርስቲያንም ሁላ እንደምታደረግ ሁሉ ከእግዚአብሔር፣ ከብርሃን፣ ማለት ከእውነት የማያዋጣ ነገር ተሸፈፍኖ ወደ ማያመልጥበት ጥላ ጨለማ ይሸሻል፡፡ ከአደሞች ተምሮ ሁሉም ቅጠል ለብሶ በማያመልጥበት ዛፍ ሥር የተሸሸገውን ሁሉ ይህ መጽሐፍ ያገኝዋል። አሁን አዳም አስቀድሞ የተደነገገውን ሕይወት ሕግ ጥሶ፣ በራሱ ላይ ፈርዶና ፈቅዶ እንደሞተ ሁሉ አሁን፣ የሞትን ሕግ ጥሶ፣ በገዛ-ራሱ ላይ ፈርዶ ፈቅዶ ከሕይወት ሞቶ የገደላትን የራሱን ነፍስ መልሶ ለመክፈል፣ ሕይወትን ሞቶ፣ ሞት ከሆነበት ሞትን ደግሞ ሞቶ ሕያው መሆን አለበት፡፡ የበላውን







ሞት፣ ለመሞት፣ በራሱ ላይ ፈርዶ በፈቃዱ ሞትን ሞቶ ገድሎ ለመክፈል በእርሱ ሕያው የሆነው ሞት፣ ክርስቶስ ሳይሆን «አጋግ» ነውና (1ሳሙ. 15፥32-33) በውስጡ ሆኖ የሞትን መራራ ፅዋ ለመጠጣት በውስጥ በጌታ ፊት ስለሚርድ ስለሚንቀጠቀጥ፣ ውጫዊ አካሉም አብሮ በሰው ፊት ይርዳል፣ ይንቀጠቀጣል፡፡ አዳምም በተጣማሪነት ያው ከሕያው ሰይጣኑ ጋር ይፈራል፣ ይርዳል፣ ይንቀጠቀጣል ማለት ነው፡፡ አንተም ከዲያብሎስ ጋር በተታማሪነት ትፈራለህ፣ ትንቀጠቀጣለህ፣ እኔም የሞትን መራራ ፅዋ ለመጠጣት ከፈሪ ጋር እንጂ ከክርስቶስ ጋር ስላልተጣመርሁ እፈራለሁ፣ እንቀጠቀጣለሁ፤ እርሱም ይንቀጠቀጣል፣ እሳቸውም፣ መጋቢውም፣ ዘማሪውም፣ ቄሱም፣ ገበዙም፣ ዲያቆኑም፣ ሽማግሌውም ወንጌላዊውም፣ ባለቴቱም ሁሉ የሞትን ፅዋ ለመጨለጥ ይፈራል፤ የሚፈራ ብቻ ሳሆን አብዛኛው ፈርቶ የሚስፈራ ብቻ ነው፤ (ዘዳ.20፡8፤ መሳ.7፡3)፡፡ (ዕብ. 2፥14-15) እንደሚያሥረዳ የኃጢአትን ዋጋ ሞትን ሞቶ ለመክፈል የሚደፍር ከቶ ስላልተገኘ ሁሉም የአዳም ዘር በአዳም የመጨረሻዋን ሳንቲም እስኪከፍል ድረስ ከቶ ወደ ማይወጣበት ጨለማ ወህኒ እሥራት ለጨካኙ ሎሌ አልፎ ተሰጥቷል፡፡ ይህን ታምናለህ ወይስ ይህንን ለመካድና ሌሎችንም ለማስካድ በቃለ አጋኖ ሃሌ-ሉያ!! አሜን፣ አሜን እያልክ በማጭበርበር ትገፋለህ? ምን ይሻላል? ምን ይሻላል? ፈርቶ ከሚያስፈራ፣ ክዶ ከሚያስክድ ጌታ ያድነኝ፡፡ አዳም ሁሉ አጋግ ነው፤ በሙሉ አጋግ። ይህ እውነት ነው ወይስ ውሸት? ሞትን ሞተህ ሕይትህን መቤዠት አለዚያ ሞቶ የሚቤዠውን ዋስ ጠርቶ ከጉያው መግባት፡፡

ስለሆነ እግዚአብሔር ተቸገረ፣ በእስራቱ ዘመን በ3/7ኛ ትውልድ ላይ እንዲያበቃ ለማድረግ መንገድ ለመቀየስ አሰበ፤ በመሆኑ ከአዳም ሀያ አንደኛ ትውልድ (3/7ኛ) ልጅ የሆነውን አብርሃምን መርጦ እስራኤልን ፈጠረና ለዓለም ትምህርት እንዲሆን እስራኤልን በግልፅ የጥላ ሞት ወደ ሆነ ባርነት አውርዶ ጠቅላላውን ዓለም በዚህ ሁኔታ ለመቤዠት ከሞት

*በሞት ወደ ሕይወት መሻገሪያ እንዲሆን ይህን የሰውን ጥፋተኝነትና የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ አምነው በተቀበሉትና በተመረጡት ሕዝቦች (እስራኤሎች) በኩል ጌታ ፋሲካን ሰጥቶ እርሱ ደግሞ እንዴት ፋሲካ ሆኖ እንደ ቀረበ ነው የተመለከትነው።*

*ስለሆነ፣ ይህች መጽሐፍ፣ ይህን ርእሰ ሀሳቡ የሆነውንና በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጭምብል {THE BIBLE DIFFEICULTIES} ከተባሉት አንዱ የሆነውን የጌታ ኢየሱስ ሥጋ በሦስት ቀን ከመቃብር ውስጥ የት ገባ? የሚለውን ጥያቄ የሞትን፣ የመቃብርን ምንነትና የሥጋን ማንነት ከትንሣኤው ጋር በተለየ ሁኔታ በመተንተን ምስጢሩን ወደ ብርሃን አውጥታለች፡፡*

*እንዲሁም መጽሐፉዋ የቀረበችው፡- እውነትን ብቻ ለመግለፅ ሳይሆን አልፎ ተርፎ ሰው ወርሶት ከኖረው ሰይጣናዊ በሆነው ከመሰሎ አጭበርባሪ እውነት ማለትም በሐሰት እውነት የተቀበረውን መለኮታዊ እውነት፣ በመለየት (በመቀደስ) ለመግለጽም ጭምር ነው፡፡*

*የእውነትን እውነት መግለጽ ደግሞ በማንም ያልታየውን እግዚአብሔርን መግለጽ ነው፡፡ እንደ ተጻፈም፣ እውነት ክርስቶስ/እግዚአብሔር ነውና፡፡ እንዲህ ብሎ መናገርም ታሪኩን ማውራት እንጂ መጋረጃውን መቅደድ ሳይደለ፣ እግዚአብሔርን መግለጽ አይሆንም፡፡ ክርስቶስ የእውነትን እውነት የገለጸው በታሪክ ደረጃ ሲነገር ታርዶ፣ ተገፎ፣ ከመጋረጃ ወጥቶ ነው፡፡ አውድማውን የሚያጠራበት ባለ መንሽም ነውና፤ (ማቴ.3፡11-12) ክርስቶስ የእውነት እውነት የሆነውን አብን ለመግለፅ ዙፋኑን የጋረደ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች (ከሰማይ እስከ ምድር) ከሁለት የቀደደው በፊደል (በገሃዳዊ) ብቻ ሳይሆን በመንፈስም ነው፣ ማለት ከሆነ እውነት*







*ይሆናል፡፡ እውነትን መግለፅ ደግሞ እግዚብሔር የሆነውን የቃሉን ምስጢር መግለፅም ነው፣ ቃሉ፣ ክርስቶስ እውነት ነው፤ በእግዚአብሔርና በቃሉ መካከል ልዩነት የለምና (መዝ.118፡142፣ ዮሐ.17፡17፣ ም.1፡1) አንተ ከመጋረጃ ሳትወጣ እግዚአብሔርን አምላክህ ነውና በብርሃን ልታሳይ አትችልም፤ አምላክህ በጨለማ ከሆነም አንተ ልትታይ ስለፈለግህ እርሱን ከልለኸው ጋርደኸው ትመላለሳለህና የሥራህን ታገኛለህ፣ እርሱን ውጠሃልና ከአዳም አትሻልም፡፡ እኔ እጠፋሁ ነኝ፣ አንተም ትፋው፡፡ በሕጉ መሠረት የዋጠ ይዋጣልና በእርሱ ተውጠን እኛምልጥ፡፡ አንተ እየታየህ እርሱን ጋርደህ ሰውረኸወው እንደ ኖርክ ሁሉ አሁን በእርሱ ከተጋረድክ ከሕጉ ፍርድ አመለጥክ፡፡ ሥራህ ተዋጠ፣ ተሠወረ፡፡ ከሥራችን ጌታ ያድነን፡፡*

*የእውነትን እውነት መግለፅ ማለትም በፊደል በልማዳዊ ሥርዓተ ሥያሜ ተሸፋፍኖና፣ ተቀብሮ በታችኛው ጉድጓድ ጨለማ ለኖረው መንፈሳዊ እውነት ትንሣኤ መስጠት ነው፣ ሙታንን አስነሡ ተብለን አልተላክንሞይ? ሞቶ የተቀበረው እውነት ነው ወይስ ሐሰት ነው? እውነትም ደግሞ ሕይወት የሆነው መንፈስ ነውና፣ (1ዮሐ.5፡7፣ዮሐ.6፡63)*

*ፍሬን ከገለባ፣ መንፈስን ከፊደል አካልን ከጥላ፣ ጨለማን ከብርሃን የእውነትን እውነት ከሐሰት እውነት ባለመለየት፣ ማደበላለቅን አይቼ፣ ተመለክቼ አረጋግጬ ይህን ለመጠቆም በተረዳሁበት መጠን በድካም በዚህች በሁለተኛ መጽሐፌ በፊታችሁ ቀርቤያለሁ፡፡*

*የቀረበው ግብግ እውነትም ሳይሆን፣ ሐሰትም ሆኖ ሚናውን ሳይለይ መኻል መተላለፊያ ላይ ደንቃራ የሆነውን ሐሰተኛ እውነት ከመተላለፊያ ላይ ለማስወገድ እምነትን የተሞላ ክንዳችንን አብረን እናንሣ ነው፡፡*

*ለ/ ክፍል አንድ፡- የእርሰ ጉዳዩ የሆነውን የጌታ ሥጋ ለማየት ማቋረጫው በተመለከተው ፋሲካ እንደመሆኑ መጠን፣ የፋሲካን ምንነት፣ ታሪካዊነት፣*

ትምህርታዊነት፣ ከሥርዓቱና ከትርጓሜው ጋር የእውነት እውነቱን የሚታይበት፤

ሐ/ ክፍል ሁለት፡- የሰገነቱ፣ ማለት ሰማያዊ ሥፍራ ራት፣ ማለትም የበጉ ሠርግ ራት የዕርቅ ደስ-ደስ ግብዣ ከተጠሩ ብፁዓን (ራዕይ 19:9) ጋር ወደ አደራሹ እንዴት መግባት እንዳለ የሚታይበት ነው።

በሰማይ የምትበላው ማን ሲሆን፣ በምድር የምትበላው ማነው? ምግቦቹ እርስ በርሳቸው ተቃራኒዎች መሆናቸውን ማስተዋል።

መ/ ክፍል ሦስት፣ ከመስቀሉ የፈሰሰው ደምና ውኃ ትንግርታዊነት ግልፅ እውነታው የሚታይበት፤

ሠ/ ክፍል አራት፣ ሥጋና አፈር በጥምረትና በተናጠል የሚታይበት ነው፤

ረ/ ክፍል አምስት፣ መቃብር፣ በውጭ በአሕዛብ፣ በውስጥ በእስራኤል፣ በውስጥ ውስጥ በመለኮት ይታይበታል፣

ሰ/ ክፍል ስድስት፣ የሥጋው መድረሻና ምንነቱ በሕይወት ብርሃን መታየት እንዳለበት ያመለክታል፤





## ክፍል አንድ

## ፋሲካ

ወደ ጌታ ሥጋ መድረሻ ስንጓዝ በፋሲካ እንደምናቋርጥ በመግቢያ ላይ አውስተናል። የፋሲካ ጅምር ከግብፅ የእስራኤል መውጣት ሌሊት የተደረገ ማዳን ከመቅሠፍት ጋር፣ መብሉ ከመራራ/መርዝ ጋር፣ ፍርድና ምህረት፣ ሕይወትና ሞት ተደባልቆ የቀረበ ነበር። ለእስራኤል ልደት፣ ሠርግ እልልታ፤ ለግብፅ ሞት፣ ዑዑታ፣ ዋይታ የተፈራረቁበት፣ መራራ ጦርነት የተካሄደበት ሥነ-ሥርዓት እንጂ እንደ ዛሬ ዓይነት በሬ፣ በግ እያረዱ በመብላት ጭብጨባ፣ ሽብሸባ፣ መሰንቆ በገና ጣፋጭ፣ ጣፋጩ ከቶ አይደለም።

የብሉይ ኪዳን ፋሲካ በውጭ በሜዳ ይደረግ የነበረው በእድገት እየተቀደሰ መጥቶ ከውጭ ወደ ውስጥ፤ ከሜዳ ወደ ጓዳ እየገባና ብሎም በትንሣኤ ከምድራዊነት ወደ ሰማያዊነት ከፍ እያለ ወደ ሰገነት ከፍታ ላይ መድረሱ ይታያል። ይህ ከግብፅ በመውጣት ሌሊት ላይ የጀመረው እስከ ውስጥ፣ ውስጥ ሕይወት ከፍታ ለመድረስ በፊደል (ፍጥረታዊ) አቆጣጠር አንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመት መጓዙን ጥናቱ ያመለክታል። የሕይወት ከፍታ ማለት የማንነት ከፍታ ለማለት ነው። ለማንም እይታ የተጋለጠው ወጫዊ፣ (ሜዳዊ) ሥርዓት በቅድስና ዕድገት ባለቤቱ ከፍ ሲል ከፍ ያላለ ከዘመናት በፊት በነበረበት ውጭ ሜዳ ጨለማ የቀረና እዚያው የሚካሄደው ሥርዓት ቅዱስ ነው ሊባል ከቶ ካለመቻሉም የማያድግ ነገር ሕይወት የሌለው በድን ነው፤ ክርስቶስ ከፍ-ከፍ እያለና እያደገ እመቅደሱ ገብቷል፤ አሁን ግን «እራቱ በጓዳ፣ ሥርዓቱ በሜዳ» (በውጪ ጨለማ፣ የጨለማ ሥራ ሆኖ የተተፋ መሆኑ አልታየ ብሏል)። ማለት አሁን በትንሣኤ እይታ የፋሲካው ሥርዓት እያደገ መጥቶ ሕያው (ሕይወት) ከፍታ ላይ በስውር የሚቀርብ ከሆነ ብቻ የእግዚአብሔር እቅድ

ፍጻሜና ቅዱስ፣ ሕያው ሥርዓት ነው ለማለት ይቻላል፡፡ አለበለዚያ እራት የሆነው ክርስቶስ በመቅደሱ የለም ከማለትም ትንሣኤውን በሥራ መካድ ይሆናል፡፡

የግብፁ የፋሲካ አፈፃፀም መመሪያና ዝግጅት ፡-

የእግዚአብሔር ምህረት የኃጢአት ዋጋ ሞት ሳይከፈል የለም፡፡ ፋሲካ ሁልጊዜም የኃጢአት ዋጋ ሞትና ምህረት ድብልቅ ሆኖ የሚታይ ነው፡፡ እስራኤል ከአባቶቻቸው አብርሃም፣ ይሥሐቅ፣ ያዕቆብ ያለማመንና አመፅ አለባቸው፡፡ አብርሃም እግዚአብሔር እንዲኖር ከፈቀደበት ከነዓን ወደ ግብፅ መውረድ፣ ይሥሐቅም ወደ ግብፅ ለመውረድ በማቀዱ ይሆናል ከለከለው እንጂ አልሸሸም ዞር ብሎ ወደ ጌራራ መሄድ፣ ያዕቆብም ወደ ግብፅ መሄድ ወደ ኋላ ወደ ዓለም መመለስ ነውና እዚህ ላይ እግዚአብሔር መቀየሙን እስራኤል በሞት ሽረት በፋሲካ መሥዋዕት ከግብፅ እስኪወጡ የተቀበሉት የብረት እቶን የተባለው የባርነት ሥቃይ ፍርድ የእግዚአብሔርን ቁጣ ይገልፃል፡፡ ዘፍ. 2፡10፣ 26፡2፣ ዘዳ. 4፡20፣ 1ኛነገ. 8፡51፣ ኤር.11፡4፡፡

ስለዚህ ፋሲካ እግዚአብሔር፣ እግዚአብሔርነቱ የኃጢአት/የበደል ዋጋ ሞት ሳይከፈል ከቶ የማይሻሻል እንደ መሆኑ መጠን የማስለቀቁ ውጊያ በእግዚአብሔር በኩል ቢሆንም እስራኤል በግብፅ ኃጢአት ላይ ከሚወርደው ፅኑ ቁጣው የኃጢአትን ዋጋ ሞትን ከፍለው፣ ከሞት በሞት/በደም ተሸፋፍነው ከግብፅ እንዲወጡ ያደረገበት ሥነ-ሥርዓት ነው፡፡

የታረደው እንስሳና ዓይነቱ፡-

1/ ተባዕት 2/ ነውር (እንከን) የሌለበት 3/ ሁለት ሰባት ማለት አሥራ አራት ቀን በቤት በስውር ተጠብቆ የተቀደሰ፤ 4/ ታርዶም ሥጋው በእሳት ተጠብሶ የተበላ እጅግ የተቀደሰ ነበር ማለት ይቻላል፤ (ዘጸ.12፡3-





6) ሁሉ በሁሉ ስውር ሆኖ መፈፀሙ ሁሉ በሁሉ የተቀደሰ ያደርገዋል፡፡ በእምነት የበላውም ሁሉ ቅድስናን ጠገበ ማለት ይቻላል፡፡

ከመጀመሪያም እስራኤል ከግብፅ ሲወጣ በቅዱስ ሥፍራ በእሳት ተጠብሶ የተቀደሰውን ሥጋ በስውር ሲበላው የተረፈውን ደግሞ እሳት ስለበላው ሥርዓቱ ከደሙ ግርዶሽ በውጭ በነበረ ሰው በማንም ሳይታይ፣ ሳይታወቅ ቀረ-ቀረ፡፡ ይህን ስውርና ቅዱስ ነገር ለመድረስ በቅድስና ኃይል በስውር ወደሚያይ አባት መግባትን ይጠይቃል፣ (ማቴ.6፡6)፡፡ ወደዚህ በስውር ወደሚያይ አባት ማዕድ ወደ ሆነው ቅድስና ሥፍራ መግባት የሚቻለው እንዴት ነው? (ዮሐ.14፡6)

የአፈፃፀሙ ሥርዓትም ቢሆን ከሥጋው አንዳች ወደ ውጭ አታውጡ ተብሎ በሕግ የታዘዘና የተበላውም በግልጽ በሰው ፊት በውጭ ሳይሆን፣ በበጉ ደም በተጋረደ ቤት፣ ወደ ውስጥ መጋረጃውን ዘልቀው መግባት በቻሉት እስራኤል ብቻ፣ በሕጉ መሠረት (ዘዳ.14፡22-26፤ 12፡5-8) በስውር በሚያይ አባት (እግዚአብሔር) ፊት (ማቴ.6፡6) በቅዱስ ሥፍራ ስለሆነ፣ የአዳሞችን ወደ ውጭ ወጥቶ የቀረውን ያልተገረዘ ዓይን ከወረሰ አዳማዊ ሰው ልጅ ማንም ሥጋው የደረሰበትን ሳያይ፣ ሳያውቀው በስውር ተደመደመ፡፡

ፋሲካ በታሪካዊነቱ፤

ፋሲካ በመሠረቱ፣ የታላቅ ከታናሽ መተላለፊያ የማህፀን በር የአልወገድም ባይነት ትግል የምጥ ጣረ-ሞት ውውታና፤ የታናሽ ልደት እልልታ የመንትያዎች ፍልሚያ ድብልቅ ታሪክ ሆኖ ይነበባል፡፡ ታላቅ፣ ትልቅ ግብፃዊ ሲሆን ታናሽ፣ ትንሹ እሥራኤላዊ ነበረ፡፡ በጌታ ፊት እስራኤላዊው ምርት ሲሆን ግብፃዊው ገለባ ሆኖአል፡፡ ይህ ሁኔታ በግብፅ እስራኤል መውጣት ላይ በግልፅ ተፈጽሟል፡፡ ክርስቶስ ቤተ-ክርስቲያንን (አዲሱን እስራኤል) ለመውለድ ይህን ምጥ ጣረ-ሞት በጌቴሴማኒ ላይ

በመቀበሉ ታሪኩ ከፍጻሜው መድረሱ ነው (ማቴ.26፥36-50)፡፡ ጌታ ኢየሱስ ይህን ትንሣኤውና መለቀቂያው ወደ ክብር ዙፋኑ መወጣጫ፣ የሰው ልጅ ዳግመኛ ልደት ብሎታልና፡፡ ግብፅም በምሳሌው በምጥ ጣረ-ሞት ተጐዳ የእግዚአብሔርን በኩር ልጅ ወለደች (ተፋች) (ዘፍ.3፡16፣ ዘፀ.4፥22)፡፡ እስራኤልን የበላ እንደ በደለኛ ይቆጠራል፣ ክፉ ነገርም ያገኘዋል፣ (ኤር.2፥3) እስራኤልን ከበላና ክርስቶስን ከበላ የባሰ ክፉ የሚያገኘው የትኛው ነው?

ፋሲካ ዛሬ፣ ሁልጊዜም የእስራኤል መለቀቅ/ልደት በተመሳሳይ ሁኔታ በፋሲካ፣ የታናሽ ልደት በታላቅ ሞት ነው፡፡ ታላቅና ታናሽ ዛሬ ማን ማናቸው? ታላቅ ሥጋ አሮጌው ማንነት ያረጀው ሲሆን ታናሽ ከእርሱ ውስጥ በነፃነት የሚያፈተልከው መንፈስ/ነፍስ ይሆናል፡፡ በጉ ለታላቅ ሞት፣ ለታናሽ ልደት ነው፡፡ ይህ አሠራር ከሞት በበጉ ሞት ተሸፍነን ከሞት ውስጥ ሾልከን በመውጣት አዲሱን ልደት የምናገኝበት ሥነ-ሥርዓት መሆኑ ነው፡፡ በጉ ለታላቅ ሞት፣ ለታናሽ ልደት የሚሆንበት ምክንያት እንዴት ነው? ታላቅ፣ ትልቅ፣ ግዙፍ የኃይልና የክብር አለቃ ክቡር ሰው በመሆኑ በቀጭኑ መንገድ ተጉዞ፣ ጠባቡ በር በሆነው ክርስቶስ በበጉ ደም ወደ ታጠረው የበጉ ሠርግ ወደ ሆነው ፋሲካ አዳራሽ ሊገባና በበጉ ሞት እንጀራና ሥጋ፣ ወይን ጠጅ ሆኖ ከተዘጋጀው መብል ሞቱን ለመካፈል መፀየፉ ስላላስቻለው የሞት ጥላ በሆነው ውጪ ጨለማ ላይ ደፍሮ፣ ደረቱን ነፍቶ ቆሟልና ግብፅን ሊመታ የተላከው መላክ-ሞት ያገኘዋል፡፡ ኃጢአቱ/በደሉ የማነው? ታናሹ ግን ትንሽ ስለሆነ በበጉ ደም ወደ ታጠረው አዳራሽ በበጉ ሽፋን ሰተት ብሎ ይገባል፡፡

ግብፅን/ዓለምን ለቀን እሥራኤላዊነትን የምናገኘው ሁልጊዜም በምጥ ጣረ-ሞት ነው፡፡ ይህ ማለት ጭማቂው፣ ጥላ የሆነውን የመካከለኛውን ምሥራቅ ቁስ አካላዊውን እስራኤል ብቻ ገለባውን የሚያመለክት ሳይሆን፣ የእውነት እውነተኛውን እስራኤል ክርስቶስንና በክርስቶስ ተሸፍነው ምርት ሆነው



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፉ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16



የሚወጡትን ሁሉ አመልካች መልእክት ነው፡፡ ክርስቶስ ታላቁን ደካማ የተባለውን ሥጋ ተሸልቅቆ ለመውጣት በጌቴሴማኒ ጭንቀት በምጥ-ጣረሞት አልፎ የተለቀቀበት የእውነት እውነቱ (ፍሬው) ጭማቂ ነው፤ (ማቴ. 2፥14-15) እስራኤልን የበላ (የዋጠ) ማለት ክርስቶስን ማለት የሕይወትን ቃል (አንዷን መክሊት) የቀበረ (የበላ) (የዋጠ) ዘንዶ ማነው? ራሳችንን በብርቱ እንፈትሽ፡፡ ዘንዶው ሁሉጊዜም ከአገልጋዩ ባሪያ ጋር እንጂ ብቻውን አይውጥም፡፡ እንደ ግብፅ ሁሉ የእግዚአብሔርን ገንዘብ በፈቃድ ሳይሆን፣ በግድ ከሆነ ከቀበርንበት ማሕፀን ተፍተን የዓይን እንባ፣ የጥርስ ማፋጨት ወደ ሆነው በውጭ ወዳለው ጨለማ እንጣላለን፤ (ማቴ.25፥30) ፍርዱ አሁን አልተፈፀመምይ?

«ፋሲካ» በትምህርታዊነቱ፤

ፋሲካ፣ ግብፃዊውን አንገዋሎ እስራኤልን ወደ ጎተራ ማስገቢያ የመከተቻ በዓል ሥነ-ሥርዓት ነው፡፡ እስራኤልን ከግብፅ ማለት፣ ፍሬን ከገለባ፣ መንፈስን ከሥጋ የመለያ የመውቂያ አውድማ ሆኖ፣ ሥራው ሁሉ መጪውን አመልካች ትንቢታዊ ነበር ደረሰን፡፡ እንዲሁም ፋሲካ በእስራኤል አንፃር የተጫነባቸው የመቃብር ድንጋይ የተፈናቀለበት ሥነ-ሥርዓት በዓል ሆኖ በእድገት ከፍ እያለ መጣና በክርስቶስ ትንሣዔ የታሪኩ እውነታው ወደ ብርሃን ወጥቷል (ተደምድሟል)፡፡

ፋሲካ (ትርጓሜው)

{Passover} የሞት መልአክ በደጅ አለፈ፣ ተብሎ ይነገራል፤ እግዚአብሔር ለእስራኤል ዘብ የቆመበት መሆኑንም የጥናቱ ታሪክ፣ ያመለክታል፡፡ ቀኑም፣ እግዚአብሔር ግልፃ ስለገባበት ቀንና ሌሊት፣ ውስጥና ውጭ፣ ብርሃንና ጨለማ ሞትና ሕይወት ግራና ቀኝ የተከፈሉበት (ሞት ወደ ውጭ፣ ሕይወት ወደ ቤት) የሆነበት ሥነ-ሥርዓት ሆኖአል፡፡



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፉ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

ሞት ወደ ቤት ሳይገባ ከደጅ የተገኘ ነገር ይዞ ሄዷል ማለት ክርስቶስ ሞትን ውስጡን ሳይነካው ከበር ውጭ፣ በመንፈስ ሳይነካ በሥጋ መቀበሉን ተንብዮአል፡፡ ፋሲካ፡- በጅምሩ ግብፅ ለእስራኤል ቤዛ (ወጀ) የሆነበት፣ እስራኤል፣ እስራኤል ሆና ነጥራ የወጣችበት፤ ዘመኗን የቆጠረችበት አዲስ የልደቷ በዓል ሥነ-ሥርዓት ጅምርም ሆኖ ሊመጣ ላለው አካል ጥላው ሆነ፡፡ ሞት ወደ ቤት እንዳይገባም በእስራኤል በሮች መቃንና ጉበኖቹ ላይ የተቀባው ደም ዘብ (መጋረጃ) ከእግዘአብሔር የተሰጠ የጽድቅ ልብስ ሆኖ የሚቆጠር ነው፡፡ ይህ የሰው ልጅ የተባለው የእግዚአብሔር በግ በሆነው ክርስቶስ እንዲጋረድ አለዚያ እንደሚጠፋ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ እስራኤልን ያዳነው በእውነት እውነቱ ሲታይ ክርስቶስ ነው እንጂ በጉ አይደለም፡፡ ክርስቶስ ቅዱስ ስለሆነ በነገሮች መጋረጃ ተሰውሮ ሥራውን ያከናውናል፡፡

ሥርዓቱም በውጭ ለእስራኤል፣ በውስጥ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠ ዘላለማዊነት ያለው፣ ያለ የነበረ የሚመጣ ስለሆነ ለልጅ ልጅ ዘለቀ፡ በሌላው አንፃር የፋሲካ ትርጉም ግን የሥጋ በመልአከ-ሞት መወገድ ወይም የመንፈስ ትንሣዔ በነቢዩ ኢሳይያስ አዋጅ መሠረት (ለእግዚአብሔር) ከመምጫው የመንገድ ጥርጊያ ሆኖ የሚታይ ነው ከእግዚአብሔር ፊት ሥጋ (ግብፃዊነት) ጥራጊ ሆኖ መወገድ ነበረበትና፤ ልብ እንበል እንጂ ወደ ውጭ በሌላ አያሳየን፡፡

ይህ አሠራር ሂዶ-ሂዶ በኢየሱስ ሥራ ተፈጽሟል፡፡ ከላይ ጥላ የተባለውም ይህን ቤት፣ የቤት ጥላ፣ በግ፣ የበግ ጥላ፣ ደም፣ የደም ጥላ፣ ሞት፣ የሞት ጥላ ስለሆነ፣ ጥላው በጥላነት እውነትን አመልካች ሆኖ ስለሚቆጠር ነው፡፡ የእውነት እውነቱ የዚህኛው መንፈሱ ነው፡፡ እግዚአብሔር ብቸኛና ብቻውን ሠሪ ነውና በሚመጣበት ፊት ሊቆም የሚችል ማነው? በተገለጠስ ጊዜ የሚቆም ማነው? (ሚል.3፡2) እርሱ በተገለጠ ጊዜ በሥጋ አካል ለመመከት ነው ወይ ደረት ነፍታችሁ ከመግባት በውጭ የቆማችሁት?



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16



የበጉን ደም ሞቱን ለመካፈሉ ያረደው ማነው? ክርስቲያን ነው ወይ? ያስፀይፋል አይደል?

ለግብፅ በኩራት መልአከ-ሞት የሆነው ይህ ፋሲካ ሲያሜ ያገኘው በዚህ፣ በእስራኤል ትንሣኤ ሥነ-ሥርዓት ላይ ነበር፤ በሌላ በኩል፣ መላከ-ሞት እስራኤልን፣ ከግብፅ ለመለየት/ለመቀደስ፣ ለማበጠር፣ በግብፃዊ እና በእሥራኤላዊ መካከል ጣልቃ የገባ ስለታም ሰይፍ ሆኖ ሊታይ ይችላል፡፡ እሥራኤላዊንና ግብፃዊውን፣ ገለባና ምርቱን ለየ፣ እንደ ተጻፈ፣ «በዚያም ቀን በምድር መካከል እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቅ ዘንድ በዚያ የዝንብ መንጋ እንዳይሆን ሕዝቤ የሚቀመጥባትን የጌሤምን ምድር እለያለሁ፡፡ በሕዝቤና በሕዝብህ መካከል እለያለሁ፤ ...» (ዘፀ.8፡22-23፤) መልአከ-ሞቱ በ እስራኤል መቃብር ላይ የተጫነውን ታላላቅ ድንጋዮችን አንከባልሏል ሰንል፣ በውጫዊ ዓይን የሚታየውን ሜዳዊ፣ ቁሳዊ የሐሰት እውነተኛውን ድንጋይ አንከባልሏል ወይስ በዓይን የማይታየውን በውስጣዊ መንፈሳዊ ጫንቃ ላይ የተጫነውን የእውነት እውነተኛውን ድንጋይ አንከባልሏል? እስራኤሎች፣ የትኛውን ድንጋይ አንከባልለው፣ የትኛውን ተሸክመው ወጡ? በመንገድ ጉዞ ላይ ወድቀው ያለቁት የትኛው ድንጋይ ከብዶአቸው ነበር? ያኔ፣ ወደ በጉ ደም አጥር ውስጥ ጎንበስ ብሎ ሾልኮ መግባት ያልቻለው ትልቁ፣ ግብፃዊ፣ ሸለፈታም ነው ተብሎ ተፈርጆ በውጪ ጨለማ ለሚያልፈው ሞት ተሰጥቷል፡፡

ዛሬ፣ ወደ በጉ ደም አጥር ውስጥ ጎንበስ ብሎ ተዋርዶ ሾልኮ ወደ እግዚአብሔር ፊት ብርሃን ቅድስና ክብር ሠርግ ፋሲካ ራት መግባትን ተፀይፎ በውጭ፣ ማለት መሬት ገዝቻለሁ፣ አምስት ጥማድ በሬዎችን እፈትናለሁ፣ ሚስት አግብቻለሁና የመሳሰለውን ውጫዊ ጥቅምንና የመሳሰለውውን አስበልጠው፣ ትዕቢትን ተሞልተው በውጪ ጨለማ የተገተሩት እውነት እውነተኛ ግብፃውያን ናቸው ወይስ የያኔው ግብፃዊ፣ ግብፃዊ ነው? በውጪ ጨለማ ዓይኑን ተጋርዶ (ታውሮ) የሚመጣውን



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

መልእክ-ሞት ባለማየት ወጭ አካሉን የተደመሰሰው በእውነት ዕውር ነው ወይስ ዛሬ መጋረጃ በተገፈፈበት ዘመን እግዚአብሔርን ባለማየት የጨለመው ዕውር ነው?

የታረደው፣ የያኔው በግ (እንስሳ) እንዴት አድኖአቸው እንዴት አወጣቸው? እንስሳው፣ ከሞት ሊከላከል በውጭ ዘብና አጥር እንደሆነ ቆሞ፤ ደግሞ ግብዣ ሊሆን ወደ ቤት ገባ፤ ተበላ፡፡ በውስጥ እልልታ፣ ደስታ፣ በውጭ ዑዑታ፣ ዋይታ ሆነ፡፡ የዛሬው እንስሳ በጉ ክርስቶስ እንዴት ያድናል? እንዴት ያወጣል? የዛሬው እንስሳ በጉ ክርስቶስ፣ የእውነት፣ እውነት ስለሆነ በውጭ ...እውነት እንደ ጋሻ ይከብሃል፤ (መዝ.91፥4) እውነት ይከበብሀ ወይስ ደሙ ይከበብሀ? በእውነትና በደሙ መካከል ልዩነት አለ ወይ? የእውነት እውነተኛው አጥር፣ «እውነት» ነው ወይስ ደም ነው? በውስጥህ ሆኖ እንጀራ፣ ወይን ጠጅ፣ ወተት፣ ፅጮማ፣ በረከት ይሆንልሃል፤ ወደ ሥርጉ ቅዱስ ብርሃን በእርሱ ቅድስና ትገባለህ፡፡ ያ የያኔው፣ የሚታየው የተፈራ፣ የተከበረ፤ ሲሆን የዛሬው የማይታየው የተናቀ፣ የተዋረደ ነው አይደል? ነቢዩ በተናገረው መሠረት የማይታየው የተናቀ፣ ያልተከበረ ነው አይደል? (ኢሳ.53፥1-3፣ ዕብ. 12፥18-21፥ ቁ. 21) እንጠንቀቅ፡፡

ዱሮ ዱሮ በሩቅ ዘመን በሩቅ አገር በውጭ፣ ውጭ ሜዳ የቀረው ግብፃዊው፣ ግብፃዊ ነው ወይስ ዛሬ ወደ እግዚአብሔር ቅድስና ብርሃን እንዳይገባ አሮጌ ሰው የሆነውን እርኩሱን ሸለፈት ተከናንቦ በውጭ የሚኳደደው ግብፃዊ ነው? ፊቱን ማየት ወደ ሚቻልበት እግዚአብሔር ብርሃን መግባት ያልቻለ እንዴት ክርስቲያን ይባላል?

ዘመን አልፎበት ለውሻ ወደ ውጭ የተጣለውን ውጫዊውን የቤትህ እንጀራ ጓደኛ የሆነውን ምግብ ወደ ቤተ-ክርስቲያን ወስደህ በማስመሰል የገዛ-ራስህን እንጀራ ትበላለህ እንጂ፣ ወደ ቤት ገብቶ በፊቱ ብርሃን







የሚበላውን ቅዱስ ፋሲካ ለመካፈል አትችልማ!! ወደ ውጭ ለውሻ የተጣለው ፋሲካ ምግብ የትኛው ነው? ውሻውስ ማነው? በግልፅ በሰው ፊት ውሻ ወይስ ከሰው በስውር በመጋረጃ ተሸፍኖ ውሻ? በውስጥ የዘላለም ውሻ መሆን ይበልጥ ርኩሰት ነው ወይስ? በውጭ በሰው ፊት ለሁለት ቀን ብቻ ውሻ መሆን ይበልጥ ርኩሰት ነው? ውሻዎች ተብሎ የተጻፈውን ታስታውሳለህ? (ራዕይ 22፥15) አስመስክር፡፡ ወደ ውጭ ለውሻ የተጣለው ፋሲካ ምግብ እዳሪ የሚሆን በታወቀው በር ወደ ውጪ ሆድ እንጂ በጠባቡ በር ወደ ውስጡ ሆድ ወደ ልብ ሊገባ የማይችለው አስመሳዩ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ እየተመለከ ያለው ሰው ሠራሹ እራት ነዋ!

የጨለማው መልእክ-ሞት ማነው? የጨለማው መልእክ-ሞት ሰይጣን ነው፤ (ራዕይ 6፥8 ፤ ም. 16፥10) ያኔ ግብፅን የመታው መልእክ-ሞት የፊደል (ፍጥረታዊ) አካል የነበረና ጎንበስ ብሎ ተዋርዶ ወደ ቤት ለመግባት፣ ጎንበስን የተፀየፈ በውጪ ጨለማ የተገተረውን የመታው መልአክ እጅግ አስፈሪ እንደ ነበረ ከመጽሐፉ ይነበባል፡፡ ለግብፅ የጨለመው ጨለማ ነበር ወይስ እግዚአብሔር ፊቱን መመለሱ ጨለማ ነበር? ብርሃን ብርሃን ነው ወይስ እግዚአብሔር ብርሃን ነው?

የዛሬው ውጭ፣ የዛሬው ቤት፣ የዛሬው መልእክ-ሞት እንዴት ይታያል? የዛሬው ውጭ፣ ክርስቲያኖችን ሁሉ በውጭ ያስቀረው፣ የሰው ፊት የሆነው ውጫዊ ስግደት፣ በድምፅ ማጉያ ገደል ማሚቶ የሆነው ውጫዊ ፀሎት፣ ውጫዊው የሰው ፊት ፆም፣ ውጫዊ አገልግሎት ሁሉ...ወዘተ ሲሆን፣ የዛሬው ቤት የዳኑ፣ ዳግም የተወለዱ፣ ከሸለፈቱ ቁርበት የወጡ፣ በዚህ ድል አድራጊነት ወደ ውስጥ የገቡ፣ የአባቱ መቅደስ አምድ (ራዕይ 3፥12) የሆኑ፣ በአሮጌው በውጫዊው ፊደል (ፍጥረታዊ) ኑሮ ሳይሆን፣ በአዲሱና በውስጣዊው መንፈስ ኑሮ የሚገዙ፣ በእውነትና በመንፈስ ለእግዚአብሔር አብ የሚሰግዱ፣ ክርስቶስ ባለበት በላይ ያለውን እንጂ በታች ያለውን የማይሹ፣ ከሙታን የተነሡ አገልጋዮች የሆኑ ክርስቲያኖች ሲሆኑ፤

የዛሬው መልአከ-ሞት ደግሞ፣ ዕለታዊና ገለባ የሆነ ውጫዊ ቁሳዊ አካል ለውነትን የሚያጠፋ ሳይሆን የጨለማ ሥራ በሆነው ውጫዊ ፊደላዊ (ፍጥረታዊ) ሥርዓቶች ለታይታ በሰው ፊት ጨለማ አገልግሎት ዙሪያ ሽርጉድ እያሉ የሰውን ኪስ ለመበዝበዝ ሲሉ በውጫዊ ጥቅሞች የተገተሩትን፣ በቀጭኑ በር ጎንበስ ብለውና ወደ ብርሃን ገብተው እግዚአብሔርን በብርሃን ያላዩ ዕውሮችን፣ በውጫዊ ሥርዓት የተጣበቁን መንፈሳዊ፣ ዘላለማዊ ሕይወትን ሳይታይ የሚያጠፋ የተናቀ መልአከ-ሞት ነው፡፡ እነዚህ ሞት ከሆነው ሥጋ ሐሳብ የተነሣ እንዳለ የሞቱ በድኖች ስለሆኑ የውጭን፣ በሰው ፊት የሚታየውን እርኩሱን ሥጋ አካልን አይንካባቸው እንጂ ለውስጣዊ መንፈሳዊ ሞት ደንታ የሌላቸው በድኖች ስለሆኑ ሞቱንም ሆነ፣ መልአከ-ሞቱን ስለሚንቁ በሞት ሆነው ያሸበሽባሉ፣ ያጨበጭባሉ፣ መድረክ ላይ እየደነሡ ይወዛወዛሉ፤ በእልል፣ እልል፣ በሃሌ ሉያ!! አሜን፣ አሜን ምድርን ያናውጣሉ፡፡

ውጫዊው እስራኤል ከግብፅ በበኩር ሞት የመውጣቱ ታሪክ ወደ ብርሃን ሲወጣ እንዴት ነው? በሜዳዊ ውኃ ውስጥ ገብቶ በመውጣት በማስመሰል ካላጭበረበሩት በስተቀር፤ የዚህ መደምደሚያውና የእውነት እውነቱ ክርስቲያን ከተጫነበት አዳማዊ ሥጋ በትክክለኛ ፊርያንን ቀብረው እንደ ወጡት እስራኤሎች ጥምቀት ዓይነት በወንዙ በሞት ተቀብረው የቀደመውን ማንነት ቀብረው መውጣትን የተረጉማል፡፡ ሞት፣ ወደ ቤት እንዳይገባም እስራኤል ከሞት ጋር የሚመጣጠን (አቻ) ሞት በበር ላይ በመለጠፍ የሞትን ፍርድ በሞት ያጣፋበትን ሥርዓት ፈጽሟል፡፡

ሞት የማያመልጡት ዕዳ የበደል ዋጋ ነው፤ (ዘፍ.2፡17፣ ሮሜ 6፡23) እንዲህ ሲባል በገሃዱ ዓለም በሚታወቀው ግልፁ ሞት የኃጢአት ዋጋ ይከፈላል ማለት ነው ወይ? ሰው የኃጢአቱ ምንጭ እውስጥ ባይሆንና በውጫዊ አካል ብቻ ላይ ቢሆን ኖሮ በውጫዊው አካል ሞት የኃጢአቱ ዋጋ ተከፈለ ማለት ይቻል ነበር፡፡ ነገር ግን እንዲህ እንዳይባል፣ ሰው





እንደ እንስሳ ቁስ አካል ብቻ ሳይሆን የውጭና የውስጥ፣ የግልፅና የስውር አካል ጥምር ፍጥረት በመሆኑ (ሮሜ 7፡22፣ 2ቆሮ.4፡16፣ መክ.3፡11) በውጭም በውስጥም ኃጢአተኛ ስለሆነ ከውጫዊው ቅፅበታዊ አካል ሞት የማያመልጥ ቢሆንም ከውስጣዊው ዘላለማዊው ሞት ሰው ማምለጥ የሚችልበትን መንገድ እግዚአብሔር በራሱ ጸጋ ቀይሷል፤ ይህም እግዚብሔር ያዘጋጀው የማምለጫ መንገድ ሰው አምኖ እንዲቀበለው በዓለም ሁሉ ታውጇል፡፡ ይህ የማምለጫ መንገድም እስራኤል በውጭ መጥቶ ግብፅን ከመታው ውጫዊ (ፊደላዊ (ፍጥረታዊ)) ጥላዊ ሞት በፍጥረታዊ ጥላዊ እንስሳ ደም ተጋርዶ በጥላ ያመለጠበትን የውጫዊን ሥነ-ሥርዓት እውነታ (አካሉን) ለውስጡም አምኖ በውስጡም እንደዚያው እንዲፈፅም ነው፡፡ የውጫዊው መቅሠፍቱም፣ ሞቱም ለውስጣዊው ጥላ ነው፡፡ የውጫዊው ሕይወትም ለውስጠዊው ሕይወት ጥላ ነው፡፡ ውጫዊው በግም (እንስሳው) ለውስጣዊው በግ ጥላ ነው፤ ውጫዊው ቤትም ለውስጣዊው ቤት ምስያ ነው፡፡ የሚታየው ነገር ሁሉ ለማይታየው ነገር ጥላ ምስያ ነው፡፡ ሰው ለማምለጥ (ለመዳን) የሚችለውም በሚታየው ነገር፣ (በጥላው) ላይ ዓይኑን በማድረግ ተጋርዶ ሳይታወር፣ በጥላው ማለት በቁሱ በኩል ጥላውን ሰንጥቆ አልፎ አሻግሮ ማየት ሲችል ነው፡፡ በፊታችን ሆኖ ዓይናችንን ጋርዶ የሚታየው ነገር ጊዜያዊ ከመሆኑም (2ቆሮ.4፡18) ብርሃን ስለማያስተላልፍ የዕውርነታችን መንስዔ ነው፡፡ ብርሃንን የማያስተላልፍ ማለትም እግዚአብሔርን የሚጋርድ ማለት ነው፡፡

የእግዚአብሔር ዓላማ እስራኤል ለእውነት እውነተኛ ደህንነቷ በዚህ በምታቀርበው በፍጥረታዊ በግ ዓይኗን ሳትጋረድ (ሳትታወር) በእርሱ (በእንስሳው) አመልካችነት ዓለማትን አሻግራ ሰንጥቃ አልፋ በማየት ዓይኗን ከውስጣዊው ሞት ሊጋርድ በሚችለው የፈጣሪ በግ በሆነው ክርስቶስ ላይ እንድታሳርፍ ነበር፡፡ ዓይን እንደ እግዚአብሔር ከውጭ ነገር አልፎ ወደ ውስጥ የሚያይ ካልሆነ ዕውር ነውና፡፡ ለመፈወስ

በእምነት ካልሆነ በስተቀር ሕጉ ዕውሩን ወደ እግዚአብሔር አያቀርብም፤ (ዘሌ.21፡16-18) የእግዚአብሔር እንስሳ፣ በግ፣ እግዚአብሔር ራሱ ነው፡፡ እግዚአብሔር፣ እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ ብቻውን ይሠራል፤ ራሱን ችሎ ይኖራል፣ ብቻውን ያድናል፣ (ኢሳ.43፡11፣ ም.45፡5-6፣ ም.59፡16፡ም.63፡3፣ 5) ከእግዚአብሔር በስተቀር የሚያድን ሌላ ምንም ተጨማሪ ነገር የለም፤ ለዘላለሙ አሜን፡፡ ከውስጡ፣ ከዘላለማዊ መቅሠፍት ሰው ተጋርዶ እንዲያመልጥ እግዚአብሔር ለሰው ያዘጋጀው የእንስሳን ደም ሳይሆን የራሱን ደም ነው፡፡ ራሱ ግን ለዘላለም ምንጭ ሆኖ ይፈልቃል፣ ጅረት ሆኖ ይፈስሳል እንጂ እንደ ግንዛቤአችን አይደማም፡፡ እግዚአብሔር በራሱ ደም ካልሆነም አይታረቅም (ወደ ማንነቱ አያቀላቅልም፡፡) የእርሱን ደም ሆነን ነው እርሱን የምንቀላቀለው፡፡ የእርሱን ሥጋ ስንበላ፣ ደሙን ስንጠጣ፣ እርሱ በእኛ፣ እኛ በእርሱ እንኖራለን፤ መጽሐፍ እንደሚል፡፡ አሁን ግን አንዱ ነገር ሁሉ፣ ሁሉ ነገር አንዱ ስለሆነ ክርስቶስን መቀበል እውነት ይሁን ብቻ ነው፡፡

የአዳም ልጅ፣ በውጭ የደቂቃዎችን ማለትም ያኛውን የእውነት እውነተኛውን የጋረደበትን ቅፅበታዊ ሞት ስለሚያይና ስለሚያውቅ እርሱን ይፈራል ዋናው ምን እደሆነም አያውቅምና አይፈራም፤ ለእርሱ ይደነግጣል፤ ይርዳል፣ ነገር ግን የውስጥ የዘላለምን ሞት እንዲያይ ከእናቱ ማህፀን ጀምሮም ዕውር በመሆኑ ከምናምን አልቆጠረም (2ጴጥ.1፡9፣ ማቴ.13፡13)፡፡ ከእናቱ ማህፀን ጀምሮም ዕውር መባሉ በቅርብ ነገሮች የተጋረደ ሰው ሁሉ ለማለት ነው።

እሥራኤል የተጋረደበት የእንስሳ ሞት፣ እሥራኤልን ከእንስሳነቱ ማለት ከውጫዊ አካል ሞት አስመልጦታል እንጂ ከውስጣዊው መንፈሳዊ ሞቱ አላስመለጠውም። ከውጫዊ ኃጢአት ባመለጡበት ደስታን ተሞልተው ውስጣዊ ኃጢአታቸውን ግን በልባቸው እንደ ያዙ ከግብፅ ወጥተዋል። ስለሆነ የውስጣዊ ኃጢአት ዋጋ ሞት ገና ስላልተከፈለ ወይም ኃጢአቱ







ከእግዚአብሔር ፊት ስላልተሸፈነ እኛም ዛሬ እንደምናደርገው ሁሉ ከውስጥ ኃጢአታቸው ጋር እያሉ አመለጥን በሚል ከንቱ ደስታ ከባሕር ማዶ እየጨፈሩ የምስጋና መዝሙር ያቀረቡ ቢሆንም ሁሉም በጉዞ ላይ በምድረ-በዳ እንደ ወደቁ ታሪክ ይመሰክራል። ምድረ-በዳ ማለት ደረቅ ምድር ነው፤ በውጩ ሜዳ በርቀት ያለ ምድረ-በዳ፣ ምድረ-በዳ ነው ወይስ ደረቁ ምድር ምድረ-በዳ ነው ወይስ ደረቁ ልብ ምድረ-በዳ ነው? ያኔ፣ በምድረ-በዳ የወደቁት በምድረ-በዳ ወድቀዋል ወይስ አሁን በደረቁ ልብ የወደቁት በምድረ-በዳ ወድቀዋል?

መለስ ስንል፣ እስራኤል በምሳሌ ያቀረቡት የኃጢአት ዋጋ ሞት፣ ከምሳሌያዊ ማለት ከቁስ አካላዊው፣ ከዚህኛው ሞት ጋርዷቸዋል። እስራኤል፣ ከውስጣዊ እውነት እውነተኛው ስውር ሞት ደግሞ ለማምለጥ የእውነት እውነተኛ እንስሳ ሞት እውነተኛ ደም ማስፈለጉን በማየቱ በግ በኩል መጪውን የእምነቱን በግ አሻግረው ለማየት እምነቱ አልነበራቸውምና በማየቱ ሳይሆን በእምነቱ የወጡ ጥቂቶች ሲያመልጡ በማየቱ በግ በኩል የወጡ ሁሉ በጉዞ ላይ እንደ ወደቁ እናነባለን፡፡ አሁን ከማየቱ ልቀን፣ እያየን ያለነው፣ በሊቀ-ካህናት ሥልጣን መጋረጃውን እየገፋፍን እስከ ጌታ ኢየሱስ ሞት፣ ደም፣ ሥጋ መድረሻና ትንሣኤ ድረስ የማይታየውን ለማየት ነው፡፡ ሞት፣ ሞትን፣ ደም፣ ደምን፣ ሥጋ ሥጋን በማመልከቱ እንጂ አለዚያ በራሱ ከንቱ ነው፡፡

እግዚአብሔር (ክርስቶስ) የማይሞት ነው፤ (1ጢሞ.6፡16) እግዚአብሔር የማይሞት ከሆነ ለአዳም ልጅ የኃጢአትን ዋጋ (ሞትን) ከቶ ማን ይከፈል? ማንም አልተገኘም፡፡ ስለዚህ የማይሞተው እግዚአብሔር፣ ቃል፣ ክርስቶስ ይሠቃይ ዘንድና ሊደማ፣ ሊሞት፣ ይችል ዘንድ ሥጋ ሆነ፤ (ዮሐ.1፡14)፡፡ ቅዱስ ታሪክ እንደሚገልፀው ያለ ሞት ሕይወት የለምና፣ ክርስቶስ በመንፈስ ሕያው ይሆን ዘንድ ሥጋ ማለት ሞትን ሆኖ በሥጋ ሞተ፤ (1ጴጥ.3፡18)፡፡ ሞትን፣ ትሞታለህ የተባለውን በመፈፀም ሞተ

ብለን እንመሰክራለን። ክርስቶስ ራሱ ሥጋን መሆኑ ወርደቱ ሞቱ ነው እንጂ ሞቱ፣ ሞቱ አይደለም፡፡ እርሱ የማይሞት ነውና፤ «...ቃሌን የሚሰማ፣ ...የሚያምን፣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ...» በሞት ከነበረበት ወደ ሕይወት ተሻገረ፤ በሥጋ ከነበረበት ወደ መንፈስ ተሻገረ፤ ሕያው የሆነ፣ የሚያምንበትም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፤ (ዮሐ.11፡25)፡፡

አንዱ እግዚአብሔር (ክርስቶስ) ብቻውን ሁሉ በእርሱ የሆነ ሁሉ ነው፡፡ ደም፣ ሥጋ፣ እንጀራ፣ ውኃ፣ ወይን ጠጅ፣ ወተት፣ ፌማ (ኢሳ.55፡1-2) ሁሉ አንድ ነገር፣ አንዱም ሁሉ ነገር ነው፡፡ በፊደል (ፍጥረታዊ) ደም የምንለው በውስጡ ያለውን ውኃ ጋርዶ የሚፈስ ቀይ ቀለም ስለመሆኑ በዚህ መጽሐፍ ተገልጧል፡፡ (በዮሐ.7፡37-39) ቃል የሚጠጣ ውኃ፣ ደግሞ መንፈስ መባሉን ስንመለከት፣ (ሕዝ.36፡25-27፤ ዕብ.10፡19-20)፣ ልብን ከእርኩሰትና ከጣዖታትም ሁሉ ረጭቶ በማንፃት አዲስ ልብ፣ አዲስ መንፈስ አድርጎ የሚለውጥ ሆኖ ሲታይ፣ በዕብ.12፡24/ የኢየሱስ ደም የመርጨት ደም መባሉ፣ በራዕ.7፡9-14/ የሚታዩ ሰዎች የለበሱት ነጭ ልብስ በበጉ (ክርስቶስ) ደም የታጠበ መሆኑን እንመለከታለን፡፡ እንዲሁም ደግሞ (በዘፍ.1፡2) የእግዚአብሔር መንፈስና ውኃ በጣምራነት ሲታዩ፣ የሕይወት ውኃ ደግሞ እግዚአብሔር ስለመሆኑ ነቢዩ ኤርምያስ በም.2፡13 እና በም.17፡13 ላይ አመልክቷል፡፡ ኢሳ.4፡3-4፤ እና ማቴ.3፡11-12) የሚያጥብና እድፍን የሚያነፃ እሳት ሆኖ ተነግሯል፡፡ እግዚአብሔር ራሱም፣ ቃሉም አንድ እየሆኑ እሳት ተብለው ቢነገሩም፤ (ዘዳ.4፡24፤ ዕብ.12፡29) በእግዚአብሔር ዘንድ ከእግዚአብሔር በስተቀር ሌላ የሚዘረዘርና የሚቆጠር ነገር ከቶ የለም፡፡ እግዚአብሔር በራሱ የሚኖር፣ ከራሱ ውጪ በሆነ ነገር በምንም ሊገለገል የማይችል ምንም የማይጎድለው ነው የሚለው ጥናት ትክክል ነው፡፡ (በዚህ አመለካከት ሁሉ ላይ በተቻለ መጠን የሚቀርበውን ጥያቄ ለመመለስ እንሞክር)፡፡ እግዚአብሔር







መንፈስም ውኃም እንደ ፈቃዱ ይፈስሳል እንጂ እንደ ገሃዱ ቋንቋ አይደማም፡፡

አሁን የኃጢአትን ዋጋ ስንጠቀልል፣ ለሞት፣ ማጣፊያ ሞትን በማቅረብና ሞትን በሞት አጣፍቶና ደምስሶ እንጂ የማይቀረውን ዕዳ ሳይከፍሉ አምልጦ ወደ ሕይወት መሻገር ከቶ አለመቻሉን አትኩረን ማየት ግዴታ ነው፡፡ ቁስ አካለዊውን ሞት እንኳ ሞቶ እንጂ ሸሽቶ ማምለጥ ከቶ የማይቻል እንደሆነ፣ ከውስጣዊ ሞትም ያለ ሞት የማናመልጥ ለመሆኑ ውጬ ለውስጥ ምስክር ነው፡፡ ከዘላለም ሞት ሕይወትን ማትረፍ የሚቻለው ሞቶ ነው ወይስ በሞት ተሸፍኖ ነው? እስራኤል በምሳሌ እያስተማረን ነው፡፡ በሞት የተጋረዱት ሁሉ ከሞት አመለጡ፤ በሞት ለመጋረድ የተፀየፉት ሁሉ ተደመሰሱ፡፡ ራሳችን ከምንሞት በክርስቶስ ሞት እንሸፈን፡፡ ከእውነት እውነተኛ ሞት መሸፈን በእንስሳ ሞት ሳይሆን በክርስቶስ ሞት ነው፡፡ ከሞት በሞት ውስጥ ተሸፍኖ መቆየት እስከ መቼ ነው? ተሸፍኜ፣ በሕይወት ተቀብሬ እስከ መቼ ልኑር? ብትል መልሱ እስራኤል ተሸፍኖ እስከ መቼ ቆየ? ነው፡፡ የመልስ መልሱ ደግሞ (ዘፀ.12፡22) እንደሚታየው «ከእናንተ አንድ ሰው እስኪነጋ ከቤት ደጅ አይውጣ» የሚል ስለሆነ፣ ለዘላለም ከምትሞት እስኪነጋ ድረስ በክርስቶስ ሞት ተሸፍነህ ብትቆይ አይሻልም ወይ? በክርስቶስ መሸፈንን ተጸይፎ ሕይወትን ወዶ የለም፡፡

እስራኤል በሕይወት ይኖር ዘንድ በብሉይ ኪዳን ሕግ መሠረት በምሳሌም ቢሆን በኖረበት ዘመን ሁሉ ከሞት በሞት (በመሥዋዕት) በመጋረድ ኖረ (ዘሌ.24፡5-9)፡፡ የአዲስ ኪዳኑ የእግዚአብሔር እስራኤል ከሚመጣው እግዚአብሔር ፍርድ የሚጋረደው ግን እጅግ በተሻለው በክርስቶስ ሞት ነው፡፡ የክርስቶስ ሞት መጋረጃው ደም ቅዱስና የእውነት እውነተኛው የዘላለም ደም ስለሆነ በእምነት እንጂ ካልተቀደሰው ቁስ ዓይን የተሠወረ ነው፡፡ ቅዱስ ነገር የዓለምን ርኩስ ነገር ሁሉ እያየ

በረከሠው ውጫዊ ዓይን አይታይም፡፡ ለእስራኤል እንስሳው ምትክ ወይም ወኪል ሆኖ ሲሞትለት፣ ወካዩ በሞተለት ወኪሉ ሞት መጋረዱ፣ (በሞት መሰወሩ) ወካዩን ከወኪሉ ጋር አብሮ እንደ ሞተ ያስቆጥረዋልና ወኪሉ ሞተ ማለት ወካዩ ሞተ ማለት ነው፤ በሞቱ ተከድኗልና፡፡ ለዚህ የተጻፈውን እናነባለን፤ «… አንዱ ስለ ሁሉ ሞተ፣ እንኪያስ ሁሉ ሞቱ፣ በሕይወትም ያሉት ስለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለ ሁሉ ሞተ፤ (2ቆሮ.5፡14-15)»

የባለ ዕዳው ምትክ/ወኪል ማለት እርሱ ራሱ በዕዳ የማይፈለግ ምትክ ሆኖ ከባለዕዳው ፊት አልፎ በጽድቁ ኃጢአተኛውን ጋርዶት /ሸፍኖት/ በመቆም ወኪሉ (ጠበቃው) (1ዮሐ.2፡1፣ ዳን.12፡1) ሞቷልና ወካይ ሳይሞት ከሞት በታች ስለተሸነጠ እርሱም ሞቷል ማለት እንጂ ወኪል ስለሞተ ወካይ በሕይወት ነው ማለት አይቻልም፡፡ የዚህ እውነታ ክርስቶስ በምትክነት ስለ ሁሉ ሞተ፣ እንኪያስ ሁሉ ሞቱ የሚለው ሐረግ ነው፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነው ወካይ፣ በወኪል ሞት ተሸፍኖና በውስጡ ተሰውሮ ከሞት ውስጥ እንጂ «በውጭ በሕይወት መኖር» ከቶ አይቻልም ማለት ነው፡፡ በውጭ መኖር ማለት፣ በኃጢአተኛ ሥጋ አመራር መንቀሳቀስ ማለት ነው፤ በሞት የተከደነ ሰው ለጽድቅ እንጂ ለኃጢአት የሞተ ነው፣ (ሮሜ 6፡2፣ 1ጴጥ.24) ይመሳከር፡፡

በዚህ ሁኔታ እስራኤል ወደ ቤቱ በመግባት በሩን በደም ጋርዶ በውስጥ መሆኑ፣ በውጭ በሞት ተሸፍነው፣ በውስጥ (በስውር) በበጉ በሕይወት መሆናቸውን ይገልፃል፤ እስራኤል በውጭ በግልፅ (በዓለም) ማለት በግብፅ ሕያው አይደለም ማለት ነው፡፡ እስራኤል በውስጥ እንጂ በውጭ የለም፡፡ ይህ ማለት ለኛ ለዛሬዎቹ በውስጥ በመንፈስ (በክርስቶስ) እንጂ በውጭ በሥጋ በሕይወት እንዳንኖር ትልቅ ትንቢታዊ መልእክት ያስተላልፋል (ሮሜ 8፡13) ይመሳከር፡፡ ከቤት ውጭ ማለት ከመቅደሰ ውጭ ማለትን ሲተረጉም፣ ከሞት ወደ ሕይወት መሻገር ማለትም ከውጭ ወደ ቤት







መግባት እንጂ ሌላ አገር አቋርጦ የትም መሄድ አይደለም:: አዳም የትም ሳይንቀሳቀስ ነው ወደ ሩቅ አገር የገባው:: የግብፃዊው ሕይወት ለእስራኤል ሞትና መቃብር ሆኖ ኖሮ ዛሬ ተገልብጦ የእስራኤል ሕይወት ለግብፃዊው ሞትና መቃብር ሆነ፡፡ ለእስራኤል በውጭ ሞታቸውን ሞቶ በሞቱ ዘበኛ ሆኖ የከለላቸው/ የሸፈናቸው በመንገድ ጉዞ ላይ ዘብ ሆኖ የጋረዳቸውና የመራቸው በእንስሳው ምሳሌ የተሠዋው ክርስቶስ እርሱ ነበር" 1ኛቆሮ.10፡1-4፡፡ ቀደም ሲል በጥላ በውጭ በደሙ ጋርዶአቸው በውስጥ በሥጋው ሕይወት የሆነላቸው እንደ ዘመኑ በምሳሌ የታደጋቸው ክርስቶስ ነው፡፡ ዋናው ትምህርት እዚህ ጋ ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚፈልገው በበጉ (በክርስቶስ) ውስጥ የተሰወረን የውስጥ ማለት የመንፈስ ሕይወትን ነው፡፡ ሰው ከእግዚአብሔር ፍርድ ክርስቶስን በልቶ በክርስቶስ ካልተሰወረና ከመጋረጃው (ከክርስቶስ) ውጭ ከሆነ ጠፍቷል፡፡ ሕይወትም የለውም፡፡ በዚህ ቀን እስራኤል በምትኩ በኩል ሞተና በሞቱ ግብፅን ማለት የዓለምን ክብርና ኃይል የሆነውን በኩር እጅ ሳይነካ ደመሰሰ፤ በቀል የእኔ ነው ራሳችሁ አትበቀሉ እንደተባለ እጅ ሳይነካ በእግዚአብሔር ጽድቅ ተበቀሉ እንደተጻፈ «…በቀልና ፍርድ የኔ ነው ዘዳ.32፡35» ከሮሜ 12፡19) ጋር ይመሳከር፡፡

የአሁኑም እስራኤል ወደ ውጭ (ውጭ ማለት የትኛው ነው) ከወጣ ሞት ያገኘዋል፤ ውጭ ማለት የትም ሳይሄድ በነበረበት ከመንፈስ ወደ ፊደል ከወጣ ማለት ነው፡፡ ፊደል ይገድላል መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣልና፡፡ በውጭ የሚታየው ቁሳዊ አገልግሎት የሞት አገልግሎት ሲሆን፣ በስውር መንፈሳዊው አገልግሎት ግን ሕይወት ያለው ነው፡፡ ይህ የእስራኤል ሥርዓት ለዛሬ አዲስ ኪዳኖች ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ በሕይወት እንድንኖር በርቀት ያመለከተው በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ተተርጉሞ የቀረበልን ከቀድሞ እስራኤል እጅግ የላቀ ዕድል ነው፡፡

በዘፀ.12፡6 ላይ «ሲመሽ» ይረዱት የሚለው እንዴት ነው? ከቀኑና ከሌሊቱ መካከል፣ ከብርሃንና ጨለማ መካከል ጣልቃ ማለት ትንቢታዊ ሆኖ፣ የክርስቶስን ጨለማና ብርሃንን፣ ሞትንና ሕይወትን የመለየት ዘላለማዊ የጣልቃ ገቢነት ሥራን አመልክቷል፡፡ የበጉ በቀንና በሌሊት መካከል ጣልቃ ሆኖ መታረዱ (ዘፀ.12፡6) ግብፃዊንና እስራኤላዊን ወደ ቀኝና ግራ፣ ወደ ቀንና ሌሊት፣ ወደ ጨለማና ብርሃን፣ ወደ ሞትና ሕይወት አድርጎ በመንሽ አለያይቷል፡፡ ዘፀ.10፡22-23/ን ከ14፡19-20 ጋር ዘፍ.1፡3-4ን እናመሳክር፤ የአሕዛብ ብርሃን በማየት የሆነ ፍጥረታዊ (ፀሓይ፣ ጨረቃና ከዋክብት) ሲሆኑ፣ (ዘዳ.4፡19) የእስራኤል ብርሃን ግን በማየት ሳይሆን በእምነት የሆነ ፈጣሪ ራሱ ነው፤ በጉ፤ (ኢሳ.60፡19-20፣ ራዕይ 21፡23፤) ፈጣሪ ሲወጣ የፍጥረት ብርሃን ይጠፋልና (ሐሥ.9፡3-9) በእስራኤል ላይ እግዚአብሔር ሲወጣ በግብፅ ላይ ፀሓይ ጠለቀች፤

በ(ዘፀ.12፡15) የተመለከተውን ቀን እሥራኤላውያን አንድ ብለው በተከታታይ እስከ ሰባተኛ ቀን እርሾ ያልገባበትን ትንቢታዊ የሆነ እንጀራ {ቂጣ} በመብላት ሊመጣ ያለውንና ያለ ኃጢአት የሆነውን እንጀራ ክርስቶስን ይሰብካሉ፡፡ ከቤቶቻቸውም እርሾ ያጠፋሉ፡፡ በእስራኤል ዘመን በብሉይ ኪዳን ከራስ ማንነት በውጭ ከሚታየው ቤት እርሾን ማስወገድ፣ በሐሰት እውነት ይፈረጃል፤ የእውነት እውነቱ በሆነው በአዲስ ኪዳን ግን ከውጪ ቤት ቁሳዊ እርሾ ማስወገድ ሳይሆን ከውስጥ ቤት (ከልቡና) ኃጢአትን በማስወገድ በንጹሕ ልብ ቀርቦ ክርስቶስን መብላትን ያመለክታል? (ያስተምራል)፡፡ በአዲስ ኪዳን እርሾ ኃጢአትን፣ ቂጣው ክርስቶስን ያመለክታል፡፡ ክርስቶስ እርሾ የሌለበት የሕይወት እንጀራችን ሲሆን፤ (ዮሐ.6፡51) ከእርሾ የፀዳ ቤት ንጹሕ ልብን ያመለክታል፡፡ ሰባት ቀን ከእርሾ የፀዳ ቤት ሰባት ጊዜ ከኃጢአት የፀዳ ልብ እግዚአብሔርን ስለሚያይ (ማቴ.5፡8) በራሱ ራሱን ችሎ መብራት ስለ ነበረ በፋሲካ ማለት በበጉ ሠርግ ግብዣ ላይ የተፈጠረና የፍጥረት





ብርሃን አልነበረም፤ «እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበረ፣ ዮሐ.5፡35» ቀድሞ ከእርሾ የተነሣ የጨለመው ቤት፣ ከኃጢአት የተነሣ የጨለመ ልብ የታወረ ሐሳብን ያመለክታል፤ (ሮሜ 1፡21፣ 2ቆሮ.4፡4፣ ኤፌ.4፡17-18፣ ከም.1፡18) ጋር ይመሳከር፡፡

በብሉይ ኪዳን የኃጢአተኛውን ኃጢአት ተሸክሞ የሚሠዋው "እንስሳ" ያለ ኃጢአት የሆነ ንጹሕ መሆኑ ኃጢአተኛውን ከእግዚአብሔር ቁጣ ጋርዶ በመካከል በመቆም ቀደም ሲል በእግዚአብሔርና በኃጢአተኛው መካከል የተዘረጋውን የጥል (የጠላትነት) መጋረጃ፣ ቋሚ ግድግዳ በሞቱ ይደመስሳል፣ በመፍረሱ ያፈርሳል፤ በመወገዱ አስወግዶ ከኃጢአተኛውና ከእግዚአብሔር መካከል የመተላለፊያ መንገድ በመጠረግ ይጠረጋል። ከእግዚአብሔር በኃጢአቱ ተሸፍኖ በሞት ተለይቶ የነበረ ኃጢአተኛ ኃጢአቱ በበጉ (በእንስሳው) ካሣ ሞት ስለተወገደ ከእግዚአብሔር ጋር ዕርቅ /አንድነት ተፈጠረ፣ ተቋርጦ የነበረ ሕይወት አሁን ቀጠለ፡፡ የዚህ የደስ ደስ ፍስሓ ልናደርግ ይገባል እንደተባለ፣ (ሉቃስ 15፡11-31) ኃጢአትን ተሞኖ የሞተ በግ ሥጋ ተጠብሶ ከአዲስ ቂጣ ጋር እየተበላ በምሳሌ (በሐሰት እውነት) መጪውን የእውነት እውነተኛውን ሠርግ በእምነት እያዩ ኃሤት ይደረጋል፤ አሜን፡፡ ትንቢታዊው የእውነት እውነቱ በግ ይመጣል፤ በእውነት እውነቱ ይሞታል፣ የማይፈርስ የእውነት እውነተኛው ዕርቅ ይደረጋል፤ የእውነት እውነተኛው የዘላለም ሕይወት ይቀጥላል፣ ለማይቋረጠው ዘላለም ደስታ በጉ ክርስቶስ የእውነት እውነተኛው ሥጋ በእውነት እውነተኛ እሳት (በመንፈስ ቅዱስ) ተጠብሶ አዲሱ ቂጣም እርሱ፣ አዲሱ ወይን ጠጅም እርሱ ሆኖ ጠፍተን የተገኘንበት ከሁሉ የተሸለ ልብስ ክርስቶስን፣ ለእግር ጫማ ለእጅ ቀለበት ጌጣ-ጌጥ ሁሉ እርሱ ሆኖ፣ ከእኛ ከአዲስ ኪዳኖች ጋር ሊደረግ ያለውን የእውነት እውነተኛውን ተስፋ በእምነት የሚያዩ እያዩ ያደርጉ ነበር እስራኤሎች፡፡

ቀደም ሲል ሕያው ያልኩትን ስናስታውስ፡ ኃጢአት ሕያው የሚያደርገው የሰውየው ሞት ነው። በሰውየው ሞት ኃጢአት ይኖራል፡፡ ኃጢአት ሕያው መሆኑን የምናውቀው በኢዮብና በእግዚአብሔር መካከል ይመላለስና ይከሠው እንደነበረ እንዲሁ በኃጢአተኛው ሰውዬና በእግዚአብሔር መካከል በአምላካችን ፊት ቀንና ሌሊት ባለማቋረጥ የወንድሞች ከሣሽ የሆነው (ራዕይ 12፥10) ሲመላለስ፡ ሲያሳጣው፣ ሲከሠው ድምፁ መሰማቱ የኃጢአት ግድግዳ በሕይወት መኖሩን ያሳያል ነው፡፡ ከዚያም ሊያሥፈርድብህና ወደ ወህኒ መቃብር ሊያወርድህ ሲከስ፣ ሰላም ሲነሣ ሲያስጨንቅ ትሰማለህ፤ «በኢየሱስ ስም!!» አሥር ጊዜ ብትልም አልሞተምና ዝም አይልም ካሰፈረደ በኋላ ኃጢአተኛውን ከኃጢአት በታች ባለው ሲዖል ወህኒ አውርዶ ከነሕይወቱ ይቀብረዋል፤ (ማቴ.5፥25-26) እርሱ ብርሃን ሆኖ በብርሃን የሚያይ ጌታ አንቀላፍቷል ያለውን ዓልዓዛርን ሞቷል አሰኝቶ እንዳስቀበረ ሁሉ በመቅደስ ውስጥ የጸሎት ካልተሰማ ሞቷል በማለት ከነሕይወትህ ያስቀብረሃል፤ ለዚህ እንቅልፍ ጸሎት ማቋረጥ ነው እንጂ ገሃዳዊ እንቅልፍ አይደለም፡፡ ኃጢአት ዕዳውን ሳንከፍለው አይለቀንም፡፡ ዕዳው ሞት መሆኑን ዐውቀን ፈርተናል፡፡ ምን ይሻላል? በሞት መግደል ብቻ ነው፣ በመደምሰስ መደምሰስ፡፡ ይህ በውጭ ነው በውስጥ? አንተና እኔ ለኃጢአት መሞትን እንፈራለን ምን ይሻላል? ሲዖል የት ነው? ትላለህ? ሲዖል ከኃጢአትህ በታች ነፍስህ በተቀበረችበት ቦታ ነው፤ እግዚአብሔርን እንዳታይ ልብህን ያሳወረው ጨለማ:: ዲያብሎስ ከማንነትህ ውጭ በምድር ውስጥ ነው፤ ብሎ የፊደሉ ወንጌል አገልጋይ አያታልልህ:: ለዲያብሎስ ከማንነት በውጭ እንክርዳዱን የሚዘራበት እርሻ የለውም::

ኃጢአትን ልንገድል አብሮ፣ ተጣምሮ መሞት ስላለ ሞትን ከሚፈረው ጋር ተጣምረናልና አብረን እንፈራለን፡፡ ለኃጢአተኛዋ ነፍስህ ትሳሳለህ? ኃጢአተኛዋ (ኃጢአትን በመሥራት የምትሞት) ነፍስህ (ሕዝ.18፥4፣ ቁ.





20) የማን ነፍስ ናት? የዲያብሎስ ናታ? የእግዚአብሔር ዘር በእርሱ ያለበት ኃጢአትን ሊያደርግ የማይችል ከሆነ (1ዮሐ.3፥8-9፣ ም. 5፥18) ኃጢአትን የሚያደርግ ዘሩ የማን ቢሆን ነው? ኃጢአትን መግደል በውጫዊው አካል (በፊደል) ሞቶ ነው ወይስ በውስጣዊ አካል በስውር ሞቶ ነው? ግልፅ ነው፡፡ ይህ ማለት ከበር ውጭ በመታየት መሞት፣ ከበር ውስጥ በእምነት መሞት ነው፡፡ ብሉይ ኪዳኖች ከበር ማለት ከመጋረጃ ውጭ ማለትም ከማንነት ውጭ በሰው ፊት መሥዋዕት የሚያቀርቡ ሲሆን፣ አዲስ ኪዳኖች ከበር (ከመጋረጃ) ውስጥ በማንነት ውስጥ በጌታ ፊት መሥዋዕት ያቀርባሉ፡፡

የብሉይ ኪዳኑ ከበር፣ ማለት ከመጋረጃ ውጭ የቀረበው መሥዋዕት አቅራቢውን ከበር (ከመጋረጃ) ውጭ አደረገው ከእግዚአብሔር አራራቀው እንጂ ወደ እግዚአብሔር አንድ አካልነት አላቀረበም፡፡ ይህ የመካከል ግድግዳ የሆነ መጋረጃ እንዴት ይወገዳል? እርሱስ ቁሳዊውን ዓይን የሚጋርድ ግድግዳ ቁሳዊ መጋረጃ ነው ወይስ መንፈሳዊ ዓይንን የሚጋርድ ግድግዳ ነው? ግድግዳው መፍረስ የሚችለው፣ ቀደም ሲል እንዳየን በሞት፣ በመፍረስ ብቻ ነው፡፡ በዕዳ የማይፈለግ ጻድቅ እንጂ የኃጢአተኛ ሞት (መፍረስ) ግድግዳውን አፍርሶ ኃጢአተኛውን ወደ እግዚአብሔር አካልነት እርቅ አያደርስም፡፡ ስለሆነ በዕዳ የማይፈለግ ክርስቶስ ተወክሎ በመሞት በመካከል ያለ ግድግዳ ገደለ፤ በመፍረስ አፈረሰው በመወገድ አስወገደው፣ ...በሥጋው ያፈረሰ ተብሎ ተጻፈ፤ (ኤፌ.2፥11-19፣ ቁ.14-15) ኃአጢአት በነበዚህ ሁኔታ በጢአት ማዕከል በነበረበት ሥፍራ አሁን ኃጢአትን እጅ ሳይነካው ከተራራው የተፈናቀለው ድንጋይ (ክርስቶስ) ደምሰሶት በማዕከሉ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ተፈጠረ፣ ስለሆነም አማኑኤል ተብሎ ተጠራ፤ (በፕሮፓጋንዳ) አይሁን እንጂ፡፡ ከሐሰት እውነት አማኑኤሎች የእውነት፣ እውነት አማኑኤሎች ይለዩ ነው፡የብሉይ ኪዳኑ በግ ደም ይህን

የኃጢአት ዋጋ ሞት መፈፀሙን ለማብሠር ገብቶ በጌታ ፊት ይረጫል። የእግዚአብሔር ቁጣ ከኃጢአተኛው ላይ ስለተመለሰና ዕርቅ ስለተፈጠረ ለዚህ ደስታ የበጉ ሥጋ ተጠብሶ ግብዣ ሆኖ በውጭ በምሳሌ ይበላል፣ ሥጋው በጠባቡ በር ወደ እግዚአብሔር ሊገባ አይችልምና በሰፊው በር ወደ ሆድ ይገባል።

ይህ ያለ ኃጢአቱ ኃጢአት የተጫነበትንና በሰው ዘር ሁሉ ፊት አልፎ በሰማይና በምድር መካከል፣ በሰውና እግዚአብሔር መካከል አየር ላይ በሰው ምትክነት ተገድሎ ውኃዊውን ደም በውጭ አፍስሶ በገዛ ደሙ ወደ እግዚአብሔር በመግባት (ዕብ.9፡ሰ12) የእግዚአብሔርን ቁጣ ከዓለም ስለመለሰ የሰማይና የምድር ዕርቅ ሠርግ ግብዣ ሆኖ በጉ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ እሳት ፍቅር ተጠበሶ፣ ብቻውን ምግብና የወይን ጠጅ ሆኖ በመቅረብ ዓለምን ሁሉ ከንጉሡ እግዚአብሔር ማዕድ በፊቱ እንድንካፈል ያበቃንን ክርስቶስ ኢየሱስን በግልጽ ይተነብያል፣ ክብር ለእርሱ ይሁን፣ ለዘላለሙ አሜን፡፡ ክርስቶስ ከውጭ ምንም ሳያስፈልግ ሁሉ በሁሉ ሆኖ በሁሉ በቂ በመሆን ቀርቧል፤ በግም፣ ወይንም፣ እንጀራም፣ ሠርግም ሠርገኛም፡፡ ፊደላዊ (ፍጥረታዊ)ው በግ ራሱ የታረደና በራሱ እሳት በስሎ ሰው ብቻ እጁን? ልቡን? ታጥቦ እንዲበላው አልቀረበም፤ ላለመሞትም ሲፈራገጥ ተገድሏል፡፡ በራሱም አልበሰለም፣ ገና ጥሬ ነውና በግድ ተገድሎ ሞቶ፣ ተጠብሶ ስለቀረበ ክርስቶስን የሚያመለክተው በመጠኑ ነው፡፡

በእግዚአብሔር የፍቅር እሳት መጠበስና መብሰል የሚቻለው እንዴት ነው? የእግዚአብሔር ፍቅር አያቃጥልም? አያነድም ወይ? ሴድራቅ፣ ሚሳቅ፣ አብድናጎ በእግዚአብሔር እሳት ገሃነም አልተቃጠሉም ወይ? እሳቱ በቁጥቋጦው ላይ እየነደደ ቁጥቋጦውን አይበላውም እንጂ፣ አልተቃጠለም ወይ? መጥምቁ ዮሐንስ እየነደደ ያበራ የነበረው (ዮሐ.5፡ 34-35) በእግዚአብሔር ቅንዓት ፍቅር እሳት እንጂ አመድ አለመሆኑ



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ እዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡ ከእነዚህ አንዷት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፣ ኢሳ.34፡16



አይገባንም ወይ? ሌሎችንም ነቢያትና ሐዋርያትን ሁሉ ሰይፍ ሆኖ የበላው፣ ጦር ሆኖ የወጋው፣ ቁልቁል ያሰቀለው የእግዚአብሔር ፍቅር እሳት አይደል? ይቅረብ፤

የብሉይ ኪዳን ሥራ፣ ኃጢአትን ማለትም ሰይጣንን በተናጠል መግደልና ጠብሶ በእግዚአብሔር ፊት መብላት ስለማይቻል ኃጢአት ወይም ሰይጣን በእንስሳው፣ «ሥጋ» እንዲሆን ይናዘዙበታል፣ ማለትም ሞት የሚገባው ለጻድቅ ወይም ለንጹሕ ሳይሆን፣ ለኃጢአት ወይም ለሰይጣን ስለሆነ፣ የሚገደል፣ ወይም የሚሞት ነገር ሞት የሚገባው ሆኖ መገኘት ስላለበት እንስሳው ሊገደል ከመቅረቡ በፊት እንደ ሌጌዎን ሰይጣን ከኃጢአተኛው ሰው ወጥቶ ወደ እንስሳው መግባት አለበትና (ማረ.5፡-13) ኃጢአት ወይም ሰይጣን የገባበትን እንስሳ ገድሎ አርዶ በጌታ እሳት ጠብሶ የሥጋውን ጣፋጭ ሽታ ማለት መንፎሱን (ጪሱን) ለእግዚአብሔር እያቀረቡ፣ ሥጋውን (ቁስ አካል) ክፍሉን ድብን አድርጎ ጠብሶ በሕጉ መሠረት በተመረጠው ሥፍራ፣ በጌታ ፊት የተቀደሰውንና የተባረከውን ከጌታ ማዕድ ሲበሉት እንዴት-እንዴት ይጥማል? ጣዕሙ ማር ነው፣ ጣት ያስቆረጥማል፣ (መሳ.14፡8-9ቀ.14፡18) ለዘላለሙ አሜን፡፡

ይህን ገለጥ ለማድረግ ወደ ጎን እናያለን፤ ሰይጣን፣ ወይም ኃጢአት ያለ ሥጋ ታርዶ፣ ተጠብሶ ለመሥዋዕት ሊቀርብም፣ ሊበላም አይችልም፡፡ ሥጋ ሲባልም፣ በአሕዛብ፣ በእስራኤል፣ በመለኮት በሦስት ደረጃ መታየት ይገባል፡፡ የመጨረሻው ሥጋ እንዲሰቀል የተፈረደበት ክፍለ አካል ስለመሆኑ የተብራራውን እንደርስበታለን፡፡ ሥጋ ሰይጣንን እንዳያመልጥ ጠፍሮ ማሠሪያና መግደያ ሆኖ የተዘጋጀ ስለመሆኑ የብሉይ ኪዳን የመሥዋዕት አቀራረብ ምሳሌ ያሳያል፡፡ ከተጠበሰው ሥጋ ለእግዚአብሔር የቀረበው ጪሱ ሰይጣን ነው ወይስ ለሰው የቀረበው ሥጋው ሰይጣን ነው? መልስ ስጥ፤ እሳት እውነትንና ሐሰትን መለያ (መቀደሻ) መሣሪያ ሆኖ ይታያል፡፡ እሳት፣ የፍርድ ምሳሌ ነው፡፡ በእሳት ካልሆነ ሰይጣን ከሥጋ



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ እዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡ ከእነዚህ አንዷት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፣ ኢሳ.34፡16

አይለይም፡፡ ከሥጋ የተለየ ሰይጣን መግቢያው የት ነው? ከእሳት ወደ ፍፁም እሳት?

እግዘአብሔር አዳምን በሥጋ ቁርበት የጠፈረው ምን ሲያደርግበት ነበር? የአዳም ሥጋ ሰይጣንን እስከ ፍርድ ቀን ከመመንት በስተቀር ወደ ፈለገበት ሁሉ እንዳይበርር የማሠሪያ ግንዴላ ነበር፡፡ በእሥር በተወሰነ ክልል ብቻ እንዲንቀሳቀስ የቅርቡን ብቻ ከሚያይ ዕውር ዓይን ጋር ገደበው፤ አሠረው፣ (ዘዳ. 32፡8፣ ሐሥ. 17፡26-27፣ ኢዮብ 14፡5) ይመሰክር፡፡

የብሉይ ኪዳን በግ ሊመጣ ያለው በግ ግርዶሽ ሲሆን፣ ኃጢአት የሰይጣን መጋረጃ ነው፡፡ ኃጢአትን መናዘዝ ሰይጣንን፣ የሞትን መርዝ ማስመለስ ነው፡፡ በቀድሞ ሥርዓት ኃጢአትን ማለት ሰይጣንን መትፋት ምትክ ሆኖ ሊሞት በተዘጋጀው በግ ላይ ነበር፡፡ ኃጢአት ወይም ሰይጣን በበጉ ላይ ሲናዘዙትም ወይም ሲተፉት ሊታረድና ተቃጥሎ ሊጠፋ ስላለ እየተንቀጠቀጠ እንደሚተፋ አሁን አንተና እኔ ኃጢአትን በበጉ ክርስቶስ ላይ ለመጫን ስንናዘዝ (ስንተፋው) ክርስቶስ እሳት በመሆኑ ኃጢአት በውስጣችን ሆኖ ፍርድ ሊቀበል ነውና አብሮን የኖረበትን ምድር፣ (አካል ምድራችንን) ሲያንቀጠቅጥ አካላችን የሆነ ነውና ከእርሱ ጋር አብረን እንንቀጠቀጣለን፣ እንፈራለን፡፡ ማንም ሰው ኃጢአቱን ወይም ነውሩን ሊናዘዝ፣ ሊተፋው የሰውን ፊት ፍርድ እንኳ ፈርቶ ይንቀጠቀጣል፡፡ የሰይጣኑ ፍርሃት፣ ጭንቀቱ ይተላለፍብናል ለማለት ነው፡፡

አሁን በእግዚአብሔር ፊት አልፎ ሊሞትልህ ሥጋህ በመሆን በተዘጋጀው በጉ ክርስቶስ ላይ በመናዘዝ ኃጢአትህን ትጭንበታለህ፡፡ ከትንግሌ ወዲህ ክርስቶስ ካንተ/ቺ በውጭ በርቀት የሚሞት ሳይሆን በማንነታችን ሆኖ ነው፡፡ እንደ ብሉይ ኪዳኑም በግ ክርስቶስ በሥጋህ ከፊትህ መሪና ቀዳሚ አርዓያ ሆኖ ሲሞት፣ አንተም ከኋላው ሆነህ አብረህ ከእርሱ ጋር ሞትክ





ማለት ነው፡፡ የብሉይ ኪዳኑ ኃጢአት የተጫነበት በግ ከተገደለ በኋላ በእሳት ተጠብሶ የሚበላ ከሆነ፣ አሁን የአዲስ ኪዳኑ በግ፣ ክርስቶስ የእኔ ኃጢአት ሰይጣኔ ተጭኖበት ለሞት ከቀረበ ዘንድ ተጠብሶ የሚበላው በምን እሳት ነው? ቢባል፣ እሳት የእሳት ምሳሌ ነው፡፡ የአዲስ ኪዳኑ የእውነት እውነተኛው እሳት እንደ ሙሴ ቁጥቋጦ አመድ ሳያደርግ የሚያቃጥለው እሳት መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ክርስቶስ ለዓለም ሕይወት ምግብ ሆኖ የቀረበው በእውነት እውነተኛ እሳት በመንፈስ ቅዱስ ስለሆነ (ዕብ.9፡"4) ቅዱስ ምግብ ነው፡፡

ጥልን፣ አንድ ሲሉ በዝርዝር 16 (የገላ.5፡19-20) ዓይነት የሥጋ ሥራዎች በጸሐፍ ሰፍረዋል፡፡ ጥል ማለት ጠላት፣ ጠላትነት ነው፣ የተጻፈው ጠላት ሰይጣን ነው፤ (ማቴ.13፡24-28፣ ሉቃስ 10፡19፣ 1ጴጥ.5፡8፣ 1ቆሮ. 15፡25፣ ዕብ. 10፡13)፡፡ የሥጋ ሥራ የሰይጣን ሥራ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሥጋና መንፈስ እርስ በርሱ ጥለኞች አንዱ ሌላውን ተቃዋሚ ነው፡፡ እነዚህ የተዘረዘሩት የሥጋ ፍሬዎች፣ የጠላቱ የሰይጣን ፍሬዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ኃጢአት እንደ መሆናቸው መጠን እንዲገደሉ የታዘዙ የሥጋ ብልቶች እንደሆኑ (ቆላ.3፡5) ይገልፃል እነዚህ በገሃዱ ዓለም በግልፅ የማይታዩ ብልቶች እንደ መሆናቸው በመንፈስ እንጂ በግልፅ የሚገደሉ አይደሉም፤ እንደ ተጻፈ፣ «... በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ፣ (ሮሜ 8፡13)» ሥጋ የተባለውም፣ ሰውነት የተባለውም፣ ብልት የተባለውም ተሰቅሎ እንዲሞት የተፈረደበት የማይታየው አካል ሰውነት ሰይጣን እንጂ ገሃዱ (ተጨባጩ) ሥጋ ሰውነት እንዳደለ ግልፅ ነው፡፡ ሥጋ እንዴት እንደሚሰቀል በዚህ መጽሐፍ በበቂ ተብራርቷል፡፡

እንዲህ ሲባልም ሥጋ ያለ ሰይጣን፣ ሰይጣንም ያለ ሥጋ የለም፡፡ ሰይጣን ያለ ሥጋ ከሆነ ተፈረደበት፣ ወደ ውጭ ተጣለ፣ ያለ መድረሻ በንኖ ጠፋ ማለት ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ በሰይጣን ላይ ፈረደበት ማለት፣ በመንሸ ከሥጋ ለይቶ ያለ መድረሻ ለዘላለም እንደ ከነፈ እንዲኖር አደረገው

ማለት ነው፤ አጋንንቱ ኢየሱስን «ልታጠፋን መጣህን?» እያሉ የሚወተውቱት ለዚህ ነበረ፡፡ ጠላት፤ ማለት ሰይጣን ከሥጋ ጋር በጣምራ ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ቅዱስ መሥዋዕት አድርጋችሁ አቅርቡ ሲል እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ቅዱስ መሥዋዕት ማለት እንዴት ነው? እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ቅዱስ ማለት በእሳት ተቀድሶ ያለፈ ሰውነት፣ ወይም ሥጋ ማለት በዘመናችን ቀዳሹ እሳት መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡

እንግዲህ ሥጋን የገደለ ሰው ማለት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሰውነቱን ከኃጢአት ለይቶ፣ ቀድሶ በጌታ ፊት አዋርዶ ሲያቀርብ መሥዋዕት አድርጎ አቀረበ ማለት ነው፡፡ በእንዲህ ሁኔታ ሥጋ ጠላቱ ተጠብሶ እርር ብሎ ሲቀርብ እግዚአብሔር ደስ ይለዋል፡፡ ጪሱም ለእግዚአብሔር መልካም መዓዛ ሆኖ ይቀርባል እንጂ ሥጋው ለአቅራቢው በጌታ ፊት በቅዱስ ሥፍራ የተባረከ የተቀደሰ መብል ይሆንለታል እንደ ሊቀ-ካህን፡፡ «ከሥጋው አንዳች ከቤት ወደ ሜዳ አታውጡ...» ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ «...አለቃው (ሊቀ-ካህኑ) በእግዚአብሔር ፊት እንጀራ ይበላ ዘንድ ይቀመጥበታል፣ በበሩ ደጀ-ሰላም መንገድ ይገባል፣ በዚያም መንገድ ይወጣል (ሕዝ. 44:3)»፡፡ ዛሬ የግል ጠላትህን በራስህ ውስጥ የራስህን አጋንንት ሥጋህን ከነተጣማሪው ትዋጋለህ፣ ሥጋህን ልትለየው ስለማትችል አጣምረህ ትገድላለህ፣ ፍሬው እስኪለይ ድረስ ከገለባ ጋር አብሮ እንደሚወቃ፡፡ ሥጋህን ከነተጣማሪው ሕያው፣ ቅዱስ መሥዋዕት አድርገህ ለጌታ ታቀርባለህ እንጂ እንደ ብሉይ ኪዳን ሥርዓት ካንተ ጋር የተዋኸደውን ተራምደህ አልፈህ ከማንነትህ በውጭ በርቀት ያለውን ጠላት ከነዓናዊን፣ ኬጢያዊን፣ አሞራዊን...ወዘተ አይደለም፡፡ ጠላት እንደ ገባዖን ሰዎች (ኢያሱ 9:1-23፣ ቁ.16፣ ቁ.22) ከውጭ ለማምለጥ ሸሽቶ እውስጥህ የገባውን ካንተ ጋር አጣምረህ ካልሆነ እንዴት አድርገህ ለይተህ ትገድለዋለህ? ጠላትን እንጀራ ይሆኑናል (ዘኁ.14:9) የተባለው የውጫዊ፣







ፊደላዊ (ፍጥረታዊ) ከማንነት በርቀት ያለ ርስት ጠላት ሥጋን አመልካች ሳይሆን የውስጣዊን፣ በአዲስ ኪዳን ስቀሉ፣ ግደሉ የተባለውን በማንነታችን ውስጥ ያሰገሠገውን ጠላት ሥጋ አመልካች ትንቢታዊ ነበር፤ መግደል ማለት በግልፅ መግደል ሳይሆን የተዋረደ የተቀጠቀጠ የተዋረደ (ኢሳ.57፡ 15፣ ም. 66፡2፣ መዝ. 51፡16-17፣ ማቴ. 20፡25-26) ለምሳሌ ሳምሶን አንበሳን ገድሎ ግዳዩን ከእናት አባቱ ጋር የበላውና ማር የሆነላቸው በውጭ የሚታየው የፊደሉ አንበሣ፣ ዛሬ በአዲስ ኪዳን ሲታይ በመጋረጃ አንበሣ፣ አስመሳዩና የሐሰት እውነቱ ሆኖ ትንቢታዊ ነበር፤ (መሳ. 14፣ 8-9 ቁ.14፣18) እንጂ ይህ ዛሬ የእውነቱ እውነቱ አንበሣ ከማንነት በውጭ፣ በርቀት ያለው ውጫዊ፣ አንበሣ አመልካች ሳይሆን፣ ውስጣዊን የሚውጠውን ሰው ሽቶ በማንነታችን ውስጥ የሚያገሣውን በሥጋችን ተሸፋፍኖና አካል ሰውነታችንን መስሎ ያለውን ዲያብሎስን ያመለክታል፡፡

ቀደም ሲል እንዳየነው ይህን አካል ሰውነታችን ሆኖ ተዋህዶን ያለ የመንፈሱን አንበሣ (ሥጋን) በመንፈስ ብንገድለው ንብ ገብቶበት የማዳዩን ግብሮ ፊደላዊ (ፍጥረታዊ)ውን ማር እንበላለን ወይስ መንፈስ ቅዱስን እንበላለን? ይህ አንበሣ ቢገደል ማር ይፈልቃል ወይስ መንፈስ ቅዱስ ይፈልቃል? መንፈስ ይፍለቅ ወይስ መንፈስ ቅዱስ ይፍለቅ? ይልቅ የሚጣፍጠው የፊደሉ ማር፣ ማር ነው ወይስ የመንፈሱ ማር፣ መንፈስ ቅዱስ ነው? ከማንነት ውጭ በሜዳ ያለውን ፊደላዊ (ፍጥረታዊ) (የሐሰት እውነቱን) አንበሣን ገድሎ ማር ካወጣው ሳምሶንና ከማንነት ጋር ተጣብቆ አካል ሰውነት የሆነውን በውስጥህ የተሰወረውን የእውነት እውነቱን አንበሣ ዲያብሎስን ገድለህ መንፈስ ቅዱስን ካፈለቅኸው ከአንተ ማን የተሻለ አድርጓል?

ጌታ ኢየሱስ አንበሣን ገድሎ ነው መንፈስ ቅዱስን ያፈሰሰው ወይስ ሥጋን ከነዲያብሎስ ገድሎ ነው? ከዚህም ጋር የአሕዛብን ወተት ትጠጪያሽ፣ የነገሥታትንም ጡት ትጠቢያለሽ (ኢሳ.60፡16) የሚለውን

እናነፃፅር፡፡ ወተትና ማር ሊፈልቅ የሚችለው በውጭ ያሉትን አሕዛብ፣ ከነዓናዊ፣ ኬጢያዊ፣ አሞራዊን ቢገድሉ ነው ወይስ በማንነት ውስጥ ያለውን አሕዛብ (አዳምን) ቢገድሉ ነው? ሌላውን ከሚገድለው ኢያሱና በራስ ማንነት ውስጥ ያለውን አሕዛብ (አዳምን) ከምትገደለው አንተ ማን ጀግና ነው? አስብበት፡፡

በሕይወት መኖር የምንችለውም በሊቀ ካህንነት ሥልጣን መሥዋዕት ዘወትር ለእግዚአብሔር ስናቀርብና የመሥዋዕቱን ሥጋ እንጀራ በተቀደሰ ሥፍራ የግዳዩን ደስ፣ ደስ በፊቱ በመበላት ነው፡፡ አለበለዚያ በእግዚአብሔር ፊት መብላት ያለብን ምንድን ነው? እኛ በክርስቶስ ጸጋ ሊቃነካህናት ነን እንላለን ስንመፃደቅ፣ ያድርገውና፡፡

እንዲህ ከሆነ የምናቀርበው እንደ ብሉይ ኪዳን ሥርዓት ከማንነት ውጫዊ የሆነ ነገር ማቅረብ እንደማንችልም ግልፅ ነው፡፡ የምናቀርበው መሥዋዕት «...ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ...» ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው (መዝ.39፡6-8፣ ዕብ.10፡5-7)፡፡ እንዲሁም ደግሞ (ሰውነታችሁን) ሥጋችሁን፣ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው፣ ቅዱስ መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ...ተብሏል (ሮሜ 12፡1) ደግመን ብናስታውስ፡፡

እግዚአብሔር ሥጋችንን ስናቀርብለት ይበላል ወይ? እንዲህ ይላል፣ «የፍሪዳውን ሥጋ እበላለሁን? የፍየሉንስ ደም እጠጣለሁን? (መዝ.50.13-14)» የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ ልብ ነው፣ (መዝ.51፡16-17) ከዚህም ሌላ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ...ከእርሱ ጋር ራት እበላለሁ፣ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል ከንጉሡ ጋር ከማዕዱ (ራዕይ 3፡20) እኛ ሥጋችንን እንጀራ አድርገን ስናቀርበለት እርሱ ከዚያ አንሥቶ ለእኛ ራሱን ሥጋውን እንጀራ አድርጎ ያቀርባል፤ እንደ ሰገነቱ ራት፡፡ ጥሬ ሥጋ በእሳት ስለ አላለፈ ሰይጣን ነውና ቅዱስ ሳይሆን እርኩስ ነው፡፡ እንደ ብሉይ ኪዳን በግ በእሳት ተቀድሰን ጣፋጭ ሽታ ሆነን ነው እንጂ፡፡







ኢየሱስሳ? የኢየሱስ ግዳይ የት ገባ? ኢየሱስ በዘላለም መንፈስ የሚቃጠል መሠዋዕት አድርጎ ራሱን ያቀረበው በሕጉ መሠረት ኃጢአትን በላዩ የተጫነበት በግ ሆኖ ነው፤ በውስጡ ግን (በመንፈሱ) ንጹሕ፡፡ በሕጉ በራሱ በኩል ነውር የሌለበት እንስሳ በራሱ ላይ በተጫነው የሰው ኃጢአት ይሞታልና፡፡ እንስሶቹ አፍ ባይኖራቸውም በባሕሪና በመሥዋዕትነታቸው ሊመጣ ላለው ክርስቶስ ምስክሮች ነበሩ፡፡

የፋሲካው ሕግ፤ (ዘፀ.12፡43-50)

የፋሲካው ሕግ በግራ በኩል የእግዚአብሔር የማዳን፣ የኃጢአት ዋጋ ዕዳ ክፍያ ሥቃይ፣ በቀኝ በኩል የዕርቅና ምህረት ደስታ፣ ፌንጠዚያ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ሆኖ መታየት ያለበት ነው፡፡ ፋሲካን መካፈል ያለበት ምን ዓይነት ሰው ነው? ዳግመኛ የተወለደ ሰው ከሙታን የተነሣ፡፡ ፋሲካ በመብልነቱ ምንድን ነው? ፋሲካ በአዲስ ኪዳን የውስጥ ሰውነት ሕይወት እንጀራ ነው፡፡ የሰው ልጅ የውጭና የውስጥ፣ የፊደልና የመንፈስ ሰውነት ጣምራ ፍጥረት ነውና፡፡

በመሠረቱ ፋሲካን የመካፈል ምስጢር የእውነት እውነቱ ምንድን ነው? ፋሲካን መብላት ማለት ክርስቶስን በአዳም ያመለጠውን በእግዚአብሔር ገነት ያለውን ሕይወትን ዛፍ በድል አድራጊነት ደርሶ መብላት ማለት ነው፣ (ራዕይ 2፡7)፡፡ በሌላ በኩል የሕይወት ዛፍ ከተሠወረ መና ጋር ባንድነት ተጠርቷል፤ (ራዕይ 2፡17) እንዲሁም ደግሞ ዛፉጋ ለመድረስ በድል አድራጊነት በበሩ መግባት ይችሉ ዘንድ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ተጋዳዮች እንደ ሆኑ (ራዕይ 22፡14) ጨምሮ ይገልፃል፡፡ ድል አድራጊ ተጋዳይ ጀግኖች ሲባል ምን ማለት ነው? ድል አድራጊ ተጋዳይ ጀግኖች ልብሳቸውን ማጠብ የሚችሉ ጀግኖች ማለት ነው፡፡ ልብሳቸውን የሚያጥቡት በምንድን ነው? በ/ራዕይ 7፡14) እንደ ተገለጠው ልብሳቸውን የሚያጥቡት በበጉ ደም ነው፡፡ የበጉ ደምስ ምንድን ነው? ከበጉ

እየመነጨ የሚፈልቀው የሕይወት መንፈስ ቃሉ ነው፡፡ በሌላ አቅጣጫም የሕይወት መንፈስ የሕይወት ውኃ ተብሏል፤ (ኤር.2፥13፣ ም.17፥13፣ ዮሐ.4፥13-14፣ ም.7፥37-39-) ይህ ልብስን ያጥባል ወይስ ልብን? ልብን ይጠብ ወይስ ልብስን ይጠብ? ወደ ፋሲካው ሠርግ አዳራሹን የሚያስገባው ንፁህ ልብስ ነው ወይስ ንፁህ ልብ ያስገባል?

በበጉ ደም ልብስ ማጠብ ጀግንነት ሆኖ ለድል አድራጊነት ማብቃቱ እንዴት ነው? ዕድፉስ ምንድን ነው? በበጉ ደም ልብስን ማጠቡ ጀግንነት ነው ወይስ ልብን ማጠቡ ጀግንነት ነው? በጠባቡ በር ወደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከተማ ለመግባት (ሉቃስ 13፥24) በተጋድሎ መወገድ ያለበት ዕድፉሙ ልብ ነው ወይስ ዕድፉሙ ልብስ ነው? ድል የነሣ የተባለው ዕድፍ የሆነ አሮጌውን ማንነት ማስወገጃ የተጋድሎ ሥነ-ሥርዓት ስለሆነ ነው የድል አድራጊነቱ ጀግንነት፡፡ የበጉ ሠርግ የሆነ የፋሲካውን ራት ለመካፈል የሚያበቃ ሸለፈት የሆነ አሮጌ ማንነት የማስወገዱ ሥነ-ሥርዓት ከሙታን መነሣት፣ ዳግመኛ ልደት ተብሏል፡፡

ፋሲካውን መብላት የሚገባው ምን ዓይነት ሰው እንደሚሆን መስፈርቱ ለእስራኤልም ሆነ፣ ለአሕዛብ በብሉይ ኪዳን ቀጥሎ ተመልክቷል፡፡

- እንግዳ ሰው ከእርሱ አይብላ፤
- በብር የተገዛ ባርያ ቢኖር ከተገረዘ በኋላ ከእርሱ ይብላ፤
- መፃተኛና ሙያተኛ ግን ከእርሱ አይብሉ፤
- በአንድ ቤትም ይበላ፤
- ከሥጋው አንዳች ወደ ሜዳ አታውጡ፤
- አጥንትም አትስበሩበት፤
- ዕንግዳ ሰው በመካከላችሁ ቢቀመጥ ለእግዚአብሔር ፋሲካ ሊያደርግ ቢወድድ አስቀድሞ ወንድ ሁሉ ይገረዝ፤ ከዚያ በኋላ ይቅረብ፣ ያድርግም፣
- ያልተገረዘ ሁሉ ግን ከእርሱ አይብላ፡፡





እንግዳ ሰው ከእርሱ አይብላ፤ ፋሲካው በበጉ አካል ብልትነት ለመጠቅለል የሱን አካል የሚካፈሉት ሲሆን፣ እንግዳ፣ ወደ መጣበት ተመላሽ፣ ስለመሸበት ያደረ፣ የዕለት ሰው መሆኑ ነው፤ እዚህ፣ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር ርስትም ውርስም፣ ተስፋም የሌለው፣ መስፈርቱንም ያላሟላ፣ የቀድሞ ወገኑን ያልተወ ወገኑም፣ ርስቱም፣ ውርሱም ውጭ ሌላ ጋ የሆነ ማለት ነው፡፡ እንግዳ ሰው ወደ ራሱ ሥፍራ ተመላሹን የአስቆሮቱ ይሁዳን ዓይነት ሆኖ ይታያል (ሐዋ.1፡25)፡፡

አዳምምኮ በልደቱ ወደ ሌላ ከተወለደ በኋላ ዘሩ ሌላ ባዕድ ሆኖ እያለ የሕይወት ዛፍ ከሆነው ክርስቶስ ገብቶ ሳይሆን እጁን ዘርግቶ ወስዶ እንዳይበላ (ዘፍ.3፥22፣ ከማር. 14፥20፣ ሉቃስ 22፥21) ተደረገ፡፡ እዚህ ላይ እንግዳውን እንግዳ፣ ባዕድ የሚያደርገው በዘሩ ሌላ መሆኑ ብቻ ሳይሆን አለመገረዙ ጭምር ነው፤ ሸለፈቱን አለማውለቁ፤ ከእስራኤል ጋር አንድ አካል አለመሆኑ አለመገረዙ ርኩስነት ከመሆኑም ከመግቢያው በር (ከክርስቶስ) በላይ መግዘፉ ነው። ከርኩሱ ጋር ቢካፈሉ ርኩሰቱ ይተላለፍባቸዋል። በዚህ አንፃር የዛሬው እንግዳችን ቀደም ሲል እንዳየነው ነገ፣ ተነገወዲያ ሊለይን ያለ ከቁሳዊ በቤታችን ጣራ ቢታች አድሮ ውሎ ሂያጅ ግልጡ እንግዳ ሳይሆን፣ ነገ፣ ተነገወዲያ አፈር ሆኖ እስኪለየን ድረስ ለጊዜው የሚያድረው ከእርሱ ጋር ኖረን የረከስንበት ተቆርጦ መጣል የሚገባው ርኩሱ እንግዳ የአዳም ሸለፈታችን ሥጋችን ነው እንጂ ከማንነታችን ውጫዊ ሰው እንዳልሆነ ልብ ማለት አለብን። ይህ እንግዳ በባለመጋረጃው ብሉይ ኪዳን ዘመን ከማንነታችን በውጭ በኩል በራሱ ልዩ አካል ሆኖ በልዩ አካል መጋረጃ ተለይቶ አድሮ ይወጣ የነበረው፣ አሁን ግን መጋረጃችንን ዘልቆ ገብቶብን የገዛ አካላችን የሆነ አዳም ነው፡፡

ከእኔና ከአንተ/ች ጋር ያለው አዳም እኛን ዘርግቶ የሕይወት ዛፍ ከሆነው አስመሳዩን እንጂ የእውነቱን እውነት ፋሲካ ቅዱሱን እንጀራ እንዳይካፈል የሕይወት ዛፍ ከሆነው ፋሲካና አዳማችን መካከል የግዝረት ሰይፈ ነበልባል ተዘርግቷል። እርሱንና ከእርሱ ጋር ተስማምተን የምንኖረውን ወገኖች ሕጉ፣ «የቁልፈቱን ሥጋ ያልተገረዘ ቆላፍ ሁሉን ከወገኑ ተለይቶ ይጥፋ እያለ ነው»፡፡ ወገኔ ሆይ፣ ከዚህ በሰይፍ ስለት መወገድ ካለበት እንግዳችን ጋር ተቃቅፈን እስካለንበት ጊዜ ሁሉ የእግዘአብሔር እራት የሆነ ፋሲካ {ክርስቶስን} መብላት ከቶ አይፈቀድም፤ "ሰማይና ምድር ያልፋል" እንጂ ሕጉ በሥራ ላይ እስካልዋለና {እስኪልተፈፀመ} ድረስ /በ/ ዝምበሎ ሊሻር ከቶ አይችልም (ማቴ.5፡18፣ 24፡35፣ ኢሳ.፡40፡8) ጋር ይነፃበር፤ የጌታን እራት የበላን በማስመሰልና በመመሰል አርቲፊሻል በሆነ ሥራ ግን መድረሻችንን ሳናውቅ በጭፍን ጉዞ መቀጠል ይቻላል። ሆኖም ይደር ይዋል እንጂ፣ ነገና ተነገወዲያ ተለይቶን ወደ ነበረበት ሊመለስ ያለ ቁርበት እንግዳችንን በስለታም ሰይፍ ፈቅደን ካልተቆራረጥንና ተቃቅፈን እስከኖርን ድረስ ከርሱም ጋር ርኩሶች ስለሆንን የፋሲካን እራት ግብዣ ለመካፈል የሕጉ አጥር ወደ አዳራሹ አያስገባንም።

በብር የተገዛ ባርያ ቢኖር፤ ከተገረዘ በኋላ ከርሱ ይብላ፤ ባርያ በእስራኤል ብር፣ በደሙ-ወዙ ከዓለም የተዋጀ የራስ ገንዘብ፣ የሆነ ሰው ስለሆነ መስፈርቱ መገረዝ፣ ቆለፈቱን ማውለቅ ይቀረዋል፤ መገረዝም ከርኩሰት ቁርበት ውስጥ መሹለክ፣ (ኢሳ.52፡1-2) ከሙታን መነሣት፣ (ቆላ.2፡13) ከቁርበት ጨለማ ግርዶሽ ወደ እግዚአብሔር ፊት ብርሃን መውጣት፣ (ዘፍ.17፡1) ዳግም መወለድ፣ ደጋግመን እናመሳክር፡፡ በእስራኤል ብር የተገዛ ባርያ በዋናው እስራኤል በክርስቶስ ገንዘብ በደሙ-ወዙ የተዋጀ ባርያን ያመለክታል፡፡ ዛሬ ቤተ-ክርስቲያንን የሞሉ ብዙዎች በክርስቶስ ደሙ-ወዝ ይዋጁ እንጂ ፊፅሞ ይገረዝ የተባለውን መሥፈርት ያላሟሉ







ቆለፈታሞች ከመጋረጃ ውጭ ያሉ ናቸው ማለት አግባብነት ያለው ምስክርነት ነው፡፡ እነዚህ ታዲያ ሥጋውያን ቆለፈታሞች ስለሆኑ የተሸፋፈኑበት የቆለፈቱ መሸፋፈኛቸው እንዲገለጥ ከቶ አይወዱም ቃሉ ክርስቶስ መጋረጃውን ከላይ እስከ ታች ቀዶ እንዳያራቁታቸው እጅግ ይጠነቀቃሉ፤ የሚሸፋፍናቸውን አገልጋይ መርጠው ያቆማሉ፡፡ እንግዲህ ያልተገረዘ ማለትም ርኩስ ከውሾች፣ ከአስማተኞች፣ ከሴሰኞዎች፣ ከነፍሰ-ገዳዮች፣ ከጣዖት አምላኪዎች ጋር በውጪ ጨለማ ያሉ እንደሆነ የፍርዱ መጽሐፍ የሆነው (ራዕይ 22፡15) ወደ ውጪ ጨለማ ዳርጓቸዋል፡፡ መጻሕፍትም ተገለጡ፤ ፍርድም ሆነ (ዳን. 7፡9-10፤ ቁ. 10/ለ፤ ራዕይ 20፡ 11-15) ተብሎ የተጻፈው አሁን ይፈጸምባቸዋል፡፡ በሌላ በኩልም ፋሲካ ቅዱስ የሆነው የልጆች እንጀራ እንጂ ለውሻዎች የሚጣል ስላይደለ ሕጉ ያግደዋል፤ አያቀርበውም፤ (ማቴ. 15፡25-28፣ ማር.7፡24-30)፡፡

መፃተኛና ሙያተኛ ግን ከእርሱ አይብሉ፤ መፃተኛና ሙያተኛ እንደ እንግዳ ነው የሚቆጠሩት፤ የዕለት፣ የውሎ ሰው የሆነ የዕለት ጥቅሙን ቃርሞ ወደ መጣበት ተመላሽ በመሆኑ በእንግዳ ላይ የተደነገገው ሕግ በእርሱ ላይ ይፈፀምበታል፡፡ ሁለቱም ከእግዚአብሔር ሕዝብ ወገን ያልተወለዱ ናቸው፡፡ መፃተኛና ሙያተኛ ዛሬ ማነው? ለዛሬው በዕለታዊ ጉዳይ የተሰበሰቡ፣ አስመሳዮች፤ በዚህ መስተዋት ማንነታችንን እንፈትሽ፡፡ ቻላ እንበል፡፡

በአንድ ቤትም ይበላ፤ ፋሲካው በአንድ ቤት ይበላ ሲባል፣ መላ እስራኤልን የሚጠቀልል ቤት ሆኖ ስለሚታይ፣ አንዱ ቤት የሰው የፊደል አካል ሰውነት ሊገባበት የሚችለው ቁሳዊ የሆነ ቤት ነው ወይ? መላ እስራኤልስ እንዴት ሆኖ በአንድ ቤት ሊሰበሰብ ይችላል? ነገሩ ትንቢታዊ መሆኑ ነው፡፡ የመላ እስራኤል ተወካዮች በመሆን ሐዋርያት የመጨረሻን ፋሲካ በአንዱ የሰገነት ቤት በመብላት ፈፀሙት፡፡ አለዚያ አንዱ ቤት እንኳ እስራኤልንና ዓለሙን ሁሉ ማለት አሕዛብንና ልሳናትን ሁሉ አንድ

አድርጎ አጠቃልሎ ሰብሳቢ የያዕቆብ አምላክ ቤት የሆነውን ክርስቶስን (አብን) ((ኢሳ. 2፥2-4፣ ሚክ.3፥1-2፣ ራዕይ 21፥22)፥) በርቀት ሲያመለክት ነው፤ ክብር ለእርሱ ይሁን፣ ለዘላለሙ አሜን፡፡ ክርስቶስ ቁስ-አካል የሆነ ሰውነትን ሰብሳቢ ቤት ሳይሆን፣ መንፈሳዊውን ውስጣዊ ሰውነትን አጠቃልሎ ሰብሳቢ የያዕቆብ አምላክ ቤት፣ የሰማይ ደጅ ነው፤ "ይህ ሥፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው፣ እንጂ ሌላ አይደለም፣ ይህም የሰማይ ደጅ ነው… ዘፍ. 28፥10-19፣ ዮሐ.2፥19-21፣ ኢሳ .2፥2-፣ሚክ.4፥2-፣ ኢሳ.66፥18) በቤት በእግዚአብሔር ፊት የሚበላውን ቅዱስ፣ ብሩክ እንጀራ (ክርስቶስን) ከንባቡ ተነሥታችሁ አስመስላችሁ አትሥሩ፤ የሚመስለው ነገር በምድር ላይ ከቶ አይገኝምና እባካችሁ፣ እባካችሁ፡፡

ክርስቶስ ፋሲካ የሚበላበት ቤት ብቻ ሳይሆን ለፋሲካው ተፈላጊ ነገር ሁሉ ነው፡፡ ቤቱ ግን መግቢያ በሩ እጅግ ጠባብ ነው፣ ክርስቶስ ወደ ሕይወት የሚወስደው ቀጭኑ መንገድም፣ ጠባቡ በርም መሆኑ ተደጋግሟል፡፡ የእግዚአብሔርን እራት ለመብላት ከዚህ ቤት ውጭ ሌላ የለምና ነው እርሱ ቤት-ኤል የተባለው የእግዚአብሔር ቤት ነውና፤ (ዘፍ.28፥10-19፣ ዮሐ.2፥19-21)

ከሥጋው አንዳች ወደ ሜዳ አታውጡ፥- ይህ ማለት፤ ከፍ ብሎ እንደ ታየውም ሕጉ በሚያዘው መሠረት «… ሁልጊዜ አምላክህን እግዚአብሔርን መፍራት ትማር ዘንድ ስሙ እንዲጠራበት በመረጠው ሥፍራ በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት የእህልህንም የወይን ጠጅህንም የዘይትህንም አሥራት የላምህንና የበግህንም በኩራት ብላ፤ ዘዳ.14፥22-27» ከሚለው ትዕዛዝ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ይታያል፡፡ … ከዚህ ጋር

«ነገር ግን አምላካችሁ እግዚአብሔር ከነገዶቻችሁ ሁሉ ስሙን በዚያ ያኖር ዘንድ ወደዚያ ወደ መረጠው ሥፍራ ትመጣላችሁ፣ ማደሪያውንም ትሻላችሁ፡፡ ወደዚያም የሚቃጠለውን ሌላ መሥዋዕታችሁንም አሥራታችሁንም በእጃችሁም







ያነሣችሁትን ቁርባን፣ ስዕለታችሁንም በፈቃዳችሁ የምታቀርቡትን የላማችሁንና የበጋችሁንም በኩራት ውሰዱ፤ በዚያም በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት ብሉ፤ /በአምላካችሁ ፊት ሲል በብርሃን ብሉ ማለት ነው/ እጃችሁንም በምትዘረጉበት ነገር ሁሉ እናንተና ቤተ-ሰባችሁ ሁሉ ደስ ይበላችሁ፣ ዘዳ.12፡5-7፤»

ከሥጋው አንዳች ወደ ሜዳ አታውጡ ሲል፣ እራቱ የተቀደሰ ነገር ስለሆነ ከሚበላው ሰው በስተቀር ሌላው እንዳያውቀው በስውር ጨርሱት (ፈጽሙት) ማለቱ ግልፅ ነው፡፡ ሰው መንፈሳዊ ነገሮችን በተገቢው መንገድ ስለማያየው ነገር ግን በሥጋ ማለት በሰይጣን ዓይን ስለሚያይ ቅዱሱን ነገር አስመስሎ እንዳይቀርፀውና ወደ ሜዳ አውጥቶ እንዳያረክሰው ማለቱ እንደሆነ ይገባናል፤ እዚህ ላይ በስውር መደረግ ያለበት ፋሲካ ብቻ ሳይሆን፣ ወደ እግዚአብሔር ፊት የሚቀርብ ነገር በሙሉ ማለት ምፅዋቱም፣ ጸሎቱም፣ ፆሙም፣ አሥራቱም፣ በኩራቱም ሁሉ በስውር እንጂ በግልጽ እንዳይደረግ በግልጽ ማስጠንቀቂያ ተደንግጓል፡፡ (ማቴ.6፥1-7) ያ የእስራኤል ቤት በአዲስ ኪዳን የአማኙን ልቡና አመልካች ነው፤ የእስራኤል ቤት በአሸዋ ማለት በፊደል (ፍጥረታዊ) ላይ እስከ ተመሠረተ ድረስ በአዲስ ኪዳን አንፃር ሲታይ እርሱ ራሱ ሜዳዊ ውጫዊ ነበረና ለዚህኛው በሰውር ለሚበላው ቅዱስ እራት ቦታ ለቆ በታላቅ አወዳደቅ መውደቁ አልታወቅ ብሏል!! ፋሲካው የተበላበት የእስራኤል ቤት በአሸዋ ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ መጠን ሊመጣ ያለውን፣ የእውነት እውነተኛ የሆነውን የዐለቱ ቤት ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ ሲያመለክትና ተንሳፍፎ ሲያገለግል በአሸዋ መሠረት ላይ ቆይቶ አሁን በአዲስ ኪዳን በታላቅ አወዳደቅ ወድቆ ስለተወገደ በትንሣኤ ወደ ሰገነቱ ፎቅ ላይ ወጥቶ በከፍታ ላይ የሚፈሰክ መሆኑ ለምን አልታየ አለ? ቤት ማለት በርቀት መቅደስን ሲያመለክት ይህም ከጥንት ተያይዞ የመጣ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ነውና፡፡ ከመቅደሱ ውጭ የሚቀርብ ነገር ሁሉ በብርሃን ሳይሆን፣ በጨለማ የቀረበ ስለሆነ በውጪ ጨለማ ለዲያብሎስ እንጂ ለእግዚአብሔር ክብር የሚውል አይደለም፤ ምግቡም

የተበላው በእግዚአብሔር ፊት ባለመሆኑ በጨለማ ነው፡፡ ከጨለማው ማዕድ መካፈልም ከዲያብሎስ ማዕድ መካፈል ነው፣ መጽሐፍ የጨለማ ሥራ የሚለው ይህን ሜዳዊ ሥርዓትን ነው (ሮሜ13፡12)፡፡ መብራት የሆነው ክርስቶስም ከጧት እስከ ማታ ባለመቋረጥ የሚበራው ከመቅደሱ ውጭ ሜዳ ነው ወይስ ከመቅደስ ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት ነው? ዘፀ.27፡20-21፣ 1ሳሙ.3፡3) ክርስቶስ ብርሃን ነው ሲባል ፊደላዊ (ፍጥረታዊ) ብርሃን ስለሆነ ነው ወይስ መንፈሳዊ ብርሃን ስለሆነ ነው? ክርስቶስ የመቅደስ ውስጥ ብርሃን ነው እንጂ የውጭ ሜዳ ብርሃን አይደለም:: በውጪ ጨለማ የሚቀርበው ነገር ሁሉ ምስጋናው፣ ክብሩ ለሰይጣን ነው፣

እንግዲህ ሰውን ከሰይጣን እንዴት ለይተን እናስቀምጣለን? በእሳት ካልሆነ? ሰው በእሳት የሚቀመመው ለምንድን ነው? (ማር.9፡49) በእሳትና በመንፈስ ቅዱስ የሚጠመቀው ለምንድን ነው? ማቴ.3፡11-12፣ ከኢሳ.48፡10፣ ሚል.3፡3፡1-4) ጽድቅን ሲያይ የሚኮንን፣ ብርሃንን ሲያይ የሚታወር፣ ሕይወትን ሲያይ ሙት የሚሆን፣ ከእውነት ወደ ሐሰት የሚሸሽ፣ ከብርሃን ወደ ጨለማ የሚበርር፣ ከእግዚአብሔር በተቃራኒ ጎራ የሚሠለፍ ነገር ሰው ነው ወይስ ሰይጣን? ከነጭ ዙፋን ፊት ጥፋ ሳይሉት በንኖ የሚጠፋው ሰው ነው ወይ? አዳም ቃሉን ሰምቶ በንኖ መጥፋቱ የቀድሞ አዳም ማንን ሆኖ መለወጡን ይገልፃል? ቀዳሚ ወላጆቻችን የእግዚአብሔር ቃል ገና በርቀት ሲሰማ ወደ ጫካ የሸሹት ሰው ቢሆኑ ነው ወይስ ሰይጣን ቢሆኑ ነው? እኛስ አብዛኛዎቻችን እውነትንና የእግዚአብሔር ቃል ከመስማት እንደ አዳሞች ከእግዚአብሔር የምንሸሽ ነን ወይስ ወደ እግዚአብሔር የምንሸሽ? ወደ ብርሃን የምንሸሽ ነን ወይስ ወደ ጨለማ? ሰው፣ በውጫዊ አካሉ፣ በሰው ፊት እየታየ ይሸሻል ወይስ በሰው ፊት አለ እንዲባል ሃሌ ሉያ፣ ጌታ ይመስገን እያለ በውስጥ፣ በስውር እግዚአብሔር በሚያይበት ይሸሻል? በጌታ ፊት፣ ማለት በብርሃን





መቆም የማይችለውና የእግዚአብሔር ብርሃን ሲበራበት ሸሽቶ መጥፊያ የሚፈልግ ሁሉ ሰው ስለሆነ ነው ወይ?

ራስን መካብ ከፍ፣ ከፍ ማድረግ፣ ሁልጊዜም፣ በሁሉም የከፍታ ጥማት፣ ለከፍታ መሽቀዳደም፣ ከበሬታ ፍለጋ ራሱ ሰይጣንነት አይደለም ወይ? (ኢሳ.14፡12-15) ሰው ነን የምንለው ቃል ከየት መጣ? ሰው የሆነውና የሰውነት መለኪያ፣ መመዘኛ ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ነው (1ጢሞ.2፡5)፡፡ ቀጥሎም፣ መልካሙን ሥራ ለማድረግ በዲዛይኑ (በመቀረጫው) በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠሩ፣ በልጁ መልክ ምሳሌ የተቀረፁት እንጂ (ኤፌ.2፡10፣ ሮሜ 8፡29)፡፡

ስለዚህ በሰው ፊት ማለትም በሰይጣን ፊት ማለትም ነው፤ ሰይጣን የሚያየውና የሚሰማው በሰው በኩል ብቻ ነው በሰው ካልተጣመረ ሰይጣን ብቻውን ጆሮ የለውም፡፡ ሰው ሰማ፣ ሰው አየ ማለት ሰይጣን አየ፣ ሰይጣን ሰማ፣ ምሥጋናው ከሰው ነው ማለትም ከሰይጣን ነው፣ (ማቴ.6፡1-7፣ ቁ16-18)፡፡ ሰው የሚያየውና የሚሰማውም በሰይጣን ዓይንና በሰይጣን ጆሮ ነው፡፡ ያልተገረዘ ጆሮ የተባለውም፣ (ኤር.6፡10፣ ሐሥ.7፡51) ያልተገረዘ ጆሮ ነው ወይስ ተቆርጦ ያልተጣለ ሰይጣን ነው? ጌታ ኢየሱስ የፈወሳቸውን ሰዎች ሲያስጠነቅቅ ለማንም አትናገር እያለ የሚያሰናብተው በሰው በኩል እግዚአብሔር እንዳይሰማ ነው ወይስ ሰይጣን እንዳይሰማ ነው? ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ፣ ማለት የሚገልፀው ግራ እጅህ አይወቅ ነው ወይስ ግራ መንፈስህ አይወቅ ነው? ቀኝ ማን ቢሆን ግራ ማን መሆኑ ነው?

ከዚህም ሌላ፣ ሰይጣን በሰው ሆኖ እውነትን በአስመሳይ ነገር በመተካት የእግዚአብሔርን ሥራ ለማክሸፍ አንተ የምታደርገውን ሁሉ (ጸሎቱንም፣ ሆነ ፆሙን፣ ምፅዋቱንም ሆነ፣ ጥምቀቱን/ግዝረቱን ፋሲካውን በትክክል በማስመሰል ይሠራል ...፡፡ አሁን በመላ ምድራችን በተጨባጭ እየተደረገ

እንዳለው ሁሉ ሁሉንም ቅዱስ ሥራ አስመስሎ ይሠራል፤) ሥራችንን ይቀዳዋል፡ ስለዚህ ነው ፋሲካው በቤት በስውር ይደረግ የተባለው፡፡ ቅዱስ ነገር ሁልጊዜም የተሰወረ፣ የተሸፈነ ነውና፤ ከማን ተሸፈነ? ፎቶ ኮፒ ከሚያደርገው ነው የተሠወረው፡፡ በስውር የሚበላ ፋሲካ በግልጽ ከሚበላ ፋሲካ ቅድስናው ከፍ ያለ ነው፡፡ ጌታም ሥጋውንና ደሙን በውጭ ሜዳ አላቀረበም፡፡ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ የሚለውስ? ዕብ.13፡12 ውጫዊውን ሥርዓት፣ ሕግን ሁሉ ፈፃሚ እርሱ እየሆነ ይህን ሳይፈፅም ረግጦ ላለማለፍ ነው፡፡

ስለሆነ አስመስሎ እንዳይሠራውና ቅዱሱን ነገር እንዳያረክሰው ፋሲካው፡ በቤት ውስጥ በስውር በሚያየው ጌታ ፊት እንዲበላ ታዘዘ፡፡ ሰይጣን ብርሃንን ማየት አይችልምና /በብርሃን ይታወራል/፡ ይህም አስቀድሞ እንዳየን በእግዚአብሔር ፊት መብላት ከማዕዱ መካፈል፣ (ሉቃስ 22፡ 28-30፣ 2ሳሙ.9፡6-11) ማለት ነው፡፡ በአዲሱ ኪዳን ማለት ውስጥን እንጂ ውጭን ባልተገረዘ እስራኤል በመንፈስ እንጂ በፊደል፣ በውስጥ እንጂ በውጭ (በሰው ፊት) የሚደረግ ነገር ሁሉ ከነኪዳኑ ወደ ውጭ የተጣለ፣ ጊዜ ያለፈበት የጨለማ ሥራ ነው፤ (ሮሜ7፡6፣ 13፡12፣ 2ቆሮ.3፡6) ይመሳከሩ፤ ቁስ አካልም፣ ቁሳዊ ነገርም ወደ እግዚአብሔር ፊት ከቶ አይቀርብም፡፡ ልብ እናድርግ፣ ውጪውና የውጪው ዕድሞ የተተወ (ራዕይ 11፡2) የጨለማው ክልል ነው፡፡

አጥንትም አትስበሩበት፡- የፋሲከው እንስሳ አጥንቱ ቅሬተ-አካሉ ከመሆኑም በላይ መጪውን የክርስቶስ አጥንት የሚጋርድ ትንቢታዊ ስለሆነ አጥንቱ እንዳይሰበር ታዘዘ፡፡ ጌታ ኢየሱስ በሥጋው ፈጽሞ በመሞቱ አጥንቱ ከመሰበር ዳነ፤ (ዮሐ.19፡31-33) ለዘላለሙ አሜን፡፡ በሥጋቸው ያልሞቱ እነዚያ ሽፍቶች ቅሬተ አካል የሆነ አጥንታቸውንም አጡ፡፡





የአጥንት ልብስ ሥጋ ነው፡፡ ሥጋው ተበልቶ አጥንት እግዚአብሔር አልብሶት እስኪያስነሣው ድረስ ራቁቱን ሆኖ የጌታን ቀን ይጠባበቃል፤ (ሕዝ.37፡1-14) አጥንት ውስጣዊ መንፈሳዊ ዘላለማዊ፣ የማይሞትና የማይበሰብስ ቅሬተ-አካል ምሳሌ ሆኖ ይታያል፡፡ ዮሴፍ የእስራኤልን ልጆች ወንድሞቹን ጠርቶ እግዚአብሔር ሲያስባችሁ አጥንቴን ከዚህ አንሥታችሁ ከእናንተ ጋር ውሰዱ ሲል አማላቸው፣ (ዘፍ.50፡25) እነርሱም በመሐላ መሠረት ከግብፅ ሲወጡ የዮሴፍን አጥንት ተሸክመው ያወጡትን፣ (ዘፀ.13፡19) ከነዓን ድረስ ይዘው ገብተው በዮሴፍ ልጆች ድርሻ መሬት ቀበሩት፣ (ኢያሱ24፡32)፡፡ ነቢዩ ዔልሣዕ፣ ሥጋው በስብሶ ቢጠፋም አጥንቱ ዘላለማዊና ሕያው በመሆኑ (2ነገ.13፡20-21) አጥንቱን የነካ እሬሣ ሕያው ሆኖ በመነሣቱ ተረጋግጧል፡፡

በሳይንሱ ረገድም «አጥንት» የሥጋ ሕይወት የሆነው ደም ከእርሱ ስለሚፈልቅ አጥንት ሥጋን በመመገብ በሕይወት ያኖራል ማለት ነው፡፡ በፊደል (በፍጥረታዊ) (በቁስ) አጥንት መኖሩ መንፈስ አጥንት እንዳለው ያረጋግጣል፡፡ የአሕዛብ አጥንት፣ ለእስራኤል አጥንት ነጸብራቅ ሲሆን፣ የብሉይ ኪዳን እስራኤል አጥንት የሐሰት እውነቱ፣ የአዲስ ኪዳን እስራኤል አጥንት የእውነት እውነቱ መንፀባረቅ ነው፡፡ አጥንት የአጥንት ምሳሌ ነው፡፡ አጥንት ከውስጥ በስውር ሆኖ የሥጋ አካልን በውጭ ያንቀሳቅሳል፣ ሕይወትም ይሰጠዋል፡፡ ሥጋ ለራሱ ብስባሽና ርኩስ ነገር ሆኖ አጥንትን ይጋርዳል፡፡ አጥንት ብስባሽ በሆነው ነገር (በሥጋ) የተሸፈነ ማለት በሥጋ የተቀደሰ እንደሆነ ሁሉ እንዲሁ የሰውን የቅዱሱ መንፈስ መጋረጃ ከብር ክሩብ መሸፈኛው፣ ከዓይናችን የጋረደው ሸለፈቱ እርኩሱ መንፈስ ነው፡፡ ቅዱስ መንፈስ በውስጠኛው ውስጣችን የማይታየው የሕይወታችን ምንጭ የማይጠፋው የዘላለም አጥንታችን ነው፡፡

እንግዳ ሰው በመካከላችሁ ቢቀመጥ ለእግዚአብሔር ፋሲካ ሊያደርግ ቢወድድ አስቀድሞ ወንድ ሁሉ ይገረዝ፣

ፋሲካ የአንድነት ማሠሪያ ነው፤ የአንድነትና የመቀራረብ ፀር የሆነውን የመሀል ግድግዳ (ሽለፈትን) በማስወገድ ከዚያ በኋላ ይቅረብ ያድርግም፣ ይህም እንግዳ ሰው ፋሲካ ሊያደርግ የሚችለው በቁጥር 48 መሠረት አንደኛ፣ በእስራኤል መካከል ተቀማጭ (ነዋሪ) ሲሆን፣ ሁለተኛ ወንድን ሁሉ ሲገረዝ፣ ሦስተኛ በመቅረብ የእስራኤል አካል ሲሆን ነው፡፡ እዚህ -ጋ ፋሲካ በማቀራረብ በ-(ኤፌ.2፡11-22) ሁሉን በአካሉ አንድ ሊያደርግ ያለውን የክርስቶስን ፋሲካነት አመልካች ነበር፡፡ ፋሲካው ወደ ቤት ገብቶ እንጂ በውጭ የሚበላ አይደለም፡፡

በመሆኑም በመንፈስ እንጂ በፊደል፣ በውስጥ በስውር የሚደረግ እንጂ በውጭ በግልጽ የማይበላ ምግብ ስለሆነ ያልተገረዘ ሰው ከቁርበቱ የተነሣ ግዙፍ ከመሆኑም ርኩስ ስለሆነ በበጉ ደም የተቀደሰው ቅዱሱ የፋሲካው ቤት የሠርጉን ቤት ጠባቡን በር ክርስቶስን አመልካች እንደ መሆኑ መጠን ከቁርበቱ የተነሣ ግዙፉን ያልተገረዘና ክቡር የሆነ ሥጋዊ ሰው አያስገባውምና ራሱ በተጋድሎ ገብቶ የሚበላ ነውና (ማቴ.7፡13-14፣ ሉቃስ 13፡24) ጉልበት ይሰጠው፡፡ የጥልን መኻል ግድግዳ አፍርሶ መሥዋዕት አድርጎ ወደ እስራኤል መቅረብም አይችልም፡፡ ምክንያቱም ያልተገረዘ ከሆነ በእስራኤልና በእርሱ መካከል ከፍ ብሎ ያየነው የጥል ግድግዳ የተባለ ቆለፈት ገና ስላልተወገደ ማዶ ለማዶ ያደርጋቸዋል እንጂ፣ አያቀራርባቸውም፡፡ በሕጉ ላይ ከተገረዘ በኋላ ይቅረብ፣ የሚለው ተቀምጧልና፡፡ እንዲሁም ደግሞ ያልተገረዘ ርኩስ ከመሆኑም ምውት መሆኑንም (ኢሳ.52፡1-2፣ ቆላ.2፡13) ተመልክተናል፡፡ እንዲህ ሲባልም በግልፅ በሰው ፊት በመልክ እርኩስ፣ ሙት ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ፊት በስውር በመንፈስ እርኩስ፣ ሙት ስለሚባል ፊሲካው የሚበላውም በቅዱሱ እግዚአብሔር ፊት በብርሃን ስለሆነ እርኩሱ ወደ ብርሃን ለመቅረብ እንደ







አዳም ድፍረት የለውም፣ ያፍራል፡፡ በአዲስ ኪዳን ሰው በእውነት እውነተኛ በልብ ግዝረት በጥምቀት ከአሮጌ ማንነቱ ቁርበት እስካልተገፈፈ እስካላፈተለከ ድረስ በተደገመው ዓይነት በቀጭኑ መንገድ፣ በጠባቡ በር ወደ ብርሃን አያስገባውም፡፡ ብርሃን ማለትም እውነት፣ ሐቅ፣ ግልፅ በመሆን ከሚሸፋፈነው ነገር ነፃ የወጣ የተገፈፈ፣ የተራቆተ እውነተኛ ሰው ማለት ነው፡፡ በ(ኤፌ.2፡11-18፣ ቁ.18) የሚታየው በአሕዛብና በእስራኤል መካከል የነበረው የጥል ግድግዳ የሆነው ሸለፈት እስካሁን ድረስ ዘልቋል፡፡ በቤተ ሰብ ሁሉ መካከል፣ በኅብረተ ሰብ ሁሉ መካከል፣ በምዕመናን ሁሉ መካከል እንዳለ ነው፡፡

በብሉይ ኪዳን ዕንግዳ ሆነ፣ የገር ሰው ፋሲካ ሊያደርግ የሚፈልግ ወንድ ሁሉ ይገረዝ የሚለው በአዲስ ኪዳን ሲታይ፤ ዕንግዳም ሆነ የገር ሰው፣ ወንድ ሆነ ሴት አሮጌ ማንነት የሆነ ሥጋ ሰውነት በጥምቀት ያልተገፈፈ ቆላፍ አሮጌ ልብስ በሆነ ቁርበቱ ጨለማ ተሸፋፍኖ ያለ በመሆኑ ይህን ልብስ አዳምን አውለቆ አዲሱን የሠርግ ልብስ ክርስቶስን ማለት ብርሃንን፣ እውነትን፣ ግልፀትን ሳይለብስ ከንጉሡ ልጅ ሠርግ ማዕድ በጉን (ክርስቶስን) አይካፈልም፣ (ቆላ.3፡10፣ ገላ.2፡27፣ ማቴ.22፡13) እስራኤል ከግብፅ በመውጣት ሌሊት በጥላም ቢሆን ይህን ሥነ-ሥርዓት በትክክል ፈፀሙ፡፡ (ዘፀ12፡22፣ ሉቃስ 24፡49) በአስመሳዩ (በሐሰት እውነቱ) ግዝረት እንጂ በጌታ ፊት ከልባቸው ግብፃዊነት ያልተገረዙ ሁሉ ዛሬም እንዳለ ሁሉ በጉዞ ላይ አለቁ፡፡ እነዚያ በግልፅ አለቁ፤ እነዚህ ግን በስውር አለቁ?

‹‹ከናንተ አንድ ሰው እስኪነጋ ድረስ ከቤቱ ደጅ አይውጣ›› (ዘፀ.12፡22) ከናንተ አንድ ሰው እስኪነጋ ድረስ ከቤቱ ደጅ አይውጣ፣ ተብሎ የታዘዘውን እንዴት እንመለከታለን? ቤት ውስጡ ብርሃን ሲሆን፣ ደጅ ጨለማ ነው፤ ማለትም የሞት ጥላ፡፡ ስለዚህ እስኪነጋ ማለት ጨለማው በብርሃን እስኪተካ ማለት መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ ብርሃን እግዚአብሔርና የእግዚአብሔር መንግሥት ምሳሌ ሲሆን፣ ጨለማው ሰይጣንና የሰይጣን

መንግሥት ምሳሌ መሆኑን መረዳቱ ቀላል ነው፡፡ እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን እስኪል በእምነትና በተስፋ የመጠበቁ ውጤት እጅግ ከፍ ያለ ደስታና በረከት ያጎናፅፋል፡፡

እስኪነጋ፣ ከቤቱ ደጅ አይውጣ፣ እስኪነጋ፣ በጨለማ፣ ጨለማ፣ ጨለማ ሳይሆን፣ ለእስራኤል ፊደል ጨለማ ነው፤ እግዚአብሔርን የሚከልል፡፡ እስኪነጋ አትውጡ ማለት ምን ማለት ነው? እስኪነጋ ደጅ አትውጡ ማለት በጨለማ አትውጡ ማለት ነው፤ ጨፍኑ፣ ተኙ እንጂ ነው፡፡ ጨለማ፣ ምንድን ነው? ጨለማ፣ መጋረጃ፣ ግርዶሽ ነው፡፡ ንጋት (ብርሃን) እግዚአብሔር ሲሆን፣ በጨለማ አትውጡ ማለት በምን አትውጡ ማለት ይሆናል? በሞት (በሰይጣን) አትውጡ ነው፡በሌላ በኩል ጨለማ፣ የብርሃን የክብር ልብስ ነው፡፡ ብርሃን በሰው ላይ በተቆጣ ጊዜ ሁሉ ፊቱን ከሰው ለመሰወር ጨለማ ይጎናፀፋል፡፡ በሌላም ጨለማ የሞት መጋረጃ፣ ብርሃንን ከሰው የሚከልል የእግዚአብሔር ቁጣ በሰው ላይ ነው፡፡ ብርሃን የለም ማለት፣ ሕይወት የለም ማለት ነው፡፡ ብርሃን የለም፣ እስኪነጋ ድረስ ጨፍን፣ ሙት፣ ተኝተህ የትንሣኤን ብርሃን ጠብቅ ነው፡፡ አትክልቶችም እስኪነጋላቸው የፀሐይን ብርሃን ሲያዩ ነው እንጂ ከምድር ጨለማ እንደማይወጡ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ ለእስራኤል መጋረጃ፣ ጨለማ፣ ጨለማ ሳይሆን፣ ፊደል፣ መጋረጃ፣ ጨለማ ነው፤ እግዚአብሔርን አለማየት፡፡ የአሕዛብ መጋረጃ፣ ጨለማ ለእስራኤል መጋረጃ ጨለማ አይደለም፡፡ ንጋት ምንድን ነው? ንጋት፣ የመጋረጃ መወገድ ነው፡፡ ለእስራኤል ፀሐይ ሲወጣ ንጋት ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ሲወጣላቸው ንጋት ነው፡፡ ለሰው ሕይወት፣ ሕይወት ሳይሆን፣ ብርሃን ሕይወት እንደሆነ፣ በተቃራኒ ሞት፣ ሞት ሳይሆን፣ ፊደል ነው ሞት፡፡ መጽሐፍ እንደሚል፣ ባንቺ ላይ ግን እግዚአብሔር ይወጣል፣ ክብሩም ባንቺ ላይ ይታያል (ም. 60፡1-2)፡፡ ደግሞም ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር የዘላለም ብርሃንሽ፣ አምላክሽም ክብርሽ ይሆናል፣ ቁ. 19-20፣ ከራዕይ 21፡23-25፣ ም.22፡5) ይመሳከር፡፡







ማለትም የእስራኤል ሕይወት እግዚአብሔር እንጂ እንደ አሕዛብ ሕይወት፣ የእስራኤል ሕይወት አይደለም፡፡ የአሕዛብ ሕይወት አብርሃም እንዳደረገ፣ እስራኤል ከወንዝ ማዶ ቆርጣ የጣለችው ርኩሱ የተባለው የሥጋ ቁርበት ነው፡፡

ይህ ርኩሱ የሥጋ ቁርበት፣ ከግንዱ ተቆርጦ ከወንዝ ማዶ በርቀት በመውደቁ ቂጥኙት፣ ተመልሶ ለመላበስ በእስራኤል ላይ እንዳዘነ፣ እንዳደባና እንደ ተቆጣ የሚኖረው፣ እንዳጋጣሚ እስራኤል አዳልጧት፣ ‹እስኪነጋ ድረስ ከብርሃን በጨለማ› በምትወጣበት ጊዜ ሁሉ ይህን እርኩስ፣ ሞት የተባለውን የሥጋ ቁርበት መልሳ እንድትከናነበውና በዚህ ሥጋ ቁርበት ታሥራ በባርነት እንድትማቅቅ ለማድረግ እግዚአብሔር ተቆርጦ በውጭ ለተጣለው ቁርበትም ሆነ ብሎ የሆነ ሕይወት ሰጥቶት ጠብቋል፡፡ የዛሬው አዲሱ እስራኤልም እስኪነጋ፣ ብርሃን እስኪሰጥ በጨለማ ከወጣ ከወንዝ ማዶ (በጥምቀት) ቆርጠን የጣልነው የማይታየው እርኩሱ ሥጋ ቁርበት በባሰ ደረጃ ወዲያው በማንወጣበት ሁኔታ ይከናነበናል፡፡ ተመልሰን ወደ ባርነት ቀንበር ውስጥ ገባን፡፡ እንደ ገና ወንዝ፣ ባሕር መሻገር፣ እንደ ገና ሁለተኛ (በድጋሚ) መገረዝ (ኢያሱ 5፡2) መከራ ፍዳ ይሆንብናል፡፡ ብርሃን ስንልም፣ በሌላ ቃል የእስራኤል ብርሃን፣ መንፈስ ሲሆን፣ ጨለማዋ (መጋረጃዋ) ፊደል ነው፡፡ ብርሃን፣ ወደ ብርሃን (PHOTOTROPISM) ወደ ላይ ዕድገት እንደሆነ፣ እንዲሁ፣ ጨለማ፣ ወደ ጨለማ (GEOTROPISM) ወደ ታች ወደ ሲዖል ዕድገት ነው ተብሏል፡፡ ጨለማው፣ የተኮረነው፣ ውጭ ዓለምን በሚያጨልም በፊደላዊ (ፍጥረታዊ) ጨለማ ነው ወይስ ውስጥ ዓለምን ልቡናን በሚያጨልም ላይ ነው?

በአዲስ ኪዳን የተገኘው አዲሱ የእግዚአብሔር እስራኤል ይህን ፊለግ ወደ ብርሃን ያወጣዋል፤ ከፋሲካው (ሥርግ) ቤት እስኪነጋ እስኪበራ እስኪገለጥ፣ የእግዚአብሔር (ንጋት) እስኪታይ፣ የፊደል ጨለማው እስኪገፈፍ፣

*መጋረጃው እስኪቀደድ ድረስ ከቤቱ ሳይወጣ በእግዚአብሔር ቃል ሕግ ታሥሮ በውስጥ በስውር በፆም ጸሎት ዓይኑን ሳይገልጥ ተኝቶ ጨፍኖ መቆየትን ይማር ነው፡፡ እስኪነጋ ዝም ብሎ በድፍረት በጭፍን ወደ ደጅ አይውጣ፡፡ በጨለማ የሚወጣ፣ በጨለማ የሚወጣ ሳይሆን፣ ያለ እግዚአብሔር የሚወጣ ነው፡፡ እኔ ስመለከት፣ ክርስቲያን የተባለ ሁሉ ማለት ያስደፍራል፣ ግብር ይውጣ፣ ጸሊያለሁ፣ ጸልዩናል በሚል መመጻደቅ ብቻ በድቅድቅ ጨለማ የሚያደርጉትን የማያውቁትን ያደርጋሉ፣ የሚሆኑትን ያልተረዱትን በድፍረት ይሆናሉ፡፡ ጸልዩናል አሜን ይሉና ብቻ፣ ገና በድቅድቅ ጨለማ ለማስተማር፤ ሥርዓት ለመፈጸም የሚነሡትን ልማደኞች እንጂ ሌላ ከቶ አላየሁም፤ ለምን እዋሻለሁ? በዚህ ቃሊም ሰባት እጥፍ ተቃጥለው (ማገዶ ሆነው) እንዳይቃጥሉኝ እናንተ በብርሃን ያላችሁ ጸልዩልኝ፤ (የእነ ሲድራቅ ሚሳቅ አምላክ ከእጃቸው ይድነኝ)*

*የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ ቅዱስ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ቅዱስ እንደመሆኑ መጠንም የሰውን ቋንቋ ተላብሶ (ተጋርዶ) ሲተላለፍ መጥቷል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ በሰው ቋንቋ (በሐሰት እውነቱ) ግርዶሽ የእግዚአብሔርን መልእክት (የእውነት እውነቱን) እንደተጋረደ ሲያስተላልፍ ኖሯል፤ ሽፋኑ እውነት ሆኖ፡፡ አሁን እስኪነጋ ድረስ፣ ሲል የሰው ቋንቋ ለሰው ማብራሪያ የማይጠይቅ ግልፅ ሲሆን፣ የእግዚአብሔር መልእክት በተጨማሪ እዚህጋ ምንድን ነው? በውጭ/ በፊደል የሚመሸው በውስጥ በመንፈስ /በልቡና ለሚመሸው ጥላ ሲሆን፣ በውጭ/ በፊደል የሚነጋው፣ በውስጥ በመንፈስ /በልቡና ለሚነጋው ጥላ ነው፡፡ የውጩ /የፊደል (ፍጥረታዊ) ምድር፣ የውስጡ የመንፈስ ምድር መንፀባረቅ ነው፡፡ የውጩ ምድር ጨለማ የውስጡ ምድር ጨለማን የሚያሳስብ ነው፡፡ ውጭንና ውስጥን ለመለየት አገላብጦ ማየት ብቻ ነው፡፡ በውጭም፣ በውስጥም የሚመሸውና የሚነጋው ከራሱ ከምድር ነው፡፡ ምድር የሚመሸው፣ ራሱ ለብርሃን ጀርባውን አዙሮ*







*ከብርሃን ወደ ጨለማ ሲሸሸ ሄዶ ይገባል፤ እኛም እንደምናደርገው፡፡ የሚነጋውም ራሱ ፊቱን ወደ ብርሃን አዙሮ ሲመጣ መሆኑ በጥናት ታውቋል፡፡*

*‹‹ምድር›› ጨለማ የምትለብሰው ቀጥተኛ ከመሆን የእግዚአብሔር ምሳሌ ከሆነው ውኃ ልክ በላይ ተንጠራርታ በገዛ-ራሷ አባጣ ጎባጣ በመሆን ከሸለቆዋ ስምጠት፣ ከተራራዋ ምጥቀት፣ ከኮረብታዋ ዕብጠት፣ ከጠማማዋ ጉብጠት የጨለማን ጥልቀት ፈጥራ ነው፤ ይህን የምንመሰክርባት ከውስጠኛው ምድር ተነሥተን ነው፡፡ ውስጠኛው ምድር በትዕቢት ከእግዚአብሔር (ከውኃ) ልክ በላይ ስትንጠራራ አባጣ ጎባጣ ተራራ፣ ኮረብታ፣ ጠማማ፣ ጉርብጥብጥ መሆኗን ነቢዩ ኢሳይያስ ተመልክቶ በ(ም.40፡3-5) ባለው በውኃ ልክ ሜዳ በመሆን የእግዚአብሔር ክብር የሆነውን ብርሃን እንድታይ ጠይቋል፡፡*

*ውስጣዊው የልቡና ምድርም በገዛ-ራሱ ብርሃን ከሆነው እግዚአብሔር ሲሸሽ ነው በጨለማ ፍርድ ውስጥ የሚገባው፡፡ ወደ ሰው በውጭ/በፊደል (ፍጥረታዊ) እስኪነጋ በጨለማ ወደ ውጭ ለመውጣት እንደሚጠነቀቅ እንዲሁ ከዚህ ተምሮ በውስጥ/በመንፈስ እስኪነጋ ድረስ በጨለማ እንዳይወጣ፤ አገልግሎት እንዳይሰጥ፣ የጨለማን ሥራ እንዳያበረክት በዚህ አጋጣሚ ይጠንቀቅ፤ እምቢ ብሎ በትዕቢት አብጦ፣ የተባለውን ተራራ፣ ኮረብታ ከወጣ በትክክል የጨለማው መንግሥት አገልጋይ ነው፡፡ የውጪ/የፊደሉ ብርሃን የውስጡ/የመንፈሱ ብርሃን መንፀባረቅ ሆኖ ያስተምራል፡፡ በውጭ ለፍጥረታዊ ጨለማ ውጫዊው ፍጥረታዊው ብርሃን የሚያገለግል ሲሆን፣ በውስጥ ለመንፈሳዊው ጨለማ ውስጣዊው/መንፈሳዊ የፈጣሪ ብርሃን ያገለግላል፡፡ ፍጥረታዊው ብርሃን ውስጥን እንደማያበራ ሁሉ እንዲሁ መንፈሳዊው ውጭን አያበራም፡፡ የእግዚአብሔር መልእክት «ምድርም እስኪጠባ ድረስ፣ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪወጣ ድረስ ሰው በጨለማ ሥፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል*

እየጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ»፣ (2ጴጥ.1፡19/ለ) የሚል ነው፡፡ የልቡና ምድር ንጋት ኮከብ የፍጥረቱ ሳይሆን፣ ፈጣሪው የሆነው ቃል፣ (ክርስቶስ) ነው፤ (ራዕይ 22፡16)

የእስራኤል ንጋት (ብርሃን) ከውጭ ሳይሆን ከራሱ ከእስራኤል ነው እንደተጻፈ፣ «...ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል ከእስራኤልም በትር ይነሣል፣ (...ዘኁ. 24፡17) ቢደገም አይጎዳምና፣ ኢሳይያስ ሲናገርም ባንቺ ላይ ግን እግዚአብሔር ይወጣል፣ ክብሩም ባንቺ ላይ ይታያል ም. 60፡1-2፣ ቁ. 19-20፣ ከራዕይ 21፡23-25፣ ም.22፡5) ይመሰክር፡፡ ፍጥረታዊው ብርሃን የተሰጠው ለአሕዛብ ነው፤ (ዘዳ. 4፡19»፡፡ የቁስ/የፊደል (ፍጥረታዊ) ሞት፣ በውጪ ጨለማ መሆኑ፣ የውስጡ/የመንፈስ ሞት በውስጡ ጨለማ መሆኑን ሊመሰክር ነው፡፡ የውስጡ ሞት የሆነው ጨለማ እስኪነጋ ማለት፣ እስኪነጋ ማለት ሳይሆን እግዚአብሔር እስኪወጣ ድረስ ማለት ነው፡፡ ንጋት እግዚአብሔር እንጂ ንጋት አይደለም፡፡ (ዘፀ. 12፡29-37) እስራኤሎች እግዚአብሔር እስኪደርስ እንጂ እስኪነጋ አልጠበቁም ወጡ እንጂ፡፡ ምሽት የሞት ጥላ፣ የሰይጣን መንግሥት መንበረ ሲሆን፣ ንጋት፣ ብርሃን፣ ሕይወት የእግዚአብሔር መንግሥት አመልካች ነው፡፡ እስራኤሎች ብርሃን እስኪሆን በጨለማ ወጥተው ሞት እንዳያገኛቸው በበጉ ደም ጥበቃ ሥር ተጋርደው በውስጥ በስውር እንዲቆዩ ታዘዙ፡፡

ጨለማ ከግርዶሽ የተነሣ ነው፡፡ ግርዶሽ፣ ሰውን በኃጢአቱ ከጌታ ፊት የሚከድን በወገኖች ሁሉ ላይ የተጣለው መጋረጃ፣ በአሕዛብም ሁሉ ላይ የተዘረጋው መሸፈኛ፣ የእግዚአብሔር ቁጣ መሆኑ ነቢዩ ኢሳይያስ ባቀረበው ገለፃ አመልክቷል፡ (ኢሳ.25፡7፣ ም.50፡3) ይህም መጋረጃ በሌላ ቃል፣ አብራምን ጭምር እስከ ዘጠና ዘጠኝ ዓመት ዕድሜ ድረስ ወደ እግዚአብሔር ፊት እንዳይወጣ አድርጎ ያቆየው ሸለፈቱ ነው፡፡ ወደ እግዚአብሔር ፊት አለመውጣትም በውጪ ጨለማ መቆየትን ያመለክታል፡ (ማቴ8፡11-12) እግዚአብሔር የውስጥ የብርሃን ገዢ እንጂ







የውጭ የጨለማው ገዢ አይደለም (ሉቃስ 22፡53፣ ኤፌ.6፡12፣ የሐ.12፡ 31)፡፡ እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ በቃሉ በተቀደሰ ውስጥሀ በስውር እንጂ በውጭ ሜዳ አይደለም፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ የጨለማ ሥራ ያለው (ሮሜ 13፡12/ለ፣ ኤፌ.5፡11-13) የጨለማ ሥራ ማለት አሻግሮ የማይታይበት {TRANSPARENT} ያልሆነ ሜዳዊ ሥነ-ሥርዓት አገልግሎቶችን ከብሉይ ኪዳንና ከመሸጋገሪያ ዘመን ጋር የተከለሰ ሥርዓት ቋሚ አድርጎ መቀጠል ማለት ነው፡፡ ሐዋርያው የጨለማ ሥራ ሲል የእግዚአብሔር ሥራ ማለቱ ነው ወይስ የሰይጣን ሥራ ማለቱ ነው? (ማቴ.6፡1-18) ሜዳዊው ሥርዓት በግልፅ የተከለከለ ሆኖ እያለ፣ በሰው እንዲታይና እንዲሰማ ተደርጎ በድምፅ ማጉያ ሁሉ ጆሮ የሚሰነጥቀው ሥርዓት ዘላለም ባለህበት እርገጥ የሆነው ሜዳዊው አገልግሎትና ሥርዓት ሸር ጉዱ ሁሉ እግዚአብሔርን የሚያገለግል ነው ወይ? የሙሴ አገልግሎት «የሞት፣ የኩነኔ አገልግሎት» የተባለው ከምን የተነሣ ነው? ሜዳዊ፣ ፊደላዊ (ፍጥረታዊ)፣ በሰው ፊት (2ቆሮ.3፡7-9) ስለሆነ አይደለም ወይ? እስኪነጋ ደጅ አትውጣ በነቢዩ፣ « ሕዝቤ ሆይ ና ወደ ቤትህም ግባ፣ ደጅህንም ዝጋ፣ ቁጣው እስኪያልፍ ጥቂት ጊዜ ተሸሸግ» (ኢሳ.26፡20) የተባለውን ያስታውሰናል፡፡ ሞትና የሞት ጥላ በውጭ ነው፡፡ በፊደሉ ላይ፡፡

የታረደው በግ፣ ውስጡን (ቤቱን) ያበራል (ራዕይ 21፡23) በቤት ብርሃን የሆነው በጉ ነበር ወይስ ደስታው እልልታው ነበር? የደስታ ብርሃን ይሻላል ወይስ የመብራት ብርሃን ይሻላል? ከውስጡ ብርሃን የተነሣም ውጪ ይጨልማል፣ የውጪ ጨለማ የውስጡ ብርሃን የክብር ክፋብ ነው፡፡ ቃየን የተቃጠለው ፊት የጨለመው፣ የአቤል ፊት ስለበራ ተመቃኝቶ አኩርፎ እንደነበረ እንዲሁ ዲያብሎስ የጨለመው እግዚአብሔር ብርሃን ስለሆነ ያለ እሳት በምቀኝነት ነድዶ፣ ተናድዶ በራሱ ተቃጥሎ፣ አርሮ ከስሎ ነው ማለት ልክ አይደል? (ሕዝ. 28፡18) ሰውም የሚቃጠለው ከውጭ እሳት ተለኩሶበት ነው ወይስ በራሱ ነው? ሰውም ሰውም

የሚቃጠለውና የሚነድደው የሚያርረውና ሊቃጠልም ያለው ከቶ እሳት ተለኩሶበት ሳይሆን፣ ያለ እሳት በራሱ ነው፤ እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ ነውና አሜን፡፡

የግብፁ ሌሊት ውጪ የጨለመው፣ ጨለማው ከውስጥ ወደ ውጭ ስለተጣለ አዝኖ ነው፤ ተበሳጭቶ፡፡ አንተም፣ ከኅብረተ-ሰቡ፣ ከኅበረቱ ወይም ቤቴ ነው ብለህ ከምትኖርበት ውጭ ብትደረግ ቃየንን ትሆናለህ፤ (ትከሰሳለህ)፣ ግብፅን እንዳጨለመ፣ ለእስራኤል ብርሃን የሆነው በጉ ክርስቶስ ለሰው ሥራውን የተሰወረውን ሁሉ ገልጦ የራሱን የመዝገቡን ያኅናዕፈዋልና በውጭ ግብፅን ጨለማ/ውርደትን ሲያኅናፅፍ በቤት እስራኤልን ብርሃንን ክብርን አለበሰ፡፡ የታረደው በግ ለእስራኤል በዚህ በኩል ሕይወትና ብርሃን በዚያ በኩል ለግብፃውያን ጨለማና ሞት ሆኖ ተገልብጦ ይታያቸዋልና እንደ ራሳቸው እይታ ሆነባቸው፡፡

ሐሰተኛ ትርጉም ለሚሰጡ ሁሉ እንዲሁ ይሆንባቸዋል፤ (ዘፀ.14፡19-20)፡፡ ጋር ይመሳከር፣ ዛሬም ለሚጠፉት እንዲሁ ብርሃን ጨለማ፣ ሕይወት ሞት፣ እውነት ሐሰት፣ ቀን ሌሊት በመሆን ተቃራኒ ፍቺ ይሰጣቸዋል፣ (ኢሳ.5፡20፣ ዮሐ.3፡19)፡፡ ያንኑ ሥራቸውን ይወርሳሉ፡፡ የበጉ (የክርስቶስ) ውጪ ሞት ውስጡ ሕይወት፣ ማለት ውጪ ፊደሉ ሞት፣ ውስጡ መንፈሱ ሕይወት ነው፡፡ ከበጉ ውጫዊነት ወደ ውስጥ እንሸሽ፡፡ በበጉ፣ ወደ በጉ፤ ከመሰል እውነቱ ወደ እውነት እውነቱ፡፡ ለምሳሌ፣ ... ያለህን ሁሉ ሽጥና ለድኖች ሰጥተህ ናና ተከተለኝ፣ (ማር. 10፡21)

ደግሞም ማንም ደፍሮ ወደ ውስጡ ብርሃን እንዳይገባ የውጪ ጨለማ (አጅሬ) የውስጡ ብርሃን የክብር መጋረጃ ዘብ መሆኑን እናስታውሳለን፤ አያንቀሳቅሰም በነበሩበት ያሥራል፡፡ ውስጡ የበራውን ያህል ውጪ ይጨልማል፤ የነቢያትና የሐዋርያት ውስጣዊ ብርሃን ኃይል ውጫቸውን ለመከራ፣ ለኀዘን፣ ለሥቃይ ለሞት ይዳርጋቸው ነበር፡፡ ለዚህ የብርሃኑ







መጠን ኃይል ወሳኝ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን፣ እህሉም በጉም፣ ወይኑም፣ ቤቱም በውጭ የነበረው በአዲስ ኪዳን ሁሉም በክርስቶስ ተጠቅልሎ ከውጭ ሜዳ ወደ እኔ፣ አንተ/ች ውስጥ ጉዋዳ መግባቱ የማይዘነጋ ጉዳይ ነው፡፡ ክርስቶስ ሁሉ በእርሱ የሆነ ሁሉ ነውና ክርስቶስ ውስጣችን መቅደስ ገብቷልና ከእርሱ ጋር በእርሱ ያልገባ በውጪ ጨለማ ቀረ አይደል? በሩም ተዘጋ በምን ተዘጋ? (ማቴ. 25፡10-11)፡፡ ይህ ሁሉ ሕዝብ ሁልጊዜ ሲያንኳኳ ያለው በምን ስለተዘጋበት የቱጋ ቆሞ ነው? አሁን በባሪያዎቹ በኩል በርህን ሲያንኳኳ አልሰማህምና ስለዘጋህ ተዘጋህ ይህ ክርስቶስ ብርሃንም መከፈቻም ሆኖ ወዳለም መምጣቱ ሁለት ጎን ስለፈጠረ ነው፤ ይከፍታል፣ ይዘጋል፡፡ በመከፈት ይዘጋል እንጂ በመዝጋት አይደለም፡፡ ክርስቶስ ሟቹን ማዳኑ ለገዳዩ ማንም ሳይነካው መሞቻው ሆነ፡፡ እርሱ በማዳኑ ይገድላል እንጂ በመግደሉ አይገድልም፡፡ ማዳኑ ነው መግደሉ፡፡ የዕውሩን ዓይን መከፈቱ ለሚያዩት በራሱ መታወሪያ የሆነ የጽድቅ ፍርድ ነው፤ ሁሉ በክርስቶስ መገልበጡን ለማስታወስ ነው የጻፈኩት፡፡ ወደ ግብፅ፣ ለዓለም መብራት የሆነው እስራኤል ከውጭ ወደ ቤት ሲገባ ጨለማ ግብፅን፣ (ዓለምን ዋጠው፡፡) ዕዳውን ማለት የኃጢአትን ዋጋ ሞት በጉን ከፍለው ወደ ሕይወት ተሻገሩ፤ ባለዕዳው ሳይከፍሉ አይለቅምና፡፡ ከሞት መሸፈኛውም በጉ ሲሆን፤ የሕይወት መብሉም በጉ መሆኑን እናስታውሳለን፡፡ በውጭም በውስጥም በጉ ከብቧቸዋል፡፡ በውጭ ሞት (በውጭ ላለው) በውስጥ ሕይወት በውስጥ ላለው፡፡ እስራኤል በበጉ በመሸፈንና በጉን በመብላት በሕይወት ኖሩ፡ «ምግብና ልብስ ከኖረን ግን እርሱ ይበቃናል፣ 1ጢሞ 6፡8».

ያልተገረዘ ሁሉ ግን ከእርሱ አይብላ፣ ያልተገረዘ ሲባል ምን ማለት ነው? ያልተገረዘ ፡ 1/ ርኩስ ነው፣ 2/ ምውት ነው፣ (ቆላ.2፡13፣ ኢሳ.52፡1-2) 3/ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ያፈረሰ (ዘፍ.17፡14) ስለሆነ ከወገኑ /ተለይቶ



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፣
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፣ ኢሳ.34፡16

እንዲጠፋ የተፈረደበት ስለሆነ ከጌታ፣ ከንጉሡ ማዕድ ሊካፈል ወደ ብርሃን ሊወጣ አይችልም፤ ወደ ውጪ ጨለማ አውጡት ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ (ማቴ.22፡13)፤ ክርስቶስን ለብሶ ውስጡ ያልገባ ሁሉ በውጪ ጨለማ ቀርቷል፡፡ ከዚህም ሌላ፣ 4/ በእርሱና በእስራኤል መካከል ያለው የጥል ግድግዳ (ሽለፊት) «ይቅረብ፣ ያድርግም» የሚለውን የ-(ዘፀ፡12፡48)ን መመሪያ ሊፈፅም አያስችለውም፣ (ኤፌ.2፡11-15) 5/ በእግዚአብሔርና በእርሱ መካከል ያለው ያለመታዘዝ በደል መጋረጃ፣ (ኢሳ.59፡1-2) የአምላኩን ፊት ከእርሱ ሰውሮታል፡፡

ፋሲካው ትንቢታዊ እንደመሆኑ መጠን፣ ወደ ሚበላበት ቅዱሱ የእግዚአብሔር ቤት ጠባቡ በር (ክርስቶስ) አያስገባውም፣ በነገራችን ቤቱም፣ በሩም መብል መጠጡም፣ ጋባዥ ንጉሥም የታረደው በግም፣ ወይኑም ሁሉ በእርሱ የሆነው ክርስቶስ መሆኑን፣ (ዮሐ.፣ 10፡9፣ 1፡3) ቀደም ሲል አይተናል፡፡ እርሱ ክርስቶስ እራሱ የሥጋን ሰውነት አውልቆ የገባበት ቤት ስለሆነ ሰው የሆነ ማንም የሥጋን ሰውነት ሳያወልቅ ከነአሮጌው ማንነት ጋር ወደዚህ ወዳጌጠ፣ ወደ ተነጠፈና ወደ ተሰናዳ የዘላለም ደስታ ወደ ሆነው መንግሥተ-ሰማያት (ሠርግ ቤት) ሊገባና ከንጉሡ እግዚአብሔር ማዕድ ሊካፈል ከቶ አይችልም፡፡ እንዳይገባና እንዳይካፈል የሚከለክል ምንም ሳይኖር ሰውዬውን የራሱ ማንነት፣ ለቁርበቱ ያለው ፍቅርና መሳሳት አያስገባውም፡፡ መግባትም፣ ከንጉሡ ማዕድ መካፈልም አሁን የተፈፀመ ትንቢት ነው እንጂ ገና ትንቢት ፈፃሚ ሌላ አይመጣም፤ ክርስቶስ ሁሉን ፈጽሞ ከሙታን ተነሥቷልና ትንቢቱ ሁሉ ተፈጽሟል፣ ቀጠሮ የለም ፡፡

ይህን የፋሲካ እራት ማንም በገዛ እጁ ከምድር በሆነ ነገር አስመስሎ ሊሠራ ከቶ አይችልም፣ ይህን አስመስሎ የሚሠራ የተረገመ ይሁን አሜን፡፡ ምክንያቱም ይህ እንጀራ በእግዚአብሔር አብ ፈቃድና ዕቅድ ከሰማይ ወረደ እንጂ ከሰው ልጅ ማንም አስቦ፣ አቅዶ፣ ፈልጎና ጠይቆ





ከሰማይ ያወረደው ነገር አይደለም፤ ምስያም፣ ምሳሌም በምድር ላይ ጨርሶ የሌለ ነገር ሲሆን፣ አስመሳዮች ምክንያት አግኝተው ከመጽሐፉ ንባብ ተነሥተው፣ በራሳቸው ቋንቋ ተርጉመውና አብ እግዚአብሔር ከሰማይ ባወረደው እንጀራ ፋንታ ከምድር የሆነውን የእጃቸውን ሥራ የሐሰት እውነተኛ የሆነ ዳቦ በመጽሐፉ ቃል ሸፍነው ሠርተውና ቆራርሰው የሚያቀርቡት አስመሳይ ሥራ ከመሆኑም ከሰማይ የወረደም አይደለም፣ ምሳሌም የለውም፣ ከቶም መታሰቢያ አይደለም፤ እውነተኛ መሠረትም የለውም፤ እጅግ ያረጀም ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## የሰገነቱ እራት

### የንጉሡ ልጅ ሠርግ፣

/ለበጉ ሠርግ እራት የተጠሩ ብፁዓን ናቸው ብለህ ጻፍ፣ /ራዕይ 19፡9/

የሰገነቱ ራት፣ በፎቅ ከፍታ ላይ የተደገሠ ራት መሆኑ ነው፡፡ ንጉሡ እግዚአብሔር ሲሆን፣ የንጉሡ ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ እንደ ሆነ በታሪክ እናውቃለን፡፡ የንጉሡ ልጅ ሠርግም የበጉ የክርስቶስ ሠርግ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ ይህ ሠርግ በምድር ላይ የሚደረግ ገሃዳዊ፣ ፊደላዊ ሠርግ ነው ወይ? አይደለም፣ (ማቴ.22፡1-13፣ ሉቃስ 14፡16-24) እንደሚያመለክተው ሠርጉ፣ የመንግሥተ ሰማያት ሠርግ እንደ ሆነ ያመለክታል፡፡ በሉቃስ 14፡15 ላይ «በእግዚአብሔር መንግሥት እንጀራ የሚበላ ብፁዕ ነው» ሲል፣ (ራዕይ19፡9) በተመሳሳይ «ለበጉ ሠርግ ራት የተጠሩ ብፁዓን ናቸው» ይላል፡፡ ለዚህ ሠርግ ራት ንጉሡ እግዚአብሔር ባሮቹን፣ እንደ እነኢሳይያስ የመሳሰሉትን (ኢሳ.55፡1-2፣ ም.25፡6) ልኮ ጥሪ ማድረጉ፣ (ከማቴ.22፡1-13፣ እና ሉቃስ 14፡15-24) ሲስተያይ ግልፅ ሆኖ ይታያል፡፡ ሠርጉ የተዘጋጀበት ሥፍራ፣ ምሳሌ 9፣ በከተማዎች ከፍተኛ ሥፍራ ሲል፣ ኢሳ. 25፤6 በተራራ ላይ የሚለው የአዲስ ኪዳኑን ፅዮን (በኢየሩሳሌም) ከተማ ከፍታ ሰገነት ላይ የቀረበውን በማመልከት ይደመደማል፡፡

ለዚህ ሠርግ ድግስ የተዘጋጀው ነገር ምንድን ነው? ማቴዎስ በተለይ የኢሳይያስን ቃል አንጠልጥሎ እንደሚገልፀው ኮርማዎችና የሰቡ ከብቶች ታርደዋል፡፡ ሉቃስ፣ ኢሳይያስና ንጉሡ ሰሎሞን በጥቂት ልዩነት እንጀራ፣ ወይን ጠጅ፣ ወተት፣ ሥጋ፣ በረከት ፍሪዳ መዘጋጀቱን ይገልፃሉ፡፡ እነዚህን ምግቦች ኢሳይያስ የሰቡ ነገሮች ከሚለው ጋር ማቴዎስ የሰቡ ከብቶች ሲል ይደመድማል፡፡ ጠቅለል አድርገን ለመመልከት፣ ለንጉሡ





ልጅ ሠርግ የታረደው፣ የተዘጋጀው ማነው? ምንድን ነው? ተብሎ ቢጠየቅ፣ በግ፣ የታረደው በግ ልጁ ራሱ ሠርገኛው ክርስቶስ መሆኑን ልብ እንበል፡፡ ለውጭም ለውስጥ፣ በፊደልም በመንፈስ፣ ለሰማይም ለምድር፣ ለእንስሳም ለአራዊት ሁሉ እንጀራም፣ ወይንም፣ ወተትም፣ ውኃ፣ ማርም፣ አትክልትም፣ ጥራጥሬም ፍራፍሬ ወዘተ... ሁሉ በክርስቶስ፣ ከክርስቶስ (በእግዚአብሔር ቃል) ሁን!! ሲባል ሆነ፡፡ ሁሉ በእርሱ፣ ከእርሱ የሆነ ነው፤ በሁሉም ነገር ውስጥ ቃሉ አለበት፤ ለዘላለሙ አሜን፡፡

በሰው ሐሳብ ተመርተን፣ በምድረ-ዓለም ላይ በተለመደው ሥርዓት የሚበላና የሚጠጣው ነገር በአፍ ወደ ሆድ የሚሆን ካልሆነ በቀር በጆሮ ለልብ (ለመንፈስ) የሚሆን መንፈሳዊ ምግብ (ቃሉን) አልበላም፣ አልጠጣም፣ ነው ወይ የምንለው?? «ቃልህ ተገኝቷል እኔም በልቸዋለሁ» ነቢዩ ኤርምያስ፡፡ «አፌንም ከፈትሁ፣ መጽሐፉንም አጎረሰኝ» ነቢዩ ሕዝቅኤል፡፡ «ከመልአኩ እጅ ታናሺቱን መጽሐፍ ወስጄ በላሁ...»፤ ሐዋርያው ዮሐንስ፡፡ ... እነሆ ድግሴን አዘጋጀሁ፣ ኮርማዎቼና የሰቡ ከብቶች ታርደዋል፣ ሁሉም ተዘጋጅቷል... ማቴዎስ የሚለው፣ ሀ. ፊደላዊ (ፍጥረታዊ) ድግስ ነው ወይስ መንፈሳዊ? ለ. እንጀራ፣ ወይን ጠጅ፣ ኮርማዎች፣ ፍሪዳዎች፣ የሰቡ ከብቶች፣ ገሃዳዊ፣ ፊደላዊ (ፍጥረታዊ) ኮርማዎች፣ ፊደላዊ (ፍጥረታዊ) ከብቶች፣ በፊደል በግልፅ የሰቡ ከብቶች፣ በፊደል (ፍጥረታዊ) ታርደው ነው ወይስ በመንፈስ የሰቡ ከብቶች በመንፈስ ታርደው ነው? ከብቶች ናቸው ወይስ እንደ ከብት የታረዱ የእግዚአብሔር ባሮች ናቸው? ሐ. ከብቶቹ የሰቡት ምን በልተው ነው? ጌታ ኢየሱስ ከኔ ጋር ከማዕዴ ትበሉና ትጠጡ ዘንድ አባቴ እኔን እንደ ሾመኝ፣ መጠን ለመንግሥት እሾማችኋለሁ የሚለው የሚበላውና የሚጠጣው ምኑ ሆኖ ነው? የእስራኤል ልጆች ለአርባ ዓመት ሙሉ በምድረ-በዳ የበሉት እንጀራ (ዘፀ.16፡14,15፣ ኢያሱ.5፡10-12፣ ነህ.9፡15) ምንድን ነው? ቁሳዊ እንጀራ ተጨባጭ ነበር ወይ? የሰማይ እንጀራ፣ የመላእክት ምግብ

አይደለም ወይ? (መዝ.78፡22-24) ይህ ሁሉ ተጠቃልሎ ሁሉም አንድ ነገር እርሱም ክርስቶስ አይደለምን? ታሪክ በግልፅ እንደሚያስረዳው እግዚአብሔር ለዓለሙ ሁሉ ሕይወት መብል አድርጎ ያቀረበው እንጀራ፣ ሥጋ፣ የታረደው በግ ክርስቶስ እና በአባሪነት የቀረቡ ሰማዕታት አገልጋዮቹ ሆነው ይታያሉ፡፡

ነቢዩ ኤልያስ ዉትና ማታ ቁራ እያመጣለት የበላው እንጀራና ሥጋ (1ነገ.17፡2-6) ከየት ነበር? ኤልያስ በአንድ ጊዜ በበላው ምግብ ኃይል አርባ ቀንና አርባ ሌሊት እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ የተጓዘበት ምድራዊ፣ ቁሳዊ ምግብ ነበር ወይ? ለዚህ ማመሳከርያ (ዘዳ.8፡2-3፣ ማቴ.4፡1-4፣ ሕዝ.2፡8-10. 3፡1-3፣ 1ጢሞ.4፡6፣ ራዕይ 10፡8-10፣ ኤር.15፡15፣ 1ነገ.19፡5-8) በርጋታ እንመልከት፡፡ ደግሞም ክርስቶስ ቃል ነው፤ ቃሉም እግዚአብሔር መሆኑ በግልጽ የተጻፈ ነው፡፡ ነቢዩ ኤርምያስ ቃሉን በላ፤ ወንጌላዊው ጢሞቴዎስም በቃሉ እንዲመገብ ታዘዘ፤ ነቢዩ ሕዝቅኤልና ወንጌላዊው ዮሐንስ መጽሐፍ ቀርቦላቸው በሉ ሙሴም ሲናገር ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ እንደማይኖር አመለከተ፡፡ ቃሉም ይሠዋና ይበላ ዘንድ ሥጋ ሆኖ የተገለጠው ክርስቶስ (እግዚአብሔር) ነው፤ ዮሐ.1፡14፡1፡1

ስለዚህ ምድረ-ዓለማዊው ፍጥረት ሁሉ እየተመገበ የሚኖርበት ነገር ሁሉ፣ በእርሱ በሆነው በቃሉ የሆነ መሆኑን የፍጥረት ታሪክ ግልጽ አድርጓል፡፡ ቃሉ አትክልት ሁሉ ሆነ፣ እህል ዓይነት ሁሉ በመሆን እንጀራና ዳቦ ሆነ፤ ቃሉ እንስሳ፣ ዓሣና ውኃ፣ ወተት፣ ማር፣ ወይን ሥጋ በመሆን በውጭ ውጫዊውን ሕይወት በጥላ የሚያኖር መሆኑ ሊካድ የማይቻል ሐቅ ከሆነ አሁን ደግሞ ቃሉ እንጀራ፣ ሥጋ፣ ወተት፣ ወይን ጠጅ፣ ሙሉ በረከት ሆኖ (ኢሳ.55፡1-3) ለውስጣዊ ዘላለማዊ ሕይወት በውስጥ፣ በስውር መቅረቡ እንዴት ይካዳል?



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፤ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፤ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16



ለንጉሡ ልጅ ሠርግ ድግሥ የታረዱ ኮርማዎችና የሰቡ ከብቶች ሲሆኑ፣ ሠንጋዎች ሳይጠቀሱና ሳይታረዱ ተዘንግተው ለምን ኮርማዎች ብቻ ታረዱ? ሠንጋ፣ ዘር መዝራት የማይችል በሰይጣን (የተኮላሸ) ከመሆኑም፣ በተጻፈው ሕግ መሠረት በእግዚአብሔር መንግሥት ሥፍራ የሌለው ነው፤ (ዘዳ.23፡1)፡፡ ሠንጋ ማለት ዘር እንዳይዘራ በሰይጣናዊ ድርጊት ተኮላሽቶ የመከነ ወንጌላዊን ያመለክታል፡፡ (ዘር ዘሪ ማነው ታዲያ ወንጌላዊ አይደል?) በእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎ ሠንጋ ሥፍራ የሌለው ሆነ፡፡ ኮርማዎች ግን የእግዚአብሔርን መንግሥት ዘር (ወንጌልን) ሲዘሩ ለንጉሡ ልጅ ሠርግ (ሠርጋቸው) ታርደው የተሠውና ድግስና ደጋሾች ሠርገኞችም ናቸው፡፡

ለፋሲካው የተሠውና የታረዱ ኮርማዎችና የሰቡ ከብቶች የጌታን መከራ (መሥዋዕትነት) እንደ ተካፈሉ ሁሉ የሠርጉ (የደስታው) ተካፋዮች ናቸው፡፡ ከእነዚህም በስም የታወቁ ማቴያስንና ጳውሎስን ጨምሮ አሥራ ሶስቱ በተራቸው ለመንፈሰ-ሙታን የሕይወት እንጀራ እና የሕይወት ውኃ በመሆን ለዓለም የቀረቡ ኮርማዎችና የሰቡ ከብቶች የጌታ አካል ክፋዮች ብልቶቹ የአዲሱ ዓለም ነገሥታትና ካህናት የሆኑ ናቸው፡፡ በፊደል የሰቡ ናቸው ወይስ በመንፈስ የሰቡ ናቸው? ለተባለው፣ እግዚአብሔር በፊደል (ፍጥረታዊ)(በግልፅ) የሰባውን ከብት ያርዳል ወይስ በስውር በመንፈስ የሰባውን ያርዳል? በፊደል (ፍጥረታዊ)ስለታም ሰይፍ ያርዳል ወይስ በመንፈስ ስለታም ሰይፍ ያርዳል? ፋሲካችን ክርስቶስ የታረደው በግልፅ፣ በፊደል ስለት ታርዶልናል ወይስ በስውር በመንፈስ ሰይፍ ታርዷል? ክርስቶስ አንድ የነበረው አሁን አሥራ አንድ ቦታ ተቆራረሰና ተባዝቶ ከራሱ ጋር በእስራኤል ነገዶች ቁጥር አሥራ ሁለት እየሆነ ቀጠለ፡፡ (ይኸው የጌታ ሥጋ የደረሰበት፣ የመጀመሪያው ዙር፡፡ እየተባዛም ቀጠለ፣ ብዙ ተባዙ የተባለው በአንደኛው አዳም የከሸፈው አሁን በሁለተኛው አዳም ይኸው፤ እየተፈፀመ ቀጠለ፡፡ በይኸው ሥርዐት ነበርና፡፡ ብዙ



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፤ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፤ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

ተባሉ የተባለው፣ ከአፉ የወጣ ቃሉ የተላከበትን ሳይፈጽም ከንቱ ሆኖ ከቶ አይቀርምና፡፡ ጌታ፣ አንዱን ራሱን አከፋፍሎ አንዱ የጥፋት ልጅ በተጻፈው መሠረት ተቆርጦ ሲቀነስ አሥራ አንድ መሆኑ አካለ ጎዶሎ ቢያደርገውም፣ በጌታ ስም ተወግሮ የሞተው ማትያስ ተተካ፣ ጳውሎስም ተጨመረ፣ ሌሎችም፡፡ ጎዶሎ ሆኖም ወደ ሕይወት መግባት ይሻላልና (ዐይንህ ብታሰናክልህ አውልቅ፣ እጅህ፣ እግርህ ብታሰናክልህ ቁረጥ ተብሏልና) ጌታ አንዱን ብልት በቃሉ ስለት ቆርጦ ጣለው፡፡ ይህ የሕይወት እንጀራ ሕይወት ካልሆነን ሞት መሆኑ አይቀሬ ነው፤ በቀኝ ለሚመጡ ሕይወት፣ በግራ ለሚመጡ ሞት ነው፡፡ እግዘአብሔር ሲያለማን ደስ እንደሚለው እንዲሁ ሲያጠፋን ደስ ይለዋል፤ (ዘዳ.28፥63) የሚያጠፋን እግዚአብሔር ሳይሆን ጽድቁ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ጽድቅ ለአብዛኛው ሰው መጥፊያ ይሆናል፤ ለመዳኛ (ለደህንነት) የቀረበለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ለሰው ኩነኔ፣ ሕይወቱ መሞቻው (መጥፊያው) ሆኖ መገኘቱ ገርሞኝ ነው፡፡

ግልፅ ለማድረግ፣ ሠርግ ደስታ ሲሆን፣ መታረድ ሞት፣ ለቅሶ ነው፡፡ ልጁ ሆኖ ሠርገኛ ከሆነ፣ እንዴት ደግሞ የታረደ በግ (ኮርማ) ሆኖ ይበላል? እርሱ ተበልቶ ከጠፋ ከየት መጥቶ ሠርገኛ ይሆናል? ቀደም ሲል እንደተጠቀሰውም፣ መታረዱ ተቆራርሶ ተበልቶ በበላው ሁሉ በኩል እርሱ ራሱ ተባዛ፣ ተራባ፤ ባጭር ቃል ይህ ደስታው በመሆኑ ሠርጉ ነው፡፡ የቀመሰው ሁሉ በእርሱ ትንሣኤ ስለሚያገኝ በበሉት ደግሞ እርሱ ሕያው ስለሚሆንና የበሉትም በእርሱ ሕያዋን ስለሚሆኑ ብዙ ፍሬ ስላፈራ ለደስታው ወሰን የለውም፡፡

ከንጉሥ ማዕድ መብላት፤ (መካፈል፤) ፊደላዊው የእስራኤል ንጉሥ የክርስቶስ አመልካች ምሳያው ነበር፤ እንደ ዳዊት በነበሩ በእስራኤል ዘመን ንጉሦች ማዕድ የሚበሉ የተከበሩና የተወደዱ ሰዎች እንደነበሩ በ(1ነገ፡1፡7፤) ይነበባል፤ ይህ ግን ከንጉሡ ነገሥቱ ከክርስቶስ ማዕድ





ሊካፈል ያለውን እጅግ የተከበረና የተመረጠ ብፁዕ ቅዱስ ሰውን አመልካች ነው፤ የእስራኤል ነገሥታት ከማንነታቸው ውጭ የሆነና ሕይወት የማይሰጠውን ውጫዊ ምግብ ያበላሉ እንጂ ሥጋቸውን መሥዋዕት አድርገው ከቶ አላቀረቡም፤ ከንጉሥ ማዕድ ውጫዊ ምግብ መብላትና ንጉሡን እግዚአብሔርን ራሱን መብላት ተዓምር የሆነ ልዩነት እንዳለው ከዚህ እንረዳለን፤ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡ ክብርን የእግዚአብሔር ማዕድ ምንድን ነው? እግዚአብሔርና ማዕዱ አንድ ብቻ እንጂ ልዩ-ልዩ ናቸወይ? ከቶ አይደሉም፡፡ በጥላም ከነገሥታት ማዕድ መካፈል እጅግ የሚያኮራ መታደል ነበር፡፡ ይህ ግን የዚያ አካልና ትርጓሜ ነው፡፡

ከእግዚአብሔር ማዕድ የሚካፈሉት እግዚአብሔርን እራሱን መካፈል ሲሆን ጥሪው የተናቀ ሆነ፤ የእግዚአብሔር ምግብና መጠጥ ራሱ እግዚአብሔር እንጂ በፊቱ የተቀመጠውን ልዩ ቁሳዊ ምግብ ነገር አይደለም፤ በእግዚአብሔር መንግሥት ከእግዚአብሔር በስተቀር ሌላ ነገር ከቶ እንደ ሌለ ተደጋግሞ ተጠቁሟል፡፡ እግዚአብሔር ከማዕዱ ምግብን ሳይሆን የራሱን ሕይወት ማካፈሉ ነው ተዓምሩ፡፡ ኢየሱስ አሮጌውን ፋሲካ ሲደመድም ወደዚህ ራሱን ወደ መካፈል ነው የሚጋብዘው፤ እንዲህ ሲል፣ "... እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው ዮሐ.6፡51፡፡ ተጨባጩን ግልፁን (ፊደላዊ (ፍጥረታዊውን) ሥጋ ነው ወይስ ስውሩን መንፈሳዊውን ሥጋ ማለቱ ነው? ሥጋ ተጨባጭ እንዳይደለ በስፋት ተብራርቷል፡፡ «እውነት እላችኋለሁ፣ በአባቴ መንግሥት ከናንተ ጋር ከዚህ ከወይኑ ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ደግሞ አልጠጣውም» (ማቴ.26፡29፤ ማር.14፡25፤ ሉቃስ 22፡17-18፤) ነገር ግን እናንተ በፈተናዎቼ ከእኔ ጋር ጸንታችሁ የኖራችሁ ናችሁ፤ አባቴ እኔን እንደ ሾመኝ እኔ ደግሞ በመንግሥቴ ከማዕዴ ትበሉና ትጠጡ ዘንድ በአሥራ ሁለቱም በእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ በዙፋኖች ትቀመጡ ዘንድ ለመንግሥት እሾማችኋለሁ፤ «ሉቃስ 22፡28--30)»

ከዚህ ከወይኑ ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ደግሞ አልጠጣውም አለ፣ እዚህ ላይ ጌታ የሚናገረው የፊደሉን ወይን ፍሬ

አሰመልክቶ ነው ወይስ የመንፈሱን ወይን ፍሬ አስመልክቶ ነው? በእግዚአብሔር መንግሥት አዲሱን የወይን ፍሬ የሚያፈራ ማነው? (ምንድን ነው?) በእግዚአብሔር መንግሥት አዲሱን የወይን ፍሬ የሚያፈራ እውነተኛው የወይን ግንድ ራሱ ጌታ ኢየሱስ የሕይወት ዛፍ ነው፣ (ዮሐ.15፡1-7) እውነት ምንድን ነው? እውነት ክርስቶስ፣ እውነት መንፈስ፣ እውነት እግዚአብሔር ነው፣ (ዮሐ.14፡6፣ 1ዮሐ.5፡7፣ ዮሐ.18፡37፣ ከ17፡17) ጋር ይታይ፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት አዲሱ የወይን ፍሬ ፊደላዊ (ፍጥረታዊ) ቁሳዊ ፍሬ ነው ወይ? የእግዚአብሔር መንግሥት የት ነው? ወይም መቼ ትመጣለች? (ሉቃስ 17፡20-21፣ ራዕይ 21፡1-4፣ ከ-2ቆሮ.6፡16) ጋር ይስተያይ፡፡

የእግዚአብሔር መንግሥት በውስጣችን ከሆነች፣ የወይኑ ግንድ እርሱም የሕይወት ዛፍ፤ (ዮሐ.15፡1) የሆነው ክርስቶስ የት ነው የሚገኘው? በፍጥረት ጊዜ ከየት ነበር የበቀለው? (ዘፍ.2፡8-9) ክርስቶስ በውስጣችን ምድር የበቀለው የሕይወት ዛፍ፤ የወይን ግንድ ነው፡፡ ውጫዊው፣ ቁሳዊው ምድር፣ ለውስጣዊው፣ ለመንፈሳዊው ምስያ ነው፡፡ የእውነት እውነተኛው ምድር ውስጣዊው፣ መንፈሳዊው ነው፡፡ ምድር ክርስቶስ በውስጥ፣ የሕይወት ዛፍ (የወይን ግንድ) ከውጭ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ወይን የወይን ምሳሌ ነው፣ የእውነት እውነተኛው ወይን ክርስቶስ ተጨምቆ የተገኘ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ አዲሱ፣ የእውነት እውነተኛውና በእግዚአብሔር መንግሥት የሚጠጣው ዘላለም አዲስ የሆነው ወይን ጠጅ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ የፊደሉን ወይን ጠጅ የሚጠጣ ሆድም በእግዚአብሔር መንግሥት የለም፡፡ ሐዋርያት ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል አይደል? (ሐሥ.2፡13) ጠጁ የተገኘው ከየት ነበር? ነቢዩ ኢሳይያስ ወደ ውኃ ኑ፣ ኑ ወይን ጠጅና ወተት ግዙ ብሉ፤ በረከትን ብሉ፣ ሰውነታችሁ በቅጫማ ደስ ይበለው (ኢሳ.55፡1-2) ያለው አንዱ ክርስቶስ ነው፡፡







በአጭር ቃል በእግዚአብሔር መንግሥት እግዚአብሔር ብቻ እንጂ ምድራዊ ነገር በእግዚአብሔር መንግሥት ርኩስ ስለሆነ ከምድር ምንም ሊታከልበት አይችልም፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እና እግዚአብሔር አንድ ስለሆኑ የእግዚአብሔር መንግሥት ራሱ በውስጣችን የሚያድረው እግዚአብሔር ነው፡፡ ወደ ሆድ የሚወርደውን ምድራዊ (ቁሳዊ) ነገር ለነፍሳችን የሚሆን ነገር አስመስለን ምድር ያፈራውን ነገር ጌታ ያቀረበውን የስገነቱን እራት አስመስለን ሥርተን ስንካፈል አለማፈራችን አስገራሚና አሳፋሪ መሆን ነበረበት፡፡ ወደ ሆድ የሚወርድ ነገር ለእግዚአብሔር መንግሥት በጭራሽ አያገለግልም፤ ሆድም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥትም ሆነ የዘላለም ሕይወት መውጫ ከልባችን እንጂ ከሆዳችን ውስጥ አይደለም፤ (ምሳሌ 4፡23)፡፡ ዋጋህን የምታገኘው ከራስህ ውስጥ ከገዛ መዝገብህ እንጂ ከሌላ ከየትም አይደለም፡፡ ከሆድ የሚወጣው ቅዱስ ነገር ሳይሆን፣ ርኩስ፣ ቆሻሻ ነገር መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

## ፋሲካን ሳይገባ ስለ መካፈል

ሳይገባው ፋሲካውን የሚካፈል በጌታ ሥጋና ደሙ ባለ ዕዳ ከመሆኑም እስከ መታመምና እስከ መሞት ድረስ እንደሚደርስ፣ (1ቆሮ.11፡26-31) የሚናገረው እውነቱ እንዴት ነው? ይህ የተጻፈው በመሠረቱ በእውነት ላይ ነው እንጂ በአሁኑ ዘመን በሚደረገው በጠቅላላ የጌታን ሥጋና ደም ያልለየ አስመሳይ ሥርዓት ላይ አይደለም፡፡ የአሁኑ ዘመን ጌታ ራት ጌታ እንኩ ብሉ ብሎ ከእጁ የሰጠው አይደለምና. ሥርዓቱን የሚካፈል ሁሉ ቁስ አካሉ ደህና ስለሚመስል ደህና ሳይሆን፣ የታመመና የሞተ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ሰው ሞቶ ሳይሆን፣ ሳይሞቱ ይሞታል፡፡ ሳይቃጠሉ ይነድዷል፤ አሜን፡፡ ይህ በግልፅ ማሳመምና መግደል ቀርቶ ጉንፋንም አያስይዝም፤ በውጭ አስመስሎ የተሠራ ግምታዊ፣ አስመሳይና የልጅ ጨዋታ ስለሆነ፡፡ በመሠረቱ ላይ

ግን ያለ አግባብ የበሉ እንደ ታመሙና እንዳንቀላፉ ጳውሎስ ይገልፃል፤ ይህ የሐዋርያት ዘመንም ከብሉይ ወደ አዲስ መሸጋገሪያ ዘመን ላይ የነበረ ሁኔታ ሆኖ መታየት አለበት፡፡ ከትንሣኤ በኋላ ግን እስራኤልን ከአዲሱ ኪዳን ጋር ለማስተዋወቅ ውጫዊው (ፊደላዊው (ፍጥረታዊው) ሥርዓት የተደረገ ሥጋዊነት ሆኖ ግማሹ ጠግቦ፣ ግማሹ ተርቦ፣ ሌላው ሰክሮ፣ ሌላውም አፍሮ፣ ተዋርዶ ጋጠ-ወጥ ሆኖ ይታያልና፤ ከብሩ ተገፈፏል፡፡ ወደ ወጭ ተጥሏል፡፡ እዚህ ላይ እውነተኞች ከሐሰተኞች እንዲለዩ መከፋፈል መፈጠሩን ሐዋርያው ጠቁሟል፡፡

የጌታ እራት አለ አግባብ የመቀበሉ መቅሠፍት ወደ አዲስ ኪዳን ሽግግር ወቅት እንደ ተከሠተ ይታያል፡፡ ዛሬ ግን በመንፈስ እንጂ በፊደል በማይሆነው በአዲስ ኪዳን መቅሠፍቱ በፊደል ይከሠታል ብሎ ማሰብ አእምሮአችን ገና ከመጋረጃው ዘመን ጨለማ እንዳልወጣ ያሳያል፡፡ የእስራኤል እውነት ዛሬ በኛ የመንፈስ እውነት ነው ፡ እንጂ በቀጥታ የፊደል (ፍጥረታዊ)እውነት አይሆንም፡፡ መንፈሳዊ ሥርዓት ማደግን ትቶ ባለህበት ርገጥ ከሆነ ጣዖት ነው፤ (ነኹሽታን) (2ኛ ነገ.18:4)

በግብፅ ፋሲካ የተካፈሉ፣ በምድረ-በዳ ከሰማይ የወረደ እንጀራ የበሉና ከዐለቱ ውኃ የጠጡ ሁሉ ሳይገባቸው ስለበሉ ሁሉም በጉዞ ላይ በመንገድ ሞተው አለቁ፣ የ(ዮሐ6፡49፣ ቁ.58/ለ፣ ኢያሱ5፡2-6) በማየት የበሉ እንዳለ ሁሉ በእምነት የበሉ አሉ (የእኛን ልብን የሚያይ ጌታ ይመስክር)፡፡ ጌታ ይህን ሲያስታውስ ነው፣ «አባቶቻችሁ በምድረ-በዳ መና በሉ፣ ሞቱም፣» የሚለው፡፡ በሰገነቱ እራትም ሳይገባው ጉርሻ ተቀብሎ በጨለማ የወጣው ይሁዳ አስቆሮቱም እንደ አባቶቹ ሁሉ ታንቆ ሞተ፣ (ዘኍ.11፡33.34፣ 1ቆሮ.1፡1-4፣ ቆሮ.11፡ 27-31፣ ዮሐ.13፡26፣ ማቴ.27፡5፣ መዝ.78፡30-31) ምግቡ ሳይገባው የሚበላውን ሁሉ ገዳይ መሆኑ ተጽፏልና፣ ይሁዳ የቀመሳት ለሞት ከሆነ ዘንድ በቂ ናትና፡፡ ለሕይወት ከሆነ ግን የአንድ ጊዜ ራት ለሁለተኛው በእግዚአብሔር መንግሥት አዲሱን እስከ





መብላትና መጠጣት እስከ እግዚአብሔር እስከ ትንቢታዊው ተራራ ኮሬብ፣ እስከ ተራራ ግብዣ (ኢሳ.25፡6-8) ድረስ ከሩቅ የመጣን እኛ በመንገድ እንዳንዝል (ማር. 8፡1-3) ይህ ወደ ቤታችን ያደርሳል፣ (1ነገ. 19፡8፣ ማቴ. 26፡29፤ ማር. 14፡25፤ ዕብ. 12.22-24፣ ኢሳ. 49፡1)

ፋሲካችን በክርስቶስ ሞትና ሕይወት ነው፤ ይህ፣ ይድናል፣ ያ፣ ይሞታል፣ ማዳኑ ሞት ሆኖበት ይሞታል፤ ግብፅ ሞት መጥቶበት ነው የሞተው ወይስ ሕይወት ሞት ሆነበት ነበር? በክርስቶስ ጨለማው ይበራል፣ ብርሃኑ ይጨልማል ብርሃኑ ጨለማ ሆኖበት፡፡ ግብፅ ጨለማ መጥቶበት ነበር የጨለመው ወይስ ብርሃኑ ጨለማም ሆነበት? ብርሃንና ሕይወት ሆኖ ወደ ዓለም የመጣው ክርስቶስ ለአንባቢው እንዴት ነው? ተቃራኒ ሆኖብህ ብርሃንና ሕይወት በመሆን ደስታና እልልታ ሆነልህ ወይስ ተቃርኖህ ጨለማና ሞት ሆኖብህ በሕይወትህ ከቦታህ የትም ሳትሄድ ወደ ጨለማ ሲዖል ወረድክበት?

ለግብፅ መደምሰስ ተጠያቂ ማነው? እግዚአብሔር ነው ወይ? ከቶ አይደለም፤ እግዚአብሔር ጻድቅ ነው። ሕይወት ሞት ሆነበት የሞተ፣ ብርሃን ጨለማ ሆኖበት የጨለመ፣ እግዚአብሔር ሰይጣን ሆኖ የተገለበጠበት ስለሆነ፣ ሕይወትን ወደ ሞት ተርጉሞ፣ ብርሃንን ወደጨለማ ፈርጆ፣ አለ መልክ መልክ አለ ባሕሪው ባሕሪ ለጥፎበት በፈረደበት ስለተፈረደበት በገዛ-እጁ የሞተበት ሁሉ ደሙ በራሱ ላይ ነው፤ ለዘላለሙ አሜን። ከዚህም ሌላ ፋሲካ ማለት የክርስቶሰ ሞት፣ ሞትና ሕይወት መሆኑ ከፍ ብሎ ተመልክቷል፤ መራራና ጣፋጭ፡፡ ክርስቶስ ለኔ ለራሴ ሞትና ሕይወት ነው፤ ደግሞ መራራና ጣፋጭ፡፡ እስራኤል ከግብፅ በወጣበት ሌሊት የበላው ምግብ ጣፋጩን ብቻ በላ ወይስ ጣፋጩን ከመራራው ጋር አምጎ በላ? ጣፋጩ ምን መራራው ምን ማለት ነው? ነቢዩ ሕዝቅኤልና ሐዋርያው ዮሐንስ የበሉት መጽሐፍ (ሕዝ. 2፡8-10፤ 3፡1-2፣ ራዕይ 10፡ 8-11) ነቢዩ፣ ኀዘንን፣ ዋይታን፣ ለቅሶን ከጣፋጩ ጋር ሲበላ፣ ሐዋርያው

መራራውን ከጣፋጭ ጋር ማለት ሞትንና ሕይወትን ተደባልቆ የቀረበ ማለት ነውና፡፡ ሁሉ ሞቱን ሳይቀበሉ ሕይወቱን መቀበል የለም፤ ሕይወቱ ከሞቱ ማዶ ነው፡፡ አንተ/ችን ለማዳን አንተ/ችን ይገድላል፡፡ አንተ ተቀብረህ አንተ ትወጣለህ፣ (ቆላ.2፡11-12) ክርስቶስ በሙታንና በሕያዋን ፈራጅ ነውና፣ (2ጢሞ.4፡1) ከተነጠቁት ወደ ተራራ ከተወሰዱት ሙሴና አሮን ጋር አራቱን ሰዎች /ከኢያሱና ካሌብ/ አዲሱን ትውልድ እንዲመሩ አስቀርቶ በሚሊዮን የሚቆጠሩትን በምድረ-በዳ ቀበረ፡፡

ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ የእውነት እውነቱ ፍርድ ግን በውጭ ሳይሆን በውስጥ፣ በመንፈስ ነው፡፡ ምድረ-በዳውም በመንፈስ መሞቱም መቃብሩም በውስጥ በመንፈስ ነው፡፡ ደጋግመን እንዳየነው ስቀሉ፣ ግደሉ የተባለው ሥጋ ለማምለጥ ከውጭ ሜዳ ሸሽቶ ወደየ ውስጥ ጓዳ ገብቶ ምሽግ ይዟልና በኢያሱ 10፡15-27፤ ቁ.18 መሠረት ለፍርድ እስኪቀርብ ድረስ የተሸሸገበትን የመቄዳ ዋሻን አፍ በታላላቅ ድንጋይ ዝጉት፡፡ ስቀሉ፣ ግደሉ የተባለው ሥጋ በውስጣችን አካላችን ሆኖ የተሠወረው ሰይጣን ነው ማለቱ ትዝ ይላችኋል፤ ሰይጣን ባይሆን ኖሮ ንፋስ እንኳ ሊገባ በማይችለው እጅግ ረቂቅና ጠባብ በሆነው በር ወደ ውስጣችን ገብቶ ከዓይነ ምናባችን ተሰውሮ ሊጠፋ ይችላል ባይ ማነው? ስለዚህ በለመደው ዓይነት ሸሽቶ በውስጣችን ዋሻ ገብቷልና የተሸሸገበትን ዋሻ አፍ በታላላቅ ድንጋይ ቆልፋችሁ በጸሎታችሁ ኃይል በጥንቃቄ ጠብቁት እንጂ እሱን በጦር መሣሪያ መጠበቅ አይቻልም፡፡

ሞቱን ከሕይወቱ ጋር የኢየሱስን ሕይወት ማፋለቁን፣ ከኢየሱስ ሞት መራራው ጋር እንቀበላለን፡፡ ይህ በዘመናችን በእምነት፣ በመንፈስ እንጂ በማየት በፊደል የሚፈጸም እንደሆነ አድርጎ ማቅረብ ሰይጣናዊ የጨለማ ትምህርት ነው፡፡ ከትንሣኤ፣ ከመጋረጃ መቀደድ ወዲህ ይህ ማለት ባጭር ቃል የውስጥ የልቡና ግዝረት፣ አዲስ ልብ፣ አዲስ መንፈስ ማለት ሆኖ ይደመደማል፡፡ በውጭ ሕያው መሆን በውስጥ ሙት ያደርጋል፣ ማለት፣



የጌታ ሥጋ መድረሻና ምንነቱ፣

እንደ ሥጋ ፈቃድ መመላለስ በውጭ በሰው ዘንድ በአስመሳዩ በሐሰት እውነት ሕያው መሆን ስለሆነ በጌታ ዘንድ በእውነት እውነቱ (በመንፈስ) ሙት መሆን ነው፡፡ በሥጋ ሕያው መሆን፣ በመንፈስ ሙት ያደርጋል፡፡ በሥጋ አለሁ ባይነት ከፍ፣ ከፍ ማለት፡፡ መላ ዓለምን ወደ ሲዖል የከተተው የአዳም ከፍ፣ ከፍ ማለት ነው፡፡ ይህ ዓይነት እግዚአብሔርን ከመንግሥቱ መገልበጥ ስለሆነ ታላቅ ኃጢአት ነው፡፡ በውጭ የሚንጠራራ በውስጡ በሲዖል ነው፡፡ ሲዖል ማለት እግዚአብሔርን አለማየት፤ ጨለማ፣ ወህኒ ማለት ነው፡፡

የሰውን ልጅ የሚያጓጓው የውሴቱ፣ የሚታየው የጊዜው ሕይወት እንጂ የማይታየው የዘላለሙ ስሜትም አልሰጠውም፡፡ በአዲስ ኪዳን ከመጋረጃ መቀደድ፣ ከትንሣኤ ወዲህ ፋሲካ ማለት ክርስቶስ ማለት ነው፤ ብቻውን ሁሉ የሆነው፡፡ ከግብፅ እንደወጡ እስራኤሎች፣ እነዚህም እነዚያም ሟቾች ሞትን ሕይወት፣ ሕይወትን ግን ሞት አድርገው ስለሚቆጥሩ ነው የሚሞቱት፡፡ አትፍረድ፣ ይፈረድብሃል ስለሚሆን ሕይወት የሆነውን ክርስቶስን ሞት አድርገው ቆጥረዋልና፡፡ ሙሴ ለሞት ከግብፅ አወጣኸን ብለው ፈረዱና ፍርዱን ተቀበሉ፡፡ እንደ እነዚያ ዛሬም ክርስቶስን መከተል ሞት፣ ክሰረት፣ ውድመት አድርገው የሚያዩ ለማለት ነው፡፡ ሞት አደርጎ ስለሚያስብ ስለሚያነብ (ስለሚመለከት) ሞት ይሆንበታልና ይሞትበታል ወገኖቼ፣ አሁን ስታነቡት ክርስቶስ ሞት፣ ጥፋት፣ ከሥረት፣ ውርደት ሆኖ ከታያችሁ እንዲሁም ነው የሚሆንባችሁ፡፡ በፈረዳችሁት ይፈረድባችኋል፤ የአስተያየታችሁንና የአተረጓጎማችሁን ያንኑ የራሳችሁን እንዳትቀበሉ ተጠንቀቁ፤ ሕይወት እንደሆነ፣ ክብር እንደሆነ በደስታ እንድንቀበለው እንመክር፤ እንመካከር፡፡



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፤ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፤ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

## ክፍል ሦስት
## ከመስቀሉ፣ የፈሰሰው ደምና ውኃ፤

1/ መስቀል፣ 2/ ደም፣ 3/ ውኃ

መስቀል፤ መሰቀል፡ በዓለሙ ቋንቋ ከፍታ ላይ ሰማይንም ምድርንም ሳይደርሱ በአየር መካከል መሰቀል ላይ፣ ተንጠልጥሎ መሠቃየት ማለት ይሆናል። መሰቀል አራት ዓይነት ሊሆን ይችላል።
አንደኛው፣ እንደ ወንበዴዎቹ በሠሩት ኃጢአት ባጋጣሚ ከጌታ ጋር በግልፅ፣ በፊደል መሰቀል፤
ሁለተኛው እንደ ጳውሎስና እጆቹንና እግሮቹን እንደ ተቸነከረው እንደ ዳዊት ከክርስቶስ ጋር በማይታይ ሁኔታ መሰቀል፤
ሦስተኛው፣ በተቃራኒ ከዲያብሎስ ጋር ለጥፋት ትዕቢትን፣ ሞራን ተሞልቶ በኩራት፣ ራስን በመካብ በዕብጠት፣ በሥጋዊ ትልቅነት ከደመናዎች ከፍታ ላይ ተሰቅሎ በከፍታ መሠውያ ላይ ለሰይጣን በእርኩሰት ደረጃ ሰይጣን እንዲኖር መሥዋዕት ሆኖ በስውር መቅረብ፤
አራተኛው፣ እንደ ፈሪሳውያን የሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን በማንፀባረቅ ራስን ንፁህ በማድረግ ሌሎችን በመናቅ በመመጻደቅ ከሁሉ የተሻሉ መምሰልና በሌሎች ላይ ለመፍረድ ከፍ፣ ከፍ ማለት፤ ስለሆነ ያው ለሰይጣን መሥዋዕ ሆኖ በስውር መቅረብ፤ (ሉቃስ 16፡15፣ ም.18፡9-14፣ ምሳሌ 16፡5)። «ቅዱሱ መስቀል» አንጠልጥሎ ከኃጢአት በማራቅ ይቀድሳል። ተቃራኒው «እርኩሱ መስቀልም» አንጠልጥሎ ከጽድቅ በማራቅ ያረክሳል። አንደኛው ኃጢአትን በመፀየፍ ሲንጠለጠል፣ ሁለተኛው ጽድቅን በመፀየፍ ይንጠለጠላል፤ አንተ ከኃጢአት ትርቃለህ እኔ ከጽድቅ እርቃለሁ ማለት ነው።

በአዲስ ኪዳን ከኢየሱስ ጋር መሰቀል ግን በልቡና ከፍታ (ተራራ) ላይ በአንተ እርሱ ሕያው ሆኖ እንዲኖር አንተ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት





ሆነህ መቅረብ ነው። ይህም ስውሩ የቅዱሳን የሆነ ሞት ነው። ላይኛውም ስውሩ የርኩሳን ሞት ነው። የጌታ መስቀልን በተመለከተም፣ የእርሱ መስቀል ደግሞ በውጭና በውስጥ፣ በፊደልና በመንፈስ፣ በሰው (እስራኤል) ፊትና በእግዚአብሔር ፊት፣ በአካልና በጥላ ሁለት ዓይነት ሆኖ እናገኘዋለን። አንደኛው (ውጫዊው) በወቅቱ የነበረ ሰው ሁሉ በዓይኑ ማየት የቻለው ከሁለት ወንበዴዎች ተቆጥሮ፣ ተደምሮ በእስራኤል ምድር በቁስ አካል ለውጫዊው እስራኤል የተሰቀለበት መስቀል ሲሆን፣ ሁለተኛው ቀደም ሲል እንዳየነው ውስጣዊው ከጳውሎስ፣ ከዳዊትና ከኢሳይያስ ጋር፣ ዛሬም ከእኛም ጋር በውስጥ በማይታየው በስውሩና በቅዱሱ መስቀል ለዓለም ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት መሰቀሉ ነው ፍጻሜው።

ይህ፣ የክርስቶስ መስቀል መንገድ ጠራጊና የበር መክፈቻ ሆኖ በሰማይና በምድር፣ በምሥራቅ፣ በምዕራብና በደቡብ (በሦስቱ ማዕዘናት) የዓለም ማዕከል ሆኖ የተዘረጋ ራስ ወደሆነው እንድመጡ በዚህ ኑ፣ የሚል ድምፅ አልባ ጠሪ ሕያው መንገድ የቀደደ መስቀል ነው። ይህ መስቀል ደግሞ በምድረ-በዳ የተሰቀለውን የሙሴን እባብ (ነሐሱ) በመተርጎም ወደ ብርሃን አውጥቷል። የብሉይ ኪዳኑ እባብ (ነሐሱ) የሐሰት እውነተኛ እባብ ውጫዊ ጊዜያዊን ሕይወት አዳኝ ሲሆን፣ የአዲስ ኪዳኑ ክርስቶስ የእውነት እውነተኛ ሆኖ ውስጣዊ ዘላለማዊን ሕይወት አዳኝ ነው።

ውኃ፡- ውኃ ከመሥመሩ ወጣ ብለን በእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ በገሃዱ ሁኔታ ስንመለከት ከጨለማ፣ ከሰማይና ምድር ጋር በአንድነት ብቅ እንዳለ እንጂ አመጣጡ በእኔ ዕውቀት ደረጃ ከዚህ በተለየ መንገድ አይታወቅም (ዘፍ.1፡2)። እንደሚያሳየው ውኃ ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ ሰፍፎ ነበር በማለት ቅድሙ-ዕውቅና እንዳለው አድርጎ ሁኔታውን መተረክ ይጀምራል፤ በዚህ ሁኔታ ሲታይ ውኃ፣ ከእግዚአብሔር መንፈስ ሥር ሆኖ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ መንሳፈፊያ፣ ማረፊያ፣ መቀመጫ

ዙፋን ወይም የመንፈስ መጓጓዣ ሆኖ እንመለከተዋለን፡፡ እንዲሁም ስናስላስለው ውኃ ከሰማይና ምድር ጋር ነባር ከሚሆን በስተቀር የተለየ ጅማሬ የለውም፡፡ ውኃ ሊመጣ ላለ ፍጥረት ሕይወትን ይሰጥ ዘንድ በእግዚአብሔር መንፈስ እየተፈወሰና እየተባረከ ከዙፋኑ ሥር ከመቅደሱ መፍለቅ ነበረበትና (ሕዝ.47፡1-12፡ቁ.12.ራዕይ 22፡1-2) ውኃው በፍጥረት ጊዜ ሲታይ፣ ከእግዚአብሔር መንፈስ በታች-ታች በጥልቁ ላይ ካለው ጨለማ ላይ ጨለማውን ሸፍኖ የተንጣለለ ሆኖ ይነበባል፡፡ በዚህ ሁኔታ በ/ 2ሳሙ.22፡12፣ መዝ.18፡11) እንደ ተገለጠው የእግዚአብሔር ዙፋንም በጥልቁ ላይ ካለው ጨለማ በላይ ካለው ውኃ ላይ ተዘርግቶ ይታያል፡፡ እንዲሁም ውኃ፣ በእግዚአብሔር መንፈስ ቁጥጥር ሥር ሆኖ የሞት ጥላ የሆነው ጨለማ ከእግሩ በታች መነጠፉን እንመለከታለን፣ ውኃ፣ በመንፈስ ቁጥጥር ሥር ካልሆነ የጥለቀልቃልና ያጠፋል ማለትም ይቻላል?

ውኃ በውስጥ፣ በውጭ፣ ከላይ፣ ከታች፣ በዙሪያው ዓለምን ይከብባል፡፡ ውኃ ሲተነተን፣ ፈሳሽ፣ ተን፣ በረዶ በመሆን በሦስት ቅርፅ ሲታይ፣ ሥላሴን ያንጸባርቃል፡፡ ፈሳሽ ሆኖ መሬት ለመሬት አንጉራትን አቋርጦ ሲጓዝ የተጠማውን ፍጥረት ሁሉ እያጠጣ ወደ መጣበት ዓለም ዳርቻ ይዞራል፡፡ ውኃ፣ ከመሬት በታች ቀላይ፣ ከመሬት በላይ ባሕር ሆኖ ይንጣለላል፣ ኩሬ ሆኖ ይተኛል፣ ምንጭ ሆኖ ይፈልቃል፣ ጅረት ሆኖ ሲፈስስ ያገኘውን ቆሻሻ ሁሉ በመጥረግ አካባቢን ያፀዳል፡፡ ጎርፍ ሆኖ የተገኘውን ጠራርጎ ዘርፎ፣ ተሸክሞ ይሄዳል፣ ወደ መጣበት ወስዶ እስኪከት ድረስ በየሥርቻ እየጣለ ይጓዛል፡፡ ለፍጥረት ሁሉ መጠጥ ሆኖ ያረካል ሕይወት ሆኖ ያኖራል፣ ተክሎች እንዲበቅሉ፣ እንዲያድጉና እንዲያፈሩ ከፀሐይ ጋር ተቀናጅቶ ይሠራል፡፡ ውኃ፣ ተጠጥቶ ጥማትን ከማርካቱም በላይ በእንስሶች፣ በአራዊት፣ በተክሎችና በሣር-ቅጠሎች አካል ሕዋሳት ውስጥ-ለውስጥ፣ የውስጥ ጅረት ሆኖ በመጓዝ የሕዋሳት ሴሎችን በማጠጣት ሕይወት ይሆናል፣ የውስጥና የውጭ ቆሻሻን በማፅዳት ንጽህና ይሰጣል፣





ተን ሆኖ በአየር ላይ ተሳፍፎ ወደ ላይ ያለ ክንፍ ወደመጣበት ባሕር ይመለሳል፣ በአየር ላይ ተንሳፍፎም ከንዳድ ጥላ ፤ ከለላ ከመሆንም ተርፎ ተመልሶ በምድር ላይ ይርከፈከፋል፣ ያርሳል፡፡ በማጠቡ ይቅርታውን ይሰብካል፡፡ በረዶ ሆኖም ከሰማይ ወድቆ ራሱ እየተቀጠቀጠ በመቀጥቀጥ ቁጣውን በምድር ላይ ይገልፃል፡፡ ነጐድጓድ፣ መብረቅ፣ ብልጭታና እሳት በመፍጠር እስከ ማቃጠል ይደርሳል። ቁጣው ከበረደለት በኋላም በንፋስ ክንፍ ተሳፍሮ ወደ መጣበት ደግሞ ይመለሳል፡፡ (ውኃ) ከጠፈር በላይ፣ ከምድር በታች፣ ውስጥ ለውስጥና ውጭ በምድር ክበብ ዓለምን ከብቦ በማጠጣት ግዑዟን መሬት የሕይወት መፍለቂያ በማድረግ እግዚአብሔርን ከማመልከቱም የጌታን ሥራ በግልጽ ይናገራል፣ ታሪኩን ያወራል፣ ክብሩን ያንፀባርቃል፣ ጥበቃውን፣ መግቦቱን፣ ፍርዱን፣ ቁጣውን በማሳየት ውኃ ብቻውን የእግዚአብሔር በቂ ምስክር፣ ሙሉ ወንጌል ሆኖ ይታያል፡፡

ውኃ ከደም ጋር

ደም በታሪክ ደረጃ፡- ደም ደግሞ ምድራዊ ነገር ነው እንጂ ሰማያዊ አይደለም፡፡ ምድራዊው ሕይወት ደም በምንለው በቀዩ ነገር የሚንቀሳቀስ ሲሆን፣ ሰማያዊው ሕይወት ግን በነጩ እንደ ብርሌ በሚያንፀባርቀው የሕይወት ውኃ ነው፡፡ የክርስቶስ ሕይወት ሰማያዊና ምድራዊ ጣምራ እንደ መሆኑ መጠን ከተወጋ ጎኑ ውኃና ደም መፍሰሱ በብርሃን ምስክር ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም የእግዚአብሔር መንግሥት ሕይወት በውኃ እንጂ በምናውቀው ደም አይደለም፡፡ ውኃ ራሱ በደም መልክ አብሮ ቀልቶ ስለሚታይ በደም ስያሜ ይገለጻል፡፡ ውኃንም በሰበዓዊ ቋንቋችን መተርጎም የተዛባ ፍቺ ያስጨብጣል፡፡

ከድንጋይ በስተቀር፣ ውኃ ያጣ ነገር ሁሉ እንደሚደርቅ እንዲሁ ደምም ውኃን ካጣ ይደርቃል፡፡ በቁሳዊው ዓለም ደም ሲባል ከእንስሳ ሥጋ

የሚወጣ ቀይ ፈሳሽ (በሳይንሱ) ከአጥንት የሚመነጭ፣ የሥጋ ሕይወት መሆኑን አጥኚዎቹ ያመለክታሉ፡፡ በውኃ አማካይነት እየተሠራጨ ሥጋን በሕይወት የሚያኖረው ደም ነውና ከደሙ የተለየ ሥጋ ምውት፣ እንደሆነ፣ እንዲሁ ከውኃው የተለየ ደምም ምውት ነው፡፡ ሥጋ ደግሞ በሕይወት የሚኖረው በደም መጋረጃ ውስጥ በተሸፈነ ውኃ አማካይነት ጭምር መሆኑ መታሰብ አለበት፡፡ በዚህ አኳያ ሲታይ፣ ደምን ውኃ ጋርዷል ወይስ ውኃን ደም ጋርዷል? የትኛው ክቡር ነው? ቆዳ፣ ሥጋንም ደምንም ጋርዷል፣ ደም፣ ውኃን ሸፍኗል፤ የትኛው ይበልጥ ቅዱስ ነው? ደም ደግሞ በመንፈሳዊ ደረጃ የሕይወት መሸፈኛ፣ ሕይወትን ቀዳሽ (ከለላ) መሆኑ (በዘፍ.9፡4፣ ዘሌ.17፡11-12) ተገልጧል፡፡ ስለሆነ ሕይወት በደም ሲሸፈን ቅዱስ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ከሕይወትና ከደም የትኛው የተቀደሰ ነው? ቀዳሹ ማነው? ተቀዳሹስ ማነው? ሰው፣ የእግዚአብሔር ምሳሌ በመሆኑ የውጭና የውስጥ አካል ባለቤት ሆኖ የውስጡ አካል ክብር በውጪው አካል መጋረጃ ጥልቀት ውስጥ ከዓይናችንና ከምናባችን ተሰውሮ ነው እንጂ፣ የውጪ ሰውነታችን ባለደም እንደ ሆነም እንዲሁ የውስጡ ሰውነታችን እጅግ በተለየ ደረጃ ባለ ደም ነው፡፡ የውጪ ሙት ደም፣ በውስጡ ሕይወት ደም ውኃ እንዲቀየር ነው፡፡ የውጭ ሰውነትም ለውስጥ ሰውነት መጋረጃ (የክብሩ) ክፉብ ነው፡፡ የሰው ልጅ የተባለ ዘላለማዊ የሚሆነውም በውስጡ ደም ነው፡፡ ውስጥን የሚያንቀሳቅሰው ደም በሰው ዘንድ እንዳይታይና እንዳይታወቅ፣ ውጭን በሚያንቀሳቅሰው ደም ተጋርዷል፡፡ ውጭም ሆነ ውስጥ ያለ ደም አይንቀሳቀስም፡፡

በሳይንሱ ረገድም ውጫዊ የሰው አካል የቀይና የነጭ የሁለት ዓይነት ደም ባለቤት እንደሆነ የተነገረን ሲሆን፣ የውስጥ ሰውነትም ከእግዚአብሔር በሚፈልቅ የቅዱስና ነጭ፣ ማለት ግልጸት {TRANSPARENT} ደምና በተቃራኒ ከዲያብሎስ በሚፈልቅ የርኩስ የጨለማው ደም ባለቤት በመሆን በሁለት ጎራ እንከፈላለን፡፡ የእግዚአብሔር ሕይወት







የሚንቀሳቀሰው ከእግዚአብሔር በሚፈሰው ደም ማለት በእግዚአብሔር መንፈስ ማለት ሲሆን፣ የዲያብሎስ ሕይወት የሚንቀሳቀሰው በዲያብሎስ ደም ማለት በዲያብሎስ መንፈስ ነው ለማለት ነው፡፡ እግዚአብሔርም ዲያብሎስም በሥጋ ካልሆኑ የገሃዱ ደም የላቸውም፡፡ ማለትም በመንፈስ ቅዱስ እሳት የሚፈላ (የሚገነፍል) (በኃጢአት ላይ ቁጣ)፤ የሰማዕቱ እስጢፋኖስ ደም ዓይነት፣ (የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን መልእክቱን ባቀረበበት ዕለት፤) እንዲሁም በተቃራኒው በርኩስ መንፈስ እሳት የሚፈላ (የሚገነፍል) የነናቡከደነፆር ደም ዓይነት፣ (በነሲድራቅ፤ ሚሳቅ፤ አብድናጐ ላይ፤) ምሳሌ ይሆናል፡፡ ብርሃን ደም ለተባለው፣ እስጢፋኖስ ዓለማትን፣ ሰማያትን ሰንጥቆ (አሻግሮ) አብ እግዚአብሔርን፣ በቀኙ የቆመውንም ልጁን ክርስቶስ ኢየሱስን ለማየት ከመብቃቱም ለጠላቶቹ በዚያ በቀውጢ ወቅት ለምህረት በመጸለዩ አማላጅ ሆኖ በተግባር መገለጡ ባለብርሃን {TRANSPARENT} ደም መሆኑን ሲያረጋግጥ፣ ጨለማ ደም ለተባለው ናቡከደነፆር ከደቂቃ በኋላ የሚሆነውን ክስተት ለማየት ባለመቻሉና የሚያደርገውን አለማወቁ በጨለማ ደም የተጋረደ ሰው መሆኑን ያሳያል፡፡ የኢየሱስ ደም ብርሃን ነው ወይስ ጨለማ? (1ዮሐ.1፡7) ይመሰክር፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ንጹሑ የሕይወት መሸፈኛ (ደምን) በማቅረብ የመጀመሪያው፣ ከፍተኛውና የተደነቀው ሰው የአዳም ሁለተኛ ልጅ አቤል መሆኑ ይታወቃል፣ (ዘፍ.4፡4፤ ዕብ.12፡24፣ 1ዮሐ.3፡12) ቀጥሎም የሰው ደም እግዚአብሔር የሰጠውና ‹‹... እኔ ለእናንተ ሰጠሁ›› (ዘሌ.17፡11) የሚለው (እርሱ) በዕዳ መልክ የሚፈልገው እጅግ ውድና ክቡር ነገር ስለሆነ፣ በምንም ሁኔታ የሰው ደም እንዳይፈስስ በማስጠንቀቂያ ደረጃ በኖኅ በኩል ለዓለም ተላልፏል፡፡ ደም በውኃ አንቀሳቃሽነት ያለ ሥጋ፣ ሥጋም ያለ ደም ተለይቶ አይኖርም፡፡ ደም፣ በበኩሉ ነዳጅ (ኦክሲጅን) ሳቢ የሥጋ አንቀሳቃሽ ማለት ነው፡፡ የብሉይ ኪዳን ደም ለአዲስ ኪዳን

ደም ጥላ፣ ምስሌ በመሆን በሞግዚትነት ሲሠራ ቆይቶ በአዲስ ኪዳን፣ ዘመን (ጊዜ) ያለፈበት ሆኖና፣ ለአዲሱ ደም ቦታ ለቅቆ ከክርስቶስ መስቀል ማዶ በኩል (ፊተኛው ኋለኛ በመሆን) መቅረቱን እያስታወሰን፣ የውጪው ፊደላዊ (ፍጥረታዊ)ው ዓለም ቋንቋ ብዛቱ ሲዘረዝርም፣ 1.ሥጋ፣ 2.ደም፣ 3.እንጀራ 4. ውኃ፣ 5.ወይን እየተባለ ይቆጠር የነበረው ዘመን ያለፈበት ስለሆነ፣ አሁን ሁሉ በሁሉ የሆነ ሁሉን ቻይ ክርስቶስ፣ ሥጋውም ደሙም ክርስቶስ፣ ውኃውም ክርስቶስ፣ እንጀራውም፣ ወይኑም ክርስቶስ ነውና ክርስቶስ አንድ፣ ሁሉና በሁሉ ነው፤ እግዚአብሔር አንድ እንጂ አይቆጠርምና፡፡

ክርስቶስን በእስራኤል ደረጃ ደምና ሥጋ እንጀራ አድርገን መቁጠር ከዘመኑ ጋር የቀረ ነገር ነው፡፡ እርሱም ከሰማይ የወረደ ሥጋ ነው እንጂ (ዮሐ. 6፡48-51) ከሥጋና ደም ከወንድ ፈቃድ የተወለደ ሥጋና ደም አይደለምና፤ የተቀበሉትም እንዲሁ (ዮሐ.1፡12-13)፡፡ የተቀበሉት የእርሱን ደም ሆኑ ማለት ነው፡፡ ሥጋውን በተለይ፣ ደሙን በተለይ፣ ውኃውን በተለይ፣ እንጀራውን በተለይ፣ ክርስቶስን በተለይ፣ አብን በተለይ አናገኝም፡፡ የሚታየው የጊዜው ነውና እስከ ጊዜው ሠርቶ ከጊዜው ጋር ከመጋረጃ መቀደድ ወዲያ ማዶ ወድቋል፡፡ የማይታየው ጊዜ የማይሽረው፣ ከጊዜ ገደብ ውጭ የሆነው የዘላለሙ፣ (2ቆሮ.4፡18፤) አንድ ብቻውን በቂው ተተክቷል፡፡ ማንኛውም የያኔው ነገር የተለያየ ነገር ነበር፡፡ ያኔ ሥጋውም፣ ደሙም የተደረገው በእውነት እውነት፣ በመንፈስ የተደረገ አልነበረም፡፡ ስለሆነም በፊደል የተደረገ የሚታየው ባለ መጋረጃ የጨለማ ሥራ ጥላ ነበር፤ አካሉ እስኪገለጥ በጊዜያዊነት ለማገልገል የተሰጠ ጥላ ነገር ነበር፡፡ ስለዚህም አካሉ በተገለጠበት በአዲስ ኪዳን ዘመን ልንጠቀምበት ብንፈልግ ደግሞም ጣኦት ነው የሚሆነው፤ ዓይንን የሚጋርድ፣ እግዚአብሔርን የሚከልል፤ በመጋረጃ እንድናየው የሚያደርግ







የእውርነት መንስዔ ነው የሚሆነው፡፡ እግዚአብሔርን በመጋረጃ ማየት ከመስቀል ማዶ በኩል ቀርቷል፡፡

«በዚያ ቀን እግዚአብሔር አንድ፣ ስሙም አንድ ይሆናል (ዘካ.14፡9፤)» የተባለው ስለተፈጸመ፤ ሥጋውም፣ ደሙም፣ ውኃውም፣ እንጀራውም አንድና አንድ ነገር ብቻ የሆነ እግዚአብሔር ለሁሉም ጉዳይ የማይጨመርበትና የማይቀነስበት ሆኖ ቀርቧል፡፡ በእግዚአብሔር ላይ ከቤታችን የሆነ ነገር፣ ምድራዊ ፍሬ (እንደ ቃየን) መጨመር ርኩሰት ነው፡፡ ሁሉ በክርስቶስ ትንሣኤ ተጠቅልሏል፤ ሁሉም ወድቆ ሰግዷል፤ ለእግዚአብሔርም እጅ ወደ ላይ ብሏል፡፡ ከእርሱ በውጭ ሌላ በአጠገቡ ምንም ነገር አይቀርብም፤ (ኤፌ.1፡10፤)

እንዲሁ በእግዚአብሔር መንግሥት አንድ ነገር እንጂ፣ ሥጋና ደም ተብሎ ዝርዝር ነገር ከቶ የለም፤ አንዱ ነገርም አንዱ እግዚአብሔር ነው፡ አንዱ እግዚአብሔር አንድ ሳይሆን ለዓለሙ ሁሉ በቅቶ የሚተርፍ እየፈለቀ የሚኖር የመብልና የመጠጥ ታላቁ (ድግስ) ነው፤ (ኢሳ.25፤6፤ ማቴ.22፤1-14)፡፡ አንድ ነገር በቋንቋችን አንድ ሲባል ቁመቱ፣ መጠኑና ልኩ ውስን ሲሆን ብቻ እንጂ መጠኑ፣ ልኩና ወሰኑ በሰው አእምሮ የማይለካውን ሰማይ፣ ከሰማያት በላይ ያለ ሰማይ ሊይዘው የማይችለውን (1ነገ.8፡27፤ 2ዜና.5፤18) ብቻውን ሁሉ በሁሉ የሆነውን እግዚአብሔር አንድ ነው የሚለው የሰው ቃል እንዳይለካውና መጠን በመስጠት የጣዖት ቅርጽ እንዳይሰጠው እጅግ መጠንቀቅ ይገባል፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚባለውም እግዚአብሔር በዙፋኑ ተቀምጦ የነገሠበት ክፍለ ዓለም ነውና፡፡

የሕይወትን ዛፍ ፍሬ የሆነውን ክርስቶስን ከማዕዱ ለመብላት አስቀድሞ ከዲያብሎስ ጋር ከማዕዱ የበላነውን የሞትን ዛፍ ፍሬ ከሕይወታችን ውስጥ ማስመለስ/መትፋት አለብን፡፡ ይህም፣ የእስራኤል ልጆች የሠሩትን

ጥጃ ያስታውሰናል፡፡ «ሰይጣን» በአሮን ጥጃ ጣዖቱ በኩል እስራኤልን አንበርክኮ እያሰገደ፣ የንግሥና በዓሉን ሲያከብርና ሲያስጨፍር ነበር ሙሴ ከተፍ ያለው፣ ከዚያም ሙሴ ምን አደረገበት? ሰባብሮት አንኮታኩቶት፣ አቃጥሎት ትቢያ እስኪሆን ድረስ ፈጭቶትና አድቆት እስራኤላውያንን መልሶ በማጠጣት ሁለተኛ በማይገኝ ሁኔታ ከምድረ-ገጽ እንዲጠፉ አደረገው፡፡ እነርሱም ጠጥተውታል/ውጠውታልና ከእንግዲህ የለም (ዘፀ.32፡20)፡፡ የተጠጣ፣ የተበላ ምን ይሆናል? መብል፣ መጠጥ ይሆናል አይደል፡፡ ይህ የጠጡትና የዋጡት የእስራኤል አምላክ ነበር ወይስ የአሕዛብ አምላክ ነበር? አማኝ የሚገድል ነገር ቢጠጣ ይጎዳዋል ወይ? (ማር.16፡18) መልስ አለው፡፡ እስራኤል በትራቸው የአሕዛብን በትሮች እንደዋጠ ሁሉ እንዲሁ አሕዛብን ከአምላኮቻቸው ጋር ጠቅልለው መዋጥ ነበረባቸው፡፡ ይህ እስራኤል ጣዖቱን ከነጥጃው መዋጣቸው በነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት መሠረት ክርስቶስ ሊመጣና ሰይጣንን ማለትም ሞትን ሊውጥ እንዳለው በተግባር የታየ ትንቢታዊ ድርጊት ነበረ፣ እንዲህ እንደ ተጻፈ፣ (.... ሞትን ለዘላለም ይውጣል፣ ጌታ እግዚአብሔርም ከፊት ሁሉ ዕንባን ያብሳል፣ የሕዝቡንም ስድብ ከምድር ሁሉ ላይ ያስወግዳል (ኢሳ.25፡8)፡፡ የክርስቶስ ሥጋ ሰይጣንን ከነኃጢአቱ ጠቅልሎበት መዋጫ አንቀልባ ነው፡፡ ሞትን ለዘላለም ይውጣል ማለት የሞት መርዝ የሆነውን ኃጢአትን፣ የኃጢአት ምንጭ የሆነውን እባብ ዲያብሎስን ሁሉ ጠቅልሎ ለዘላለም ይውጣል ማለት ነው፡፡ ሲሰድቡት አልተሳደበም፣ በሸላቾቹ ፊት ዝም እንደሚል በግ ዝም አለ ምን ማለት ነው? እንዳያፈተልክ ውጦት፣ ዘግቶ፣ ቆልፎ ይዞት ዝም ባለበት ሞቶ ደመሰሰው፡፡ አንድ አላመለጠም ሲገርፉት፣ ሲጎሽሙት፣ ሲተፉበት፣ በበትር ሲሉት፣ በምስማር ሲቸነክሩት ሥጋ፣ ማለት ሰይጣን ጮኾ ይውጣ፣ ያምልጥ ብለው ነበር፡፡ ነገር ግን የሚዘጋ፣ የሚከፍት የሌለ፣ የሚከፍት የሚዘጋ የሌለ ነውና ቆልፎ ይዞ ዝም አለና ሞቶ ድብን ብሎ ድብን አደረገው፣ እርሱ ግን በእምነት ስለሞተ ተነሣ፡፡







ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ፣ ማለት ‹‹ሞትን›› ሕይወት ዋጠው፣ ሐሰትን እውነት ዋጠው፣ ኃጢአትን ጽድቅ ጋረደው፣ ጨለማን ብርሃን ሸፈነው፣ ከደነው ከእግሩ በታች አደረገው፡፡ የሚገድል ነገር ቢጠጡም አይጎዳቸውም ተብሎ የተጻፈው ተፈጸመ፡፡ ደዌአችንና ሕመማችንን ሁሉ ወሰደ፡፡ እኛን የሚገድለው ደዌና ሕመም ነበር፡፡ «አንዱም ለአንዱ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች» ምድር በብርሃን ተሸፍናለች (ኢሳ.6፡3)፡፡ ምድርን ብርሃን ውጧል አሜን፣ ክርስቶስ ነገሠ፣ ተቆጣጠረ፣ ሁሉም ከእግሩ በታች ተገዛለት ማለት ነው፡፡

በመሠረቱ ቃል እግዚአብሔር ነው፣ (ዮሐ.1፡1)፣ ቃል መንፈስ ነው፣ (ዮሐ..6፡63)፣ ቃል ሕይወት ነው፣ (ዮሐ..6፡63)፣ ቃል ክርስቶስ የሕይወት ቃል ነው፣ (ዮሐ.6፡68)፡፡ ቃል ሥጋ ሆነ ማለት እግዚአብሔር ሥጋ ሆነ፣ ክርስቶስ ሥጋ ሆነ ማለት ሆኖ፣ አማኑኤል ሆነ፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ሆነ ማለትን ያረጋግጣል፡፡ ከዚህም ሌላ እግዚአብሔር ሰውን ሆነ ማለትን ሲያመለክት፣ በሌላ ሥፍራ ቃል ክርስቶስ የሥጋ ሁሉ ገዢ መሆኑን እናነባለን፣ (ዮሐ.17፡2) በሥጋ ላይ ሥልጣን ማለት፣ ሥጋን ማለት ሞትን ተቆጣጠረ፣ ከጫማው በታች አደረገው ብለን፣ ቃል ሥጋን (ሞትን) ዋጠው ከሚለው (ኢሳ. 25፡8)፣ ጋር እና፣ ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ ከሚለው (1ቆሮ.15፡54) ጋር ይስማማል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ቃል ፈጣሪ፣ ሕያው ሽክላ ሠሪ እንደ መሆኑ መጠን ቃል (ክርስቶስ) ሙሴ ሞክሮት የተወውን ማደሪያውን፣ ተንቀሳቃሽ መቅደሱን፣ መቀመጫ ዙፋኑንና የእግሩን ማረፊያ ሠራ፣ ፈጠረ ማለት መሆኑን (ሕዝ.43፡1-7፣ ቁ.7፣ 2ቆሮ.6፡16) ጠቅሼ አረጋግጣለሁ፡፡ ቃልም ሥጋ ሆነ፣ ጸጋና እውነትን ተሞልቶ በእኛ አደረ፡፡ ታላቁ መጋረጃ በሚለው ወደ ፊት በሚወጣው መጽሐፌ በስፋት ታትቷል፡፡

ሥጋ ሞት ነው፤ ሕያው ቃል አድሮ ለሞት ሕይወትን ሰጠ እንጂ፡፡ ክርስቶስ ሰይጣንን በሥጋው ጠቅልሎ (ተቆጣጥሮ) ውጦ ሞቶ ነው የገደለውና የደመሰሰው፡፡ ሥጋ ባይሆን ኖሮ ቃል ሰይጣንን ድል አይመታም ነበር፡፡ ክርስቶስ ሰይጣንን ወደ ውጭ ለእስራኤል፡ እስራኤልን ለማስለቀቅ (ነፃ ለማውጣት)፣ ወደ ውስጥ ለዓለም፣ ዓለምን ነፃ ለማውጣት ተዋጋ፣ እየተዋጋም ከተሸነጠበት ሥርቻ ሁሉ ያባርራል፡፡

ጌታ ኢየሱስ በእስራኤል ሲዋጋ ከሰው የሚወጣው ሰይጣን/ሞት ወዴት ይደርስ ነበር?

ሀ/ በአየር ላይ ይጠፋ ነበር?

ለ/ ባሕር ውስጥ ይገባ ነበር?

ሐ/ ወደ መሬት ይገባ ነበር?

መ/ ወደ ሌላ ሰው ይገባ ነበር?

ቢባል መልሱ፣ ዛሬ የእውነት እውነተኛ ወንጌል ሲተላለፍ ከሰው የሚወጣው ብዙ ጋኔን ወዴት ይገባል? የሚለው ጥያቄ መልሱ፣ መልስ ሲሆን፣ ያን ጊዜም ከሰዎች የሚወጣው ጋኔን ወደ አለቆች ይገባና ያስኮርፋቸው፣ ያስቆጣቸው፣ ክፋትን ይሞላባቸው፤ ሴራ ያስጠነጥናቸው እንደ ነበረ አሁንም ከሰዎች የሚወጣው ጋኔን ወደ አለቆች፣ ወደ አመራር አካላትና አጫፋሪዎቻቸው ይገባል፤ (ማር.3፡1-6፣ 12፡9፣ ሉቃ.13፡14፣ ዮሐ.9፡24፣ ዮሐ.5፡10-16)፡፡ መረጃው ምንድን ነው? ቢባል፣ ቀደም ሲል የተሰጠው መልስ ነው፡፡ ወደ እነርሱ ለመግባቱ፣ ማስቆጣቱ፣ ዓይናቸው ደም መልበሱ፣ ክፋትን መሞላታቸው፣ እውነትን የገለጠውን አገልጋይ ለማስጠፋት ሴራ ማስጀመሩ ሸር፣ ተንኮል ማስጠንጠኑ በግልፅ (በተጨባጭ) የሚታይ ነው፡፡ ጋኔኑ በእነርሱ ገብቶ እነርሱን ወደ ራሱ (ጋኔንነት) ይለውጣቸዋል፤ እውነት ነው፡፡ ከአሁን ጀምሮም ጋኔን መሣሪያውን አንግቦ ሠራዊቱን አሰልፎ ወደ ግልፅ ይወጣል፤ (ዮሐ.12፡31)፡፡ ተቃዋሚዎችን ክፋትን አስታጥቆ፤ ተንኮልን አጎናፅፎ እየነዳቸው







ወደ ውጭ ይወጣል መልእክቱ መጋረጃውን ከላይ እስከ ታች ቀድዶ ከፉውን ራቁት ያደርጋልና ዕፍረቱ ውጭ ሜዳ ላይ ይዘረገፋል (ኢሳ.3፡17)፡፡ እፍረቱ ምንድነው?

ያኔ አጋንንትን ያወጣ የነበረው ማን ሲሆን ዛሬ የሚያወጣውስ ማነው? ያኔም ያወጣ የነበረው እውነት ሲሆን፣ ዛሬም ያው እውነት ነው፡፡ እውነት ሲሰራጭ አጋንንቱ በአለቆች ውስጥ ሆኖ ሰላም ያጣል፣ መግቢያ መውጫ መድረሻ ያጣል፡፡ አሜን መድረሻ ይጣ!!

ክርስቶስ የሥጋ ሁሉ ማለት የአጋንንት ሁሉ ጠቅላይ ገዢ ነው፡፡ ክርስቶስ እንደ ሙሴ ለራስ ከሞት ርቆ ቆሞ ሌላውን ኃጢአተኛ ገዳይ ሳይሆን፣ ያለ ኃጢአት ሳለ በመሞት ኃጢአተኛውን ገዳይ ነው፡፡ ያለ ኃጢአት መሆኑ ነው ገዳይነቱ፡፡ አማኝ ማለት በሞት የሚጠመቅ ሰው ነው፤ አንጂ ከሞት ሸሽቶ ርቆ ቆሞ አሥር ጊዜ በኢየሱስ ስም!! የሚል መፈክረኛ አይደለም፡፡

ይህን የመሞትን እውነተኝነት ማረጋገጥ የምንችለው አስመሳይ ባልሆነ ጥምቀት እኛ ራሳችን ሞቱን በሚመስል ሞት ሞተንና ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ስንነሣ ነው (ሮሜ 6፡5)፡፡ ጥምቀት ማለትም፣ አዲሱ አዳም እንዲነሣ አሮጌውን አዳም በእውነትና በእምነት ሞቶ መግደልና ተቀብሮ መቅበር ነው፡፡ የዚህ ጽሑፍ ዋና ዓላማ ፍሬው፣ የእውነት እውነቱ ከገለባው፣ ከሐሰት እውነቱ የሚለይበትን አቅጣጫ ለመጠቆም በገለባው፣ በሐሰት እውነቱ ላይ ያነጣጠረ መልእክት ነው፡፡ አዲስ ኪዳን በመንፈስ እንጂ በፊደል አይደለም፤ አዲስ ኪዳን በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ የሚገዙበት እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ የሚገዙበት አይደለም፤ ስግደቱ በስውር በእውነትና በመንፈስ እንጂ በተራራም ሆነ፣ በኢየሩሳሌምም አይደለም፤ የተመለከትነው ምፅዋት፣ ጸሎት ፆም በስውር እንጂ ከንቱ በተባለው በአደባባይ (በግልፅ) አይደለም፤ (2ቆሮ. 3፡6፣ ሮሜ 7፡6፣

ዮሐ.4፡23-24)፡፡ በተራራ ማለት ምን ማለት ነው? በተራራ ማለት በከፍታ፣ ከፍ ብሎ ተኩራርቶ፣ ገዝፎ፣ ተጨብጭቦለት ማለት ነው፡፡

ደም ሳይፈስ ሥርየት የለም፤ የኃጢአተኛው ድፍርሱ (ቀዩ) ደም የክርስቶስ ንጹሕ ደም (ውኃውን) (ማቴ. 27፡3) የምህረትን ደም ሸፍኖ፣ አብሮ መሥዋዕት ሆኖ ሲፈስ ሥርየት ተገኘ ማለት ነው፡፡ ይህ እንዴት ይሆናል? ቢባል፣ መመሪያውን ከብሉይ ኪዳን እናገኛለን፡፡ በብሉይ ኪዳን አንድ ኃጢአተኛ ለኃጢአቱ የሚያቀርበውን እንስሳ (በግ) ይዞ ይመጣና በቤተ-መቅደስ ደጅ ካህኑ ፊት በጉ ራስ ላይ እጁን ጭኖ ኃጢአቱን ማፍሰሱ (መናዘዙ) የውስጡን ሰውሩን ርኩስ ደም በንጹሕ በግ ላይ ሲያፈስ (ሲናዘዝ) ትክክለኛው (የመንፈሱ በኃጢአት የተበከለው ደም) ከውስጡ ወደ ውጭ ፈስሷል ማለት ነው፡፡ ከዚያም የንፁሁ በግ፣ ንጹሕ ደም፣ ንጹሕ ስለሆነ ከኃጢአተኛው የፈሰሰውን ውኃ ርኩሰቱን (ድፍርሱን፣ ማለት ኃጢአቱን) ሸፍኖ አብሮ መፍሰሱ ነው፡፡ በዚህም በጉ ኃጢአትን/ሞትን ውጦ ሞቶ ኃጢአትን በንፁህ ደሙ ከደነው፣ ለዘላለም ባይሆንም ዋጠው ማለት ነው፡፡ ይህ ሊመጣ ያለውን ከጌታ ጎን ፈስሶ ኃጢአትን ለዘላለም ሊከድን፣ ሊውጥ ያለውን ውኃ ንፁህ ደም አመልካች ነበር፡፡

ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በጦር በተወጋ ጊዜ ከጎኑ ደምና ውኃ መውጣቱ በ(ዮሐ.19፡34) ይነበባል፡፡ ይህ ምን ማለት ነው? ኢ.መ.ት ደምና ውኃ መፍሰሱን ድነትና መንፃት ብሎታል፡፡ የዚህ ጽሑፍ-አቅራቢ ግን ደም ሳይፈስ ሥርየት የለም የሚለውን በማስታወስ፤ (ዕብ.9፡ 22) ደም ለመፍሰስ ውኃ እንደሚያስፈልገው አገናዝቦ፣ ደምና ውኃ ፍርድ /መሥዋዕትና ምህረት፤ ሞትና ሕይወት፣ ማለትም ደም፣ ሞት፣ መሥዋዕት ሲሆን፣ ውኃ፣ ምህረት ሕይወት ይላል፡፡ በቆሻሻ ደማችን ማለት በአመድ ዱቄት ገዛን፤ በአመድም ፋንታ አክሊልን (ኢሳ. 61፡3)፡፡





እንደዚህም ሲባል የጌታ ቀኝና ግራ እጅ መዘርጋቱ ይታያል፤ ቀኙ ምህረት ግራው ፍርድን ያመለክታል፡፡ በደም የተሸፈነ ውኃ፣ በሞት የተሸፈነ ሕይወት ነው፡፡ ሕይወት በደም ውስጥ የተሸፈነ ነውና (ዘሌ 17፡ 11፣ ዘዐ 12፡13)

ውኃ በደም ተሸፍኗል፡፡ ይህም ደምን አንቀሳቃሹም ሆነ ገላጩም ውኃው ስለሆነ ነው፡፡ ደም፣ መሥዋዕት ሲሆን፣ ውኃ፣ መሥዋዕቱን ማቅረቢያ፣ ማጓጓዣ (ማድረሻ) ማለት ነው፡፡ ደምን ውኃ ተሸክሞ በመውጣት ይገልፀዋል (ያሳየዋል) ከውስጥ ወደ ውጭ ያወጣዋል፡፡ ከጎኑ ደምና ውኃ መውጣቱ ደም በተለምዶ ውኃን ሸፍኖ ቀይ ብቻ ሆኖ ማለት እየከሰሰ (እየራጨኸ) (ዘፍ.4፡9/ለ) ይፈስሳል እንጂ እንደዚህ ሁለት ዓይነት በደም ያልተበከለ ውኃ በደም ከተበከለ ውኃ ጋር ጎን ለጎን ፍርድና ምህረት፣ ሞትና ሕይወት፣ ኃጢአትና ጽድቅ ሆኖ መፍሰሱ ነው ታሪካዊነቱ፡፡ በደም (የቀላ) ውኃ ካልቀላ ንጹሕ ውኃ ጋር ጎን ለጎን ፈስሷል፡፡ አሁን ደምና ውኃ እንዴት ከአንድ ቦታ፣ ባንድ ላይ ለየቅል ሆነው ይወጣሉ? ከሰው ጎን ቢሆን ደምና ውኃ ከአንድ ቦታ ለየቅል ታይቶ ከቶ አይወጣም፤ ይህ በእስራኤል (ለዮሐንስ) የታየው ከጌታ ኢየሱስ ጎን የፈሰሰው ደምና ውኃ የተለየና (ቅዱሱ) አስገራሚ ክስተት ነው፡፡ ደም ከውኃ ጋር ካልሆነ ፈሳሽ አይደለም፡፡ ደም የተባለውም ደም የተቀላቀለበት (የተበከለ) ውኃ ሲሆን፤ ቆሰሎ እየተሠቃየ እንዴት ያልቀላ ንጹሕ ውኃ ፈሰሰ? የሚለው ነው ጥያቄው፡፡ ዮሐንስ ባመለከተው (ዮሐ 19፡34) መሠረት ውኃውና ደሙ ሲፈስስ ለየቅል ሆኖ መታየቱ፡፡ የኃጥዑ፤ የነፍሰ-ገዳዩ ደም እንዲፈስስ፣ የጻድቁ ንጹሕ ደም ፈሰሰ፤ ፈስሶ አፈሰሰው እግዚአብሔር ማለት የሕይወት ውኃ እንጂ የሕይወት ደም አይደለም፡፡

ከፉን አትቃወሙ፣ ስለሚበድሉአችሁም ጸልዩ የሚለው ጌታ ለከፉ አድራጊዎች ራሱን አሳልፎ ከመስጠቱም በላይ ለአመፀኞችም ማለደ ተብሎ እንደ ተጻፈ በጸሎቱ ማለደላቸው እንጂ እንደ ሙሴያዊ አሠራር

የተደረገበትን ክፉ በክፉ በመመለስ አልተበቀለም፡፡ በቀል ለኔ ነው እንደ ተባለ ምህረትን ተሞልቶ ክፉን ተቀበለ፡፡ «የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለእናንተ መከራን ተቀብሎአልና፣ እርሱም ኃጢአትን አላደረገም፣ ተንኮልም በአፉ ውስጥ አልተገኘበትም፣ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፣ መከራንም ሲቀበል አልዛተም ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ (1ጴጥ.2፡21-23)» ተብሎ እንደ ተመሠከረ ሆኖ ተገኘና በእግዚአብሔር ከለላ ውስጥ ሆኖ ተልእኮውን ፈጸመ፡፡ ስለሆነ፣ ስለእናንተ የሚዋጋላችሁ እግዚአብሔር ነው፤ እናንተም ዝም ትላላችሁ፣ እንደ ተባለ እርሱ ዝም ስላለ እግዚአብሔር ከለላ ጋሻ በመሆን የሚያደርጉት ክፋት ወደ መልካምነት እየተለወጠለት ክፉዎችን ሥራቸው ራሳቸውን ይዋጋ ነበረ፡፡ አይታ·ይም እንጂ፡፡

ክርስቶስ አልፎ ስለተሰጠ ጠላቱ የጻድቁን ደም አፈሰስኩ እያለ ማንም ሳይነካው የገዛ-ራሱን ደም በገዛ-እጁ አፈሰሰ፡፡ ምን ማለት ነው? ቀዩ የሰው፣ የደም አፍሳሹ ደም በራሱ እጅ ሲፈስስ፣ ውኃው በጽድቅ የተበቃዩ (የክርስቶስ) ደም አብሮ ፈሰሰ፡፡ «የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» እንደ ተባለ፣ የተጻፈው ሕግ በራሱ ተግባራዊ ሆኖ (ዘኍ. 35፡33-34) ጽድቁ ለዘላለም ይኖራል፣ ተብሎ ተጻፈ፤ የጻድቁን ጎን የሚወጋው በሕጉ መሠረት ጎኑ ተወግቶ ይገኛል፡፡ በቀል የኔ ነው ተብሎ ተጽፎአል (ሮሜ 12፡19፣ ዘዳ. 32፡34-35)፡፡ ሕጉ ቃሉ ነው፣ ቃሉ ክርስቶስ (እግዚአብሔር) ነውና ሳይነካ ይበቀላል፡፡ «የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» ሲል የሚያደርጉትን የማያውቁት ምን ስለሆነ ነው? በጨለማ ስለ ሆነ ነው፡፡

(እግዚአብሔር በራሱ እግዚአብሔር እጅ አይበቀልም፣ በበደለኛው በራሱ እጅ እንጂ)፡፡ ይሁዳ አስቆሮቱን በራሱ በባለቤቱ እጅ ተበቀለው (ማቴ. 27፡3-5)፡፡ እግዚአብሔር ጻድቅ ነው፤ በደለኞችን ሥራቸው ገደላቸው፡፡







ፈርዖን ከነሠራዊቱ ማንም ሳያስገድደው በገዛ ራሱ ባህር ውስጥ ገብቶ ሰጠመ (ዘፀ. 14፡26-28)፤ እስራኤልን ሊዋጉ የተሰለፉ ምድያማውያን በገዛ እጃቸው ሰይፍ ተደመሰሱ፤ (መሳ. 7፡22) ...ወዘተ፡፡ የጻድቁን ደም የሚያፈስሰውን ደም እግዚአብሔር በጽድቅ ያፈስሳል? ይህ በትክክል በኢየሱስ በኩል ተፈጽሟል፣ ማለት ነው፣ እግዚአብሔር ለሚታመኑበት ጋሻ ነውና፣ (ዘፍ 15፡1)፤ ጦሩ በጋሻው ተመትቶ ወደ ወጋው ተመልሶ ባለቤቱን ሳያውቀው ይወገዋል፤ በኢየሱስ ላይ የተሰነዘረ ነገር ሁሉ በአምላክ ላይ የተሰነዘረ ስለሆነ ክፉ እቅዱ ሁሉ ተመትቶ በሰባት እጥፍ ተባዝቶ ወደ ባለቤቱ ይመለሳል፡፡ መልካም ሥራ ሲሆን በመቶ ይባዛል፣ (ማር.10፡29-30፣ ማቴ.19፡29-30)

ስለሆነም ኢየሱስ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነውና መቼም ስለማይቆስል አይደፈርስምና ምንጩ በንፅህና የተጠበቀ ነው፡፡ ቁስል ደግሞ ከእግዚአብሔር መራቃችንን ያረጋግጣል ኢየሱስ በውጭ ለመቁሰሉ ደም፣ በውስጥ ላለመቁሰሉ ውኃ (በውጭ ድፍርስ በውስጥ ንጹሕ፣) በውስጡ እግዚአብሔር ስላለ፣ የጌታው ደም ሲፈስስ የባርያው ደም ሊረጋ ከቶ አይችልምና የግድ የእርሱም ደም ባፈሰሰው ሁኔታ ይፈስሳል፡፡ በሞቱ ገድሎታል የሚለውንም እናስታውስ፡፡

የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነው ሰው የውጭና የውስጥ አካል ባለቤት ስለሆነ በውጭና በውስጥ (በፊደልና በመንፈስ) ደም አለው፡፡ ሲቆጣም ሰው ደሜ ፈላ ይላልና፡፡ የሚፈላው ደም የትኛው ነው? ቁሳዊው ወይስ መንፈሳዊው? ደም ደግሞ የደም ጥላ እየሆነ፣ ውጫዊ ደም ማለት ፊደላዊ (ፍጥረታዊ)ው የውስጣዊ ደም (የመንፈሱ) ግርዶሽ መሆኑን ቀደም ሲል አይተናል፣ ደሜ ፈላ የሚባለውም ውጫዊው ምስያ ደም ሳይሆን፣ ውስጣዊው በዓይን የማይታየው የእውነት እውነተኛው ደም ነው፡፡ ውጫዊው (መጋረጃው) ሲወገድ ውስጣዊው ይገለጣል፡፡ ደምና ውኃ ስንት ነገር፣ ስንት መልክ አላቸው? ደምና ውኃ ሁለት መልክ ሆነው፣ ውኃ

ብቻውን ንጹሕ ሲሆን፣ ደም ድፍርሱ ውኃ ነው፡፡ ደም ማለት ደም ያደፈረሰውና ደም ያላደፈረሰው ውኃ ማለት ነው፡፡ ውኃ ባይኖር ደም አይኖርም ከውስጥ ይቀራል እንጂ፡፡ ሊገለጥም፣ ሊታወቅም አይችልም፣

ታዲያ ደም ማለት የደፈረሰ ውኃ ማለት ነው ወይ? አዎን፣ ውኃ ብቻውን ሲሆን ንጹሕ ስለሆነ መልክና ቀለም የለውም፤ ድፍርሱን ውኃ ያለ መልኩ መልክ ሰጥቶ (ኮንኖ) ያደፈረሰው ነገር ደም ነው፡፡ ደም ኃጢአት ነው፡፡ የቀላ ውኃ በኃጢአት የተሸፈነ ውኃ፡፡ ክርስቶስን ቀይ ልብስ ያለበሱት ንፁሁን ሰው በኃጢአት ሲሸፍኑት ያለ መልኩ መልክ ሲሰጡት ነው፡፡ በውጭ ቀይ ቀቡበት የራሱ ያልሆነውን ከሌላ ቦታ አምጥተው ለጠፉበት፡፡ ‹‹የሥጋ ሕይወት በደም ውስጥ ነው›› (ዘሌ 17፡11) የሥጋ ሕይወት በደም ውስጥ የተሰወረው፣ የተከደነው ውኃ ነው፡፡ በመሥዋዕት ጊዜ ውኃ ደምን ተሸክሞ ወደ ውጭ ወጥቶ አጋልጦ ያስፈርዳል፣ ደም የሚረጨውም በውኃ አማካይነት ነው ፡፡ ከዚያም ውኃ ከደም ውስጥ ነፃ ይወጣል ተንኖ በነፋስ ላይ ተሳፍሮ ወደ መጣበት ባሕር ይመለሳል፡፡ በግፍ የፈሰሰ ደምም ውኃው ተንኖ ሲሄድ አፈሩ ላይ ስለሚቀር ምድርን ያረክሳታል፤ (ዘኁ.35፡33)፡፡ ያለ ቃል ኃጢአት ከሰው ውስጥ ወደ ውጭ ሊፈስና ሊጋለጥ አይችልም፡፡ በቃል አማካይነት ኃጢአት ተጋልጦ ይሠዋል፣ ይፈረድበታል፡፡ ያለ ኃጢአት የሆነ ቅዱስ ቃል ከእግዚአብሔር ስለሆነ ወደ እግዚአብሔር ይወጣል፡፡ ከቃልህ የተነሣ ትኮነናለህ፣ ከቃልህም የተነሣ ትጸድቃለህ (ማቴ.12፡36) ተብሎ ተጻፈ፡፡ ክፉ ቃል በኃጢአት ከደፈረሰ ምንጩ (ከልብ) ድፍርስ ሆኖ ሲፈልቅ፤ በደም እንደቀላ ውኃ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ፣ የጻድቅ ሰው ደም ቀለሙ በምን ተለይቶ ይታወቃል? የጻድቅ ደም ቀለሙ የማይታወቅ ነጭ ነው፤ የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም፣ ብርሃን ነው፤ ብርሃን ደግሞ ከኃጢአት ሁሉ ያጥባልና (1ዮሐ.1፡5-7፣ ቁ.7 ልብስ በጻድቅ ደም ሲታጠብ ነጭ ይሆናልና፣ ራዕይ







7፡13-14) ቀዩ ኃጢአትን ያሳያል፣ ውኃው ኃጢአትን ያጥባል፤ ለዘላለሙ አሜን፡፡

ያለ ውኃ ደም ሥራ የለውም ከቦታውም አይንቀሳቀስም፣ አይፈስስም፣ ነገር ግን ደም ውኃን ሸፍኖ፣ አቅልቶ፣ ጎልቶ ስለሚታይ ውኃ ተሰውሮ ደም ተብሎ ይጠራል፡፡ በአንድ ላይ ከፈሰሱት ደምና ውኃ ንፁሁ ደም (ውኃው)፣ የትኛው ሲሆን፣ ድፍርሱ ደም ቀዩ የትኛው ነው? ሕያው ደም ድፍርስ ያልሆነው ንፁሕ እንደ ብርሌ የሚንፀባርቀውና ከመቅደሱ (ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን) የሚወጣው (ሕዝ 47፤12፤ ራዕ 22፤1፤ ዮሐ 2፤19-22) ያለ ኃጢአት የሆነ ንፁሁ ውኃው ሲሆን፣ ምውት ደም፣ ድፍርስ የሆነው ቀይ ቀለም ደም ለበስ ውኃ ነው፤ ቀይ ፍርድን (በቀልን) ያመለክታል ነገሩ ውጭና ውስጥ ገጽ አለው እንጂ፡፡ ማሥረጃውም የሥጋ ሕይወት በደም ውስጥ ሲሆን (ዘሌ. 17፡11፣ ዘፍ. 9፡4)፣ የመንፈስ ሕይወት ግን በውኃ ውስጥ ነው፡፡ ማለትም፣ መንፈስ በቃል ውስጥ (አብ በክርስቶስ ውስጥ) ነው የማለትን የሚያመለክት ነው፡፡ ክርስቶስ ሕያው የሆነው በደም ሳይሆን፣ በመንፈስ ነው፣ (1ጴጥ 3፡18) በውኃ፣ ውኃ መንፈስ (እግዚአብሔር) ነውና፡፡ ኢየሱስ የተወለደውም ከደም ሳይሆን ከቃል (ከመንፈስ) ነበርና (ሉቃስ 1፡34-35) ሕይወትን የሚሰጥም መንፈስና ቃልም ነውና፤ (ዮሐ 6፤63) ስለሆነ፣ ደሙ የዲያብሎስ፣ ውኃው የክርስቶስ ነው፤ ሁለቱም ለየቅል ደም ናቸው፡፡

ስውሩ መንፈሳዊው ውኃ የሕይወት ቃል ወይም መንፈስ ነው፤ እርሱም ክርስቶስ ነው (ዮሐ 4፡10፣ ቁ.13-14/ን፣ ከ7፡37-39፣ 6፡68፣ 1ዮሐ.1፡1) እናመሳክራለን፡፡ ተቃራኒውም ክፉ መንፈስና ክፉ መንፈስ ካደረባቸው ዓለም ሰዎች የሚፈልቀው ቃል (መንፈስ) የሰውን ሕይወት የሚመርዘው፤ የሚያደፈርሰው፣ የሚያቃጥለው፤ የሚያረክሰው፣ የሚያቆሽሸው ትፋት የሆነ እንዲሁም ከአውሬው አፍ የሚጎርፈው ተቃራኒው የሞት ውኃ አለ፤ (ያዕ 3፤6፣ ራዕይ 12፡15-16፣ መዝ 18፡16፣ ራዕይ 17፡15/ን ብናመሳክር

ጭብጡ ግልጽ ይሆንልናል፤ አውሬው ሰው ነው፤ የአውሬው አፍ የሰው አፍ ነው፤ ሰው ለእግዚአብሔር አፍ መሆን እንደሚችል ሁሉ እንዲሁ የአውሬው አፍ ሆኖ ኖሯል፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ በእሳት ከተቀደሰ በኋላ ነው ሲናገር በተደጋጋሚ ይህ የእግዚአብሔር አፍ ነው ለማለት የደፈረው፡፡ (ቲቶ 1፡12፣ 2ጢሞ.4፡17፣ ኢሳ.65፡25፣ ዳን.4፡28-33) ይነፃፀር፡፡ ከሰው በውጭ ሜዳ ላይ አውሬ ከቶ የለም፡፡ የምድር አራዊት፣ የሰማይ ወፍ፣ የምድር ተንቀሳቃሽ፣ ሰጎን፣ ቀበሮ ሰው እንደሆነ ተጽፏልና፤ (ሆሴዕ 2፡20-22፣ ኢሳ. 43፡20-21)፡፡

ጌታ፣ ጌታ ስለሆነ፣ ሰማዕቱ እስጢፋኖስ ለገዳዮቹ ንጹሕ ደሙን መሥዋዕት አድርጎ ማፍሰሱን በ(ሐሥ.7፡60) ‹‹ጌታ ሆይ፣ ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው›› ሲል ምልጃውን ማቅረቡን ከ(ሉቃስ 23፡34) ጋር እንመለከታለን፡፡ ድፍርሱ የሙታን ማለት የኃጥአን ደም በቀልን የተሞላ ሲሆን፣ ንፁሁ የጻድቃን ሕያው ደም ነው ምህረትን የተሞላ ደም እንደ ብርሌ የሚያንፀባርቀውና ከመቅደሱ፤ ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚወጣው፤ (ሕዝ 47፡12፡ ራዕይ 22፤1፡ ዮሐ 2፡19-22) ውኃው ያለ ኃጢአት የሆነ ንጹሕ ሲሆን ንፁሁና ነጩ ደማችን የጠግነው የክርስቶስ ደም ነው፤ (ዮሐ 4፡10፣ ቁ.13-14) (1ጴጥ 3፡18) የሕይወት ውኃ የተባለውም መንፈስ መሆኑን (ዮሐ 7፡37-39 ቀ.39) ያስረዳል፡፡ (ከመንፈስ) ነበርና፣ (ሉቃስ 1፡34-35) ሕይወትን የሚሰጥም መንፈስና ቃልም ነውና፤ (ዮሐ 6፤63)

ከጎኑ ውኃ መፍሰሱ የጠላቶቹ ኃጢአትና ክፉ ሥራ በውጭ ማለት በመጋረጃው ላይ ማለት በውጭ አካሉ ላይ ከመድረሱ በስተቀር የኢየሱስን የውስጥ ንፅህና ሊያደፈርስ፣ ብርሃኑን አደብዝዞ ፊቱን ሊያጨልም አለመቻሉን ጨምሮ ይገልፃል፡፡ የአዳም ልጅ የተባልን ሰድብ ወይም አንድ ጥፊ ሲደርስብን ወዲያው ከመቅፅበት ከውስጥ አስከ ውጭ







ጨለማ እንለብሳለን፣ ሁለመናችን ይደፈርሳል፣ ከአንደበታችንም የሚወጣው ነገር መራራና ድፍርስ ይሆናል፡፡

ኢየሱስ፣ ቅያሜ ወይም የፊት መጨማደድ ሳይኖረው ለክፉ አድራጊዎቹ እንኳን ምህረትን ተሞልቶ ከውጭ በደረሰበት አደጋ ሳይሆን በገዛ ፈቃዱ መሞቱን በተጨማሪ እንመለከታለን፤ የጠላቶቹ ክፉ ሥራ ደሙን አለማሳደፉን፣ ብርሃኑን አለማጨለሙን ከጎኑ ከፈሰሰው ንጹሕ ውኃ ጋር ከአፉ የወጣው ምህረትን የተሞላ ቃል አረጋግጧል (ሉቃስ 22፡50-51፣ 23፡34)፡፡ ሰማዕቱ እስጢፋኖስም እንደዚሁ ተጨማሪ ምሳሌ በመሆን የጠላቶቹን ኃጢአት በገዛ ንጹህ ደም ሸፍኖ ተገኝቷል፤ ከበደላቸው በቃሉ ውሃ ረጭቷቸዋል (ሐ/ሥ 7፡60) ከበደላቸው በነፃ አሰናበታቸው፡፡ (…እኛም የበደሉንን ይቅር እንደ ምንል…አሜን፡፡)

ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ቢባል፣ መልሱ በእስጢፋኖስ ላይ ከሚወርድበት የድንጋይ ውርጅብኝና በእስጢፋኖስ መካከል ኢየሱስ ግልቃ ገብቶ ጋሻ ስለ ነበረ እነርሱ ጻድቁን ሲወግሩ እግዚአብሔርን ይወግራሉና የወጋሪዎች ድንጋይ፣ በዓለቱ ማለት በክርስቶስ እየተመታ ወደ ኋላ ተመልሶ ወጋሪዎቹን ይመታቸው ስለነበር እስጢፋኖስ በጌታ ከለላ ውስጥ ነበር፡፡ በሕጉ መሠረት በድንጋይ ወጋሪዎቹን ድንጋይ ይወግራቸው፣ ገዳዮቹን ይገድላቸው ነበረ እንጂ፣ እስጢፋኖስን አልነካውም ነበር ለማለት ነው፡፡ (ግልፅ ለማድረግ፣ የክርስቶስን መልእክተኛ መውገር ራሱን ክርስቶስን መውገር በመሆኑ የሚያደርጉትን የማያውቁ እውሮች ስለነበሩ፣ (ሉቃስ 23፡34) እስጢፋኖስን ወገርን ሲሉ የሚወረውሩት ድንጋይ የተገኙን ዓለት (ክርስቶስን) እየመታ ወደ ኋላ ወደ ወጋሪዎች ይመለስ ነበር ማለት ነው፡፡

አንባቢ ሆይ እስኪ ድንጋይን ከመሬት አንሥተህ ዓለቱን በቀጥታ ውገር፣ ድንጋይ፣ ድንጋይን መውገር ስለማይችል ተፈናጥሮ በሕጉ መሠረት ወደ ራስህ ይመለሳል፤ በቀጥታ ከሆነም አንተውኑ ይመታል፡፡ ሌላ ማስረጃ

ከተፈለገ እስራኤል ከግብፅ በወጡበት ሌሊት ጨለማውን እያበራ ከፊታቸው ይሄድ የነበረው የብርሃን አምድ፣ መልአክ ወይም ክርስቶስ ከግብፃውያን ጦር የእስራኤል ተገን ለመሆን ፈቀቅ አለና በግብፃውያንና በእስራኤል መካከል ጣልቃ ስለገባ በእስራኤል ላይ ያነጣጠረውና ያንዣበበው፣ በግብፃውያን ልብ የሠፈረው የሞት ጥላ (ጨለማ) የእስራኤል ኃይል በሆነው በክርስቶስ (በብርሃኑ) (ዘፀ.14፡19-20፤ ም.13፡21-22) ተመትቶ ወደ ኋላ ተፈናጥሮ ስለተመለሰ ለእስራኤል ያዘጋጁት የሞት ጥላ ለራሳቸው ሆነ፣ እንደ ቃየን ፊት ፊታቸው እንደ ጠቆረ ተጽፎ እናነብባለን፡፡ (ግብፃውያን ሊጠፉ ስለተወሰነ በዚህም አልነቁምና ያንዣበበው የሞት ጥላ ወደ ሞት ተለወጠ፤ ክብር ይሆን አሜን)፡፡ ይህ የብርሃን አምድ ከእስራኤል ፊት ሲሆን ብርሃን የነበረው ወደ ኋላቸው ሲያልፍ ግን ጨለማ መሆኑ ተለዋዋጭ መሆኑ ነው ወይ? አይደለም፤ እግዚአብሔር ለየሰው ሥራውን ገላጭ ብርሃን እንጂ ለእስራኤል ብርሃን ሆኖ፣ ለሕዝብ ተለውጦ ከቶ ጨለማ አይሆንም፡፡ እግዚአብሔር አንድ ነው፣ ማለትም ተለዋዋጭ አይደለም ማለት ነው፤ (ያዕ.1፡16-17)፡፡ የሰው ሥራ ማለት ሁል ጊዜም በልቡ ማለት በመዝገቡ የሠፈረው ነገር ማለት ነው፡፡ እንዲሁም ሰው የዘራውን ያጭዳል ማለት የልቡን ያጭዳል ማለት ነው እንጂ ከገዛ ማንነቱ በውጭ ሜዳ የዘራውን ማለት ከቶ አይደለም፡፡ አሁን ግብፃውያን ፊት የሆነው ጨለማ ለእስራኤል በልባቸው የሠፈሩት ሞት ነበረና ያንን የራሳቸውን ጨለማ እግዚአብሔር በብርሃኑ ኃይል ሥራቸውን በፊታቸው ከመግለፁ በስተቀር (እግዚአብሔር) ጨለማና ብርሃን የሆነ ሁለት ዓይነት ገጽታ የለውም፡፡ ግብፃውንያን በእስራኤል ያፈነጠቁት ጨለማ በእስራኤል ብርሃን ተጋጭቶ ወደ ራሳቸው ተመልሷል፡፡ የልባቸው ከሰው የተሠወረው በፊታቸው ተዘረጋ፡፡ በልብህ ያለው ብርሃን የሆነው ክርስቶስ ከሆነ በክርስቶስ የሆነ ሁሉ ያንተ ነው፤ በልብ ጨለማ የሆነው ዲያብሎስ ከሆነ በእርሱ የእርሱ የሆነውን ሁሉ ትወርሳለህ፡፡ ሁለታችንም እንጠንቀቅ፡፡







(ዘፀ.14፡19-20 ቁ.27-28፡፡) ለግብፃውያን በፊታቸው የተደቀነ ጨለማም በልባቸው መዝገብ የሰፈረ ሥራቸው ነበረ፡፡ ጨለማው የእስራኤል ጋሻ በሆነው በክርስቶስ ተመትቶ ወደ ራሳቸው ተመለሰ ሥራቸው ነውና)፡፡ በእስጢፋኖስ ላይ የወረደው ድንጋይ በዓለቱ፣ ክርስቶስ ላይ ይወርድ ስለነበረ ተፈናጥሮ ወደ ኋላ ሲመለስ ከወጋሪዎቹ ማንን አገኘ? ከወጋሪዎቹ ውስጥ በጥቂቱ ሳውልን አገኘ፡፡ እስራኤል እንዲድን ግብፃዊው፣ መንፈስ እንዲድን ሥጋ መሥዋዕት ሆኗል፤ ሕዝብ ለእስራኤል ቤዛ ነውና (ኢሳ.43፡3)፡፡ የጳውሎስ የቀድሞው ባሕሪ ለአዲሱ ሕይወት ቤዛ ሆኗል፡፡

የእስጢፋኖስ ገለባ በደስታ ተወቅቶና ተንገዋልሎ ሲወድቅ እርሱ ግን በእልልታና በሆታ ተዓምር በሆነ ሐሤት ተሞልቶ፣ ምርት ሆኖ ወደ ጎተራ ሲገባ፣ ሳውል ሥራው አገኘውና በፈረደበት ፍርድ በእስጢፋኖስ ቦታ ለውቂያ በአውድማው ላይ ቀረበ፡፡ ከዚያም ደግሞ ተወቃ፣ ተወቃ፣ ማለትም ለአርባ አንድ ሲጎድል አምስት ጊዜ በግርፋት፣ ሦስት ጊዜ በዱላ፣ አንድ ጊዜ በድንጋይ፣ በእሥራት በስደት፣ በሌላ ሌላ መከራ ተወቃ፡፡ በመጨረሻም ሲተረክ እንደሰማሁት ስለ ክርስቶስ አንገቱን ተቀልቶ በመሞት የሥራውን ዋጋ ለማግኘት ዕድለኛ ሆነ፡፡ እግዚአብሔር ክፉውን በመልካም የሚያሸንፍ፣ በመልካም የሚቀጣ ተአምረኛ አምላክ ነውና እንደ እስጢፋኖስም ሆኖ ተወቅቶ ወደ እግዚአብሔር ጎተራ ገባ፡፡

የተጻፈው እውነት ስለ ሆነ እስጢፋኖስ በእግዚአብሔር ከለላ ውስጥ ስለነበረ ኢየሱስን በአብ ክብር እያየ ወደር በሌለው ክብር በደስታ ባሕር ውስጥ «ይህችን ኃጢአት አትቁጠርባቸው ሲል የማለደው፡፡ በአብ ቀኝ ቆሞ የክብርን ብዛት አሳይቶት ባርያውን ላዳነ ጌታ አምላኬ ክብር፣ ምስጋና ይሁን፣ ለዘላለሙ አሜን፡፡ በዚህም የምንመለከተው ቀደም ሲል እንዳየነው ለእስጢፋኖስ ብርሃን፣ ለወጋሪወቹ ጨለማ ነበረ፤ (ከወዲህ ብርሃን፣ ከወዲያ ጨለማ)፡፡ ይህንም የሚገልፅልን ተጨማሪ ሐሳብ

እስጢፋኖስ ቃለ-መልእክቱን ሲደመድም ትኩር ብሎ ወደ ሰማይ ሲመለከት የእግዚአብሔር ክብር የሆነውን ብርሃን (ክርስቶስን) መመልከቱ ነው፡፡

ደምና ውኃ፡- «...ደምና ውኃ ወጣ» ውኃ ከደሙ ጋር የታየው፤ ቀስቲቱ ከደመናው ጋር እንደምትታይና ሕይወት ከሞት ጋር ይሆን ዘንድ ማዳን ከፍርድ ጋር ነው፡፡ ደመናው ውኃ አዘል ብቻ ሳይሆን፣ ቁጣ አዘልም ጭምር ነው፡፡ መብረቅም፣ ነጎድጓድም በረዶም፤ ውሽንፍርም ያካተተ ነው፡፡ ቀስቲቱ ቀልታ ደም በመሆንና በደመና በመታየት መብረቅም፣ ነጎድጓድም በረዶም፤ ውሽንፍርም ያካተተና በቁጣው የተሞላውን ጥቁሩን ደመና በመከላከል ሊመጣና ዓለምን ከጥቁሩ የእግዚአብሔር ቁጣ በደሙ ሊጋርድ ያለውን ክርስቶስን ታመለክታለች፤ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን፣ አሜን፡፡ እግዚአብሔርን ከቁጣው ለመመለስ ደም ሞት ነውና ሕይወትን ማለት ውኃን ጋርዶ መታየት አለበትና ነው፡፡ በደም ውስጥ ያልሆነ ሕይወት ሁሉ ጠፊ ነው፡፡ ደም ማለት ከፊት አልፎ፣ ጋሻ ሆኖ በመከለል ሕይወትን ከሞት ያድናል፡፡

ዲያብሎስ የአዳምን ልጆች በነኑ አሰልፎ በሰማያዊ ሥፍራ አየር ላይ (በተንጠለጠለበት) በጌታና በመሢሁ ላይ፣ በተጻፈው መሠረት ውጊያ ከፍቶ ነበር፡፡ በ(ራዕይ 12፡7-9፣ ኤፌ.6፡12) የተመለከተውን ሰማያዊ ሰልፍ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ጌታ ከተያዘበት ደቂቃ ጀምሮም ሥጋን፤ ሥጋ እንዲያንገላታው አሳልፎ በመስጠት ሰይጣን ከነሠራዊቱ ራሱ በራሱ እንዲገዳደልና እንዲተላለቅ አድርጓል፡፡ እኛ ሥጋውያን ሥጋን (ሰይጣንን) የገዛ ነፍሳችን አድርገን ስለምንመለከት ለእንዲህ ዓይነት ውርደትና ሥቃይ አሳልፈን አንሰጥም፤ ከራሳችን ልዩ አድርገን የምናይበትም ዓይን ገና አልተከፈተም፡፡ ሥጋ የሰይጣን አሳብን ያስተናግዳል ስለዚህም ማደሪያ፣ ካባ ቀሚሱ ነው፤ የውስጥ ልብሱም ውስጥ ሌላ አለ፡፡ ሥጋ ከሌለ ሰይጣን ለፍርድ ይጋለጣል ወደ ውጭ





ተጣለ፣ በንኖ ጠፋ ማለት ነው (ዮሐ.12፡31፡፡) የክርስቶስን ሥጋ ያንገላታው፣ ያሰቃየው የገደለው፣ በጦር የወጋው እግዚአብሔር ሳይሆን ሰይጣን ራሱ በራሱ መሆኑ ይገባናል፡፡ ሥጋን በማዋረድ በመደምሰስ ሰይጣን በጨለማ ያለ ዕውር ነውና ራሱን ደመሰሰ፣ ያለ ሥጋ ሆኖ ተራቁቶ ወደ ውጭ ሜዳ ተጣለ፤ (ዮሐ 12፡31)፡፡ ሞትን ስንመለከት ሥጋን እየተመለከትን ነው፡፡ ሰው ሥጋ የተባለውንና አካሉ (ሰውነቱ) ሆኖ የቀረውን አዳማዊ አሮጌ ማንነት ዘልሎ አልፎ ሰይጣንን መዋጋት ከቶ አይችልም፡፡ ጌታ ኢየሱስ በሥጋ ሁሉ ላይ ጌታ ነው ተብሎ የተጻፈው እርሱ የማን ጌታ ስለሆነ ነው? ያንተ/ቺ፣ የኔ? ወይስ የራሱ? «በመንፈሱ የሚገዛ ከተማን ከሚወስድ ይበልጣል...» (ምሳሌ 16፡32) ራሱን የማይገዛ የሌላውን ሰው ሥጋ ሊገዛ አይችልም፤ የውስጥን ዓለም የባሕርን ዓሦች፣ ሞገዱንና ማዕበሉን፣ የሰማይን ወፎች፣ በሰማይ የሚበርረውንና የሚከንፈውን፣ ውሽፍሩንና ወጨፎውን፣ ነጎድጓዱንና መብረቁን ጠቅልሎ፤ ምድርንና የምድርን አራዊት እንስሳውን፣ እባቡንና ጊንጡን {ሉቃስ 10፡ 20፣ መዝ.90፡13} በምድር ላይ የሚቅመደመደውን፣ የሚሽከረከረውን ፍጥረት ጠቅልሎ፣ እሾኹንና አሜከላውን፣ እባቡንና ጊንጡን፣ አንበሳውንና ድቡን፣ የምድር መናወጡን ሁሉ ሰጥ-ለጥ አድርጎ ከሚገዛና ከማንነቱ በርቀት ያለውን የውጭን ዓለም ከተማ ከሚገዛና ከሚቆጣጠር ማን ይበልጣል? በእርግጥም መንፈሱን የሚገዛና የሚቆጣጠር ሰው በእግዚአብሔር ሥልጣን ስለሚገዛ ከተማን በጡንቻና በጦር መሣሪያ ከሚቆጣጠር /ከሚገዛ/ ከሚቆጣጠር/ ሰው ይበልጣል ማለት ነው፡፡

የጌታን ሞት ስንመለከት፣ ኢየሱስ በተሰቀለበት ከፍታ ላይ ፈጽሞ መሞቱን ለማረጋገጥ ነው ጎኑን የወጉት፡፡ በተለምዶ ፈጽሞ ያልሞተ ሥጋ በተወጋ ወይም በተነካ ጊዜ ምን ይሆናል? ይፈጫል፣ ያለቅሳል፣ ይንፈራገጣል፤ ያጓራል፤ ይቆጣል፤ ያኮርፋል፤ ይናደዳል...፡፡ የሚፈጨውም፣ የሚንፈራገጠውም፣ የሚያጓራውም፣ የሚቆጣውም ሥጋው

ማለት ሰይጣኑ ነው እንጂ ሰውዬው አይደለም፤ አልሞት ባይ ተጋዳይ፡፡ ኢየሱስ (ሥጋው) ፈጽሞ ሞተ ማለት ኃጢአት ወይም ሰይጣን ፈጽሞ የለበትም ማለት ነው፡፡ አንተ ፈጽሞ ሞተሃል? ባንተ እየው፡፡ ኢየሱስ ከውጭ እስከ ውስጥ፣ ከሰው ፊት እስከ እግዚአብሔር ፊት ፈጽሞ መሞቱን በመጠራጠር በውጭ ብቻ እንደ አስመሳይ ጥሬና አታላይ ክርስቲያን መሰሎአቸው ለመፈተሽ ውስጥ-ውስጥ ድረስ አጥልቀው ወጉትና ተወግቶ ወጋቸው፡፡ ሥጋ ሞተ ማለት የሥጋ ሕይወቱ የሆነው ሰይጣን ወጣለት/ተለየው ማለት ነው፡፡ የማይታየውን የሰይጣንን መሞት የሥጋ ሞት ይገልጻል፡፡ አብን ፈጽሞ ያከብራል (ዮሐ.7፡49፣ ም.17፡4) ኢየሱስ ፈጽሞ ባይሞትና በተወጋ ጊዜ ቢጮኽ፣ ቢያለቅስ ቢንፈራገጥ ኖሮ ምን ይሆን ነበር? ጠሩ ለሥጋው ትንሣኤና ሕይወት ሰጥቶት ነበር ማለት ነው፡፡ እንዲህም ቢሆን ኖሮ ተሰቅሎም እንደማይሞተው የሽፍቶቹ ዓይነት ሥጋ ስለሚሆን ተቀጥቅጦ አጥንቱ ተሰብሮ ስለሚሞት ነፍሴን ከእኔ ማንም አይወስዳትም የሚለውም ትንቢት (ዮሐ.10፡17-18) ተሻረ፣ ሳይፈጸም ቀርቶ ነበር፤ እግዚአብሔር ሆይ ለዚህ ድንቅ አሠራርህ አመሰግንሃለሁ፡፡

ነገር ግን የሚደንቀኝና እያየሁ ዝም ማለት የማልችለው ነገር መጽሐፍም ሆነ፣ መጽሐፉን የሚየነቡ ኮፒ አድርገው የሚያወሩ ሰዎች የሚሉትን ሳያውቁ ኢየሱስ ሞተ ሲሉ መስማቴ ነው፡፡ ኢየሱስ ሞተ ማለት ምን ማለት ነው? ኢየሱስ ሞተ ማለት ሰው ወይም እንስሳ ሞተ በማለት ትርጉም እንደሚተላለፍ አገላለፅ ነው ወይ? የሚሞት ነገር ከምድር የሆነ፣ በሥጋው እንስሳ ቢሆን ነው አይደል? ከሞተም የሚበሰበስ፣ የሚተላ፣ የሚሸት መሆን አለበት፡፡ ኢየሱስ እንደዚህ አልሞተም፡፡ ሥጋውም እንደተለመደው ምድራዊ ሳይሆን፣ ከሰማይ የወረደ ለመሆኑ በሰፊ የብርሃን ምስክሮች ቃል ተረጋግጧል፡፡







አልሞተም ማለትስ? ምን ማለት ነው? ሞተ ማለት ያለ ኃጢአት ኖረ፣ ማለት ሆኖ፣ አልሞተም ማለት በኃጢአት ይነዳል፣ በኃጢአት ይመላለሳል ማለት ነው፡፡ የኢየሱስ መሞት፣ ከሰማይ መውረዱ እንደሆነ በዚህ መጽሐፍ ተገልጧል፡፡ በሌላ አንጻር ኢየሱስ ገዳይ ነው እንጂ ሟች አይደለም፡፡ እኔም፣ አንተ/ችም፣ ማንም፣ ሁሉም ከኢየሱስ ርቆ የቆመው ለምንድን ነው? አዳሞች ገና በሩቅ ድምጹን /ክርስቶስን ሲሰሙ ወደ ጫካ ጨለማ የገቡት ለምንድን ነው? ከሞት ነው ወይስ ከውርደት ነው? ቢባል ኢየሱስ ገዳይ ስለሆነ ብቻ ነው፡፡ ገዳይነቱ በገሃድ የሚታወቀው ዓይነት ነው ወይ? እርሱ ምንም ሳያደርግ ኢየሱስን በዓይኑ ያየ፣ ቃሉን የሰማ ሁሉ በገዛ-ራሱ ይሞታል፡፡ ይሞታል ማለትም ከተሰቀለበት ከሰማይ ከፍታ ኢየሱስ እስከ ደረሰበት ምድር ታችኛ ክፍል ድረስ ከኢየሱስ ጋር ይወርዳል ማለት ብቻ ነው፡፡ ሞተ!! በቃ፡፡ በዕብጠቱ፣ ትዕቢቱ ከፍታ ላይ መርገጥ፤ መዋረድ እንጂ የተለመደ ሞት አይደለም፡፡

የእስራኤል ልጆች «እንሞታለን» በማለት ርቀው የቆሙት ለምንድን ነው? ኢየሱስ ሞትን የማይፈራው ለምንድን ነው? ሞትን የሞተ ይፈራል ወይስ በሕይወት ያለ ይፈራል? በሕይወት ያለ፣ በሕይወት የመኖሩ ትርጉም ሞትን መፍራት ነው፡፡

ወደ ጀመርነው ሀሳብ ስንመለስ በጦሩ ቦታ ደም መውጣቱ ምህረት ለማድረግ በደልን መግለጥ ግድ ስለሆነ ነው (ኢሳ.6፡5-7) ምህረት በደሉን ለተረዳ ሰው ነው እንጂ በደፈናው፣ ባለቤቱ ጥፋቱን ሳያውቀው የሚደረግ ምህረት አይደለምና፤ ጥፋቱን ሊክድም ይችላልና፡፡ ,የኛው ካልቀላ (ካላደፈ) ይህኛው አያነፃምና፣ ካልቀላም ኃጢአተኛ፣ በደለኛ መሆኑ አልተገለጠም፡፡ ደም ከውኃ ጋር መፍሰሱ በደሉን ብቻ ሳይሆን ምህረቱንም መታጠቢያውን ጭምር በአንድ ላይ ገልጾ አቀረበለት ማለት ነው፡፡ ጭቅቅቱም፣ ውኃውም ይኸው ብትፈልግ ታጠብ ነው፡፡ ኃጢአታችን እንደ ደም ቢቀላ ነው እንደ ባዘቶ የሚነፃውና (ኢሳ.1፡18)፡፡

ክርስቶስ በግራው ሞት፣ በቀኙ ሕይወት መሆኑም በዚህ ትዝ ይለናል (ማቴ.25፡33- 34፣ ቁ.41)፡፡ ኢየሱስ በሥጋ የተገለጠበትን ተልእኮ ሥጋውን እየነዳ ስለፈፀመ አሁን በጦር ከመወጋቱም በፊት በራሱ ፈቃድ በመሞት ሥጋውን ማለት ሰይጣኑን ገድሎ ድል አድርጎ ጠብቋል፡፡ አለበለዚያ (ተቀጥቅጦ ቢሞት ኖሮ) ጀብዱው የሰይጣንና የመልእክተኞቹ ይሆን ነበር፡፡

የሞተ ሥጋ ማለት ከሰይጣንና ከኃጢአት የተለየ (ሥጋ) ማለት ነው፡፡ እንኳ አንድ ጊዜ ተወግቶና አሥር ጊዜ ቢወጉት ያለ ሰይጣን የሆነ ሥጋ አያምም፡፡ ሕመም ብቻ የሆናችሁት ከአደረባችሁ ከሰይጣኑ የተነሣ ነው፡፡ ጥዝጣዜ፣ መመረር፣ መከንከን፣ መገንፈል ...ወዘተ ከኃጢአት ወይም ከሰይጣን ነው፡፡ እስቲ ከክርስቶስ ጋር ሞቻለሁ ከሚሉት ክርስቲያን ጎረቤቶች፣ ጓደኞች አንዱን/አንዷን ፈጽሞ ሞቶ/ታ እንደሆነ ለመፈተሽ በአዲስ ኪዳኑ በምላስ ጦር ወጋ እናድርገው፣ ትንፍሽ! ሳይል ፀጥ ካለ አጥንቱ ከመሰበር ዳነ፡፡ ግን ከተንፈራገጠ፣ ካቃሠተ ውሸቱን ለማስመሰል የተሰቀለ ስለሆነ አጥንቱ ተሰብሮ ከተንጠራራበት ይወርዳል፣ ወሸቱ ይጋለጣል ይዋረዳል፡፡ ሥጋ ሞተ ማለት የሥጋ ሕይወት የሆነው እስትንፋስ (ሰይጣኑ) ወጣለት/በት ማለት ነው፡፡ ሥጋ የሚሞተው ሰይጣን ሲወጣበት ነው እንጂ ነፍስ ሲወጣበት አይደለም፡፡

በምድራዊ አካል በውጭ የሞተ ነገር በቀላል ስለሚታወቅ ወግቶ መፈተሽ አያስፈልግም ነበረ፡፡ ይህ በዘመኑ በእስራኤል ዓለም የተከሠተ ታሪክ መሆኑን መዘንጋት ስህተቱ ነው፡፡ በተለምዶ ፈጽሞ ያልሞተ ሥጋ በተወጋ ጊዜ ምን ይሆናል? እንደሚጮኽ፣ እንደሚያለቅስ፣ እንደሚንፈራገጥ፣ እንደሚንፈራፈር ሁላችንም ቢሆን እናውቃለን፡፡ ይህ የሚሆነው፤ ድረሱልኝ፤ አድኑኝ፣ በዳዩን ያዙልኝ፣ ተበቀሉልኝ ነው፡፡ መቼም ቢሆን ሥጋ የሚጮኸው ሰይጣኑ እንዳይወጣበት ለማዳን ለማቆየት አድኑኝ፣ ድረሱልኝ ለማለት ነው፡፡ ሥጋ፣ ሰይጣኑ ነው እንጂ







ተጨባጩ የአፈር አካል አለመሆኑን አንዘንጋ፡፡ ሰይጣን የማይታይ አካል መሆኑን እናውቃለን፤ ሥጋም እንዲሁ ተመሳሳይ የማይታይ ክፍለ-አካል ነው፡፡ እኛ በሥጋችን እንድንሰቀል ለማሳየት ኢየሱስ በሥጋ ተሰቅሏል፡ በሥጋ እንድንሞት ለማሳየት በሥጋ ሞቷል፡፡ ጳውሎስ በሥጋ ተሰቅሏል፡፡ ኢየሱስ ንስሓ የማያስፈልገው በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረ ትክክለኛው፣ የመጀመሪያው አዳም ይዘት የነበረውን ሥፍራ የያዘ ኋለኛው አዳም ነው፡፡ እርሱ የውስጠኛው ዓለም አካል የውስጠኛው ዓለም ሰው ነው፡፡ የውስጠኛው ዓለም ገዥ፣ የውስጠኛው ዓለም ንጉሥ ነው፡፡ ይህን የሚያብራራልንን አንድ ምሳሌ እንመልከት፡-

አንድ ጊዜ አንድ ሥጋዊ ሰው አንድ ክርስቲያን የሆነ ጎረቤቱን ልቅሶ ነገር አልደረሰም በሚል ሰደባሁ ብሎ «የሞትህ!!» ሲለው ክርስቲያኑ ሰውዬ ሰድቡን እንደ ውዳሴ ቆጥሮ ከደስታው ብዛት የተነሣ እግዚአብሔር ይመስገን! በማለት በምሥጋና ተቀበለው ከዚያም ተሳዳቢው ሰውዬ ያልጠበቀው ተገላቢጦሽ ሁኔታ ሲከሠት ጊዜ መደነቅና እፍረት ሆኖበት ነበር፡፡ የሞተ!! ማለት ምን ማለት ነው? የሞተ ማለት እኮ ቀደም ሲል እንዳየነው፣ ሰይጣን ወይም ኃጢአት የሌለበት ማለት ነው እንጂ በቁስ አካሉ የሞተውን እሬሣ የሞትህ!! ብሎ በጭራሽ አይሰድበውም፡፡ የሞተ!! የተባለው ሰው በሰዳቢው ቃል ሕይወት ዘርቶ፣ ትንሣኤ አግኝቶና ጠሩን ሰብቆ ጋሻውን አንግቦ በቁጣ ተሞልቶ ሰድቡን ለመበቀል ተፍጨርጭሯል ወይስ በሞቱ መጽናቱን ለመግለጽ የባሰውን ምሥጋና አቀረበ? ሰዳቢው፣ በሰድቡ ቃል ከሙታን ሊያስነሣው ሞክሮ ነበር፡፡

አንድ ጊዜ ደግሞ አንድን ወንጌላዊ፣ አንድ የሚያውቀው ሰው፣ ለሰላምታ ጢጋ የሚል መስሎ አንተ ሰው ለመሆኑ ‹‹ሰው ነህ? ወይስ ዝንጀሮ››? ብሎ ሲጠይቀው፣ ወንጌላዊው በድንገት ባልተጠበቀ ሁኔታ በደስታ እየፈነደቀ ድምፁን ከፍ በማድረግና እጁን ወደ ሰማይ በመዘርጋት ከፍ ባለ ቃል በመደጋገም እባክህን ጌታ እግዚአብሔር ሆይ!! እኔ ዝንጀሮ

መሆን እፈልጋለሁ፤ ሞቶ አፈር ከሚሆን በስተቀር ዝንጀሮ ምንም ኃጢአት ቢሠራ ስለማይመዘገብበት ዝንጀሮ አድርገኝ እርሱ የገሃነም ፍርድ የለበትም፤ ዝንጀሮ እንድሆን አንተም እባክህን በጸሎት እርዳኝ፣ ሲል ጊዜ ሰድቡን የሰነዘረው ሰውዬ ነገሩ ድንገተኛ ክስተት ሆነበትና ደንግጦ ፈዝዞ ዝም አለ፡፡ ይህ የሞተ ሥጋ ምሳሌ ማለት ነው አይደል?

ተሰዳቢው ተናድዶና ቆጣ ተሞልቶ ለበቀል ቢነሣሣ ኖሮ ምን ተፈጽሞ ነበር? ቢባል፣ መልሱ፣ ሰውዬው ሥጋውን ከሰቀለበት አውርዷል ማለት ነው፡፡ ሰውዬው በሞት በመጽናቱ እግዚአብሔር ሰድቡን በምስጋና ለውጦለት በመቀበሉ በሰዳቢው ላይ ምን ሥራ ሠርቷል? ራሱን በራሱ እንዲሰድብ፣ ራሱን በራሱ እንዲያዋርድና ቀላል ሰው እንዲሆን አድርጎታል፤ እንግዲህ በእጅ ሳይነኩ ማዋረድ፣ መግደል ማለት እንዲህ ነው፤ ሰድቡ ወደ ወጣበት ባለቤት እንዲመለስ ማድረግ፡፡ ቃሉ ከአፉ፣ የተላከበትን ሳይፈጽም በከንቱ ተዋርዶ ባዶ እጁን ወደ ባለቤቱ ተመልሷል (ኢሳ.55፤11) ተሰዳቢውም ሰዳቢውን በሞቱ ገደለው፣ (2ቆሮ.5፡14) በውርደቱ አዋረደው፣ የጌታን ምሳሌ ተከትሏል ማለት ነው አይደል? በጥቂቱም ቢሆን የጌታን ሥራ በተግባር ገለጠው፡፡

➢ የተሰደበው ሰውዬ በቁሳዊ ጦር ተወግቷል ወይስ በመንፈሳዊ ፍላጻ ተወግቷል?
➢ ከጌታና ከባርያው በአደገኛ ደረጃ የተወጋው ማን ነው?
➢ በፊደል (በቁሳዊ) ጦር በግልጽ ከተወጋው ጌታና በመንፈስ ጦር በስውሩ ከተወጋው ባርያ የትኛው ከፍ ያለ አገልግሎት ነው? በእርሱ ከእርሱ እንድንበልጥ የተነገረው የጌታ ቃል ይህ ነው፤ (ዮሐ.14፡12) ክብር ይሁን አሜን፡፡
➢ ከጌታ ቁስል ደምና ውኃ የፈለቀ ሲሆን ከባርያው የፈለቀው ምንድን ነው? ቁሳዊ ደምና ውኃን ካመነጨው ጌታና መንፈሳዊ ደምና ውኃ ካመነጨው ባርያ ማን ይሻላል?







➢ ከሰውዬው ከተወጋበት ቁስል የመነጨው ነገር ምንድን ነው?
➢ እንደ ጌታ ኢየሱስ ደምና ውኃ ፈሰሰው?
➢ ድፍርስ ደምና ውኃ ፈሰሰው ወይስ ንጹሕ ውኃና ደም ፈሰሰው?
➢ ከሰዳቢው ምንጭ ወደ ተሰዳቢው የፈሰሰው ንጹሕ ደምና ውኃ ነበር ወይስ ድፍርስ (አደፍራሽ) ደምና ውኃ ነበር?
➢ ተሰዳቢው በደስታ ምሥጋና ማቅረቡ ምንን ያመለክታል?

ስለዚህ ጌታ፣ ሰይጣን፣ ሰይጣንን እንዲዋጋ አድርጎ እርሱ ዝም ብሎ ይመለከት ነበር፤ (ዘፀ.14፡14) እስራኤላውያን ዝም ያሉት ጉዳይ የጌታ ባሕርይን የሚመለከት በመሆኑ ነው፣ እርስ በራሱ እንዲተላለቅ ማድረግ፤ በከበደ አድሮ ክፉ ሠሪም በበቀለ አድሮ ክፉ ሠሪም ክፉን በክፉ ያው ያው ክፉ ነው፡፡

እግዚአብሔርን የሚዋጋውን ፍጥረት ራሱ ይዋጋዋል፣ ቀኑና ሌሊቱም፣ በጋና ክረምቱም፣ መዝራትና ማጨዱም፣ ብርድናሙቀቱም፣ አየሩ ነፋሱም፣ ባሕሩ ውቅያኖሱም፣ እህሉና ውኃውም፣ መብሉ መጠጡም... ይዋጋዋል፤ በእግዚአብሔር ላይ በተነሣ ላይ፣ ይህ ሁሉ ይነሣበታል፤ ጀርባውን ላዞረበት ሁሉም ነገር ጀርባውን ያዞርበታል፡፡ ለኃጥአን የመጣ በመካከላቸው ለተቀመጡ ጻድቃን ይተርፋልና ስለዚህ ውጡና የተለያችሁ ሁኑ ተብሎ ተጻፈ (ኢሳ. 52፡11-12፣ ዘኁ. 16፡25-27፣ 2ቆሮ.6፡17-18)፡፡ ለሰው መልካሙም ክፉውም በውጭ ያለው ሁኔታ ሳይሆን በውስጡ ያለ መንፈሱ ነው፡፡ በውስጡ ያደረ መንፈሱ እንጂ በውጭ ከማንነት በርቀት ያለ ሁኔታ አይደለም፡፡ በውጭ ካንተ በርቀት በመሆኑ በጎም ክፉም የለም፡፡ በጎም በዓይንህ የምታየው ሆኖ ክፉም በዓይንህ የምታየው በሆኑ ነው፡፡ በውጭ ላሉት ክፉ የሆነ ነገር፣ በውስጥ ላሉት ከእግዚአብሔር ጋር ስለሆነ በጐ ስለሚሆን እንጂ የውጩ ሁኔታ ተለውጦለት አይደለም፡፡ እግዚአብሔርን ለሚፈሩት ግን በጎ ሕሊና ብሩክ አእምሮ ስለሚሆንላቸው ሁሉ መልካም ሆኖ ይለወጥላቸዋል፤ (ዘፍ.50፡20፤ ሮሜ.8፡28፤) መርዝ

መድኃኒት፤ ሞት ሕይወት ሆኖ፣ ጨለማ ብርሃን አጠፌታ (ብድራት) ሆኖ ይለወጥላቸዋል፡፡ ይህን በታሪክ ጥሩ አድርገን እናውቃለን፡፡ «በውኃ ውስጥ ባለፍህ ጊዜ ካንተ ጋር እሆናለሁ፤ በወንዞችም ውስጥ ባለፍህ ጊዜ አያሰጥሙህም፤ በእሳትም ውስጥ በሄድህ ጊዜ አትቃጠልም፣ ነበልባሉም አይፈጅህም፤ ኢሳ.43፡2» የተባለው ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

ክርስቶስ፣ ለሙታን ሕይወት፣ ለሕያዋን ሞት፣ ክርስቶስ ለሞተው መንፈስህ ሕይወት ሲሰጥ ገዳዩ ሥጋህ ብድሩን ይቀበላል፡፡ ለዕውሮች ብርሃን፣ ለሚያዩ ጨለማ፣ (ዮሐ. 9፡39) ለጠፉት መገኛ፣ ላልጠፉት መጥፊያ ነው (ሉቃስ 15፡25-32)፡፡ እርሱ ለሁሉ ብድር ከፋይ ነው፡፡ ስለ ክርስቶስ ይህችን ቅፅበታዊ ሕይወትህን ስለሰጠህ ብድርህን፣ ስለጠፋህ ብድርህን፣ ስለታወርክ ብድርህን፣ በእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ እንደ ተጻፈ ወለዱን ጭምር ታገኛለህ፤ (ማቴ.19፡29/ለ፣ ማር፣10፡29-30) ይታይልኝ አልዋሽሁም፡፡ በዲያብሎስና በአገልጋዮቹ በኩል ከአቤል ደም ጀምሮ በምድር ላይ ፈሰሶ በጨለማ ጥልቀት የተሸፈነውን (የተቀበረውን)፣ የጻድቃንን ደም ሁሉ ክርስቶስ በታላቅ ብርሃኑ መጋረጃውን ገልጦ፣ መክደኛውን ሰንጥቆ አልፎ የዲያብሎስንና የአጋሮቹን የዓመፅ ሥራ ሁሉ ይፋ ያወጣ ስለነበርና ወንጀለኞቹን ማንም ሳይጠይቅ ከፋ ሥራቸው ያገኛቸው ነበር፡፡

ክርስቶስ በዲያብሎስ ጨለማ መንግሥቱ ላይ ብርሃን ሆኖ መገለጡ ብቻ ራሱ ውጊያና ፍርዱ ነበረ፡፡ ማለት ተቃራኒው በክፋ ሥራው እንዲያፍርና እንዲዋረድ ከማድረጉ በስተቀር ምንም አልበደለም ክርስቶስ ማንንም ሳይፈርድ ለዓለም መገለጡ ብቻ ፍርድ ነው፡፡ ክርስቶስ ብርሃንነቱ ተፈጥሮው ነው እንጂ ለዲያብሎስ ሲል አሁን ብርሃን አልሆነምና፡፡ በደሉ እንዲጋለጥ ግን መብራት ሆኗል፤ በዚህም አልበደለም ግን ዲያብሎስ እንደበደለኛ ቆጥሮት መታሁት ሲል ተመታ፤ ደመሰስሁት ሲል ተደመሰሰ፡፡ በዲያብሎስ መንግሥት ጻድቅ ለዲያብሎስ የማይገዛና አልፎ







ተርፎም የዲያብሎስ ጉድ እንዲወጣ ምክንያት በመሆን የሚያዋርደው አመፀኛ ሆኖ ስለተገኘ ክርስቶስ ለዲያብሎስ ኃጢአተኛ ነውና፡፡

እንግዲህ በርቀት ቆመን ታሪካዊ ሥራውን እንድናደንቅና በቃላት እንድናወድሰው ሳይሆን፣ ክርስቶስ ፈለጉን እንድንከተል ነው፡፡ ተራውን የእኛ ሲያደርገው እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ ሲል በራሱ አክብሮ ሾሞናልና እንግዲህ እኛ አንባቢያን እስቲ ወገባችንን በእውነት ታጥቀን የጽድቅንም ጥሩር ለብሰን በተመሳሳይ የዓለም ጨለማ ከሆንንበት፣ የዓለም ብርሃን ለመሆን እንድንነሣ የበኩሌን ግብዣ በትሕትና አቀርባለሁ፡፡ የተጫነብን ብርሃን ምንድን ነው? ጨለማውስ ምንድን ነው? የተጫነብን ብርሃን የእግዚአብሔር ክብር መንጸባረቅ ሲሆን፣ ጨለማው የዲያብሎስ ክብር መንጸባረቅ ነው፡፡ በኛ ማን ይንጸባረቃል? ክርስቶስ የእግዚአብሔር ክብር መንጸባረቅ ነው፤ (ዕብ.1፡3፣ 2ቆሮ.4፡4) በተሾምህበት ክብር መመላለስ እንጀምር፤ ባርያ ከጌታው አይበልጥም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሕይወት ምንም፣ ማንንም በእጅ ሳንነካ ለዓለሙ ፍርድ፣ ውርደት፣ ሞት ይሆንበታልና አስቀድሞ ከቤተ-ሰብ ጀምሮ እንጠላታለን፣ እንሰደዳታለን፣ እንንገላታታለን፤ መጠላት፣ መሰደድ፣ መንገላታት እንጀምራለን፡፡ በነገር ሁሉ ለጌታ ክብር ይሁን፤ አሜን፡፡

ቃል፣ ውኃ ስለመሆኑ፤ (ኤፌ. 5፡26ለ፣ ዮሐ. 4፡13-14፣ ራዕይ 12፡15-16)

የደምና የውኃን ጥምረትና ልዩነት ስንመለከት በአንፃሩ ደግሞ የቃልና የውኃን አንድነትና ሞክሼነት መመልከቱ አስተሳሰባችንን ሰፋ እንዲል ያደርገዋል፡፡ በመስቀሉ ላይ ደምንና ውኃን ለያይቶ ማጋለጥና ማሳየት የቻለው ብርሃን የሆነው የክርስቶስ መስቀል በመካከል አልፎ መሰንጠቁ ነው፡፡

ነቢዩ ኤርምያስ በም.2፡13 እና በም.17፡13 ላይ እግዚአብሔርን የሕይወት ውኃ ምንጭ ብሎታል፡፡ በተመሳሳይም ጌታ ኢየሱስ እና ነቢዩ ኢሳይያስ

ቃሉን በውኃ መስለው በማቅረብ ለሕዝባቸው ጥሪ አድርገዋል፤ እንዲሁም በ(ዮሐ.7፡37-39) ባለው ክፍል ላይ ውኃና መንፈስ አንድ መሆናቸውን እናነብባለን፡፡ ከዚህም ሌላ የዚህ ተቃራኒ የሆነ ቃል (ውኃ) ሆኖ መጠቀሱን በ(ራዕይ 12፡15-16)ን ማንበብ እንችላለን፡፡

ቃል ውኃ ነው ሲባል ከቅዱስ መንፈስ የሚፈልቀው የተባረከና የሚባርክ፣ የሚያረካ የሚፈውስ ቃልና ከርኩስ መንፈስ የሚፈልቀው የሚያረክስ የሚያቆስል የሚያሳምም ቃል መኖሩን ልናስታውስ እንችላለን፡፡ ቃል ውኃ ነው ሲባል በቁሳዊው ዓለም ቋንቋ ነው ወይ? ቃልስ የውኃን ሥራ ሊሠራ ይችላል ወይ? ውኃ ከውጭ ወደ ውስጥ፣ ቃል ከውስጥ ወደ ውጭ ነው፡፡ ነቢዩ ሕዝቅኤል ጥሩ ውኃ የሚለውን፣ ነቢዩ ኢሳይያስ ወደ ውኃ ኑ የሚለውን፣ ኢየሱስ እኔ የምሰጠው ውኃ ከሚለው ጋር ስናስተያይ ውኃ፣ ውኃ ተራ የዕለት ተዕለት መጠቀሚያችን ውኃ ሳይሆን ቃል መሆኑ በግልጽ ይታያል፡፡ ደሙም ውኃውም የሚመነጨው ከእርሱ ቢሆንም የሕይወት ውኃ ምንጩ ክርስቶስ (እግዚአብሔር) ተባለ እንጂ ቀዩ ደም፣ የሕይወት ደም ምንጭ አልተባለም፡፡ ውኃ፣ ጥሩ ውኃ ተብሎ የተጠራው ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን እየተጣራ ሲወጣ እንደሆነ እንዲሁ በተመሳሳይ ቃልም መድኃኒትና ፈውስ መሆን የሚችለው ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን እየተጣራ ሲፈልቅ ነው፡፡ ይህንንም ከዚህ ውኃውንም ከመድኃኒት ምንጮች በደስታ ትቀዳላችሁ ከሚለው ጋር ስናገናዝብ የቃልንና የውኃን ሞክሼነት በእርግጠኝነት እንመለከታለን፡፡

የሰው ቃል እንደ ቃልና እንደ ውኃ ሲያገለግል፤ ሰው የእግዚአብሔር ምሳሌ ነበረና ተመሳሳይ በሆነ መንገድ በተቃራኒ መንፈስ ስለ ተጠመቀ የንን የምሳሌነቱን ኃይል፣ ጥበብና ክብር ለተቃራኒ አገልግሎት ለኃጢአት ከመጠቀሙ በቀር፤ በዚህ ኃጢአተኛና ተቃራኒ በሆነ ቃሉ በውጪው ዓለም ከፍ ያለ ሥራ መሥራት ችሏል፡፡ ሰው በቃሉ ያንቀላፋውን ጠርቶ ያስነሣል፡፡ የጠፋውንና የራቀውን ጠርቶ ያቀርባል፤







ያመጣል፡፡ በክፉ ቃሉ ረግሞ፣ ሰድቦ የሰውን ውስጣዊ ሕይወት ይመርዛል፤ ያቆሸሻል፤ ያቆስላልም፡፡ በመልካም ቃሉ ይፈውሳል፣ ያጥባል፣ ይጠግናል፡፡ ደግሞም ይህን በተፈጥሮም ያደርጋል፡፡ በጽድቅ ደረጃ፣ ይስሐቅ በቃሉ ባርኳል፣ ረግሟልም፡፡ ያዕቆብ፣ ሙሴም እንደዚሁ በአንደበታቸው ባርከዋል፣ ረግመዋልም፡፡ በለዓምም እንዲሁ ባርኳል፤ ረግሟልም፡፡ ኢየሱስ በቃል ከኃጢአት፣ ከበሽታም ያነፃል፣ ይፈውሳል፡፡ እስጢፋኖስ በቃሉ ለገዳዮቹ በደልና ኃጢአት ይቅርታን ለመነ (ሐሥ.7፡59-60)፡፡ ሰው በቃሉ ይኮነናል፤ ያጸድቃልም (ማቴ.12፡36-37)፡፡ ከቃሉ የተነሣም ሊኮነንና ሊጸድቅ ይችላል፡፡

ሰው ቃሉን በርቀት ልኮ ማሳደድ፣ ማስደንገጥ፣ ማንቀጥቀጥ፣ ሰማይንና ምድሩን ማለትም የሰውን ውስጥና ውጪን፣ መንፈሱንና ሥጋውን በቃሉ ማናወጥ፣ ማርበትበት ይችላል (1ነገ. 19፡1-4)፡፡ የዳዊት ቃል በሰሎሞን ሥጋ አድሮ፣ የሰሎሞን ቃል በበናያስ ሥጋ አድሮ አዶንያስንና ኢዮአብን ወዘተ...ገደለ (1ነገ. 2፡5-32)፡፡ በበናያስ ሥጋ የሰሎሞን ቃል ስንት ሰው ገደለ? በኢያሱ ሥጋ አድሮ የሙሴ ቃል አማሌቅን እንዴት አሳደደ /ደመሰሰ/? ቃላችን ደግሞ ውኃ ሆኖ የሚያገለግል በመሆኑ በኃጢአት የቆሸሸ ውስጣችንን፣ የረከሰ ደማችንን ከኃጢአት ርኩሰቱ ከውስጣችን አጥቦ አንጽቶ ጭቅቅቱን ተሸክሞ ወደ ውጭ አውጥቶ በመድፋት (ኑዛዜ) ያነፃናል፡፡ ከቃላችን የተነሣ ታጥበን እንጸድቃለን (ማቴ.12፤36)፡፡ ቃላችን ኃጢአታችንን ከውስጣችን አጥቦና መሥዋዕት አድርጎ ወደ ውጭ ሜዳ በማፍሰስ ያነፃናል፡፡ የረከሰ ነገር ሁሉ ከውስጣችን ወደ ውጭ ወጣ ማለት ርኩስ የሆነውን ሁሉ አውጥተን መጣል፤ መትፋት፣ ማስመለስ፣ ማጋለጥ፣ ማዋረድ፣ ማርከስ፣ መናዘዝ ...ወዘተ የምንችለው በቃላችን አማካይነት ነው፡፡ ቃል ውስጣዊ፣ መንፈሳዊ መጥረጊያ እጃችንም መንፈሳዊ ትውኪያ ማድረግያም ጭምር ነውና፡፡

ኃጢአት ማለት ሞት፣ ርኩሰት ማለት ነውና፣ ሞትን፣ (ኃጢአትን) በቃል አማካይነት መግለጽ፣ ደምን በውኃ አማካይነት ከማፍሰስ ይበልጣል፡፡ ቃል ደግሞ ውስጣዊ ውኃ ነውና፡፡ የእውነት እውነትን ደም ስለ ማፍሰስ፣ ለአመለካከቱ ምሳሌ የሚሆኑ በርከት ያሉ ታሪኮች ቢኖሩም ተነግሮኝ የሰማሁትን አንድ ታሪክ ምሳሌ አድርጌ ላቅርብ፡፡ ‹‹ሲዳማ ዳዋዌሳ›› በተባለ ቀበሌ የሚኖሩ አንዲት እግዚአብሔርን የሚፈሩ፣ እማዬ የተባሉ ባልቴት ነበሩ፡፡ አንድ ቀን ለአጠቃላይ ክርስትያኖች ኮንፍራንስ ላይ ለሕዝቡ የተዘጋጀውን ምግብ እንዲጠብቁ ታዝዘው ብቻቸውን ነበሩ፤ በወቅቱ ርቦአቸው ስለነበር ከዚህ ምግብ ብዪ-ብዪ!! ተቆጥሮ ተሰፍሮ አልተሰጠሽም እኮ! የሚል ስሜት ወጥሮ በመያዝ ስለተፈታተናቸው ተሠቃዩና የሚሆኑትን አጥተው በአካባቢው የነበሩ ሰዎች ሁሉ እስኪሰሙ ድረስ ጮኸ በማለት «በልሎ መገኖ፣ እት ያኖኤዌ» እያሉ ዑዑታቸውን አቀለጡት፡፡ ከዚያም ይህን የሰሙ ሰዎች ከያሉበት በመምጣት ስለደረሰባቸው ነገር ቢጠይቋቸው፣ እንዲህ አሰቃይቶኝ ማምለጫ አጥቼ ጮኽኩ በማለት የከፉውን ደም ከገዛ ደማቸው ጋር አፈሰሱት፤ በጩኸት ራሳቸውን አዋርደው ከፉውን አዋረዱትና ነፃ ወጡ፤ (ጸሓፊው ሊለው የፈለገውን ነገር በራሱ አባባል አቅርቧል፡፡) ኃጢአትን ማስወገድ እንደዚህ ነው እንጂ፣ ከሰውዬው ነጥለን ብቻውን ውጣ!! እናስወጣለን!! እያሉ የታመመን ሰው ማሰቃየት አይደለም፡፡ ከእንደዚህ ያለው ጭፍን አድራጎትና የጌታን ቅዱስ ሥራ ከማራከስ፣ ተጠብቀን በቀረበው ምሳሌ መሠረት የስህተት አሠራርን አስወግደን ከድርጊቱ እንድንመለስ በዚህ አጋጣሚ እመክራለሁ፡፡

ከጭፍሮች አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው ሲባል፣ ዓይኑ እንደምታይና ጆሮው እንደምትሰማ በውጭ ማለት በመልክ ፈራጅ በሆነው ሰው ፍርድ፤ የወጋው ከጭፍሮች አንዱ ነው፡፡ ይህ ፍርድ ግን በሐሰት እውነቱ በፊደል መፍረድ ነው፤ በመልክ መፍረድ ነው፡፡ በዚህም ሰው በጨለማው







የዲያብሎስ ወንበር ተቀምጦ ፈራጅ ስለሆነ፣ ሁልጊዜም ለዲያብሎስ በመወገን ፈራጅ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፍርድ ግን እንዴት ነው? ወታደሩ አልወጋም ማለት ነው ወይ? የእግዚአብሔር አዳኝነቱ ዓይኑ እንደምታይ በመልክ የማይፈርድ፣ ጆሮው እንደምትሰማ የማይበይን (ኢሳ.11፡3፣ ዮሐ.7፡24) ስለሆነ፣ በመልክ በወታደሩ ላይ ሳይሆን፣ በወታደሩ ተጋርዶ ወታደሩን ልኮ በወጋው መንፈሱ ላይ በመሆኑ ፍርዱ የእውነት እውነተኛ ነው፡፡ ለእግዚአብሔር የሚፈርዱትም በነጩ በእግዚአብሔር ዙፋን ተቀማጮች ዓይናቸው መጋረጃውን አሻግሮ አይቶ የሚፈርዱ በመልእክተኛው ሳይሆን በላኪው ላይ፣ በመኪናው ላይ ሳይሆን በነጂው ላይ የሚፈርዱ ለአምላካችን ነገሥታትና ካህናት የሆኑ ናቸው፡፡ ለዲያብሎስ የሚፈርዱ በነጂው ላይ ሳይሆን በመኪናው ላይ የሚፈርዱ በጨለማ ዙፋን የሚቀመጡ ዕውሮች ስለሆኑ ፍርዱ በራሳቸው ላይ ነው የሚዞረው፡፡

ሰው በዓይኑ አይቶ በእርሱ ላይ እንዳይፈርድበት ዲያብሎስ የሰውን ሁሉ ዓይን ያሳወረ ስለሆነና ክፉ ሥራውን የሚያይ አንድም ሰው ስለማይኖር ጭፍራውን (ወታደሩን) አስወንጅሎ (አስኮንኖ) ለራሱ ለማምለጥ በወታደሩ ውስጥ ምሽግ ይዞ የጌታን ጎን በተከራየው በወታደሩ እጅ ወግቷል፡፡ ዲያበሎስ በጭፍራው ማለትም በወታደሩ መጋረጃነት ስለተሰወረ በሰው ዘንድ የሚወነጀለው (የሚኮነነው) በግልጽ የሚታየው አካል ወታደሩ ነው፡፡ የማይታየው አካሉ ተሰውሮ ስለቀረ እስካሁን መጽሐፉ ጭምር ጭፍራውን እየወነጀለ ኖሯል፡፡ ይህም ዲያብሎስ ጦሩን ለመያዝ ቁሳዊ እጅ ስለሌለው በተከራየው እጅ ተጠቅሞ ነው ተልእኮውን የፈጸመው፡፡ በእውነት እውነቱ ማለትም ውስጣዊ በሆነው እውነት የጌታን ጎን የወጋው ዲያብሎስ ራሱ ሲሆን፣ በሐሰት እውነት ማለትም በውጫዊ እውነቱ የወጋው ወታደሩ ነበር፤ በድርጊቱ ውጩና ውስጡ በኅብረት የተቀናጁ ቢሆኑም፣ ኢየሱስ ውጭን ልብስን የተወጋ ሲሆን፣ ወጊው ግን ልብን፣

ውስጥን ነው የተወጋው፡፡ (ዮሐ.2፡19-22፣ ክራዕይ 21.22) ጋር እናመሳክር፡፡

ጌታን እስኪወጉት ድረስ ወታደሩና የወታደሩ መንፈስ አንድ ነበሩ፡፡ ነገር ግን ከወጉት በኋላ ማቴዎስ እንዳረጋገጠው ጎብረታቸው መፍረሱ ይታያል፡፡ ማለትም በማቴ.27፡54) ላይ «የመቶ አለቃም ከእርሱም ጋር ኢየሱስን የሚጠብቁ መናወጡንና የሆነውን ነገር አይተው ይህ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ ብለው እጅግ ፈሩ» የሚል ይነበባልና፡፡ እዚህ ላይ በእርግጥ መጸጸታቸው ይታያል፡፡ በዚህም ሰዎቹ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን መቀበላቸው ስለሚታይ በወታደሩ አድሮ የወጋው ክፉ መንፈስ ከወጋው ወታደር ተወገቶ መውጣቱ ይታያልና፡፡ ክርስቶስ በክፉም ቢሆን የነካው ይፈወስበታል፣ ክብር ለእርሱ ይሁን፡፡ እንግዲህ ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው በሕጉ መሠረት የወጋ ይወጋል፣ ያውም ጻድቁንና ቅዱሱን የወጋ እንዴት ይበልጥ አይወጋ!! ጻድቁ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለሆነ ገና ከመወጋቱ ወዲያው ይፈውሰዋል የሚለው ዲያብሎስ ራሱን በራሱ እንዲደመሰሰው አደረገ ከሚለው ጋር እንዴት ይጣጣማል?

- የኢየሱስ ግራ እጁ የማልኮስን ጆሮ ቆርጦ ከመጣሉ ፍጹም እንዳልተቆረጠ አድርጎ ቀኝ እጁ ወዲያው ፈወሰው፤ (ዮሐ.18፡10) ለማለት ይቻላል፡፡ ጴጥሮስ በወቅቱ ገና ወደ ቀኝ እጅነት አላለፈም ነበርና፡፡
- ምድር፣ ከፈሰሰባት ደም የምትነጻው በደም አፍሳሹ ደም ነው፣ የሚለው (ዘኁ.35፡33) ለዚህ መልስ ይሆናል፡፡ ከዚህም ሌላ፣ በዘጸ.21፡ 23-25 የተመለከተው ‹‹ያረገዘች ሴት ጉዳት ግን ቢያገኛት ሕይወት በሕይወት፣ ዓይን በዓይን፣ ጥርስ በጥርስ፣ እጅ በእጅ፣ እግር በእግር፣ መቃጠል በመቃጠል፣ ቁስል በቁስል፣ ግርፋት በግርፋት ይከፈል››፣



የጌታ ሥጋ መድረሻና ምንነቱ፣

የሚለው በገዛ እጅ መበቀል ሆነ እንጂ ለተበቃዩ መፈወሻ ነበር፡፡ እንደተደረገብን እንዲሁ ማድረግ ለጊዜው መፈወሻ ነው (መሳ.15፡9-11)፡፡ ኢየሱስን የወጉት በጥላዊው (በፊደላዊ (ፍጥረታዊው)) ጦር የፊደል አካሉን የወጉት ሲሆን፣ ክፉን ለመልካም በመለወጥ ደምና ውኃ ፍርድና ምሕረት ተገልጦ የጌታ ቀኝና ግራ እጁ ለጠላቶቹ መዘርጋቱ እንዲገለጥ አድርጓል፡፡ ወታደሩ የሚያደርገውን የማያውቅ ዕውር ሆኖ ጌታን ወጋሁ አለ እንጂ የመንፈሱ የሆነውን እውነተኛ ጦር ወደራሱ ተመልሶ በገዛ-እጁ ተወግቷል ማለቴ ነው፡፡

በሌላ አንፃር ደግሞ ወታደሩንና የወታደሩን ክፉ መንፈስ ሳመለየትና ከመንፈሱ እጅ ወታደሩን ለመንጠቅ ክፉን በመልካም አሸናፊ የሆነው ክርስቶስ በመካከላቸው ጣልቃ ገብቶ መሞቱን እንመለከታለን፡፡ ወታደሮቹንና ክፉውን መንፈስ አለያየ፡፡ እርሱ ሊገድሉት ከያዙት ጠላቶች ጆሮው የተቆረጠበትን ሰው በዚያ በቀውጢ ወቅት እንኳ ክፉን በመልካም በማሸነፍ የፈወሰ ነውና የማዳኑ ተአምር፣ የእይታው አድማስ የማይወሰንና የማይመረመር ጥልቅ ነው፤ እይታውን ሁኔታዎች አይገድቡትም፡፡ ይህን አሳብ ወደ ፊት በሚወጣው «ክርስቶስ በሙታንና በሕያዋን መካከል» በሚለው መጽሐፌ በግልጸት ያገኙታል፡፡

በሕጉ የደም አፍሳሹ ደም አድሮ ውሎ ይፈስሳል፤ በመስቀሉ ላይ ግን ንጽሑን ደም ያለ ኃጢአት በራሱ ፈቅዶ የሞተውን ወግቶ ደም አፍስሷልና ባፈሰሰበት ተግባሩ ደሙም አብሮ (በአንድነት) ፈሰሰ፡፡ በሕጉ «የሰውን ደም የሚያፈስስ ሁሉ ደሙ ይፈስሳል፣ ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጥሮታልና፣ ዘፍ.9፡6» ቀደም ሲል ይህን አይተናል፤ እዚህ-ጋ ልብ ማለት ያለብን፤ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረው ሰው እርሱ ማን ነው የሚለውን ነው? አዳም ነው ወይስ ሰው ተብሎ የሚጠራው የሰው ልጅ ሁሉ ነው? በእግዚአብሔር መልክ ምሳሌ የተፈጠረው አዳም የእግዚአብሔር መልክ ምሳሌነት መንጸባረቁ ወደ ትውልዱ ሁሉ

ተላልፏል ወይስ ወዲያው በሰይጣን መልክ ምሳሌ ተለውጦ ከስሟል? አመድ ሆነ ወይ? (ሕዝ. 28፡18)፡፡

አሁን በአጭሩ ስንመለከት የእግዚአብሔር መልክ ምሳሌ፣ ቋሚውና ትክክለኛ ነጸብራቁ ከክርስቶስ ኢየሱስ ሌላ እኔ ክርስቶስን እመስላለሁ የሚል ካለ በቀር የለም፤ (2ቆሮ.4፡4፣ ቆላ.1፡15፣ ዕብ.1፡3፤) በመሆኑ፣ የሰውን ደም የሚያፈስስ ሁሉ ደሙ አውቆ በራሱ ፈርዶ ይፈስሳል፣ ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጥሮታልና የተባለለት ክርስቶስ ኢየሱስ ስለሆነ፣ የእግዚአብሔር መልክ ምሳሌና ክቡር፣ ቅዱስ የሆነውን ሰው የክርስቶስን ንጹህ ደም ለፍተሻ ወግቶ ያፈሰሰው ሰው ደም ወዲያውኑ በጣምራ ፈሰሰ፤ ክብር ይሁን አሜን፡፡ (የደሙ መፍሰስ ባይታይም ተሰምቷል)፤ ይህስ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ የሚለው የውስጡን መሰበር የሚያሳይ ነውና፡፡

ከክርስቶስ ጎን የወጣው ቀዩ ደም የብሉይ ኪዳንን ደም ሲደመድም፣ (ሲዘጋ፤) ውኃው አዲስ ኪዳንን ይከፍታል፡፡ ቀዩ ቀይነቱ በቀለሙ (በመልኩ) የሚታይ በመሆኑ ጨለማ ነው፤ ይጋርዳል፡፡ ውኃው ቀለም አልባ ስለሆነ ብሩህ ሆኖ፣ ያሳያል፡፡ አሮጌው የብሉይ ኪዳን ባለ ግርዶሽ ደም ለአዲሱ ደም የሚሆነውን እይታችንን እንዳይጋርድ መጋረጃው በወንጌል ቃል ከላይ እስከ ታች ከሁለት ይቀደድ ለማለት ነው የምንዋጋው፡፡ እግዚአብሔር የደምን ምንነትና አገልግሎት ለማስተማር ከዚሁ ከቁስ (ከገሃዱ) ዓለም በመጀመር ሰው ከኃጢአቱ በእግዚአብሔር ፊት እንዲሸፈንበት (ዘሌ.17፡11-12) ደምን ሰጥቷል፡፡ ይህ በአዲስ ኪዳን በክርስቶስ መሸፈንን የሚያመለክት ነው (ገላ.3፡26-27፣ ቁ27/ለ እና ዕብ.10፡20፤) ክርስቶስ (ደሙ) ወደ አብ መግቢያ መጎናጸፊያ መሸፈኛ ነው፡፡ «በእርሱ ... ወደ አብ መግባት አለንና»፤ (ኤፌ.2፡18፣ 3፡12፣ ዮሐ.14፡6)







ደምና ውኃን እንደ ሁለት ነገሮች እንያቸውና፣ አብንና የአብ ክብር ነጸብራቅ የሆነውን እንዴት እንመለከታለን? በክርስቶስ የሚኖረው አብ ሕያው ነው፡፡ ሕያው አብ የላከው ሕያው መሆኑ ተጽፏል፡፡ አብ በክርስቶስ የጐደለበት ሳይኖር በሙላት፣ ሕዋሳቱ በሙሉ ከአፍ እስከ ገደፍ ጥም ብሎ ሞልቶ ያደረበት ስለሆነ ራሱ ከሕያው አብ ጋር ፍጹም አንድ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሕያው የሆነው ክርስቶስ ከሕያው አብ የተነሣ ሕያው መሆኑ ከመመስከሩም በላይ ሕያው የሆነውን ክርስቶስን የሚበላ ሰውም ጭምር «ሕያው አብ እንደ ላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን እንዲሁ የሚበላኝ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል» (ዮሐ.6፡57) ተብሎ እንደተጻፈ ከእርሱ የተነሣ ሕያው ነው በሚል በራሱ ደረጃ ጠርቷል፤ እኛም እንደዚሁ ከእርሱ የተነሣ ሕያው መሆናችንን በምን እናውቃለን? እኔን ያየ አብን አየ፣ እኔን የተቀበለ አብን ተቀበለ፤ እናንተን የተቀበለ እኔንና አብን ተቀበለ ማለቱ ለዚህ መልስ ነው፡፡ (ዮሐ. 13፡20፣ 19፡34፣ ማቴ.10፡40)፡፡ ስለዚህ፣ ኢየሱስን የወጋው አብን ወጋው፡፡ አገልጋዮቹን የሚወጋ እርሱ ኢየሱስን አልፎ ተርፎም አብን ወጋ፡

ነፍሰ-ገዳዩና ተበቃዩ

«ደም፣ ምድሪቱን ያረክሳታልና የምትኖሩባትን ምድር አታርክሱአት፣ በደም አፍሳሹ ደም ካልሆነ በስተቀር ምድሪቱ ከፈሰሰባት ደም አትነጻም፤ እኔ እግዚአብሔር በእስራኤል ልጆች መካከል አድራለሁና፣ የምትኖሩባትን በመካከሏም የማድርባትን ምድር አታርክሱአት» (ዘኁ.35፡33-34)፡፡

ይህ በመጋረጃው ዘመን የተሰጠ ትእዛዝ ነው፡፡ መጋረጃውም አለመገረዝን አመልካች መሆኑን እያየን መጥተናል፡፡ የጌታ ነገር ለሰው በባለቤቱ ሁኔታ ራሱን የሚያይበት መስተዋት ሆኖ ይገለጣል፤ የማንነቱ መንጸባረቅ

ሆኖ ይታየዋል በገዛ-ራሱ ላይ ይፈርድ ዘንድ፡፡ ለምሳሌ፣ 2ሳሙ.22፡26-27 እና መዝ.18፡25-26) እንዲህ ይነበባል፤ (ጌታ) ለቸር ቸር፣ ለቅን ቅን፣ ሲሰማው ወይም ሲያነብበውና ሲያገናዝበው ቸር፣ መልካም ብሩክ ነገር ሆኖ ይሰማዋል፤ ይታየዋል፤ ለንጹሕ ሰው ንፁህ ሆኖ የገዛ ራሱ መስተዋት ይሆናል፡፡ ደግሞም የተወደደ አንባቢው ሲያነበው፤ ሰሚው ሲሰማው የተባረከ፣ ቸር፣ ቅን፣ ንጹሕ ሆኖ መለወጡ ከውስጡ ይሰማዋል፡፡ ለጠማማው ሰው ግን የተጣመመ ነገር ሆኖ ተጣምሞ ይታየዋል፡፡ የራሱን ማንነት ራሱ መለሶ እንዲያይ ያደርገዋል፡፡ ደግሞም ጠማማው ከቶ አይባረክበትም፤ አይፈወስበትምም፡፡

ነፍሰ-ገዳዩ ማን ነው? ቢባል፣ ነፍሰ-ገዳዩ ዲያብሎስ መሆኑን ይገልጻል፡፡ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ነፍሰ-ገዳይ ነው (ዮሐ.8፡44)፡፡ ዲያብሎስ እየታየ ይገድላል ወይስ ተሰውሮ ይገድላል? ዲያብሎስ በውስጥ/በመንፈስ ሲገድል ባሮቹ በግልጽ (በፊደል) ነፍሰ ገዳይ ናቸው? ዲያብሎስ በውስጥ በመንፈስ እንጂ በውጭ ተገልጦ አይወጣም፡፡ በውስጥ ራሱ ሲገድል፣ በውጭ አገልጋዮቹን ልኮ ይገድላል፡፡

ዲያብሎስ ማንን ነው የገደለው? ነፍስስ የማን ገንዘብ ነው? (ሕዝ.18፡4) እንደሚያመለክተው የአባት ነፍስ የእግዚአብሔር እንደሆነ፣ እንዲሁ የልጅ ነፍስ የእግዚአብሔር ነው፡፡ ከዚህም ሌላ እግዚአብሔር ሰውን መጀመሪያ ፈጥሮ ከምድር አፈር ባበጀው ጊዜ በገዛ ራሱ እስትንፋስ ሕያው አድርጎታልና፣ (ዘፍ.2፡7፡፡) የሰው ሕይወት የእግዚአብሔር ነው፡፡ ለሰው የተሰጠችውን የእግዚአብሔርን ነፍስ ከፍጥረት ሁሉ እጅ፣ ከሰው ወንድም እጅ፣ ከባሕርም ውቅያኖስ እጅ፣ ከሞትና ሲዖልም እጅ፣ (ራዕይ 20፤13) ከበላው፣ ከዋጠው ሁሉ እጅ የገዛ ራሱን ንብረት/ገንዘብ የሆነችውን ነፍስ ሊያስተፋ እግዚአብሔር አምላክ ራሱ በሰው መልክ ምሳሌ የሰው ወኪል በመሆን ሰው ሆኖ ተገልጧል፡፡







ክርስቶስ የደም አፍሳሹን (የዲያብሎስን) ደም እንዴት አፈሰሰ? ዲያብሎስ መንፈስ እየሆነ ሊደማ እንዴት ይችላል? ቢባል፣ ዋናውና የእውነት እውነተኛው ደም መንፈስ ነው የሚለው ለዚህ መልስ ሊሆነን ይችላል፡፡ መንፈስ ጠጣር ሳይሆን ፈሳሽ ነው፤ (ኢሳ.32፡15፣ 44፡3፣ ኢዩ.2፡28፣ ሐሥ.2፡16-17፣ ቁ.33፣ ቲቶ.3፡6-7) «ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስ የተወለደም መንፈስ ነው (ዮሐ.3፤6) ሲል የመንፈስ ተቃራኒነት ከአፈር አካል ሰውነታችን ጋር ሳይሆን ከሥጋ ጋር ሆኖ እንደሚታይ መገንዘብ ያሻል፡፡ ማለትም ዐረፍተ-ነገሩ ሥጋን ከመንፈስ ጋር ተነጻጻር ማድረጉን ለማስገንዘብ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሥጋ አሳብ ሞት ነው፤ በተቃራኒ ደግሞ የመንፈስ አሳብም ሕይወትና ሰላም ነው፤ (ሮሜ.8፡6) የሚለውን ስናይ፣ የሥጋ አሳብ የሆነው ሞትም፣ የመንፈስ አሳብ ለሆነው ሕይወትና ሰላም ተቃራኒ ነው፡፡ በሥጋ የሚያስቡ ሰዎችም በመንፈስ ለሚያስቡ ሰዎች ፍፁም ተቃራኒ የሆነ ሕይወት የሚኖሩ ናቸው፤ (ሮሜ.8፡5) እንደ ሥጋ አሳብ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁ፤ በመንፈስ የሥጋን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ» ከሚለው ስንነሣ ሥጋና መንፈስ ተቃራኒ፤ የሥጋና የመንፈስ ሐሳብም ተቃራኒ፤ ሥጋ የመንፈስ ተቃራኒ፤ መንፈስም የሥጋ ተቃራኒ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከዚህም ተነሥተን ሥጋ ከመንፈስ  አንፃራዊ ተነጻጻር የሆነ የማይጨበጥ ስውርና አደገኛ አካል መሆኑን መገንዘብ እንችላለን፡፡

የመንፈስ አሳብ የሚለው ቃልም ቅዱሱ የእግዚአብሔር መንፈስ ማለት ሆኖ፣ ሥጋና የሥጋ አሳብ ማለትም የዚህ ተቃራኒው የሰውና የሰይጣን አሳብ እንዲሁም ፈቃድ ሆኖ ይታያል፡፡ በሥጋ የሆነ ሰው የሚኖርበት አሳብም በሰይጣን ቁጥጥር ሥር የዋለ አሳብ ነው፡፡ ሥጋና የሥጋ መንቀሳቀሻ ኃይል የሆነ ደምም ከሰይጣን ተጽዕኖ ያላመለጠ ነው፣ ሥጋ ተጨባጭ እንዳልሆነ ሁሉ ደሙም ተጨባጭ ያልሆነው ከሰይጣን የተነሣ ነው፡፡ የሥጋ መከራ፣ የሥጋ ሥቃይ ሁሉ ከዲያብሎስ እንጂ የሥጋ

መከራ፣ የሥጋ በሽታ፣ የሥጋ ሞት ገና ከጥንቱ መነሻው ሌላ ሆኖ አይደለም፡፡

ሥጋን የሚያንቀሳቅሰው (ራሱ ሥጋ፣ የሥጋ ኃይል) የኃጢአት አቀጣጣይ የሆነው ዲያብሎስ ነው እንጂ፣ መንፈስ ቅዱስ አይደለም፡፡ ሥጋና መንፈስ ፍጹም ተቃራኒ የሆኑ ጠላቶች ናቸው (ሮሜ.8፡6-7)፡፡ ክርስቶስን መከራ ያበላው፣ የተፈታተነው፣ ያንገላታው፣ እንዲሁም እርሱ የተዋረደው፣ የጣረው፣ የተገረፈው፣ የተመታው፣ የተቸነከረው፣ በጦር የተወጋው፣ የቆሰለው፣ ደምና ውኃ የወጣበት፣ የተሠቃየው፣ የሞኀው ከኃጢአት ጣጣ ተጽዕኖ የተነሣ በሥጋው ነው፡፡ ሥጋን በመንፈስ ገድሎት ግን የደም አፍሳሹን (የሥጋን) ደም አፍስሶ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር በስውር የሚያድርባትን ስውር ምድራችንን (ውስጣችንን) አነጻው፡፡ በመንፈስ ሥጋን ገድሎ የሥጋን ደም አፍስሶ ተበቅሎ፣ ወደ ክብሩ የገባው ደግሞ በመንፈስ ነው፡፡

እዚህ ላይ «ሥጋን» በመንፈስ መግደል እንዴት ነው? መንፈስ ሥጋን መግደያ ብቃት ያለው ነው ወይ? አዎ!! መንፈስ ሥጋን የመግደል ብቃት እንዳለው ሁሉ እንዲሁ ሥጋ መንፈስን የመግደል ብቃት ያለው ነውና፡፡ የአንደኛው በጽድቅ የሌላኛው በኃጢአት ከመሆኑ በቀር ብቃታቸው አሌ የማይባል ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ መንፈስ ረቂቅ እንደሆነ ሥጋም ረቂቅ ነው፡፡ መንፈስና ሥጋ አቻና ተመሳሳይ፣ ተመጣጣኝ የሆኑ ጠላቶች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ «…ሥጋ በመንፈስ ላይ፣ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና እነዚህ እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ…» (ገላ.5፡16-17) ሲጠቀለልም መንፈስና ሥጋ በክርስቶስና በዲያብሎስ የሚመሩና የሚታገዙ ናቸው፡፡

የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነ ምድር ከማንነት በውጭ የሚታየው ቁሱ የሰው መኖሪያ ምድር ነው ወይ? ቁርበታችንን (ሽለፈታችንን) ተገፍፈን





ከጌታ ጋር በጥምቀት ተቀብረን ቀብረነዋልና ከቁርበት ጨለማ ስለወጣን የብርሃን ልጆች፣ የቀን ልጆች ሆነን በብርሃን ስናየው ጌታ የሚያድርባት ከእርሱ ጋር የምንኖርባት የተባረከችው እውነት፣ እውነተኛዋ ምድርም፣ የአዲስ ኪዳኑ የእግዚአብሔር እስራኤልም (ገላ.6፡16) ክርስቶስ ተዘርቶ ከእርሱ የበቀልን እኛው ነን፡፡ እግዚአብሔር እንደ ተናገረ «…ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑኛላችሁ፣ ዘፀ.19፡5/ለ፣ 1ቆሮ.3፡9» እኛ የእግዚአብሔር ማደሪያው የሆንን ርስቱ ነን፡፡ በዚህ በቅዱሱ ምድር የጻድቁ የክርስቶስ ደም በከንቱ ፈስሶ እንዳይቀር ነው፡፡

እስራኤላውያን ምንም የተገረዙና ከአንደኛ ሽለፈት ግርዶሽ የወጡ ቢመስሉም፣ የወረሱት ምድር በአሕዛብ አንፃር ሲታይ የተቀደሰ ምድር ቢባልም፣ ይህን መመሪያ የሰሙት ባልተገረዘ ጆሮ ያዩትና የተቀበሉት ደግሞ መጋረጃው ሳይቀደድ ነበር፡፡ መገረዛቸው ከመጋረጃ ግርዶሽ ወደ እግዚአብሔር ብርሃን የሚያወጣቸው መሆን ነበረበት፡፡ ነገር ግን፣ የጌታ ትእዛዝ በሰይጣን ጣልቃ ገብነት ምክንያት ሁልጊዜም ተቃራኒው እየተሰማ፣ ተቃራኒው ስለሚተገበር፣ ነገራቸው ሁሉ፣ ሥርዓታቸውም ሁሉ በመጋረጃ የተሸፈነ ሆኖ ከሕግ በታች አድርጓቸው ኖሯል፡፡ እግዚአብሔር በመካከሏ አድርባታለሁ ያላት ምድር፣ እስራኤልም፣ የእስራኤል ልጆች ነበሩ፡፡ ምድሩን የሚያረክሰው ደምም በአዲስ ኪዳን ብርሃን ሲታይ፣ ባለመጋረጃ ሆኖ ጨለማ ነበረና ወደ ውጭ የቀረ ምድር፣ ወደ ውጭ የቀረ ሕዝብ፣ በውጭ የቀረ መካከል፣ «የውጪን ዕድሞ ተወው» ተብሎ እንደተጻፈ፣ ውጫዊ ደም ሆኖ የተተወ ነው (ራዕይ 11፡1-2፤)፡፡

በዚያ ምድር እግዚአብሔር በእስራኤል ልጆች መካከል በአጥርና በመጋረጃ ተለይቶአቸው በምሳሌ ያድርበት ነበር እንጂ፣ እንደ ዛሬው አማኑኤል ሆኖ ተቀላቅሎአቸው አልነበረም፡፡ ያ ምድራቸው በራሱ ምድር ሳይሆን፣ አሁን እግዚአብሔር አማኑኤል ሆኖ ተቀላቅሎን ከእኛ ጋር የሚያድርበትን ምድር እርሻው /ሕንፃ የሆነውን የሥጋ አካላችንን

(1ቆሮ.6፥19-20) አመልካች ነው፡፡ ስለሆነም ከእስራኤልም በላይ የእግዚአብሔር እስራኤል (ገላ.6፥16) በክርስቶስ ደም የክርስቶስ አካል የሆንን እኛ ስንሆን፣ ማደሪያውም እጅ ያልሠረውና የእግዚአብሔር ማደሪያ ነው፡፡ እርሱ በመካከላችን በማደሩ ምድራችን (ልባችን) በደም መርከስ የለበትም፡፡ የጻድቅ ደም ማለትም ቀደም ሲል እንዳየነው ሁሉ ጻድቅ ሰው (የሚመላለሰውም) የሚንቀሳቀሰውም በእግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ (ሮሜ 8፥14)፣ ሊመጣ ያለውን ጻድቁን (ክርስቶስን) የሚያመለክት ነጸብራቅ ልንሆን ይገባል፡፡ እርሱ የእግዚአብሔር መልክ ነውና፡፡ እግዚአብሔር በከንቱ የፈሰሰውን የጻድቁን ደም ይሻል፤ አጥብቆም ይፈልገዋል (ዘፍ.9፥4-6፣ ማቴ.23፥34-36፣ ሉቃስ 11፥49-51፣ ራዕይ 6፥9-10፣ 18፥24ን እናመሳክር)፡፡ ሰውን በመልኩ ፈጥሯል የሚለውም ጻድቁ ሰው እንደ አቤል ሊመጣ ያለውንና ፍፁም የእግዚአብሔር መልክ ምሳሌ፣ ክብር የሆነውን ክርስቶስን ስለሚያንፀባርቅ መልኩ አለበትና እግዚአብሔር የጠፋ መልኩ፣ ምሳሌው የሆነውን ሰው ደም ይፈልጋል፡፡ የእግዚአብሔር መልክም ቁስ-አካሉ ሳይሆን፣ ደሙ ነውና፡፡ የጻድቃንና የነቢያት ደም የክርስቶስ ደም ስለሆነ እግዚአብሔር የሚፈልገው ደም ነው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በአዲስ ኪዳን ብርሃን፣ በተቀደደ መጋረጃ (ማቴ.27፥50-51) በተከፈተ በር፤ (ራዕይ 3፥8፤ ም.4፥1) ስንመለከት ይህ የጻድቃን ደም፣ ስለክርስቶስ ምስክር የፈሰሰ ለራሱ ለክርስቶስ ክብርና ለወንጌል መዳረስ ፋይዳ ያለው መሆኑን እንረዳለን፡፡ ደሙን ፈላጊ መብራትም፣ ከተቀበረበት ሲያል፤ ከተደበቀበት ጉድጓድ ፈነቃቅሎ ለማውጣት፣ ከፍቶ ለማጋለጥ ብርሃን፣ የሲያልና የሞት መክፈቻ ያለው፣ ከጠፋበት ዓለም ዳርቻ ድረስ በፉጨት ጥሪ ሰብሳቢም፣ በብርሃን ፈራጅም፣ ደሙን በጽድቅ ተበቃይም ሆኖ የተሾመው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡፡ የዮዳሄ ልጅ ነቢዩ ዘካርያስ በግፍ ተወግሮ ሲሞት፣ «እግዚአብሔር ይያው፣ ይፈልገውም»







ሲል ለእግዚአብሔር አመልክቶ በነበረው መሠረት ያንን አስታውሶ ጌታ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደመሆኑ መጠን የባርያውን ደም ሲፈልግ፣ «...ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ የፈሰሰው የነቢያት ሁሉ ደም ከአቤል ደም ጀምሮ በመሠውያና በቤተ-መቅደስ መካከል እስከ ፈሰሰው እስከ ዘካሪያስ ደም ድረስ ከዚህ ትውልድ እንዲፈለግ አዎን፣ እላችኋለሁ ከዚህ ትውልድ ይፈለጋል» ሲል የቅዱሳን ደም በምድር ላይ ፈስሶ እንደማይቀርና እግዚአብሔር በጽድቅ እንደሚፈርድ አስታውቋል (ሉቃስ 11፥50-51)፡፡ እግዚአብሔር እስከ አሁን፣ እስከ ብዙ ሺህ ዓመታት ደማቸውን ሳይፈልግ ዘግቶ ዝም ብሎ ያዘገየው ለምንድን ነው? (ማቴ.23፥34-36፣ ራዕ፤6፥9-11) የሟች ሰማእታት ቁጥር ድምር ተጠቃሎ እስኪቀርብ ድረስ አዘገየው፡፡

በዚያ ዘመን ያልነበረ፣ የዛሬው ሰው የክርስቶስን ደም በግፍ እንዳፈሰሰ ሊቆጠር የሚችለው እንዴት ነው? የዚህን መልስ፣ በጥያቄና በመልስ እንመለከታለን፤ ለምሳሌ፣ ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍስ-ገዳይ ነው፤ (1ዮሐ.3፥15) የማንን ነፍስ? ነፍስ የማነው? «እነሆ ነፍሳት ሁሉ የእኔ ናቸው የአባት ነፍስ የእኔ እንደ ሆነች ደግሞ የልጅ ነፍስ የእኔ ናት፣... ይላልና ሕዝ.18፥4» ነፍስ የእግዚአብሔር ናት፡፡

ስለሆነም፣ ዛሬ ወንድሙን የሚጠላው የእግዚአብሔር ገንዘብ የሆነችውን ነፍስ ገዳይ ሆኖ ቀድሞ ነፍስ ከገደለው ቃየን ጋር ግብረ-አበር ተደርጎ ተከስሷል (1ዮሐ.3፥12-13)፡፡ ይህ እንዴት ይሆናል ቢባል፣ የእግዚአብሔር ፍርድ በመንፈስ በልቡና ላይ እንጂ በቁስ-አካል ላይ አይደለምና፡፡ አንተ ዱሮ ባትኖርም የወረስኸው መንፈስ፣ የዱሮ ያ- አቤልን በጥላቻ ተነሣስቶ የገደለው የጥል መንፈስ በመሆኑ ዛሬ ወንድሙን የሚጠላው ራሱ በዚያ መንፈስ ተጽዕኖ ሥር ነውና (1ዮሐ.3፥12-13) ወንድሙን የሚጠላ ነፍስ-ገዳይ ስለሆነ፣ ዛሬ የጥልን መንፈስ አስተናጋጅ ሰው ከመንፈሱ ጋር ተጣምሮ ተከስሷል፡፡ ጥል ደግሞ በሌላ መጽሐፍ የሥጋ ሥራ ተብሎ ከመግደል ጋር በአባሪነት ተዘግቦ ይነበባል (ገላ.5፥19-20)፡፡ ከዚህም በላይ

አስቀድሞ አቤልን ጀምሮ ነቢያትን ሁሉ እየገደለ መጥቶ ክርስቶስን የገደለ የጽድቅ ሁሉ ጠላት፡፡

- ወንድሙን የሚጠላ ነፍሰ-ገዳይ ነው ሲባል፣ ደም አፍስሷል ለማለት እንዴት ይቻላል? የሰው ልጅ የውጭና የውስጥ ሰውነት ስላለው የውጭና የውስጥ ደም አለው፡፡ እንዲህም ሲባል የፊደልና የመንፈስ ደም፣ ከሥጋ ወላጅና ከመንፈስ ወላጅ የሚወረስ ደም (ውስጣዊ ሕይወት) አለው ለማለት ነው፡፡
- ወንድሙን የሚጠላ ሰው፣ ኃጢአተኛውን ወንድም ስለሚጠላ ነው ወይስ ጻድቁን ወንድሙን ስለሚጠላ ነው፣ ነፍሰ ገዳይ የተባለው? የተጠላው ጻድቅ ከሆነ ጻድቁ ማን ነው?
- በ(ማቴ.23፡34-36 እና ሉቃስ 11፡49-51) ሲታይ ከአቤል ደም ጀምሮ የፈሰሰው የጻድቃንና የነቢያት ሁሉ ደም ከዚህ ትውልድ ይፈለጋል ይላልና፣ ጻድቁን ስለሚጠላ ጽድቅን ይጠላል፡፡ አንተም ወንድምህን ትጠላለህና፣ በሰልፉ ከነፍሰ-ገዳይ፣ የቃየን ግብረ- አበር ነህ? ቃየን የዲያብሎስ ግብረ-አበር (ጣምራ) ነበረና ዲያብሎስ በቃየን መልክ ምሳሌ ቁርጥ፣ ቃየንን መስሎ ተገለጠ፡፡ ንስሐ ካልገባህና መንገድህን ካላሳመርህ በአንተም እንደዚሁ ይገለጥብሃል፡፡
- የንስሓው ጥሪ፣ ያን- በጻድቁ ደም የተነከረውን ወንጀለኛ መንፈስ ዛሬ አንተ ተቀብለኸው በአንተ ዘንድ፣ በጓዳህ ውስጥ ስለምታኖረውና ለኃጢአት ሥራ ስለምትገለገልበት፤ ወንጀለኛው ለፍርድ ሲፈለግ ማለትም ቤትህ ሲበረበር በአንተ ጓዳ ውስጥ ተሸሽጎ ተገኝቷልና፣ አንተን ራስህን አባሪ ተነባባሪ ወንጀለኛ ስለሚያደርግ ቶሎ ብለህ ይህን ደመኛ ከጓዳህ አውጥተህ ለደም ተበቃዩ ጌታ አሳልፈህ ስጥ ነው፡፡
- የሥጋ አሳብ ሞት ነው፤ የመንፈስ አሳብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው የሥጋ አሳብ የማን ሞት ነው? ሥጋ ማንን ገደለ? ማንንስ በደለ? የሥጋ አሳብ ሞት ነው ሲባል፣ ለመሆኑ ሞቱ ሥጋን ይገድላል ወይስ







መንፈስን ይገድላል? የሥጋ አሳብ የቅዱሱ መንፈስ ሞት ነው? ወይስ የርኩሱ መንፈስ ሞት ነው? አንተ በአንተ ዘንድ በከፍተኛ ፍቅርና ክብር የምታኖረው ሞት የሆነውን የሥጋ አሳብ ነው ወይስ ሕይወትና ሰላም የሆነውን የመንፈስን አሳብ ነው? ከገደለ ዘንድ ደም አላፈሰሰም ወይ? በ(ማቴ.25፡40፣ 45 ም.10፡40 እና ዮሐ.13፡20) ላይ ሲታይ፣ የጌታን መልእተኞች የተቀበለ ጌታን ተቀብሏል፣ እነርሱን ያስተናገደ ክርስቶስን፣ በክርስቶስም አብን አስተናግዷል፡፡ መልእክተኞቹን፣ (አገልጋዮቹን) ያልተቀበለ፣ የናቀ፣ የጠላ፣ ያዋረደ፣ ያሳደደ፣ የገደለ፣ የበደለ ሁሉ እርሱ ክርስቶስን፣ በክርስቶስም አብን ጨምሮ የናቀ፣ የጠላ፣ ያዋረደ፣ ያሳደደ፣ የበደለ፣ የገደለ፣ ማለትም ደሙን ያፈሰሰ ነው፡፡

- በብሉይ ኪዳን አሥራ ሁለቱም ወገኖች ነገደ-እስራኤል ማለት ሮቤልን አንድ ብሎ ብንያም ድረስ እያንዳንዱ ምድራቸው በደም እንዳይረከስ በየራሱ ኃላፊና ተጠያቂ ሆኖ ይጠብቅ ነበር፡፡ እስራኤላውያን ይህን ትዕዛዝ በዲያብሎስ ጣልቃ ገብነት ከመጋረጃ ውጫዊ ገፁን በውጭ ጆሮ ሰምተው ከማንነታቸው ወደ ውጭ በመተርጎም ውጫዊው (ፊደላዊ (ፍጥረታዊ)) ደም በውጫዊ (ፊደላዊ) ምድር ላይ እንዳይፈስስ ይጠብቁ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት እግዚአብሔርም በእስራኤላውያን አንፃር ወደ እያንዳንዱ ሰው ውስጥ ሳይገባ በመጋረጃ በውጭ ቆይቷል፡፡ ይህ ከፍ ብሎ እንደታየው በእርግጥ በግልጽ የሚሆነው አሁን በመካከል ግድግዳ የሆነውን መጋረጃ በቀደደው በአዲስ ኪዳን ብርሃን ሲታይ ነው፡፡
- አሁን፣ በመንፈስ እንጂ በፊደል በማይሆነው በአዲሱ ኪዳን፣ (2ቆሮ.3፡ 4-6፣ ሮሜ 7፡6) የትኛው ደም፣ የትኛውን ምድር ያረክሳል? ግልጹ ደም ግልጹን ምድር ማርከሱ ስውሩ ደም ስውሩን (ቅዱሱን) ምድር ማርከሱን አመልካች ነው፡፡ የምትረክሰውም ምድር፡-

ሀ/ እግዚአብሔር በመካከልህ የሚኖርባትን ምድር ሲል ከሁሉ በላይ የሆነ ከፍተኛውን ምድር (መዝ.37፥34) ማለትም የተቀደሰውን ተራራህን ጽዮንን፣ የመቅደሳችን ሥፍራ የሆነውን፣ ከፍ ያለውን የክብር ዙፋኑን፣ (ኤር.17፥13) በክርስቶስ ትንሣኤ ከፍ-ከፍ ያለውን (ውስጥህን) ያረክሳል ማለቱ ነው፡፡

ለ/ «አቤቱ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል በተቀደሰውም ተራራህ ማን ይኖራል? ...መዝ.15፥1» የእግዚአብሔር ድንኳን የሆነውን የተቀደሰውን ተራራ ያረክሳል፡፡

ሐ/ «በእኔ የታመነ ግን ምድሪቱን ይገዛል፣ የተቀደሰውንም ተራራዬን (ክርስቶስን) ይወርሳል፤ ኢሳ.57፥13/ለ» ይህን ምድሩን ማለት የተቀደሰውን የእግዚአብሔር ተራራ እያንዳንዱ ግለ-ሰብ እንደ እስራኤል ነገዶች ዓይነት ከደም መጠበቅ ያለበት ነው፡፡ አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና፤ (ምሳሌ 4፥23)

የክርስቶስ ደም እንደ ፊደል (ቁሳዊ) ደም ውስን ነገር ሳይሆን፣ ለመብላት እንጀራ፣ ሥጋ፣ ለመጠጣትም ደግሞ ውኃ፣ ወተት፣ ወይን ጠጅ፣ ሳይጨመርበትና ሳይቀነስበት ብቻውን በቂ የሆነ ሕይወት ለሰው ልጅ ዘላለማዊ ሁለመናው ነው፤ (ኢሳ.55፥1-2፤ ዮሐ.4፥10፤ ቁ.13-14፤ ም.7፥37-39፤ ም.6፥35፤ ቁ.41፤ ቁ.50-58ሰ) ከኃጢአት (ከማይታይ ሞት) ከለላ፣ መጋረጃ፣ (ዘፀ.12፥6፤ ቁ.21-23) ከቅጠል ራቁትነት (ዘፍ.3፥7-10፤ ራዕይ 3፥17-18፣ ከገላ.3፥27 ጋር) የክብር መጎናፀፊያ ወደ አብ እግዚአብሔር መግቢያ ልብሳችን...ወዘተ ነው፡፡

ዲያብሎስ ደምን በማፍሰስ ከአቤል ጀምሮ ይፈጽመው የነበረ ተግባሩን በመቀጠል የሕይወት ራስና መደምደሚያ የሆነውን ጌታ (ክርስቶስን) በመግደል ፅዋውን ሞላ፣ ደመደመ፡፡ ከዚህ በኋላ ማን የተረፈ አለና ይገደል? 2ቆሮ.5፥14/ለ፡፡ ይህ ደምን የተቃባ ወንጀለኛ ከደም ተበቃዮች ሸሽቶ አንተን እንደሽማ ተከናንቦ አሳዳጆቹ እስኪመለሱ በአንተ ጓዳ







ይሸሸጋል (መሳ.4፥17-19)፡፡ ቢጠይቁህ አንተም እርሱን በኢየሱስ ስም በማለት ጭምር ሸሸገኝ ይላል፡፡ አሳዳጆቹ ከተመለሱና ጸጥታ ሲሆን የአንተን ልብስ ለብሶአልና ቁርጥ አንተን መስሎ ይወጣል ይገባል፤ ሥራም ይሠራል፤ ይነግዳልም፡፡ አንተንና እርሱን ለይቶ የሚያውቅ ስለሌለ በቤተ-ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ጭምር ይሳተፋል፡፡ ሃሌ-ሉያ፣ ኢየሱስ ጌታ ነው ማለትን ያበዛል፤ በቃ አሸነፈ ማለት ነው በአንተ ተሸፋፍኖ ተጠመቀ ክርስቲያንም ሆነ፡፡

የክርስቶስ ውጫዊው ፊደላዊው ደም (ቀዩ) በውጫዊ ምድሬ አልፈሰሰም ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን፣ የክርስቶስ ያልቀላው ደም ውኃው በጀሮዬ አልፎ በውስጠኛው ምድሬ (በልቤ) አልፈሰሰም የሚል ማን ነው? በምድርህ ንጹሕ ደም መፍሰሱ የታወቀ ነውና ምድርህ ረክሷል፡፡ ያለ ደም አፍሳሹ ደምም ምድርህ ከቶ አይነጻም፡፡ በምድሬ የማን ደም ፈሰሷል? ትላለህ? ከንጹሕም ንጹሕ የሆነ የክርስቶስ ደም (ውኃው) ፈሰሷል፡፡ ይኸውም፣ አባቶች በሙሉ፣ ‹‹ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን!›› (ማቴ.27፥25) ሲሉ በውል ተስማምተው የተቀበሉት፣ ከእነርሱም አልፎ በእኛ ሁሉ ላይ ሆኗል፡፡ በምድር ላይ ሳይሆን በእነርሱና በልጆቻቸው ላይ በላያቸው ሆኗል፡፡ በላያችን ሲባል በሰውነታችን ላይ ማለት ነው፡፡ ይህም በእውነት እውነተኛ ምድር፣ አፈር በሆነው ሰውነታችን ላይ ማለት ነው፡፡ በአባቶች ላይ የሚታየው የጊዜው ደም (1ቆሮ.4፥18) የፈሰሰ ሲሆን፣ በእኛ በልጆች ላይ የማይታየው የዘላለም ደም ፈሰሷል፡፡ የክርስቶስ የዘላለም ደም ማለት ቃሉ (መንፈሱ) ነውና፡፡ በምድራችን ላይ የዘላለም ሕይወት የሆነው ቃሉ በምድራችን (በልባችን) ላይ በከንቱ ፈስሶ አፈር ለብሷል፡፡ መድኃኒት በመሆን ፈንታ ከንቱ ሆኗል፡፡

አንባቢ ሆይ ለመሆኑ ከኃጢአትህ በምን ትነጻለህ? ደም አፍሳሹም፣ ሕይወት ደምሳሹም ሁልጊዜም ዲያብሎስ ነው፡፡ ያለ ዲያብሎስ ደም

አፍላሽ፣ ሕይወት ደምላሽ ሌላ የለም፡፡ ያለ እርሱ ምንም ክፉ ነገር አይደረግም፡፡ ደም ነፍስ ነው፤ እንደ ተጻፈ፣ «ነገር ግን ነፍሱ ደሙ» ያለችበትን ሥጋ አትብሉ፤ ነፍሳችሁ ያለችበትን ደማችሁን በእርግጥ እሸዋለሁ፣ ከአራዊት ሁሉ እጅ እሸዋለሁ፣ ከሰውም እጅ፣ ከሰው ወንድም እጅ የሰውን ደም እሸዋለሁ፡፡ የሰውን ደም የሚያፈስ ሁሉ ደሙ ይፈሰሳል፤ (ራሱ ይፈሰሳል፡፡) ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጥሮታልና» (ዘፍ.9፡4-6) ተብሎ ተጻፈ፡፡

የሰውን ደም የሚያፈሰስ ደሙ ይፈሰሳል የሚለውን ሕግ በመናቅ ዲያብሎስ ደምን በማፍሰስ ከአቤል ጀምሮ የቀጠለውን የሕይወት ራስና ድምዳሜ የሆነውን የክርስቶስን ደም በማፍሰስ ፅዋውን ሞላ፡፡ ይህን ክፉ ተግባሩንም ሲፈጽም ኖረ፡፡ ከዚህ በኋላ ማን ቀረና ይገደል?? አንባቢ ከዚህ እንዴት ይነሣል? የክርስቶስ ደም ስለ እኔ ፈሰሷል በሚል መፈክር? ብቻ ወይስ የደመኛውን ደም በማፍሰስ ነው? ይህን በተግባር የሚናገረው ያንባቢ ሰልፍ በየትኛው በኩል ነው? ከደም አፍላሹ ወይስ ከከሳሹ (ተበቃዩ)? (ዮሐ.5፡45፣ ሮሜ 11፡2፣ ም.3፡9-18...) የአንባቢ ቤት ቢበረበር ደም አፍላሹ ከወንጀል ሥራው ሸሽቶ ተደብቆ በዋሻህ (በጓዳህ) አይገኝም ወይ? የደመኛውን ቦታና ክፍል ሰጥቶ መደበቅ መከለል፣ እየመገቡት ማኖር በግብረ- አበርነት አያስጠይቅም ወይ? አንተ ከለላ ከሆንከበት አብሮ ከመጥፋት ማን ያድንሃል? ለእርሱ ሽፋን ከሆንንበት ቶሎ ዞር ብሎ እርሱንም ሥራውንም ማጋለጥ ብልህነት ነው፡፡ ይህን መለኮታዊ የሆነ የእግዚአብሔርን ጥሪ አንናቀው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የእግዚአብሔር ደም ስለሆነ እግዚአብሔር ያለውን (የተላከበትን) ሳይፈጽም በምድር ላይ በከንቱ ፈሶ ከቶ የማይቀር ነገር ነው (ኢሳ.45፡23፣ ም.55፡10-11)፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የማይጠፋ ዘር ነውና፣ ከቶ የሚጠፋ ዘር አይደለም፣ (1ጴጥ.1፡23) ይህም ደሙ ካላለማን ያጠፋናል እንጂ ከንቱ ሆኖ አይቀርም ማለት ነው፡፡







እንግዲህ ዲያብሎስ የክርስቶስን ደም ሲያፈስስ የሁላችንን ደም አፍስሶ አምላካችን እግዚአብሔር በመካከላችን አማኑኤል ሆኖ የሚያድርባትን ምድር ያረከሰ ስለሆነ ደማችን በእጁ ፈስሶ ደሙ እንዲፈስ በተለያዩ ውጊያዎች ውስጥ ለእግዚአብሔር መፍቀድ የእኛ ፈንታ ነው፡፡ የክርስቶስ ደም ደማችን ነው፤ ደግሞም የአገልጋዮቹ ደም የእርሱ ደም ነው፡፡ ወደዚህ ጥበብና ኃይል የሚመራን የተጻፈ መመሪያ አለን (1ጴጥ.3፡9፣ ማቴ.5፡44፣ ሮሜ 12፡19-21)፡፡ ይህን መመሪያ እንደ-ጋሻ ይዘን ብንገለገልበት ክፉ አድራጊውን በራሱ እጅ ገደልነው፤ እኛም ከደሙ ንጹሐን ሆንን ማለት ነው፡፡ ለዚህ የሚያበቃንም ከሰማይ አባት የሚገኝ የልጅነት ሥልጣን ነው፡፡

ክፉ አድራጊውን በራሱ እጅ ገደልነው፤ ለሚለው የሚሆን የሚከተለውን ምሳሌ እንመለከታለን፡፡ አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት በወኪሉ በኩል ጸሓፊው የማያውቀውን ክርስቲያን ሰው ከቶ በማያውቀው በሌላ ሰው ጀርባ ሆኖ በአውራጃ ፍርድ ቤት ከስሶት በገንዘብ እንዲቀጣ አስፈረደበት፡፡ ተከሣሹም ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ብሎ ከሰዓት ችሎት ለመቅረብ ምሳውን ለመብላት አንድ ምግብ ቤት ገባ ብሎ እጁን ሲታጠብ ከሣሹም እንዳጋጣሚ እጁን ሊታጠብ መጥቶ በተከሣሹ ጎን ፈንጠር ብሎ የቆመውን ሰውዬ ተከሣሹ እንደ ድንገት ያየውና ወንድሜ! የእኔ መጽሐፍ ቅዱስ ጠላትህን ውደድ ይላልና እባክህን ምሳ ልጋብዝህ! ሲለው ከሳሹ በመደነቅ ድንግጥ ካለ በኋላ እሺ! ሲለው ተከሣሹ ከደስታ ብዛት የተነሣ የፈለገውን እንዲበላና እንዲጠጣ አድርጎት ነበር፡፡ ከሣሹ ከዚያ ቀን ጀምሮ የልቡ ጥላቻ ሞተና በፍቅር ዓይን ተከሣሹን ማየት ጀመረ፡ ከዚያ ቀን ጀምሮ በተከሣሹ ላይ ጠንካራ ቃል ለመተንፈስ አልቻለም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የክርስቶስ ደም ምንድር ነው? ትሉ ይሁን? ክርስቶስስ ምንድን ነው? ክርስቶስ በመጀመሪያ የነበረ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረ፣



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አሬ አሂልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፣
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

እግዚአብሔር የሆነ ቃል ነው፡፡ ቃል ሌላ፣ ክርስቶስ ሌላ ከቶ አይደለም፡፡ ሁሉ በእርሱ የሆነው ቃል ነው፤ ስሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአልና (ራዕይ 19፡13ለ)፡፡ ክርስቶስ ሕያው ቃል ነው፤ የሕይወት ምንጭም ነው፡፡ ይህም ምንጭ ለዘላለም ዓለም ሕይወት የሚፈልቅ ነው፡፡ ክርስቶስ፣ ቃሉ፣ ደሙ ከቅድመ-አያቶቻችን ጀምሮ በእኛም፣ በልጆቻችንም ላይ ሆኗል፡፡ ቃሉ፣ (ደሙ) ያልነካው ሰው የለም፡፡ የክርስቶስን ደምም ሆነ ሥጋውን፣ ቡተመለከተ አሁን ቁሳዊነት ማለትም ፊደላዊነት የለውም፡፡ ሁሉም በክርስቶስ ሥራ አንድ ነገር ብቻ ሆኖ በእርሱ በሰማኸውና በተቀበልኸው ክርስቶስ ተጠቅልሏል፤ እርሱ ሁሉ በሁሉ ነውና፡፡ ምንም አይጨመርበትም፣ አይቀነስበትም፡፡

እስራኤላውያን በአሮጌው በፊደል ኑሮ የሚገዙ ሲሆን፣ እኛ ከመጋረጃው መቀደድ በኋላ የተጠራን፣ በአሮጌው በፊደል ኑሮ የምንገዛ ሳይሆን፣ በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ የምንገዛ ነን (ሮሜ7፡6)፡፡ ቁሳዊ (ፊደላዊ) ደሙ ነው፣ ብለን የምንገምተው በመስቀል አየር ላይ ማለት በሰማያዊ ሥፍራ ከፍታ ላይ ሲፈስስ፣ ለዮሐንስ እንደ ራዕይ መታየቱ ተጻፈ እንጂ በሌላ በየትም አልተጠቀሰም፡፡ ያ- ደም አሁን ቢኖር እንኳ ባለመልክ ማለት ባለጥላ (ባለጨለማ) ቁሳዊ የሆነው በጠባቡ በር ወደ ውስጣችን ገብቶ በልባችን ሊረጭ ከቶ የማይችል ስለሆነ ውስጣችንን ከኃጢአታችን አጥቦ ሊያነፃ፣ ሊቀድስና ሊያድስ አይችልም፡፡ የእነዚያንም ውስጥ አላነፃም፡፡ ውጫዊ ሥርዓት ሁሉ ማስመሰያ ስለሆነ የሐሰት እውነተኛ ሥራ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ ወደ ውስጥ ማለትም ወደ ልብ ያልዘለቀ ውጫዊ ሥራ የጨለማ ሥራ ስለሆነ ለብርሃን ልጆች፣ ለቀን ልጆች ስለማያገለግል በውጭ እንዳያስቀረን በምንም አቅጣጫ ወደ ውጭ አንውጣ (ገላ.4፡17፤)፡፡ ይላል መልእክቱ፡፡ «ድል የነሣውን በአባቴ መቅደስ አምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ፤ ወደ ፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም ..." ራዕይ 3፡12፤ ይህ ድል አደራጊ ሰው በአብ ማለት በመንፈስ ቅዱስ፣ በወልድ፣ በአዲስቱ







ኢየሩሳሌም ስም የታተመና የእግዚአብሔር ገንዘብ የሆነ ሰው ነው፡፡ ከአዲስ ኪዳን ደሙ በውጭ ያሉ ግን ዮሐንስ በራዕዩ እንዳመለከተው ውሻዎች፣ አስማተኞች፣ ሴሰኞች፣ ነፍሰ-ገዳዮች ማለት ወንድምን የሚጠሉ፣ ጣዖትንም የሚያመልኩ፣ ማለት የሚመኙ፣ ውሸትን የሚወዱና የሚያደርጉ ናቸው፤ (ራዕይ 22፡15)፤ ጣዖትን የሚያመልኩ፤ (ከፉ ምኞትን የተሞሉ፣ ኤፌ.5፡5) ናቸው፡፡

እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል በእኛ ላይ "አትርፎ አፈሰሰው" የተባለው ቅዱሱ ደም (ቲቶ.3፡4-7፣ ኢዩ.2፡28-29፣ ኢሳ.32፡15፣)፤ እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ "በዚያ ቀን ለዳዊት ቤትና በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ኃጢአትና ከርኩሰት የሚያነፃ ምንጭ ይከፈታል" (ዘካ.13፡1) ይህ፣ ከኃጢአትና ከርኩሰት የሚያነጻ ምንጭ የሚከፈተው ከዳዊት ቤትና ከኢየሩሳሌም በውጭ ለሚኖሩ አይደለም፤ ምንጩ ቅዱስ ነውና፡፡ ከዚህም ጋር ትንቢተ ሕዝቅኤል 36፡25-27 የተመለከተውን እናመሳክራለን፡፡ ይህኛውም ምንጭ ደግሞ የሚረጨው ከአሕዛብ መካከል ለወጡ፣ ከየአገሩ ሁሉ ለተሰበሰቡት ሰዎች ነው፡፡ የእውነት እውነተኛውና የዘላለም ሕይወት የሆነው የክርስቶስ ደም ይህ ከኃጢአትና ከርኩሰት የሚያነጻው ምንጭ ነው፡፡ ለዚህ የምንጠቅሰው፡-

1. በ(ዕብ.10፡22)፤ ከክፉ ሕሊና ለመንጻት ልባችንን የምንረጭበት ጥሩ ውኃ፣
2. በ(ቲቶ3፡3፣ ከተዘረዘረ ኃጢአታችን ሊያነፃን (ቁ.4-7) የሚነበበው የእግዚአብሔር ቸርነቱና ምሕረቱ በተገለጠ ጊዜ ለአዲስ ልደት በሚሆን መታጠብ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል በእኛ ላይ ተትረፍርፎ የፈሰሰው አማቢው የፈላ ሣሙና ውኃ (ሚል.3፡1-4) መንፈስ ቅዱስ ሲሆን፣

3. በ(ሕዝ.36፥25-27) ክርኩሰት፣ ከኃጢአት እና ከድንጋይ ልብ አጽድቶን አዲስ ልብ፣ አዲስ መንፈስ አድርጎ የሚለውጠው የመርጨቱ ጥሩ ውኃ፣
4. በ(1ዮሐ.1፥5-7፤ ቁ.7) ላይ የተመለከተው ከኃጢአታችን ሁሉ የሚያነጻ ብርሃን የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው፣ ወደ ብርሃን ስትወጣ ኃጢአትህ ተወገደ፤ አንተ ወደ ብርሃን እርሱ ወደ ጨለማ፡፡
5. በ(1ቆሮ.12፥13) ላይ እንደሚነበበው «አይሁድ ብንሆን፣ የግሪክ ሰዎችም ብንሆን፣ ባሪያዎችም ብንሆን፣ ጨዋዎችም ብንሆን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንሆን ዘንድ ተጠምቀንበትና ከአንዱ ፅዋ የጠጣነው አንዱ መንፈስ» ነው የክርስቶስ ደም፡፡
6. በ(ዮሐ.4፥10፥13-14፤ 7፥37-39) የተመለከተው ጌታ ኢየሱስ የሚሰጠውና ከጠጣው ሰው ውስጥ፣ (ከሆዱ) ለሌሎችም ሕይወት ይሆን ዘንድ የሚፈልቀው መንፈስ የሕይወት ውኃ የክርስቶስ ደም ነው፤ ማለትም ይህን ውኃ በ(ኤር.2፥13፤ ም.17፤ 13) በሚታየው ዓይነት የሕይወት ውኃ ራሱ እግዚአብሔር ሆኖ እናገኘለን፡፡ ከኃጢአት ክርኩሰት ሊያጥብ የሚችለው እግዚአብሔር ወይስ የተባለው ደም ነው? ኢየሱስ በሽተኞችን ከበሽታቸው፣ ኃጢአተኞችን ከኃጢአታቸው ለምጻሞችን ከለምጻቸው ያነጻ፣ ሙታንን ያሥነሣ የነበረው ከውጫዊው አካል ከሰውነቱ በሚፈስስ ደም ነበር ወይስ ከውስጣዊ ሰውነት ከማንነቱ በሚፈስሰው ቃሉ በመንፈሱ ነበር? ኢየሱስ ይፈውስ፣ ያጥብ፣ ያነፃ የነበረው ከውስጥ ማንነቱ በሚፈልቀው ቃሉ ማለትም በመንፈሱ እንጂ ከውጫዊ ማንነቱ አልነበረም፡፡ (ማቴ.8፥8፤ ቁ.17/ለ፤ 15፥28፤ ማር.1፥40-42፤ 2፥1-5፤ ሉቃስ 7፥48-49፥17፥12-15፤ ዮሐ.5፥2-9...) ዓለማትን በፈጠረበት በቃሉ (በልጁ) (ዕብ.1፥2) ሁሉ በእርሱ በሆነበት በቃሉ፤ (ዮሐ.1፥1-4) ሁሉም ቃሉ፤ ሁሉም በቃሉ መሆኑን እንዳንዘነጋ ልንጠነቀቅ ይገባል፡፡ ቃሉን ማለት መንፈሱን በማጠቡና በማንጻቱ አገልግሎት አንፃር ስናይ ምን እንበለው? አዎን፣ ደምና ውኃ



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፤ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፤ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16



እንላለን፡፡ በአዲስ ኪዳን የሚፈለገው የውጫዊ አካል መንፃት ነው ወይስ የውስጣዊ አካል መንጻት? የብሉይ ኪዳኑ ቁሳዊው (ፍጥረታዊ) ደም ውጭን ያነጻል ወይስ ውስጥን? ያኔ ቢሆንም እኮ ቅዱስ በመሆኑ ሳይታይ በውስጥ በቀዩ ደም መጋረጃ ተሸፍኖ ደም መሆኑ ሳይታወቅ ይፈስ የነበረው የማንፃት ደም መንፈሱ/ቃሉ ነበረ፡፡ ውስጣዊው ደም ውጭን፣ ውጫዊው ደም ውስጥን አይሸፍንም፡፡ በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ከማንነት በውጭ በመጋረጃ በሚመለክበት ገዜ ውጫዊ መንፃት፣ ውጫዊ በረከት፣ ውጫዊ ሰላም ይገኝ ነበረ፡፡ በውጭ በሆነበት ጊዜ ይፈራል፣ ይከበራል፡፡

አሁን እግዚአብሔር ወደ ውስጣችን ቅዱስ መቅደስ ገባ ብለን በምንሰብክበት አዲስ ኪዳን ዘመን ሊሆን የማይችለውን፣ ውጫዊውን ለውስጥ፣ ውስጣዊውን ለውጭ በማድረግ በማደበላልቅ ብዙ ጊዜ ግራ ስንጋባ እንታያለን፡፡ በእጅ ያለ ወርቅ፣ አይደምቅ እንደሚባል በውስጣችን ማንነት አማኑኤል ሆኖ እጅግ ሲቀርብ ጊዜ እንደ ቀድሞው አይፈራም፣ አይከበርም ተናቀ፡፡ በውጭ የነበረ ሕጉም ክርስቶስ ራሱ እየሆነ ከሕግ በታች በመምጣቱ ውጫዊው እስራኤል ከውጫዊ በሽታ፣ ከውጫዊ ሞት ተፈወሰ፤ ለውጫዊ ረኃብ ቁሳዊ እንጀራ ባረከ፣ በውጭ መገበ፤ ዘላቂና ዘላለማዊ ያልሆነ ሥራ ሠራ፡፡

ደምን በተመለከተ ስንነጋገር፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው ዓለም ሁሉ አጽንኦት ሰጥቶ የሚሰብከው የእውነት እውነተኛ ደሙን ማለትም ከውስጥ ማንነቱ የሚፈልቀውን ቃሉን ነው ወይ? አይደለም፣ ከውጭ ማንነቱ ለጊዜው የፈለቀውን ደሙ እንጂ ከውስጥ ማንነቱ ዘላለም የሚፈልቀው ቃሉ የተናቀ ነውና፡፡ ስለደሙ ጭምር የሚነግረንን ቃሉን፣ በቃሉ ከተገለጠው ደሙ ለይተን መመልከቱ አደገኛና አሳሳች ማስጨበጡ ተዘነጋ፡፡ የኢየሱስ ደምም በቁሳዊነት መልኩ ብቻ የሚታይ ሳይሆን መንፈሳዊ ገጽታው ከቃሉ ጋር የተሳሰረ መሆኑ ነው አልታይ ያለው፡፡ እኛ ግን የሚታየውን የጊዜውን ሳይሆን የማይታውን የዘላለሙን እንሰብካለን፡፡



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፤ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፤ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

## ክፍል አራት
## ሥጋ እና አፈር

«ሥጋ» ማለት ምን ማለት ነው? በተለምዶ ሥጋ የሚባለው ሲተረክ በውጭ የሚታየው እርጥቡ፣ ከባዱ፣ መጠንና ልኩ ውስን፣ ንብረትነቱ የምድር የሆነና ወደ ምድር ተመላሹ፣ ክፍለ-አካል ቁሱ ነው፡፡ እግዚአብሔር አፈር ያለውን ሰውነት እኛ፣ በተቃርኖ ሥጋ ነው ማለታችን፣ ሰው የተባለውን ሁሉ ሰው የእግዚአብሔር ተቃራኒ አድርጎታል፡፡ ዳዊት ሲናገር፣ «ፍጥረታችንን እርሱ ያውቃልና፣ አቤቱ እኛ አፈር እንደ ሆንን አስብ (መዝ.104፡14)»፡፡

ሥጋ ደግሞ በአዲስ ኪዳን አስተምህሮ መሠረት በመጋረጃ ባልተከደነ ፊት (2ቆሮ. 3፡15-18) ሲታይ እንዴት ነው? ሥጋ በአዲስ ኪዳን ከላይ እንዳየነው እንደ አፈሩ አካል ሰውነት እርጥቡ፣ መጠንና ልኩ ውስን የሆነ ሳይሆን፣ ሥጋ የማይጨበጥ፣ የማይዳሰስ፣ መልክና መጠኑ፣ ልክና ቁመቱ፣ ክብደቱ፣ ወርድና ስፋቱ የማይታወቅ፣ የቅዱሱ መንፈስ አቻ ተቃራኒ የሆነ ባሕሪ ያለው፣ በገሃድ የማይታወቅ ረቂቁ ውስጣዊ ክፍለ-አካል ነው፡፡ የሥጋ ባሕሪው፡- ሥጋ በውጫዊ አካል ውስጥ ኃቢና ቁጭ ብሎና ቁሳዊ አካልን እየላከ ባሠራው ክፉ ሥራው የውጩን ምድራዊ ክፍለ-አካል እርጥቡን እያስወነጀለ፣ እያሰቃየ፣ እያስኮነነና ለአደጋ ሁሉ እየዳረገው የሚኖርና በሠራው ኃጢአት እንዲሰቀል እግዚአብሔር የፈረደበት (ገላ.5፡ 24፣ 2፡20) ወንጀለኛ የሆነ ልዩ የውስጥ ሰውነት ነው፡፡ ውጫዊው አካል አፈር ሆኖ ሳለ በዚህ በውስጣዊው በወንጀለኛው አካል ሰያሜ ሥጋ ተብሎ ከመጠራቱም የእርሱን ክፉ ሥራ በአባሪ ተነባባሪነት ከውስጥ ወደ ውጭ እያስተላለፈ ከመኖሩም የሚመጣበትንም ውጫዊ ፍርድ በጋሻነት በውጭ እየተቀበለ ይኖራል፤ እስከ ሞት ሽረት ድረስም ይመክትለታል፣ (ይዋጋለታል)፡፡





ሥጋ በእውነት እውነቱ ሲመረመር በአዳም ኃጢአት የተጫነብን ጥምብ ዕዳ፣ የሞት ጥላ ጭምብል ነው፡፡ ሥጋ የመንፈስ ተቃራኒ ግራ ጎኑ፤ ወደ ግራ ሳቢ አደገኛ ኃይልም ነው፡፡ በብርሃን ሲታይ ሥጋ በኃጢአት ምክንያት እንሰቃይበት ዘንድ የተለጠፈብን ሞትህ፣ ገዳይህና ሰይጣንህ ነው እንጂ ሕይወትህና አካል ገላህ ከቶ አይደለም፤ በብርሃን ካልሆነም ሥጋ ሰይጣን ስለሆነ ከቶ የሚታይና የሚጨበጥ ነገር አይደለም፡፡ አረጋግጠን በተረዳነው መሠረት ደግሞ ሞት፣ ሞት ሳይሆን፣ ኃጢአት ነው ሞት፡፡ እርሱም የዘላለም ሞት፡፡ ከዘላለም ሞት ነፃ መውጣት የሚቻለው ጊዜ ሳይሰጡ አሁን፣ ዛሬ ኃጢአትን መትፋተና ከትፋቱ ደግሞ መሸሸ ሲሆን ለዚህ ችላ ማለትና ጊዜ መስጠት ራሱ ሌላ ተጨማሪ ኃጢአት ነው፡፡ ችላ የምትለውም አንተ ራስህ ሳትሆን በማህፀን ተለውሶ አብሮ ተፈጥሮ የተወለደ (መዝ.58፡3፣ ም. 51፡5) መቶ በመቶ አንተን ራስህን ማንነትህን ሆኖ ተዋኸዶ የኖረ፣ ያለ እግዚአብሔር ብርሃን መነፅር ማየትና መለየት የማይቻለው አካል ነው፡፡

ሥጋ፣ የሥጋ ቁርበትም ሆኖ አብርሃም እርሱን ገፍፎ እስኪጥል ድረስ ወደ እግዚአብሔር ፊት ብርሃን ሊወጣ ያልቻለው መጋረጃ በእግዚአብሔርና በእኛ መካከል ተዘርግቶ ብርሃን እንዳይደርሰን የጋረደና በውስጣዊ ጨለማ እንድንዋጥ መንስኤ የሆነ የጥል ግድግዳ የተባለው ነው፡፡ እርሱን በትክክለኛ ንሥሓና በዳግም ልደት በማፍረስ ከወዲህ ጨለማ ግርዶሽ ግድግዳውን ሰንጥቀን ወደ ማዶ ወደ እግዚአብሔር ሕይወት ብርሃን እንሻገር ነው፤ (ዮሐ.5፡24) ጥያቄው፡፡ ሥጋ ቀደም ሲል እንዳየን ሁሉ የገዛ አካል ሰውነታችን መስሎ በውስጣችን መሽጎ የሚኖረውን አቅፎ መመሳለስ ከሞት ጋር ተቃቅፎ መመሳለስ ለመሆኑ ውስጥ፣ የልቡና፣ የኩላሊት የመቅኔ ብርሃን የሆነው የእግዚአብሔር ቃል መጽሐፍ ምስክር የሚያረጋግጠውን መናቅ በገዛ-ራስ አላይም፣ አልሰማም ብሎ ገደል መግባት ነው፡፡ ሥጋ ደግሞ የመንፈስ ተቃራኒና የውስጣችን

የውስጠኛው ጥቁር መጋረጃ፣ የልቡና ጨለማ ሆኖ የእግዚአብሔርን ክብር ከማየት የታወርንበት ክፍለ ሰውነታችን ነው፡፡

መንፈስ ማለት እግዚአብሔር ራሱ ስለሆነ ሕይወት፣ ብርሃንና ሰላም ሲሆን፣ «ሕይወት» ደግሞ የሞት ተቃራኒ ነውና የመንፈስ ድምፅ ሕይወት ሰላምና ተስፋ ነው፡፡ እንግዲህ ሕይወት የሞት ተቃራኒ ከሆነ፣ መንፈስ የሥጋ ተቃራኒ፣ እንደ ተጻፈውም የመንፈስ አሳብ የሥጋ አሳብ ተቃራኒ ነው፡፡ «ሥጋ» ሞት ነው፤ ሥጋ ያለ ምንም ጥያቄ የሰይጣን አካል ብልት ጉዳዩን አስፈጻሚ ነው፤ የመንፈስ ሕይወት ምንጭ እግዚአብሔር እንደሆነ የሥጋ ሕይወት ምንጭ ያለ ጥያቄ ሰይጣን ነው፡፡ ያለ ሥጋ ሰይጣን እንደልቡ ሊፋንንም ሆነ ራሱን ሊገልጥ አይችልም፡፡ ይህን ከሮሜ 8፡5-7 ጋር ስንመለከት የበለጠ ግልጽ ይሆንናል፡፡

ሀ/ እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉ (ቁጥር 5) ከሥጋን ነገር አሳሳቢው የትነኛ፡፡

ለ/ ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነው፤ (ቁጥር 6) (ራዕ.6፡8)፡፡ ሞት፣ ነፍሰ-ገዳይ ማለትም ሰይጣን መሆኑ ተጽፏል (ዮሐ.8፡44/ለ፤)

ሐ/ ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነው፤ ቁጥር 7፤ «ጥል» ጠላት ሰይጣን መሆኑ ደግሞ ተጽፏል፤ (ማቴ.13፡28፣ ቁ.39)፡፡ የሥጋ ፍሬ እርሱም የሰይጣን ፍሬ ማለት ነው (ገላ.5፡20)፡፡ ሥጋ፣ የሰይጣን መራቢያ ስለሆነ ሰይጣን አድሮበት ክፉ ፍሬ ያፈራል፡፡ የሥጋና የሰይጣን አሳብ አንድ ነው የተባለውን ይህ ግልፅ ያደርገዋል፡፡

በተጨማሪም የዓለምን፣ የሰይጣንና የሥጋን ቁርኝት ያዕቆብ ሲገልፅ ታችኛዪቱ ጥበብ የሥጋ፣ የምድርና የአጋንንት ናቸው ብሏል፤ (ያዕ.3፡15-18)፡፡ ሰይጣን፣ ውጫዊ፣ ቁስ አካላዊ ሞት ነው ወይስ ውስጣዊ፣ መንፈሳዊ ሞት ነው? ነፍሰ-ገዳይ ተብሏል እንጂ ሥጋ ገዳይ አልተባለም፡፡ ሥጋ በውጭ፣ የውስጥ ሥጋ ጥላ (መንፀባረቅ) ሆኖ የውስጡ መገለጫ ነው፡፡



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፤ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፤ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16



እግዚአብሔር የውስጥን ማንነት ስለሚመለከት በፊቱ በደም ያልተሸፈነ ሥጋን ማየት አይፈልግም፡፡ ውጩ በደም ሊሸፈን ከቶ አይችልም፣ እስራኤላዊ ማንነት ከሸለፈት የወጣ ማንነት ስለሆነ አሕዛባዊ ማንነት አይደለም፤ ደም የሚሸፍነው በእግዚአብሔር ፊት የሚታየውን ማንነት እንጂ ከሸለፈቱ ማዶ ለቀረ አሕዛባዊ ማንነት አይደለም፡፡ በነቢያት የተራቆተውን ብታይ ታለብሰው ዘንድ ሲል፣ (ኢሳ.58፡7/ለ፣ ኢዮብ 31፡19፣ ሕዝ.18፡7ቁ.16፣ ማቴ.25፡36)፣ በውጭ በሰው ፊት የተራቆተውን ወይስ በውስጥ በጌታ ፊት የተራቆተውን ነው? እግዚአብሔር ሰው እንዲያይ ያያል? አያይም፤ (1ሳሙ.16፡6-7) እግዚአብሔር የተራቆተውን ሲያይ ምንን ያለብሳል? በፊቱ መራቆት እንዴት ነው? በእግዚአብሔር ፊት መራቆት፣ ልብስ ተገፍፎ መገኘት ነው ወይስ ሸለፈትን ተገፍፎ መገኘት ነው? ሸለፈትን ተገፍፎ መገኘት ሁሉንም ተገፍፎ መገኘት ነው፤ ከምንም ሥራችን ባዶ፣ ዜሮ ሆኖ መገኘት ድል አድራጊነት ሆኖ የሚታይ ነው፡፡ አዳም ባዶ፣ ዜሮ ሆኖ ከመገኘት ምን እንደሆነ እናስታውሳለን፤ (የእጅ ሥራ የሆነ ቅጠላ ቅጠል) ይህ ለእኛ ብርቱ ማስጠንቀቂያ መሆን አለበት፡ ፡ ይህ ባሕሪ ከዲያብሎስ ነው ወይስ ከእግዚአብሔር? መጽሐፍ የሞተ ሥራ የሚለው የትኛውን ነው? ልብ እንበል፤ ያ ዲያብሎሳዊ የሆነው የአዳም ባሕሪ አልለቅ ብሎን፣ በጌታ ፊት ርኩስ በሆነው የድካማችን ውጤት፣ በጸሎታችን፣ በፆማችን፣ በምፅዋታችን፣ በጥምቀታችን፣ በአገልግሎታችን እንሸፋፈናለን፡፡ እስራኤል ሸለፈቱን ተገፍፎ እንደተራቆተ ስለሚታሰብ፣ እግዚአብሔር እስራኤልን ደምን ማለት፣ ጽድቅን ያለበሰዋልና በዚያ ተምረን፤ የአዳም መሸፈኛ የሆነ የሞት ቁርበት አስወግደን በፊቱ ብንራቆት እግዚአብሔር ሕይወትና የጽድቅ ልብስ የሆነውን ደም፣ ክርስቶስን ያለብሰናል (ገላ.3፡27)

ሥጋና መንፈስ፡- መንፈስና ሥጋ ሁለቱም እንደ ርብቃ ዕንስ በማህፀናችን ውስጥ የሚገኙ ዔሣውና ያዕቆብን የሚወክሉ እርስ-በርስ አቻ



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፤ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፤ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

ጠላቶች ናቸው፡፡ ያለ ሥጋ ሰይጣን ሆነ መከራ፣ በሽታ ሆነ ሥቃይና ሞት የለም፡፡ መንፈስን መግደያ ሥጋ እንደሆነ ሁሉ ሥጋን መግደያ መሣሪያም ደግሞ መንፈስ ነው፡፡ ሥጋ፣ ኃጢአት፣ ሰይጣን ተጣምረው ነው እግዚአብሔርን ለመጻረር የቻሉት፡፡ ሰይጣን፣ ሥጋ፣ ኃጢአት፤ አንድ ሆነው፣ በተቃራኒ ሦስትና አቻ የሆኑ ርኩሳን ሥላሴዎች ናቸው፡፡ 1/ ሰይጣንን፣ 2/ ሥጋን፣ 3/ ኃጢአትን፣ መከፋፈል ከቶ የማይቻል ነው፡፡ እንዲህ ያለ ከፋፋይ ከተገኘ ቅዱሳን ሥላሴንም ከፋፍሎና ለያይቶ ሦስት በማድረግ በሦስት በተለያየ ቦታ ማስቀመጥ ይችላል ማለት ነው፡፡

ከሰይጣን አካላት አንዱ አካል የሆነው ሥጋ ከኃደለ ቀሪው አካል ተንቀሳቃሽ (Active) መሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ ሥጋን በወንጌል ስለት ተቆርጠን ቆርጠን፣ በጥምቀት ተቀብረን የምንቀብረው ሥጋን በማስወገድ ዲያብሎስን በውስጡ ምድራችን እንዳይንቀሳቀስ አካለ-ጎዶሎ (ሽባ) ለማድረግ ነው፡፡ ሥጋ ከሌለ ዲያብሎስ የለም፡፡

ሥጋን በተመለከተ ስንነጋገርም፣ መሠረታዊው፣ የአዳምን ሥጋ ከጌታ ኢየሱስ ሥጋ ጋር ማየት አለብን፤ የአዳም ሥጋ ከምድር ምድራዊ መሆኑን የፍጥረትና የእርግማኔ ታሪክ ይመሰክራል፤ በታሪክ ደረጃ፤ (ዘፍ.2፡7፣ 3፡19/ለ፣ መክ.12፡7፣ 1ቆሮ.15፡47-48፤) የኢየሱስ ሥጋ ከሰማይ ሆኖ (ዮሐ.6፡50-58፣ ቁ.38፣ ቁ.50-51፤) ወደ ነበረበት ተመላሽ መሆን ያለበትን፣ አለ ቦታው ወደ ምድር የቀበሩት በጣም ጥሩ ሆኖ ተመልሶ ወደ መጣበት ሰማይ ሲመለስ ከምድር ውስጥ ቀድሞ አለአግባብ ተቀብረው ለተገኙት የሕይወት ምግብና ኃይል ሆኖአቸው አወጣ፡፡ እርሱ የተቀበረበት ምድርም ቢሆን የእግዚአብሔር ዓይን የማይለየው የእሥራኤል ምድር መሆኑ የእስራኤል አገር የሞትና የትንሣኤያቸው ልዩነት በሚለው ርእስ ሥር ታትቷል፡፡ በታሪክ ደረጃ ሲነገር የኢየሱስ ሥጋ መድኃኒት ከመሆኑም በእኔና በአንተ ውስጥ ተዘርቶ የምንበቅልበት ዘር እንጂ በስብሶ እዚያው የሚቀር ነገር አይደለምና፡፡ ክርስቶስ ከሰማይ







የሆነና፣ በሰማይ የሚኖር ነው፤ (ዮሐ.3፡13፣ ም.6፡62፣ ም.6፡38) ...ወዘተ ክርስቶስ ቃል የሆነ ከሰማይ የወረደ የእግዚአብሔርን ድንኳን፣ ማደሪያውን፣ ሕያው መቅደሱን (ዙፋኑ) ሆኖ ራሱ የተሠራበት ቃል ነው፤

ሙሴ ኮፒውን፣ ምስሉን ይዞ ሲወርድ፣ ኢየሱስ ዋናው ሆኖ መጣ፡፡ ሥጋ የሆነው ቃለ-እግዚአብሔር ማደሪያው የሆነ ድንኳኑን ራሱ ሠርቷል (ዮሐ.6፡49-51፣ ቁ.38፣ 41፣ ሉቃስ 1፡38)፤ ሰው ራሱ ፈራሽ እንደ መሆኑ መጠን እንደ ራሱ ፈራሽ የሆነ ድንኳን ከማንነቱ በውጭ ሠራ እንጂ ሕይወት ያለውን (ሕያው ማደሪያ ሊሠራ) አልቻለም፡፡ እግዚአብሔር ለራሱ የሚሆን እንደ ራሱ ሕያው የሆነ ድንኳን ራሱ ሠራ፡፡ ነቢዩ ሙሴ በተራራ ላይ በነበረበት ወቀት ይህን ዘላለማዊ ድንኳን (ክርስቶስን) በማየቱ ነው፣ ምሳሌውን በምድር ላይ መሥራት የቻለው፤ (ዕብ.8፡5፣ ዘፀ.25፡40)

መለስ ስንል፣ የጌታ ሥጋ ከማርያም ተወሰደ እንጂ ከሰማይ ነው ለማለት እንዴት ይቻላል? አንደኛ ሥጋው ከሰማይ መሆኑን ከፍ ብሎ የተመለከቱ ታሪካዊ ጥቅሶች በማያሻማ ሁኔታ ይመሰክራሉ፡፡ ሁለተኛ፣ የእግዚአብሔር ዘር የሆነው ቃል (ማቴ. 1፡3-42) በገብርኤል ወንጌላዊነት በማርያም ጆሮዋ በኩል በልቡናዋ (በእስራኤላዊ ማሕፀን) ተዘርቷል፡፡ ማስተዋል ያለብን ሰማይም፣ (የእግዚአብሔር) መንግሥትም ፊደላዊ (ፍጥረታዊ)ው ገሀዱ ሰማይ ሳይሆን፣ በተቀደሰ፣ በተሰወረ፣ በመጋረጃዎች በተሸፈነ፣ በስውር ያለ ሰማይ መሆኑን ነው፡፡ (ሉቃስ 17፡20-21፣ ራዕይ 21፡1-4፣ ዘሌ. 26፡11-12፣ 2ቆሮ.6፡16፣ ኢሳ. 40፡22) በጽሑፉ ጭብጥ መሠረት ሲታይ ቅዱስ የሆነ ነገር ሁልጊዜም ካልተገረዘ ዕይታ የተሰወረ ነው፡፡ የጌታ ሥጋ ከአንደኛ ሰማይ በመልአኩ በኩል ወደ ሁለተኛ ሰማይ ወደ ማርያም ከፍታ ወደ ልቧ ወርዷል፤ ትንቢቱ በእስራኤል እንዲፈጸምም ከልቧ ወደ ማኅፀኗ ወርዷል (ወደ እስራኤላዊ ማህፀን)፡፡ እስራኤል ቅዱስ ሕዝብ ሲሆን፣ እሷ ያልተበከለች ስለሆነች ይበልጥ ቅድስት በመሆኗም

ቃሉ የተዘራበት በተቀደሰና ከእኛ ወደ እግዚአብሔር ከፍ ባለ ሥፍራ ነው፡፡ ስለዚህ ቃሉ (እግዚአብሔር) በቅድስና ከዚህም የሚበልጥ ሕያው መቅደስ ክርስቶስን ለራሱ ሠርቶ በሰዎች መካከል ሆኖ የፍቅር ግዳጁን ተወጥቷል፡፡ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር እንጂ ከሥጋ፣ ከደም፣ ከወንድ ፈቃድ አይደለም፤ የክርስቶስ የሆኑትም እንዲሁ በተመሳሳይ ደረጃ፣ (ዮሐ.1፥12-13)፣ "ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ፣ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም፡፡ ሥጋ ከሰማይ ወረደ ማለትን እንዴት እንመለከታለን? የአፈር አካል ሳይሆን ሥጋ ሁልጊዜም ከፍታን፣ ክብርን ዕብጠትን፣ መንጠራራትን ስለሚወድድ እግዚአብሔርን ሲቀናቀን በሰማይ ላይ ነው፡፡ የክርስቶስ ሥጋ ግን መሥዋዕት ሊሆን ወረደ፣ ተዋረደ ነው፡፡ የሰው ያልተገረዘ ሥጋ በትዕቢት ከፍ፣ ከፍ በማለቱ ምክንያት በተመለከትነው ሁኔታ ዕብጠትን ይፈጥራል፤ ዕብጠቱ ደግሞ በጌታ ፊት መግል ይፈጥርና ርኩስ፣ ብስበስ ስለሚሆን ለመሥዋዕትነት አያገለግልም፡፡

ቃል ሥጋ ሆነ

ክርስቶስ ማለት ቃል ማለት መሆኑን እያስታወስን፣ የአሮን በትር ትርጉም ምንድን ነው? የሐሮን በትር የእስራኤል በትር ነው፤ የእስራኤል በትር ክርስቶስ ነው፡፡ በትሩ እባብ የሆነውስ ለምንድር ነው? ቃል ሥጋ የሆነው ነው፡፡ የሐሮን በትር እባብ ሆና እባቦችን ማለት ሞትን ሁሉ እንደዋጠች ክርስቶስ ሥጋን (ሞትን) ሁሉ መዋጥ ይችል ዘንደ ሥጋ /ሞትን ሆነ፡፡ አስቀድሞ ወድቆ፤ ማለት በመዋረድ ወድቀው እንዲዋረዱ አደረገና ወድቆ ግለ፣ ተወርዶ አወረደ ሞቶ ገደለ ነው፡፡ የአሮን በትር እባብ የሆነው፣ የግብፃውያንን በትሮች ወደ እባብ ለመለወጥ፣ ለመዋጥና ለመደምሰስ አስቀድሞ አይቶ ነው፡፡ የግብፃውያን በትሮች የሚያደርጉትንና የሚሆኑትን ማየት ስለማይችሉ ዕውሮች ናቸው፡፡



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16



የአሮን በትር፣ ሆኖ አድራጊ ነውና አስቀድሞ እርሱ እባብ ሆነ፡፡ ተመልሶ በትር ለመሆን እምነት አለውና፡፡ እባብ ሰይጣን ነው፡፡ የእስራኤል በትር የግብፅን በትሮች ሁሉ ስለማረከ አሁን በነርሱ እነርሱን መታ፡፡ በራሳቸው በትር ራሳቸው ተማቱ፣ የእግዚአብሔር ጥበብ ነው፡፡ እግዚአብሔር ብቻውን የእባቡን ራስ (ፈርዖንን) ይቀጠቅጥ የነበረው፤ የግብፅ በትሮች በሙሉ ተውጠዋልና ነው፡፡ ትርጉሙም፣ ከያዕቆብ የሚወጣው ኮከብ፣ ከእስራኤል የሚነሣው በትርና ከእሴይ ግንድ የሚወጣው ቁጥቋጥ የእስራኤል በትር ክርስቶስ ነው፤ (ዘኁ.24፥16፣ ኢሳ.11፥1) የሙሴ (የአሮን) በትር፣ እንደ ፍጥረቱ በትር ሆኖ ኖሮ ቢመጣ የግብፁም በትር ያው እንደ ነበረ በትር ሆኖ ይቀራል እንጂ ወደ እባብነት አይለወጥም፣ አይዋጥም ነበረ፡፡ አንድን ነገር መዋጥ የእባብ ተግባር እንጂ የበትር ተግባር አይደለምና ይህ ክስተት ነበረ፡፡ እርሱ ሥጋ ሳይሆን ሥጋ ሆነ፡፡ ተመልሶ ቃል ለመሆን እምነት አለውና፡፡ ቃል ሥጋ የሆነው ሥጋን ለመዋጥና ለመደምሰስ ነው፡፡ እርሱ ወረደ፣ ሁሉ ወረደ፤ እርሱ ተዋረደ፣ ሁሉ ተዋረደ፣ ሁሉ ተዋረደ፣ እርሱ ሞተ፣ ሁሉ ሞተ፣ እርሱ ሁሉ ነውና፡፡ ሞቶ ሞትን ገደለው፣ ዋጠው፣ ጣፋጭ ምግብ ነው፡፡ እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ «... ሞትን ለዘላለም ይውጣል፣ ጌታ እግዚአብሔርም ከፊት ሁሉ እንባን ያብሳል፣ የሕዝቡንም ስድብ ከምድር ሁሉ ላይ ያስወግዳል...ኢሳ.25፥8፤ ከ1ቆሮ.15፥54» ጋር ይነጻጸር፡፡ ሞትን ለዘላለም ይውጣል ሲባል፣ ምንን ይውጣል? ሞት ምንድን ነው? በተመለከትነውና ባረጋገጥነው መሠረት ሞት ሰይጣን፣ ሥጋ፣ ኃጢአት ነው፡፡

ክርስቶስ ሞትን ለምን ዋጠ? ሞት ማለት ሰይጣን ሕይወትን ስለዋጠ፣ የዋጠ እንዲዋጥ፣ የገደለ እንዲገደል የበላ እንዲበላ በሙሴ ሕግ የታዘዘው ፍርድ እንዲፈጸም ክርስቶስ በቀል የእርሱ ነውና ሕይወትን ውጦ የደመሰሰውን ውጦ መደምሰስ ስላለበት ሞትን/ሰይጣንን ዋጠው፡፡ ሰይጣን ሕይወትን የዋጠው እንዴት አድርጎ ነበር? ሰይጣን ሥጋ ካልሆነ



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

ሕይወትን መዋጥ ስለማይችል የእባብን መርዛም ሥጋ ሆነና ውጦ መግደል ቻለ፡፡ አዳሞች መዋጣቸውን ሳያውቁ ተዋጡ አንባቢ ያውቃል ወይ? ተዋጡ፣ ማለት በኃጢአት ውስጥ ሰጠመ ማለት ነው፣ ሰይጣንና ኃጢአት በሥጋ ክብር መጋረጃ ውስጥ የሚኖሩ ናቸው፡፡ ሥጋ እነርሱን ለመጋረድ የተቀባ እርኩስ ኪሩብ ነው፤ መንጸባረቃቸው፡፡ ስድብስ ምንድን ነው? (ኢሳ.25፥8) ስድብ፣ በ(ራዕይ 13፥1) ላይ እንዲህ ይነበባል፤ "አንድ አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፣ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፣ በቀንዶቹም ላይ ዘውዶች፣ በራሶቹም ላይ የስድብ ስም ነበረው፡፡ በስድብ ስም የሚጠራ አውሬ ሰይጣን ስለሆነ ጌታ እግዚአብሔር የሆነው ክርስቶስ ሞት የሆነውን ሰይጣን እርሱንም ኃጢአትን ከነስሙ (ስድብ) ጋር ጠቅልሎ ዋጠው (ቀበረው) ማለት ነው እንደ አሮን በትር፡፡ እንዲህ ባይሆንና ክርስቶስ በአምላክነቱ ክብር እና ግርማ ወይም በትር እንደሆነ ወደ ዓለም ቢመጣ ኖሮ 1/ አቻ አይደለም፤ 2/፣ ከሰይጣን (ከሥጋ) አንዱም (ሊጋጠመው) ሊዋጋው አይወጣም ይሸሽዋል እና አይዋጥም ነበር፡፡ ስለሆነ አሁን ክርስቶስ ሥጋ ሆነና መስሎአቸው ቀረበ፣ ሁሉም ሰይጣኖች ደፍረው ቀረቡትና በሥጋው ጠቅልሎ በማያዳግም ሁኔታ ደመሰሳቸው፡፡

የአዳም ሥጋ ለመሥዋዕት የማይሆን ርኩስ የሆነው የሰይጣን ቃል (መንፈሱ) በእባቡ መልእክተኝነት በኩል ተልኮ ስላደረበት፣ ስለተዘራበት ርኩስ እንደሆነ ሁሉ፣ እንዲሁ ይህ የክርስቶስ ሥጋ፣ መንፈስም፣ እሳትም የሆነው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ስላደረበት በራሱ፣ በመቅደስ ውስጥ ከዉት እስከ ማታ ድረስ ብቻ ሳይሆን፣ ዘወትር እየነደደበት የኖረ (ዘፀ.27፡31) በመሆኑ የተቀደሰ ሕያው መሥዋዕት ሆኖ ለእግዚአብሔር ዘወትር ባለ ማቋረጥ ሊቀርብ ችሎአል፤ ክብር ይሁን፡፡ ሥጋ ለክርስቶስ ማለት ለመንፈስ ተገዝቶአል፣ ሰይጣን በኢየሱስ ላይ አዳች የለውም፤ (ዮሐ.8፥49) እሳቱ ዘወትር ይነዳል!! አይደፍረውም፡፡ ክርስቶስ ከአብ የተነሣ በሥጋ ሁሉ ላይ ባለሥልጣን ገዥ እንደሆነ፣ (ዮሐ.17፥2)







ይገልፃል፡፡ (ማንም ሰው ለአብ ተገዢ ከሆነ በሥጋ ሁሉ ላይ ገዢ ነው፡፡) አብ በአንተ ገዥ፣ አንተ በአብ ሁሉ ላይ ገዥ፤ እርሱ ከላይ ነውና፡፡

ክርስቶስ በሥጋ ሁሉ ላይ ሥልጣን አለው ማለት በሰይጣን ሁሉ ላይ ገዥ ነው ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ሥጋ፣ ከክርስቶስ ጫማ ሥር ሆኖ ለሰላሣ ሦስት ዓመት ቆይቶ (መዝ.110፥1፤ ዕብ.1፥13) በመጨረሻ ታርዶና ተቃጥሎ ተኑ፣ (እንፍዋሎቱ) በእሳት ስላለፈ ተቀድሷልና ለእግዚአብሔር ቀርቧል፡፡ የተረፈ ትርፍራፊ (ፍርፋሪ) ለእኛ ለቡችሎችም (ማቴ.15፥21-28፣ ቁ27) ቃሉ ክርስቶስ ቅዱስ በመሆኑ ተጋልጦ ሳይሆን፣ በምግቡ ተጋርዶ በሰገነቱ ፋሲካ እራት ላይ ቀርቧል፤ ተበልቷል፤ (አንኩ ብሉ) ቃሉ ራሱ ነው፤ ውኃ በደም ተሸፍኖ ደም ነው ሲባል እንደሚቀርብ ቃሉ በምግቡ ሽፋን ምግብ መስሎ ቀርቧል፡፡ ፋሲካ የማለት እውነታው ይህ ነው፡፡ ፋሲካው በሰገነቱ ላይ ሁልጊዜ ቀርቦ እንዳለ ነው፡፡ እሳቱ የት ነበር? ለሚለው ጠያቂ መልሱ፣ እንደ ተጻፈ ሁሉ ቃሉ እሳት፤ ድንጋዩን የሚያደቅ መዶሻ አይደለምን? (ኤር.23፥29) የማይታይ የመንፈስ እሳት፤ ዲያብሎስን እንኳ ከቁርበቱ (ከሸለፈቱ) ጋር አቃጥሎ ጢሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ይወጣል፤ ይህም በንሥሐ ዲያብሎስን ከሸለፈቱ ጋር ቆርጦ በመጣል አልለይ ያለ ሰው ሁሉ ነው፡፡ ከሸለፈቱ ሊቆራረጥ ሲሳሳ ሰውዬው ከዲያብሎስ ጋር በዘላለም እሳት እየጤሰ የእግዚአብሔርን ዕዳ እስከ መጨረሻዋ ሳንቲም ድረስ ለዘላለም ዓለም ሲከፍል ይኖራል፤ ጢሱ የጌታ ገንዘብ ነውና ገቢ ይሆናል፤ የእግዚአብሔር ገንዘብ ተበልቶ (ተውጦ) ከንቱ ሆኖ አይቀርምና፤ ከዚህ ዕዳ ሽሽተን ከማምለጥ በስተቀር የምንከፍልበት ብቃት ከቶ ስለሌለን እግዚአብሔር ራሱ በመሸሸ ብቻ የምናመልጥበትን መማፀኛ ከተማ የሆነውን ክርስቶስን ራሱ አዘጋጅቷልና ቶሎ ወደ እርሱ እንሸሽ (ኢያሱ 20፥1-9፣ ዘኁ.35፥9-34፣ ዘዳ. 4፥41-43)፡፡

ኢየሱስ በፋሲካ እራት ላይ ደቀ-መዛሙርቱ ካዘጋጁት ምግብ አንሥቶ/ለይቶ፣ ትንሣኤ ሰጥቶ፣ ባረከው/ቀደሰው ማለት በምን ቀደሰው?

*በቃሉ፣ (ዮሐ.17፡17) ማለት በሌላ በኩል በእሳት አሳለፈው ማለት ነው፤ ቃሉ እሳት ነውና፡፡ (የተራ ሰዎች ቃል እሳት ሆኖ ነው በጸሎት መሰል ቃል ምግብን እንቀድሳለን በሚል የሚንጠራሩት?) ማንኛውም ነገር ያለ እሳት አይቀደስም፤ አይባረክም፤ ለእግዚአብሔርም አይቀርብም፡፡ እግዚአብሔር ባርኮ ቀድሶና ቆራርሶ ለዓለሙ ሁሉ ሕይወት እንዲሆን የላከው እንጀራ ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ ይህ ልማዱ እንዳይቀርና ለጉራ የተባረከ ነገር የሚበላ ሰው ለመምሰል ብቻ በየቋንቋ፣ በየቤቱ በየቡና ቤቱ ማንም ከምንም ያልተለየ ሁሉ ጌታን ለመምሰልና ጸለይን በሚል ቃል ብቻ ድምፅ ወርውሮ ሲበላ ደግሞ በሌላ መንፈስ ሆኖ ያግበሰብሳል፤ ይህ በጌታና በቅዱስ ሥራው ላይ ምሀረት የሌለው ኃጢአት፤ አስመሳይ እርጉም ሥራ፡፡ መሥዋዕት ግን በሕጉ መሠረት አስቀድሞ ጌታ እግዚአብሔር ማለት እሳት ሳይበላው ባሪያ ማለትም ሰው (በቅድሚያ) ሊበላ አይፈቀድለትም፤ (ሉቃስ 17፡7-8) ሰው ባርያ ስለሆነ ከጌታው ቀጥሎ ይበላል፡፡ የእስራኤል ካህናት እሳቱ (እግዚአብሔር) ሳይበላ ቀድመው ሊበሉ አይፈቀድላቸውም፤ (1ሳሙ.2፡15-16፣ ቁ29፣ ዘሌ.3፡12-17) ክርስቶስ መፈተን፣ መከራ መቀበል መሞትና የኃጢአትን ዕዳ መክፈል የሚችለው በሥጋ ስለሆነ፣ ሥጋ ሆነ፡፡ በሥጋ ሆኖ በመንፈስ በመመላለሱም የእግዚአብሔር ልጅነቱን አስመሰከረ፤ (ሮሜ 8፡14)፡፡ እንደ ግብፅ እስራኤል ለአሥራ አራት ቀን ታሥሮ ለሞት እንደቀረበ አንበሳ ክርስቶስ፣ ሥጋን በመንፈሱ ሥልጣን ኃይል ኃጢአት እንዳይሠራ ሠላሳ ሦስት ዓመት ጠፍሮ አሥሮት፣ በቁጥጥር ሥር አቆይቶት ለመሥዋዕት ቀርቦ አቅርቧል፡፡ ባየር ላይ ከፍ ብሎና ከፍ አድርጎት ተሰቅሎ ሰቅሎት ሞቶ ገድሎት ሲያል ጉድጓድ ገብቶ፣ ሲያል ጉድጓድ ከተተው፡፡*

*ጌታ ኢየሱስ ከመሰቀሉ በፊት የፍጥኝ አሠሩት፣ ኮረኩሙት፣ በጥፊ አሉት፣ በበትር መቱት፣ ጎሸሙት፣ ገረፉት፣ ገፉት፣ ሰቀሉት ...ወዘተ*





*በእርሱ ላይ የደረሰው ማንኛውም በሰው ምስክርነት ሲቀርብ የሐሰት እውነት ይሆናል። እነርሱ በፊደል (በግልፅ) ገፉት፣ አንተንና እኔን በባሰ ደረጃ በስውር (በመንፈስ) ከመግፋት እርሱ ራሱ ያድነን፡፡ ነገር ግን የእውነት እውነቱ በእርሱ የተደረገው ሁሉ በፈቃዱ ብቻ እንጂ ያለ ፈቃዱ ተገድዶ የተቀበለው ነገር ምንም እንደ ሌለ ማስተዋል አለብን፡፡ ፍቅሩ እንጂ ሰማይና ምድር ሁሉ ተባብሮ ምንም ነገር በጉልበት ሊያደርግበት ከቶ አይችልም፡፡ ተገድዶ መከራ ከተቀበለ ደግሞ መከራ የተቀበለው፣ የሞተው እርሱ ራሱ አይደለም፡፡ ተሰቀለ ማለት ሥጋውን (ሰይጣኑን) እንዲሰቀል የተፈረደበት ወንጀለኛውን በመሆኑ ሁሉ እንዲሁ፣ ሥጋውን ተሰቅሎ እንዲፈርድ ምክንያት በመሆን በመስቀል ላይ ፍርድ ሰጠ፡፡ ክርስቶስ አብ ቀድሶት ወደ ዓለም የላከው ነው፤ (ዮሐ.10፡36)፡፡ ኢየሱስ ሥጋውን ራሱ በራሱ ላይ ዳኛ ስለሆነ በመለኮት ኃይሉ ፈርዶበት ገደለው፡፡ ሥጋው ቀድሞም በራሱ ሥልጣን የተገደደውን ቀድሞም የታሠረውን፤ ሳይሞት በፈቃዱ የሞተውን፣ ሳይሰቀል የተሰቀለውን ለፈቃዳቸው አሳልፎ ሰጠ፡፡ የኢየሱስ ሥጋ የደከመው፣ የተጨነቀው፣ የተሠቃየው፣ የተራበው ከምን የተነሣ ነው? ከኢየሱስ ብርቱ ክንድ የተነሣ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ሥቃይ ከማንነቱ በውጭ፣ በመጋረጃ በርቀት ስለሆነ ወደ እርሱ አልቀረበም፡፡ ኃጢአትን እንዳይቀምስና እንዳይጠጣ በሕይወት እንዳይኖር አድርጎ አስራበው አስጠማው፤ አሠቃየው፤ ቀድሞውኑ አንጠልጥሎ ሰቅሎ ገድሎ አቆየው፡፡ ኃጢአት እንደ ውኃ ይጠጣልና፣ (ኢዮብ 34፡9)፡፡*

*ሥጋ፣ የአፈር ክፍለ አካል ተጨባጩ እንዳይደለ በዚህ መጽሐፍ በግልፅ ተብራርቷል፤ ኢየሱስ ሰይጣንን ያሠረበትን ሥጋ ተሸክሞ ራሱ መስቀል ላይ ወጣና ለእግዚአብሔር ተሰቅሎ ለእግዚአብሔር ሰቀለው፤ (ዘኁ.25፡4) ለእግዚአብሔርና ለሰው ሞቶ ለእግዚአብሔርና ለሰው ገድሎት የመሥዋዕቱን ግብግ ለሰማይና ለምድር፣ ለእግዚአብሔርና ለሰው ግዳዩን*

(ምርኮን) አቀረበው፡፡ ብሉ ኢየሱስን ጠጡ ተብላችኋል (ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷል)፡፡ ዓለሙ ሁሉ ለግብግው በወንጌል ቃል ተጠርቷል፤ (1ቆሮ.5፡7፣ ማቴ.22፡1-14፣ ሉቃስ 14፡15-24)፡፡ ጆሮ ያለው ይስማ፡፡ በዚህ ዓለም ግብዣ ሲደረግ ዝርዝሩ እጅግ ብዙ ነገር ተሰብስቦ ይዘጋጃል፣ በእግዚአብሔር መንግሥት ግን ሁሉ በአንድ ላይ ተጠቅልሎ ክርስቶስ ብቻ ነው፤ ልብ እንበል፣ በእርሱ ላይ ምንም አትጨምሩበት አትቀንሱበትም ተብሎ በሕግ ተጽፏል፡፡

መሰቀል እንዴት ነው? የመሰቀል ታሪክ የየት አገር ታሪክ ነው? ለደህንነት መሰቀልና ለጥፋት መሰቀል እንደሚለያዩ የምናውቀው ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ለጥፋት መሰቀል ከጌታ ጋር ተሰቅሎ የጠፋው ሽፍታና የሓማ መሰቀል ዓይነት ሲሆን፣ ለደህንነት፣ ደግሞ የዳነው ሽፍታ በግድ ቢሆንም ለደህንነት የሆነለትና የጳውሎስ ከሰው ዓይን ስውር ቅዱስና እርኩስ ዓይነት መሰቀል የሆነው ከክፍሉ መመልከት ይቻላል፡፡

ነገሩ በወቅቱ የእስራኤል አገር የቅዱስ ሕዝብ ታሪክ ሲሆን አሁን፣ ከትንሣኤ ወዲህ ለእግዚአብሔር ከዓለም፣ ከኃጢአት ለመራቅ ለመቀደስ በስውር መንጠልጠልን ያመለክታል፤ ገላ.2፡20፣ 5፡24፣ ም.6፡14) ይመሰክር፡፡ እኛም ይህን ምሳሌ በመከተል ሥጋን (ሰይጣንን) ተሸክመነው በሰማያዊ ሥፍራ ከፍታ ላይ ተንጠልጥለን ማንጠልጠል ነው፡ ለእግዚአብሔር በፊቱ ተሰቅለን እንድንሰቅለውና ለእግዚአብሔር ሞተን ጠላቱን በመግደል ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንሆን ዘንድ ሕያው፣ ቅዱስ መሥዋዕት ሆነን እንድንሠዋው ያስተምረናል፣ (ገላ.5፡24) ለሰውም፣ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ የመሥዋዕት እንጀራ መሆን የምንችለውም በዚያን ጊዜ ነው፡፡ በሰማያዊ ሥፍራ ለእግዚአብሔር መሞትና በምድር መሞት ቅዱስና እርኩስ ሞት ሆኖ በዚህ ይለያል፡፡ በሌላ አቅጣጫ ስናይ፣ ክርስቶስን ያንጠለጠለው የመስቀሉ ምስማሩ ነጡ ወይስ ፍቅሩ ነው? ከፍቅርና ከመስቀል የትኛው ብርቱ መንጠልጠያ ነው? እኛንስ መስቀሉ





ቢያንጠለጥለን ዋጋ አለው ወይስ ፍቅሩ ቢያንጠለጥለን ዋጋ አለው? ሞት የሞት ምሳሌ ሲሆን፣ መሥዋዕት የመሥዋዕት ምሳሌ ነው፤ የሚታየው ለማይታየው፣ ውጫዊው ለውስጣዊው፤ ምስያ ጥላ ነው፡፡ የሚታየው፣ ጥላው የሐሰት እውነቱ ሲሆን፣ የማይታየው አካሉ የዘላለሙ፣ የእውነት እውነቱ ነው፡፡

የጌታ ጠላቶች የሆኑ ወዳጆች በከፋት ታላቅ ጥቅም ያስገኙት በበኩላቸው ሊገድሉት ሲያዘጋጁት፣ ቀይ ልብስ (ሐምራዊ) ማልበሳቸው፤ (ዮሐ.19፡2/ን ማብራሪያ በአ.መ.ት ይታይ፡፡ የእሾህ አክሊል በራሱ ላይ መጫናቸው፤ በትረ መንግሥት በእጁ አስይዘው የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፣ ሰላም ላንተ ይሁን እያሉ በፊቱ ተንበርክከው መዘባበታቸው፣ አስመሳይ የሽርደዳ ክብር መስጠታቸው፣ የራስ ቅል ወደ ተባለ ከፍታ ላይ አውጥተው በምስማር መቸንከራቸውን፣ እዚያ ላይም፤ እመስቀል ከፍታ ላይ ከፍ አድርገው ሰቅለው የመግደላቸውን ሥነ-ሥርዓት ሁሉ እንዴት እንመለከታለን? ይህ ኢየሱስን ከፍ፣ ከፍ ማድረጋቸው መሆኑን ኢየሱስ ራሱ በ/ዮሐ.8፡28) ላይ ከተናገረው ስንረዳ፣ የእርሱ የራሱ ትንቢትም ፍፃሜ ሲያገኝ መሆኑን እንመለከታን፡፡ እዚህ ላይ ኢየሱስ ሲናገር፣ ‹‹የሰውን ልጅ ከፍ- ከፍ ባደረጋችሁ ጊዜ እኔ እሆን ዘንድ አባቴም እንዳስተማረኝ፣ እነዚህን እናገር ዘንድ እንጂ ከራሴ አንዳች እንዳላደርግ በዚያን ጊዜ ታውቃላችሁ›› ያለው ቃል በትንቢቱ መሠረት ገዳይ ሟቾች ክብር ሁሉ ከሰጡት በኋላ ደግመው ውርደትን ሁሉ እስከ መግደል ድረስ ሲሰጡት ቀዩን ልብስ ገፈፉ፤ በትሩን ከእጁ ነጥቀው ራሱ የሆነውን አብ እግዚአብሔርን መቱ፤ (1ቆሮ.11፡3) እየጋፉትም ወስደው ባዘጋጁት ከፍታ ላይ እንደ ትንቢቱ እንደሰቀሉት ተጽፎ እናነባለን፡፡ ሰዎች ሆነን በጊዜያዊ ከፍ፣ ከፍ እንታወራለን፡፡ ይህ የሞት፣ ሞት መሆኑ አይታየንም

በኢየሱስ ላይ የደረሰ ውርደትና መከራ በራሱ ፈቃድ ብቻ የሆነ ለዚሁ ጉዳይ በዓለማ የተዘጋጀ የገዛ-ራሱ ሥጋ ነው እንጂ ሌላ ማንም አይደለም። ክርስቶስ ለዓለሙ ሁሉ የሚሆነው የዘላለምን ክብር ውጤቱን አስቀድሞ አይቶና ሀውቆ የገባበት ጉዳይ ስለነበር በኢየሱስ ላይ ለደረሰ ውርደትና መከራ ክብር እየሰጠን ማክበርና ማፍቀር እንጂ ምን ዐውቀን እናዝንለታለን? ነገሩ በግርዶሽ በምናየው በእኛ ዓይን ውርደትና መከራ ይምሰል እንጂ ለኢየሱስ ይህ የጊዜው መከራ የዘላለምን ክብር ብዛት እንደሚያፈራ እየተመለከተ መሽሩን ለማጨድ በጉጉት ይጓዝ ነበረ፡፡

እግዚአብሔር ሰውን የሚያውቀውና የሚጠራው በባሕሪውና በመንፈሱ እንጂ በመልኩ ከቶ አይደለም፤ (ማር.3፡17፣ ዮሐ.1፡46፣ ማቴ.3፡7፣ ሉቃ.13፡31-32)፣ የሰው ውስጡ እንጂ የውጪ ገለባው ሰውነት አይቆጠርማ! የውጪ ዕድሞ ከቁጥር ውስጥ አይገባም (ራዕይ 11፡1-2)፡፡ ወንጌላዊ ትምህርት በእምነት እንጂ በማየት አይደለም፡፡ የሰው አልጠግብ ባይ፣ መጨረሻ የሌለው እንጦርጦስ የሆነ ጥማት ከሰይጣን የተገኘ የባሕሪ ውርስ ነው፡፡ እንጦርጦስ በውስጡ እያለ የውጭውን እንጦርጦስ ያወራል፣ ለውስጡ ዕውር ነውና፡፡ እግዚአብሔርን የሚፈራ ግን ጠግቦ የኖራል ምሳ.19፡23ለ፡፡ ምኑን ጠግቦ ይኖራል? ሀብትን ነው ወይስ እግዚአብሔርን ራሱን? ሰው የአምላኩን (የእግዚአብሔርን) አሊያም የሰይጣንን ፈቃድ እንጂ ከራሱ አንዳች አያደርግም፤ ሰው በጨለማ ስለሆነ የሰይጣንና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለይቶ/ቀድቶ እስከሚያውቅ ድረስ ፈዝዟል፡፡ በኃጢአት የተገኘውንም ነገር እግዚአብሔር ሰጠኝ ሲል በሰፊው ይደመጣልና፡፡

የሥጋዊ ሰው ሁሉ ትግል በጨለማ ልቡ ምን እንደሚያደርግ ሳያውቅ እግዚአብሔርን ከከፍታ ለመጣልና ቦታውን ለመውሰድ ነው፡፡ ወንጌል ሲሰብክ ሁሉ ራሱን ከፍ፣ ከፍ ማድረጉ፣ ባለማቋ/ጥ የከፍታ የሞቅታ፣ የከበሬታ፣ የዝና ጥማቱ፡፡ ይህ ከልቡናው ከፍታ እግዚአብሔርን







ማፈናቀል መሆኑን ጨርሶ አያውቅም፡፡ ለዚህ በቀንም በሌሊትም እንቅልፍ የማይዘው ሰይጣን/ሉሲፈር ከአዳም ጀምሮ ተፈናጥጦ ይነዳዋል። ለምሳሌ፣ የባቢሎን ግንብ፣ (ዘፍ.11፡1-4) የባቢሎን ንጉሥ የተራራ ሰልፍ፤ (ኢሳ.14፡12-13) በሰማይ የተካሄደው የዘንዶው ሰልፍ፤ (ራዕ.12፡7) መመልከት እንችላለን፡፡ ይህ የማያቋርጥ የዘላለም ሰልፍ ነው፡፡ በሰይጣን ከፍታ መውጣት ማለትም በጨለማ መገሥገስ ማለት ስለሆነ ማንም ሰው የሚያደርገውን አያውቅም፡፡ እንዲህ ተጽፏልና፣ በጨለማ የሚመላለስ ወዴት እንደሚሄድ፣ ምን እንደሚያደርግም አያውቅም፤ (ዮሐ.12፡35፣ 1ዮሐ.2፡11፣ ከሉቃስ 23፡34)፡፡

የምንመለከተው፣ በኢየሱስ ትንቢት መሠረት አይሁዶች ጌታን ከፍ ከፍ በማድረግ ሰቅለው የመግደላቸውን ምሥጢር (ዕንቆቅልሽ) ነው፡፡ ሰውን ከፍ ከፍ በማስደረግ ሰማይ አየር ላይ አውጥቶና ሰቅሎ ከመስቀል ከፍታ ላይ መግደል እንዴት ነው? እዚህ ላይ ኃጢአተኛው ጻድቁን ሰቅሎ ከፍታ (ሰማይ) ላይ በእግዚአብሔር ፊት ማለት ነው መግደልና ኃጢአተኛው፣ ኃጢአተኛውን ሰቅሎ መግደል ሁለቱ የተለያዩ ዓይነት ይሆናል፡፡ በሰማይ ላይ መግደልና በምድር ላይ መግደል ደግሞ ሁለት ነው፡፡ በምድር ላይ መግደል በሰው ፊት በአካል መግደል ሲሆን፣ በሰማይ ላይ መግደል፣ ሳይገደሉ በቁመና በመንፈስ መግደል ነው፡፡ ሰቅሎ መግደል እንደ ኢየሱስ ቃል ከክብር ወደ ክብር ከፍ ከፍ እያደረጉ መግደል ነው፡፡ እዚያ ተራራ ላይ ባለ ደመና ጨለማ ውስጥ ሰውዬው በሰማይ በእግዚአብሔር ፊት እንጂ በምድር በሰው ፊት በሕይወት አለ፤ ይበላል ይጠጣል፣ ያጌጣል ይሽሞነሞናል፣ ይንደላቀቃል፣ አቶ፣ ዶክተር፣ ኮሎኔል፣ ጀኔራል፣ ፕሬዚዳንት፣ ክቡር ሆይ... ወዘተ እየተባለ የሚደረግበትን ሳያውቅ በቆዳው እተኮፈሰ በሕይወት ይኖራል፡፡

ይህ ሁሉ አክብሮት ከመስቀሉ እንዳይወርድ የእውነት እውነተኛ ምስማር ነውና የቀረውንም አካል ሞት እዚያው በተሰቀለበት ይሞታታል እንጂ

ከዚያ ከቶ ቁልቁል ወርዶ በሰው ፊት በሰው ዘንድ የተናቀውን ክርስቶስን ተቀብሎና ተዋርዶ አንቱ በተባለበት ምድር አንተ ተብሎ ተንቆ መታየት በእርሱ በኩል የሞት ሞት ስለሆነ ከቶ አይሆንለትም፡፡ ይህ ዓይነቱ ሞት ለእርሱ የሞት ሞቱ ሆኖ ይታየዋልና ከቶ አይጥመውም፡፡ ርኩስ ሞት፣ ለጊዜያዊ ክብርና ዝና ሲል ወደ ምሥራቅና ምዕራብ በአየር ላይ በጉራ ተወጥሮ፣ ገድሎ በማይገድል ምስማር በተቸነከረበት አለ ሲባል ከአሮጌ ማንነቱ ሳይገረዝ ጥምብ የሆነ ሞት ሞቷል፣ እግዚአብሔር ምስክር ነው? ‹‹በልቡ የታበየ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ርኩስ ነው››፤(ምሳሌ 16፥5)‹‹ ...በሰው ዘንድ የከበረ በእግዚአብሔር ፊት ርኩስ ነውና›› (ሉቃስ 16፥15) ሥጋዊ ሰው ወደ ብርሃን ያልወጣ ዕውር ስለሆነ የሚሆነውንና የሚያደርገውን አያውቅምና አንዱ በሌላው እየተሞጋገሠ፣ እየተከባበረና ከፍ፣ ከፍ እየተደራረገ በምድር ሳይሆን በሰማይ ከፍታ ላይ ተሰቅሎ ርኩስ ሞት የሞተ ብቻ ሆኖ በወንጌል ብርሃን ቁልጭ ብሎ ለሁላችንም የሚታይ ነው፡፡ ጭኑ ካልተሰበረ በስተቀር አይዋረድም ከዚያ ላይ አይወርድም፣ አይሞትም፡፡ ((ዕንቆቅልሹ ሐቀኛ፣ ትርጓሜውም እውነተኛ ነው))፡፡

ዲያብሎስ በዚህ ዘዴ ነው ሰው ተብዬውን ሕፃን አዋቂ ሳይቀር፣ በየሙያው መስክ የተሠማራውን ሁሉ በእርስ በርስ ከንቱ ክብር በእርስ በእርሱ ከፍ፣ ከፍ በመደራረግ እጅ ሳይነካው በአየር ከፍታ ላይ ተንጠልጥሎ ትዕቢትን ተሞልቶ በሰው ፊት በሕይወት እያለ በእግዚአብሔር ፊት ርኩስ ሞት እንዲሞት ያደረገው፡፡ የተሰቀለበት የተራራው ከፍታና የመስቀሉ ርዝመት ይነስ ይብዛ እንጂ ሁሉን እንደየ ደረጃው በጌታ ፊት ራሱን ዝቅ አድርጎ እንዳይወርድ፣ እንዳይዋረድ ቸንክሮ ያንጠለጠለው፣ የሰቀለው ማን ነው? ሁሉን በአንቱታ፣ በክብር፣ በማዕረግ፣ በዝና፣ በጉበዝና... ወዘተ በማይረቡ በዕለት ነገሮች ጋርዶና አሳውሮ በመንፈስ ሞት ፈጅቷል፡፡ በትንቢተ ኢሳይያስ 14 እንደሚያመለክተው ዲያብሎስ የባቢሎንን ንጉሥ ልኩና መጠኑ በምድር







ላይ መስፈርያ መለኪያ በሌለው በልዑል እግዚአብሔር ልክ በሰሜኑ ዳርቻ በመሰብሰቢያ ተራራ ላይ ከሸፈኑ ደመናዎች ከፍታ በላይ ሊያንጠለጥለው ከፍ፣ ከፍ እያደረገው ይዞ ሲገሠግስ ነበር ተመትቶ ወደ ጉድጓድ ውርደት እንዲወርድ የተደረገው፡፡ እንዲሁም አዳሞችን በተመሳሳይ ደረጃ ከሁሉ በላይ እንደ እግዚአብሔር አዋቂዎች እንዲሆኑ ለማድረግ ከፍ፣ ከፍ እያደረገ ተንጠራርተው ውጤቱ ምን እንደሚሆን እንዳያዩ በክብር ምኞት ጋርዶ አሳውሮአቸው የዛፉን ፍሬ ወስደው በልተው በሕይወት ወደ ሲዖል መቃብር እንዲወርዱ ያስደረገው (ዘፍ.3፥16-24)

የሐሰት እውነቱ ውጫዊው የፊደል አካል የሚሰቀልበት ለውስጣዊው የመንፈስ አካል ለሚሰቀልበት ለእውነት እውነተኛው መስቀል ምስያ (ምሳሌ) ነው፡፡ ውጭ ውጫዊው ዓለማዊው መስቀል በሰው ዘንድ ሥጋ የተባለው አሕዛባዊው ሽለፈታሙ አካል ሰውነት የሚሰቀልበት ሲሆን፣ ውስጣዊው እስራኤላዊው መስቀል ከሥጋ ቁልፈት የወጣው አካል ሰውነት የሚሰቀልበት፣ ውስጥ ውስጣዊው ዋናውና ዲያብሎሳዊው ረቂቁ ሥጋ ሰውነት የሚሰቀልበት መስቀል መሆኑ ነው፡፡

ግዝረት፤ የተሰጠው የሰይጣን መጋረጃ (መሸፈኛ) የከብሩ ክሩብ የሆነው ሥጋ ቁርበት በስለታም ሰይፍ ተገፍፎ (ተገርዞ) ሲጣል ሰይጣን ተራቁቶ ርኩሰቱ ተጋልጦና ወደ ውጭ ተጥሎ ፍርድ እንዲቀበል (ዮሐ.12፡31) ነው፡፡ በአጭር ቃል እውነትን ስንናገር ሳይጣን ወደ ውጭ ወጣ፣ ተተፋ ለማለት ይቻላል፡፡ ምንም ይሁን ምን፣ ማረጋገጫ የሌለው ነገር ተጨባጭ ሆኖ ያልተረጋገጠውን ነገር እውነት ነው ብለህ አትቀበል፤ ሃይማኖታዊ አስተማሪዎች ከማንም በላይ ውሸታሞች ናቸው፤ የሚሉት ነገር ቀድሞ የተባለ ስለሆነ በምስክር ብዛትና በመደጋገም ብቻ እውነት የሆነ ነውና ለሚናገሩት ነገር አንድ ማረጋገጫ ሊሰጡ ስለማይችሉ ዘላለም ዘወርዋራ መንገዶችን ሲጓዙ ይኖራሉ፤ ለጥያቄ ደረት የሰጡ አይደሉም፡፡ እውነት በመናገር ብቻ ሰይጣንን ያን ጊዜ መውጫ መግቢያ አሳጣህ ማለት ነው፡፡

ለዚህ ተግባር በያለንበት ክንዳችንን ብናነሣ በሰይጣን ላይ ፈራጆች ሆንን ማለት ነው፡፡ ሰይጣን ምን ማለት ነው? ሐሰት፣ ማስመሰል፣ መዋሸት፣ ማጭበርበር፣ ማታለል፣ ሥርቆት ...ሰይጣን ነው፡፡

"የሰውን ልጅ ከፍ፣ ከፍ" ሲል፡- ልክ አዳሞችን ከፍ፣ ከፍ አድርጎ በመንጠራራት መስቀል ላይ ከፍታ ላይ አውጥቶ በቁመና በመስቀል ሞት በገደለበት ልምድ መሠረት ኢየሱስንም ቀደም ሲል በእግዚአብሔር ልጅነት ሥልጣን ድንጋይን ዳቦ እንዲያደርግ፣ በቤተ-ከፍታ ላይ ከፍ፣ ከፍ፣ ተራራ ከፍታ ላይ ከፍ፣ ከፍ በማድረግ ሰቅሎ በከፍታ ላይ አንጠራርቶ ሊገድለው ሞከረ፣ በትረ-መንግሥት አስይዞ በፍቱ በመንበርከክ የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፣ እያሰኘ ከፍ፣ ከፍ ለማድረግ ሞከሯል፡፡ በሌላ አንፃርም ቀደም ሲል ‹‹ሰይጣን በእውነት ወደ ዓለም ሊመጣ ያለው ነቢይ ነው›› በማለት ሊያነግሡት ሞክረዋል፤ (ዮሐ.6፡14-15)፡፡

አሁን ደግሞ ዲያብሎስ በሠራዊቱ በኩል፣ ራሱ ፈቅዶ ካልሞተ በስተቀር በማይገድለው ዘዴ ጭኑን ሰብሮ አዋርዶ አውርዶ ለመግደል ባለ ዕቅድ ነበር መስቀል ከፍታ ላይ ያወጣው፡፡ ግን ኢየሱስ በራሱ ስለሞተ የዲያብሎስ ጭኑን ሰብሮ የመግደሉ እቅድ ከሸፏል፡፡ ‹‹ጭን›› ኃይል ብርታት ሆኖ ይታያል፡፡ ሳምሶን ፍልስጥኤማውያንን መጀመሪያ ሲመታ ጭን፣ ጭናቸውን በመስበር ነው፤ (መሳ.15፡8) ጭን ደግሞ በአካል ሰውነት ውስጥ ዋናው አጥንት ከመሆኑም የሥጋ ሕይወት የሆነው ደም ከእርሱ ይመነጫል ይባላል፡፡ በኢየሱስ እይታ በኩል የከፍታ ላይ ሞት፣ በእግዚአብሔር ፊት ሥጋን ሕያው ቅዱስ መሥዋዕት አድርጎ በመሠውያ ላይ (በመንፈስ) ማቅረብን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም መጽሐፍ እንደሚገልፅ ከፍ፣ ከፍ. አድርጎ የመግደል ሙከራ በኢየሱስ ላይ በርከት ያለ ነው፡፡ (በሉቃስ 4፡28-30) ላይ እንደሚታየው፣ «...በምኩራብም የነበሩ ሁሉ ይህን ሰምተው ቁጣ ሞላባቸው፣ ተነሥተውም ከከተማ ወደ ውጭ አወጡት፣ ከከፍታ ይጥሉት ዘንድ ከተማቸው ተሠርታበት ወደ







ነበረችበት ወደ ተራራው አፋፍ ከፍ፣ ከፍ እያደረጉ ወሰዱት፤...» ኢየሱስ ግን እንደ ተራ ሰው በከፍ፣ ከፍ ክብርና ጥቅም ዓይኑን ያጣ፣ የታወረ ሳይሆን፣ ከዚህች ከጥቂት እርምጃ ወዲያ ሊደርስበት ያለውን ቀርቶ ዘላለምን አሻግሮ ሁሉን የሚያይ ነውና ወደ ገደል ከመገፍተራቸው በፊት በመካከላቸው አልፎ ሄደ፡፡ በዚያኔው ገደል የኢየሱስን ውጨዊ ጊዜያዊ ሕይወት የሚያጠፋ የሚታይ ግልፅ ገደል ነበር ወይስ ውስጣዊ ዘላለማዊ ሕይወትን የሚያጠፋ የሚታይ ስውር ገደል ነበር? የዛሬው ሰይጣን እኛና ለወገኖቻችን ዓይናችንን በጥቂት እርምጃ ከፍ፣ ከፍታ እርምጃ በኋላ ገፍትሮ ሊጥለን እየመራን ያለው ተጋርዶ አልታይ ያለን ገደል ምን ዓይነት ነው? አዳም በጥቂት እርምጃ ከፍ ከፍታ ተጋርዶ የገባበት አሁን ድረስ ለዘሮቹ ሁሉ አልታይ ብሎን የታወርንበት ገደል፣ ገደል ነው ወይስ ገሃነም? ከፍታ የሚመኝ ሁሉ ከጥቂት እርምጃ በኋላ ቀጥሎ ባለው ገደል የሚገባ መሆኑ የማይቀር የተረጋገጠ እውነት መሆኑን ልብ እናድርግ፡፡ ባለቤቱ ከፍ ሊያደርገን ለከፍታ ሥርግ የጠራን ስለሆነ ከፍ በሉ እስኪለን ድረስ በዝቅተኛ ወንበር ላይ እንቆይ፣ ይላል ጠሪ መልእክተኛው ሉቃስ፣ (14፡7-11)

አንተንም፣ አንችንም፣ እርስዎንም በእግዚአብሔር ፊት እንደ አለቃችን ኢየሱስ ምሳሌ ፈቅደን ሞተን ዝቅ፣ ዝቅ ብለን እንዳንወርድ እንዳንዋረድ ከፍ፣ ከፍ አድርጎ፣ ሰቅሎ አንጠልጥሎ በቁመና የገደለ ማነው? በምድር ላይ የሚበዛው ሰው ሰይጣን በውስጡ ባዶ ጭድ ሞልቶበትና በቁርበት ሸፍኖ ሕይወት በሌለው በሙት መንፈሱ በወናፍ የሚያንቀሳቅሰው ብቻ ሆኖ ይታያል፡፡ ሰው ሁሉ ማለት ይቻላል በውስጡ ሙት በውጬ ሕይወት ነው የሚንቀሳቀሰው፤ በውስጡ ኃጢአት በውጬ በሕይወት አለ ማለት ሰውዬው በማንነቱ፣ (በእሱነቱ) ሙት ማለት ነው፡፡ የዘላለም ሕይወት የአለው፣ በውስጡ የዘላለም ሕይወት የሆነው «ልጁ» ያለው ነው ወይስ ነገ ዕዳሪ የሚሆነው ዳቦ ያለው ነው? (1ዮሐ.5፡12) የዘላለም

ሕይወት የሆነው እውነተኛው አምላክ ማነው? 1ዮሐ.5፡20) ሕይወት የሚሆነው ሕያው ሆኖ በውስጥህ የሚኖር ነገር ነው ወይስ ከደቂቃ በኋላ እልም ብሎ ጠፊው ነገር ነው?

ሰይጣን፣ በሰው ፊት ውጭህን (ገጽህን) ቀባብቶ አሳምሮ አደልቦ፣ ውጭ አካልን አደንድኖ ውስጥህን የገደለ ነቀዝ ነው፡፡ በውስጥ ብርሃን ሲበራ ይህ እውነት መሆኑ ግልፅ ሆኖ ይታያል፡፡ ነቀዝ የዘሮችን ውስጥ ቡቃያ የሚሆነውን ሕይወት ክፍል እንደሚያጠፋ ሁሉ ሰይጣን እንዲሁ ውጭን አደልቦ ውስጥን ባዶ ያደርጋል፡፡

ከጌታ ጋር የተሰቀሉ ሽፍቶች እንደ ጌታ በፈቃዳቸው ሳይሆን በግዴታ የተሰቀሉ ስለሆነ እንኳን በምድር ሆነውና ተሰቅለውም የራሳቸው ዕዳ የሆነ የኃጢአትን ዋጋ በፈቃዳቸው ሞተው ሊከፍሉ ፈቃደኞች ያልሆኑ የባሰውን አመፀኞች ስለ ነበሩ ሁለቱም እኩል ተገድደው እንደ ተሰቀሉ ሁሉ ዕዳቸውንም እኩል በዱላ ተቀጥቅጠው በግዴታ ከፈሉ፣ በፈቃድ ስላይደለ ከፈሉ አይባልም እንጂ፡፡ በተንጠለጠሉበትምኮ ኃጢአት ይሠሩ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ ሁላችንንም እጅግ ሊያስጠነቅቀን ይገባል፡፡ ተገደሉ እንጂ አልሞቱምኮ!! እኔሳ? ሞቻለሁ ወይስ ተገድያለሁ?

ጌታ ኢየሱስ ግን የተደረገበት ሁሉ በፈቃዱ ብቻ ስለ ነበረ ያለ ኃጢአት የሆነ ሥጋ ብቻ ስለ ለበሰም የኃጢአትን ዋጋ ሞትን (ዕዳ) ማንም በዱላ ሳይቀጠቅጠው ሳይጠይቀው ገና ገዳዮቹ ሳይመጡ ቀድሞ በራሱ ሥልጣን (በፈቃዱ) ከፍሎ ጠበቃቸው፤ (ዮሐ.19፡32-33)፡፡ በሥጋው ላይ ራሱ ባለ ሥልጣን፣ በራሱ ላይ ራሱ ዳኛ (ፈራጅ) ነውና ሌላ ፈራጅ አልሠለጠነበትም፡፡ ኢየሱስ በተናገራቸው ትንቢት መሠረት ነፍሱን ሊያኖርና ሊያነሣ ባለው ሥልጣን (ዮሐ.10፡17-18) ሥጋውን በሥልጣኑ እንደ ሰጠ ሁሉ ነፍሱንም በሥልጣኑ ሰጠ፣ (ማር.15፡37) በሌላ ገጽ እንደ ተመለከተ ክርስቶስ የማይሞት ነው፤ (1ጢሞ.6፡16) ማንም በማይቀርበው







ብርሃን የሚኖር ብርሃን ስለሆነ ሞት ማለት ጨለማ ወደ እርሱ አይቀርብምና ሞትን በርቀት በዓይኑ ብቻ ያያል፡፡ ክርስቶስ አይሰደብም፣ ስድብ ወደ እርሱ አይቀርብም በርቀት ግን ይሰማዋል፡፡ ክርስቶስን ማንም በጥፊ፣ በበትር፣ በአለንጋ አልመታውም፤ ውርደት፣ ሥቃይ፣ መከራ፣ ሕመምም የሰይጣን ሥራ ሁሉ በዓይኑ ከማየት በስተቀር ወደ እርሱ አይቀርብም፤ እንደተጻፈ ..."እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ፣ ከሚያስደነግጥም ነገር ያድንሃልና፡፡ በላባዎቹ ይርድሃል፣ በክንፎቹም በታች ትተማመናለህ፣ እውነት እንደ ጋሻ ይከብብሃል፡... በአጠገብህ ሺ በቀኝህም አሥር ሺ ይወድቃሉ፣ ወደአንተ ግን አይቀርብም፡፡ በዓይኖችህ ብቻ ትመለከታለህ... "(መዝ.91፡1-8፣ በውሃ ውስጥ ባለፍህ ጊዜ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፡፡ በወንዞችም ወስጥ ባለፍ ጊዜ አያሰጥሙህም፤ በእሳትም ውስጥ በሄድህ ጊዜ አትቃጠልም፣ ነበልባሉም አይፈጅህም፤ ኢሳ. 43-1-2፣ ከዳን. 3፡21-27፣ ም. 6፡16-18)...ወዘተ

ሰዎች ስንባል፣ እንኳ በምድር ላይ ስንንቀሳቀስና ተሰቅለንም በተንጠለጠልንበትም አየር ላይ የግል ዕዳችንን ላለመክፈልና ለማዘግየት ባለን ምኞት ይህ ኃጢአተኛው ዕድሜአችን እንዲረዝምልን የምንፈልግና ለዚሁም የማንጸልይ ሰንቶች ነን? ዋና የምንመለከተው ነጠብ፣ ሰይጣን ከፍ፣ ከፍ ሲያደርገን ሁሉ በዚያ ከፍታ ክብርና ዝና ላይ የምንሰነብት መስሎን መጃጃላችንን ነው፡፡ በጌታ ላይ፣ በከፉ መልካም አድራጊዎች ያደረጉት ሁሉ በከፋት ጨለማ ተጋርደው (ታውረው) የሚያደርጉትን ሳያውቁ ያደረጉበት ሲሆን፣ ኢየሱስ ግን የሚሆንበትን ሁሉ አስቀድሞ ያይ፣ ያውቅ ነበርና ሥጋውን ዐውቆና ፈቅዶ አሳልፎ የሰጠበት ጉዳይ ነበር፡፡ ወገኔ ሆይ እንደ ኢየሱስ፣ እንደ አብርሃም፣ ይስሐቅ ያዕቆብ ነፍሳችንን ማንም ከፉ እንዳይወስድብን በዱላም፣ በጦርም፣ በአደጋም፣ በበሽታም ...ወዘተ ሳንጠየቅ፣ ሳንገደድ ለእግዚአብሔር አሳልፈን እንስጥ የአዳም ልጆች፣ ራሳቸው አዳም (ሉሲፈር) መሆናቸውን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየው በተሰቀሉበት መስቀል ላይ ተንጠልጥለውም እንኳ ትዕቢትን ተሞልተው የሚንጠራሩ መሆናቸው የባሕሪያችን ናሙና ነው፤ ለዚህ

ምሳሌ የሚሆነውም ከሽፍቶቹ አንዱ በኢየሱስ ላይ በመንጠራራት ሞራ ተሞለቶ የተናገረው የስድብ ቃል ነው፤ (ሉቃስ 23፡39)፡፡ ኢየሱስ የሚሆንበትን ሁሉ አስቀድሞ ማየትና ማወቅ ሲችል እነርሱ (ጠላቶቹ) ለምን አያዩም? ለምንስ የሚያደርጉትን ጭምር አያውቁም? ዓይንን የሚያሳውር ነገር ምንድን ነው? የእነርሱ ዓይን የጠፋበት ምክንያት፣ አንደኛው ጥል፣ ጠላትነት፡፡ ሁለተኛው፣ ጉቦ፣ ጥቅምን፣ ክብርን መመልከት ነበር፣ ነውም፡፡ ዘዐ.23፡8-9፣ 1ሳሙ.12፡3፣ 1ዮሐ.2፡11-12) ሰው እግዚአብሔርን እስካላወቀ ምንም ሊቅ፣ ሳይንትስት ይሁን የሚያደርገውንም፣ የሚሆነውንም አያውቅም፤ በጨለማ ነውና፡፡ ኢየሱስ ዘላቂውን ክብር እንጂ የቅርቡን አያይም፣ የቅርቡን የሚያይ ዕውር ነው (2ጴጥ.1፡9)፡፡ እንደ ሰዎች የቅርቡ የሩቁን ሊጋርድበት አልቻለም፡፡

ጌታን ክፉ፣ ክፉ ያደረጉና የሰቀሉት አይሁዶች ናቸው ወይ? እርሱ ክፉ፣ ክፍን አልተቀበለምና እዚያው ከፍታ ላይ በሥልጣኑ ሙትት ድብን፣ አለባቸውና ጠላቱን ሙትት ድብን አደረገ፣ ወረደ ተዋረደና ጠላቱን አወረደ፣ አዋረደ፤ ከሰው ጫማ በታች ካለው አፈር በታች ሆኖ መሥዋዕት ሆነና ጠላቱን ከሰው ጫማ በታች ካለው አፈር በታች አደረጎ መሥዋዕት አደረገው፡፡ እዚህ ላይ ጠላቱን ስንል ማንን ተመልክተን ነው? ጠላቱ ራሱ አካል ሰውነቱ (ሥጋው) ስለሆነ በእንዲህም ዓይነት ነው ጠላቱን (ሥጋውን) እንበላው ዘንድ ፋሲካ አድርጎ ያቀረበልን፡፡ አይሰወርበትምና ይህንን ሁሉ እየየ አደረገ፡፡ ሰዎች ግን ተሰውሮብን ጠላታችንን አካል ሰውነታችን ነፍሳችን መስሎን ለአጅሬ ስለምንሣሣለት ለእግዚአብሔር የሚገባ መሥዋእትነት ማቅረብ አልቻልንም፤ ከምናየው ጥቅማ ጥቅም የተነሣ አይታየንምና (ጥቅሙ አሣወረን)፡፡ በኢየሱስ ብርሃን ስናይ ጠላታችን ማነው? የለየለት ጠላታችንን አካል ገላችን መስሎ ተዋኽዶን በስውር የሚኖረው ሥጋችን/ሰይጣኑ ነው፡፡ ጠላት እንዴት እንጀራ





እንደሚሆን በካሌብ ትንቢት፣ በኢየሱስ ሥራ አይተናል፡፡ የሚገድል ነገር ቢጠጡም አይጎዳቸውም የተባለው ዕንቆቅልሽ እዚህ ተተርጉሟል፡፡

ጌታን የሰቀሉት አይሁዶች ናቸው ወይ? ማለት፣ ሰይጣናዊ ፍርድ ነው፤ አጅሬ ሰይጣን ከፍርዱ ለማምለጥ በውስጣቸው በመጋረጃ ራሱን ሰውሮ ጋሻ ጃግሬነት ተከልሎ የጌታን ደም በእነርሱ ላይ ለማላከክ በአይሁዶች ላይ ያስፈርዳል፡፡ አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ፍርዱን ለመቀበል ከተደበቀበት መጋረጃ ውስጥ ወደ ውጭ ይጣላል፤ (ዮሐ.12፡31) ይኸው! ተጣለ፡፡ ያኔ ኢጋቢና ውስጥ በስውር ተቀምጦ ለክፉ ሥራ ሁሉ ሲነዳን እርሱ መሆኑ አልታወቀም ነበር፡፡ በኢየሱስ ሥራውን ሁሉ የሚሠራ አብ እንደ ነበረ (ዮሐ.14፡10፣ 2ቆሮ.5፡19) እንዲሁ፣ በሰው ሁሉ ሆኖ ወደ ጥፋት ሁሉ እየመራ ሥራውን ሁሉ የሚሠራ እርሱ ዲያብሎስ ነው፡፡ ክፉ፣ ክፉ የሚያደርግህ ሰው ሁሉ አክባሪህ አይምሰልህ፣ እመስቀል ከፍታ አየር ላይ ተንጠልጥለህ በርኩሰትህ እንድትሞት የሚያደርግ ገዳይህ ሌባ ነው!! እዚያ ትሞታታለህ እንጂ፣ ሳትሞት ከዚያ እንዳትወርድ ምን አድርገውብሃል? ከመስቀሉ ጋር በማይታይ ምስማር ቸንክረውሃል፡፡ ምስማሩ አይታይም ግን አይለቅህም፣ ቆራጥ እምነት የለህምና ከዚያ መውረድ መናቅ አትችልም አይደል? ምስማሩ ማን መሰለህ? የማይላቀቁት ዲያብሎስ ነው፤ ከዲያብሎስ ጋር ከተሰቀሉበት፣ ከፍታ ላይ ሆነው ሰው ሁሉ ሲሰግድላቸው ክቡር፣ ክብርት፤ አንቱ፣ ጌቶች፣ እመቤት፣ መምህር ከተባሉበት አየር ከፍታ ወርዶ ማንነቱን መሥዋዕት አድርጎ የሚድን ማነው? ምስማሩ አይነቀልም አይደል? እንደ ጌታ እዚያው በአምላክ ፊት ሙትት ማለት ያድን ነበር፡፡

ከመስቀል ወርዶ ተዋርዶ አንቺ፣ አንተ ተብሎ ተንቆ፣ የተናቀውን ጌታ ለመቀበል ከሚታየው ከፊደል መስቀል ምስማርና ከማይታየው ከመንፈስ መስቀል ምስማር ለመንቀል የሚቀልለው የትኛው ነው? ክርስቶስ ሲሰቀል በውሬ ከዲያብሎስ (ከሥጋ) ጋር ስለ ተሰቀለ ከመስቀል በጀግንነት

የመውረዱ ስሜት ከብቦ ይዞት እስቲ ከመስቀል ውረድ!! እያለ (ማር.15፡ 31) ቢፈትነውም በውስጡ ከእግዚአብሔር ጋር ስለ ነበር በእግዚአብሔር እጅ በቀላሉ ሞቶ ያንን አንጣጭ (ከሣሽ) ሰይጣንን ገደለና ድምፁን ጭጭ አደረገ፡፡ ያ ጌታን በመስቀሉ ዙሪያ ከብቦ ያሳጣው የነበረ ሠራዊት ዛሬ አለ ወይስ የለም? ያ ከሣሽ መንፈስ ሳይሞት በሕይወት ለመኖሩ እኛም ዛር እንደ ሽፍቶቹ ሁሉ ለሞትና የኃጢአትን ዋጋ ለመክፈል ሳይሆን፣ የጌታን ቅዱስ የመስቀል ሞት ለማርከስ የተሰቀልን አስመሳዮች በመሆናችን በውስጣችን ዙሪያ የከበበን የክስ ድምፅ ማስረጃ ነው፤ ይኸው! በሕይወት አለና በክስ ተወጥረናል፡፡ ስለዚህ ዱላው እየቀጠቀጠን ነው፡፡ ጌታ ግን በእስራኤል የተገለጠውንም ውጫዊ ሞት ጭምር በመሞት ከፍ ብሎ እንዳየነው ማንም ሳይጠይቀው የኃጢአትን ዋጋ (ዕዳ) በፈቃዱ ከፍሎ ስለጠበቀ ዕዳ አስከፋዮቹ በነፃ በመሰናበት አልፈውት የቀሩትን ከፈሉ በሚል በዱላ ጠየቁ፡፡

ይህች እኔ ወደ እናንተ የላከኋት ያሁኗ ዱላ ለሞት ሳይሆን የጌታን መስቀል መስለው ለማከሸፍ በሐሰት እውነት ከጌታ ጋር ተሰቅለናል!! ለማለት ጉራ የተሰቀሉትን ሁሉ ጭን፣ ጭናቸውን እየቀጠቀጠች ነው አይደል? ሰይጣን ሁልጊዜ በሁሉ የጌታን የእውነት እውነተኛ ሥራ ለማከሸፍ ከግብፅ ጠንቋዮች ጀምሮ እንደ እንደቀጠለ ኖሯል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ራሳችን በራሳችን ላይ ብንፈርድ ባልተፈረደብንም ነበር፡፡ ክርስቶስ በራሱ ላይ ራሱ ባለ ሥልጣን ነውና በፈቃዱ ሞተ፡፡ እኛ ግን በሌላ ላይ ለመፍረድ እንጂ በራሳችን ላይ ጉቦ በልተናልና የጥቅሙ ምንጭ ይደርቅብሃል የሚል የሰይጣን ማስጠንቀቂያ ከገዛ-ራሳችን ውስጥ ከዙፋኑ ሲለፈፍ ስለምንሰማ እንፈራለን፣ ከእርሱም ጋር ሰውነታችን ይርዳል፡፡

ክርስቶስ በሥጋ ሁሉ ላይ ሥልጣን አለው ሲባል፡ የሚያቅተው ነገር ሳይኖር በአመፃ ሁሉ ማለት ሆኖ «በተኩላውና በእባብ ላይ ትጫማለህ፡





አንበሳውንና ዘንዶውን ትረግጣለህ፣ (መዝ.91፡13፡ ሉቃስ 10፡19)» የሚለው ተፈጽሞአል፡፡ ለመሆኑ በፊደል በቁሳዊ ዘንዶው፣ በገሃዱ ተኩላውና እባብ በሐሰት እውነቱ ላይ ትረግጣለህ ማለት ነው ወይ? በገሃዱ ተኩላውና በእባብ ላይ፣ በቁሳዊ አንበሳ፣ ዘንዶ ከመጫማት ከመርገጥና መንፈሳዊ የሆነውን ተኩላ፣ ዘንዶና እባብ፣ በእውነት እውነቱ ላይ ከመጫማት የትኛው ይበልጣል? ይህ ማለት ቀደም ሲል እንዳየነው ሁሉ በሥጋ፣ በአመፃ ሁሉ ላይ ማለት ነው፡፡

ናቡከደነፆር በውጭ በሜዳዊው አንፃር ለማይ ጠቀስ ዛፍ ሆኖ ሁሉ የሚበላው ክፋትና ዓመፅ (አራዊትና እንስሳ፣ በራሪና ተሽከርካሪ) በሥጋው ሥር የተከማቹና በእርሱ መኖነት እንደኖረ ለዚህ ሁሉ መኖ ሆኖ እንደ ተቆጣጠረ ሁሉ ክርስቶስ በግልባጩ በውስጣዊው ኃይል በመንፈሱ የሚገዛ ነው፡፡ ምድር፣ ማለት ሥጋ ሁሉን አጠቃልሎ ዕቃ ስለሆነ ምድርን ማለትም የሥጋ ጠቅላይ ገዥ በመሆኑ ማንኛውንም በምድር ማለት በሥጋ ላይ የሚገኘውን ዓመፅ ተኩላውን፣ እባቡ ላይ ትጫማለህ፣ አንበሳውንና ዘንዶውን ትረግጣለህ፣ እንዲኖር የተፈቀደውን ነገር ከሥጋህ (ከምድር) ጋር ጠቅልለህ ትረግጣለህ፣ ትቆጣጠረዋለህ ማለት ነው፡፡ ክርስቶስ በሥጋ ሁሉ (በፍጥረት ሁሉ) ላይ ሥልጣን አለው ማለት፣ ከውድቀት በፊት የነበረ የአዳም በባሕር ዓሦች ላይ፣ በሰማይ ወፎች ላይ፣ በምድር አራዊትና እንስሳ ሁሉ ላይ፣ ከሚገዛበት ሥልጣን፣ በመፈንቅለ መንግሥት የወደቀበትን መብት ክርስቶስ መልሶ ለመያዝ በነፃ አውጪነት ስለተሾመ ነው፤ (ሉቃስ 2፡ 35፣ ማቴ.28፡ 18)፡፡

መንፈስ ረቂቅ መሆኑ የታወቀ ሲሆን፣ ሥጋም አቻና ተነጻጻሪ ረቂቅ ነገር መሆኑን ሰዎች አልተረዳንም፡፡ ሥጋና መንፈስ ማለት፣ እግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ እንደሆነ እንዲሁ ሥጋም ርኩስ ከመሆኑ በስተቀር ሁለቱም ወገኖች እርስ በርሳቸው አንፃራዊ ባላጋራዎች ናቸው፡፡ ከሥጋ የተወለደ፣ ከመንፈስ ለተወለደ አንፃራዊ ባላጋራ ነው፡፡ ሁለቱም በአየር

ላይ የሚዋጉ ናቸው፣ እንጂ ሥጋ በምድር ላይ፣ መንፈስ በሰማይ ላይ ሆነው አይደለም፤ ሥጋ የሰይጣን ተጣማሪ ነው፡፡ ከሥጋ የተወለደው ከመንፈስ ለተወለደው ጠላት ነው፤ (ገላ.4፥29)፡፡ ከሥጋ የተወለደ ከውጭ (ከጨለማ) የተወለደ ሲሆን፣ ከመንፈስ የተወለደ፣ በተቃራኒ ከቤት/ከውስጥ ከብርሃን በእውነተኛ መንገድ ስለተወለደ የብርሃን ልጅ ነው፡፡ እንዲሁም ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ገለባ ነውና ከውጭ፣ (ከገለባ፣ ከሚባለው) ተወለደ፣ ከሥጋ የተወለደ ስለሆነ ተገፍፎ እንዲጣል፣ እንዲሰቀል ከተፈረደበት ወንጀለኛ ከርኩሱ የተወለደ ነው፡፡ ሰይጣን በሥጋ ቁርበት ጥልቅ ጨለማ መጋረጃ የተሸፈነ ጨለማ ነው፤ ክርስቶስም ሰይጣንን ሊመክተው ወደ ዓለም ሲመጣ በተመሳሳይ ተቃራኒ፣ ሰው ክብሩን ዓይቶ አይድንምና (ዘፀ.33፥20) በሥጋ ቁርበት ጨለማ የተሸፈነ ብርሃን ሆኖ ነውና፡፡ ክብሩ ሦስቱን ደቀ-መዛሙርት እጁን ጭኖ እስኪያድናቸው ድረስ እንደ መታቸው በአክብሮት እናነባለን፡፡ እግዚአብሔርም ከእስራኤል ዙሪያ ከበብ ቀጥሎ፣ ከከበበው ጥቁር መጋጃ ጨለማ የተጋረደ ብርሃን ነበረ ማለት ይቻላል፡፡ እስራኤል ደግሞ ራሷ በዙሪዋን በነበሩ አሕዛብ ጨለማ መንግሥታት የተከበበች ብርሃን ነበረች፡፡ እስራኤል ሸለፈትን ቆርጠው መጣላቸው አሕዛብን ቆርጦ የመጣል ፍርድ ነበረ፡፡

አዳምና ሚስቱ ከእግዚአብሔር አምላክ ፊት ሸሽተው በገነት ዛፎች ጥላ ጨለማ የተሸሸጉት ለምንድን ነው? ሰይጣን ያለበሳቸውን ገፍፈው ለመጣል ሳስተው/ራርተው፣ አዝነውለት ነው፡፡ ይህ በተግባር ሲታይ አንተና እኔ ከሰይጣን የሆነ ቅጠል ሥጋ ቁርበት ገፍፈን ከመጣል ራርተን ከዚህ ይልቅ ከእግዚአብሔር ድምፅ በሕይወት ዘመን ሁሉ መሸሸ ማለትን ይተረጉማል፡፡ መጽሐፍ አዳምና ሔዋን ሸሹ የሚለው እነርሱ የለበሱት ጨለማ፣ ብርሃን ከሆነው እግዚአብሔር ቃል ከክርስቶስ ፊት አዳሞችን ሊሸፍን ባለመቻል እነርሱን ለፍርድ እርቃናቸውን አሳልፎ ሰጥቶ ጥሎአቸው ሸሸ እንጂ፡፡







ሰይጣን በእስራኤል ሥርዓት ተራቁቶ ከመገኘት ገደል መግባትን መምረጡን የእግዚአብሔር ድምፅ ከሆነው ክርስቶስ ፊት ሸሽቶ ወገኑ ወደ ሆነው ዛፎች ጥላ ጨለማ መሸሹን ተጽፎ እናነባለን፣ (ዘፍ.3፥8) ቁርበት ምንድን ነው? በቁርበትና በሰይጣን መካከል ልዩነቱ ምን ያህል ነው? ቁርበት ተቆርጦ ወደ ውጭ እንዲጣል የተፈረደበት የሥጋ ቁልፈት የተባለው ክፍለ አካላችን ለመሆኑ ተጽፏል፣ (ዘፍ.17፡ 11፣ ቁ. 14) እርሱም ርኩሰት፣ (ኢሳ.52፥1-2)፤ ሞት፣ (ቆላ. 2፡13)፡፡ እርኩስ ምን ሲሆን፣ ርኩሰት ምንድን ነው? በርኩሰትና ርኩስ መካከል ምን ያህል ልዩነት አለ? ርኩሰት ርኩስ ነው እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ ሞት፣ ርኩስና ርኩሰት ማነው? አዳሞች ከእግዚአብሔር ፊት የሸሹት ቅጠል ስለለበሱ ነው ወይስ ርኩሰት የተባለውን ስለለበሱ ነው? ወደ ብርሃን (ወደ እግዚአብሔር) የሚሸሸ ሰው ቅድስናን የለበሰ ነው ወይስ ርኩሰትን የለበሰ ሰው ነው? ወደ ጨለማ (ወደ ሰይጣን) የሚሸሸ ሰው ርኩሰትን የለበሰ ሰው ነው ወይስ ቅደስናን የለበሰ ሰው ነው? ቅድስናን የለበሰ ማለት ክርስቶስን የለበሰ ሲሆን፣ ርኩሰትን የለበሰ ሰው ማንን የለበሰ ሰው ነው? ስለ ሆነ አዳሞች ከእግዚአብሔር ፊት የሸሹት ርኩሰትን (ሰይጣንን) ስለለበሱ ነው እንጂ ቅጠል ስለለበሱ አይደለም፡፡ በቁርበት፣ በሞትና በርኩሰት መካከል ልዩነት የለም፡፡ ቁርበት ቁርበት ሳይሆን፣ ሰይጣን ቁርበት ነው፡፡ ሞት፣ ርኩሰት፣ ቁርበት፣ የስጋ ቁልፈት ነው፡፡

ይህ እውነት ነው ወይስ ሐሰት? የሐሰት እውነት ነው ወይስ የእውነት እውነት? በውጭ፣ በብዙ ዘመናት ርቀት፣ በብዙ ኪሎ ሜትሮች ርቀት፣ ከማንነታችን በርቀት፣ በታሪክ ብቻ የሰማነው (ያነበብነው) እውነት፣ ነው ወይስ ዓይናችን ያየው፣ ጆሮቻችን ያረጋገጠው፣ በሕይወታችን ተገልጦ ያየነው እውነት ነው? የእውነት እውነት በርቀት በወሬ የታወቀ እውነት ሳይሆን፣ በሕይወት የተገለጠ ተጨባጭ ሲሆን ነው፡፡ ለሰይጣን ሞት፣ ሞት ነው ወይስ ብርሃን ሞት ነው? (እግዚአብሔር?) ለሰይጣን፣ ብርሃን ብርሃን

ነው ወይስ ጨለማው ብርሃን ነው? ለሰይጣን መኅናፀፊያ መኅናፀፊያው ነው ወይስ ጨለማ መኅናፀፊያው ነው? በእንዲህ ሁኔታ ሰው ከእግዚአብሔር ፊት ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ፣ ወደ ጨለማ ከሸሸ እርሱ ሰው መሆኑ ነው ወይስ ሰይጣን መሆኑ ነው? በመጀመሪያ ሰይጣን በገነት ከእግዚአብሔር ፊት ሲኮበልል፣ ራቁቱን ኮበለለ ወይስ የሥጋ ቁርበት ተከናንቦ ነው የኮበለለው? ሰይጣን በዚያን ጊዜ ሸሽቶ አሁን አርፏል ወይስ ከእግዚአብሔር ያኔ የጀመረውን ሽሽት መድረሻ አጥቶ እስከ ዛሬም ድረስ በረራ እንደ ቀጠለ ነው? ያኔ ሰይጣን ራቁቱ ሆኖ ተገለዖ ሸሸ በአዳሞች ተሸፍኖ ከነርሱ ጋር አንድ አካል፣ አንድ አባል ሆኖ ተዋኽዶ እጥልቅ ውስጥ-ውስጥ ሆኖ መጽሐፉ ጭምር ተሳስቶ የሚሸሸው ማን እንደ ሆነ ለይቶ፣ አበጥሮ የእውነት እውነቱን ሳይመሰክር አልፎ አዳምና ሄዋን ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ እስኪል ድረስ አንድ አምሳል፣ አንድ አካል ሆኖ ነበር የሸሸው? ዛሬስ ራቁቱን ሆኖ በግልፅ እየሸሸ ነው ወይስ ጨለማ ተጎናፅፎ እየበረረ ነው? ጨለማው ምንድን ነው? በጥሩ ሁኔታ መሸፈን የሚችለው ጨለማ ነው ወይስ የሥጋ ቁርበት ነው? ያኔ የሥጋ ቁርበትና ሰይጣኑ በፍፁም አንድነት ይሸሹ ነበር ወይስ የሥጋ ቁርበት የሆኑት አዳሞች ወደ እግዚአብሔር ሲሸሹ ሰይጣኑ ተነጥሎ ብቻውን ወደ ተቃራኒ ሸሽቷል? ዛሬ ሰይጣን ወደ እግዚአብሔር እየሸሸ ነው ወይስ ከእግዚአብሔር እየሸሸ ነው? በግልፅ እየሸሸ ነው ወይስ ተሠውሮ፣ ተሸፋፍኖ እየሸሸነው? ያኔ የሥጋን ቁርበት ተከናንቦ ሸሸ፣ ዛሬ በምን ተሸፋፍኖ ማንን ተላብሶ እየሸሸ ነው? ያኔ ከእግዚአብሔር ድምፅ ሲሸሽ የተጎናፀፈው፣ የሥጋ ቁርበትን ነው ወይስ ሰውን ነው? ዛሬ ቁርበቱን ነጥሎ ተከናንቦ እየሸሸ ነው ወይስ ቁርበቱን ከነሰውዬው ተጎናፅፎ ነው? የዛሬ ሰዎች ከአዳሞች ስለሚሻሉ ከሰይጣኑ በተቃራኒ ወደ እግዚአብሔር እየሸሹ ነው ወይስ ከሰይጣኑ ጋር ፍፁም አንድ አካል፣ አንድ አምሳል ሆነው በጣምራ ከእግዚአብሔር (ከብርሃን፣ ከእውነት፣ ከግልጸት) እንደ ጥንቱም እየሸሹ ነው? አንባቢና እኔስ እንዴት ነን? አዳም፣ (ሰይጣን) ከሸለፈቱ







ያልወጣ፣ የተሸፋፈነ ስለሆነ ሁልጊዜም በብርሃን ከመገለጽ ይሸሻል፡፡ ይህን ከሰይጣን፣ ምንም ሳይለይ በጣምራ ከእውነት የሚሸሸውን ሁሉ ሰው ነው ለማለት እንዴት እንችላለን? ነው፣ ጥያቄው፡፡ አሁን ሰይጣን በሰው ተዋኽዶ በተጨባጭ ማለት በእውነት፣ እውነት ቤተ-ክርስቲያን የሞላውን አንድ ብሎ ከታላቁ ጀምሮ እስከ ታናሹ በየጋቢናቸው ተቀምጠ በከፍተኛ ፍጥነት እየነዳ ሽሽት ላይ ያለው ለኔ ይታያል ላንተ አይታይሞይ? ዓይንህን አልተገረዝክሞይ? ያለው

የሥጋን ምንነትና ፍርዱን አስፋፍተን ለማየት በነዚህ ጥቅሶች ብርሃን እንታገዝ፣ (ገላ.2፡20፣ 5፡24፣ መዝ.22፡16-18፣ ኢሳ.50፡6) ጳውሎስ በ(ገላ.2፡20፤) ላይ ከክርስቶስ ጋር ስለመሰቀሉ ሲመሰክር፣ ንጉሡ ዳዊት (መዝ.22፡16-21) በሚነበበው ከክርስቶስ ጋር ብዙ ውሾች ከብበውት እንደነበር፣ የክፉተኞች ጉባዔ ይዞት፣ እጆቹንና እግሮቹን ተቸንክሮ፣ አጥንቶቹ ሁሉ፣ ተቆጥረው፣ ...ልብሱን ተከፋፍለውበት፣ ቀሚሱ ላይ ዕጣ ተጣጥለውበት እንደነበር ሲገልጽ፣ ነቢዩ ኢሳይያስም በ(ም.50፡6) ላይ ከክርስቶስ ጋር ጀርባውን ለገራፊዎች፣ ጉንጩን ለጠጉር ነጪዎች ፊቱን ለውርደትና ለትፋት ሰጥቶ እንደ ነበር እናነብባለን፡፡ እንዲሁም ደግሞ በ(ገላ.5፡24) ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር የሰቀሉ መሆኑን ያመለክታል፣ ይኸውም ከክርስቶስ ጋር የተደረገ ድርጊት ነው፡፡ ይህ ሁሉ የተፈጸመውና እንዲፈጸም የተነገረው በውጫዊ (ፊደላዊ) ማንነት ላይ ሳይሆን፣ በውስጥ መንፈሳዊ ማንነት ላይ ነው፡፡ እንግዲህ ሥጋ ማለት ውስጣዊ የዓመፅና የክፉ ኃይል መሆኑን አውቀን ሥጋን ማለት ሰይጣንን (ጠላት መሆኑን ተረድተን) ከክርስቶስ ጋር በመስቀል ላይ ማለት በሰማያዊ ከፍታ ሥፍራ ላይ ተሰቅለን ሰይጣንን ሰቅለነው እንድንገድለውና ወርደን አውርደነው ደግሞ በጥምቀት መቃብር ሲያል ተቀብረን እንድንቀብረው ይህ አስቸኳይ ጥሪ ይሁንልን፡፡

በዚህ ሁኔታ ስንመለከት ሥጋ እኛ በውጭ የምናውቀው ግልጹ አካል ሰውነት እንዳይደለ ተጨማሪ ማረጋገጫ ይሆነናል፡፡ ይህ የጳውሎስም ሆነ የእኛ ሥጋ በውጭ በሚታየው በቁሳዊ መስቀል እንደተሰቀለ ሳይሆን በማይታየው በውስጥ በኃጢአተኛ ሰውነት መሰቀልን ይገልጻል፡፡ ተደጋግሞ እንደተነገረው ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉት ማለት በአጭር ቃል ሰይጣንን ጠቅልለው ከነሥራው ሰቀሉት ማለት ነው፤ በመሞት እሱን እናጠፋና እንሻገራለን፡፡ አንድ ሰው የተሰቀለውን ክርስቶስ ሊከተል ሊወስን፣ ወይም የኢየሱስ ክርስቶስ የሆኑቱ ሥጋቸውን ከክፉ መሻቱና ምኞቱ ጋር ሰቀሉ ሲል የተሰቀለው ሰው በፈቃዱ ይሰቀላል ወይስ ሌላው ሰው አስገድዶት ይሰቅለዋል?

በጥምቀት ከእርሱ ጋር ሲቀበር በራሱ ፈቃድ ይቀበራል ወይስ ተገድዶ ነው የሚቀበረው? ክፉ (ማቴ.13፥19) መሻትና ምኞት ከሰይጣን ነውና፡፡ ጌታ ኢየሱስ በግልጽ አካል ሕይወቱ በሰው ፊት በውጫዊ የእውነት ገጽታነቱ ከመሰቀሉም በፊት በስውር (በእግዚአብሔር ፊት) ከክፉ መሻቱና ምኞቱ ጋር በእውነት እውነቱ የተሰቀለ ነበር፡፡ ደግመው በሰው ፊት በግልጽ (በጥላ) የሰቀሉት፤ ማለት በመንፈስ የተሰቀለውን በፊደል ሰቀሉት፡፡ ጳውሎስ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ምኞቱ ጋር በእግዚአብሔር ፊት ውስጣዊ በሆነው እውነት በስውር እንደ ተሰቀለ እንዲሁ እኛም ሥጋን ከክፉ መሻቱና ምኞቱ ጋር በእግዚአብሔር ፊት በእውነት እውነቱ በስውር ለእግዚአብሔር እንድንሰቀል ጥሪ ያደርጋል፡፡

ሰውምኮ ለአንድ ነገር መድረስ ሲያቅተው ተሰቅያለሁ፤ ተንጠልጥያለሁ እያለ የሚናገረው በውጭ በቁስ-አካል ሰውነቱ እየተንቀሳቀሰ በውስጥ አካሉ መንጠልጠሉን ሲገልጽ ነው፡፡ እርግጥ ያልሆነ ነገር ሁሉ በጭፍን ስለሆነ ጣዖት ነው፣ ሰይጣን የዕውሮችን ዓይን ሊገልጥ ብርሃን ሊሰጥ ይችላልን? (ዮሐ. 10፥21)



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፉ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16



የዚህኛው ዓለም ተጨባጩ ቁስ አካላዊው ሥጋ፣ የዚያኛው የመንፈሳዊ ዓለም ሥጋ ምሳሌ፣ ምስሉ (ጥላው)፣ ጣዖቱ ነው፡፡ ምስያ ነገር ሁልጊዜም ዋናውን ሊሸፍንና ሊያስረሳ፣ ሊከልል የተፈጠረ ጣዖት ነውና፤ ጣዖቱ ስልም ጥላ/ጨለማ የሚፈጥር ነገር ሁሉም ማለቴ ነው፡፡ ሰዎች ሥጋ እያልን የምንጠራው ጥላውን (ጣዖቱን) የሐሰት እውነቱን ነው፡፡ (መክብ.12፥7)፡፡ አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ፤ (ዘፍ.3፥19፣ መዝ.103፥14) የተባለው፡፡

የምንመለከተው የዚያኛው ዓለም ቋንቋ፣ አባባልና ሥርዓት እስከሆነ፣ በእግዚአብሔር ዓለም ሥጋ የተባለው በሰው ዓለም ፍቺው ይኸው ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ የጌታን ሥጋም በተመለከተ በዚያኛው በእግዚአብሔር ዓለም «ሥጋ» የሚባለው በሰው ዓለም ረቂቅ (መንፈሳዊ) ስለሆነ ተጨባጭ በሆነው በሰው ዓለም ቋንቋ ለመግለፅ ቀጥተኛ መንገድ የለውምና ስለሆነም ጠመዝማዛ መንገድ ተጓዝን፡፡ «ሥጋዬን የሚበላ፣ ደሜንም የሚጠጣ» የሚለው በመንፈሳዊውና በብርሃን ዓለም ቋንቋ ነው እንጂ በሰውና በጨለማ ቋንቋ ከቶ አይደለም፡፡

በተጨማሪም «እግዚአብሔር አንድ ነው» የሚለው ቃል መሠረታዊ እውነት ነው፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ከአንዱ እግዚአብሔር በስተቀር ሌላ የሚቆጠርና የሚዘረዘር ነገር ከቶ የለም፤ ጥላ የለምና፡፡ እግዚአብሔር የማይጨመርበትና የማይቀነስበት አንድና ሁሉ ነገር ሆኖ፣ ሁሉም ነገር ደግሞ አንድ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ እንዲህ ማለትም ሥጋውም፣ ደሙም፣ እንጀራም፣ ውኃም፣ ወተትም፣ ዳቦም፣ እግዚአብሔር ወይም የእግዚአብሔር ቃል እርሱም ክርስቶስ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ነውና፡፡ ደም የምንለው በዚህኛው ዓለም ደም እንደሆነ በዚያኛውም ዓለም ደም እንደሆነ፣ የሚዘልቅ ነገር ሳይሆን፣ ያኛውን ጠቁሞ ለራሱ የሚጠፋ ምግዚት ስለሆነ ቋሚው ደም ከቅዱስ መንፈስ የሚፈልቀው ቃል



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፉ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

ሆኖ ይቀራል፡፡ ውኃ፣ ውኃ ሳይሆን ከቅዱስ መንፈስ የሚፈልቀውን ቅዱስ ቃል ጠቁሞ የእኛ ውኃ፣ ውኃነቱ ይጠፋል፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ወይም ጉዳይ የሚፈጽመው በአንድ ነገር በቃሉ ማለት በክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ ሙሴ በአንዲት በትር እርስዋም ክርስቶስ የሆነች ለአገልግሎት ሁሉ በቂ ነበረች፡፡

የምንመለከተውን ሥጋ ግለፅ ለማድረግ እየሄድን ነው፡፡ ውጫዊው ተጨባጩ አካል አፈር እንጂ ሥጋ አይደለም፤ የሰውን ውስጥ ለራሱ መሰወሪያነት ለመገልገል ሲል ተጨባጩን አካል ሥጋ ነው ብሎ የስሕተት ስያሜ ያስጨበጠው ሰይጣን ነው፡፡ በውጭ በመልክ ተርጓሚውም ፈራጁም እርሱ ስለሆነ፣ በክፉ ሥራ ሁሉ የሚከሰሰው፣ የሚወቀሰው፣ የሚወነጀለው ቁሳዊው አካል ውጩ ሆኖ ቀረና ሰይጣን በሥጋው ማለትም በመሰወሪያው እንዳይታወቅ ከውስጥ ተሸሽጎ የብርሃን ወንጌል እስኪበራ ድረስ ማንም ሳይነካው በሰላም መኖር ችሏል፡፡ በውጪው ዓለም የታወቀው ሥጋ በሐሰት እውነት ነው፡፡

ሥጋን ደግሞ ከአፈር ለይተን (ቀድሰን) ማስቀመጥ አለብን እንጂ ማደበላለቅ፣ ማዳቀል አይቻልም፡፡ ትንሣኤ ማለት ከአፈር መለየት ሳይሆን፣ አፈር በቦታው እያለ ከሥጋ መለየት፣ ሥጋን ገፍፎ መጣል ከሥጋ ቆለፈት ውስጥ መውጣት (መገረዝ) ነው፣ (ቆላ.2፡11-12፣ 3፡9-10)፡፡ በውጭ ተንቀሳቃሹ የአፈር አካላችን በእውነት እውነት አፈር ሲሆን፣ ረግጠን የምንመላለስበት የውጭ ሜዳው ግኡዙ አፈር፣ የሐሰት እውነት አፈር ነው፤ የሐሰት እውነት ሲባልም፣ ጥንት ሰው ከሰይጣን የወረሰው መሰል እውነት፣ ምስያ እውነት መሆኑ በመግቢያ ላይ ታትቷል፤ የመንፈስ አፈር ደግሞ የፊደል (ፍጥረታዊ)አፈር አይደለም፤ የውጭ ምድር የውስጥ ምድር አይደለምና፡፡ ውጫዊው አፈር የአፈር ምስል ጥላ ነው፡፡ አፈር፣ አፈር ነው እንጂ፣ ሥጋ አይደለም፡፡ ሥጋ አፈር







አይደለምና ወደ አፈር አይመለስም፤ አይበሰብስም፤ አፈር አይደለምና አፈር አይሆንም፡፡

አፈር ግን ወደ ተገኘበት አፈሩ ወደ ምድር ይመለሳል (መክ.12፡7፣ ዘፍ.3፡19/ለ ...)፡፡ ሥጋ ቢበሰብስ ኖሮ ፍርዱ ቀላል ነበር፣ ግን ፈቅዶ ስለማይበሰብስ የሥጋ ፍርድ ገሃነመ እሳት ሆነ፡፡ ሥጋ፣ የሥራውን ያመረተውን የኃጢአት ዋጋ ሥቃይን የመቀበያ ክፍለ-አካላችን ነው፣ ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች የሚለው ኃጢአት የሥጋ ሥራ ስለመሆኑ ተጽፏል፡፡ ውጫዊው አፈር ክፍለ-አካል የሥጋ ሥራ ውጤት በውጭ የሚገለጥበት ነው እንጂ ሥራው የሥጋ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሥጋንና ነፍስን ባንድነት በገሃነም እንደሚያጠፋ ደግሞ ተጽፏል፤ (ማቴ.10፡28) አብርሃም፣ ይሥሐቅ፣ ኢየሱስ፣ እስጢፋኖስ በሥጋ ከመሞታቸው ቀድመው ነፍሳቸውን ለእግዚአብሔር እንዳስረከቡ ታሪክ ይገልፃል፡፡ ነፍስን ቶሎ ቀድሰን ለእግዚአብሔር ካላስረከብን፣ ከሥጋ ጋር ሆና የሠራችው ኃጢአት ዋጋ የዘላለም ሞት እንዳያገኛት ማሸሽ ነው፡፡ ኃጢአት እሳት የሚቀጣጠልበት ደረቅ እንጨት ነው፡፡ ሥጋ ከገሃነመ-እሳት ጋር ተመጣጣኝ ነው፡፡ አይሞትምና የመቋቋም ብቃት አለው፡፡ ሥጋን ጊዜ ሳይሰጡ ቶሎ ብሎ አሁን ገፍፈው ካልጣሉት ለገሃነመ እሳት መለኮሻነት ያገለግላል፡፡ የአፈር አካል ለገሃነም እሳት ብቁ ስላይደለ የእርሱ ፍርድ በስብሶ አፈር ሆኖ መቅረት ብቻ ነው፡፡ አፈርን የሰጠው አፈር ነውና ንብረቱን መልሶ ይረከበዋል፡፡ አፈር የባርነት ቀንበር፣ የቁርኝት ግንድ ነው፡፡ አፈርን ማራገፍ አህያ ጭነቱን እንደ ማራገፍ ነው፡፡ ተቃራኒዎች መንፈስና ሥጋ ናቸው እንጂ፣ አፈርና መንፈስ አይደሉም፡፡

- የሥጋ አሳብ ሞት ነው፣ የመንፈስ አሳብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው እንጂ (ሮሜ8፡6) የአፈር አሳብ ሞት ነው አይልም፡፡
- አንድ ሰው ለሥጋ እያሰበ ለመንፈስ ሊያስብ አይችልም፤ ቁ.6፤

- ስለሥጋ የሚያስቡ ከእግዚአብሔር ጋር ጥለኞች (ጠላቶች) ናቸው፤ ቁ.7፤
- በሥጋ የሚመላለስ ለእግዚአብሔር ሊገዛ ከቶ አይችልም፣ ቁ.8፤
- በሥጋ የሚኖር በመንፈስ መኖር አይችልም፣ ቁ.9፤
- በሥጋ አሳብ ማለት በሰይጣን አሳብ የሚመሩ ሁሉ በሥጋ ሕያዋን በመንፈስ ግን ሙታን ናቸው፤ ቁ.13፤
- በመንፈስ የሥጋን ሥራ የገደለ በሕይወት ይኖራል ቁ.13/ለ፤ እንጂ፣ በመንፈስ የአፈርን ሥራ የገደለ በሕይወት ይኖራል አይልም፤
- በሥጋ የሚመሩ ሳይሆን በመንፈስ የሚመሩ ብቻ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው፤ ቁ.14፤
- የቆላስይስ ቤተ-ክርስቲያን ምእመናን የሥጋን ሰውነት የተገፈፉ ናቸው፣ እንጂ የአፈርን ቁርበት የተገፈፉ አይደሉም፤
- ጥምቀት የአፈር ሰውነት ተገፎ የሚቀበርበት የሚታይ መቃብር ሳይሆን፣ የሥጋ ሰውነት ተገፍፎ የሚቀበርበት የማይታይ ጉድጓድ ነው፡፡ (ቆላ.2፡11-12) ሥጋን የሚታየው መቃብር ሊይዘው አይችልም፡፡
- ሥጋ እንዲሰቀል የተፈረደበት ክፍለ-አካል ነው እንጂ አፈር እንዲሰቀል አልተፈረደበትም፣ (ገላ.5፡24) ሥጋን ማንጠልጠል የሚችል ቁሳዊ መስቀል አይደለም፡፡

እስተውለን ስንመለከተው ሥጋና መንፈስ የሞትንና የሽረትን ያህል ሲቃረኑ የሚኖሩ በየምድራችን ላይ፣ በየማህፀናችን ውስጥ የሚታገሉ (ዘፍ.25፡21-26) የዕድሜ ልክ ሠልፈኞች፣ በአንድ አካል ሁለት አባል ናቸው፡፡ ሥጋንና አፈርን ለይቶ አለመመልከቱ የወንጌልን ፍቺ ያዛባል፡፡ በ(ገላ.2፡20) ላይና (6፡14) ላይ ጳውሎስ ከጌታ ጋር ከዓለም መሰቀሉን፣







ዓለምም ከእርሱ መሰቀሉን የሚመሰክረው በስውር አካል በሥጋ እንጂ በተጨባጭ በፊደል (ፍጥረታዊ)አካል በአፈሩ አይደለም፡፡

በ(ገላ.5፡24) ላይ ደግሞ እንደሚያመለክተው የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ምኞቱ ጋር የሰቀሉ ናቸው እንጂ አፈሩን ቁሉን የሰቀሉት አይደሉም፡፡ በተመሳሳይ ረድፍ ዳዊት...እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ ሲል፣ ኢሳይያስም ጀርባዬን ለገራፊዎች፣ ጉንጬን ለጠጉር ነጩዎች ሰጠሁ (መዝ.22፡16-18፤ ኢሳ.50፡ 6፤) የሚሉበት በእውነት፣ እውነት በሥጋ ላይ የተቀበሉት መከራ እንጂ በሐሰት እውነት በውጭ በተለመደ አፈር በሆነው አካል ላይ የተፈጸመ ፊደላዊ (ቁሳዊ) መከራ አይደለም፡፡ በ(ገላ.5፡19-21) ላይ የተዘረዘሩት የሥጋ (የሰይጣን) ፍሬዎች ናቸው እንጂ፣ የአፈር ፍሬዎች አይደሉም፡፡ የሥጋ ሲባል የሰይጣን ነው፡፡ ሥጋ ሚስት ስለሆነ ከሰይጣን እየጸነሰ ነው እነዚህን የጥፋት ፍሬዎች የሚወልደው፡፡

የሰው ሥጋ ተቃራኒነት፣

የምናውቀው የሰው ሥጋ ይበሰብሳል፣ የምናውቀው ሥጋ ለማናውቀው ሥጋ ጥላ ሲሆን፣ የምናውቀው መበስበስም ለማናውቀው መበስበስ ጥላ ነው፡፡ የጥላ መበስበስ የአካል መበስበስ ነጸብራቅ ነው፡፡ በሚታየው የማይታየውን እናይና እንማርበት ዘንድ እንታረምበትም ዘንድ ይህ ለዚያው ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ የውጪው ሥጋ በሰው ፊት እንደሚበሰብስና እንደሚሸትት፣ እንዲሁ የውስጡ ሥጋ በውስጥ በጌታ ፊት ይበሰብሳል፤ ይሸትታልም፡፡ የውጭ መበስበስ ከባክቴሪያ ሲሆን፣ የውስጥ መበስበስ ከኃጢአት ነው፡፡ ባክቴሪያ ውስጥን ሊያበሰብስ ሊገባ በሩ ጠባብ ነው፡፡ ኃጢአት ግን በጠባቡ በር ወደ ወስጥ ይገባል፤ ያበሰብሳል፡፡ የሰው በውጭ የሚታየው ትዕቢት የውስጡ ዕብጠት ነው፡፡ የአካባቢዩ ሰው ትዕቢተኛውን ሰው ‹‹ይመግላል፣ ትመግላለች›› ይላል፡፡ የውስጣዊ መበስበሱን ይገልፃል፡፡

*ነቢዩ ኢሳይያስ ሲናገር ‹‹ከእግር ጫማ አንሥቶ እስከ ራስ ድረስ ጤና የለውም፤ ዕበጥና የሚመግልም ነው...ኢሳ.1፥6›› ይህም በእግዚአብሔር ፊት ስላልተቀመጠ (ዘፀ.16፥33፣ ዘዳ.28፥35) ሰው በውጭም በውስጥም ይተላል፣ ይሸትታል፤ ትዕቢቱ መግል የያዘ ዕብጠቱ ነው፤ (ሐሥ.12፥23፣ 13፥36፣ ኢሳ.14፥11፣ ኢዮብ 21፥26፣ 17፥14/ለ 25፥6፣ መዝ.38፥5) ይመሳከር፡፡ የመንፈስ ትል ምንድን ነው? መንፈስን፣ (ውስጥን የሚያበሰብስ የመንፈስ ትል ሰይጣን ነው፣ ኃጢአት፡፡*

*ሰው የተባለ የውጪ ነገርና የውጭ ሰውነቱ ሲተላ ያውቃል ወይስ የውስጡ ነገርና የውስጡ ሰውነት ሲተላ ያውቃል? ውጪው የሚተላው ስለ ውስጡ ምስክር ሆኖ ነው፡፡ ውስጥን ከማየት ስለ ታወርን በውጪው ሊያስመሰክርብን አመጣብን፡፡ ውስጡ መትላቱን አናውቅ ብለን፣ ከነ ውስጣዊ ትሉ ስለምንጀንን፣ ስለምንኮራ፣ ከበሮ መሰንቆ ወስደን ስለምንዘፍንና ስለምንደንስ ጌታ ውርደቱን በውጭ በሰው ፊት ሊያስመሰክርብን የውስጥን ትል ሥጋ አልብሶ ወደ ውጭ አውጥቷል፡፡ የበላነው የተከበረ ነገር ይበሰብሳል፣ ይተላል፤ ይገማል፤ የጠጣነው እጅግ ውድ የሆነ ነገር ይበሰብሳል ይገማል፣ ወደ ውጭ ወስደን አፍንጫ ይዘን ጥለን እጅግ ንጹሕ፣ ትልቅና የተከበረ፣ አንቱ እየተባልን ከእርስ በርስ ክብር እየተቀባበልን አንዱ ከሌላው (እንደ አዳምና ሔዋን) ከእርስ በእርሱ፣ በጨርቅ ተሸፋፍነን እየተንቀባረርን እንመላለሳለን፡፡ ከዚያም ሞተን፣ ተዋርደን ሌላው ሰው አሥሮ ገንዞን አፍንጫ ይዞ አውጥቶ በጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ይጥለናል፤ ክቡር ሆይ የተባልን ሁላ፣ እንበሰብሳለን፣ ሁላችንም እኩል እንገማለን፡፡*

*(መዝ.38፥5) ንጉሡ ዳዊት ከስንፍናዬ የተነሣ ቁስሌ ሸተተ፣ በሰበሰም ... የሚለው በውጪ የፊደል (ፍጥረታዊ)አካሉ ቆስሎበት ነው ወይስ በውስጥ የስውር አካሉ ቆስሎ በሰብሶበት ነው? መልሱ ግልጽ ነው፤ ዳዊትን ማንም ምንም በግልጽ አላቆሰለውም አልሸተተም፣ ከቶ የማደፍረውም*







*አልነበረም፤ ነቢይ ስለነበረ በውስጥ መቁሰሉንና መበስበሱን አይቶ ውርደቱን ለእግዚአብሔር ሲያጋልጥና ሲናዘዝ ነው፡፡ የጢሮስ ንጉሥ በሰው ፊት በሕይወት ነኝ፣ ጤናማ ነኝ ክቡር ነኝ ሲል ከውስጥ በስውር መበስበሱን እንዳያይ የተጋረደበትን ነቢዩ እንደነቢይነቱ አይቶ መስክሮበታል፡፡ ከላይ እንዳየነው ሰው በውጭም በውስጥም ይቆስላል፣ በውጭም በውስጥ ይበሰብሳል፣ <<ይህ አሳብ በሐሰት እውነት ላይ የቀረቡ ሦስቱ ምስክሮቼ በተባለ መጽሓፌ «ገሃነመ-እሳት» በሚለው ክፍል በይበልጥ ተብራርቷልና ወደፊት ያገኙታል>>*

*ክርስቶስም ቢሆን፣ በተግባር ተጨባጩን በሰው ቋንቋ ሥጋ የተባለውን መቼም፣ ለማንም አላቀረበም፡፡ በማግስቱ የተሰቀለውና የሞተው፣ ማታ ሲበሉት በተረፈ ግማሽ አካል ሳይሆን፣ በሙሉ አካል ሰውነቱ እንደነበረ ነው፡፡ አፈርን ሳይሆን ሥጋውን በሕይወት እያለ ማካፈሉ በብርሃን ምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ ቅዱስ ነገር ከእርኩሱ ሰው ሁል ጊዜም የተጋረደ ነውና ቅዱሱን ሥጋ በእንጀራ ሸፍኖ አቅርቧል፤ መጋረጃውን ገና አልቀደደም ነበርና፡፡ ቃሉ ፈጣሪ ነው፤ ቃሉ እውነት ነው፣ ከአፉ እስከ ወጣ የተባለውን ፈፃሚ ነው እንጂ ባዶውን የማይመለስ ነውና የሚለው የዘላለም እውነት ነው፡፡ ውኃውን በትእዛዙ ወደ ወይን የለወጠው ዓልአዛር ሆይ፣ ና ውጣ፤ አልጋህን ተሸከመህ ሂድ...ወዘተ፤ ይሆናል፣ ያደርጋል ከንቱ ሆኖ አይቀርም፡፡ ሁሉንም ያደረገ ቃል እርሱ ነውና ይህ አያስደንቅም፡፡ ኢየሱስ ቃል ነው፣ ቃሉን በእንጀራ ሸፍኖ (ጋርዶ) ሰጥቶአቸዋል፡፡ እንጀራው የቃሉ መጋረጃ ነው፡፡ ገናም መጋረጃውን አልቀደደምና ከመጋረጃ መቀደድ በኋላ ግን ያልተሸፋፈነውን ራሱን (መንፈስ የሆነ ቃሉን) በብርሃን በቀጥታ እንካፈላለን፡፡*

*በሰውም ዘንድ ስናይም እንጀራ ተበልቶ ነው ሥጋ የሚሆነው፡፡ እርሱ ግን ሰማይንና ምድርን በውስጣቸው ያሉትን ነገሮች ሁሉ ወደ መኖር እንዲመጣ ሁሉ ቃል የበላውን ወደ ሕይወት ማምጣቱ የሚያስደንቅ*

አይደለም፡፡ በውጭም የምንበላው የምንጠጣውም ሁሉ እኮ በእርሱ በቃሉ የሆነ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ቃል ጭምር እንጂ፣ ሰው በእንጀራ ብቻ በሕይወት አይኖርም (ዘዳ.8፡3፣ ማቴ.4፡1-4) ነቢዩ ኤርምያስ ቃሉን በላ (15፡16)፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ቃሉን እንዲመገብ መከረው፤ (1ጢሞ.4፡6) ነቢዩ ሕዝቅኤልና ወንጌላዊው ዮሐንስ መጽሐፍ በሉ (ሕዝ.2፡8-10፤ 3፡1-3፣ ራዕይ 10፡8-11)፡፡ ቃሉም፣ መጽሐፉም ክርስቶስ መሆኑ የሚታይ ነው፡፡

ጌታ በተሳተፈበት በአንደኛ ፋሲካ በውጭ ሜዳ እንጀራ በቆረሰ ጊዜም የተበላው ወደ ሰው ሕይወት ሲዛወር የተረፈውም ቁርስራሽ አንድ እንዳይወድቅ በአሥራ ሁለቱ መሶቦች ተሰብስቦና ተነሥቶ፣ ተወስዶ የተበላ ስለሆነ ወደ ሰው ሕይወት የተዛወረ /Transferred/ (ዮሐ.6፡12፣ ማቴ.14፡13-21) መሆኑን እናያለን፤ በሁለተኛ ፋሲካም በተመሳሳይ፡፡ በሦስተኛው ፋሲካ እንዲበሉ የሰጣቸው ሥጋ ከነደሙም ስለነበረ ሕያው መሥዋዕት ነው፡፡ የሥጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና፣ (ዘሌ.17፡11፣ ዘፍ.9፡4) ይህ ደም ሥጋን የሚነዳ አንቀሳቃሹ ደም ነው ወይ? የሥጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና  ደምን ከሥጋ ጋር እንዳይበሉ ታዟል፡፡ የእርሱ ደም ግን እርሱ ባለቤቱ ደሜ ነው ጠጡ ብሎ ባርኮ በወይኑ መሸፈኛነት የሰጠው ቅዱስ ደም እንጂ ሰዎች የምናውቀው የፊደላዊ (የፍጥረታዊ) ሥጋ ደም አይደለም፡፡ ክርስቶስ ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ እንጂ ከሥጋ የተወለደ ሥጋ አይደለም፤ የተለመደውን ሥጋ ደም አላቀረበም፡፡ ማስተዋል ያለብን፣ የክርስቶስ ሥጋ የሰው ሥጋ አለ መሆኑን፤ ማለትም ቀደም ሲል እንዳየነው የሰው ሥጋ ከምድር ሲሆን፣ የክርስቶስ ሥጋ ከሰማይ መሆኑን ነው፣ ዮሐ.6፡50-51፣ 8፡23)፡ የሰው ሥጋ ከምድር የሆነ ሥጋ ሲሆን፣ የክርስቶስ ሥጋ ከምድር፣ ከሥጋና ደም ፡ ከወንድ ፈቃድ አይደለም፤ እርሱን የተቀበሉትም እንዲሁ (እንደ እርሱም) ከሥጋና ከደም ከወንድ ፈቃድ አይደሉምና (ዮሐ.1፡11-13)፡፡







ሥጋው ሰማያዊ እንደመሆኑ መጠን ለሰማያዊ ሕይወታችን የሚሆን እንጂ፣ ለምድራዊ ሕይወታችን የሚሆን ወደ ቁሳዊ ወደሆነ ሆድ የሚወርድ አይደለም፡፡ ይኸውም አሁንም በሰማያዊ ሥፍራ በፊቱ ከማዕዱ እየተካፈልን በሕይወታችን ውስጥ እየተሠራጨ ይገኛል፣ ሁልጊዜም ይቀጥላል፡፡

የሥጋን ምንነት በተለይ እስከናይ ድረስ፣ የክርስቶስ የት ገብቷል? ለሚለው ጠያቂ መልሱ፣ የክርስቶስ ሥጋ ከውጭ ወደ ውስጥ፣ ከፊደል ወደ መንፈስ ከጥላ ወደ አካል፣ ከሙታንነት ወደ ሕያውነት ተቀየረ፡፡ ሥጋው ተበላ፣ ደሙ ተጠጣ፤ ቀሪው በአሥራ ሁለቱ ተንቀሳቃሽና ሕያዋን መሶቦች ሙሉ ሆኖ ተነሣ፤ ገና ሊበሉ ላሉት ሁሉ ወደ ዓለም ሁሉ እየተላከ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ አገልግሎቱን እንደ ቀጠለ ነው፡

ክርስቶስ ሕያው ሆኗል የማለት ማረጋገጫም በእነዚህ ተመልሶ መንቀሳቀሱ ነው፡፡ እርሱ በእነርሱ በበሉትና በጠጡት ሕያው፣ እነርሱ በእርሱ በበሉትና በጠጡት ሕያዋን ሆኑ፣ (ዮሐ.6፡56-57) ይመሰክር፡፡ ክርስቶስ እየተቆራረሰና እየተበላ ይባዛል፤ ቀደም ሲል እንዳየነውም ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሉ ተብሎ የተጻፈው እየተፈፀመ ነውና፡፡ ልዕለ ሰበዓዊ አበዛዝ፣ {SUPPERNATURAL WAY OF MULTIPLICATION} የፋሲካው ሕያው እንጀራ በነዚህ መሶቦች ተንቀሳቅሶ ወደ ዓለም ሁሉ ተዳርሷል፡፡

(ሞትና ሕይወት፣ በሥጋና በመንፈስ መካከል፤)

የሥጋህ ሞት ለመንፈስህ ሕይወት ሲሆን፣ የመንፈስህ ሞትም ለሥጋህ ሕይወት ነው፡፡ ሕይወት ሲጠፋ ሞት ይነግሣል፣ ሞት ሲጠፋ ሕይወት ይነግሣል፡፡ ነገሩ አንደኛው ሲጠፋ ሳይሆን አንዱ በሌላኛው ቁጥጥር ሥር ሲሆን ማለት ነው፡፡ ሕይወትና ሞት ይፈራረቃሉ፤ ማለት ሥጋና መንፈስ ይፈራረቃሉ ነው፡፡ የሥጋ ሞት ሲባል የፊደል (ፍጥረታዊ)አካል የቁሱ



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አሬ አሏልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

መሞት ማለት አለመሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡ ሥጋና መንፈስ በመለኮታዊና በሰበዓዊ አገላለፅ ሆኖ አለመጣጣምን ከመፍጠሩ በስተቀር ሁለቱም እቻ ተነጻጻሪና ተመሳሳይ እንጂ አንዱ ጉልህ ሌላው ረቂቅ አካል አለመሆናቸውን ደጋግመን ማየታችን ነው፡፡ ፍልሚያቸውና መሟሟታቸውም በውስጥ በጌታ ፊት፣ ሕይወታቸውም በውስጥ በጌታ ፊት እንጂ በውጭ በሰው ፊት የሚታይ አይደለም፡፡

አዳም፣ አዳማዊውን ሁሉ ይዞ በመንፈስ ሞቶ በሥጋ ሕያው ሲሆን፣ ክርስቶስ ደግሞ በተቃራኒ ክርስቶሳውያንን ሁሉ ይዞ በሥጋ ሞቶ በመንፈስ ሕያው ሆኗል፤ (1ጴጥ.3፡18)፤ ይህ የሚያሳየው ኢየሱስ በቁሳዊ መስቀል ላይ በቁስ-አካል ሞቶና በቁስ-አካል ተቀብሮ መነሣቱን ብቻ የሚያሳይ ሳይሆን ኢየሱስ መቼም ቢሆን ምልልሱ በመንፈስ እንጂ በሥጋ ስላልነበረና ከአብ ስላልተለየ በመንፈስ የሥጋን ሥራ የገደለ በመሆኑ፣ ሥጋው ከመንፈሱ የተነሣ በቁመና የሞተ ስለነበረ የኢየሱስ ሕያውነቱ ተቋርጦ የቀጠለ ሳይሆን ሁልጊዜም ሕያው ነበረ፤ ነውም (ዮሐ.14፡19-20፤ ሉቃስ 24፡23፣ ዕብ.9፡14) አዳምና አዳማዊው የሆነ የሰው ልጅ ሁሉ በቁመናው ሙት ሲሆን፣ ክርስቶስና ክርስቶሳውያን የሆኑት ሁሉ በቁመናቸው ሕያዋን ናቸው፣ ማለትም የተቀበሉት ክርስቶስ ሕያው ስለሆነ፣ ከተቀበሉት ሕያው ቃሉ ማለት ከመንፈሱ (ከእርሱ) የተነሣ አሁኑኑ ከሞት ወደ ሕይወት የተሻገሩ ሕያዋን ናቸው፡፡ «አሁን ነው» ተብሎ እንደተጻፈ፤ (ዮሐ.5፡24-25) ከትንሣኤ በኋላ በተፈጸመ ዘመን ውስጥ ቀጠሮ የለም፡፡ ስለሆነም ሥጋውያን ሁሉ አዳማውያን ስለሆኑ አሁኑኑ ሙታን ናቸው እንጂ፣ ቀጠሮ የለም፡፡ እርሱ ከአብ የተነሣ ሕያው ሲሆን እኛ ከእርሱ የተነሣ ብቻ ሕያዋን ነን (ዮሐ.6፡57)፡፡ ሰው ያለ ክርስቶስ መድረሻ የሌለው ለነፋስ የተሰጠ ዱቄት ነው፤ ነፋስም ዲያብሎስ፡፡ አሁንም ያለ ክርስቶስ በመሆኑ ያለ መድረሻ እየሸሸ ይታያል፣ በሰው ፊት ሰላማዊ ይመስላል እንጂ ውሸቱን፡፡ ከሕይወት ወደ







ሞት መሸሸ፤ አዳም እንደደረገ ነው፡፡ «እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ፤ አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሔር ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ፤ (ዘፍ.3፡8)»

ለሰው ልጅ መሞቱ ኃጢአት ሳይሆን፣ መጥፊያው ሙት መሆኑን አለማመኑና መካዱ እሬሣውን በእጅ ሥራው መሸፋፈኑ ነው፡፡ ይህም የብርሃንን ምስክር አለማመኑ፡፡ ክርስቶስ ሕይወት ከሆነ፣ አዳም ሞት ነው፡፡ እንዲህ ማለትም ሥጋውያን ሙታን፣ መንፈሳውያን ሕያዋን ናቸው ማለት ነው፡፡ ይህ፣ መንፈሳዊው ትንሣኤና መንፈሳዊው ሕይወት በአዲስ ኪዳን የመጣ ሲሆን፣ በብሉይ ኪዳን የመጣው ቁሳዊ ሕይወትና ውጫዊ ትንሣኤ ነበር፡፡ ነገር ግን ታናሹ ከነረቂቅ አዋጁ እንዲከበር ታላቁ ከነጉልህ ሥርዓቱ ሥፍራ ይለቅ ዘንድ የሚገባ ነው፡፡

## ክፍል አምስት
## መቃብር

መቃብር፣ ከጽሑፉ መንፈስ አንፃር ሲተረክ፣ የጨለማው ምድር፣ የሙታን ሠፈር፣ የአጋንንት መንደር ነው (ኢዮብ 10፥20-22፣ መዝ.88) ይህ የእውነት እውነቱ ነው፡፡ በተለመደው አገላለጽ፣ ነፍስና ሥጋ የተባሉት በውሕደት ተጣምረው ከሚኖሩበት ሲፋቱና ሲለያዩ ነፍስ የተባለው ሥጋ የተባለውን ሲያንቀሳቅስ ከቆየበት ቤቱን በርግዶ ወጥቶ ሲሄድ፣ በፊደሉ/በግልፅ ንባብ መሠረት (መክ.12፥7) ሥጋን ወደ ምድር ጥሎ ለራሱ ወደ ሰጠው እግዚአብሔር ሲመለስ፣ አፈርም ወደ ነበረበት ምድር የሚመለስበት ሥነ-ሥርዓት ማለት ነው)፡አፈር ውጫዊው የውስጣዊ አፈር ምሳሌ ሲሆን፣ ሥጋ፣ የውስጣዊ ሥጋ ምሳሌ፣ መቃብር፣ የውስጣዊ መቃብር ምሳሌ መሆኑን እናስታውስ፡፡ የሚታየው ለማይታየው ምስያ ነው፡፡ «መቃብር፤» ሥጋን በማስወገጃ ጉድጓድነቱ ትንቢታዊ ፤ አስተማሪም ነው፡፡ የትንቢቱ ጉልህ ፍጻሜም ታሪካዊና የመጽሐፉ ስያሜ የሆነው የክርስቶስ ሥጋ የተወገደበትና በሦስት ቀን ውስጥ ከቦታው ጠፍቶ ዕንቆቅልሽ የሆነው መቃብር ሲሆን፣ በዚህም አንፃር የትንቢቱ (የትምህርቱ) ተጨባጭ ወደ ሆነው የፍጻሜ-ፍጻሜ ስንጓዝ የጌታ ኢየሱስን መቃብር ከነጓዙ ለማየት ልንመለስበት የሰገነቱን ቁሲካ ምክንያቶችና ምንነቱን ከመሠረቱ ትዝታውን ጨምረን እንድንመለከት ያደርገናል፡፡ የትንቢቱን የፍጻሜ-ፍጻሜና ትምህርቱንም ስንጓዝ እናገኘዋለን?

መቃብር በውጭ በአሕዛብ፤

በውጭ በአሕዛብ፣ ማለት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ስንመለከት፣ አሕዛብ ከገነት ማለት ከእግዚአብሔር ፊት ወደ ውጭ ከተወረወረው አዳም በውጭ ከሥጋ እንደተወለደ በውጭ ያደገ፣ በውጭ የቀረ ሕዝብ ማለት ነው፣ እስራኤል ግን ከውጭ ወደውስጥ ከመጠራቱም ከቆለፈቱ



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፥16

የጌታ ሥጋ መድረሻና ምንነቱ፤

ቁርበት ከተገፈፈው አብርሃም የተወለደ ልዩ ሕዝብ ነው፣ በሌላም፣ አሕዛብ ማለት ከነገደ እስራኤል ውጭ ያለውን ሕዝብ ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ የአሕዛብ መቃብር፣ መቃብራቸው ከሸለፈቱ ሳይለዩ ማለት ሳይቀደሱ፣ ወንዝ ሳይሻገሩ፣ እስራኤል አገር ሳይገቡ ከነሥጋ ቁርበት ጋር፣ ገለባውና ፍሬው እንዳለ ሞቶ የሚቀበሩበት ሜዳዊ ግልጽ መቃብር ማለት ነው፡፡

ቡተጨማሪ አሕዛብን በውጭ መቅረታቸው፣ አስማተኞች፣ ሴሰኞች፣ ነፍሰ-ገዳዮች፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ ውሸትን የሚወዱና የሚያደርጉ ከማድረጉም በላይ፣ በዚህ ሰበብ ከውሻዎች ጋር ደባልቋቸዋል፣ (ራዕይ 22፥15)፡፡ በውጭ ያሉ የሚለውን ቃል ስንመለከት፤ በውጫዊ ሕይወት በቁሳዊ እንጂ በውስጥ (በመንፈስ) ሕይወት የሌላቸው ሰዎችንም ያጠቃልላል፤ በሚታየው ነገር የተጠመዱትን፡፡ እነርሱ፤ ግን በውጭ ናቸው ማለት ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ፊት ከመጋረጃ ውጭ ማለት ነው፡፡ የአሕዛብ መቃብር እግዚአብሔር በክርስቶስ ያልሰወረው ለማለት ነው፣

በውጭ ያሉቱ ደግሞ በአዳም ቁርበት እንደተጠቀለሉ ወደ ውጪ ጨለማ የተጣሉ ቁርበታሞች ናቸው (ማቴ.8፥11-12፣ 22፥13፣ 25፥30) በውጭ ይበላሉ፣ ይጠጣሉ፣ ውስጣቸው ግን ባዶ ነው፤ ራስን ለመደለልን ለከንቱ መፅናናት ይጨፍራሉ፣ ይዘፍናሉ፣ እልል ይላሉ፣ በውስጥ ግን ሰላምና ጤና እርካታ የላቸውም፡፡ በውጭ ይነግዳሉ፣ ከማንነት በውጭ ያተርፋሉ፣ ይበለፅጋሉ፣ ውጫዊ አካል ቀፎአቸው የተከበረ ነው፤ ነገር ግን ሁሉም ነገራቸው ከማንነት በውጭ ሜዳ ላይ የተረገዘ (ECTOPIC PREGNANCY) ማለት ነው፡፡ ይህ ሁሉ ቢሰበሰብ ልብ እርካታ፣ እፎይታ የማያገኘው ለምንድን ነው? ከዚህ ምድራዊ ከሆነ ነገር ምንም ጠብታ ያህል እንኳ በጠባቡ በር ወደ ልብ ስለማይገባ ልብን የሚያጠግብ ምንም ነገር አንዳች ጠብታ በውስጥ ሰለሌለ እርካታና እፎይታ የለም፤ ይህንንም የሚረዳው እስራኤል እንጂ፣ አሕዛብ፣ ይህን በውጪ ጨለማ መሆናቸውንም በሞት ጥላ መኖራቸውንም አይረዱም፡፡ በውጭ ያሉ



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፥16

እያዩ አያዩም እየሰሙ አይሰሙም፣ አያስተውሉምም፣ (ማር.4፡12) በውጭ ያሉ ሁሉም የማያይ ዓይን፣ የማይሰማ ጆሮ፣ የማያስተውል ልብ አላቸው፡፡ ወስጥን ያዩ፣ ይሰሙ፣ ይረዱ ዘንድ ዓይናቸውን፣ ልባቸውን፣ ጆሮአቸውን ባለመገረዛቸው በቆለፈቱ ቁርበት የተሸፈነ፣ የተደፈነ ነው፤ (ኤር.6፡10፣ ሐሥ.7፡51)፡፡ እነዚህ የበደላቸውን ይቅርታ ያላገኙ ናቸው፤ (ማር.4፡12) በውጭ ያሉ በበደላቸውና ሥጋቸውን ባለመገረዛቸው በሞት፣ በመቃብር (ጨለማ) እያሉም በሕይወት ያሉ በማስመሰል ደግሞ ይዋሻሉ፤ ውሸትን የሚወዱ ተብሎ የተጻፈ ነውና፡፡ ይህ ፍርድ በሰው ፊት ውጭን ተገርዞው በእግዚአብሔር ፊት ውስጥን ልብን ያልተገረዙ እስራኤላውያንንም ያጠቃልላል፡፡ ውጭን መገረዝ አንደኛ ልደት ስለሆነ ውስጥን በመገረዝ ዳግመኛ ካልተወለዱ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማየት የለም፤ (ዮሐ.3፡3)፡፡ የእስራኤል እድገትም ውጭን ተገርዞ በውጭ በሰው ፊት እየተኩራሩ በውጭ መቅረት ሳይሆን፣ ውስጥን በመገረዝ ብርሃን {PHOTOTROPISM} ወደ ሆነው ውስጥ-ውስጠኛ ክፍል ወደ እግዚአብሔር ፊት ፍጹም ሙላት መድረስ ነው፡፡ በፊቱ በብርሃን ማደግ፤ ልብን መገረዝ ከጨለማ ወደ ብርሃን ስለሚያወጣ በብርሃን ማደግ ደስታን ስለሚሞላ ይመቻል፡፡ በውጭ ከሆነ፣ እንደ አትክልቶች ሥር ወደ ላይ ሳይሆን፣ ወደ ጨለማ ወደ {GEOTROPISM} ማደግ ነው፤ ከብርሃን መሸሽ፡፡

በውጫዊ ሥርዓት በውጭ መቆም ሌሎች ሊገቡ የሚመጡትን እንዳይገቡ በሩን ዘግቶ መያዝ በመሆኑ ተደራቢ ኃጢአት ሆኖ ወዮላችሁ የሚል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶበታል፤ (ማቴ.23፡13) ወደ ጌታ መጪዎች ከውጪ ጨለማ ዓለም የጌታን ብርቅርቅታ ብልጭታ ዓይተው ሲመጡ አንተም የጨለማ ሥራ በሆነው ሜዳዊ አገልግሎት ሥነ-ሥርዓቶች የተጣበቅህ ስለሆነ አንተጋ ይቀርና በጨለማ ባለህበት እርገጥ ይቀጥላል፡፡

በውጭ ያሉ በሰው ፊት በውጪ የሥርዓት ሃይማኖተኞች አስመሳዮች በመንፈስ፣ በእግዚአብሔር ፊት የሌሉ ሰልፋቸው በ(ራዕይ 22፡15)





ከተዘረዘሩት ጋር ከአዲሲቱ ኢየሩሳሌም በውጭ ባለ ጨለማ ነው፡፡ ውጭን፣ ውጫዊ ዝናን፣ ውጫዊ ጥቅምን፣ ውጫዊ ክብርን፣ ውጫዊ ሕይወትን መርጠዋልና ውርሳቸው አሁን በልባቸው መዝገብ ተሰፍሮ የሞላ ጨለማ ነው፡፡ ሰው ሥራውን፣ ከማንነቱ ከመዝገቡ ውጭ ውርስ የለውም፡፡

ትኩረታችን በመቃብር ላይ ሲሆን፣ መቃብር የሙታን ማረፊያ መሆኑን ከቁሳዊው መቃብር እናስታውሳለን፤ (ኢዮብ 10፡21-22) የማንም መቃብር ውስጡ በንስሃ ከሚነፃ በስተቀር ያው እንደ ውጫዊውም መቃብር የሙታን አጥንት፣ ርኩሰት የሆነ ብስብስ ነው፤ (ማቴ. 23፡27፤ ሉቃስ 11፡44)፡፡ በውስጥ ግን በእግዚአብሔር ስም ተሠውተው (ሞተው) እግዚአብሔር የሚቀብራቸው ቅዱሳን መቃብሮችና በዲያብሎስ ስም ተሠውተው ዲያብሎስ የሚቀብራቸው እርኩሳን መቃብሮች ሁለት ዓይነት ናቸው፡፡ ውጨ በውጭ በሚፈርደው ፊት ሲሆን ውስጡ በውስጥ በሚፈርደው ፊት መሆኑ የሚታወቅ ነው፡፡

‹‹መቃብር››፣ በውጭ፣ ውጫዊው ቁስ አካል ሞቶ ከውጭ ሕያዋን ፊት ተወግዶ የሚቀበርበት እርኩስ መቃብር እንዳለ ሁሉ፣ እንዲሁ በውስጥ ውስጣዊው ሰውነት በልቡና ሞቶ ከሕያው እግዚአብሔር ፊት የሚወገድበት መቃብር አለ፡፡ መቀበር፣ ከብርሃን ጨልሞ በጨለማ መሠወር ማለት ሲሆን፣ ሌላው ዓይነት መቀበር እግዚአብሔር አዳምን በቁርበቱ ሸፍኖ ሸፍኖ ከፊቱ ብርሃን ወደ ውጪ ጨለማ ያወጣበት መቃብር መሆኑ ትዝ ይለናል፡፡ ይህ በውጪ ዓለም የታወቀው ከማንነት ወጭ አካላውያን ሙታን ማለት ነው፡፡ ከማንነታቸው በውጪ ጨለማ እርኩስ መቃብር የሚቀበሩ ሲሆን፣ በውጪ ቅዱስ መቃብር የቀድስት አገር ሕዝብ፣ የእስራኤል መቃብር ነው፡፡ በወጪ ቅዱስ ማለትም እስራኤልን ከአሕዛብ የሚቀድስ/ የሚለየው የመካከል ግድግዳ ሥጋ ቁልፈት ነው፤ (ኤፌ.2፡11-16)፡፡ ስለዚህ አሕዛብ በጨለማና በሞት ጥላ

የሚኖሩ ተብለው በነቢይ ተጽፏል፤ (ኢሳ. 9፡1-2፣ ማቴ.4፡-16) እንደገናም ይህ ምሳሌ ሆኖ በአዲስ ኪዳኑ ደረጃ ሲታይ እስራኤልን ከእስራኤል በሚበልጥ ደረጃ የሚቀድስ /የሚለይ አዲስ ሥርዓት በዕድገት የመጣው ውጫዊ አካልን የተገረዙ እስራኤልን ውስጥን /ልብን ከተገረዙ እስራኤል በመለየት ውጭና ውስጥ፣ ጨለማና ብርሃን፣ ግራና ቀኝ፣ ፍየልና በግ የሚያደርግ የመጨረሻው የመደምደሚያው መልእክት ነው፡፡ በአዲስ ኪዳን ደረጃ ላይ ሲኮን ደግሞ በሚበልጥ ደረጃ የሚቀድሰው ውስጥን/ልብን የተገረዙ የእግዚአብሔር እስራኤልን ውጭ አካልን ከተገርዙ እስራኤል ቆርጦ የሚቀድሰ/የሚለይ ከአፉ የሚወጣው የአዲስ ኪዳኑ ስለታም ሰይፍ መጥቷል፤ «ሰይፍ ሆይ፣ ባልንጀራዬ በሆነው ሰው በእረኛዬ ላይ ንቃ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፣ እረኛውንም ምታ፣ በጎቹም ይበተናሉ...(ዘካ.13፡7፣ ማቴ.10፡34»፡፡ ይህ ሰይፍ በውጭ ሰውን ከአባቱ፣ ሴት ልጅን ከእናቷ፣ አማትን ከምራቷ መካከል ገብቶ የሚገርዝ ከመሆኑም፣ ሰውን ከራሱ ከማንነቱ መኻል ሰንጥቆ በመቀደስ/በመለየት አንተን ራስህን ከራስህ ከፍሎ ወደ ውጭና ውስጥ፣ ወደ ጨለማና ብርሃን፣ ወደ ቀኝና ግራ፣ ወደ በግና ፍየል፣ ወደ ሞትና ሕይወት የሚገርዝ ከሰው አፍ የሚወጣ ቀዝቃዛ ወነወጌል ሳይሆን፣ በቀጥታ ከአፉ የሚወጣ ስለታም ወንጌል ነው፤ አትናቁት፡፡ ከስለታም ሰይፉ ማዶ በኩል ያሉት እንዳለ አሁን ተፈርዶባቸው ብርሃንን ማለትም ከእግዚአብሔርን የማያዩ በውስጥ ውጪ ጨለማ በቁመና መቃብር የቀሩት ሙታን ናቸው፡፡ ይህን በወንጌል ቃል አምነው እጅ ለጌታ ቢሰጡና በእውነት አቤት ቢሉ እንደ ፈቃዱ ከመቃብር እሥራት ይፈታሉ፡፡ ግን ጉራ ተሞልተው አመቃብር ውስጥ በፊደል (ፍጥረታዊ)ጨለማ ሃሌ ሉያ!! ጌታ ይባረክ ካሉ ፍርዱ ተፈፅሟል፡፡

እነዚህ፣ ልብን የተገረዙ ከማንነታቸው ጨለማ ስውር መቃብር የወጡ ልበ ንፁሆች (እግዚአብሔርን የሚያዩና) ልብን ባለመገረዝ ከማንነታቸው ርኩስ





ጨለማ መቃብር ያልወጡ ውስጠ ሙታን ውጪ ሕያዋን ሆነው ይለያያሉ፡፡ የሙሴን መቃብር ማንም ያላየው ለምንድን ነው? የሙሴ መቃብር ቅዱስ ስለሆነ ከማንም የሰው ዓይን ተሰውሯል፡፡ የዚህ የማንነት መቀበር ዓይነት መቀበርም በወንጌል እውነት ሲታይ፣ አዲሱ የዳኑ ሰዎች የማይታየው ዘላለማዊ ማንነት በክብር እስኪገለጥ ድረስ በሚታየው በአሮጌው ማንነት መጋረጃ ጨለማ ተውጦ ሰጥሞ መኖር ማለት ነው፤ በሕይወት ሳሉ ወደ ሲዖል መውረድ፣ አሁን እግዚአብሔር በማይታይበት ጨለማ መኖር ነው፡፡ አሮጌው ማንነት በአዲሱ ማንነት፤ የሚሞተው ማንነት በማይሞተው ማንነት፣ ጊዜያዊው ማንነት በዘላለሙ ማንነት መሸፈን፣ መዋጥ ነበረበት፤ በዚህ ፋንታ አዲሱ ማንነት በአሮጌው ማንነት፤ የማይሞተው ማንነት በሚሞተው ማንነት፣ ዘላለማዊው ማንነት በጊዜያዊ ማንነት መዋጡ ነው ክስረቱ፡፡ እንዲሁም ኃጢአት ድል በመነሣት በጽድቅ ይዋጥ ዘንድ፣ የግብፅ ብዙ በትሮች በአንዱ በእስራኤል በትር ይዋጡ ዘንድ ነው፡፡ይህ የእውነት እውነቱ ነው፡፡ ይህ መቼ ነው? ቢባል፣ መልሱ አዲሱን ልደት ስናገኝ (አሁን) ነው፡፡ ሕይወትን የዋጠው ሞት፣ ተራውን በሕይወት እንዲዋጥ ነው (1ቆሮ.15፡53-54፣ 2ቆሮ.5፡4)፡፡ ሰው የውጭ ጊዜያዊ ሰውነትና የውስጥ ዘላለማዊ ሰውነት ባለቤት ነውና፡፡ በውጫዊው በጊዜያዊ ማንነት፣ ውስጣዊው ዘላለማዊው ማንነት (ሮሜ 7፡22፣ 2ቆሮ. 4፡16-18፣ ኤፌ. 3፡16፣ 1ጴጥ. 3፡3-4፣ መክ. 3፡11) ሰጥሞና ተረስቶ ጠፍቶን ኖረናል፡፡

አዳም ማለት የሁለቱ ፆታዎች የጋራ መጠሪያ መሆኑን እያስታወስን፣ (ዘፍ.5፡1-2) እንግዲህ አዳም ከገነት ወደ ውጭ ተጣለ ማለት (አዳሞቹ) ከነበሩበት ቦታ ንቅንቅ ሳይሉ ዓይናቸው (ብርሃናቸው) በጨለማ ሲዋጥ፣ የሩቁን ሳይሆን የቅርቡን የሚያይ ዕውር ዓይን ወደ ውጭ ወጣ ማለት ነው፡፡ ዓይን ወደ ውጭ ወጣና ወደ ነበረበት አልመለስ ማለቱ ነው የሰውን ልጅ ጠፉ የሚያሰኘው፡፡ በአዳም የውስጥ መበራታችን ጠፍቶ

ሲቀር፣ የውጪ መበራታችን በርቶ ቀርቷል፡፡ ሰው ማለትም በዋናነትም አሕዛብ ስለተለማመደበት፣ የውስጡን ጨለማ ዕውርነት፣ በሽታ፣ ሞት፣ መቃብር ሁሉ እንደጤና፣ እንደ ሕይወት ቆጠረ፤ በውጭ ካላየው አላውቅ፣ አላምን ብሎ ካደ፤ ከዚህ ጋር ይህን ለመካድ ከበሮ፣ መሰንቆ፣ በገና አዘጋጅቶ ምስጋና ደስታ፣ ሽለላ ቀረርቶ፣ ሠርግና ምላሽ አደረገ፤ ዝና አተረፈ፤ ላቀ፣ መጠቀ፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር የውስጡ እንዳለ ሆኖ መከራን በውጭ በእጥፍ ድርብ ደግሞ አመጣበት፡፡ በተጻፈው ታሪክ መሠረት የውጭ ናሙና የሚሆኑን የከለዳዊና ዑር ግብፅ ይሆናሉ፡፡ ትልቁ የእስራኤል ወላጅ የሆነው አብራም በዑር ከለዳውያን የተወለደው በወገኑ ከለዳዊ ነበር፡፡

እግዚአብሔር አብራምን ከዚያ ሲጠራው፣ በአዳም ከወጣበት ውጭ ጨለማ ወደ ውስጥ ወደ ኋላ ወደ እግዚአብሔር ፊት ሊመልሰው ነበር፡፡ ለዚህ ነው አብራም በናሙና ደረጃ የአዳማዊ ሥጋ ሰውነትን በስለት (በግዝረት) እንዲያስወግድና ወደ እግዚአብሔር ፊት ብርሃን እንዲወጣ የታዘዘው፡፡ እዚሁ-ጋ ነበር አብርሃም ከአሕዛብ የተቆራረጠው፡፡ ሰው፣ ከነቁርበቱ ሸፍንፍን ባለበት ከነቆለፈቱ ፍፁም ሊሆንና በፊቱ ሊመላለስ አይችልምና፡፡ አብርሃም የአሕዛባዊነቱን ቁርበት ከራሱ ላይ ገፍፎ ወደ ውጭ ስለጣለ ወደ ውስጥ መግባት ቻለ፤ (ዘፍ.17፡1-14፣ ቁ.23-27)፡፡ እግዚአብሔር አዳምን ከገነት አወጣው ሲባል፣ ከገነት የወጣው አዳም ሳይሆን ዓይኑ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ ማለት ወዴት ተሄዶ ነው የሚበራው? የልባችን ዓይኖች ሲበሩ ማለት መቼ የጨለሙት ሲበሩ ነው?

አብርሃም ቆርጦ የጣለው ቁርበት (ሸለፈት) ርኩሰትና ሞት የተባለ፣ (ቆላ.2፡13፣ ኢሳ.52፡1-2)፡፡ በአዳም የተከናነብነው የኃጢአት ዋጋ ነው፡፡ «እግዚአብሔር አምላክም ለአዳምና ለሚስቱ የቁርበትን ልብስ አደረገላቸው አለበሳቸውም»፤ (ዘፍ.3፡21)፣ «አዳምንም አስወጣው፣ ወደ



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡ ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16



ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍ በዔድን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ፡፡» (ዘረጋው) (ዘፍ.3፡24) የሚለው ነገሩ የነበልባል ሰይፍ ማለት እጅግ ስለታም ሰይፍ ማለት ነው፡፡ ሰይፉ ሰይገዘግዝ፣ ሳይታወቅ ቆርጦ የሚጥል ትእምረኛ ስለታም ስለሆነ ነው እሳት የተባለው፡፡ ሰይፉ እሳት መሆኑ በሌላ አንፃር ሲታይ ደግሞ መቀደሻ ማለት ነው፣ በእሳት ካለፈ ዘንድ ማንኛውም ነገር ቅዱስ ይሆናልና ነው፣ (ዘኁል.16፡35-38...) ይህም የእሳት ጥምቀትንም ያመለክታል፤ (ማቴ.3፡11)፡፡ አዳም በዚህ ነበልባል ሰይፍ ተጠምቆ ወደ ወጣበት መመለስ ይፈቀድለት ነበር፡፡ በገነት መግቢያ ምሥራቅ በር ላይ የተዘረጋው ነበልባል ሰይፍ አዳምና ዘሩ ሁሉ እንዲቆረጡበት (እንዲገረዙበት) ከለበሱት ቁርበት እንዲገፈፉበት ነበር፡፡ ሰይፉ፣ ነበልባል መምሰሉ ወደ ውጭ በወጣው በውሸተኛ ሰይጣናዊ ዓይን በርቀት ስለሚታይ ነበር (ነውም)፡ የሰይጣን ዓይን ማለት የሰው ዓይን ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ላይ የተዘጋጀ የሐሰት ምስክር ነው፡፡

የአሕዛብ እውነት እውነተኛው መቃብር ግን እነርሱ የማይረዱት የእውነት እውነተኛው ዘላለማዊ ማንነታቸው ከቀዳሚ ወላጆቸ ጋር በጊዜያዊ (ዕለታዊ) ቁርበት ውስጥ ተከትተው ከገነት በተወገደበት ዕለት የቀብሩ ሥነ-ሥርዓት የተፈጸመበት ተንቀሳቃሽ መቃብርነው።

አብርሃም በዘጠና ዘጠኝ ዓመት ዕድሜ ላይ ሸለፈቱን ተገፍፎ ወደ እግዚአብሔር ፊት ብርሃን እስከ ወጣበት ዕለት ድረስ በዚሁ በአዳማዊ መቃብር ውስጥ ነበር የቆየው፡፡ አብርሃም መጀመሪያ ባሕር ተብሎ በተጠራው (መዝ. 69፡1-2፣ ራዕይ 17፡1፣ ቁ.15፣ 20፡13) ዓለም ሕዝብ ውስጥ ሰጥሞ ከኖረበት ጥልቀት ውስጥ ከሰጠመበት የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቶ ነበር ወጣ ለማለት የሞከረው፤ እግዚአብሔርን የሚሰማ ከሞት ይነሣል፣ ከመቃብር ይወጣል፤ (ዮሐ.5፡25-29፣ ም. 11፡43-44)

የቀረው አሕዛብ አብርሃም ቆርጦ ከጣለው ሸለፈት (አዳም ቁርበት) ጋር በርቀት ከወንዙ ማዶ ከተገረዘው አብርሃም በጣም ሩቅ ጥልቀት ሰጥመው



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡ ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

*በመቃብር እየኖሩ ለአሕዛብ በተተወውና በተደጋጋሚ በተረገመ ዓለም በተወለደበት በውጩ ዕድሜ (ራዕይ 11፡1-2) ምንም ተስፋ ሳይጨብጥ፣ ከእስራኤልና ከተስፋው ርቀው ከወንዙ ማዶ በአውሬ እንስሳ ደረጃ ሞተው በውጭ የሚቀበሩት ዓለም የሚያውቀውና የሚያየው ግልጹ ቁሳዊ መቃብር ነው፡፡ በእስራኤል ደረጃ ሲታይም የአሕዛብ መቃብር ከነሸለፈቱ ቁርበት ስለ ተቀበረ መቃብሩም ጭምር ርኩስ ነው፡፡ የአሕዛብ መቃብር ቁርበትን በተከናነቡበት ጨለማ ዓለም ኖሮ ብርሃንን ሳያዩ በጨለማ ሞቶ ወደ ጨለማ የሚወርዱበት ከማህፀን ሳይወጣ ከእናቱም ጋር እንደ ሞተ ሽል የሚቆጠር የቀብር ሥነ-ሥርዓት ዓይነት ነው፡፡ እስራኤል በናሙና ደረጃ ቆለፈቱን የተገፈፈ በመሆኑ ወንድ ሁሉ በዓመት ሦስት ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ሊታይ ወደ ታላቅ ብርሃን ስለሚወጣ በእግዚአብሔር የታወቀ ሕዝብ ነው፤ (ዘፀ.23፡17፣ ም.28፡29) አሕዛብ ወደ እግዚአብሔር ፊትም ሳይወጣ ሳይታወቅም በውጩ ጨለማ የቀረ ሕዝብ ነው ከፉ የሚያደርግ ሁሉ ወደ ብርሃን አይመጣምና፡፡ ለምን ሴት ወደ እግዚአብሔር ፊት አይወጣም ነበር? ሴት፣ የሥጋ ሰውነት የሆነውን ቆለፈት በስለት ሊገፈፍ አይደፍርም? በአዲስ ኪዳን በዳግመኛ ልደት ማንም የሥጋን ሰውነት በመገፈፍ ወደ እግዚአብሔር ፊት ብርሃን ሊወጣ ይችላል፤ (ዮሐ.3፡3፣ ቆላ.2፡11-12)*

*እስራኤላዊነት ደግሞ ዘላለማዊነት ከመሆኑም ሕይወት ያለበት ስለ ሆነ እስከ ፍፃም ሙላት የሚያድግ ነው፡፡ ብሉይ ኪዳኑ ግልፁ ወደ አዲስ ኪዳኑ ሰውር እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ፊት በማደግ ነው ሐዋርያትን የተካው፡፡ እግዚአብሔር ዓለምን የሚያውቀውም በዚህ በእስራኤል ስም ብቻ ነው፤ በአዳም በኩል የተረገመው የምድር አሕዛብ ሁሉ በረከቱን የሚያገኘው በአብርሃምና በዘሩ በኩል ብቻ ነውና፤ (ዘፍ.12፡3፣ ም.28፡ 14)፡፡ እስራኤል ዘላለም ነው ማለት ደግሞ ሁሉን በሥሩ ጠቅልሎ ከክብር ወደ ክብር እየተለወጠ ያድጋል፣ አይቆምም ለማለት ነው፡፡ ይህም*



*በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፤ አፉ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡ ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፤ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16*



*ዘላለማዊነት በእስራኤል ከእስራኤል ስለሆነ ነው፡፡ የእስራኤል እድገትም ከውጭ ወደ ውስጥ፤ ከፊደል ወደ መንፈስ፣ ከሜዳ ወደ ጓዳ፣ ከሰው ፊት ወደ እግዚአብሔር ፊት፤ ከጨለማ ወደ ብርሃን ነው (በፎቶ-ትሮፒዝም)፣*

*የሚያድግ ነገር ሁሉ ከጨለማ ወደ ብርሃን {PHOTO-TROPISM} ነው እንጂ ከብርሃን ወደ ጨለማ {GEOTROPISM} አይደለምና፡፡ ስውሩ፣ የመንፈስ እስራኤል የእውነት እወነተኛ እስራኤልና ስውሩ የልቡና ግዝረት የእውነት እውነተኛ ግዝረት ሆኖ ቦታውን ስለሚይዝ፣ የፊደል ማለት ግልጹ እስራኤል ደግሞ በግልጽ ከሚታይ አካላዊ ግዝረቱና ሥርዓቱ ጋር በአዲሱ ኪዳን የሐሰት እውነተኛ ሆኖ ስፍራውን ለአዲሱ ትውልድ (ለቤተ ክርስቲያን) ለቅቆ ወደ ውጪው ጨለማ ተጥሏል፤ (ሮሜ 2፡28-29፣ ማቴ.8፡11-12) ግልጹ፣ የሰው ፊቱ ነገር እውነተኛ ሊሆንም፣ ቅዱስ ሊሆንም አይችልም፡፡ በዚሁ አንፃር፣ በግልጥ በአካል የሚታየው የእስራኤል ምድርም፣ የእስራኤል መቃብርም፣ በግልጽ የሚታየው የአካል ትንሣኤም ውጫዊ፣ ሜዳዊ ሆኖ በስውሩ በመንፈሳዊው ትንሣኤ ተተክቷል፡፡*

*መቃብር በእስራኤል፤*

*እስራኤል ልደቱን ከግብፅ/ከዓለም አግኝቶ አሮጌውን ዓለምና አሮጌውን እትብት እየቆረጠ፣ አሮጌውን ትውልድ እየሻረና እየጣለ በረጅም የጉዞ እድገት ከነዓን መግባቱን እናስታውሳለን፤ (ዘፀ.12፡1-2፣ መዝ.80፡8-13) በእስራኤል፣ ይህ ወር፣ የዓመቱ መጀመሪያ ወር ሆኖ ነው የተቆጠረው፡፡ ከግብፅ ወጡ ማለት በኩርን ቀብረው ከአንደኛው መቃብራቸው ወጡ ማለት ነው፡፡ ሁለተኛው መቃብር ከወንዙ መውጣት፣ ሦስተኛው በምድረ-በዳ አባቶቻቸውን መቅበር፣ አራተኛው ከዮርዳኖስ ድንጋይን ቀብረው መውጣት፣ አምስተኛው በከፍታ ላይ ከማንነታቸው መቆራረጥ፡፡ ይህ በአዲስ ልደት የንስሓ ጉዞ እድገትን አመልካች ነው፡፡ ሰው በሃይማኖቱ*



*በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፤ አፉ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡ ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፤ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16*

እስከ ሙላቱ ልክ እስኪደርስ ድረስ የማያድግ ከሆነ ሕይወት የሌለው ሃይማኖት መባል አለበት፡፡ (ሕይወት ያለው ነገር ያድጋል፣ ይራባል፣ ያረጃል፣ ሌላውን ተክቶ ይሞታል፡፡) ሕይወት በውጭ እንደ ሆነ እንዲሁ በውስጥም ነውና እድገት በውጭ እንደ ሆነ እንዲሁ በውስጥም መሆን እንዳለበት እንዳይዘነጋ ነው፡፡ ውጫዊ ዕድገት የጨለማ ዕድገት ሲሆን፣ ዕድገት ሆኖ አይቆጠርም፤ ውስጣዊው መንፈሳዊ ስለሆነ በብረሃን ነውና ዕድገት ነው፡፡

ክርስቶስ ወደ ዓለም በመምጣቱ ምክንያት እግሩ ላይ የተጣበቀውን ትቢያ (ዕድፍ፣) ወንድ ሁሉ በስምንተኛው ቀን ይገረዝ የተባለውን በመፈፀም በስምንተኛው ቀን (እሁድ) አረግፏል፤ ይህ ዳግመኛ ልደቱ ነውና፡፡ (ግልፅ አይደለም) ዳግመኛ ልደት ከሞት መቃብር ማፈትለክ {BURSTOUT} ነው፤ ...ከሙታን በኩር ... (ራዕይ 1፡4-5፣ 1ቆሮ.15፡20፣ ማቴ. 19፡28፣) እስራኤል በሚያድግ ጉዞ ሥርዓት፣ ከግብፅ የተጣበቀባቸው እትብቱና ሸለፈቱ በግብፃውያን ምስክር እንዲሆን ከዚያ የተጣበቀ ትቢያ (ዘዐ.8፡26፣ ርኩሰት ነውና በግብፅ መራገፍ አለበትና፡፡ ከማር.6፡10-11፣ ከሉቃስ 9፡4-5) ጋር ይመሳከር፡፡ ይህ ማለት ለግብፃውያን ስድብ፣ ማርከስ ከመሆኑም ፍርድ ነበረ፡፡ ይህን ርኩሰት አራግፈው ከወጡ በኋላ ወደ ግብፅ ወይም ወደ ዓለም ቢመለሱ ያራገፉትን ትቢያ፣ የርኩሰቱን ሸለፈት በትንሣኤ ከመቃብር አውጥተው መልሰው ይጎናፀፉታል። ገና በሩቅ እነርሱን ሲያይ የተራገፈው ትቢያ፣ ተቆርጦ የተጣለው የርኩሰቱ ሸለፈት፤ አሮጌው ማንነት በሰባት እጥፍ ሰባት አጋንንት ሆኖ ከመቃብር ተነሥቶ ከተለያየን ብዙ ጊዜ ሆኗል፤ እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ዘልሎ ተነሥቶ አቅፎ በመሳም ይጠመጠማችዋል፤ ይጠመጠምብናልና ከዚያ በኋላ ከፊተኛው እጅግ የከፋ ሕይወት ውስጥ እንሰጠማለን፤ (ማቴ. 12፡43-45፤ ሉቃስ 11፡24-26) የመስከር፡፡





አብራም የከለዳዊነቱን ርኩሰት (ትፋት) ተሸክሞ ሲጓዝ መጥቶ በሰባ አምስት ዓት ዕድሜው በካራን አንድ ብሎ ቀበረ፤ (ዘፍ.11፡32)፡፡ ከዚያ እየተጓዘ ቆይቶ ይህን አስፀያፊና ወደ እግዚአብሔር ፊት እንዳይወጣ እፍረትና ርኩሰት ሆኖ በውጭ ያቆየውን ሸለፈት በመቶ ዓመት አፋፍ ላይ ደረሰና በስለት ቆርጦት ወደ ውጭ ጣለውና እርሱ ሸሽቶ አምልጦ ወደ እግዚአብሔር ፊት ብርሃን ገባ፡፡ ያ ተከትሎ ወደ ብርሃን እንደይመጣ እፍረት ስለሆነ እንደ አንተና እኔ ብርሃንን እንደ ጦር ይፈራልና ከስለቱ ማዶ አብርሃም ወዲህ ማዶ የተያየሉ ሦስተኛውን 175 ዓት ዕድሜ ድረስ ተሸክሞት ሲዞር ቆይቶ እስኪቀብረው (ዘፈ.25፡7-8) ድረስ ይህ የ(ዘፍ.17፡23-27) ሁለተኛው ነበረ፡፡ ውሸታም እኔንና አስመሳይ እናንተን ብርሃንን (እግዚአብሔርን) እንዳናይ አድርጎ እስካሁን በውጪ ጨለማ ሲያል ያቆየውን እንዳንዋሸና ኀጢአትም እንደይደረብብን አንካድና ተቃቅፈን የምንኖረው እስከ መቼ ነው? እንጠያየቅ፡፡ በራስ ላይ መፍረድ በገዛ-ማንነት ላይ የጌታን ሰይፍ መምዘዝ በባላጋራው ላይና በዓለም ሸለፈት ሁሉ ላይ በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ ተቀምጦ ፈራጅ ዳኛ መሆን ከንዳችንን አስቀድሞ በራሳችን ላይ እናንግሣ፡፡የራስ አካል መስሎ ከዓለም የተጣበቀብንን ርኩሰት የሆነ አሮጌ ማንነት ቆርጦ ውጭ መጣል ዓለማዊነትን ቆርጦ ወደ ውጭ መጣል ለዓለማውያን ስድብ፣ የሞትና የመቀበር ፍርድ ይሆንባቸዋልና፡፡ ዓለምን ላለመምሰል የምንወስደው እርምጃ መልካቸውንና ክብራቸውን መገፈፍ ልብሳቸውን አውልቆ መጣል ነው፤ ከእግራችን ትቢያቸውን ማራገፍ፡፡

በግብፅ የተቀበረ እስራኤል ሁሉ ሳይቀደስ፣ ቆርጦ ከጣለው እርኩሰት ሳይርቅ ተመልሶ እዚያው፣ ርኩሰቱ በተቀበረበት ሞቶ እግዚአብሔር እስካለበት ሳይደርስ የተቀበረ ስለሆነ የፍርደ እንጂ የሕይወት ትንሣኤ ዕድል አለው ወይ? (ዕብ. 6፡4-8፤ ም.10፡28-29) እኛም ቆርጠን የጣልን እያስመሰልን እዚያው ከዓለማውያን እርኩሰት ጋር ተመልሰን ተጋብተን

የምንኖር እዚያው ሞተን ስንቀበር የትንሣኤ ዕድል አለን ወይ? የእኛ ዕድልማ ባለቀ ዘመን ላይ በመሆኑ አሁን፣ ከውጭ ሳይሆን ከውስጥ፣ በፊደል ሳይሆን በመንፈስ አሁን፡ አሁን ነው፤ (ዮሐ.5፡25-29፣ 2ቆሮ. 6፡ 2)፤ መጽሐፌን ከተቹት አንዱ፣ በውይይት መልክ ስንነጋገር በምድረበዳ የተቀበሩት እስራኤሎችም ይድናሉ ብሏል፤ እኔ አሜን ያድርገውና ብዬው ነበር፡፡ አሁን ግን ሐሳቡ የእግዚአብሔርን ባሕሪይ ከመንፈሳዊ ጉዞ ጋር ኣላገናዘበም፤ እስራኤል ወደ ተስፋ ምድር ሲጓዝ፣ የጉዞው ዕንቅፋት የሆኑ የሥጋ ሐሳብና ኃጢአት «ክፉውን ከመካከላችሁ አስወግዱ›› ተብሎ በታዘዘው መሠረት በጉዞአቸው ላይ ክፉ የተባለውን ኃጢአትን፣ (አመፅን) እየቀበሩ የተጓዙ፣ እኛ በክርስትና ጉዞአችን አደናቃፊ የሆኑ ከመካከላችን በየእርምጃችን እየቀበርን እንድንጓዝ የሚያስተምር እንጂ የተቀበረው አመፅ፣ ክፉትና ኃጢአት ይድናል ብሎ ማስተማር ስህተት ነው፤ እያልኩ፣ እስራኤል የቀበሩአቸው እስራኤልን ሳይሆን አመፅን ክፉውን እንጂ እስራኤልን አይደለም እላለሁ፡፡

የያዕቆብ ሥጋ፣ የዮሴፍ አጥንት በግብፅ ያልተቀበረው ለምንድን ነው? ያዕቆብ ተስፋ ከሌለባት ምድር ወደ ተስፋይቱ አገር አስከሬኔን ያደርስልኛል የሚል እምነቱን በዮሴፍ ላይ ጥሎ እምነትንና ተስፋን ተሞልቶ እንደ ሞተ፣ ዮሴፍም እንዲሁ ከግብፅ ሲወጡ አጥንቱን ይዘው እንደሚወጡ እምነቱንና ተስፋውን በወንድሞቹ ላይ ጭኖ በተስፋ እንዳንቀላፋ፡፡ ትንሣኤ ፈላጊ ማንም ሰው ሞቶ እንደ ያዕቆብና ዮሴፍ በሰው ትከሻ፣ አለዚያም እንደ ካሌብና ኢያሱ በሕይወቱ፣ በራሱ እግር ወደ እስራኤል አገር ገብቶ ካልተቀበረ በቀር በግብፅ (በዓለም) የትንሣኤ ዕድል ለማንም የለውም፡፡ ትንሣኤ የሚገኘው በአባቶች፣ በአብርሃም፣ ይስሐቅ ያዕቆብ መቃብር፣ በእናቶች፣ በሣራ፣ ርብቃ፣ ልያ መቃብር ሲቀበሩ ነው፤ (ዘፍ.47፡29-31፣ ም. 49፡29-33፣ ም.50፡25፣ ዘፀ.13፡19፣ ኢያሱ24፡32፣ ከ1ነገ.13፡22) ጋር ይመሳከር፡፡







ከነዓን ለእስራኤል እግዚአብሔር በተስፋ የሰጣቸውና ራሱ እግዚአብሔር በመካከላቸው የምያድርበት በመሆን የእግዚአብሔር መንግሥት መንፀባረቅ ከመሆኑም ሊመጣ ያለው ክርስቶስም ሊመጣ ያለው ወደ ከነዓን በመሆኑም ጭምር ያዕቆብ ልጁ ከግብፅ ተወሰዱ፡፡ እንግዲህ ልብ ልትለው የሚገባህ በል፣ የእግርህን ትቢያ ባራገፍህበት፤ ሽለፈትህን ቆርጠህ በጣልህበት ተመልሰህ እንዳትኖር የሚፈለግ መሆኑን ነው፡፡ አሕዛብ ከነሽለፈቱ ጥምብ ጋር እንደ ተሸፋፈነ ሳይገፈፍ በተወለደበት ሞቶ ይቀራል፡፡ ያዕቆብን በግብፅ አለመቅበራቸውና የዮሴፍን አጥንት ተሸክመው መሄዳቸው ለዓለም ሁሉ ታላቅ ምልክትና ከፍ ያለ ፍርድ ነበረ፡፡

ይህ በውጪ ዓይን የምናየው ምሳሌ ውስጣውያን ለሆንን ለእኛ ጥሩ ትምህርትና መመሪያ ነው፡፡ ከነዓን መግባት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የመግባት ውጫዊ ገጽ ነው፡፡ የሰው ዓይን ያየው፡፡ እዚያ ሞቶ መቀበር ለአዲስ ኪዳኖች ፊደል (ውጭ) ቢሆንም በጊዜው በጌታ ፊት የማረፍ፣ በጌታ እጅ የማንቀላፋት ምሳሌ ሆኖ መንግሥቱን ለመውረስ ለተጠራነው ለታናሹ መንጋ ትክክለኛ መመሪያና መንፀባረቅ፣ ዱካም ነው፡፡ የብሉይ ኪዳኑ (ታላቁ መንጋ) ከባቢሎን (ከግብፅ) ጀምሮ ያደረጉት ልፋትና ጉዞ መሥዋዕትነት ሁሉ መጥቶ- መጥቶ ወደ ቤት ሳያስገባቸው በውጫዊ ሥርዓትና በውጫዊ ጽድቅ በሰው ፊት እያኩራራቸው በሜዳ አስቀራቸው፡፡ እራሳቸውን ሳይሆን ታናሹን መንጋ ሸኝተው በውጭ ቀሩ፡፡ ለምሳሌ፤ ታናሹ ልጅ ከሙታን ሲነሣ፣ ከጠፋበት ሲገኝ፣ ታላቁ እንደ ባሪያ ሲለፋ ኖሮ ያከማቸውን ሀብት ሁሉ ለታናሹ አስረክቦ ተግባሩንና መሥዋዕትነቱን በድምፅ ማጉያ እያወጀና ሞቶ የተነሣውን ወንድሙን እየኮነነ ተኩራራ፣ ከታናሹ ጋር አብሮ መውረስን ተፀየፈ፣ "የእኔ የሆነው ሁሉ ያንተ ነው"፣ ቢባልም አልተቀበለም፤ የአባት ሃብት የሆነ ሁሉ እርሱ በፈረጠጠበት በውጪ ጨለማ ሳይሆን በውስጡ

ብርሃን ነው። የጸሎተኛውን ፈሪሳዊ ምሳሌነት ተከተለ፤ (ሉቃስ 15፡11-32፣ ም.18፡9-13) ይመሰክር። ከዚህ የምንማረው፣ ገዳይ ከሆነው ሜዳዊ፣ ድርጊታዊ ከሆነ ሃይማኖታዊ፣ ተግባራዊ ሥርዓት ልቡናችንን ባዶ አድርገን በስውር በሚያየው አባት ፊት በተሰበረ ልብ ብቻ እንድንወድቅ ነው ቃሉ ለኛ የሚለግሳት ምክሩ (ማቴ. 6፡1-18)።

በገለጸ ደረጃ እስራኤል ማለትም ወንዝ የተሻገረ (በውኃ ያለፈ) የታጠበ፣ ከቀለፈቱ የወጣ፣ (ከክንብንቡ) የተጋለጠ፣ ስንል ኃጢአቱን ያጋለጠ፣ ወደ እግዚአብሔር ፊት የወጣ፣ ንስሐ የገባ ሰው ምሳሌ ነው። ስለሆነም እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ፊት ብርሃን የወጣ ሕዝብ በመሆኑ በቅዱስ ዓለም በተስፋ ኖሮ በተስፋ ተኝቶ ያንቀላፋል፤ የእነርሱ ሞት ሳይሆን እንቅልፍ ነው፤ (ዘፍ.47፡30፣ 1ነገ.2፡10፣ መዝ.16፡9፣ ማቴ.9፡23፣ ዮሐ.11፡11፣ ሐሥ.7፡60)። ከዚህም ሌላ፣ አብርሃም ነፍሱን በፈቃዱ ሰጠ፣ ይስሐቅ ነፍሱን በፈቃዱ ሰጠ፣ ያዕቆብም፣ በፈቃዱ እጁንና እግሩን ሰብስቦ ሞተ፤ ኢየሱስ ነፍሱን በፈቃዱ ከማስረከቡ ጋር ሁለመናውን ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠቱ በስፋት ታይቷል። (ዘፍ.25፡7-8፣ ም.35፡28-29፣ ም.49፡33 ማር. 15፡39፣ ማቴ. 27፡50) ያንቀላፋ ስለሆነም በተነካ፣ በተቀሰቀሰና በተጠራ ጊዜ ሁሉ ከመቃብሩ ይነቃል። (1ሳሙ.28፡11-19፣ 2ነገ.13፡20-21፣ ዮሐ.11፡43)። እኛም ሕይወታችንን በፈቃዳችን ለእግዚአብሔር ሳንሰጥ ቀርቶ ሌላው ኃይል ቀጥቅጦ ከወሰዳት ከሥረናል። እስራኤል ከተቀበረ በኋላም እንዳይረክስና በስብሶ እንዳይቀር ብስብሱን ቆዳ አስቀድሞ በፈቃዱ እንደ ተገፈፈና እንደቀበረው (ከሬዲት) ስለሚያዝላቸው አፈር ሆነው የሚቀሩ ሳይሆን ከተቀበሩ በኋላ የምድርን መንገድ ሁሉ የሚጓዙም ናቸው፣ (1ነገ.2፡2)

የእስራኤል መቃብር በቀድሞ ኪዳን በመካከለኛው ምሥራቅ የሆነው አሁን ልብን በሚገረዙበት በአዲሱ ኪዳን የት ነው? በኢየሱ ስለታም ድንጋይ ከቆለፈታሙ ሥጋ የተደረገው ግዝረት የአሁኑን የልብ ግዝረትን



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፣ ኢሳ.34፡16



አመልካች ነበር። በአጭር ቃል አሁን ሞታችንና መቀበራችን ከውጭ ማለት ከግብፅ (ከዓለም) ወደ ውስጥ ተጉዘን፣ ከሸለፈቱ በተገረዘው በየራሳችን ማዕከል ባለ ስውር መቃብር ከአብርሃም፣ ከይስሐቅም፣ ከያዕቆብም ከሚሻለው ከጌታ ኢየሱስ ጋር በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም፣ በቅድስቲቱ ከተማ ነው፤ ትንሣኤያችንም፣ ሕይወታችንም፣ ውርሳችንም ከኢየሱስ ጋር ነው፤ (ሮሜ 8፡17)፣ የዚህ ማረጋገጫ ከእርሱ ጋር መሞታችን ነው፤ (2ጢሞ.2፡12) ደግሞ እንደተጻፈ፣ «ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን» (ሮሜ 6፡2-4)፤ ... በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀበራችሁ፤ በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ባሥነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ፣ (ቆላ.2፡11-12፣ ቁ.12) በእርሱ ተሰወርን ማለቱ የአዲስ ኪዳኑ እውነት ነው።

በአዲስ ኪዳን እስራኤል አገር ገብቶ ለመቀበር አባቱን ወስዶ ከቀበረው ከዮሴፍ የተሻለ፣ የዮሴፍን አጥንት ተሸክሞ ከወጣው ከሙሴ የተሻለ በከንቱ እስከ ከነዓን (አዲሲቱ ኢየሩሳሌም) የሚያደርሰን፣ በትከሻው ተሸክሞ ወደ ቤቱ የሚያደርሰን ታላቅ ኃይል፣ ቸር አባት አለን፣ (ዘፀ.19፡4፣ ኢሳ.46፡3-4፣ ራዕይ 12፡14፣ ሉቃስ 15፡5-7)። የብሉይ ኪዳን እስራኤል ምሳሌ ወደ ሆነችው ምድራዊቱ ኢየሩሳሌም የተጓዘው በሙሴ ትከሻ ሲሆን፣ (ዘኁ.11፡11-14) የሙሴ ትከሻ ከምድራዊቱ ከነዓን አላሳለፈም። የኢየሱስ ትከሻ ግን እውነት እውነተኛዪቱ ወደ ሆነችው ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም የሚያደርስ ትከሻ ነው። በታላቁ ንሥር ክንፍ፤ (ዘፀ.19፡4፣ ራዕይ 12፡14) ከአብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ ጋር በምድራዊቱ ኢየሩሳሌም ከተቀበረው ከፊተኛው፣ (ከታላቁ መንጋ) ይልቅ ከአብ፣



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፣ ኢሳ.34፡16

ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ጋር በሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም የሚቀበረው ታናሹ መንጋ የላቀ ዕድለኛ ነው፣ ከአብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ጋር መቀበር እንዴት ነው? ለሚለው፣ መልሱ ከኢየሱስ ጋር መቀበር፣ ከአብ፣ ወልድ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መቀበር ነው፣ የሚለው ይሆናል፡፡ (ዮሐ.10፡30) ይህ በማየት የሚደረግ ሳይሆን በእምነት የሚፈጸም ነው፡፡ በማየት አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ በእምነት የአብ፣ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ናቸው፡፡ የብሉይ ኪዳን ኢየሩሳሌም፣ ምድራዊቱ፣ የአዲስ ኪዳን ኢየሩሳሌም የሰማያዊቱ ምሳሌ ናት፤ (ዕብ.12፡22፣ ራዕይ 3፡12)፣ አሮጌዋ በማየት፣ አዲሲቱ ቅድስቲቱ ስለሆነች በእምነት ትታያለች፡የብሉይ ኪዳን ነገር ሁሉ ምሳሌና ጥላ፣ የጨለማ ሥራ በመሆኑ ከአዲስ ኪዳን ፊት ሥፍራውን ለቆ በንኖ ይጠፋል፤ (ሮሜ 13፡12/ለ፣ ኤፌ.5፡11-13፣ ራዕ.20፡11)፡፡

የእስራኤል አገር የሞትና የትንሣኤያቸው ልዩነት፤

‹‹ልዩነት›› ማለት ቅዱስነት ማለት ነው፡፡ የእስራኤል አገር እግዚአብሔር ከዓመቱ መጀመሪያ እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ዓይኑ በእርሷ ላይ ሆኖ ጉብኝቱ፣ ቁጥጥሩ የማይለያት (ዘዳ.11፡10-12) ከመሆኑም እርሱ እግዚአብሔር በመካከልዋ የሚያድርባትና፣ (ዘኍ.35፡33-34)፤ በመካከላቸው ያድር ዘንድ ከእስራኤል ጋር ከግብፅ ወጥቶና አውጥቶአቸው መጥቶ የገባባት፣ (ዘፀ.29፡45-46) አገር ናት፡፡ ቀደም ሲልም ከእስራኤል ጋር ወደ ግብፅ ወርዷል፤ (ዘፍ.46፡1-4) የእግዚአብሔር ዓይን የእግዚአብሔር ብርሃን በዚህች በእስራኤል አገር ላይ ነው ማለትም የእግዚአብሔር እረኝነት የማይለያት በአስተዳደሩ ሥር የምትገኝ የእግዚአብሔር መንግሥት ክልል የሆነች ምድር ናት ማለት ነው፡፡ የዚህ እውነታ ምንድን ነው? ለሚለው ከዘፍጥረት (ዘፍ.3፡7-8) ስንመለከት፣ ... እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምፅ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ፤ (ይልና) አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሔር ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ፣ ይላል፡፡





የጌታ ሥጋ መድረሻና ምንነቱ፣

ይህ አመለካከት ከፍ ብሎ ካየነው፣ (ዘዳ.11፡10-12) የእግዚአብሔር ጉብኝት ከማይለያት አገር ጋር አንድ አገር ሆና ይህች እስራኤል የገባባት አገር በአዳም የወጣንባትን ገነት ታንፀባርቃለች፡፡ አዳም ወጣባት፣ እስራኤል ገባባት (ዘፍ.3፡10፣ ኢያሱ 5፡10-12)ን እናመሳክር፡፡ አዳም ስላልተገረዘ ነበልባል ሰለት ፈርቶ ከነዘሩ እስካሁን በውጭ ቀረ፤ አንተም ፈርተህ በውጭ ነህ ወይ?

በእኛ በአዲሱ ኪዳን ውጭን ሳይሆን፣ ውስጥን በተገረዙት እንዴት ነው? እስራኤል በሐሰት እውነት ውጭን የተገረዙ ስለሆነ የሐሰት እውነተኛ የሆነውን ውጫዊውን ገነት (ከነዓንን) በውጫዊ ጦር ዕቃ ተዋግተው (2ቆሮ.10፡3-4) የሚታየውን የጊዜውን፣ (2ቆሮ.4፡18) ወረሱ፡፡ የአዲስ ኪዳን እሥራኤል ግን በእውነት እውነተኛ ግዝረት ውስጥን የተገረዙ የእውነት እውነተኛ የእግዚአብሔር እስራኤል (አዲሱ ፍጥረት) በመሆን፣ እግዚአብሔር ራሱ የፈጠረውን አዲስ ሰማይንና አዲሱን ምድር (አዲሲቱን ኢየሩሳሌም) ይወርሳሉ አሁን ውጫዊ እስራኤል፣ እስራኤል አይደለም (ሮሜ 2፡28-29)፡፡ ይህን ወደ ፊት በሚወጣው ታላቁ መጋረጃ («ሰማይና ምድር ወለልና ጣራው...» በተባለ መጽሐፌ ያገኙታል)፡፡ ስለዚህ ነቢዩ ኢሳይያስ ሲናገር፣ «ጽዮን ሆይ፣ ተነሺ፤ ተነሺ፤ ኃይልሽን ልበሺ፣ ቅድስቲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ያልተገረዘና ርኩስ ከእንግዲህ አይገባብሽምና ጌጠኛ ልብስሽን ልበሺ፤ ኢየሩሳሌም ሆይ ትቢያሽን አራግፊ፤ ተነሺ፣ ተቀመጪ ምርኮኛዪቱ የፅዮን ልጅ ሆይ፣ የአንገትሽን እሥራት ፍቺ፡፡» (ኢሳ.52፡1-2) ይላል፡፡

አሁን በአዲሱ ኪዳን ውጫዊ ኢየሩሳሌም ከነሕጉና ሥርዓቱ ለአሕዛብ ወደ ውጪው ጨለማ የተተወ (ራዕይ 11፡1-2) አሮጌው ዓለም በመሆኑ፣ በአሮጌው፣ በውጫዊው ኢየሩሳሌም የተቀበሩም አሮጌ ውጫውያን ግዝረተኞች ትንሣኤ የላቸውም፡፡ ክርስቶስ ማለት ራሱ የተቀደሰውና ከፍ ያለው የእስራኤል ተራራ ነው፤ መሰላል (ኢሳ.57፡13/ለ፣ ሕዝ.20፡40፣



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፉ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፣
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

2ጴጠ.1፡18) ይህ ተራራ በራዕይ 21፡10-11) የምትታየው ታላቅና ረጅም ተራራ የተባለችው፣ ቅድስቲቱ ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ናት፡፡

የማያድግ እስራኤል፣ እስራኤል አይደለም፣ ሕይወትም የለውም (በተወለደበት የቀረ)፡፡ እስራኤል ወደ ውስጥ፣ በስውር ወደሚያይ ወደ እግዚአብሔር ብርሃን ያድጋል፤ ወደ ውስጥ ወደ ጌታ ብርሃን የማያድግ ሁሉ ወደ ሰው ፊት ወደ ጨለማ በሰው ለመታየት ያድጋል፡፡ ክርስቶስ ያድጋል (ሉቃስ 2፡52)፡፡ ነገር ግን ይህ በውስጣችን የፀነስነው የማያድግ ነገር ከሆነ እርሱ በድን ነገር እንጂ ክርስቶስ አይመስለኝም፡፡ ...ክርስቶስ ግን ሕያው ድንጋይ ነው (1ኛ ጴጥ.2፡4-6፣ ኢሳ.28፡16)፡፡ እርሱ አዲስ የፈጠረውን ሕዝብ፣ አዲስ ከፈጠረው ኢየሩሳሌም ጋር ይዞ በእድገት ከፍ፣ ከፍ እያለና ሁሉን ወደራሱ እየሳበ ሄዷል፣ መጥቷል፤ (ኢሳ 65፡17-18፣ ኤፌ 2፡10፣ 2ቆሮ 5፡17፤ ዮሐ 12፡32) ምን ትፈልጋላችሁ እዚህ የለም (ሉቃ.24፡5)፡፡ ወገኖቼ ሆይ፣ እርሱ እዚህ የለም ተነሥቷል፣ በተኛበት፣ ባንቀላፋበት ዘመናትን አይፈጅምኮ!

ስለሆነም እስራኤል ከክርስቶስ ጋር በእድገት ከክብር ወደ ክብር ከፍ እያለ መውጣት ነበረበት፡፡ አሁን እርሱ ቀዳሚውን እስራኤል ከቀዳሚው ኢየሩሳሌም መቃብር ትንሣኤ ሊሰጥ ቃርሚያውን ለመልቀም ወደ ኋላ ደግሞ እንዳይመለስ ሕጉ ይከለክላል፤ (ዘሌ19፡9-10፣ ም. 23፡22፣ ሩት 2፡ 15-16) ሕጉም ራሱ ነውና፡፡ አዲሲቱ ኢየሩሳሌምም ትንሣኤና ሕይወት የሆነው ክርስቶስም ከክርስቶስ ጋር በእድገት ከፍ እያለ ወደ ላይ ወጥቶ የሕይወት መውጫ በሆነው ልባችን ውስጥ በመቅደሱ ይኖራል፤ (ምሳሌ 4፡23፣ 2ቆሮ. 6፡16፣ ራዕይ 21፡1-5)፡፡

አሁን እንግዲህ፣ በዳግመኛ ልደት ሊወገድ ካለው፣ ቆለፈቱ ግርዶሽ የተነሣ ገና ግልጽ ባትሆንም የአዲሲቷ እስራኤል አገር አዲሲቱ ኢየሩሳሌም በውስጣችን የተሰወረችው የእግዚአብሔር መንግሥት ናት፤





(ሉቃስ 17፡20-21) ከዓይናችን መሠወሯ ከቅድስናዋ የተነሣ ነው፤ ያልተገረዘ ቆላፍ በመጋረጃ የተሸፈነ ስለሆነ በዳግም ልደት መጋረጃው እስኪገፈፍለት ድረስ አያያትም፤ (ዮሐ.3፡3)፡፡ ሐዋርያው ዮሐንስ ማየት የቻለው ጠቅላላው መጋረጃ ስለተወገደለት ነበር፤ (ራዕይ 21፡1) አብራሃም ከቆለፈቱ እንዲወጣ (ዘፍ 17፡1-14) የታዘዘውም ይህችን ምድር ማየት ይችል ዘንድ ነበር፤ «እኔ ወደ ማሳይህ ምድር ውጣ» (ዘፍ.12፡1) ‹‹ውጣ›› የሚለው ቃልም በቆለፈቱ ጨለማ ጥልቀት (ውስጥ) ገና ሰጥሞ ስለነበረ ነው፤ ከራስህ ውስጥ ውጣ ነው፡፡ ወደፊት በሚወጣው መጽሐፌ ከራስ መውጣት እንዴት እንደሆነ በበቂ ተብራርቷል፡፡ ቀዳሚው እስራኤል በውጫዊ ኪዳን፣ ከማንነት በውጭ የሆነ፣ ውጫዊ ግዝረትን የተቀበለ ሕዝብ ስለ ነበረ ውጫዊን ምድር (የሚታየውን የጊዜውን) (2ቆሮ 4፡18) ወረሰ፤ የአዲስ ኪዳኑ እስራኤል ግን በውስጣዊ ኪዳን በውስጣዊ ልቡና ግዝረት ውስጣዊውን የማይታየውን፣ ማለት ዘላለማዊውን እርስት ለመውረስ አዲስ የተጠራን ታናሽ መንጋ ነን፡፡ ጥሪውም «አንተ ታናሽ መንጋ መንግሥትን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነውና አትፍሩ»፤ ....(ሉቃስ 12፡32)፡፡

በመልእክቴ ዋናው ነጥብ የሆነው ሐሳብ ከጨለማ ጋር ያለ ትንቅንቅ ነው፡፡ ሰይጣን ሁልጊዜ፣ ባለማቋረጥ ውጭ ጀርባ፣ ጨለማ ገጽ በማሳየት የአዳምን ልጆች ሁሉ ዓይን እንድናጣ እያደረገ ይኖራል፡፡ እግዚአብሔር ሁልጊዜም የነገርን ሁሉ ውስጣዊ፣ ብርሃን ገጽን በማሳየት ነው ዕውርነትን የሚገፍፈው፡፡ አዳምን ጀምሮ፣ እግዚአብሔር ለአዳም ሞትን ትሞታለህ ሲል ውስጥን አስመልክቶ ሲሆን፣ ሰይጣን ግን ሞትን አትሞቱም ሲል የነገርን ውጭ ጀርባ ገጽ አስመልክቶ ነው የአዳምን እይታ ያሳጠረው፡፡ አብርሃምን እግዚአብሔር ከአገርህ፣ ከዘመድህ፣ ከአበትህ ቤት እኔ ወደ ማሳይህ ምድር ውጣ ሲል እንኳር መልእክቱ በውጭ አካል ውጣ ሳይሆን በውስጥ ሰውነትህ ከራስህ ውጣ ነበር (እግዚአብሔር የሚያየውና

የሚያሳየው ምድር) በወስጣችን ተሰውሯል፤ እግዚአብሔር ከሰው በተቃራኒ ያያል እንጂ እንደ እኛ አያይም፡፡ ሰው የእግዚአብሔርን ጥሪ መረዳት የሚችለውና ብርሃንን ማየት የሚችለው በውጫዊ አካሉ ከአገሩ ሲወጣ ሳይሆን ከአሮጌ አካሉ ከራሱ ሲወጣ ብቻ ነው፡፡ ሰው ከገዛ-ራሱ ሳይወጣ ከምን፣ ምን ቢወጣም እግዚአብሔር የሚያሳየውን ምድር ማየት አይችልም፡፡ ተገረዝ ማለት ከገዛ-ራስህ ቁርበት ውስጥ ውጣ ማለት ነው፡፡

ምሳሌያዊው እስራኤል ይህን (የእግዚአብሔርን ምሳሌያዊ መንግሥት) ለመውረስ ወረድ ብሎ በተዘረዘረው ዓይነት በውጭ አምስት ዙር የሞትን ወንዝ (ጥምቀት) መሻገሩ ይታያል፡፡ ሞት የሆነውን ግብፃዊነትን ሕይወት ተሸክሞ ወደ እግዚአብሔር ሕይወት መሻገር የማይሆን ነውና፡፡

አምስት ዙሩ የእስራኤል ሞትና መቀበር

አንድኛ፣ በጫንቃቸው ላይ ተጭኖ የኖረው ግብፃዊው በኩር (ታላቅ) ከላያቸው ላይ ተንከባሎ መቀበር፡፡ እስራኤል ሲባል እስራኤል የምንለው ሳይሆን በውስጣቸው የተሸነጠውን ከመጋረጃ በስቲያ ያለውን እስራኤልን ያመለክታል፡፡ እግዚአብሔር ከእስራኤል እስራኤል እንዲወጣ እንጂ የተባለውን እስራኤል አይፈልግም፡፡ እንዲህ ሲባልም እግዚአብሔር የሚፈልገው እስራኤል ከእስራኤል ይወጣል እንጂ ከዓለም አይደለም፡፡ ይህ አሁን በቀጥታ ከግብፅ የሚወጣው እስራኤል የመጀመሪያው ገለባ የሐሰት እውነቱ እስራኤል ነው፡፡ አሁን የተባለት እስራኤል ወደ ወጡበት ግብፅ ማለትም ወዳለም ዓለም ተመልሰዋልና ዱሮ ቆርጠው ከወንዝ ማዶ የጣሉት ዓለማዊነት እነርሱ ወደ ጣሉት ስለተመለሱ ለመቀበል ከሙታን ተነሥቶና ከራሱ የከፉ ሰባት አጋንንት ሆኖ የጠፋው ልጅ ተመለሶ መጥቶበታልና አንገቱን አቅፎ በመሳም ዋጥ አደረገው፡፡ «እስራኤል ለእግዚአብሔር ቅዱስ ነበረ፣ የቡቃያውም በኩራት፣ የበሉት እንደ በደለኛ ይቆጠራሉ፣ ክፉ ነገርም ያገኛቸዋል፡ (ኤር.2፡3)» ስለዚህ እግዚአብሔር







የተዋጠበትን በኩሩን ለማስተፋት የግብፅን ተንከባሎ መቀበር አንደኛ መቃብር ተብሏል፡፡

በዚያች ሌሊት እዚህ በእስራኤል ቤት በግ ታርዶ መገፏ፣ እዚያ በግብፃዊው ቤት ያለ የግብፅ በኩር እጅ ሳይነካው ታርዶ መገፋፍና የታላቁ ሽለፈት ቀብር ሥነ ሥርዓት (ዘፀ.12፡29) ነበር፡፡ ይህ ዱሮ፣ ዱሮ ቆርጠው የቀበሩት የግብፃዊነት ሽለፈት በተቀበረበት በስብሶ ያለ አድራሻ የጠፋው እንዴት ከብዙ ዓመታት በኋላ ከየት መጣ ለሚለው ጥያቄ መልሱ በዚህ መጽሐፍ በሌላ ገጽ የተሰጠውን መመልከቱ በቂ ነው፡፡ ከዚህም ሌላ እግዚአብሔር የአባቶችን ኃጢአት በልጅ ልጅ እስከ አራት ትውልድ የሚያመጣ (ዘፀ. 34፡7) አምለክ እንደ መሆኑ መጠን ከአብርሃም ጀምሮ የተከማቸ ኃጢአት በልጅ ልጆች (ዘፍ.15፡13-14) አምጥቷል፡፡ ይግብባያን እርኩሰት በእስራኤል ላይ ጠጣብቆ እንደ ነበረ በጌልገላ ላይ በስለት ተቆርጠው መለየታቸው ተጨማሪ ማሥረጃ ነው፤ ስለዚህ ከዚህ ከተጫነባቸው ውዝፍ ኃጢአት ጭነት ክብደት የተነሣ እስራኤል ሬሙኸ፣ ፊደላዊ/ሥጋዊ ጩኸት ሰው ሲሰማው የውስጣቸውን የመንፈሱን ጩኸት እግዚአብሔር ሰምቷል፡፡ የነፍስን ድምፅ አልባ ጩኸት እንጂ የሥጋን ድምፃዊ ጋጋታ ጩኸት እግዚአብሔር አይሰማም፡፡ ሳትለምኑት፣ (ሳትናገሩት) ይሰማል ይላል እንጂ ስትነግሩት ይሰማል አልተባለም፡ (ማቴ.6፡8፤ ኢሳ.65፡24፤ ዘፍ.21፡15-19) ሲታይ አጋር ድምፅዋን አሰምታ ሬሙኸች ይልና እግዚአብሔር የሬሙኸውን ብላቴና ድምፅ ሰማ ይላልና ...ወዘተ፡፡ የግብፅ እስራኤል የውጩ ጭንቀትና የውጩ ቀንበር የሐሰት እውነተኛው ቀንበርና ጩኸት ሲሆን፣ የውስጡ ጭንቀትና ቀንበር የእውነት እውነተኛውን ቀንበር ሊያመለክት ተፈጠረ፡፡

ሁለተኛው መቃብር፣ እስራኤል ወንዝ ሲሻገር፣ በገዛ-ራሱ እጅ ተከትሎ ባሕር በመግባት ከእስራኤል ላይ ተገፍፎ ግብፃዊ ሠራዊትና ሕዝብ የተቀበረበት የባሕር ጥልቀት (ዘፀ.14፡27-31፤ 1ቆሮ.10፡1-4) ነው፡፡

ሦስተኛው መቃብር፣ ከእስራኤል እስራኤል ይወጣ ዘንድ በምድረ-በዳ ተገፍፎ የወደቀው የተቀበረው ግብፅን የቀመሰና ዲቃላው እስራኤል የተቀበረበት የምድረ-በዳው መቃብር፤ (ዘኁ 14፡20-35፤ ም. 32፡10-13) ዲቃላ እስከ አሥር ትውልድ ድረስ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይገባም፤ (ዘዳ.23፡2) ዲቃላ ማለት በጉዞ ላይ የተቀበሩ ግብፃዊ እስራኤል፣ ማለት ዛሬ ዓለማዊ ክርስቲያን ማለት ነው፡፡

አሥር ትውልድ፤ አሥር ትውልድ ማለት ምን ማለት ነው? አሥር ትውልድ ማለት አሥረኛው ልጅ ነጥሮ እንዲወጣ ዘር እየተካ የዘጠኝ አባት ሞቶ መቀበር ነው፡፡ አሥረኛውን ልጅ ለማስገባት ዘጠኝ አባት ይሠዋል፡፡ እኔ ከነዘጠኝ ልጅ ልጆቼ ተቀብሬ ቀርቼ አሥረኛው የልጅ ልጄ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ እንዲገባ ማለት ነው ወይ? ይግባኝ ለጽድቅ ፈራጅ፤ ይህ ይሻላል ወይስ እኔ ራሴ አሥር ጊዜ ሞቼ ሞቼ፣ ብድግ ብዬ በራሴ እግር ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ በቀጥታ ብገባ ይሻላል? የዚህ ቀጥተኛው (ጥሬ ትርጉም) ግን በአዲስ ኪዳን አንድ ሰው በአሥር ሞት ጥምቀት ሞቶ ትንሣኤ በማግኘት ነጥሮ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ማለት ይሆናል፡፡

አራተኛው፣ መቃብር 12ቱ ሕያዋን ድንጋዮች (1ጴጥ 2፡4-5) ከጥልቀት ይወጡ ዘንድ በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ከእግዚአብሔር ዙፋን (ከታቦቱ) በታች-ታች የተቀበሩበት የምትክ ድንጋዮች መቃብር ነው (ኢያሱ 4፡8-9፣ 1ጴጥ 2፡4-6) አመሳክር፤

አምስተኛው መቃብር፣ በጠቅላላ የግብፅ ርኩሰት ተገፍፎ በሰማይና ምድር መካከል ተራራ፣ ከፍታ /ጌልገላ/ ላይ በጌታ ፊት የወደቀው የሸለፈት፤ (ኢያሱ 5፡7-9) ይህ ሁሉ በአሕዛብና በእስራኤል መካከል የተደረገ የመራራቂያ ገደል እንዲሰፋ የሚያደርግ የቅድስናቸው ምጥቀት ሆኖ







በጥላ የሚታይ ነው፡፡ አሕዛብ ከፈለገ የእስራኤልን ፈለግ በእድገት ተከትሎ በዚሁ ሥርዓት በመጓዝ ደርሶ ከእስራኤል ጋር መቀላቀል ይችላል፣ (ኢሳ 2፡2-4፣ ም.66፡18-22፣ ዘካ 8፡20-23)

እንግዲህ የኢየሱስ መቀበር፣ መቀበር ሳይሆን፣ ትንቢቱ (ኢሳ.53፡9፣ ማቴ.16፡21) ይፈፀም ዘንድ በመቃብር ውስጥ ገብቶ በምድር ልብ እስከ ሦስተኛ ቀን መቆየቱ የተረጋገጠ ሆኖአል፡ ከዚህም ሌላ እግዚአብሔር የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው፣ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና ተብሎ የተጻፈው ደግሞ መፈጸም ነበረበትና (መዝ.15፡8-11፣ ሐሥ.2፡24) የሞት ጣር ሰውን መያዝ የሚችለው የኃጢአትን ዋጋ (ሞትን) (ሮሜ.6፡23) ዕዳ ከባላጋራ ጋር በመንገድ ሳለ ሳይከፍል ከወህኒ እንዳይወጣ (ማቴ.5፡25/ሉ-26፣ ም.18፡34) ስለሚታገት ነው። የኃጢአት ዋጋ ጨርሶ ከተከፈለ ጣዕረ-ሞት ጨርሶ አይኖርም። አሁን ጣር እየተሰማህ ከሆነ አልከፈልክም ማለት ነው።

ሞት በውጭ በፊደል፣ ለውስጣዊ (መንፈሳዊ) ሞት ምሳሌ ሲሆን፣ ውጫዊ መቃብርም እንደዚሁ ለውስጣዊ መቃብር ምሳሌ ነው፡፡ የአዳም ልጅ በአካለ ሕይወት እያለም በውስጣዊው (በመንፈስ) ሞት በኃጢአት የሰጠመ ነው፡፡ ይህንንም እስከማይረዳ ድረስ የጠፋ ነው፡፡ ውጫዊው ፊደላዊ (ፍጥረታዊ)ው ሞት የሐሰት እውነት ሞትና መቃብር ሲሆን፣ ውስጣዊው የቁመና ሞትና መቃብር እውነት እውነተኛው ሞት ነው፡፡ በውስጥ በሞት መኖራችንን ለመካድና ለመሸፋፈን ለዚጎች ለተውሶ ሕይወት በአስመሳይ ምሥጋና እግዚአብሔርን ለመደለል እንጥራለን፡፡

ተጨማሪ አሥረጅ፣ «ታላቅም ድምፅ ከሰማይ፣ እነሆ፣ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው፤ ከእነርሱም ጋር ያድራል፣ ... እንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል፣ ስለሆነ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፣ ኀዘን ቢሆን፣ ወይም ጩኸት፣ ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም ... ራዕይ 21፡3-4» ሕመም፣ ቁስል ሥቃይ ማለት ኃጢአት ወይም ሰይጣን ያደረበት ሰው ሲሆን ነው እንጂ ኢየሱስ

ከእግዚአብሔር ጋር እግዚአብሔር ሆኖ የተጣበቀ አንድ ስለሆነ፣ እነዚህን (ጣር፣ ሥቃይ፣ ሞት) የተባሉ ነገሮችን በዓይኑ ከሚያይ በስተቀር አያስተናግዳቸውም፤ ወደ እርሱም አይቀርቡም፤ (91)፡1-8፣ ዘፀ 14፡14፤) ጋሻ ይሆልና፡፡

ኢየሱስ ግን መከራን የተቀበለው በተጻፈው መሠረት ከበር ውጭ ማለት የውስጥ መንፈሳዊ ማንነቱን ሳይነካ ማለትን ይገልጻል ውጭ፣ (ሉ.ቃ.13፡ 33) በኢየሩሳሌም ውስጥ በፊደል አካሉ ላይ መሆኑ ይታያል፤ ውስጡ እጅግ ቅዱስ ነውና፡፡ ቃል ሥጋ የሆነው መከራ መቀበያ ሆኖ በዕቅድ የተዘጋጀ ነበረና (ኢሳ 53፡7)፡፡ ከበር ውጭ ማለት ከተለምዶ ቤት በር ውጭ ማለት ሳይሆን፣ ከቤተ-መቅደስ በር ውጭ-ውጭ ከማንነቱ በርቀት ማለት ነው (ዕብ 13፡12)፡፡ እርሱ ራሱ ቤተ-መቅደስ ለመሆኑ /ዮሐ.2፡19-21/ን እናስመሰክራለን፡፡ ከፊደሉ ኢየሩሳሌም በውጭ መከራ መቀበሉም የብሉይ ኪዳንን ትንቢት መፈጸሙ ነበር፤ በዕብ.13፡12 ላይ አዲሱ መደበኛ ትርጉም የሰጠውን ማብራሪያ ሉቃስ 13፡33/ን የሚቃረን ይመስላል፡፡ (ሉቃስ በኢየሩሳሌም ውስጥ ከበር ውጭ ያለውን የዕብራውያን ማብራሪያ ከከተማ ውጭ በማለት)፡፡ ነገር ግን ክርስቶስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ፣ ማለት በፊደል (በሰው ቋንቋ) ከበር ውጭ ማለት ሳይሆን፣ ከመቅደስ ከእግዚአብሔር ማደሪያ በውጭ ማለት ነው፡፡ መከራው በአጥሩ (በመጋረጃው) ላይ በውጭ ቀርቷል እንጂ ወደ ማደሪያው ውስጥ ሊገባና ማንነቱን ሊነካ ከቶ አይችልም፡፡

መቃብር በመለኮታዊ፣ (በሰማያዊ) ሥፍራ

ሞት መቃብር በውጪ በሰው ፊትም በኃጢአትም ቢሆን ራስን ሙሉ በሙሉ መጣል፣ ራስን እስከ መርሳት መዋረድ ሆኖ የሚታይ ነው፡፡ ይህ ቁስ አካላዊው ከማሰብ፣ ከማስታወስ ውጭ ሆኖ ሰው የፈለገውን እንዲያደርግ በሰው እጅ መጣል ሲሆን፣ ይህ ዓይነት መሥዋዕት በራስ





ፈቃድ ካለመሆኑም ወደ ላይ ለእግዚአብሔር ከፍ ብሎ መቅረብ ሳይሆን፣ ወደ ታች ወደ እናት አፈር መሥዋዕት ሆኖ መጥፋት ነው፡፡ በቁስ ወደ ቁስ፡፡

ሌላው ግን ከማሰብ፣ ከመፍቀድ ጋር በእምነት ለጌታ ታዝዘን ትዕዛዙ እውነት መሆኑን አምነንና፣ የሚበልጠውን በመምረጥ ለሚሻለው ዕድል ራስን ሙሉ በሙሉ የፈለገውን እንዲፈፅምብን በጌታ ትዕዛዝ በራስ ፈቃድ ለጌታ አልፎ መስጠት ነው፤ የተሻለ ሕያው ቅዱስ መሥዋዕት (ሮሜ12፡1)፡፡ ሕያው ማለት ሳትሞት ማለት ሆኖ፣ ቅዱስ ማለት

ምሳሌውም፣ አብርሃም ልጁን ሊሠዋ በታዘዘ ጊዜ ከነበረበት ተለይቶ ሦስት ቀን መንገድ እንደተጓዘ፤ (ዘፍ.22፡1-4)፤ መሴ በ(ዘፀ.8፡26-27) እንዳመለከተው፣ በጌታ መሪነት ከዓለም ሦስት ቀን መንገድ ተለይቶ መራቅ፤ ይህን ለመፈፀም ኢየሱስም ሦስት ቀን ተጉዞ ለእግዚአብሔር ሕያው ሆኖ እንደቀረበ ማለት ቻላል፡፡ ኃጢአትን መሥዋዕት አድርጎ መቅበርን አመልክቷል፡፡

አሁን ግን የመለኮታዊ ደረጃ መቃብርም መሥዋዕቱም ውጫዊ ሳይሆን ውስጣዊ፣ ቁሳዊ ሳይሆን መንፈሳዊ፣ ምድራዊ ሳይሆን ሰማያዊ ነው፤ ማለት በጌታ ፊት ከፍታ ላይ ከሰው እይታ ተጉዞ ርቆ የሚፈጸም ስውሩ ቅዱስ የሆነ የሕይወት መሥዋዕት ማለት ነው፡፡ ጸሓፊው የዳዊት (መዝ. 116፡15)ን መሠረት በማድረግ የቅዱሳን፣ ቅዱስ ሞት ብሎታል፡፡ ዘመኑ እንደሚፈቅደው፣ ይህ ሙሴና ሐሮን የተቀበሩበት ከፍታ መለኮታዊውን ያመለክታል፡፡ ሥጋው ጪስ ሆኖ ለእግዚአብሔር ቀርቦ እንዲጠፋ በጌታ ፊት መሥዋዕት ሆኖ የመቅረብ ሥነ-ሥርዓትን ለዛሬዎቹ ያመለክታል፡፡ ጢሱ፣ ነፍስን፣ (መንፈሱን) ከሥጋ በእሳት አበጥሮ አፅድቶ (ንፁኅ) አድርጎ ለባለቤቱ (ለእግዚአብሔር) ማቅረብ ማለት ነው። ተራራ ላይ መሞት በመሠውያ ከፍታ ላይ መሥዋዕት እንዳቀረበው ኖኅ ነው። እግዚአብሔር

የሠራው መሠውያ ሰው ከሠራሽ መሠውያ እጅግ የላቀ ቅዱስ ነው፤ (ዘፍ.22፡1-2፣ ከሕዝ.20፡40) ይመሰክር።

በዚህ ሁኔታ ቀዳሚ ሆኖና ሞቶ በጌታ ፊት ከፍታ ላይ የተቀበረው እንደኛው ሊቀ-ካህኑ አሮን በሖር ተራራ (ዘኁ.20፡22-28) ወደዚያ ወጥቶ እንዲሞትና እንዲቀበር ከልጁ ከዓልአዛር ጋር የሙሴ እርዳታ ይታያል እዚያም የክብርና የጌጥ ልብሱን ከአሮን ላይ ያወለቀውም ራሱ አሮን ሳይሆን አለቃው ሙሴ ነበር፡፡ እንደተጻፈ፣ «...እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን በኤዶምያስ ምድር ዳርቻ ባለው በሖር ተራራ እንዲህ ብሎ ተናገራቸው፡- አሮን ወደ ወገኑ ይከማች፤ ... አሮንና ልጁን አልዓዛርን ይዘህ ወደ ሖር ተራራ አምጣቸው»፤ አምጣ ማለት ወደ ራሱ ወደ እግዚአብሔር ስለሆነ በፊቱ መሞት መታደል ነው፡፡ ከአሮንም ልብሱን አውጣ፤ ልጁንም አልዓዛርን አልብሰው፤ አሮንም ወደ ወገኑ ይከማች፣ በዚያም ይሙት፡፡ (ለዳግመኛ ልደት ዳግመኛ ቆለፈት ማውለቅ)፡፡ ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ፡፡ ማህበሩም ሁሉ እያዩ ወደ ሖር ተራራ ወጡ፡፡ ሙሴም የአሮንን ልብስ አወጣ፣ ልጁንም አልዓዛርን አለበሰው፤ አሮንም በዚያ በተራራው ራስ ላይ ሞተ፤ ሙሴና አልዓዛርም ከተራራው ላይ ወረዱ፡፡» ይህም በራሱ እግር ተራራ ወጥቶ በገዛ ፈቃዱ (እንደ ኢየሱስ) ከሞተውና እግዚአብሔር ከቀበረው ሙሴ ጋር ሲነጻጸር አሮን የተገደደ ይመስላል፣ ተራራ ላይ ድረስም በሙሴ መወሰዱ፣ የክብርና የጌጥ ልብሱንም ራሱ ሳይሆን ሙሴ ማውለቁ ይነበባልና ሆኖም የተቀባ (የታተመ) ነውና አይጣልም፡፡

የሙሴ መቃብር በተለይ፡-

ሁለተኛው፣ ሙሴ ወጥቶ የሞተው በናባው/ፊስጋ ተራራ ከፍታ ላይ በጌታ ፊት (1ነገ.19፡11) ሲሆን፤ የተቀበረው ግን እዚያው በሸለቆ ውስጥ እንደሆነ የተገለጠው (ዘዳ. 34፡1-8፤) መውረድን፣ መዋረድን ያመለክታል፤







ይህም በጌታ ፊት ስለሆነ መባረክ ነው፡፡ ሙሴ ግን እንደ አሮን ከሌላ ሰው ሰምቶ በሰው ድጋፍ ተሸኝቶ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር በቀጥታ እንደ ሰማው ቃል ታዝዞ ተራራ ወጥቷል፤ በዚህም ከፍታ ላይ ቆሞ እስራኤል ሊወርሰው ያለውን ምድር ከዳን እስከ ቤርሳቤህ፣ ከዳር እስከ ዳር አይቶና ካርታ አንሥቶ ውርሱን ጨብጦ በጌታ ፊት በፈቃድ ራሱን አቅርቧል፡፡ ሙሴ ግን ተራራውን በሞቱ፣ ሸለቆውን በመቀበሩ ውርሷል፡፡ ይህ ማለት፣ አንተም ዕብጠትህን፣ ከፍታህን ትዕቢትህን ረግጠህ ወጥተህበት ገድለህ ከፍታህ ላይ ረግጠህ ወጥተህበት ብትሞት ሞትህ ሕይወት፣ መሥዋዕትህ በጌታ ፊት እንጀራ ይሆንልሃል፤ ትጠግባለህ፡፡

ይህን የሙሴን አሟሟት ከልቤ እያደነቅሁ ከእስራኤል ሕዝብ ጋር የለቅሶው ተካፋይ ሆኜአለሁ፡፡ እንዲህ ለመሆን የረዳው አምላክ፣ እግዚአብሔር ይባረክ እላለሁ፡፡ይህ በእስራኤል ገኻዱ የፊደል (ገሃዳዊ) ከፍታ ቢመስልም በየራሳችን ልቡና ከፍታ፣ ሰማያዊ ሥፍራ ላይ እንሞት ዘንድ ተራራን የተቆጣጠረው አሞራዊ ተደምስሰን እንደመስስ ዘንድ አበክሮ ያስተምረናል፡፡እንዴት ለሚል? ይህም ዘመናችን እንደሚያዘው የልቡናችንን ከፍታ እብጠቱን ማቅለጥ፣ መሠዋት ማለት መዋረድ ነው፡፡ ይህም ከሸለፈት ግርዶሽ ጨለማ ወጥተን በብርሃን ስናየው፣ ሰማያዊ ሥፍራ፣ የመጀመሪያ ትንሣኤ ሆኖ ይታያል፤ (ራዕይ 20፡6) ሙሴና ኤልያስ የተገለጡበት የተቀደሰ፣ ታላቅና ረጅም ተራራ መሥዋዕት ሁሉ የሚቀርብበት ተራራ ይኸው ነው፤ (ሕዝ 20፡40፣ መዝ 48፡1-2፣ 2ጴጥ 1፡ 18፣ ማቴ 17፡5-6...) እንስሳን ከሚሠዋ ራስን የሚሠዋ እጅግ ይበልጣል፡፡

ሙሴ በመቶ ሃያ ዓመት ዕድሜው መቼስ ያለ እግዚአብሔር ምርኩዝ ያን አሁን በእምነት ራዕይ የምናየውን ቅዱስና ታላቅ ተራራ (ራዕይ 21፡10-11) እግዚአብሔር እስከ አለበት ድረስ እንዲሁ በራሱ አልወጣም፡፡ የሙሴ በትሩና ምርኩዙ ምንድር ነው? ማን ነው? (መዝ.23፡4/ለ) ወደ እግዚአብሔር መውጫው መሰላሉ መንገዱስ ማን ነው? (ዮሐ.14፡6)



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

እግዚአብሔር ለደካማ ኃይልን ይሰጣል፣ ጉልበት ለሌለውም ብርታትን ይጨምራል፣ (ኢሳ.40፡29) ሙሴ ጉልበት አለው ወይ? ጉልበት ላለውሳ? ጉልበት ላለው ብርታትን እጨምራለሁ አላለም፤ ጉልበት ያለው ምሥጋና አይሰጥማ የሚበልጠውን ምሥጋና ለራሱ ያስቀራል እንደ ሐናንያና ሰጲረ። ጉልበት ያለው ማንም በተራራ ወደ እግዚአብሔር አልወጣም፤ አይወጣምም፤ ከቶ ፍፁም መሥዋዕት አይሆንም። (አንተ ግን የራስህ ብርታት ስለሚሰማህ ወደ እግዚአብሔር በተራራ መውጣትን አልቻልህም መሰለኝ?) ሙሴ፣ በዚያ፣ በእግዚአብሔር ፊት፣ ከሰው ማንም ያላየውን ስውር ሞት ሞቶ ማንም ባላየው በተሰወረ ቅዱስ መቃብር ተቀበረ፤ በክርስቶስ ክብር ከወንድሙ ከኤልያስ ጋር እስኪገለጥ ድረስ 1500 ዓመታት ያህል በክርስቶስ ተሰውሮ ቆየ፤ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን ለዘላለሙ አሜን፤ (ሉቃስ 9፡28-31፣ ቆላ.3፡1-4፣ ቁ.4)። መቃብሩ ቅዱስ ስለሆነ እስከ ዛሬ ድረስ ማንም አላየውም። የሙሴ ትንሣኤ ከሄኖክና ከኤልያስ ቀጥሎ ሦስተኛ ደረጃ እንደተከሰተ መነጠቅ ሆኖ ሊታይ ሲቻል፤ የአሮን ደግሞ አራተኛ ነው ሊባል ይቻላል። ስለዚህ የአሮን ቅዱስ፣ የሙሴ የቅዱስ ቅዱስ፣ የሄኖክ እጅግ ቅዱስ የሆነ ቀብር ሥርዓት መባል ያለበት ነው። የአንተ ሥጋ በክርስቶስ ሞት ጥምቀት የተቀበረበትን መቃብር ማን አይቷል? እግዚአብሔር ውስዶታልና አልተገኘም ወይ??

ሙሴ፣ ከያዕቆብና ከዮሴፍ ጋር በመቃብር ተመሳሳይ የሚሆንበት በምንድን ነው? ቢባል፣ ሙሴ ወደ እስራኤል አገር በሚያደርገው ጉዞ ላይ በሕዝቡ ምክንያት ስለተደናቀፈ፣ ጥላዊ /ቁሳዊ/ ወደ ሆነችው አገር በጥላ አካል እንዳይገባ ተከለከለ። ቢሆንም በተራራ ላይ ማለት በክርስቶስ ላይ ሆኖ የእስራኤልን አገር ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ድረስ ቆላ ደጋውን ሁሉ በእግዚአብሔር መነጽር እንዲያይ ስለተደረገ በመንፈሱ፣ በልቡ ወደ እስራኤል አገር እንደገባና እንደ ወረሰ ይቆጠራል፤ ደግሞም የመንፈስ ነገር ከቁስ ነገር እጅግ የሚበልጥ መሆኑ ይታወቃል። እንዲሁም





በተራራው ላይ በከፍታ (በእግዚአብሔር ፊት) መሞቱ ከነያዕቆብና ዮሴፍ በሚበልጠው ትንሣኤ እንደ ተነጠቀ እሙን ነው (ዕብ.11፡35/ለ። በፊደል፣ በቁስ የሚወረስ ነገር የጋራ ሲሆን በልብ የሚወረስ ነገር፣ ግን የግል ነው። ደግሞም ወደ ተስፋይቱ ምድር በንጥቀትም፣ በመለወጥም ይገባልና ሙሴም በንጥቀት ገብቷል ማለት ይቻላል፤ (1ተሰ.4፡17፣ 1ቆሮ.15፡52)

እነዚህ፣ አሮንም፤ ሙሴም ሞቱ የሚለው የፊደሉ ቃል ጥላዊ እውነት ነው። በሚስጢር ሞቱ እንጂ። ሐሮንም በሚገርም ሁኔታ፤ ሙሴ በጣም በሚገርም ሚስጢር ሞተ። ኤልያስ እጅግ በሚገርም ሁኔታ፣ ሄኖክ እጅግ በጣም በሚገርም ደረጃ በተራራ (በከፍታ) ሞት ለእግዚአብሔር ሕያው መሥዋዕት ሆኖ መቅረብ ነውና። ሄኖክና ኤልያስ ቢለዩም፤ ይህ ዓይነት መሥዋዕትነት የተሰበረ መንፈስ፣ የተዋረደ ልብ፣ (መዝ.51፡16-17)፣ የተቀጠቀጠ መንፈስ፣ የተቀጠቀጠ (የደቀቀ) መንፈስ፣ (ኢሳ.57፡15) መዋረድን ያመለክታል። አሮን በሰው ፊት ሳይሆን፣ የክብርና የጌጥ ልብሱን በእግዚአብሔር ፊት ተገፍፎ በጌታ ፊት በከፍታ ላይ ተራቆተ፣ እዚያው ተዋረደ። ሞት፣ ሞት ሳይሆን፣ መዋረድ ነው። እግዚአብሔር የሚፈልገው በተለምዶ ሞት የሞተውን ሳይሆን፣ መዋረድን ነው።

እኔ፣ አንተ/ቺ ለእግዚአብሔር ሕያው ቅዱስ መሥዋዕት እንድንሠዋ ስንቴ ተመከርን? (ሮሜ 12፡1) ለእግዚአብሔር የሞተውን ሳይሆን ሕያው፣ (የበከተውን) እርኩስ ሳይሆን ቅዱስ፣ ከራስ ማንነት ሌላውን ሳይሆን፣ የገዛ ሰውነትን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ ከፈሪሳውያንና ከጸሐፎች ጽድቅ በላይ እንሆናለን፣ (ማቴ.5፡20)። የራስን ስም፣ ዝና ቀዳሚውን ባሕሪ (የራሱ ነው) ከእግዚአብሔር ፊት ጠርጎ በማውጣት ባዶ መሆን ማለት ነው፤ (ፊል.2፡7‹ ሉቃስ 11፡41) (የራስን አገልግሎት፣ የራስን ፆም፣ ጸሎት ጥምቀት፣ ምፅዋት) ቀኝህ ያደረገውን ግራ እንዳያውቅ፤ እንዲህ ማለት አንተ የምታደርገውን አንተ አትወቅ ነው። አንተ በቀኝህ በግ፣ በግራህ ፍየል ነህ ማለት ነው፤ (ማቴ.25፡31-33) ስለሆነ ቀኝህ በሩክ ግራህ

እርጉም ነው፡፡ በመሆኑ በክርስቶስ ሰይፍ ለሁለት ተከፍለህ ግራህ ወደ ገሃነም፣ ቀኝህ ወደ ገነት ማለት ነው፡፡ ከግራህ ጋር ቀኝህ በጣምራ ወደ ገሃነም እንዳትገባ ቆሎ እጅህ፣ እግርህ ብታሰናክልህ ቁረጥ፤ ዓይንህ ብታሰናክልህ አውልቅ የተባለው ለዚህ ነውና፡፡

ይህ የሙሴ መቃብር የአዲስ ኪዳኑ በጥምቀት አሮጌው ማንነት በእጅ ባልተደረገ ግዝረት ከኛ ተቆርጦ የተቀበረበት የማይታየው የልቡና ከፍታ መቃብርን አመልካች ነው፡፡ በአዲስ ኪዳን በክርስቶስ በሞቱ መጠመቁና በትንሣኤው መነሣቱ የመጨረሻ መደምደሚያ ነው፤እንዴት (ሮሜ.6፡3-11፣ ቆላ.2፡11-12፣ ም.3፡1-2፣ ቁ. 9-10) በአፅንዖት እንየው፡፡ «የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቋልና» (ሮሜ 6፡6) የተባለው ተግባራዊ እንዲሆን የኃጢአት ዋጋ (ዕዳ) ሞትን በፈቃዳችን የምንከፍለውም በዚህ ጥምቀት ቁም ሞት ነው፡፡ እንግዲህ መቃብር በመንፈሳዊ ደረጃ ርኩሰት፣ ሙት (ኢሳ 52፡1-2፣ ቆላ 2፡13) ተብሎ የተኮነነውን ሸለፈት (አሮጌ ማንነት) ከእግዚአብሔር ፊት ማስወገጃ (መቅበሪያ) ጉድጓድ የዘመኑ አስመሳይ ያልሆነ ጥምቀት ነው፡፡

እንግዲህ የእኛ ችግር፣ መጽሐፍ ቅዱስን ባልተገረዘው በሰው አእምሮ ማለት በጨለማ መመልከቱ ነው፡፡ የሰው አእምሮ እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን፣ እስካላለ ድረስ ጨለማ ስለሆነ እውነቱን ሳይሆን ሐሰቱን፣ ፍሬውን ሳይሆን ገለባውን ያስጨብጣልና፡፡ የእኛ የውስጡ ዘላለማዊ ሕይወትም በውጬ ሟች እና ጊዜያዊ ማንነት የተከበበ ነው፡፡ ኃጢአትና ሰይጣን ኢየሱስን ሊቆጣጠረው አልሠለጠነበትም፡፡ በእግዚአብሔር ፊት መበስበስ እንደሌለ በዚሁ መጽሐፍ ቀደም ሲል ተመልክቷል፡፡ ሞትን ሳያይ ተወሰደ የተባለው ሄኖክ ከእግዚአብሔር አንድ የሆነ ሳይሆን፣ ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል አካሔዱን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረጉ ይነበባል፡፡ ክርስቶስ ኢየሱስ ግን አብና እኔ አንድ ነን፣ እኔን ያየ አብን አየ፣ እኔ በአብ፣ አብም በእኔ ይኖራል ሲል በሥልጣን ቃል ተናግሯል፣ (እኛ





እንዲህ ልንናገር ብርታት እናጣለን፡፡) ይህም ምስክርነቱ እውነት እንደሆነ የተመሰከረለት ይልቅ እንዴት ሞትንና መበስበስን ያያል? አብ በእርሱ ይኖራል ማለት እርሱ የእግዚአብሔር መቅደስ እንደመሆኑ መጠን በእርሱ የሚኖረው አብ ለዘላለም የሚነድድ እሳት (ኢሳ.33፡14) በእርሱ ሲነድ ለዘላለም ይኖራልና ኃጢአት (ሞት)፣ መበስበስ ቦታ የለውምና መበስበስን አላየም ተብሎ ተመሰከረ፡፡

ሞትና መበስበስ በውጭና በውስጥ፡- የአዳም ልጆች ሞትንና መበስበስን የሚያዩት ለምንድን ነው? ሞት መበስበስ፣ ትል፣ መግል የኃጢአት ውጤት ምርቱ ነው፤ ሰው የዘራውን የግል መዝገቡን፣ አንጡራ ገንዘቡን፣ ያጭዳል፡፡ አሜን የራሱን ይጨድ ወይስ ሌላው የዘራውን የሌላን ሰብል ሌላው ይጨድ? የራሱን፣ ከሰው በስውር ጨለማ የዘራውን በእግዚአብሔር ፊት በብርሃን ያጭዳል፡፡ ሁሉም የራስ፣ የራሱን ስለሚያጭድ የሌላን ሊያጭድ አያደርሰውም፡፡ ታዲያ የቱጋ የዘራውን ነው የሚያጭደው? በውጭ ሜዳ የዘራውን ያጭዳል ወይስ በውስጥ ጓዳ የዘራውን ያጭዳል? የራሱን ማለት የውስጥ ጓዳውን፣ የመዝገቡን ማለት ነው፡፡ ሞትና መበስበስ ምንድን ነው? ኃጢአት፣ ትዕቢት (የልብ ዕብጠት) ሲሆን፣ የገሃዱ በሰው ፊት ሞትና መበስበስ የእግዚአብሔር ፊት ሞትና መበስበስ፣ ትል፣ መግል ምስክር ነው፡፡ ያልሞተ ነገር አይበሰብስም፣ አይመግልም፣ አይተላም፡፡ ተሸፋፍኗል እንጂ ሰው ሁሉ በስብሷል፤ ተልቷል፤ ይመግላል፡፡ በምን እናውቃለን? ሰው ሁሉ ለእግዚአብሔር ሊሰግድ፣ ሊንበረከክ፣ በፊቱ ሊዋረድ፣ ሊሠዋ በስውር ያለው የልቡ ዕብጠት በሰማይ ከፍታ ላይ ሰቅሎታል፤ ቀደም ሲል እንዳየነው ተንጠልጥሏል፡፡ ይህ ዕብጠት መግል፣ ትል፣ መበስበስ ነው፡፡ ለዚህ የባቢሎንን ንጉሥ (ኢሳ.14፡4-20፣ ሐሥ.12፡ 20-23)

ቀደም ሲል እንዳየነው ውጫዊ መበስበስ የውስጣዊ መበስበስ ምስል ነው፡፡ ወደ ውጭ ወጥቶ የሚታየው ሞት ውስጥ ሞት መኖሩን ሊናገር ነው፡፡

መበስበስ፣ ትል፣ መግል በውጭ ወጥቶ የሚታየው ከውስጥ ላለው መበስበስ ምስክር ሆኖ ነው፡፡ ሰው የተባለ ሁሉ በውጭ፣ በግልፅ የሚበሰብሰው የሥራው የመዝገቡ በስውር በጨለማ የፀነሰውን ጌታ በግልፅ በብርሃን ሲከፈለው ነው፡፡ የአዳም ልጅ ወለ-ንጉሠ-ነገሥት ዘ-ኢትዮጵያ ቀርቶ፣ ዘ-ዓለም ቢሆን እንኳ በቁስ አካሉ መበስበሱና መግማቱ አይቀርለትም፡፡ ይህም ሊደርስበትና ሊያጭደው ያለው ምን እንደ ሆነ ማስጠንቀቂያው ነው፡፡ ሰው፣ ከውጭ አካል መበስበስ ከቶ የማያመልጥ ቢሆንም፣ በዚህ ተምሮ ዘላለማዊ ከሆነው ውስጣዊ መበስበስ እንዲያመልጥ ይህ አዋጅ ነው፡

እንግዲህ ሁሉም በየደረጃው የዐቅሙን ያህል ራሱን ከፍ-ከፍ አድርጓል!! ሰው ሁሉ ከዲያብሎስ ጋር ዙፋኑን ከእግዚአብሔር ከዋክብት በላይ የዘረጋ ነው፡፡ ሁሉ በምላም የከበሬታ ሥፍራ፣ በምኩራብም የከበሬታ ወንበር፣ በገበያም የከበረ ሰላምታ፣ መምህር ሆይ፣ ክቡር ሆይ አንቱ፣ …መባልን ከፍ-ከፍ መደረግን ለጊዜው መርጠዋልና ራሱን ከፍ፣ ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋርዳል፣ ርኩስ ነው ተብሎ በተጻፈው መሠረት አፍንጫ እስኪይዙበት ድረስ ሞቶ በስብሶ ይዋረዳል፤ ትልና ብል መደረቢያው ይሆናል፤ /ኢሳ.14፡10-20፤ ማቴ.23፡6-12፤ ሐሥ.12፡21-23/ ብሉና ትሉ ገኘነመ-እሳት የሚነድበት ማገዶ መሆኑም በብርሃን ምስክርም ፈራጅ ዳኛም በሆነው ጌታ ቃል የተረጋገጠ ነው፡፡

የአዳም ልጅ በመንፈስም፣ በአካልም፤ በውጭም በውስጥም ትል ማለት ነው፡፡ ከሰው ፊት ተሸፋፍኖ ክቡር ሆይ እየተባለ ከድኖ ያቆየው ትሉና ብሉ ይጋለጣልና፡፡ ሞትንና መበስበስን የሚያይ ሁሉ በፈቃዱ አልሞትም፣ ፈቅጄ አልበሰብስም፣ አውቄ አልዋረድም፣ ለእግዚአብሔር አልንበረከክም ነው፡፡ ለእግዚአብሔር በመንበርከክ ብቻ የሚከፈለውን ዕዳ የኃጢአትን ዋጋ እምቢ አልከፍልም? ለእግዚአብሔር መንበርከክን ሞት ነው አታሳዩኝ ትላለህ? ለእግዚአብሔር መስገድ፣ ለእግዚአብሔር መሸነፍ







ሞት ነው ወይ? ለሰይጣን የተሸነፈ፣ የተንበረከከ፣ የሰገደ፣ ያጎበደደ ሁሉ ለእግዚአብሔር የተንበረከከውን ይንቃል፣ ይፀየፋል? ክብር ለሚገባው እግዚአብሔር ክብርን በፈቃደኝነት አልከፍልም ያለ ሁሉ እምቢተኛ ትዕቢተኛ ልቡ መግል ይዞ ያበጠበት መሆኑን አንባቢውና ጸሐፊው እንመሰክራለን፡፡

ለእግዚአብሔር አልንበረከክም፣ ፈቅጄ አልገዛም ባይ ትዕቢተኛ ሁሉ ከባቢሎን ንጉሥና ከሄሮድስ ጋር የተመደበ መግልና ትል፣ ብል የተሞላ ብስባሽ፣ ርኩስ ግም ነው፡፡ እዚሁ በሰው ፊት ጤናማ ትልቅ ክቡር፣ አንቱ እየተባለ በጊዜያዊ ክብርና በዕለት ጥቅም ተደልሏል፣ ተሞኝቷል፣ ትርፉ የዘላለም ኪሣራ መበስበስ ነው፡፡ ብስበስ፣ ብስብስ ነወይስ ሰይጣን/ኃጢአት ያረፈበት ሰው ብስብስ ነው? ጊዜያዊው አጉል ውዳሴ ርኩሰቱን እንዳያይ ጋርዶበት ተታልሏል፡፡ በሁሉም ረገድ የተጭበረበረ ምስኪን ሰው ነው፡፡ ይህ ውሸት ነው የሚል ካለ ከክቡራን ነገሥታት መቃብር ጀምሮ እስከ መጨረሻ ድሀ መቃብር ከፍቶ በማየትና በማሽተት ማረጋገጥ ይችላል፡፡ ለዚህም ነው ማርታ የአላዓዛር መቃብር እንዲከፈት በታዘዘ ጊዜ «እነሆ ከሞተ አራት ቀን ሆኖታልና አሁን ይሸታል» ብላ የሬሙኸችው፡፡ ሰው በውጭ የሚሆንበት ነገር ሁሉ በውስጡ ይሆናል በብሉይ ኪዳን እስራኤል በአሕዛብ አፍንጫ ላይ ሸለፈቱን ውርውሮ ወደ ውስጥ የገባ ሕዝብ ሆኖ ይቆጠር ነበር፡፡

የእነሙሴ የተራራ ሞት በአሁኑ አዲስ ኪዳን ሰውነትን በጌታ እግዚአብሔር ፊት በመቅደሱ ከፍታ ውስጥ (ላይ) ሥጋ የተባለውን ሕያው፣ ቅዱስ መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ መሆኑ ተደግሟል፤ (የተሰበረ ልብ)፡፡ ይህ አሳብ በ(ሕዝ.20፡40፣ ኢሳ.66፡20፣ እና ሮሜ 12፡1) የተነገረውን የሚተረጉም ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ሙሴና አሮንም በመጠነኛ ልዩነት በተራራ ከፍታ ላይ ወጥተው በጌታ ፊት ሰውነታቸውን ሕያው፣ ቅዱስ መሥዋዕት አድርገው በሕይወት እያሉ ፈቅደው ለእግዚአብሔር

*አቅርበዋል፡፡ ሕያው መሥዋዕት ሆኖ በተራራ ከፍታ ላይ መቅረብ ማለት የመፍቀድ ጊዜህ ከማለፉ በፊት በጌታ ኢየሱስ ምሳሌ «ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ አኖራለሁና፤ ስለዚህ አብ ይወደኛል እንዳለው ነፍሳችንን ስናኖር ((አብ እኔን አንተን/ችን በክርስቶስ እርሱን እንደ ወደደው ይወደናልና እኛም ነፍሳችን በእምነት ለእግዚአብሔር አሳልፈን እንስጥ፡) እኔ በፈቃዴ አኖራለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም፡፡ ላኖራት ሥልጣን አለኝ፣ ደግሞ ላነሣት ሥልጣን አለኝ፡፡ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀብያለሁ» (ዮሐ.10፡17-18) ባለው ዓይነት ውጫዊው አካል ከመፍረሱ በፊት በፍጥነት በአንተው ጉዳይ አንተው ራስህ በተሰጠህ የሊቀ-ካህንነት ሥልጣን ራስህን (የገዛ ሥጋህን) መሥዋዕት ቁርባን አድርገህ ማቅረብ ማለት ነው፡፡ ልጠይቅህና፤ ራስህን ሕያው ቅዱስ መሥዋዕት አድርገህ በመንፈስ ካቀረብከው ከአንተና፣ ከራሱ በውጭ ያለውን እንስሳ መሥዋዕት አድርጎ በፊደል ካቀረበው የብሉይ ኪዳን ሊቀ-ካህን ማን የተሻለ አቅርቧል? ኢየሱስ ነፍሱን ለማንሣት ሲል የማኖርን ሥልጣን ከአባቱ ተቀብሏል፤ አንተስ ይህን ሥልጣን ከማን ተቀበልህ? ከአባትህ ከኢየሱስ? አዎን፣ ኢየሱስ ከአብ የተቀበለውን ሥልጣን ለራሱ ሊይዝ ነው ወይስ ለልጆቹ አሳልፎ ሊሰጥ ነው? ከአብ እየወሰደ፣ ለእናንተ እኮ ነው የሚሰጠው፡፡*

*በእንዲህ ዓይነት መሥዋዕት ሆነን በፊቱ ስንቀርብ ሙሴን እንደ ቀበረ እርሱ እግዚአብሔር እንዲቀብረን በእጁ ላይ መውደቅን ያስተምረናል፡፡ ጌታ ነፍሴን አነሣት ዘንድ አኖራለሁ ሲል፣ የት አኑሯት ከየት ነው የሚያነሣት? ይህ አሠራሩ አልተካደም፤ ነገር ግን «ዐወቅህ» የሚል መልስ ተሰጠ እንጂ፡፡ ታዲያ ይህ ከዚህ ጋር እንዴት ይስማማል? የጌታ ገንዘብ ቃሉ ነው፡፡ ቃሉ ሕይወቱ ነፍሱ ነው፡፡ እርሱ ራሱን፣ ነፍሱን ነው የሚዘራው፡፡ ቃሉ (ነፍሱ) ሲዘራ ድርጊቱን በዓይን በማየት አይታወቅም፡፡ ነገር ግን ሲሰበሰብ ያታወቃል ይላል መጽሐፉ፡፡ ሲሰበሰብም በማየት*





*ሳይሆን፣ በእምነት ነው የምናስተውለው፡፡ በሌላ በኩል ቃሉ (ክርስቶስ) የሚሰበስብ ሰብሳቢም ጭምር ነው (ኢሳ. 2፡2፣ ም. 66፡18፣ ሉቃስ 13፡ 34)፡፡ «ቀብር» እግዚአብሔር ቀበረ ሲባል ምን ማለት ነው? እንዴት ነው? እግዚአብሔር በክብሩ፣ በጽድቁ ሸፈነ፣ በጽድቁ ጥልቀት ውስጥ አኖረ ማለት ነው፡፡ ሰይጣን ከኃጢአት በታች እንደሚቀብር እግዚአብሔር በተቃራኒ በጽድቁ ጥልቀት ውስጥ ይከድናል፡፡ ታላቅ ዕድል፤ እርሱ በክብሩ፣ በጽድቁ እንጂ ሌላ መሸፈኛ የለውም፡፡ አንተ ግን በገዛ ጽድቅህ ተሸፋፍነህ ከተገኘህ ከሥረሃል፡፡ በተቃራኒው ግን አዳምን በቁርበት፣ በውርደት ከደነው፡፡ በራሱ ጽድቅ (በእጁ ሥራ) ተሸፋፍኖ ተገኝቷል! በአዲስ ኪዳን ደረጃ ስንመለከተው ደግሞ እነሙሴ መሥዋዕት ሆነው የቀረቡት በውስጣዊ በማንነታቸው ተራራ ላይ ሳይሆን በጣም በርቀት ላይ በነበረ ውጫዊ ተራራ ላይ በመሆኑ የእነርሱ አሁን በወንጌል ብርሃን ሲታይ በጥላዊ እውነት ደረጃ ይፈረጃል፡፡*

*በአሁኑ አዲስ ኪዳን ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ሆነን የምንቀርበው በውስጣችን፣ በልባችን ከፍታ ላይ በመሆኑ የእስራኤልን ማለት የእነሙሴን አስመሳይና (ምስያ)፣ የሐሰት እውነቱ አድርጎት ወደ ውጬ ዕድሞ ይጥለዋል፤ አይቆጠርም (ራዕይ 11፡1-2)፡፡ የውጭ ሥርዓት(የትኛው) ደግሞ በውጭ ያስቀራል፡፡ የአዲስ ኪዳኑ ከፍታ መቃብር «...በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀበርን» የሚለው ከእርሱ ጋር በመሆኑ የመጨረሻውና የእውነት እውነቱ መቃብር ስለሆነ ማንም በማያውቀው በእምነት እንጂ በማየት ባልሆነው መቃብር ቀባሪው በሙሴ ዓይነት ጌታ እግዚአብሔር ነው፡፡*

*አንባቢ ወገኔ ሆይ፣ ጌታ እግዚአብሔር ሲቀብር በምን ገንዞ እንዴት እንደሚቀብር ትዝ ይልሃል? ሙትህን፣ ሕይወት አልብሶ፣ ኃጢአትህን በጽድቅ ሸፍኖ በፍቅር ገመድ ጠፍሮ ገንዞህ በጽድቅ አስጥሞህ ተውጠህ በራሱ ፑርጋቶሪ (የዕረፍት ቦታ) የባሮች ባልንጀሮችህና የወንድሞችህ*

ቁጥር እስኪፈጸም ድረስ በክብር ያስተኛሃል፤ (ራዕይ 6፡9-10)፡፡ ሕይወትንና የራሱን ጽድቅ አልብሶ ስንል ምን ያለብሳል ማለት ነው? ይህን የሚበሰብሰውን ሥጋ የማይበሰብሰውን ያለብስሃል፡፡ የማይበሰብሰው ምንድነው? ክርስቶስን የለበሰ መበስበስን የሚያይ ይመስልሃል? (መዝ 15፡8-11፣ ሐሥ 2፡25-28፣ ገላ 3፡27) በከፍታ ላይ፣ በእግዚአብሔር ፊት መበስበስ አለ ወይ? (ዘፀ 16፡32-33) በእግዚአብሔር ፊት መበስበስ የለም፡፡ እነሙሴ የሞቱበትና የተቀበሩበት ተራራ ወደ እግዚአብሔር መውጫ መሰላል የሆነው ተራራ እርሱ ክርስቶስ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ «ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፣ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን (ኢሳ.1፡18) እንደ አመዳይ ትነጻለች (ገላ 3፡27) እንደ ደምም ብትቀላ (ኢሳ 1፡18) እንደ ባዘቶ ትጠራለች፡፡ (ዳን 7፡9/ሀ) ትጠራለች»፤ እንደ አለላ ብትሆን በአመዳይ (በጽድቅ) ትሸፈናለህ፣ እንደ ደም ብትቀላ በባዘቶ ትከደናለህ። ነገር ግን፣ እምቢ፣ እንደ አመዳይ እሆናለሁ ካልህ፣ በአለላ ትሸፈናለህ፤ እንደ ባዘቶ እሆናለሁ ካልህ፣ በደም ትሸፈናለህ። ልባድርግ!! በቅጠል ተሸፋፍነህ ብትገኝ የቁርበትን መበስበስ፣ ግማት ትጎናጸፋለህ፤ (ዘፍ.3፡21)፡፡ አፍንጫ ተይዞ ከአፈር በታች ይከደናል፡፡ «... ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ፣ ይህ የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና፡፡ ዳሩ ግን ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሲለብስ፣ ይህ የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ በዚያን ጊዜ፣ ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈፀማል» (1ቆሮ 15፡51-54)፤ ድል ዋጠው፤ በድል ተከደነ፣ ድልን ተጎናፀፈ።

የመለኮታዊው ደረጃ መቃብር ይኸው፣ መንፈሳዊ ነው፤ በእምነት እንጂ በማየት ያልሆነው፡፡ በተራራ በጌታ ፊት በልቡና ከፍታ ላይ የሚቀርበው መሥዋዕት፤ (ሕዝ 20፡40) ሆኖ መቅረብ ነው፡፡ ለማጠቃለል ያሀል ምለስ ስንል አንደኛው፣ ሊቀ-ካህኑ አሮን የተቀበረበት ከፍታ፣ የሖር ተራራ (ዘኁ







20፡23-28)፣ ሁለተኛው፣ ሙሴ ወጥቶ የተቀበረበት ናባው/ፈስጋ/ ተራራ (ዘዳ.34፡1-8)፣ ሦስተኛው፣ የእስራኤል ልጆች ሸለፈት ተገፍፎ የተቀበረበት ጌልገላ ኮረብታ (ኢያሱ 5፡2-8) አራተኛው፣ የነዌ ልጅ ኢያሱ በተሰፋ ምድር የተቀበረበት ኤፍሬማዊው ተራራ (ኢያሱ 24፡29-30)፣ አምስተኛ፣ ሊቀ-ካህናቱ የሐሮን ልጅ ዓልአዛር ሞቶ የተቀበረበት ኤፍሬማዊው ተራራ፣ (ኢያሱ 24፡33) ስድስተኛው፣ ጌታ ኢየሱስ የተቀበረበት ከፍታ ጐልጐታ (ቀራኒዮ) አትክልት ሥፍራ (ዮሐ 19፡41-42) ሆኖ ይታየኛል፡፡ ይህ በእስራኤል ገሃዱ የፊደል ከፍታ ቢመስልም፣ በየራሳችን ልቡና ከፍታ፣ በሰማያዊ ሥፍራ ላይ እንሞት ዘንድና ማንም ባላወቀበት (በማያይበት) ቅዱስ መቃብር እንድንተኛ አበክሮ ያስተምረናል፡፡ ይህም መንፈሳዊ መቃብር ሲሆን፣ እኔነታችንን፣ ለራሳችን አሳብና ፈቃድ በመሞት ማለትም ባለመገዛት ለጌታ አሳብና ፈቃድ በመኖር የወደቀ አዳማዊ ባሕርይን በመግደል "የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ምኞቱ ጋር ሰቀሉት" ገላ.5፡24 እንደሚል የሥጋን ሥራ ሁሉ መግደል/ማስወገድ ነው፡፡ (እንዴት) ከዚያም ከትዕቢትና ከትምክህት ሕይወት ነጽተንና ጸድተን አስቀድሜ እንዳልሁት በተሰበረ ልብና በተዋረደ መንፈስ፣ በጌታ ፊት በትሕትና መመላለስ ነው፡፡ አንተና እኔ ሞተን የተቀበርነው በእምነት ነው፣ ይህ እንጂ የማይታየው ተራራ ከሁሉ የተሻለ ነው (ራዕይ 21፡11፣ 2ጴጥ.1፡18)፡፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን

ፍሬ ነገሩን ከሸለፈት ግርዶሽ ወጥተን በብርሃን (በክርስቶስ) ሆነን ስናየው፣ በሰማያዊ ሥፍራው በተራራ ሞት የሞቱት አስቀድሞ የሚነሡ በክርስቶስ (በጌታ) ሆነው የሚሞቱን (ራዕይ 14፡13) (1ተሰ.4፡16) ያመለክታል፡፡ በባለ መጋረጃው ብሉይ ኪዳን ሰው በቁስ አካል ወደ እግዚአብሔር ይወጣ የነበረው በተራራ እንደ ነበረ በስፋት ይታያል፡፡ ዛሬ ግን በመንፈስ አካል ወደ እግዚአብሔር መውጫም ሆነ መቅረቢያ የማይታየው ተራራ ክርስቶስ መሆኑ በታሪክ ግልፅ ነው፡፡ ፊተኛው

ክርስቶስ ነው፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም (ራዕይ 1፡18) እርሱ ነው፡፡ ፊተኛውም፣ ትንሣኤውም ከሙታን በኩርም እርሱ ነውና፡፡ እርሱ፣ ማንኛውም ነገር የሆነው በእርሱ ነውና ምንም ነገር ከእርሱ ውጭ ባዶ ነው፡፡ ዛሬ በክርስቶስ የሚሞቱት ሞቱን ሞታቸው አድርገው የተቀበሉ ስለሆነ፣ ያለ ጥርጥር ትንሣኤው ትንሣኤያቸው ነው፡፡ ሁሉንም በእርሱ መሆን ይቻላል፡፡ «... ከእንግዲህ በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው፣ ...ራዕይ 14፡13» በእርሱ ሆኖ በኩር መሆንም፣ ፊተኛ መሆንም በእርሱ ነው፡፡ «በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕ ቅዱስም ነው»፤ (ራዕይ 20፡6) በክርስቶስ የፊተኛውን ትንሣኤ ያገኙትን ሰዎች ሁለተኛ ሞት የሆነው የእሳቱ ባሕር አይጎዳቸውም (ራዕይ 2፡11) ማለት ነው፡፡ እነዚህ በፊተኛው ትንሣኤ እሳቱ ሊጎዳው የሚችለውን የሥጋን ሰውነት ለመንፈስ ቅዱስ እሳት ጥምቀት ገፍፈው ሰጥተዋልና እሳትን ያለፉትን እሳት የሆነው ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፤ (ከሥጋ ሥራዎች ቁጥጥር ውጭ በሆነ ሰው ላይ ሞት የሚባል ነገር ሥጋ ስለሌለ ሥልጣን የለውም፡፡) ሞት የሚያሳድደው በሥጋ የሆኑትን ነው፤ እነርሱ በሥጋ ሞት የሚከፈለው ዕዳ የሚፈለግባቸው ናቸውና፡፡ ሞት ሥጋ ነውና ሥጋ ከሌለ፣ ሞት የሚገድለው ነገር የለም፤ በዚህ አሳብ ትስማማለህ? የሥጋ ሞት ከሚመጣው ቁጣ ማምለጫ ብቸኛ መንገድ ስለሆነ የሞትን ፅዋ ከጥምቀቱ ጋር መቀበል እጅግ አፋጣኝ ጉዳይ ነው፤ (ማቴ.20፡22፣ ማር.10፡38)፡፡ ሞትን ፈርቶ ሞትን መሻገር አይቻልም፡፡ ይህ ዓይነት ሞት ቁስ አካልን በሞት መለየት ነው ወይስ አሮጌውን ልብ በሞት መለየት ነው? አዲስ ሕይወት ተብሎ የተጻፈው (ሮሜ 6፡4) አዲስ ሕይወት ወይስ አዲስ ልብ ነው? ጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀበራችሁ፣ ተነሣችሁ የሚለው (ቆላ.2፡12)፣ የእኛን አካል ሰውነት መቀበርንና መነሣትን ያመለክታል ወይስ አሮጌውን ኃጢአተኛውን ልብ ሞቶ መቀበርንና በአዲስ ልብ መነሣትን ያመለክታል? አካል ሰውነት በሞት መቀበርን ያመለክታል ወይስ አሮጌው ልብ በሞት መቀበርን



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16



ያመለክታል? እግዚአብሔር የሚፈልግብን አካልን እንድንቀብር ነው ወይስ አሮጌውን ልብ እንድንቀብር ነው? አሮጌው ልብ ኃጢአተኛውን ልብ አሮጌ ነው? ሞት፣ ሞት ነው ወይስ አሮጌው ልብ ሞት ነው? ሞትን ስለምንፈራ ከሞት ማምለጥ አልተቻለም (ዕብ.2፡14-15)፡፡

የሚፈራው፣ ለሞት የሚንቀጠቀጠው እኛ ሳንሆን እኛን ሆኖ በእኛ አካል ተዋኽዶ ተቃራኒ አማኑኤል የሆነው እርሱ ነው እንጂ፡፡ ሞት ለእኛ ትንሣኤ ሲሆን ለእርሱ ለተጣበቀብን ሲያል መውረጃ ነውና ይፈራል፡፡ በሞት ስንቀበር የምንቀበረው ለምንድነው? በሞት የምንቀበረው እኛ ሳንሆን፣ ባላንጣችንን ሸኝተን ሲያል አድርሰን ለመመለስ እንቀበራለን እንጂ፡፡ ይህን ስል የሥጋን ሥራዎች በመንፈስ የምንገድልበትን ሞት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ የፊተኛ ትንሣኤ ዕድለኞች፡- በዚህ ጥምቀት ወንዝ የሚሻገሩ ናቸው፡፡ ግብፃውያን ከአንደኛው የበኩር ሞት ያመለጡት በሁለተኛው በእሳት ባሕር ባይጣሉም በውኃ ባሕር ተጣሉ እንጂ ከሁለተኛው ሞት አላመለጡም፡፡

አንደኛው ሞት በሆነው በዮሐንስ ጥምቀት በውኃው ያላለፉ ሁለተኛው ሞት በሆነው በኢየሱስ እሳቱ ጥምቀት አላለፉም፤ (ሉቃ. 7፡29-30) ለእነዚያ ሁለተኛው ሞት የሆነው የእሳቱ ባሕር፣ ለእነዚህ ለፊተኛው ትንሣኤ ዕድለኞች ሁለተኛ ጥምቀትና ፈወስ ይሆናቸዋልና ነው፡፡ እጠቅሳለሁ፤ ለነዚያ (ለኃጢአተኞች) ሥርና ቅርንጫፍን አንድዶ አመድ የሚያደርገው እሳት ለነዚህ እግዚአብሔርን ለሚፈሩት ፈወስ፣ በክንፎችዋ ሥር የሆነ የጽድቅ ፀሓይ ይሆንላቸዋል፤ (ሚል.4፡1-3፣ 2፡16-18) ጥበብ ያለው አእምሮ በዚህ ነው (ራዕይ 17፡9) ለዘላለሙ አሜን፡፡

ሙሴና ኤልያስ በክርስቶስ ክብር የተገለጡበት ቅዱስ፣ ታላቅና ረጅም ተራራ (ሕዝ 20፡40፣ መዝ.48፡1-2፣ 2ጴጥ.1፡18፣ ማቴ.17፡5-6...) እግዚአብሔር በክርስቶስ ማለት በጽድቅ የሠወራቸው (ቆላ.3፡3-4) ሰዎች



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

ከፍ ተደርገው የሚገለጡበት ተራራ መሆኑ ይታየናል፤ አዳምን ለቁጣ በቁርበት የሸፈነ ሲሆን፣ እነዚህን ለምህረት በክርስቶስ ከድኖአቸዋል፤ (ሸፍኖአቸዋል)። ቅዱስ ማለት ስውር (ጥልቅ) ሆኖ ቆይቶ በባለ መከፈቻው በክርስቶስ የሚገለጥ ማለት ነው፤ (ቆላ.3፡1-4) በቁ.4 ላይ እንደሚታየው ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ በመስቀል ላይ ሙታን ናቸው፣ አገላብጠን እንይ። እስከ ክርስቶስ ክብር መገለጥ ድረስ ተቀብሮ በውርደት መቆየት በክብሩ ለመገለጥ እጅግ ይጠቅመናል።

በዚሁ መሠረት የሰው ዓይን እውነቱን ሳይሆን ሐሰቱን፣ እርግጡን ሳይሆን ግምቱን፤ ፍሬውን ሳይሆን ገለባውን ያስጨብጣልና፣ ከዓይናችችን እንጠነቀቃለን። ይህ በአዳም ከሰይጣን የተገጠመልን ተራውን ሰው ቀርቶ ነቢያቱን እንኳ እንደሚያሳስት ተጽፎ እናገኛለን፤ (1ሳሙ.17፡6-7፣ መሳ.14፡1-3፣ ም.16፡1 2ሳሙ.11፡2...ወዘተ)።

እንግዲህ እስራኤል ቅዱስ ሕዝብ ሆና በዙሪያዋ በአሕዛብ የተከበበች ብትሆንም ደግሞ በቀደሳት የእግዚአብሔር እሳት በሆነው በሕጉ (በቃሉ) ብርሃንና በደመና የተከበበች እንደ ነበረ፣ እንዲሁ ኢየሱስ በውጫዊ ሁኔታው በሥጋ የተከበበ ቢሆንም፣ በውስጥ ውስጠኛው ክፍል በእግዚአብሔር እሳት (መንፈስ ቅዱስ) ዙሪያው የታጠረ ነበር። ከዚሁ የተነሣም በሥጋ ቢሆንም ከመሞቱ በስተቀር፣ መበስበስና ትል ወደ እርሱ አልቀረቡም ብንል፤ የዛሬ ማመሳከሪያችን ምንድንነው? እስራኤል በቁሳዊ (በፊደላዊ (ፍጥረታዊ)) ሁኔታ በአሕዛብ ማለት በሞት እንደተከበበች እንዲሁ ዋናው እስራኤል የሆነው ክርስቶስ በውስጣችን ሆኖ በአንተና በእኔ ሥጋ የተከበበ መሆኑ እውነት ሲሆን፣ «ቃልም ሥጋ ሆነ» እንላለንና።

ይህ እርሱ በሥጋችን መከበቡ በዚያ በመለኮትነቱ ደረጃ በየመቃብራችን ውስጥ ሆኗል ማለት ሆኖ መበስበስን አላየም፤ መበስበስ ወደ እርሱ







አልቀረበም ማለትም መሆን አለበት። እርሱ ባረፈበት በእኔ ሥጋ ጀርሞች፣ ትላትሎች ማለትም ኃጢአትና ሰይጣንን አላየም፣ መበስበስ የሆነው ኃጢአትና ሰይጣን አልቀረቡበትም ማለት ካልሆነ ምስክርነታችን እውነታነት የለውም። ዱሮ ሆኖ ያለፈውን ታሪክ ከመጽሐፍ ንባብ አግኝተን ከምናወራ በስተቀር ማለት ነው። ይህም ከሕይወታችን ውጭ የተከሠተውን ታሪክ ስናወራ፣ ስንሰብክ የሰይጣን ወንጌል ነው የምንሰብከው ማለት ነው። የክርስቶስ ሥጋ መበስበስን አላየም ስንል ያኔም፣ አሁንም ለዘላለምም ሥጋው መበስበስን አላየም፣ አላስተናገደም ማለት መሆን አለበት።

የኢየሱስ ሥጋ አሁን እርሱ ያደረበትና የሚቆጣጠረው ሥጋ ነው እንጂ ከማንነታችን ውጭ፣ ከዘመናት ውጭ፣ ከዕድሜአችን ውጭ በርቀት የሆነውን መስበክ ከሰይጣን ነው። የሰይጣን ትግል የክርስቶስ ታሪክ በሕይወታችን ላይ እንዳይገለጥ ማድረግ ነው። የጸሎቱና የቅድስናው ኃይል ይዋጋለት ስለነበረ ወደ እርሱ አልቀረበም። ኢየሱስ በተጻፈውና በተረዳነው መጠን እንደ ሄኖክ ከሄኖክም ይበልጥ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሆነ እንደመሆኑ መጠን እግዚአብሔርም ራሱ እሳት እንደመሆኑም መጠን መበስበስን ትልን አላየም ክርስቶስ። ውጫዊው ሥጋችን ከእግዚአብሔር ማለት ከመቅደሱ በውጭ፣ በርቀት ያለ ነውና እንኳን ሞቶና በቁመና እንኳ ብስባሽ ነው። ስለሆነ ለውጪ ውጫዊ ሲሆን፣ ለውስጡ ለማይታየውና እንዲሰቀል ለታዘዘው ሥጋ የማይታየው ውስጣዊ ትሎች ተዘጋጅተለታል። መጽሐፍ ቅዱስ የውስጥን የማናየውን ሊያሳይ፣ የማናውቀውን ሊያሳውቅ ተጻፈ እንጂ የውጩን፣ ግልጹ የሆነውን ሊገልጽ፣ የምናውቀውን ሊያሳውቅ አይደለም። ይህም እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፣ «ነገር ግን ዓይን ያላየችው፣ ጆሮም ያልሰማው፣ በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው» (1ቆሮ.2፡9)



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡ ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

እንግዲህ በውስጣችን የሞት፣ የመበስበስ፣ ሁሉ ምክንያት የሆነው ኃጢአት ማለትም የሰይጣን ሥራ ካለ የማይበሰብሰው ክርስቶስ የለም ማለት ነው፤ ስለዚህ ከሥጋ የሆነው ከውስጥ እየወጣ ይመሰክርብናል፤(መዝ.5፥9፤140፥3፤ ሮሜ 3፥13-14፤ ማቴ.12፥34-35)፡፡ (ጀርም) ምንን ያመለክታል? የእውነት እውነተኛው ውስጥን የሚያበሰብስ ጀርም (ትል) የሆነው የኃጢአት ሁሉ ምንጭ ሰይጣን ነው፡፡ ያለ ሰይጣን መትላት፣ መበስበስ፣ መግማት የለም፡፡ የእውነት እውነተኛው መበስበስ በውጭ በሰው ፊት መበስበስ ነው ወይስ በውስጥ፣ በእግዚአብሔር ፊት የሚገኝ መበስበስ ነው? ውጫዊ ትልንና መበስበስን እንጸየፋለን፤ ውስጣዊ ትልና መበስበስ በሆነው በሰይጣን አሠራርና ወረርሽኝ ተሞልተን እያለ ትልቅና ቆንጆ ሰዎች እንመስላለን፤ ዘውትርም ውሸታሞች ነን፡፡ ይህ እንግዲህ በማየት ሳይሆን በእምነት የሚነገር ንግግር ነው፡፡

ሞትን ሳያይ ተወሰደ የተባለው ሄኖክ ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ያደረገ ብቻ ሳይሆን፣ ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል አካሔዱን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረጉ በመጽሐፍ ቅዱስ ይነበባል፡፡ ክርስቶስ ኢየሱስ ግን አብና እኔ አንድ ነን፣ እኔን ያየ አብን አየ፡፡ እኔ በአብ፣ አብም በእኔ ይኖራል ብሎ እውነትን በብርሃን የመሰከረ ሰው ይልቅ እንዴት ሞትንና መበስበስን ያያል? ሰውን ከአብ ጋር አንድ እንዳይሆን በመለየት ለትልና ለመበስበስ የሚዳርገው በመካከል ያለ ግድግዳ ምን እንደሆነ? በትንቢተ ኢሳይያስ (59፥1-5፤ ም.25፥7) ተመልክቷል፡፡ በሌላ አገላለጽ ሰው ተሻግሮ ወደ እግዚአብሔር እንዳይቀርብ ይህን ግድግዳ በእግዚአብሔርና በአዳም ልጅ መካከል በወገኖች ሁሉ ላይ የተጣለ መጋረጃ፣ በአሕዛብም ሁሉ ላይ የተዘረጋ መሸፈኛ አዳም ከገነት ሲወጣ የተከናነበው የሞት ጥላ ቁርበት ነው፡፡ ይህን «ከፍጥረት እስከ ውድቀት» በሚለው መጽሐፌ በጥልቀት ተብራርቶ የሚቀርብ ስለሆነ ወደፊት የምታገኙት ይሆናል፡፡







## ክፍል ሰድስት
## በሦስተኛ ቀኑ ባዶ የሆነው መቃብር፤
## (የሥጋው መድረሻና ምንነቱ፤)

በግብፅ፣ በመጀመሪያው ፋሲካ ላይ የቀረበው እንስሳ ሥጋ ወዴት ገባ? ቢባል መልሱ ሰው በላው ከሆነ፣ ሰው እንዲበላው ለምን አስፈለገ? ሕዝቡ ከሄደበት ስደት ወደ ቤቱ እየተመለሰ ስለሆነ «...ያማቸውን ወደ ቤታቸው ባሰናብታቸው በመንገድ ላይ ይዝላሉ» ተብሎ እንደተጻፈ፣ በልተው ለጉዞው ብርታት እንዲያገኙበት ጭምር የጌታ ዕቅድ ነበር፤ (ማር.8፥1-3) ሕዝቡ ሥጋውን ሲበላው በውጭ ሜዳ በሰው ፊት በላው ወይስ በውስጥ ጓዳ በእግዚአብሔር ፊት በሰውር፣ (በቅድስና) ሥፍራ በላው? አዎን!! ሕዝቡ ወደየቤቱ ገብቶ ክፉ እንዳያገኘው በሩን በእንስሳው ደም አሽጎ በውስጥ በጌታ ፊት ሆኖ በላው፡፡

ከሥጋው እስከ ነገ የተረፈውስ ወዴት ገባ? እሳት በላው፡፡ እሳት፣ በውጭ ሜዳ በርኩስ ቦታ የሚነድድ እሳት በላው ወይስ በውስጥ ጓዳ በቅድስና ሥፍራ የሚነድድ ቅዱስ እሳት በላው? በዚህ አንፃር እሳት ምንን ያመለክታል? ምንድን ነው? ይህ ሐሳብ «ታላቁ መጋረጃ፣ ቡተሰንው» መጽሐፌ «ገሃነመ-እሳትና አድራሻው» በተሰን ክፍል በሰፋት ተብራርቷል፡፡

ሥጋውን የበላው ሰው (የዋጠው) መቃብሩ ነው ወይ? በሦስተኛው ቀን እመቃብሩ ውስጥ ሥጋው ነበር ወይ? እውስጥህ ገብተህ እይ፡፡ የሥጋው መድረሻ በሌላ ክፍል እንደ ተጠቀሰው ሥጋው በበሉት ሆኖ የመጀመሪያን ትንሣኤ በመስጠት ከግብፅ እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ ድረስ ይዟቸው ወጣ፡፡ እርሱ የንሥር ክንፍ ነውና (ዘፀ.19፥4)፡፡ የተጻፈው ምን ይላል? «በዚያ ምግብ ኃይል እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ ድረስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ሄደ፤ (1ነገ.19፥8»)፡፡

ሥጋን ጠብሶ ስለ መብላት፡- አሥራ አራት ቀን (ዘፀ.12፡6) (ሁለት ሰባት) ታሥሮ የተጠበቀ እንስሳ ሥጋ ነው ለመሠዋዕት የቀረበው፡፡ እንስሳው ምን በደል ፈፅሞ ነው እጥፍ በእጥፍ የታሠረው? ሥጋ ካልታሠረ አይቀደስም፡፡ የዚህ ሥጋ በገመድ ተጠፍሮ፣ ታሥሮ ለግዱ ሳይቀደስ ተቀድሷል ወይስ ፈቅዶ፣ በደስታ፣ በእልልታ፣ በፍቅር ታሥሮ ነው የተቀደሰው? ሥጋን ከእግዚአብሔር ሕግ በስተቀር በሰንሰለት፣ በእግር ብረትም ቢሆን ማንም ሊያሥረው እንደማይችል፤ (ማር. 5፡1-5} ይነበብ መንፈስም ቢሆን በፈቃዱ ካልሆነ በአዲስ ገመድ፣ ባልደረቀ ጠፍር፣ በተገመደ ድር ማንም ሊያሥረው ከቶ እንደማይችል የተጻፈው ይታይ፣ (መሳ. 16፡1-21) ሥጋ ምን ስለሆነ ነው የሚታሠረው፣ የሚገደለው፣ የሚጠበሰው፣ የሚታኘከው፣ የሚበላውና የሚዋጠው? ምን ተቃዋሚዎች ቢነሡም ሥጋ ሰይጣን ነው፡፡ እንዲሁም ደግሞ ይህ እንስሳ «ሥጋ» ሰይጣን ስለሆነ ወለ-ምን አሥራ አራት ቀን ቢታሠርም፣ ምን ቢታረድም በእሳት ተጠብሶ እስኪጠመቅ ድረስ፣ ድብን ተደርጎ እስኪታኘክ ድረስ፣ ተማምኖ ሊዋጥ፣ አጅሬ ተዋኸዶ ጤና ሊሰጥ (ሰይጣን) አይችልም፡፡ ነቢዩ ሙሴ በጥጃው ጣዖት ላይ ምን ዓይነት እንደወሰደ በዚሁ መጽሐፍ አመልክቻለሁ፡፡ ሥጋው የሚበላው ለምንድን ነው? ሥጋው ማለት ሰይጣኑ የሚበላው አካልህ (አንተውኑ) ሆኖ ስለሚቀር አካል ነውና ልትቆጣጠረው (ልትገዛው) ይቀላል፡፡ አሁን ራስህን ትገዛለህ፡፡ ሰይጣን ስለተጠበሰ፣ ስለተበላ ቀርቶ በገኘነም እንኳ ማገዶ ሆኖ ይኖራል እንጂ ጨርሶ ይጠፋል ወይ? ስለዚህ ምን ይሻላል? መልሱን ፈልጉ፡፡

ከሥጋ ስለማይለይ ሥጋ አይቀደስም፡፡ ሥጋን በእሳት ድብን አድርጎ ጠብሶ፣ አቃጥሎ፣ እኝክ አድርጎ ቆርጥሞ መብላት የእግዚአብሔርን ቁጣ በጠላቱ ላይ መግለጥ ነው፡፡ እሳት ማለት ቁጣ ሲሆን፣ መጥበስ ቁጣን መግለጥ ማለት ነው፡፡ መብላት፣ መቆርጠም፣ ድብን አድርጎ ማድቀቅም ቁጣ መግለጥ ነው የሚል መልስ አቀርባለሁ፡፡ እሳት የሆነውንና ምህረት





የሌለውን የእግዚአብሔርን ቁጣ በሰይጣን ላይ አለመፈጸም ያን ቁጣውን ወደ ራሳችን አዞርን ማለት ነው፣ ለምሳሌ፣ በሳዖል ላይ ተጭኖ የተላከው የእግዚአብሔር ቦምብ ሙሉ በሙሉ በአማሌቅ ባለመፈንዳቱ የቀረው መልሶ ሳዖልን በላው፤ ይህ ከሰማሁት ቦምብ ጣይ አይሮፕላን አሠራር ጋር ይስማማል፡፡ በተቃራኒው ደግሞ የእግዚአብሔርን የቁጣ እሳት እንደሚገባ ጨርሶ በማራገፍ በልዩ የእግዚአብሔር ቃልኪዳን ውስጥ የተጠቃለለውን የአሮንን የልጅ ልጅ የፊንሐስን ተግባር ደግሞ እናስታውሳለን፡፡ 1ኛ ሳሙ.15፡10-23፣ ዘሁ.25፡7-13፡፡

አስቲ ሥጋህን በጌታ ትዕዛዝ መሠረት ለአሥራ አራት ማለት ሁለት ሰባት ቀን በነፃነት እንደ ፈለገ የትም ከሚቦርቅበት ወደ ቤት አስገብተህ የፍጥኝ አሥረህ አቆይተህ ለእግዚአብሔር አቅርብ፤ ሕያው፣ ቅዱስ መሥዋዕት ይሆንልሃል፡፡ ተቃዋሚዎች እያሉም ሥጋ ሰይጣን ነው ብያለሁ፡፡ ሥጋን ማሠር ሰይጣንን ማሠር ነው፡፡ ያለ ሥጋ ልበለና እንደ ልማድ፣ ያለ ሥጋ ሰይጣንን ከነፋስ የባሠውን በአየር ላይ የተበታተነ ረቂቅ ነገር እንዴት አድርገህ ይዘህ ማሠር ትችላለህ? ሰባት ቀን ማለት ቅዱስ ቀን ማለት መሆኑን (ዘፍ.2፡2-3) የፍጥረት መደምደሚያ ታሪክ ያሥረዳል፡፡ በቤት ተዘግቶ መታሠር የጾም ጸሎት (ቅድስና) ነው፡፡ ክርስቶስ ሁል ጊዜም በሰውና በእግዚአብሔር ፍቅር ራሱን በራሱ የታሠረ ቢሆንም በውጭ በፊደልም ታሥሮ ለመሥዋዕት ቀርቧል፡፡

በሦስት ቀን ውስጥ ከመቃብር የጠፋ ሥጋ? የሦስተኛው ቀን የእሁድ ለት ጥያቄ ነው፤ እስከ ዛሬ ድረስ የቀጠለ፡፡ መቃብር ምንድንነው? መቃብር ማለት በሐሰት እውነቱና በእውነት እውነቱም ደረጃ ሲታይ፣ የሙታን አጥንት፣ ርኩሰትም የሞላበት (ማቴ.23፡27፣ ሉቃስ 11፡44) ጉድጓድ ነው፣ ይህ በውጭና በውስጥ፣ በፊደልና በመንፈስ ነው፡፡ ውጫዊው የውስጣዊው መንፀባረቅ፡፡ ያአዳም ልጅ ሁሉ የኃጢአቱን ዋጋ ሞትን እንዲከፍል የተፈረደበት ባለዕዳ ስለሆነ ከሄኖክና ከኤልያስ በስተቀር ከአካል ሞት

በኋላም ወደ ወህኒ ይወርዳል፤ ከባላጋራው ጋር በመንገድ ጉዞ ላይ እያለ አልታረቀምና፤ «አብረኸው በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋራ ፈጥነህ ተስማማ፥ (ታረቅ) ...»፤ (ማቴ.5፡25-26) ወህኒው ይህ ያልታወቀው ስውር መቃብር ነው፡፡ በሰው ዘንድ የሚታየው ውጫዊው ግልፁ አካል እየታየ ገብቶ የሚቀበርበት ውጫዊው ((ፊደላዊ ((ፍጥረታዊ)) መቃብር ለእውነት እውነተኛው መቃብር መንፀባረቅ {Illustration} ነው፡፡ ዋናውና የእውነት እውነተኛው መቃብር ግን ዳኛው ለሎሌው፣ ሎሌው ወደ ወህኒ የሚያስገባበት ቁም መቃብር ነው፤ (ኢዮብ 34፡22፣ መዝ.88፡5-6፣ ኢሳ.9፡2፣ ዮናስ 2፡3-4) ይመሰክር፡፡

ሄኖክና ኤልያስ በመንገድ ገና ጉዞው ላይ እያሉ ከባላጋራቸው ጋር የታረቁ (የተስማሙ) ስለሆነ በዕዳ ለሎሌው አልፈው አልተሰጡም ወደ ወህኒም አልወረዱም፣ ፡፡ ከባላጋራ መታረቅ ማለት እንደ ገኸዱ ዓለም ሥርዓት ይቅርታ ተደራርጎ ወደየቤት መግባት ሳይሆን፣ በባላጋራው ጉያ ሙሉ በሙሉ ገብቶ መሸጎጥ ነው፤ የራስን ዕድፋሙን፣ እንደ ደም የቀላውን ልብስ አውልቆ እንደ ባዘቶ በነፃው በባላጋራው ካባ መሸፈን ነው፤ (ኢሳ.1፡18፣ እና ዘካ.3፡1-5) ይመሰክር፡፡ ሄኖክንና ኤልያስን የተከተሉ ሙሴና አሮን አሉ፤ አሮን በመንገድ ጉዞ ላይ ከባለጋራ ጋር ይበልጥ፣ ሙሴ በመጠኑ ስለተጋጩ በልዩ ወህኒ ቆይተዋል ነገር ግን ሙሴ ከኤልያስ ጋር እኩል በጌታ ክብር ተገልጧል፡፡ ኤልያስም በመንገድ ላይ እያለ በጥቂቱ መጋጨቱ ይነበባል፡፡ ክርስቶስም አምላኬ፣ አምላኬ ለምን ተውኸኝ ያለው በዋስትና ምክያት ከልዩ ባላጋራው ጋር ተጋጭቶ ስለነበረ በመስቀል ላይ ሦስት ሰዓት፣ በሲዖል ውስጥ፣ ሦስት ቀን ወዳልሞላው ወህኒ ወረደ፣ መውረዱ ለጥቅም ሆነ እንጂ፡፡ ነገር ግን «ሎሌው» የሙሴን ሥጋ በዕዳ ለመያዝ ፈልጎ ከመላእከት አለቃችን ጋር ክርክር ማንሣቱ በይሁዳ መልእክት (9) ላይ ተጽፎ ይነበባል፡፡ ሙሴ፣ እነቆሬ፣ ዳታን፣ አቤሮን የንን በመንገድ ጉዞ ላይ ባላጋራቸው ከሆነው



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ እፌ አሂልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16



መሪ ጋር ስላልተስማሙ ከነቤተሰቦቻቸውና ከንብረታቸው ሁሉ ጋር ወደ ወህኒ እንዲወርዱ ለሎሌው አሳልፎ ሰጥቷቸዋል፤ (ዘኁ.16፡1-) ጳውሎስም እንዲሁ በጉዞ ላይ ስላልተስማሙ ሄሜኔዎስንና እስክንድሮስን ለሎሌው አሳልፎ ሰጥቷቸዋል፤ (1ጢሞ.1፡19-20፣ 1ቆሮ.5፡5)

አንባቢ ወገኔና እኔ በመንገድ ላይ በጉዞ ላይ ነን ወይስ (ጉዞ) ጨርሰናል? እንዲህስ ቢሆን የምንጓዘው ከባላጋራ ጋር ተስማምተን (ታርቀን) አካሉ ሆነን ወዳጃችን አድርገነው ነው ወይስ እየተጋጨን ባላጋራው ባላጋራ ሆኖብን እያለ ነው? ድንገት ለሎሌው አሳልፎ ሰጥቶን ወህኒ ወርደን ይሆን? ወህኒው በፊደል ካንተ በውጭ ሜዳ ላይ ነው ብለህ እንዳታስብ በውስጥህ ነው፡፡ ብርሃንን፣ (እግዚአብሔርን) በማናይበት ሁኔታ መኖር ነው፡፡ በውጩ ሜዳ (በፊደሉ) ወህኒ በሰው ፊት ከመታሠርና በውስጡ ጓዳ (በመንፈሱ) በጌታ ፊት ወህኒ ከመታሠር የትኛው የከፋ ነው? ወህኒ ማለት ምን ማለት ነው? ጨለማ አይደል? ታዲያ፣ እርሱ በብርሃን እንዳለ እንዲሁ በብርሃን ትመላለሳለህ ማለት ነው ወይ? አለዚያ በወህኒ ነና! ለምን ጥቅም እንዋሻለን? ይህ የማይታየው የእውነት እውነቱ የዘላለም ወህኒ ሲሆን፣ የሚታየው የጊዜው የሐሰት እውነቱ ወህኒ ነው፡፡ በወህኒ ውስጥ ከተገኘህ በዕዳ ተይዘህ በእውነት እውነተኛው መቃብርህ ውስጥ ነህ፡፡ ያልሞተ ሥጋ፣ ያልሞተ ሰይጣን ስለሆነ ሥጋ በሕይወት ካለ ሰይጣንህ በሕይወት አለ፡፡ ጥምብ የአሞሮች መሰብሰቢያ እንደሆነ እንዲሁ ሥጋ የአጋንንት መሰብሰቢያ ነው፡፡ ክርስቶስ አጋንንትን በሥጋው ሰብስቦ ነው ገደል የከተታቸው፣ ምሳሌውን (ከማር. 5፡1-20፣ ሉቃስ 8፡27-39) መመልከት ይቻላል፡፡

መቃብር እንደ ዳዊት ዓይነት አመፀኛ ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን አልፎ የሚሰጥበት የጨለማው ግዞት መሆኑን እናስታውስ፡፡ መዝ. (88)፡5-6 ንጉሡን (እግዚአብሔርን) ያላየ ሁሉ በዕዳ ምክንያት በጨለማ የቁም ግዞተኛ ነው፤ የመጨረሻዋን ሳንቲም ሳይከፍል ከዚያ ከቶ አይለቀቅም፡፡



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ እፌ አሂልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

ንጉሡን እግዚአብሔርን ያላየ ሁሉ በጨለማ የሆነው የጌታ ገንዘብ የሆነችውን የመጨረሻዋን ሳንቲም ያልከፈለ ሁሉ ስለሆነ አሁን በወህኒ ይኖራል፣ አሁን ተፈርዶበታል፤ (ዮሐ.3፡18-19።) አሁን ቢከፍል አሁን በምህረት ይወጣ ነበር፤ (ማቴ.25፡14-30) ይመሳከር። ዘመኑ የተለወጠ ነው፤ አሁን በአዲስ ኪዳን ነገር ሁሉ በቀጠሮ ሳይሆን ፍርድ ሁሉ በቁመና አሁን ያለቀ ነው። መለኮታዊ ሥራ ሁሉ በራስ ውስጥ እንጂ ከራስ ማንነት በውጭ ይሆናል ብሎ በግምት መጓዝ ከሰይጣን ነው።

ይህ፣ ምድርን የሞላ ያልሞተ ሥጋ ሁሉ ባለዕዳም መንገደኛም እየሆነ ከባላጋራው ጋር አልታረቀም፤ ለሎሌው አልፎ የሚሰጠው መቼ ነው? ለሎሌው አልፎ የሚሰጠው በቀጠሮ ወደ ፊት ሳይሆን አሁን በብርሃን ያልሆነ ሁሉ በወህኒ ነው። በጨለማ ከሆነም፣ ለሎሌው አልፎ የተሰጠ ነው። እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን የማይመላለስ ሁሉ በጨለማ ወህኒ አይደለም ማለት እጅግ ከፍ ያለ ስህተት ነው። ተጨባጭ፣ አካል ሰውነት የሚጋዝበት የፊደል ወህኒ ካልሆነ አያስደነግጥም? ስሜትም አይሰጥም አይደል? አያስደነግጠውም፣ ስሜት አየሰጠውም እንጂ ሰው ሁሉ በቁም እሥር ቤት፣ በእውነት እውነተኛው መቃብር ውስጥ ጨለማ በሎሌው ቁጥጥር ሥር ይገኛል። ይህንን በመካድና ያልደረሰበት በማስመሰል ከሚኖር በስተቀር። አስመሳይነት ያጋንንትና የአገልጋዮቹ፣ የጠንቋዮች ሥራ ነው። ኢየሱስ በራሱ ባለዕዳ ባይሆንም ዋስ ሆኖ የለበሰውን ሥጋ ከመቀበሩ በፊት በመስቀል ላይ በሦስት ሰዓት ውስጥ ፈጽሞ በመሞት ፈጽሞ ከፍሏል፤ (ዮሐ.19፡34-35) እንደሚገልጠው፣ ሎሌው፣ ዕዳውን ፈጽሞ መከፈሉን ለማረጋገጥ በጦር ጎኑን በመውጋት አረጋግጧል። ይህንም ያየው መስክሯል ምስክሩም እውነት እንደሆነ ያውቃል፤ ለዘላለሙ አሜን። አሁንም ዕዳውን የጨረሰ ቢሆንም ባለመታመኑም ደግሞ ወደ ወህኒ ቢያወርዱትም የባሰውን ቀድሞ በዕዳ ምክንያት በወህኒ ለነበሩ እሥረኞቹ ዕዳ ከፋይ ሆኖ ነፃ አወጣቸው። ይህ አነጋገር በማየት



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡ ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16



ሳይሆን በእምነት፣ በፊደል ሳይሆን በመንፈስ እውነት ነው። የኢየሱስ ሥጋ፣ እንደ ቁርስራሽ የማይጠፋ (ዮሐ.6፡12) መድኃኒት ስለሆነ፣ በዚህ ሁኔታ መድኃኒትና ሕይወት ሆኖ አለቀ። እርሱ የተሳከበትን ይፈፅማል እንጂ በከንቱ ወደ ላኪው አይመለስም፤ (ኢሳ.45፡23፣ ም.55፡10-11) ተልእኮውን ሳይፈፅም የማይመለስ «ቃሉ» ክርስቶስ ነውና።

በመሠረቱ የኢየሱስ ሥጋ፣ በእግዚአብሔር ቅድመ ዕውቀቱ ታቅዶና ተዘጋጅቶ ለሰው ልጆች ሕይወት መሥዋዕት ሆኖ ሊቀርብና የበሉትን ሙታን ማሥነሻ (መዝ.40፡6፣ ዕብ.10፡5) ሆኖ ከሰማይ የወረደ፣ ሕይወትን የሚሰጥ (ሕያው) እንጀራ እንጂ እንደ ተለመደው ሞቶ ተቀብሮ እንደሚቀር በሰው ዘንድ ሥጋ ተብሎ የሚጠራው ሥጋ ዓይነት አይደለም። የአፈርን አካል «ሥጋ» ብለን ስለምንጠራ ግራ ተጋብተናል የሰው አፈር አካልና ደሙ ለሰው መብልና መጠጥ ሆኖ ያውም በሰገነት ከፍታ ፎቅ ላይ ወጥቶ ሊቀርብ ከቶ አይችልም። ኢየሱስ ያቀረበው አፈሩን አካል ሳይሆን ከሰማይ የወረደ ሥጋውን ሐሙስ ማታ በሰማያዊ ሥፍራ (ኤፌ. 1፡21፣ ም.6፡12) ሰገነት ከፍታ ራት ላይ ከነደሙ ለሕያዋን (በሕይወት ላሉት) አቅርቦ ተበልቷል፤

ነገሩ መንፈሳዊ ሆኖ ረቂቅ በመሆኑ ለመረዳት ብንጠያየቅ፤ ሰገነትን እንዴት እንመለከታለን? ሰገነቱ ቤት ከሆነ የየት አገር ቤት ነው? እስራኤል ቅዱስ (ልዩ) ሕዝብ መሆኑን አስታውሰን፣ አጠቃልለን ስንመልስ ይህ ፋሲካ የተበላበት ሰገነት፣ የአሕዛብ ቤት ሳይሆን የእስራኤል ቤት ከመሆኑም፣ የምድር ቤትም ሳይሆን ከምድር ከፍ ያለ በሰማይና በምድር መካከል ከፍታ ላይ ይበልጥ ተቀድሶ የተሠራ የእስራኤል እንግዳ ቤት ነው። የእስራኤል ቤት ከአሕዛብ ቤት እንዴት ያለያል? ቢባል፣ እስራኤል የቁልፈቱን ሥጋ በስለት ተገፍፎ ወደ እግዚአብሔር ፊት ሊወጣ የቻለ ሕዝብ ነው። ቤታቸውም ያልተገረዘ አሕዛብና ውሻ የማይገባበትና እንደ እነርሱም ቅዱስ የሆነ ነው። ራቱ



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡ ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

ላይ ሲበላ የተረፈው ወዴት ገባ? እንደ ተጻፈ፣ ለሙታን ሕይወት ሆኖ ወደ ምድር ታችኛ ክፍል ወደ ነበሩት ወርዷል፣ (ኤፌ.4፥8-10፣ 1ጴጥ.3፥18-19) ማሥነሻ ነውና፣(ወሀኒ) ለሚለው አሳብ ከ(ማቴ 5፥25-26) ጋር ም.18፥21-35/ ወደ ብርሃን አውጥተን እንመልከተው፡፡

«ወሀኒ» በእስራኤል፣ በእስራኤል ዘመን ወሀኒ መቃብር (ታችኛው ጉድጓድ) ነው፤ (መዝ. 88፥6) ማለት ወደ ጨለማ መውረድ፡፡ ሰው ሁሉ በየደረጃው ዕዳ አለበትና የመጨረሻዋን ሳንቲም ለመክፈል ለእሥራት ወደ ወሀኒ (መቃብር) ይወርዳል፡፡ በሙታን ሥፍራ፣ (በወሀኒ) ሆነው አቤቱታ አቅራቢዎችም ነበሩ ብቻ ሳይሆን፣ አሉ፤ (ሕዝ.37፥1-14፣ ራዕይ 6፥9-11፣ ዮናስ 2፥2-11፣ መዝ.88፥6) ጴጥሮስ እንዳመለከተው በመንፈስ ሕያው ይሆን ዘንድ በሥጋ ሞተ፤ ካለ በኋላ፣ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወሀኒ ለነበሩ ነፍሳት ሰበከላቸው ይላል፡፡ ክርስቶስ በሥጋ በመሞቱ ዕዳቸው የመከፈሉን ብሥራተ ወንጌልን በመንፈስ አሰምቶ ከወሀኒ ማስወጣቱ ይታያል፡፡ ክርስቶስ ሞተ ማለት እንደ ግንዛቤአችን ሳይሆን ኃጢአትን ተበቀለ፣ ገደለ ማለት ነው፡፡ አለዚያ እርሱ በተለየ ቦታ ከወንዝ ማዶ ሞቶ እንዴት! ከነ ኃጢአትህ ትድናለህ ማለት ነው ወይ? እንዲህ ከቶ አይደለም፤ ፎቅ ቤት ሲደረመስ በውስጡ የተገኘውን ሁሉ ይዞ እንደሚደመሰስ እርሱ ሲሞት ገድሎህ ይሞታል፤ ማለት ሳይሆን፣ በማንነትህ ሞቶ ይገድለሃል፤ እንደ ድሮ ኮሶ መድኃኒት ከኃጢአትህ ያሽረሃል፣ ያጠራል፡፡ በሞቱ ኃጢአትህን (ሰይጣንህን) ገድሎልሃና ሊከሠሥ አይችልም፡፡ አንተ ኃጢአትህን (ሰይጣንህን) ልትገድል ትፍጨረጨራለህ፣ ነገር ግን ከእርሱ ጋር ጣምራ የሆነ ሞት መሞትን ስለምትፈራ (ዕብ.2፥15) ልትገድለው አልቻልክምና ስለዚህ ኢየሱስ ምትክ ሆኖ ሞትህን በሞቱ ሞቶ ገዳይህን ካንተ ጋር ገድሎ ግድያውን አብልቶሃል፡፡ ለዚህ ምሳሌ ምንድን ነው? የአሮንን ጥጃ ሙሴ እንዳደረገ፣ ሳምሶን አንበሳውን ወደ ማር፣ የሚበላውን ወደ መብል እንደ ለወጠ፣







ገዳይህ የነበረውን ገድሎ የበላህን አብልቶሃል፡፡ አውሬ በመልክ አውሬ ሳይሆን አውሬነቱ በመንፈሱ ነው፡፡ ለሰው ሁሉ እንደ ለመለመ ቡቃያ መብል ሆኖ ተሰጥቶ ነበር፤ (ዘፍ.9፥3) በእግዚአብሔር አስተዳደር ውስጥ ሁሉ መብል ነው፤ የሚገድል ነገር እንኳ ቢጠጡ አይጎዳቸውም ተባለ፣ (ማር.16፥17) እባቡ አይነድፍም፣ እሾኹ አይወጋም፣ እሳቱ አያቃጥልህም፣ ነበልባሉም አይፈጅህም፡፡

የሄኖክ፣ የሙሴና የኤልያስ ሥጋ ወዴት ደረሰ?

(ማስገንዘቢያ፤) አንተ/ች በጥምቀት ስትቀበሩ ሥጋችሁ ወዴት ገባ? በጥምቀት የተቀበርነው ቀብረነው ለመውጣት አይደለም ወይ? በእግዚአብሔር መንግሥት ሊኣው ሰው የሌላን ሰው ሥጋ አይቀብርም ባለቤቱ እንጂ፡፡

ሔኖክ ሸለፈቱን (የሥጋ ቁልፈቱን) በሕይወቱ በራሱ ፈቃድ ማስወገዱ ሞቶ ወደ መቃብር ጉድጓድ ከመውረድ አድኖታል፤ ማለትም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ማድረጉ ነው፡፡ ሸለፈቱ ወደ እግዚአብሔር በቀረብን መጠን ከኛ ይሸሻልና፤ (ያዕ.4፥7-8) ከፍ ብሎም ሥጋ ሰይጣን እንደሆነ ተመልክተናልና፡፡ ሸለፈቱ በእኛና በጌታ መካከል የመኻል ግድግዳ ነው፤ (ኤፌ.2፥14-15) ጌታን ለመልበስም ማውለቅን ይጠይቃልና፤ (ገላ.3፥27) ሙሴና ኤልያስም ሄኖክን ይከተላሉ፡፡ በ(ዘፍ5፥24) ላይ ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘምም፣ የሚለው ዘመኑ እንደሚፈቅደው፤ የሚታይ አካሉ በንኖ ጠፋ ማለት ነው፡፡

ለዚህ አሳብ ምሳሌ የሆኑ ምሁራን ሲናገሩ የሰማሁትን ላስታውስ፣ ምድር አሁን ከምትሽከረከርበት ዛቢያ ትንሽ ወደ ፀሐይ ፈቀቅ ካለች ፀሐይ ምድርን ከነባሕር ውቅያኖሱ፣ ከነእንስሳ አራዊቱ፣ ከነተክሎቹ፣ ከነሣር ቅጠሉ ወደ ራሷ ስባ ስለምትውጥ እንዲያውም ከግለቷ ኃይል የተነሣ ምድር ገና ወደ ፀሐይ ከመድረሷ በብዙ-ብዙ ማይል ርቀት እየለች

ሁሉም ነገሯ በኖ ጪስ ሆኖ ይጠፋል ነው ያሉት፡፡ እግዚአብሔር ማንም ሊቀርበው የማይችል (1ጢሞ. 6፡16) እንደ መሆኑ ዓይነት፣ እንዲሁም ፀሓይ የእሳት፣ ረመጥ ከመሆኑ የተነሣ ምንም ነገር የማይቀርበው ሆኖ የእግዚአብሔር ምሳሌ ነው፤ ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም፣ ሄኖክ ሊታይ ወደማይችለው እግዚአብሔር ቅድስና ውስጥ ገብቷል ማለት ነው፡፡ ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፣ ማለት ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል ከፍ በሚለው እግዚአብሔር መንገድ ተጓዘ (ተመላለሰ) ለማለት እንችላለን፤ (ኢሳ.55፡9) ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ ሲባል እግዚአብሔር የፍቅር እሳት ስለሆነ አካሄዱን ከዚሁ እሳት ረመጥ ጋር አደረገ በተጨማሪ ማለት ይቻላል፤ ሥጋው በዚህ ፍቅር እሳት ሕያው መሥዋዕት ጢስ (መንፈስ) ሆኖ በኖ ወደ እግዚአብሔር አካል አንድነት ገብቷል ማለት ይሆናል፤ በነበረው ዘመን፡፡ እግዚአብሔር በፍቅሩ እሳት ኃይል ስቦ ወስዶ ውጦታል፡፡

ሄኖክ እግዚአብሔር ወስዶታልና ያልተገኘ ከሆነ ኢየሱስስ እንዴት ይገኛል? እግዚአብሔር ወስዶታልና "አልተገኘም" ማለት ሌላው ጎኑ መልስ አይሆንም ወይ? ማለት እግዚአብሔር አይገኝም (አይታይም) ማለት  አልታየም ከሰው እይታ ጠፋ ሙሴም ተራራ ሲወጣ እየታየ ሄዶ ከእይታ ጠፍቷል፣ ኤልያስም፤ ኢየሱስም ሲወሰዱ ከእይታ ጠፉ፡፡ የሄኖክ ሥጋ በ(1ኛቆሮ.15፡54) እንደሚያሥረዳው በቅጽበት ዓይን ስለተለወጠና ወደ እግዚአብሔር ምንነት እንደገባ ነው የሚታየው፡፡ ስለሆነ ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ማስማማቱን፣ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አለመመላለሱን ከጌታ ጋር የአንድነት ፀር የሆነውን የመኻል ግድግዳ (አሮጌውን ሰው) ያስውገደ መሆኑን ያመለክታል፡፡ እንዲህ ሲባል፣ ሰው አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ካደረገ በመንፈስ ስለሚሆን በሥጋ ማለት በ(ገላ.5፡19-20) በተዘረዘሩት የሥጋ ሥራዎች በሥጋ አይታይም ማለት ነው፤ እናስተውል፡፡





ከዚህም ሌላ በ(ሮሜ8፡6-8) የሥጋ አሳብ ሞት ነው፣ ከእግዚአብሔር ጋር ጥል ነው፣ በሥጋ የሚመላለሱ እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙ አይችሉም፣ ስለሚል ሄኖክም ከመወሰዱ አስቀድሞ ከነዚህ የሥጋ አካሄድ በመራቅ እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ (ዕብ 11፡5-6) የተመሰከረለት ነው፡፡ አሁን፣ አንተ/ቺ እኔ በተጻፈው መሠረት ክርስቶስን ከለበስንኮ ተሰወርን፣ ክርስቶስ ይታያል እንጂ እኛ ጠፋን፣ እኛ ጠፋን ሕይወታችን በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሯል፤ (ቆላ.3፡3) ክርስቶስ ይታያል፤ ክብር፣ ምሥጋና፣ ውዳሴ ለእርሱ ይሁን ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

ሙሴ፣ ሩጫውን በጨረሰ ጊዜ በእርሱ ላይ የነበረውን ክብር በኢያሱ ላይ ጭኖ በደከመ ጉልበቱ (በ120 ዓመት ዕድሜው) በእምነቱ ኃይል ወደ ተራራው ወደ እግዚአብሔር እንደ ወጣ በ(ዘዳ.34፡1፣ 5-6) ላይ ተገልጿል፣ ሙሴም ሀሮንም ወደ ተራራ ወጥተው መሞታቸው ከዓለም ርቀው፣ «ከዓለም ከመጀመሪያ ትምህርት ርቃችሁ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ...በዓለም እንደምትኖሩ ስለምን ትገዛላችሁ?...» (ቆላ.3፡20-22) ከፍ ብለው በክርስቶስ (በሰው ልጅ) ላይ ወጡ፣ በሱ ላይ ሞቱ፤ ተራራው ወደ አብ እግዚአብሔር መሄጃ መንገድ ክርስቶስ ነውና፤ (ዮሐ.14፡6፣ ም.1፡52፤) ይህም ባየር መነጠቅ ነው፡፡ ይህ ዓለምን መተው (ትንሣኤ) ማለት ስለሆነ የሚያስደንቅ ነገር አይደለም፣ (በዕብ.12፡22፣ ከኤፌ.2፡6-7፣ እና ከቆላ.2፡11-12፣ 3፡1) ጋር ስንመለከት በክርስቶስ ሞት የተጠመቁትን እንደተነጠቁና ወደ ፅዮን ተራራ በክርስቶስ በአብ ቀኝ እንደተቀመጡ ያመለክታልና፡፡

ሙሴ በተራራ ወደ ተራራ ራስ ወጣ ማለት በክርስቶስ ወደ ክርስቶስ ማለት ራስ ወደ እግዚአብሔር ወጣ ማለት ነው፤ የክርስቶስ ራስ አብ ነውና (1ቆሮ.11፡3)፡፡ ወደ እግዚአብሔር መውጫ ተራራ (መሰላል) ክርስቶስ ነውና፤ .(ዘፍ.28፡10-17፣ ዮሐ.1፡52፣ 14፡6) ሙሴ በክርስቶስ ተወሰደ፤ የሙሴ የቀብር ሥነ-ሥርዓት፤ «የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴም

እንደ እግዚአብሔር ቃል በዚያ በሞዓብ ምድር ሞተ፤ በቤተ-ፌጎርም ፊት-ለፊት በሞዓብ ምድር በሸለቆው ውስጥ ተቀበረ፤ እስከ ዛሬም ድረስ መቃብሩን ማንም አላወቀም፤ ዘዳ.34፡5-6»፡፡ የዚህ ትርጉም የጌታን ሥጋ መድረሻ ቢመለከትም ሥጋው ወዴት እንደ ተወሰደ፣ የእኔ፣ የአንተ/ቺ አሮጌው ሥጋ ወደ ሸለቆው ወርደን በጥምቀት ስንቀበር (ጥምቀቱ እውነተኛ ከሆነ) ሥጋችን የደረሰበትን ከሰው ማንም ያውቀዋል ወይ? የእውነት እውነቱ መቃብር ይህ ነው፤ እግዚአብሔር ቀብሮታልና ከሰው ማንም አያውቅም፡፡ የሙሴን ሥጋ እግዚአብሔር ቀበረው ማለትም (ቆላ.3፡3) እንደሚያሳየው የሙሴ ሕይወት በእግዚአበሔር ከክርስቶስ ጋር መሰወሩን (መዋጡን) ሲሆን፣ በ(ማቴ.17፣ 1-8፣ ማር.9፣ 2-8፣ ሉቃስ 9፡28-36) ላይ እንደተገለፀው ጌታ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብና ዮሐንስን ይዞ ወደ ረጅምና ታላቅ ተራራ በወጣበት ጊዜ ሙሴ ከኤልያስ ጋር በክርስቶስ ክብር ተገልጧል፡ ለዘላለሙ አሜን፡፡ ገላጩ፣ ብርሃን መጋረጃ አሰወጋጁ ክርስቶስ ነውና፡፡

ኤልያስ፣ ኤልያስም እንዲሁ የኃይሉንና የክብሩን መጎናፀፊያ ቀጥሎ ሊያገለግል ላለው ኤልሣዕ ሁለተኛ ጊዜ ጥሎለትና አሥረክቦ መወሰዱን (2ነገ.2፡13-14) ያስረዳል፤ በእሳት ሠረገላ ማለት በእሳት ተጠምቆ መሄዱ ነው፣ (ማቴ.3፡11-12፣ ሐሥ.1፡5) እዚህ ላይ በእሳት የሚያልፍና በውኃ የሚያልፍ ነገር አለ፤ (ዘኍ.31፡21-23) አካል (ሥጋ) በውኃ፣ መንፈስ ደግሞ በእሳት ያልፋል፡፡ «እዚጋ በእሳት ተጠምቋል ሲባል የምንጨብጠው ነጥብ ምንድን ነው? የኤልያስ ሥጋ» በመጨረሻ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው ቅዱስ መሥዋዕት ሆኖ (ሮሜ12፡1) በመንፈስ ቅዱስ እሳት (ፍቅር) መቅረቡን፣ እናያለን፡፡

«ኤልያስ» ሠረገላውም እሳት፣ ፈረሱም እሳት ለሆነ «እሳት» ቀርቧል፤ .(2ነገ.2፡11)፤ እውነት ነው፤ የኤልያስ ጸሎቱም ተፈጸመ፤ (1ነገ 19፡4) አመዱ መጎናፀፊያው ነው፡፡ ኤልያስ በጸሎቱ ነፍሴን ውሰዳት አለ እንጂ







ሥጋዬን ውሰድ አላለም፤ ኤልያስ እንዲሞት ለመነ ፣ ግን እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ እንደ ሰው ሳይሞት በእሳት ጥምቀት ወሰደው፡፡ እግዚአብሔርን ውሰድ ማለት እሳትን ውሰድ ማለት ነውና ቀልድ የለም፡፡ አንባቢ በእውነት ሲጠመቅ ይህን አመለካከት በሕይወቱ ተፈጽሞ ያገኘዋል፡፡

በሙሴ ሕግም ሥጋ በእሳት ነው ለእግዚአብሔር የሚቀርበው፤ በእሳት ተሻግሮ ሽታው የሥጋው መንፈስ ማለት ጪሱ እንጂ በቀጥታ ሥጋ፣ ቁስ-አከል ነገር ስለሆነ ባለጥላ ወይም ጥላ ለእግዚአብሔር አይቀርብም፤ አካል እንጂ፡፡ አካል ማለት መንፈስ እንጂ ቁስ ወደ እግዚአብሔር አይቀርብም፣ ቁስ (ፊደል) ጥላ፣ ጨለማ ፈጣሪ ነውና፡፡ እሳት ምድራዊው ሳይሆን፣ ሁልጊዜም ከእግዚአብሔር ነው፡፡ ኤልያስ ራሱ በቀርሜሎስ ተራራ ላይ ሥጋን ከሰማይ ለሆነ እሳት አቀረበ፤ እርሱ ራሱም ከሰማይ ለሆነ እሳት ቀረበ፡፡ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚሆነው እሳት ሁልጊዜም ከሰማይ (ከመቅደስ) ነው እንጂ በምድራዊ እሳት አለመሆኑን እናስተውል፡ መቅደስ (ዙፋኑ) ሰማይ ነው፡፡

ሥጋና ደም ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱምና፤ የእነ ሔኖክ፣ ሙሴ፣ ኤልያስ ሥጋ ስናስብ፣ ሥጋ ሰይጣን ማለት ሉሲፈር እንደመሆኑ መጠን ከፍ-ከፍ ከማለት ባሕሪዩ ጋር ሆኖ ከክብር ወርዶ በሕፃን ደረጃ በተዘጋጀ በር ራሱን አሳንሶና አዋርዶ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም፤ እግዚአብሔርና መንግሥቱ እሳት ስለሆነ የእነ ሔኖክ ሥጋ በዚህ ሁኔታ መሥዋዕት መሆኑ ግዴታ ነው፡፡ እግዚአብሔር የኔንም፣ የናንተንም ሥጋ በ/ማቴ.3፡11-12፣ ሐሥ.1፡5) እንደተመለከተ በእሳት ነው የሚቀበለው፡፡ ሙሴ ከመወሰዱ ቀድሞ የእስራኤልን ልጆች አርቆ ባቆመው እሳት ውስጥ ይገባ ይወጣ እንደነበረ ስለሚታይ ሙሴ በዚህ አመዱ የደረሰበት ሳይታወቅ በሚያቃጥል እሳት ቀድሞ የተጠመቀ (ዘፀ.3፡1-3፤) መሆኑ ይታያል፤ በ(ዘፀ.19፡24፣ 15-18፤)

የሙሴን ሁኔታ ከሌላው ሕዝብ ሁኔታ ጋር ስናስተያይ ከሊቀ-ካህኑም ይልቅ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሰው መሆኑ በግልጽ ይነበባል፡፡ ይህም (ዘሁ 20፡11) ... ምድርና ሰማይ ከፊቱ ሸሹ፣ ሥፍራም አለተገኘላቸውም የሚለውን ከዚህ ሁኔታ ጋር ስናስተያይ ማንኛውም በእሳት የማያልፍ ነገር ከፊቱ በንኖ ይታያል፡፡ የመንፈስ ቅዱስ (የእሳት) ጥምቀት አመዱ የደረሰበት ሳይታወቅ ሥጋን አቃጥሎ በኖ እንዲጠፋ ያደርጋል ነው፤ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አሮጌው ማንነትህ አመዱ የደረሰበት ሳይታወቅ ተቃጥሎ በንኖ ይጠፋል፤ አሜን፡

ወደ እርዕሰ-ሐሳቡ ስንመለስ፡ የጌታን ሥጋ ፍለጋ፤ በተመለከተ የነማርያምና፣ የነጴጥሮስ እይታ በጥቂት ልዩነት ተመሳሳይ ነበር ወይስ የተለያየ? የሦስቱም እይታ ወደ ውጭ-ውጭ ሜዳ ላይ ነበር ወይስ ወደ ውስጥ-ውስጥ ጓዳ ነበር? ሶስቱም የፈለጉት ከራሳቸው በውጭ እርሱ ታገኙኛላችሁ ባላለበት ትናንት በተቀበረበት ሥፍራ ነበርና ተመሳሳይ ነበር፡፡ የማርያም ፍለጋ በተመሳሳይ ወደ ውጭ ቢሆንም ግን ከነጴጥሮስ ፍለጋ የበረታ ነበርና በአንድ አቅጣጫ ብቻ የተገተረ አልነበረም፤ ወዲያና ወዲህ በመዟዟር አቅጣጫ በመቀያየር ዝቅ ብላ እመቃብር ውስጥ በማየት በለቅሶ በጩኸትም ጭምር እጅግ ፅኑ ፍለጋ አድርጋለች፡፡ ለቅሶ መሥዋዕት የተሞላ ጸሎት ነበር፡፡ የመላእክትንም፣ የጌታንም ድምፅ እስከትሰማ ድረስና እስኪረጋገጥላት ድረስ ብርቱ ነበር፡፡ ይህ ዛላለም ወደ ውጭ በማየት በአንድ አቅጣጫ ብቻ የተገተርንን ሰዎች ይገሥፃል፡፡ «ሕያው ነው!!» የሚለው ምስክር ድምፅ ከመላእክት ማለት ከፊደል ሳይሆን፡ ከመንፈስ ሲሰማ ነው እውነት የሚሆነውና የሚረጋገጠው፣ የሚያፀናን፤ ከፊደል መጽሐፍ ሲሆን ከማንነታችን በውጭ ስለሆነ ሊረጋገጥና ሊያፀናን አይችልም፤ ጥያቄም ከአእምሮ አይጠፋም፡፡ በትናንትና ቦታ፣ ትናንት በተቀበረበት፣ አምና እንጀራ በቆረሰበት፣ አቻምና ሙታንን ባስነሣበት፣ ባሕሩን በሰነጠቀበት፣ ከአመታት በፊት







ታሪክ በሠራበት ቦታ ወደ ውጭ-ውጭ እግዚአብሔርና ሥራው ከፍ እያለ ያድጋል እንጂ በነበረበት ከቶ አይገኝም፣ ጣዖት አይደለምና እንጠንቀቅ፡፡ ዮሐ.6፡23-26

ለአንባቢያን፣ የጌታ ደምና ሥጋ ለዓለም ውስጣዊ ሕይወትና ትንሣኤ ምግብና መጠጥ እንጂ (መሥዋዕትነቱ) በእግዚአብሔር ፊት ያቀረበው የኃጢአት ዋጋ (ሥጋው) ከማንነታችን በውጭ በሩቅ አገር በሌላ ዓለም፣ (በእስራኤል ምድር) በሌላ ዘመን ያቀረበው መስሎ ቢታየን ከሥረናል፡፡ ሥጋ ደሙ ሥጋችን ደማችን ሆኖ በገዛ ውስጣችን መቅደስ በእግዚአብሔር ፊት ያቀረበው ሆኖ መታየት አለበት፡፡ ሰይጣን የሰውን ልጅ የገደለው የውጭን ዓይን በመግለፅ፣ ውስጥን በማሳወር መሆኑን እናስታውስ፡፡ ትንሣኤና ሕይወት የሆነው የክርስቶስ ሥጋና ደሙ በልተነውና ጠጥተነው ሕይወትና ኃይል ሆኖ የሚያንቀሳቅሰንን፣ የሚያኖረንን በሰበዓዊ ቋንቋ ተርጉመን ከራስ ማንነታችን በውጭ ሜዳ እንደ ቁሳዊ ዕቃ መፈለግና ማሰብ፣ መተርጎም ስህተት ነው፡፡ ደግመንም ብናስብ፣ ኢየሱስ ራሱ ሊነሣ፣ ለራሱ ሊበላ፣ ለራሱ ሊጠጣ ሳይሆን ለሌሎች (ለዓለም) የሕይወትና የኃይል፣ መድኃኒትም የሆነ ሁሉ ሆኖ ሁሉን የሚችል፣ ሁሉን የሚፈጽም የአብ እግዚአብሔር እንጀራ ሆኖ ሊበላና ሙታንን ሊያሥነሣ በሽተኛን ሊፈውስ ማሥነሻ መንጠቆ ሆኖ መጥቷል፡፡

ከፍ ብሎ እንደተብራራ በሙሴ ሕግ መሠረት ግን እጅግ በላቀ እርሱ ቆስሎ አቁስሎ፣ ሌሎችን ሊፈውስ፣ እርሱ ሞቶ ገድሎ ለሌሎች ሕይወት ለመሆን መጥቷል፤ ተገርፎ ሊገርፍ፣ ተዋርዶ ሊያዋርድ፣ የክፋው ኃይል ለሌሎች ሲል አጥልቆ በቆፈረው ጥልቅ ጉድጓድ ተቀብሮ ሊቀብር (ዘፀ.21፡23-25፤ ማቴ.5፡38) ጻድቅ ፈራጅ ሆኖ መጥቷል፤ አትፍረድ ይፈረድበሃልና፡፡ ሁሉንም በሥጋው ፈጸመው፡፡ ሁሉንም በራሱ በሰይጣን

እጅ አከናወነ፡፡ በመቃብሩ ውስጥ የኤልያስ መንፍዐፊያ ከፊት ወድቆ ተገኝቷል፤ ያነሣው ሰው እንደ ኤልሣዕ ይሆናል፤ ታምራት ይሠራበታል

የቀብሩ ሥነ-ሥርዓት፤

የጌታ ኢየሱስን ሥጋ አቀባበርን በተመለከተም ከዮሐንስ ወንጌል በስተቀር በሶስቱ ወንጌሎች ሲታይ፣ በተሰቀለበት ዕለት ምሽት ላይ የአርማትያሱ ዮሴፍ ሥጋውን ከመስቀሉ ላይ አውርዶና የቀብር ጨርቅ ገዝቶ ብቻውን እንደ ቀበረው ሲታይ፣ ዮሐንስ ግን ኒቆዲሞስ መቶ ንጥር ያህል የከርቤና የእሬት ቅልቅል ይዞ በመምጣት ከዮሴፍ ጋር ሁለቱም በአይሁድ አገናነዝ ልማድ ከሽቱ ጋር በተልባ እግር ልብስ ገንዘው በኅብረት እንደቀበሩት አስረግጦ ይመሰክራል፡፡ በውስጥ ጓዳ እንጂ በውጭ ሜዳ የሚቀበር ሥጋ አልነበረም፤ ሕይወትን ሊሰጥ ሲል፣ በዘላለም ዕቅዱ ሙት ሆነ እንጂ ሙት አልነበረም፡፡ የማቴዎስ ወንጌል ግን በተለይ ጌታን የአርማትያሱ ዮሴፍ ከዐለት በወቀረው በራሱ መቃብር እንዳኖረው ያመለክታል፤ /ማቴ.27፡57-60/ ማርያም እኔ እወስደዋለሁ ስጠኝ ያለችው ትክክል ነው፡፡ ባታውቀውም ሥጋውን እንዲሰጣት እርሱን ራሱን መጠየቋ ትክክል ነበር፤ ውድና መድኃኒት ነገር፡፡ ሁለቱም ቀባሪዎች በአይሁድ ማኅበረ-ሰብ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የነበራቸው ሰዎች እንደሆኑ ታሪኩ ሲያሥረዳን፣ ሁለቱም ሰዎች በጥቂት ልዩነት ኢየሱስ በቅርብ ቀን ይሁን በርቀት ከሙታን እንደሚነሣ ተስፋ የሚያደርጉ የነቢይነት ጭላንጭል ያለባቸው ሰዎች ይመስላሉ፡፡

ኢየሱስን ዮሴፍ በገዛ-ራሱ መቃብር መቅበሩ እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋውን ያመለክታል በእስራኤል አስተሳሰብ፡፡ ሁለቱም በፊደል ሳይሆን በመንፈስ የኢየሱስ ደቀ-መዛሙርት ነበሩና፤ የሐሰት እውነተኞች በፊደል (በግልፅ) ደቀ-መዛሙርቱ የነበሩት ሲበታተኑ እነዚህ የእውነት እውነተኞች ከስውር ወደ ግልጽ ወጥተዋል፡፡ ግን ሁለቱም የተከበሩ ሰዎች በዚህ ተግባራቸው







ለኢየሱስ ያላቸውን ታላቅ አክብሮትና አፍቅሮት በእይታቸው ልክ የገለፁ ሲሆን፣ የኢየሱስን ሥጋ የተባለውን አካል፣ በአይሁድ ሥርዓት ሲገንዙ ሥጋውን ውድ በሆነ ነገር በከርቤ፣ በእሬትና በሽቱ አሳምረው በተከበረና በውድ ጨርቅ ገንዘው መቅበራቸው ሲታይ፣ የኢየሱስ ሥጋ እጅግ ውድና ብርቅ ነገር መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ነገር ግን በፊደላዊ (ፍጥረታዊ)ው (በውጫዊ) ዕውቀታቸው መጠን በተረዱበት ደረጃ ፍቅርና ቅንነት በተሞላ አመለካከታቸው መልካም ሥራ በመሥራታቸው (እነሱ) ሥጋውን ሲነኩ፣ ይዘው ሲገንዙና ተሸከመው ወስደው ሲቀብሩት መጠንና ልክ በሌለው በረከትና ፈውስ እንደተሞሉ ይሰማኛል፤ በእግዚአብሔር ፈቃድ የሞተ ሥጋና መንፈስ ብቻ ነውና ቀባሪዎቹ ተባርከዋል፡፡ ክርስቶስ ኃጢአታቸውን በሥጋቸው በእስራኤል ሥጋ በመስቀል ላይ ሞቶ መታየቱ የመግደሉን ግድያ ማሳየቱ ነበር፤ ይህ ደግሞ የእስራኤል ጠላት የነበረውን ፈርዖንን ከነሠራዊቱ በባሕር መግደሉን ዓይተው እንዲያምኑ ግድያውን በባሕሩ ዳር አውጥቶ በግልጽ የአሳያቸው ፍጻሜ ወይም ድምዳሜ ነው፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቱ ይኸው፣ የኃጢአታችሁን እሬሣ ተንጠልጥሏል ዓይታችሁ እመኑ ነው፡፡

ነገር ግን የዓይናችን እውነተኝነት ምን ያህል ነው? ውሸታምነቱስ ምን ያህል ነው? ውሸታምነቱ ከ-እስከ ነው፡፡ ጨለማውን ብርሃን፣ ክፉውን መልካም፣ መራራውን ጣፋጭ፣ ሞትን ሕይወት አድርጎ ያሳያል፡፡ ለምሳሌ፣ ሔዋን የሞትን ዛፍ ፍሬ ያየችበት ዓይን፣ (ዘፍ.3፡6)፤ የእግዚብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች መልካሞች እንደሆኑ ያዩበት ዓይን፣ (ዘፍ.6፡2)፤ ሎጥ ሰዶማንና ገሞራን እስከ ዞዓር ድረስ ያየበት ዓይን፣ (ዘፍ፡13፡10)፤ በሙሴ መሪነት የተሰበሰቡ ሕዝብ በሲና ተራራ ላይ የሚነደውን እሳት ያዩበት ዓይን፣ ዘፀ.20፡18) በኢያሱ የተመሩ አሥሩ የከነዓን ሰላዮች የዔናቅን ልጆች ያዩበት ዓይን፣ (ዘኊ.13፡28-29) ዓካን በዘረፋው መካከል የሰናዖረን ካባ፣ በርኖስና ገንዘብ ያየበት ዓይን፣

(ኢያሱ7፥20-21) ሳምሶን በሶሬቅ ሸለቆ «ደሊላ» የተባለችን ሴት ያየበት ዓይን፣ (መሳ.16፥4-21) የእስራኤል ሠራዊትና ሳዖል ጎልያድን ያዩበት ዓይን፣ (1ሳሙ.17፥4-11) ዳዊት የዖሪዮን ሚስት ያየበት ዓይን፣ (2ሳሙ.11፥2-5) ...ወዘተ ያልተገረዘ ዓይናችን መልክና ማንነት (OBJECT & IMMEGE) ሆኖ የተገሳበጠ መልክ ያሳያልና ከቶ ሊታመን አይችልም ነው፤ እንዲሁም ያልተገረዘ ጆሮአችን የሚሰማው የተገለበጠውን ፍቺ ነው፡፡ ስለዚህ በዓይናችንና በጆሮአችን መታመን እንደ ሌለብና ይህ ያስጠነቅቀናል፡፡

የቀብሩን ሁኔታ ስንመለከት፣ ትናንት ማታ በፋሲካው እራት ላይ ቀርቦ የተበላው ይህ የተቀበረው ቁሳዊ አካል ተቆርሶና ተቀንሶ አለመሆኑን ቀድመን የተመለከትን ሲሆን፣ ክርስቶስ ገና መጋረጃውን አልቀደደምና ቃሉን በእንጀራው ጋርዶ አቅርቧል፤ እንጂ የታወቀውን ሥጋ አይደለም፤ የመጋረጃው ዘመን ጊዜው ገና ነበርና ገና አላለፈም፡፡ የመጋረጃው መቀደድ ሁሉን ነገር ወደ ብርሃን ያወጣል፡፡ የብሉይ ኪዳኑ ቅዱስ ነገር ማለት ስውር ነገር ሁሉ ማለት፣ ላይ፣ ከምድር በላይ መቅደስ (ከፍታ ላይ) ታች፣ ከምድር በታች ዝቅታ ውስጥ (መቃብር) ስውር፣ ዝግ፣ ዕሽግ፣ ሽፍን ከነበረበት ወደ ግልጽ የወጣው ከመጋረጃ መቀደድ በኋላ ነው ለማለት ነው፡፡

ጌታ «ሥጋ» ብሎ ሲጠራም፣ እንደ ሰው በመልክ በመጋረጃ ዓይኑ እንደምታይ በሰው ስያሜ የሚጠራ አይደለም፤ በእንጀራው የተሸፈነውን ቃሉን ነው፤ የዘላለም ሕይወት፡፡ ከተበላው ነገር ሁሉ ቅዱሱ የተጋረደው ቃሉ ክርስቶስ ነው፡፡ እንጀራ፣ ሥጋ የሚያሰኘው፣ ፋሲካ ጥንት በጅምር ላይ ሲበላ ሥጋው ከእንጀራ ጋር በአንድነት የተበላ ስለሆነ፣ አሁን ከሰማይ የወረደውን ሥጋ በእንጀራ መጋረጃነት አቅርቧል፡፡ የፋሲካው ተካፋዮቹም ከውጫዊነት ገና ወደ ውስጥ-ውስጠኛ ክፍል አሊገቡም ነበርና፡፡ ከመጋረጃ መቀደድ ወዲህ የመጣ «አዲስ ፍጥረት»







በእግዚአብሔር መንግሥት የሚበላውን (የሚጠጣውን) አዲሱንና (ማቴ.26፥29፣ ማር.14፥25ሉቃ 22፥17-18) እጅግ ቅዱሱን ወይን (ክርስቶስን) በሩ ላይ ቆሞ ከሚያንኳኳ ጌታ ጋር በቤት ውስጥ-ውስጠኛ ክፍል ይካፈላል፡፡ እዚህ ላይ ልብ ማለት ያለብን ቁም ነገር፣ በሦስቱም ወንጌሎች በአባቴ መንግሥት፣ በእግዚአብሔር መንግሥት፣ የእግዚአብሔር መንግሥት እስክትመጣ ከአሁን ጀምሮ አዲሱን ወይን ፍሬ ከናንተ ጋር እስከምጠጣ ከዚህኛው አልጠጣውም ማለቱን ነው፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት አንዱ ነገር ሁሉ፣ ሁሉ ነገርም አንድ መሆኑን እንድናስተውል ነው፡፡ አንድ ካልሆነም የተከፋፈለ፣ ቁርጥ-ራጭ ባለጥላ፣ ባለጨለማ ይሆናል ማለት ነው፡፡ «አዲሱ ወይንም»፣ (ዮሐ.15፡1) ማለዳ፣ ማለዳ አዲስ እርሱ ራሱ ስለሆነ አንዱ ሁሉ ነው፡፡

እንደ ተጻፈ፣ ከሰማይ የወረደ እንጀራ ሥጋው ነው፡፡ ቃሉ ውኃም፣ ወይንም፣ ወተትም፣ ሥጋም፣ እንጀራም ፊኤማም፣ በረከትም ነው፤ «እራቱ የጌታ! ወይስ ነኹሽታ-ን!! በተባለ መጽሐፌ ይመልከቱ»፡፡ ለጥናት በሌላ አቅጣጫ ስንመለከት ግን ሙት ነገር መሸፋፈን፣ ሽታውን ማሳመር፤ ለማሻሻልና አስፀያፊ ነገርም ስለሆነ በሚል አጥልቆ ቆፍሮ መቅበር፣ መሰወር፣ መሸፋፈን የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም፡፡ ሙትን ለእግዚአብሔር ብናጋልጥ ሕይወትና ጤና ይሆናል፤ ግማቱን፣ ትሉን ብናጋልጥ የተባረከ ሽታ ይሆናል፤ ኃጢአትን ብናጋልጥ ጽድቅ ሆኖ ይለወጣል፡፡ ምክንያቱም መራቆት፣ ውርደት፣ ሞት ኃጢአት ወለድ ነገር ሲሆን፣ መሸፋፈንም አብሮ መምጣቱን ተጽፎ እናነባለን፤ (ዘፍ.3፡7-8) አዳሞች፣ መሸፋፈን መከዳደን ማሸሽ፣ መሰወር የጀመሩት ምናቸውን ነበር? ራቁትነታቸውን ሳይሆን ኃጢአታቸውን ነው፤ ሞታቸውን፤ ውርደታቸውን፣ አልሞትኩም አልተዋረድኩም በሕይወት ነኝ፣ አለሁ፣ ለማለትና መሞትንና ውርደትን ለመካድ መግደርደሪያ ነበር፡፡ ለሰው



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፡16

ኃጢአት የሚሆነው፤ ኃጢአት መሥራቱ ሳይሆን፣ ኃጢአትን መሸፋፈኑ መከዳደኑ፣ መሰወሩ ማሸሹ ንጹሕ ሰው መምሰሉ ነው፤ ኃጢአት፡፡

ሞትን መበስበስን፣ ትልን፣ ግማትን፣ ውርደትን ራቁትነትን መደበቅ፤ መሰወር፣ ማሸሽ፣ በማጭበርበር ጤናማ፣ ቆንጆ መስሎ በሰው ዘንድ ለመታየት ነው፡፡ በዚሁ መልኩም ነው አርማቲያ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የጌታን የወዳጃቸውን ውርደት ከሰው ፊት ለማሳመር፣ ለመሸፋፈን፣ ለመሠወር የመጨረሻ ጥረት ያደረጉት፡፡ ይህ ሁሉ ልፋታቸው በሦስተኛ ቀን ሲታይ ጨርቁ በቦታው ቀረ እንጂ ለሥጋው ፋይዳ አልሆነም፣ ጌታ በሰው እጅ ሥራ አይገለገልምና፡፡ የሞተውን መሰወር ማሸሽ መሸፋፈን በውስጣችን አካላችን ሆኖ የሚኖረው የሰይጣን ምክር ነው፡፡ ይህም እንደ እግዚአብሔር አለማሰብ ሆኖ ያሰቃየናል፡፡ ኃጢአትን መሠወር ሞትህን መሠወር ሞት እንዲኖርብን ከሚያደርግ በስተቀር ምንም ዋጋ የለውም፡፡ የጌታ ኢየሱስ ሥጋ ተራቆተ፣ ተዋረደ ቆሰለ፣ ሞተ ይበሰብሳል፣ ይተላል፣ ይሸታል ብሎ ማሰብ ስለተጋረደብን መስሎን እንደግንዛቤአችን ከውርደቱ፣ ከቁስሉ ከመበስበሱ፣ ከመትላቱና ከደረሰበት ነቀፌታው ተፀየፍነው ርቀን ቆምን እንጂ ኢየሱስ በዚህ ሁሉ ድንቅ፣ ተዓምር እየሠራበት ስለነበር ለእርሱ የክብር ብዛት እንዲጨምርለት የሚደርገውን ያየልና ያውቅ ነበር ለእይተው ኃይል ክብር እየሰጠሁ ለዘላለሙ አሜን እያልኩ ከአንባቢዎቼ ጋር አብሬ እንበረከካለሁ (ሮሜ.8፡18፣ 2ቆሮ.18፤ 5፡ 11-12፣ ሉቃስ 6፡22-23) ነው፡፡

አንድን ነገር የምንፈርደው አይተን አስበን፣ አነፃፅረን ነው፡፡ የምናየውና የምንፈርደው፣ በፍፁም ልብ፣ በፍም ሐሳብ፣ በንጹሕና በቅዱስ አእምሮ ሳይሆን፣ በአዳም በኩል ከዲያብሎስ በወረስነው በተቃራኒ በሚያየው ሐሰተኛ ዓይን፣ ዓይተን፣ እንደተጻፈ በደንዳናውና በጨለማው ልባችን አመዛዝነን እንደግንዛቤአችን ነው፡፡ ለዚህ ማሥረጃው፣ የቀድሞ እኔን ጨምሮ ኢየሱስ ላይ ለደረሰው ውርደት፣ ትፋት፣ ጥፊ፣ ፌዝ፣ ስድብ ዱላ





ምት ከአብ አባት በላይ ማዘናችን ነው፡፡ እርሱ የተቀበለው የውርደት ውርደት የክብር ክብር መሆኑን ያውቃል፡፡ እኛ ግን ውርደትን ስንሸፋፍን ውርደትን በሰባት ዕጥፍ፣ ኃጢአትን ስንሸፋፍን ኃጢአትን በሰባት ዕጥፍ፣ ግማትን ስንሸፋፍን፣ ግማትን፣ ርኩሰትን በሰባት ዕጥፍ በወለድ እናጭዳታለ፡፡ (ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም፤ (የሚተፋት፤ የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምህረትን ያገኛል፣ (ምሳሌ 28፡13) (በልቡ የታበየ ሁሉ (ራሱን የካበ) ስለሆነ ርኩስ ነውና፤ (ምሳሌ 16፡5፣ ... በሰው ዘንድ የከበረ የተሸሞነሞነ በእግዚአብሔር ፊት ርኩሰት ነውና፣ ሉቃስ 16፡ 15 አርማቲያ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ትልቁ ዋጋ ያለው ሥራቸው ሲቀብሩት እግዚአብሔር ሥራቸውን ሳይሆን ልባቸውን ማየቱ ነው፡፡ በእግዚአብሐር ፊት ሞቱን በመቀበል ሞተዋል፣ አብረውትም ተቀብረዋልና፡፡ በሌላ በኩል፣ በሕጉ መሠረት የሠሩት ሥራቸው ያገኛቸዋል፤ ቡተከበረ ነገር ሸፍነውታልና በእግዚአብሔር ክብር ይሸፈናሉ፣ ቀብተዋልና፣ የተቀቡ፣ የተባረኩ ይሆናሉ፡፡ ውጨዊው ሁኔታቸው ውስጣቸውን ያሳያልና፡፡ ወደ ውጭ የወጣውም የውስጣቸው ነበር፡፡ የሞተውን፣ የተዋረደውን መቀበል ሞቱንና ውርደቱን መቀበል፣ ስለሆነ በዚሁም ሕይወቱንና ክብሩን የተረጋገጠ ነው፡፡ ውርደቱ ክብሩን፣ ሞቱ ሕይወቱን መቀበያ መሻጋገሪያ ድልድይ ነው፤ ክብሩ ከውርደቱ፣ ሕይወቱ ከሞቱ ማዶ በኩል ነውና፡፡ እንደ እነጳውሎስ በሞቱ የሕይወቱ ምስክሮች ነን፣ (2ቆሮ.4፡11-12፤) ከሞቱ የሚሸሽ ሁሉ ወደ ዘላለም ሞት የሚሸሽ መሆኑን አረጋግጠን እንመሰክራለን፡፡ መግደላዊት ማርያምም በእነ አርማቲያ ዮሴፍ በተመሳሳይ ሁኔታ ነበረችና አትክልተኛው መስሎአት በከፍተኛ ጉጉት «ጌታ ሆይ፣ አንተ ወስደኸው ከሆነ ወዴት አኖርከው እኔም እወስደዋለሁ» አለች፣ (ዮሐ.20፡15፤)፡፡ እኛ ግን በሰይጣን ምክር በጠቅላላ ከሞቱ በብዙ ርቀት ቆመን በውስጣችን ያልሞተ ሥጋ እያስተናገድን ኢየሱስ ሞቷል! ተነስቷል! ሕያው ሆኗል! እያልን የውሸት ፕሮፓጋንዳ እየነዛን ምድርን አዳረስናት፤ የክርስቶስን ሞት የተፀየፈ፣ ከሞቱ ርቆ የቆመ የሞቱ ምስክር

አይደለም፡፡ ከገዙ-ራስ ማንነት ውጭ በርቀት፣ ያውም በውጭ አገር፣ (ከባሕር ማዶ)፣ በብዙ ኪሎ ሜትር በርቀት፣ ከዘመናት በፊት፣ በሌላ ቁስ አካል የሞተውን በሕይወታችን ያልተካፈልነውን ከመጽሐፉ በንባብ አማካይነት ብቻ አግኝተን፣ በማውራት እውነትን ሸጠን ለራሳችን መኖ መግዣ በማድረጋችን ሁላችንም ተከሰሰናል፡፡ ከዚህ ክስ የሚያድነን በአስቸኳይ ሞቱን ሳንጸየፍ በውስጣችን መቀበሉ ነው፡፡ ከሞት፣ ሞት ያድናል፤ ከግዴታ ሞት ወደ ሞት ያድናል፡፡ ከሞት በሞት (በክርስቶስ ሞት) መጋረድ፤ (ዘፀ.12፡12-13፣ ቁ.21-22፤) ያስፈልጋል፡፡ የሰውን ልጅ ከሞት የሚያድነው «ሞት» ክብርን፣ ክብር ለሚገባው እግዚአብሔር ማስረከቡ ነው፡፡ ክብርን ለእግዚአብሔር ማስረከቡ ለሰው እንዴት ሞት ይሆናል? ክብርን ያስረከበ ሰው ውርደቱን ለራሱ ስለሚቀበል ሞት ሆኖ ይሰማዋልና ነው፡፡ ክብርን ለእግዚአብሔር ያስረከበ ሰው እንደ ክርስቶስ በሁሉ ራሱን ባዶ ያደረገ ሰው ነው፡፡ «ከፍ ያለችው የሰው ዓይን ትዋረዳለች፣ የሰዎችም ኩራት ትወድቃለች፣ በዚያን ቀን እግዚአብሔር ብቻውን ከፍ-ከፍ ይላል» (ኢሳ.2፡11)፡፡ (ፊል.2፡5-8፣ ኢሳ.42፡1፣ ም.53፡ 11-12) እናመሳክር፡፡ ከዚህ ውርደት ከሆነው ሞት ነው ሰይጣን ይዞን በክንፍ እያሸሸን ያለው ማንኛውም ሰው የተባለ ከዚህ ዓይነት ሞት ነው፡፡ (የዚህ ዓይነት ሞት፣ ለራስ ሞቶ ለጌታ መኖር ነው፤፤ በሌላም አባባል ለኃጢአት ሞቶ ለጽድቅ መኖር ነው፡፡)

ክብርን ለእግዚአብሔር ማስረከቡ ሞት የሚሆነው፣ ውስጣዊ ሞት ነው ወይስ ውጫዊ በግልጽ በገሃዱ ዓለም የሚታወቅ ሞት ነው? አንተ በቁመና ስትሞት ሀ/ አንተ ትሞታለህ? ለ/ ባአንተ ላይ ሊሠለጥን የሚሻው ከፍ፣ ከፍ ማለትን ወዳዱ ሉሲፈር (ሰይጣን) ይሞታል? ይህ ውርደት የሚሆነው ሉሲፈር ነው ወይስ አንተ ነህ? ከክርስቶስ ጋር በመስቀል (ከፍታ) ላይ መሞት (ሥጋን ከክፉ ምኞቱና መሻቱ ጋር መስቀል) እውነት እውነቱ ይህ ነው፡፡ ይህ ነው፣ ቅዱስ ቅዱሳን የሆነው፣ የማይታየው (ስውር) ሞት







ይህም በገዛ ራስ ፈቅዶ መሞት (የሥጋን ሰውነት መገፈፍ)፡፡ በለዓም ሲናገር፣ የጻድቃንን ሞት እኔ ልሙት (ዘኍ.23፡10) አለ፤ ሄኖክን፣ አብርሃምን፣ ይስሐቅን፣ ያዕቆብን፣ አሮንን፣ ሙሴን፣ ዳዊትን፣ ኢየሱስን ሞት የሚመስል ሞት፡፡ ከዚህ ሞት የሚሸሽ ሁሉ ከሞት ለማምለጥ ሳይሆን ወደ ዘላለም ሞት የሚሸሽ መሆኑን በግልጥ እንመሰክራለን፡፡ ክብርን፣ ክብር ለሚገባው ለባለቤቱ ከማስረከብ ሞቼ እገኛለሁ የሚል መንፈስ ያለበት ሁሉ ሰው ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ክብሩን በዘላለም ባንክ የማያስቀምጥ፡፡

እንምረጥ፣ ከዲያብሎስ ጋር ከክብር ወደ ክብር ከዚያም ወደ ገደል/ሲዖል እንደ አዳም? ወይስ ከክርስቶስ ጋር ከውርደት ወደ ዘላለም ክብር ማምራቱ ይሻለናል? ጌታ ኢየሱስ ክብርን ክብር ለሚገባው ፈጽሞ ማስረከቡ ፈጽሞ ሞተ አሰኘው፤ (ዮሐ.19፡32-33) ክብርን ፈጽሞ ለእግዚአብሔር ማስረከብ ዕዳን ፈጽሞ መክፈል ነው ወይስ ፈጽሞ መሞት ነው? ሰይማናዊ በሆነ ትርጉም ክርስቶስ ፈጽሞ ሞተ ማለት በመለኮታዊ ትርጉም ዕዳን ፈጽሞ ከፍሏል ማለት ነው፡፡ ዕዳን፣ ፈጽሞ መክፈሉ ይሻላል ወይስ ጥቂት አስቀርቶ ከፍሎ እየተከሰሱ ለዘላለም መኖሩ ይሻላል? ክብርን ፈጽሞ ለእግዚአብሔር ማስረከብ ፈጽሞ መሞት ነው ወይስ ክብርን በዘላለም ዓለም በባንክ ማስቀመጥ ነው? ስንጸልይ ግን፣ ጌታ ሆይ፣ ክብርን ጠቅልለህ አንተው ውሰድ ስንል፣ እኛ ዘንድ ከክብር ምንም ሳናስቀር ጠቅልለን እናስረክብ ነው ወይስ በማስመሰልና በሽንገላ የገዛ ራሳችንን ክብር በምንሻበት ልብ (በተከፋፈለ ልብ) ሆነን ነው? እንዲህ ስንል ውርደቱን የቱጋ ወርውረን ነው? ለውርደቱ ቦታ ሳይገኝ እግዚአብሔር ክብርን ይቀበላል ወይ? እንደ ክርስቶስ ውርደቱን አንተው፡፡ ስለወንጌል፣ ስለጌታ መዋረድን ተቀብለህ ከሆነ፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ ከፍ-ከፍ እንዳለ፣ በአንተም እንዲሁ ከፍ-ከፍ ይላል፡፡ አለዚያ በአጭበርባሪው ከንፈራችን ላይ ፍርዱ ይገለጣል (ኤር.12፡2፣ ማቴ.15፡8-

9፣ ም.12፥36-37)፡፡ ክርስቶስ ፈጽሞ ሞተ የማለት የእውነት እውነቱ ትርጉም ክርስቶስ እስከ መጨረሻ ተዋረደ ማለት ብቻ ነው እንጂ፣ ክርስቶስ አልሞተም፤ አይሞትምም፣ ሕያው ነው፡፡ ሕያው ነው ማለት ደግሞ ሞትን ፈጽሞ (ጨርሶ) ደምስሶ ነጥሮ ወጣ ማለት ነው፡፡ «እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል (1ጢሞ.6፥16)»፡፡ ሞት ጨለማ ስለሆነ እርሱ ጌታ ወደሚኖርበት ብርሃን ሊቀርብ ከቶ አይችልም ጌታ ሞት (ሰይጣን) ስለሌለበት የማይሞት ነው፡፡ የአዳም ልጆች ሞትን የሚሞትልንን ሰላማን እርሱ በእኛ ምትክ ሕይወቱን መሥዋእት በማድረግ ሞቶ፣ ሞትን ደምስሷል እንጂ፣ እርሱ ሊሞት የሚገባው ወይም ሞት የሚሠለጥንበት አልነበረም (1ጢሞ.6፥16/ሀ)፡፡ በሌላ አንፃር ቀደም ሲል እንዳየነው፣ ሞትን በሞት አጣፋ (ደመሰሰው)፤ ሰዎች ክርስቶስ ለእኔ ሞተ ሲሉ ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት በርቀት በሌላ ዓለም (በእስራኤል) በራሳቸው ሥጋ በማንነታቸው ውስጥ ሳይሆን በሌላ ሰው ማለት በእስራኤል ሥጋ መሞቱን ያወራሉና፡፡ ክርስቶስ ያንተን ዕዳ ለመክፈል የሞተው ባንተ ሥጋ በማንነትህ ውስጥ እንጂ በሌላ ሰው ሥጋ ላንተ አይሞትም፡፡ በአንተ ሥጋ ፈጽሞ ሞተ የሚያሰኘውም ያአንተ ሥጋ ፈጽሞ ሞቶ ከሆነ ነው፡፡ እርሱ ስለአንተ ፈጽሞ ተዋርዶ ክብርን፣ ክብር ለሚገባው አስረክቦልሃል፤ አንተም እንደዚሁ ከእርሱ ጋር እስከ መጨረሻ ተዋርደሃል ማለት ክብርን ጠቅልለህ ለእግዚአብሔር ሰጥተኸዋል፤ ደግሞም ክብርን አንተው ጠቅልለህ ውሰድ ብለህ የጸለይኸው ጸሎት ከእውነትና ከልብ የተደረገ መሆኑ በዚህ ይረጋገጣል፡፡ ነገር ግን ይህ ባልሆነበት አንተ በሥጋህ እየተጀነንህ ክርስቶስ ስለ እኔ ሞቷል ብትል ይህ እውነት፣ (ሰይጣናዊ እውነት) ነው፡፡







ደቀ-መዛሙርቱ በመቃብር ዙሪያ
ሕያውን በሙታን መካከል ሲፈልጉ

ደቀ-መዛሙርቱ የጌታን ሥጋ ከትናንት ወዲያ በተቀበረበት ውጫዊ መቃብር ውስጥ መፈለጋቸው ሕያውን በሙታን መካከል መፈለጋቸው ሆኖ በመላእክቱ ተነቅፏል (ሉቃስ 24፥5፤ ቁ.22-23)፡፡ ሕያውን በሙታን መካከል መፈለግ ማለት ምን ማለት ነው? ሞት ዲያብሎስ እና ኃጢአት የተያያዙ ሲሆኑ፣ ሙታን ማለት በወጬ መቃብር ያሉ በፊደል ሙታን ማለት ሳይሆን፣ ኃጥአን ማለት በውስጥ በመንፈስ ሙታን የሆኑ ማለት ነው፡፡ ደቀ-መዛሙርቱ ሥጋውን የበሉ፤ ደሙን የጠጡ ሕያዋን ሰዎች ሲሆኑ፣ በእነርሱ ያለውን እርሱን ሳላወቁ ራሳቸውን አላወቁም፤ እርሱ የሚኖረው በልተውት ሕያዋን በሆኑ ሰዎች ውስጥ ሲሆን፣ በእነርሱ «አማኑኤል» ሆኖ ያለው አልታይ፣ አልታወቅ ብሏቸው ልባቸው (ውስጣቸው) በጨለማ ስለተጋረደባቸው ወደ ውጪ ሜዳ መቃብር ተሯሯጡ፡፡ አብሮ እያለ፣ የማይታወቅ ነውና፣ በዓለም እያለ ዓለሙ ያላወቀው፣ በራሱ እጅ እያጠመቀው መጥምቁ ዮሐንስ ያላወቀው፣ መግደላዊት ማርያም አጠገቧ ቆሞ ሲያዋራት ያላወቀችው፣ የኤማሁስ መንገደኞች አብሯቸው ሲጓዝ ያላወቁት፣ እነፊልጶስ ይህን ያህል ዘመን አብሯቸው ሲኖር ያላወቁት ስለሆነ፣ በዚህ ነገር አይፈረድባቸውም፡፡ ዝንጉነትና፣ አለማስተዋል አለባቸው ይባላሉ እንጂ፡፡

ኢየሱስ በማየሻማ ቃል፣ በሦስተኛው ቀን እነሣለሁ፣ ወደ ገሊላ ተራራ፣ (ከፍታ) እልፋለሁ፣ እዚያ ታዩኛላችሁ ብሎ በግልጽ የነገራቸውን፣ «እኔም ከምድር ከፍ-ከፍ ያልሁ እንደሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ» ያለውን ሁሉ ማስታወስና ማገናዘብ ተስኖአቸው ይታያሉ፡፡ ይህ ሁሉ መቅበዝበዝ ወደ ራስ ወደሆነው ውስጥ መግባትን አለማወቅ፣ ውስጥን ለማየት ዓይን ማጣት፣ ዛሬም በዚህ ዘመን በተመሳሳይ ይታያል፡፡ በዕለቱ ወደ መቃብሩ የማለዱ ሁሉ ከሁኔታቸውና ከአጠያየቃቸው ሲገመገሙ የኢየሱስ ሥጋ

እስከ ሦስት ቀን ድረስም እመቃብር ውስጥ ተጋድሟል፣ ደግሞም ይበሰብሳል፣ ብለው እንዲህ ያለውን ምስል በልባቸው የቀረጹና የልቡናቸውን ትርጉም ተከታዮች ሆነው ይታያሉ፡፡ ለዚህም ነው አስከሬኑን ለመቀባት ቅባትና ሽቱ ገዛዝተው በርከት ብለው እርሱ በውስጣቸው እያለ ከያሉበት ርቀት ተሰባስበው ቀበሌ አቋርጠው ተጉዘው፣ ቀድሞ በሦስተኛ ቀን እነሣለሁ፣ ወደ ገሊላ እቀድማችኋለሁ ያለውን ቃለ ትንቢት የማያሰላስሉ ተቃራኒውን ጎን የሰሙ ተቃራኒ ጆሮ የነበራቸው ሆነው ሲታዩ፣ ሴቶቹም የእርሱን አካል ሽቱ ቀብተው ጠረኑን ለማሳመር ነበር በሌሊት የወጡት፡፡ በሁላቸውም ልብ ይህ ተመሳሳይ አመለካከት ነበረ፡፡ ዋናው የዕውርነታቸው መንስዔ ምን ነበር? ውስጣቸው እመቃብር ውስጥ በተጋደመው ቁሳዊ አካል በሆነ አስከሬን ጥላ ግርዶሽ መሸፈኑ፣ ዓናቸው ከዚያ ላይ አለመነሣቱ ነበር፡፡

እንዲሁም ሲሆን በወቅቱ የነበሩ ደቀ-መዛሙርት እያንዳንዳቸው በየራሳቸው እስከ መቃብሩ ደርሰውና በየራሳቸው ዓይን አይተው እንጂ አንዱ የሌላውን ምስክርነት የማያምኑ እንደነበርም በየግላቸው ወደ መቃብር ስፍራው መሽቀዳደማቸው ይገለጻል፡፡ የጌታን ማለት የባለቤቱን ምስክር ያላመኑ የሰውን ሊያምኑ እንዴት ይችላሉ? (የእግዚአብሔርን ምስክር የማያምን የሰውን ማመን እንደማይችል ተጽፎአልና (ሕዝ.3፥7)፡፡ ለዚህም የምንጠቅሰው በዮሐንስ አገላለጽ መሠረት የማርያምን ምስክርነት በየራሳቸው ለማረጋገጥ ጴጥሮስ በራሱ ሲሮጥ ዮሐንስ በራሱ መሮጡ ነው፡፡ አንዱ የሌላው ሩጫ በቂ ነው ብሎ አለማረፉ፣ ዮሐንስ ቀድሞ እመቃብሩ ደርሶ ክፍት መሆኑን ባየው ጴጥሮስ አለማመኑና በራሱ እስከ ውስጥ ድረስ መግባቱ፣ ዮሐንስም ደግሞ ጴጥሮስ በገባውና ባየው ባለመርካት ራሱ ደግሞ መግባቱን እንመለከታለን፡፡ ማርያምም ደግሞ በጉዳዩ ቀዳሚ ብትሆንም የጌታን ድምፅ በገዛ-ራስዋ ጆሮ እስክትሰማና ጌታን በዓይኗ አይታ እስክታረጋግጥ ድረስ በመላእክቱ ምስክርነትም አልረካችም







(ዮሐ.20፥1-18፣ ማር.16፥14)፡፡ የመላእክት ምስክርነት የመንፈስ ምስክርነት ስለሆነ ማሳረፍ ነበረበት ‹‹መንፈስም እውነት ነውና የሚመሰክረው መንፈስ ነው›› (1ዮሐ.5፥7)፤ ቶማስም እንዲሁ በገዛ-ራሱ ዓይን እስኪያይና በራሱ እጅ እስኪዳስሰው ድረስ ትንሣኤውን በሌሎች ምስክርነት አላመነም፡፡ የእኛ የዛሬዎቹ አማኞች ሁኔታስ? በወሬ ማመን ነው፣ አይደል? በፕሮፓጋንዳ አሜን ብሎ ማጨብጨብ ከኅብረቱ ላለመውጣት አንዱ በሌላ የተንተራሰ፣ ያልተረጋገጠ እምነት፣ በሰው ጆሮ ሰምቶ በሰው ዓይን ማመንና በራስ አለመመራመር ለሙታን ትንሣኤ ቀርቶ ለተራ ታሪክም እርግጠኛ ባያደርግም በጭፍን መጓዝ የእኛ እጣ ፋንታ ከሆነ ውሎ አድሮአል፡፡

ይህ ሁኔታ የጌታን ትንሣኤና ሕያውነቱን እያንዳንዱ ሰው በሰው ምስክር ብቻ ሳይሆን በየራሱ መርምሮ ማረጋገጥ ያለበት መሆኑን ያስተምረናል፡፡ በወሬ ወይም ከንባቡ የሚያምን ሁሉ የእግሩ ማረፊያ የሌለው በአየር ላይ የተንሳፈፈ የኖኅን ቁራ ይመስላል፡፡ ሆኖም «በሦስተኛው ቀን እነሣለሁ» ያለውን የጌታ ቃል ለጊዜው ባይገናዘብም በዓይኑ ካየው ሁኔታ ጋር መጻሕፍትን በማስታወስ ትንሣኤውን በማመን ዮሐንስ ቀዳሚ መሆኑን ቁጥር 9 ላይ እናገኛለን፡፡ ዛሬ ክርስቶስ በቁስ አካል ሳይሆን በመንፈስ ሕያው መሆኑ የተዘገበ ሲሆን፣ (1ጴጥ.3፥18) «ዛሬ» ማለት ምን ማለት ነው? ከትንሣኤ ወዲህ ያለው የምሕረትና የዕረፍት ሰባተኛው ቀን የሆነው ክርስቶስ ማለት ነው ዕብ.4፥-10) ትንሣኤውን እንደ እነዮሐንስ፣ ጴጥሮስ በየራስ ማረጋገጥ የሚቻለው እንዴት ነው? ወደ ውጩ መቃብር በየራስ በመሮጥ ነው ወይ? አይደለም፣ የተጻፈው በመንፈስ ሕያው ነው፣ ማለትም በውስጥ በልቡና ሕያው ነው ማለት መሆኑን እንመን፡፡ ክርስቶስ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ ማለት እኛ በሥጋችን ሙታን፣ በመንፈስ ግን ሕያዋን ሆነናል ማለት ካልሆነ ካልተረጎመ ባዶ ወሬ ይዘን እንጓዛለን፡፡ ክርስቶስ ሞተ ማለትም በውስጥ በመቅደስ ውስጥ በኪሩቤል

ላይ በተቀመጠው እግዚአብሔር አምላክ ፊት ባለ መሠውያ ላይ ስለአንተ/ች መሥዋዕት ሆኖ ለመቅረብ በሥጋችን (በውስጣችን) መሞቱ ቀድሞ በውጭ ዓለም በፊደል የመሞቱ እውነታ ሲሆን፣ በሞቱም አንተ/ችን አጠቃልሎ በአዲሱ ማንነት ከራሱ ጋር ያስነሣ ዘንድ በአሮጌ ማንነቱ አሮጌ ማንነታችንን ለመደምሰስ ከራሱ ጋር እስራኤልንና አሕዛብን፣ በውስጥም በውጭም የነበሩትን ሁሉ ጠቅልሎ ሞተ ማለት ነው፤ (2ቆሮ.5፡14-15፤) ይህ ማለትም በሕይወት ሳለን የዋጠንን አበሳችንን በታላቅ ፍቅሩ በሞቱ አሮጌ ማንነታችንን ጠቅልሎ ገድሎና ቀብሮት ሊያወጣን ያደረገው የጽድቅ ፍርድ መሆኑን በታላቅ ምሥጋና እንቀበላለን አሜን፡፡

ክርስቶስ ተነሣ ማለትም በክርስቶስ የሞተና በክርስቶስ የተቀበረ ሁሉ ተነሣ ማለትን እውን ካላደረገ ውሸታም ምስክሮች ነን ማለት ነው፡፡ (ሮሜ.6፡3-5፣ ቆላ2.11-12)ን በታሪክ ደረጃ ማመሳከር ይቻላል፡፡ ያለ ክርስቶስ ማለት ከእርሱ በተለይ የሞተውንና በተለይ የተቀበረውን ማን ያስነሣዋል? በክርስቶስ ያልሞተና በክርስቶስ ያልተቀበረ በዲያብሎስ ሞቶ በዲያብሎስ ይቀበራል፣ በዲያብሎስ ሕያው ሆኖ ዓለምን ይበጠብጣል፣ ደግሞም አይሞትም፣ ደግሞም ሕያው አይሆንም፡፡ ከዲያብሎስም ከክርስቶስም ተለይቶ በብቸኝነት የሚሞቱበትና በተለይ ተቀብሮ ሕያው የሚሆኑበት መንገድ የለምና፡፡

የእውነት እውነቱ መቃብር ውጭ የቁስ አካሉ የተቀበረበት ሰው የሚያውቀው ጉድጓድ ሳይሆን በውስጥ ያለው የሰው ማንነት የመንፈስ አካሉ በቁሙ የተቀበረበት እግዚአብሔር የሚያውቀው ሲዖል ነው፡፡ የሰው መቃብሩ ራሱ ቁም ሰውነቱ (አካሉ) ነው፣ (መዝ. 88፡3-6፣ 30፡3/ን ከዮናስ 2፡1-8) ዳዊትና ነቢዩ ዮናስ በጥፋታቸው ምክንያት በማንነታቸው ወደዚህ ወደ እውነት እውነተኛ እሥር ቤት ወደ ሲዖል መውርዳቸውን ጥቅሶቹ ይገልጻሉ፡፡ ከእግዚአብሔርና ከሰው ማን አይቶ አረጋግጦ ይመሰክራል? በመጋረጃ ግርዶሽ በጨለማ ዓይቶ ከሚመሰክርና በዘላለም ብርሃን አይቶ ከሚመሰክር የትኛው እውነተኛ ምስክር እንደሚሆን እናያታለን፡፡ አይቶ





ከሚመሰክር ሳያይ የሚመሰክር ይልቅ እውነተኛ ሊሆን ይችላል ወይ? አይቶ ከሚመሰክር ሳያይ የሚመሰክር ሊታመን ይገባል? ውስጡን ፍሬውን ከሚያይና ከነገለባው እንደተሸፈነ አይቶ ከሚመሰክር የትኛው ይሻላል?

እኛ አሕዛብ በትንሣኤ ዙሪያ፤?

አሕዛብ በብሉይ ኪዳን ዘመን ከምድር አራዊት፣ ከሰማይ ወፎች ከምድር ተንቀሳቃሽ (ኢሳ.43፡21፣ ሆሴ.2፡20፣ ሐሥ.10፡9-16) ተቆጥረዋል፡፡ ባለመገረዝ ምክንያትም በቁመና ሙታን፣ እርኩሳን የተባሉ (ቆላ.2፡13፣ ኢሳ52፡1-2) ነበሩ፡፡ አሕዛብ በምድር ያለ ተስፋ ኖረው፣ ያለ ተስፋ የሚሞቱና ያለ ተስፋ (ኤፌ.2፡12/ለ) የሚቀበሩ፣ በውጪ ጨለማ የተተው (ኢሳ.9፡2-3፣ ማቴ.4፡14-16፣ 8፡11-12) የማይቆጠሩ፣ (ራዕይ 11፡1-2፤) ሆነው በክርስቶስ በር እስከ ተከፈተላቸው ድረስ ስለ ቅዱሱ ሙታን ትንሣኤ ከእስራኤል በጆሮ በመስማት ሰሙ እንጂ የቅዱሳንን ሞት ስለማያውቁ ቅዱስ የሆነ ትንሣኤ ምን እንደሆነ ሳያውቁ ኖሩ፡፡ እስራኤል ከዚህ ከአሕዛብ ከወጣ አብርሃም በመገኘታቸውና በተቀበሉት መገረዝ ምልክት ምክንያት አንደኛ ደረጃ ትንሣኤ በማግኘት ወደ መላእክት ደረጃ ከፍ ያሉና ራሳቸው ሙታንን የሚያሥነሡና ብዙ ምልክቶችን የሚያደርጉ ቢሆኑም እንኳ፣ በመቃብር ዙሪያ ከታየባቸው ሁኔታ ሲገመገሙ፣ በጌታ ትንሣኤ ሰማይ ምድር ዞሮባቸው ተደነጋግረው ነበር፡፡ ነገር ግን፣ ሰውን ወደ ፍጹምና ቅዱስ ሰውነቱ ለመመለስ የሚያስችል መገረዝ አሁን ተዘጋጅቷል፡፡

አሕዛብ እስራኤል ሆኖ መለወጡ ለእሱ አንደኛ ደረጃ ትንሣኤ ማለት መገረዙ (ከቆለፈት ግርዶሽ ጨለማ ውስጥ ወደ ብርሃን መውጣቱ ነው፡፡ ለዚህ አብርሃም ከአሕዛብ መካከል ወጥቶ ግዝረትን በመቀበል ወደ እግዚአብሔር ፊት መውጣቱ ምልክትና ምሳሌ ነው (ዘፍ.17፡1-14፣ ቁ.1-

2)፡፡ ለሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር ፊት መውጣቱና ብርሃንን ለማየት መቻሉ ትንሣኤ ነው፤ ራሱን በመሠዋት ወደ እግዚአብሔር ክብር ገብቷል፤ ለዘላለሙ አሜን፡፡

በዚህ ሁኔታ አብርሃም በአንደኛ ደረጃ ትንሣኤ ወደ እግዚአብሔር ፊት ማለት ወደ አንደኛ ብርሃን፣ ወደ አንደኛ ሰማይ መውጣት ቻለ፡፡ አሕዛብ ተነሥቶ የእስራኤልን ቦታ ሲይዝ፣ እስራኤል የቀድሞን ቦታ ለቅቆ የክርስቶስን ቦታ ለመያዝ ከፍ ሲል ክርስቶስ ደግሞ መሪና መንገድ (ምልክትም) እንደመሆኑ መጠን እስከ ፍፁም ሙላት የአብን ደረጃ ለመያዝ ከፍ በማለት ሁሉን ማከታተል አለበት፡፡ አለዚያ ቀዳሚው በነበረበት ከቀጠለ ተከታዩ በነበረበት ይቀራልና፡፡ አብርሃም እንደ ሄኖክ ጨርሶ ሳይሄድ በአንደኛ ሰማይ ላይ በሰማይና በምድር መካከል መሆኑ በርቀትም ቢሆን አሕዛብ ሊያዩትና ሊከተሉት ያስችላቸዋል፡፡ (ሄኖክ ግን አልተገኘም፡፡) ነቢዩ ኢሳይያስ በም.30.26 ላይ፡... እንዳመለከተው የጨረቃ ብርሃን የፀሓይን ብርሃን ሲያክል፣ የፀሓይ ብርሃን ደግሞ የነበረበትን ደረጃ ለጨረቃ ለቅቆ ከፍ በማለት ሰባት ጊዜ ሰባት እጥፍ ይሆናል፡፡

እድገት እንዲህ እየሆነ ይጓዛል እንጂ፣ ቆሞ ባለህበት እርገጥ ከቶ አይጠቅምም፡፡ በየዘመኑ ሁሉ ሃይማኖታዊ ልማድ ሰውን ቆሞ ባለህበት እርገጥ አድርጎ ገድሏል፡፡ በዕድገቱ ደረጃም ከአሕዛብ ቀጥሎ እስራኤል ስንልም ከእስራኤል ቀጥሎ እስራኤል ከፍ ያለው እስራኤል ክርስቶስ ለማለት ነው፤ ዋናው እስራኤል ክርስቶስ ሆኖ፣ በክርስቶስ ሞት ደሙ ተዘርቶ የተገኘው እስራኤል ደግሞ በእውነት እውነቱ እስራኤል ስለሆነ፣ የእግዚአብሔር እስራኤል ተባለ፤ (ገላ.6፡16፤) አሁን ያ ታላቁና ፊደላዊው እስራኤል ለዚህኛው ወንበሩን ለቅቆ ወርዷል፡፡ ታላቁ ለታናሹ ይንበርከክ የተባለ ነውና ሥፍራውን ለታናሹ እስራኤል ለቅቆ መንበርከክ ይሻለዋል፡፡ ታናሹ እስራኤል፣ ታናሹ መንጋ ስለሚሆን የመንግሥቱ ወራሽ ነው፤





(ሉቃስ 12፡32-34) የክርስቶስ ትንሣኤ በቁስ አካል (በፊደል) መተርጎሙ ከፊተኛው እስራኤልም ጋር ተጠቅልሎ ጊዜ ያለፈበት ወሬ ነው፡፡ ታላቁ ነገር ሁሉ ከታናሹ ነገር ጫማ በታች እንዲነጠፍ (እንዲሰግድ) ሕጉ ያዛል፡፡ የክርስቶስ እንኳ ታላቅ አካል የሆነው ግዙፉ (ሥጋው) ታናሽ አካል ለሆነው ለመንፈሱ ፊቅዶ ስለተንበረከከ የተባረከ መሥዋዕት ሆነ፡፡

ክርስቶስ በትንሣኤ የሥጋን ሰውነት መገፈፉን ከ(ቆላ.2፡11-12) ስለምናነብብ፤ በክርስቶስ የሚጠመቁ ሁሉ ማስመሰል ካልሆነ በስተቀር እንዲሁ ናቸው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደ ተረከው የክርስቶስ የሥጋን ሰውነት በመገፈፍ መገረዙ በታሪክ ደረጃ በሰውኛ አስተሳሰብ ስንመለከተው በብሉይ ኪዳን ፊፅሞ ይገረዝ (ዘፍ.17፡13) የተባለውን ሥጋን ጨርሶ ስለተገፈፈ ተግባራዊ ስለሚያደርግ የእውነት፣ እውነተኛ መገረዝ ነው፤ (ቆላ.2፡11-12)፡፡ በመሠረቱ ለአብራም የተነገረው የእግዚአብሔር ዓላማ በግዝረት የሥጋ ሰውነት ሲገፈፍ የመንፈሱ ሰውነት ከቁርበቱ ግርዶሽ ጨለማ ወደ ብርሃን በመውጣት ትንሣኤ እንዲያገኝ የነበረው ትዕዛዝ በክርስቶስ የሥጋን ሰውነት መገፈፍ ፍጻሜ አግኝቶ በክርስቶስ ትንሣኤ ተደምድሟል፡፡ የትንሣኤ አካል የሚባለውም የክርስቶስ ትንሣኤ አካል ነው፡፡ «የፈጠረውን ምሳሌ እንዲመስል ዕውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታልና» የተባለው አዲሱ የትንሣኤ ሰው ክርስቶስ ነው፡፡ ይህ የምንለብሰው አዲሱ ሰው (ክርስቶስ) ወደ አብ እግዚአብሔር መግቢያ የሠርግ ልብሳችን ነው፤ (ቆላ. 3፡9-10፣ ማቴ. 22፡ 11-13)፡፡ በእንደዚያ ዓይነት አዲሱን ማንነትን ማለት የሠርግ ልብስ የሆነውን ክርስቶስን ለመልበስ አሮጌን ማንነትን (አዳምን) ማውለቅ (ገላ.3፡26-27) ነው፡፡

ትንሣኤ በጥምቀት ከሥጋ ሰውነት ማለት ከሰውር ቁርበቱ ተሸልቅቆ ወደ እግዚአብሔር ፊት መውጣት ሲሆን፣ የእውነት እውነተኛ ጥምቀት (ግዝረት) ቦታውን ሲይዝ የቀድሞውን ውጭ አካላዊ የሆነውን ግዝረት

ጨምሮ፣ በቁሳዊው ወንዝ ውኃ ገብተው የሚወጡትንም ሜዳዊ ሥርዓትን አጠቃልሎ የሐሰት እውነተኛ (አስመሳይ) በማድረግ፣ ውጫዊ ድርጊታዊ የሆነ ሥርዓትን በሞላ ያለ ልዩነት ወደ ውጪው ጨለማ ይጥለዋል፤ ይኮንነዋል፡፡ በእግዚአብሔር መንግሥት በሆነ ነገር ሁሉ መለኪያው ክርስቶስ ብቻ ስለሆነ፤ በዚህ ደረጃ ያልተገረዘ እስራኤልን ጨምሮ ዓለም በሞላ በቁርበት ጨለማ ሞት ጥላ ግርዶሽ ውስጥ ያለ ነው፤ (ቆላ.2፡13) ማለት ወደ ብርሃን ያልወጣ፣ ማለትም እግዚአብሔርን ያላየ፡፡

አሁን አሕዛብ መገረዙ፣ (ከቆለፈት ግርዶሽ ውስጥ ከጨለማ ወደ ብርሃን መውጣቱ) ትንሣኤ የሚሆነው፣ እስራኤልን አልፎ በክርስቶስ ደረጃ እንጂ በቀድሞ እስራኤል ደረጃ አይደለም፡፡ ተጠማቂውን ወደ ብርሃን ካላወጣውም ጥምቀቱ የተሳሳተ ነው፡፡ ለምን እናስመስላለን? መቃብር ማለት የትም ይሁን የት፣ መቼም ይሁን መቼ፣ ጨለማ ሲዖል ወደ የሰይጣን መንግሥት መግባት ከሆነ፣ ትንሣኤ ማለት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ብርሃን መውጣት ነው፡፡ ይህ በፊደል በውጭ የሚሆን ነው ወይስ በመንፈስ በውስጥ የሚሆን ነው? የእውነት እውነተኛው የሰይጣን መንግሥት ጨለማው ውጫዊ ቁስ ዓለም ነው ወይስ ከውስጥ መንፈስ ዓለም ነው? የውስጥ የልብ ጨለማ አደገኛ ነው ወይስ የውጭ ሜዳ ጨለማ አደገኛ ነው? ወደ ብርሃን መውጣትም፣ ወደ ጨለማ መግባትም በውጭ በቁስ አካል ነው ወይስ በውስጥ በመንፈስ አካል ነው?

መንፈሳዊው የአዲስ ኪዳን እስራኤል ሕይወት ይዘራና ትንሣኤ ያገኝ ዘንድ አሮጌው የፊደል እስራኤል ሞቶ ብስባሽ መሆን ነበረበት፤ (1ቆሮ.15፡42-44) የክርስቶስ በፊደል (በቁስ አካል) «ሞት መቀበርና መነሣት» ለብሉይ ኪዳን የፊደል እስራኤል በሞት ወንዝ ወደ ክብር መመለሻ መንገድ መሪ ታቦት (ኢያሱ 3፡2-4) ከመሆኑም፤ ሞቶ የመቀበራቸውና የመነሣታቸው ምልክት ሆኖ የተሾመ ነው፤ (ሉቃስ 2፡35)፤ ገኸዳዊ እስራኤል እንግዲህ እንዳይኖር የነርሱን ሥጋ ለመቅበር





በነርሱ አካል ሥጋ ክርስቶስ ሞቶ ተቀበሯልና፡፡ የብሉይ ኪዳን እስራኤል ከነሕጉ ሥርዓቱ ጋር ተጠቅልሎ በክርስቶስ ሞት የተቀበረ ስለሆነ አዲስ ኪዳን ከነአዲሱ እስራኤል ቦታውን ወርሷል፡፡

አሕዛብ ለእስራኤል ሸለፈት እንደሆነ እንዲሁ የበሉይ ኪዳን እስራኤል ለአዲስ ኪዳን እስራኤል ሸለፈት ነውና፤ ግልጽ ስናደርግ፣ ውጫዊው የክርስቶስ የፊደል (ገሀዱ) አካል እዚህ ሞቶ መቀበርና መነሣት እዚያ ያለው ቀዳሚውን የብሉይ ኪዳን (የፊደሉን) እስራኤል እጅ ሳይነካው ከነሥርዓቱ ገድሎ ቀብሮት የመንፈሱን እስራኤል ማሥነሻ ኃይል ነው፡፡ አሕዛብ ለእስራኤል ሸለፈት ለመሆኑ አብራም፣ በእስራኤልና በአሕዛብ መካከል ግድግዳ የፈጠረውን ሸለፈት ማስወገጃ ሥነ-ሥርዓት (ግዝረትን) መቀበሉ ነው፡፡ ያራራቃቸውም አብርሃም፣ (ኤፌ.2፡13-15) ከሀገሩ (ከከለዳውያን) ተነሥቶና ረጅም ርቀት ተጉዞ ከመራቁም በግዝረት ከለዳዊነቱን ተገፍፎ መቀበሩ አሕዛብን (ከለዳዊውንም መቅበሩ ነው፡፡ አብርሃም እርኩሰታቸውን ስለሚሠዋ ከነርሱ ከከለዳውያን ረጅም ርቀት መጓዝ ነበረበት፤ (ዘፀ.8፡25-27) ይመሰክር፡፡ የኛ የአሁን ጉዞአችን በክርስቶስ፣ በአዳም ወደ ወጣንበት ክብር ለመመለስ ነውና አሕዛብ እስራኤልን፣ እስራኤል ክርስቶስን መከተል ግድ ነው፡፡ ንስሓ፣ ወይም መመለስ ማለት በዚሁ ሁኔታ በእምነት ኃይል ወደ ወጣንበት ክብር ወደ ኋላ እንደ አብርሃም ከለዳዊነትን ተቆርጦና ቆርጦ መመለስ ማለት ነው፡፡

ወደ ክብር መመለሻ (መተላለፊያ) መንገዳችን ላይ የተደቀነው ታላቁ ተራራ ማነው? የሚል ካለ፤ እርሱ ባንተ መንገድ ላይ አሮጌውና ሥውሩ አንተ፤ በእኔ መተላለፊያ ላይ አሮጌውና ሥውሩ እኔ፣ የአንቺ ደንቃራ አሮጌዋና ሥውሯ አንቺ … ነን፡፡ «…በጥምቀትም ከርሱ ጋር ተቀበራችሁ…» (ቆላ.2፡12) በተባለው መሠረት ተቀብረን ይሆን ቀብረነው ስንወጣ የክርስቶስን በከፍታ መስቀል አየር ላይ ሞቶ ወርዶ ተቀብሮ፣ ቀብሮ መውጣቱን ቁልጭ አድርጎ ይተረጉማል፡፡ አንተ/ች በጥምቀት

የተቀበራችሁበት መቃብር በሰው ፊት ብቻ ሆኖ አስመሳይ ካልሆነና የእውነት እውነተኛ ከሆነ የጌታን መቃብርና ትንሣኤን አረጋግጦ፣ ወደ ግልጽ አምጥቶ ለዓለም አሳይቶ ይመሰክራል፡፡

ጌታ ኢየሱስ በዚህ ሁኔታ ነው ድልን የተቀዳጀው፡፡ ሰዎች ዝም ብለው ሲያሰቃዩት፣ ሲያንገላቱት፣ ሲሰቅሉትና ሲገድሉት በመተላለፍ ኃጢአት ውስጥ ገቡ እንጂ፣ ምልክታችንና መመሪያችን የሆነው ኢየሱስ ለሰው አልተገለጠም እንጂ በቁመናው እያለም ራሱ በሥልጣኑ የተንገላታ የተዋረደ፣ የሞተ፣ በፈቃዱ የተቀበረ ነበር፤ ለእግዚአብሔር ግን የተገለጠ የክርስቶስ ውርደት፣ ወደ አብ እግዚአብሔር ክብር መግቢያ መንገዳችንን ጠራጊ፣ ሞቱ ደግሞ ወደ ሕይወት መሻገሪያ ዕንቅፋት አስወጋጅ፣ በር ከፋች ኃይል መሆኑን በአክብሮትና በአድናቆት መመልከት አለብን፡፡

ይህ ጌታ ኢየሱስ የተቀበረበት መቃብር በዘመኑ የእስራኤል ማለት የቅድስት አገር፣ ቅዱስ መቃብር ሆኖ በዘመንና ዘመን መካከል የተከሰተ አሕዛብንና እስራኤልን የሚጠቀልል ባልቃ መሆኑን መዘንጋት የለብንም በቀደመው ሥርዓት መቃብር በኛ በአሕዛብ፣ መቃብር በእስራኤል፣ መቃብር ደግሞ በመለኮት ደረጃውና ፍቺው ተመሳሳይ አይደለም፡፡ የእስራኤልን ከዘመን ማዶ የቀረውን ወደዚህ ጎትተን እንዳለ ማሻገር አይቻልም አይጠቅምም፡፡ ከኛ ከአሕዛብ ተመሳሳይ ረድፍ ላይ አድርገን ማየትም አይቻልም፤ ከሞት ዘመን ወደ ሕይወት ዘመን ተሻግረን ከወዲህ ሆነናልና፡፡ የቀደመው ሥርዓት ሞት ነው፤ (ራዕይ 21፥3-4፥ቁ.4)

ክርስቶስ (ሥጋው) ተቀበረ የሚለውን በንባብ ያወቅን ቢሆንም አሁን በመንፈስ ዘመን በፊደሉ ጀርባ በመጋረጃ በተጋረደ ፊት እንደዚያ አናየውም (2ቆሮ.5፥16፤ ም.3፥18) ቀደም ሲል እንዳየነው ሁልጊዜም በነበረበት ቦታው የሚገኘው፤ ሙት ወይም ግዑዝ ነገር ነው ይህ፣ የጌታ ሥጋ በሕያው መንፈስ የሚንቀሳቀስ መሥዋዕት በመሆኑ በሶስተኛ ቀን







ባኖሩበት ቦታ አልተገኘምም፡፡ እንደ ዳዊት የምድሩን መንገድ ሁሉ ሄዷል (1ነገ.2፥1-2፤ ቁ.2)፡፡ በሕጉ መሠረትም ቢሆን ሲበላ ተርፎ ያደረው ሥጋ ለእሳት እንዲሰጥ ያዛልና ለእሳት እንደቀረበ ይታያል፡፡ ለእሳት የሚቀርብ ነገር ጪሱ ወይም ተኑ ማለት የሥጋው መንፈስ ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርብ ነው፡፡ ሥጋው ሥጋ ለሆነው ሰው ሲቀርብ፤ መንፈሱ፣ ተኑ፣ መንፈስ ለሆነው እግዚአብሔር ይቀርባል፡፡ በመቃብር ውስጥ እሳት ከየት መጣ የሚል ይኖራልና፣ ሰው ሳይቀደስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንደማይችል እናውቃለን፡፡ ሰው የሚቀደሰው በእሳት ነው፤ (ማር. 9፥49፣ ኢሳ.48፥10፣ ሚል. 3፥1-3)፡፡ ቀደም ሲል እንዳየነውም፣ ሥጋ ሞቶ፣ ከሞተ በኋላ በእሳት ተጠብሶ ተኑ ለእግዚአብሔር ይቀርባል፤ (ዘፍ.8፥20-21) እሳት በውጭ እንዳለ ሁሉ፣ እሳት በውስጥ አለ፤ እሳት በፊደል እንዳለ ሁሉ፣ እሳት በመንፈስ፣ በመቅደስ ውስጥ አለ፤ መንፈስም ራሱ እሳት ነው፡፡ የእውነት እውነቱ እሳት የሆነው መንፈስ ቅዱስ ባንተም ውስጥ ቀድሶህ የእግዚአብሔር ገንዘብ ሊያደርግ ያለ በውስጥህ ነው፡፡ ተጠቀምበት፡፡ መቃብር፣ ደግሞ ምንድን ነው? ከኃጢአት ዕዳውን ከፍሎ መውጣቱ አቅቶህ፣ ተስፋ ቆርጠህ፣ ለዕዳው የመጨረሻዋን ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ፣ ለሎሌው አልፌህ እጅ ተሰጥተሃል እንበል፡፡ ይህ እውነት ነው፣ ደግሞ ብዙዎችን ያቀፈ ነውና፡፡ ስለሆነ በዕዳ ተይዘህ በኃጢአት ገመድ እጅና እግር፣ (እግር-ተወርች) (ማቴ. 22፥12-13) ታሥረህ ገብተህ የተኛህበት እግዚአብሔር የሚያየው ስውር መቃብር ወህኒ ቋም ሲያል ነው፤ ማንም ከወህኒ ወጥቶ የእግዚአብሔርን ፊት አላየምና፣ (ማቴ. 5፥25-26፣ 1ጴጥ. 3፥18-19፣ ኤፌ.4፥8-10) እናመሳክር፡፡ የኢየሱስ ሥጋ ፈጽሞ መሞቱ በእስራኤል በጦር ሁሉ ተወግቶ፣ ተፈትሾ በትክክል የተረጋገጠ ነው፡፡ ምን ማለት ነው? እናንተ እንደምትሉት የሞተ ነወይ? የሞተው እናንተ እንደምትሉት በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ነወይ? የተሰቀለው መቼ ነው? በሌላ ክፍል እንዳየነውም ሁሉ፣ ኢየሱስን በፈቃዱ እንጂ ሰማይና ምድር ተሰብስቦ ይዞ



በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም፣ አፌ አዟልና መንፈሱም ሰብስቦአቸዋልና፡
ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም፣ ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም፤ ኢሳ.34፥16

አሥሮት አንገላትቶ፣ ሊሰቅለው አይችልም፡፡ 1/ መሰቀል ከኃጢአት ለመቀደስ ነው፤ ሰማይ ላይ መንጠልጠል፡፡ እርሱ ቀድሞውኑ በሰማይ የሚኖር፣ (በመጽሐፉ ውስጥ አለ፤) የተቀደሰ፣ ከኃጢአት ርቆ የተሰቀለ የተሠቃየ፣ እንደምትሉት ሳይሆን በቁም የሞተ ነው፡፡ 2/ ፈፅሞ ሞተ ማለት ኃጢአት ፈፅሞ የለበትም ማለት ነው፡፡ ሰው ሁሉ ሐሰተኛ የሚሆነው በዚህ ነው፤ (መዝ. 116፡2፣ ሮሜ 3፡4) ኢየሱስ አሁን ሞተ ማለት እስከዚህ ድረስ ያለ እግዚአብሔር መንፈስ ኖሯል፤ ያለ እግዚአብሔር መንፈስ አገልግሏል፣ ማለትን ይገልፃል፤ መንፈስ በሞተ ሥጋ ያድራልና ቀድሞውኑ ከሥጋ ሳይሆን ከእግዚአብሔር መንፈስ የተፀነሠ፣ ያደገ፣ ያገለገለ፣ በሞት የኖረ መንፈስ ያደረበት ሥጋ ነው፡፡ ሥጋው የመንፈስ ማደሪያ መቅደስ ሆኖ ካኖሩበት መቃብር በሕያው መንፈሱ ተንቀሳቅሶ በወህኒ ለነበሩት ነፍሳት ሕይወትን ሊሰጥ እስከ ምድር ታችኛ ክፍል ወረደ (ኤፌ.4፡8-10፣ 1ጴጥ.3፡18-19) ተብሎ የተጻፈው በእስራኤል እውነት ነው፡፡

በሕጉ መሠረት እሳቱ እመቅደስ ውስጥ ከጧት እስከ ማታ ይነዳል? ዘፀ.27፡20-21፣ ዘሌ.24፡1-4 አይነድም ወይ? ቀዝቅዘናል፣ ሞተናል ማለት ነው ወይ? በየመቅደሳችን ውስጥ ክርስቶስ እሳቱ አይደለም ወይ? በሌላ በኩል ክርስቶስ ራሱ/ በጉ መቅደስ መሆኑ በግልጽ ተጽፎ ይነበባል፤ {ዮሐ.2፡19-22፣ ራዕይ 21፡22}። የብሉይ ኪዳኑ መቅደስ የሐሰት እውነተኛ መቅደስ ሲሆን፣ ክርስቶስ የአዲስ ኪዳኑ፣ የእውነት፣ እውነተኛ መቅደስ ነው። በመቅደስ ውስጥ ባለማቋረጥ ከጧት እስከ ማታ የሚነደው የእውነት እውነተኛው እሳትም መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ ራሱ እግዚአብሔር እንደመሆኑ መጠንም ከጧት እስከ ማታ ለዘላለም የሚነድድ እሳት ነው፣ {ኢሳ.33፡14}

እንዲሁም ክርስቶስ ቃል ነው፣ ቃልም እሳት፣ ድንጋዩን የሚያደቅ መዶሻ፣ {ኤር.23፡29} የክርስቶስ ሥጋ በገዛ-ራሱ እሳት በመቅደሱ ውስጥ እስከ







ዛሬም፣ ለልጅ ልጅም፣ ለዘላለምም በሥጋ ላይ ለሚነደው እሳት ቀርቦ የሙሴ ቁጥቋጦ ነውና አመድ ሳይሆን አሁንም፣ ቀድሞም፣ ለዘላለምም ነድዷል፣ እየነደደም ነው፣ ይነዳልም። በእሳት ያልተጠበሰ የተከለከለውን ጥሬ ሥጋውን ትበላላችሁ ወይ? ጥሬ ከበላችሁ ጥሬ ናችሁ፤ ቀደም ሲል አይተናል፤ በእሳት ያልተቀደሰውን? በእሳት ያላለፈ፣ የእሳት ጥምቀት ያልተቀበለ/ያልሞተ፣ ያልበሰለ ራሱ ዲያብሎስ ነው። ያልሞተ ሥጋ ማለት ኃጢአት ወይም ሰይጣን ያለበት ማለት ሲሆን፣ የሞተ ሥጋ ማለት ከኃጢአት ወይም ከሰይጣን የተለየ ማለት ነው፡፡ በእንዲህ ሁኔታ ማታ ሲበላ እስከ ነገ ያደረው የጌታ ሥጋ በእምነት እንጂ በማየት አልተገኘም፣ እንደ ሄኖክ፣ ሙሴ፣ ኤልያስ ሥጋ ዓይነት፤ እሳት በላው፣ እየበላውም ነው፤ እመሰክራለሁ፣ ክብር ይሁን፣ ለዘለዓለሙ አሜን።

መንፈስ የፊደል/የቁስ ተርጓሚና የፊደልን እውነት ወደ ብርሃን የሚያወጣ መደምደሚያ ስለሆነ በመንፈስ መቀበሩ እውነት ሳይሆን በፊደል መቀበሩ እውነት አይሆንም፡፡ ኢየሱስ በፊደል (በውጭ አካል) ሞተው በፊደል (በውጭ) ለተቀበሩት እስራኤል በፊደል፣ (በውጭ) ትንሣኤ ሊሰጥ በፊደል አካል በውጭ በመጋረጃ መጣ፣ በውስጥ በስውር ሳይሆን በውጭ ታይቶ ሞተ፣ በውጭ ተቀበረ፤ ከዚያም ወደ ውስጠኛው መጋረጃ ወዳንተ/ች ገባ እንላለን፤ (ዕብ.9፡11-12)፡፡ ወደ ውስጥ በቀጭኑ መንገድ በጠባቡ በር መግባት ይችል ዘንድ ውጫዊ ልብሱን ግዙፉን ቁርበት ተገፈፈ፡፡ ከውጭም ውጫዊውን ዐውቀው ገፈፉት፣ ውሥጣዊውን ሳያውቁ ገፈፉ ከፉ ሥራቸው ለመልካም ሆነ፣ ለዘላለሙ አሜን፡፡ ኢየሱስ በውጭም በውስጥም ትንሣኤ ነው፤ በውጭ በእስራኤል፣ በውስጥ በቤተ-ክርስቲያን፡፡ የማሥነሻ መንጠቆ ሆኖ መጣ እንጂ ወዴት ደረሰ? የሚሉት አይደለም፡፡ በመንፈስ (በውስጥ) ሞተው በመንፈስ ለተቀበሩት ትንሣኤ ሊሰጥ ደግሞ በመንፈስ መቀበሩ የእውነት እውነተኛ መቃብሩ ይሆናል፡፡ የኢየሱስም አገልግሎት ቢሆን፣ የውስጣዊው የእውነት እውነተኛ ይሆን ዘንድ

*ውጫዊው (ፊደላዊው) አገልግሎት በሐሰት እውነት ክፍል ይመደባል፡፡ በውጭም፣ በውስጥ ትንቢት ፈፃሚ ሆኖ መላኩ ግን እውነት ነው፡፡*

*አሁን የዛሬዎቹ ከአሕዛብ ወገን የመጣን እኛም ወደ ውስጣችን መመልከት አቅቶን ጌታ ከዘመናት በፊት ተቀብሮበት ወደ ነበረው መቃብር ወደ ውጭ፣ ከውጭም ወደ መካከለኛ ምሥራቅ በታሪክ ደረጃ ወደ ሰማነው እናያለን፡፡ ወደ ራስ ማንነት ለመግባትም የመንገዱ መሪና መብራት ሲያስፈልግ፣ ጌታ የተጓዘበትን መንገድ ከራስ ማንነት በውጭ መፈለግ ወደ ውጭ ማየት ተደጋግሞ እንደ ተመለከተው ሁሉ በጨለማ መርመስመስ ነው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ትምህርት፣ አምልኮም ቢሆን ከራስ ማንነት በውጭ ማድረግ በመጋረጃ ስለሚሆን ሥነ-ሥርዓቱ ከመጽሐፍ እውነታ ውጭ የሚያስወጣ መሆኑን ይህ ጥናት አበክሮ አረጋግጦ ይገልፃል፡፡ መንፈስ ያልሆነ ነገር ሁሉ ጣዖት እንደሆነ አረጋግጬ እመሰክራለሁ፡፡ ሥጋውን በውጭ የሚፈልገው ሁሉ በውስጡ ጉድጓድ ቆፍሮ የቀበረው ሰው ነው፤ (ማቴ.25፡18) ይመሰክር፡፡*







## *ማጠቃለያ፡-*

*ዋና የመንፈሳዊ ጥያቄ ሰበብ የእግዚአብሔር አለመታየት ፅልመት ነው፡፡ መብራት ከሌለም በጨለማ ማየት፣ መፈለግ፣ ማግኘት አይቻልም፡፡ መጽሐፉ ትኩረት ያደረገው በዚህ ፅልመት ላይ መሆኑ ግልፅ ነው።*

*እግዚአብሔር በማንም አልታየም (አልታወቀም) ከተባለ ዘንድ፣ አምላክን ከሰው የጋረደው የሸፈነው የመካከሉ የጥል ግድግዳ የነበረው ነው፡፡ የብሉይ ኪዳኑ የፊደሉ፤ ውጫዊው /ምሳሌያዊው መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ እንጂ፤ ዋናው፣ የአዲስ ኪዳኑ የእውነት እውነተኛው ልብን ያጨለመው ውስጣዊው የጥል ግድግዳ ገና አልተቀደደም፣ ማለትን ያረጋግጣል፤ እግዚአብሔር አልታየምና፡፡ እግዚአብሔርን አላየንም፣ አላወቅነውም ከተባለም፣ እግዚአብሔርን አለማየት፣ ብርሃንን አለማየት በመሆኑ በጨለማ መሆንን ምህረት አለመልበስን እርቅ አለመደረጉን ግልፅ ያደርጋል፡፡ የተጻፈውም «በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፤ ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም፤ አላወቀውምም (1ዮሐ.3፡6» ይላልና፡፡ ቅዱሱን (እግዚአብሔርን) ማወቅ የጥበብ መጀመሪያ ፩ኛ ነገር መሆኑ የተጻፈ ሲሆን፣ (ምሳሌ 9፡10) እግዚአብሔርን አለማወቅ በብርሃን ሳይሆን በጨለማ (በኃጢአት) መኖር ነውና በጨለማ፣ ማለት በሲዖል መኖር ስለሆነ፣ በጨለማ፣ በሲዖል ሥራና ሐሳብ፣ ጥበብና ዕወቀት እንደሌለ ደግሞ ተጽፏል፣ (መክ. 9፡10) እግዚአብሔርን አለማወቅ ምንም ነገር አለማወቅ ነው፡፡ እግዚአብሔርን ያላየ ምንንም አላየም፤ በጨለማ ዓይን የሌለው ዕውር ነው፡፡ ዓይን፣ ዓይን ነወይስ እግዚአብሔር ዓይን ነው? ቢባል፤ እግዚአብሔር ለሰው ሁለንተና ነው፡፡ በጨለማ ማለትም በሲዖል ማወቅ፣ ማወቅ አይደለም፤ ከአንተ በርቀት በውጭ ቆዳህ ላይ ውጭ የሚቀር ውጫዊ የጨለማው ዕውቀት፡፡*

የእግዚአብሔር ምስጢር የሆነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ከእኛ የተሠወረ ከሆነ፣ ወዳጆቹ ሳንሆን ገና ባሮች ስለሆንን ከአብ የሰማውን ሁሉ ገና አልነገረንም፤ አልገለፀልንም ማለትም አልተቤዠንምና፤ ባርያ ጌታው የሚያደርገውን አያውቅም (15፡15)፡፡ አለማወቅም ገና አለመታተምን፣ አለመቀባትን፣ አለመታረቅን ያመለክታል፤ የተቀባ፣ የታተመ ሁሉን ያውቃል፣ በደሉም አይቆጠርበትም፣ የተጻፈውም ሲናገር፣ «እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብታችኋል፣ ሁሉንም ታውቃላችሁ (1ዮሐ. 2፡20፣ ቁ. 27፤ ኤር. 31፡ 33-34» ይታይ፡፡ የጌታ ኢየሱስ ሥጋ ወዴት ደረሰ? ከሚለው ግርዶሻዊ ጥያቄም ሆነ፣ ከሌላ ሌላ ግርዶሽም ሰውን የሚያድነው የሕጉ በልቡናችን መታተሙ፣ በደላችን አለመቈጠሩ፣ ኃጢአታችን በጌታ ፊት አለመታሰቡ (መረሳቱ)፣ ምህረቱን ማጎናፀፉን፣ መታረቁን፣ መቀባቱን፣ መሾሙን ይገልፃል፡፡

ሀ/ የጌታ ኢየሱስ ‹‹ሥጋ›› ቅዱስ እንደ መሆኑ መጠን ሥጋ በሚለው በሰው ቋንቋ መጋረጃ ክብር ጨለማ ካልተገረዘ እይታ ተሸፍኖ የቀረበ፤ እኔ የማደርገውን አሁን አታውቅም የተባለ፣ (ዮሐ. 13፡7) በዓለም ሳለ በእርሱ የሆነው ዓለም ያላወቀው፣ ዮሐ. 1፡10፣ ዮሐንስ በእጁ ይዞ ሲያጠምቀው ያላወቀው፣ ዮሐ. 1፡33) ደቀ-መዛሙርት ይህን ያህል ዘመን አብረውት ሲኖሩ ያላወቁት፣ ዮሐ. 14፡8-10) እነቀላዮጳና የኤማሁስ መንገደኞች አብረውት ሲጓዙ ሲያዋሩ በስህተት ትርጉም እስኪገስፁት ድረስ ቅድሰናው በሰው መልክ ምሳሌ ተሸፍኖባቸው ያላወቁት (ሉቃስ 24፡13-35)፤ ማርያም፣ ከእርሷ ጋር አብሮ ቆሞ ሲያነጋግራት በአትክልት ጠባቂ ሰው ምሳሌ መልክ ተጋረደባት በስህተት ተተርጉሞ (ዮሐ.20፡11-15) የቀረበ ...ወዘተ ሲሆን፣ ይህ መጽሐፍ ራሱ ጥንት ከመለኮት ክብር ብርሃን ሥርዓተ ቋንቋ፣ ከሰይጣን፣ በእባብ፣ በሄዋን፣ ወደ አዳም ተለውጦ ወደ ተፈጥሮአዊ ወደዚህ ወደ ውጪ ጨለማ ዓለም በሰይጣናዊ ሥርዓተ ቋንቋ ሌላ ባዕድ ትርጉም ይዞና በሰው ፊደል ጨለማ መጋረጃ ተሸፍኖ







በወደቀው ሰው ልማዳዊ ሥርዓተ ቋንቋ ተለውጦ ሌላ መልክ ሆኖ በባዕድ ቋንቋ የቀረበ ቅዱስ፣ ሰውር ፍቺ ያለው መጽሐፍ መሆኑ መታመን አለበት፡፡

የሥጋው ታሪክ ግን ድል የነሣው ደርሶት የሚበላው በእግዚአብሔር ገነት ውስጥ የሚገኘው የሕይወት ዛፍ እንደሆነ፤ (ራዕይ 2፡7) ወደ ዛፉም ለመድረስ መንገዱ ኢየሱስ አቋርጦ በተሸገረበት በሚገለባበጠው ነበልባል ሰይፍ መታጠሩን (ዘፍ.3፡24፤ ዘካ.13፡7)፤ ድል የነሣው ማለትም በዚህ ኢየሱስ በተሻገረበት እሳታማ ሰይፈ ነበልባል ጥሶ የሚሻገር አንተን የሚመስል የእምነት አርበኛ ማለት ነው፡፡ ለ/ ክርስቶስ ኢየሱስ (ሥጋው) በማድጋ ሙሉ ለልጅ ልጅ ይጠበቅ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት የተሠወረ መና መሆኑ፤ (ራዕይ 2፡17፣ ዘፀ.16፡32-34) ሐ/ ክርስቶስ ኢየሱስ (ሥጋው) በማየት ሳይሆን በእምነት የሚበላና የሚጠጣ ምንም ማለት በርበሬ፣ ጨው፣ ሽንኩርት፣ ቅመም፣ ...ወዘተ ሳይታከልበትና ከእርሱም ሳይቀነስበት ብቻውን የሚበቃ ሁሉ በእርሱ የሆነ የሕይወት እንጀራና ሥጋ፣ የሕይወት ውኃ፣ ወተትና ወይን ጠጅ፣ በረከትና ሙሴ፣ (ኢሳ.55፡1-2) መድኃኒትና መብል፣ ትንሣኤና ሕይወት እንጂ በሰይጣናዊ ሐሳብ ተነሣሥቶና ተፈርዶ ጉድጓድ ተቆፍሮ የሚቀብሩት ከንቱ የሆነ ቆሻሻ ነገር አይደለም፡፡ ጉድጓድ ቆፍረህ ከቀበርኸውም እርሱ በእግዚአብሔር ይወጣል አንተ ግን የራስህ ግል ጉድጓድ ስለሆነ በቆፈርከው ጉድጓድ ትገባበታለህ፤ አሌ የማይሉት ሐቅ፣ የማይሻር ፍርድ ነው፡፡

አራቱም ወንጌላት እንደሚገልፁ፣ የእኔ አባት የሆነው አርማቲያ ዮሴፍ ሥጋውን የሰወረው ራሱን በሌላ ላይ ሳይሆን፣ በራሱ ላይ ፈርዶ ሊገባበት በነበረው፣ ለራሱ በቆፈረው መቃብር ለመቀደስ መድኃኒት ስለሆነ ከኒቆዲሞስ ጋር ሆኖ ወስዶ ለራሱ ሰወረው አኖረው እንጂ በተንኮል ለማጥፋት አልቀበረውም፡፡ «ወደ ሕይወት ዛፍ (ወደ ሥጋው) ለመድረስ በደጆቿም ወደ ከተማይቱ እንዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን

ናቸው» (ራዕይ 22፡14)፡፡ ልብሳቸውን የሚያጥቡና እነርሱ ሊገቡ ጭቅቅቱን ከከተማ ውጭ፣ በረከሰ ሥፍራ የሚደፉ ብፁዓን ናቸው፡፡

በብሉይ ኪዳን፣ በፍጥረት ጊዜ የሕይወት ዛፍ ሆኖ የተገለጠው፣ በአዲስ ኪዳን ሥጋው (የሕይወት እንጀራ) የተባለው ክርስቶስ ለመሆኑ የሚያጠያይቅ አይመስለኝም፡፡ ይህ የሕይወት ዛፍ እግዚአብሔር አምላክ የፈጠረውን ሰው ባኖረበት ተድላ ገነት የተፈጠረው ሰው ወደ ሞት ዛፍ እንዳይሻገር ለመቋቋም፣ ለመከላከልና በሕይወት ለመጠበቅ ለሰው ዘብ ሊቆም ከምድር የበቀለና በፈጠረው ሰውና በሞት ዛፍ መካከል ጣልቃ የቆመ ዛፍ ነበረ፡፡ ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ፦ በደጆቿም ወደ ከተማይቱ ለሚገቡ፤ ዛፉ አለበት ድረስ መጓጓዣው መንገድ ደግሞ መጽሐፍ እንደሚገልጸው፣ «እኔ መንገድና እውነት፣ ሕይወትም ነኝ»፤ ያለው (ዮሐ.14፡6) ወደ ሕይወት የሚያደርሰው ቀጭኑ መንገድ ጠባቡ በር (ማቴ.7፡13-14) የታረደው በግ ክርስቶስ ፋሲካችን ነው፤ እርሱ በፋሲካ እየተቆራረሰ ሲበላና ሲባዛ ምድርን ሲሞላ ደስታው እጅግ ታላቅ ነው፡፡ የስንዴ ቅንጣት ስትሞት ወደ ፊት ብዙ የመሆኗን ተስፋ ከሞቷ ማዶ ተመልክታ በደስታ ትሞታለች (እንበልና)፡፡ ጌታ ራሱ የተናገረው ትንቢት ነው፤ (ዮሐ.12፡24)







## ጸሐፊው ራሱን በቅፅል ስም ‹‹ከኖ›› ያለበት ምክንያት

«ከኖ» ማለት ውሻ ማለት ነው፡፡ ውሻ እንስሳ ወይም የአራዊት ወገን መሆኑ ይታወቃል፡፡ እንስሳ ለሠራው የኃጢአት መዝገብ የለውም፡፡ መዝገብ እስከ ሌለውም ድረስ የኃጢአቱን ዋጋ በአካል ሞት ብቻ ከፍሎ አፈር ሆኖ ያርፋል በቃ፣ ገሃነመ-እሳት ፍርድ የሚባል ሥቃይ የለበትም፤ ‹‹ዕረፍት››

ሰው ግን የውጭና የውስጥ አካል ጣምራ ፍጥረት ሆኖ ዓይኑ ያየው፣ ጆሮው የሰማው፣ አፉ የተናገረው፣ ልቡ ያሰበው ሁሉ አንዳች ሳይቀር በውሥጡ ሰውነት ተመዝግቦ ለፍርድ ይቀርባልና (ራዕይ 20፡12፣ ዳን. 7፡10) አሁን በእግዚአብሔር የተዘጋጀ ዕድሉን ተቀብሎ የኃጢአት መዝገቡን በንሥሓ አስቀይሮ በአዲስ ልብ፣ በአዲስ መንፈስ ሌላ ሰው ሆኖ ተለውጦ ካልጠበቀ መሄጃው ወደ ገሃነመ-እሳት መሆኑ የተረጋገጠ ነው፤ (ሕዝ.18፡30-32)፡፡ የእግዚአብሔር ቁጣ በልቡ (መዝገብ) ላይ ነውና (ሚል.4፡5-6) የሽማግሌውን አሮጌ መዝገብ ከቤትህ አውጣ፡፡

ስለሆነ፤ ስለሆነ
ምንነው አህያ በሆንኩ?
የጤፍ ኩንታል ተጭኜ በዞርኩ?
ፋንዲያዬን በሰው ባስጠረግኩ?
የዱላ ንረታ ጠግቤ በሞትኩ?
ለጅቡ ራትና ቁርስ በሆንኩ?
ከዘለለሙ ገሀነም ባመለጥኩ፤ ሃ!!-ኧ፣ ሃኧ፣ ሃኧ-ሃኧ፣ ሃኧ፣
ከሞትኩም ጅቡ እንዲቀብረኝ ፈቅጄአለሁ

በፀጋው የሆነ ከኖ፣ የተባለው ሳሙኤል
በስውር የኢየሱስ ደቀ መዝሙር፤ (ዮሐ.19፡38)